# ማ ው ጫ ።

## የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
## የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ።

### መጀመሪያ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።
### ጠቅላላ ፡ ክፍል ።

### ፩ኛ ፡ መጽሐፍ ።
### የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ስለ ፡ መጣስና ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ አድራጊው ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።
### የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የሥራው ፡ አፈጻጸም ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### የሕጉ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ።


| ቁጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፩ | ጉዳዩና ፡ ግቡ ። | ፩ |
| ፪ | የሕግነቱ ፡ መሠረት ። | ፩ |
| ፫ | ስለ ፡ ልዩና ፡ ስለ ፡ ማሟያ ፡ ሕግ ። | ፪ |
| ፬ | በሕግ ፡ ፊት ፡ ትክክል ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፪ |


### ምዕራፍ ፡ ፪ ።
### ሕጉ ፡ የሚጸናበት ፡ ወሰን ።

### ክፍል ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ።


| ቁጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭ | የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ የማይሠራ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፪ |
| ፮ | ከሕጉ ፡ ስለ ፡ መለየት ፤ የተሻለውን ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፫ |
| ፯ | ስለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ። | ፫ |
| ፰ | ስለ ፡ ይርጋ ፡ አፈጻጸም ። | ፫ |
| ፱ | አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ በተሰጡት ፡ ፍርዶች ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ አፈጻጸም ። | ፬ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፲ | ስለ ፡ ፍርድ ፡ መሰረዝና ፡ ስለ ፡ መሰየም ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ አፈጻጸም ። | ፩ |


ክፍል ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ቦታ ፡ ሁናቴ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ዋናው ፡ አፈጻጸም ።


| | | |
|---|---|---|
| ፲፩ | በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ ደንበኛ ፡ ሁናቴ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፫ |
| ፲፪ | ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፤ ስለ ፡ መወከል ። .... .... .... .... | ፫ |
| ፲፫ | በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .. .... .... .... .... | ፬ |
| ፲፬ | በውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ ስለሚሠራቸው ፡ ወንጀሎች ። | ፬ |
| ፲፭ | የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆነው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... | ፭ |
| ፲፮ | በውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፍርድ ። .... .... .... .... .... | ፮ |


ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

ተከታይ ፡ አፈጻጸም ።


| | | |
|---|---|---|
| ፲፯ | በማኅበራዊ ፡ መብት ፡ ላይ ፤ ወይም ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ። .... .... .... .... | ፯ |
| ፲፰ | በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሠሩ ፡ ሌሎች ፡ ወንጀሎች ። .... .... | ፰ |
| ፲፱ | ይህ ፡ ሕግ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ፋንታ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ። | ፰ |
| ፳ | በውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፍርድ ። .... .... .... .... .... | ፱ |


ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ።


| | | |
|---|---|---|
| ፳፩ | አሳልፎ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። .. .... .... .... .... .... .... | ፱ |
| ፳፪ | የውጭ ፡ አገርን ፡ ፍርዶች ፡ ስለ ፡ ማወቅ ። .... .... .... .... | ፲ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ወንጀልና ፡ ስለ ፡ አሠራሩ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ።


| | | |
|---|---|---|
| ፳፫ | ስለሚያስቀጡ ፡ ወንጀሎች ። .... .... .... .... .... .... | ፲፩ |
| ፳፬ | ውጤቱ ፡ ከነገሩ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። .... | ፲፩ |
| ፳፭ | ሕግ ፡ መጣስ ፡ ስለ ፡ ተሠራበት ፡ ስፍራና ፡ ጊዜ ። .... .... . | ፲፩ |


### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### የሕግ ፡ መጣስ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ደረጃ ።


| | | |
|---|---|---|
| ፳፮ | የመሰናዳት ፡ ተግባሮች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፲፪ |
| ፳፯ | ስለ ፡ መሞከር ። .... .... .... .... .... .... .... | ፲፪ |
| ፳፰ | ስለ ፡ መተውና ፡ ስለ ፡ መጸጸት ፡ ተግባር ።.... .... .... .... | ፲፫ |
| ፳፱ | ሊፈጸም ፡ ስለማይቻል ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... | ፲፫ |
| ፴ | የተለየ ፡ የወንጀል ፡ ሙከራ ። .... .... .... .... .... .... | ፲፬ |
| ፴፩ | የዳኛ ፡ ግምት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፲፬ |


### ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።


| | | |
|---|---|---|
| ፴፪ | ስለ ፡ ዋና ፡ ወንጀል ፡ አድራጊውና ፡ ስለ ፡ ግብረ ፡ አበሮች ። ... | ፲፬ |
| ፴፫ | ልዩ ፡ ወንጀል ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ። ... | ፲፭ |
| ፴፬ | የኅብረት ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... .... .... | ፲፭ |
| ፴፭ | ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ። .... .... .... .... | ፲፭ |
| ፴፮ | ስለ ፡ አባሪነት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፲፮ |
| ፴፯ | በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መስማማትና ፡ ስለ ፡ ማደም ። ... .... | ፲፮ |
| ፴፰ | የወንጀል ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ። .... .... .... ... | ፲፮ |
| ፴፱ | ወንጀለኛን ፡ ስለ ፡ መርዳት ። .... .... .... .... .... | ፲፮ |
| ፵ | የግል ፡ ምክንያቶች ፡ ለሌላ ፡ የማይተላለፉ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ። | ፲፮ |


### ምዕራፍ ፡ ፬ ።

### ታትመው ፡ በሚወጡ ፡ ጽሑፎች ፡ በሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።


| | | |
|---|---|---|
| ፵፩ | መሠረቱ ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፲፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፹፪ | ዋና ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፲፰ |
| ፹፫ | ታትመው ፡ በሚገለጹ ፡ ጽሑፎች ፡ በሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ ምክትል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፲፰ |
| ፹፬ | የጽሑፍን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ ማክበር ። | ፲፱ |
| ፹፭ | በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ወሬን ፡ በመንዛት ፡ ምክትል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፲፱ |
| ፹፮ | ሁለተኛ ፡ አላፊነትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ። | ፲፱ |
| ፹፯ | በጽሑፍ ፡ ጕዳይ ፡ የማይደፈር ፡ መብት ። | ፲፱ |


## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## ወንጀል ፡ አድራጊውን ፡ የሚያስቀጡ ፡ ሁኔታዎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የወንጀል ፡ አላፊነት ፤

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### መደበኛ ፡ አላፊነት ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፹፰ | ለወንጀል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆንና ፡ ስላለመሆን ። | ፳ |
| ፹፱ | የተቀነሰ ፡ አላፊነት ። | ፳ |
| ፺ | ከአላፊነት ፡ እድናለሁ ፡ በማለት ፡ ዘዴን ፡ ስለ ፡ መፍጠር ። | ፳ |
| ፺፩ | አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ። | ፳፩ |


#### ክፍል ፡ ፪ ።

#### ጥፋተኞች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ወጣቶች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፺፪ | ስለ ፡ ሕፃናት ፡ የዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስላለመፈጸማቸው ። | ፳፪ |
| ፺፫ | አካለ ፡ መጠን ፡ ባልደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ። | ፳፪ |
| ፺፬ | ስለ ፡ ዳኛ ፡ ግምት ። | ፳፪ |
| ፺፭ | ስለ ፡ ማጣራት ፤ ስለ ፡ ልዩ ፡ ምርመራና ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ ምርመራ ። | ፳፫ |
| ፺፮ | አካለ ፡ መጠን ፡ ከማድረስ ፡ አስቀድሞ ፡ ያለው ፡ መካከለኛ ፡ ጊዜ ። | ፳፫ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በወንጀል ፡ ሥራ ፡ አጥፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **አሳብ ፤ ቻልተኛነትና ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ።** | |
| ፶፯ | መሠረቱ ፡ የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ። | |
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **ስለ ፡ ቀላል ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛነት ።** | |
| ፶፰ | ዐውቆ ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። | ፳፬ |
| ፶፱ | በቸልተኛነት ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥፋት ። | ፳፭ |
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ወንጀሎች ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለ ፡ ጥፋተኛነት ።** | |
| ፷ | ላንድ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፳፭ |
| ፷፩ | አዲስ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትል ፡ ጥፋትን ፡ የመደጋገም ፡ ሥራ ። | ፳፮ |
| ፷፪ | የተቀራረበ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ስላለው ፡ ጥፋተኛነት ። | ፳፮ |
| ፷፫ | የተቀላቀለ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ስላለው ፡ ጥፋተኛነት ። | ፳፮ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በሕግ ፡ የተፈቀደ ፡ አድራጎት ።** | |
| | **የማያስቀጡና ፡ ይቅርታ ፡ የሚያሰጡ ፡ ሁኔታዎች ።** | |
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በሕግ ፡ የተፈቀደ ፡ አድራጎት ።** | |
| ፷፬ | በሕግ ፡ የታዘዙ ፡ ወይም ፡ የተፈቀዱ ፡ ተግባሮች ። | ፳፯ |
| ፷፭ | የሞያ ፡ ሥራ ፡ ግዴታ ። | ፳፯ |
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **የማያስቀጡና ፡ ይቅርታ ፡ የሚያሰጡ ፡ ሁናቴዎች ።** | |
| ፷፮ | ስለ ፡ ተበዳይ ፡ ፈቃድ ። | ፳፯ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፹፯ | በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ። | ፴፯ |
| ፹፰ | እጅግ ፡ ቀላል ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ጕዳዮች ። | ፴፯ |

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ደንበኞች ፡ ቅጣቶች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ዋና ፡ ቅጣቶች ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

የገንዘብ ፡ ቅጣቶች ።

ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

በገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ስለሚደረገው ፡ ቅጣት ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፹፱ | መቀጮ ፡ መሠረቱ ። | ፴፰ |
| ፺ | መቀጮን ፡ ነጻነትን ፡ ከማሳጣት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ መደረብ ። | ፴፰ |
| ፺፩ | ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ስሜት ፡ ገንዘብን ፡ ለማግኘትና ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፴፱ |
| ፺፪ | የመቀጮ ፡ ገንዘብን ፡ ስለ ፡ ማስገባት ። | ፴፱ |
| ፺፫ | የመቀጮውን ፡ ገንዘብ ፡ በሥራ ፡ ስለ ፡ ማስከፈል ። | ፵ |
| ፺፬ | የግዴታው ፡ ዋስትና ። | ፵ |
| ፺፭ | የመቀጮ ፡ ገንዘብ ፡ ስላለመክፈል ፡ መቀጮውን ፡ ነጻነትን ፡ በሚያሳጣ ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። | ፵ |
| ፺፮ | ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቆም ። | ፵፩ |
| ፺፯ | መቀጮን ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። | ፵፩ |
| ፺፰ | ንብረትን ፡ ስለ ፡ መውረስ ። | ፵፩ |
| ፺፱ | ንብረት ፡ ስለማስያዝ ። | ፵፪ |

ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

ወንጀሉ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ሌሎች ፡ የገንዘብ ፡ ውጤቶች ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፻ | ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ሊሆን ፡ ስለሚገባው ፡ ሀብት ። | ፵፪ |
| ፻፩ | ስለ ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ። | ፵፫ |
| ፻፪ | ለተበዳይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ካሣ ። | ፵፬ |

| ቍጥር ፤ | አርእስተ ፡ ነገር ፤ | ገጽ ፤ |
|---|---|---|
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚቀንሱና ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ።** | |
| | **ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ የሚያስከፍሉና ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጡ ፡ የተቀላቀሉ ፡ ቅጣቶች ።** | |
| ፻፪ | ከገቢው ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚከፈል ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ። | ፺፮ |
| ፻፫ | የግል ፡ ነጻነትን ፡ ከመቀነስ ፡ ጋራ ፡ ስለሚወሰን ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ | ፺፮ |
| ፻፬ | ስለ ፡ ድንገተኛ ፡ ሕመም ። .... .... .... .... .... | ፺፮ |
| | **ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ነጻነትን ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ።** | |
| ፻፭ | ስለ ፡ እስራት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፺፯ |
| ፻፮ | ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ በሌላ ፡ ስለ ፡ መተካት ። | ፺፯ |
| ፻፯ | ስለ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፺፯ |
| ፻፰ | የወል ፡ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፺፯ |
| ፻፱ | በእስር ፡ ቤት ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ ስለ ፡ መለያየትና ፡ በየተወሰነላቸው ፡ ስፍራ ፡ ነጥሎ ፡ ስለ ፡ ማኖር ። .... .... .... | ፺፰ |
| ፻፲ | ስለ ፡ እስረኛው ፡ ግዴታ ፡ ሥራና ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ዋጋ ። .... ... | ፺፰ |
| ፻፲፩ | የተቀጪውን ፡ የእስራቱን ፡ ደረጃ ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ። .... .... | ፺፱ |
| ፻፲፪ | አስቀድሞ ፡ በአመክሮ ፡ ስለ ፡ መፈታት ። .... .... .... .... | ፺፱ |
| ፻፲፫ | ስለ ፡ ወታደር ፡ የእስራት ፡ አስተዳደር ። .... .... .... | ፻ |
| ፻፲፬ | ለመጠበቂያ ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መቍጠር ። | ፻ |
| ፻፲፭ | የታመመውን ፡ እስረኛ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማግባትና ፡ የታመመበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መቍጠር ። .... .... .... .... | ፻ |
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **ስለ ፡ ሞት ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ።** | |
| ፻፲፮ | መሠረቱ ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፩ |
| ፻፲፯ | ሞት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ እስኪፈጸም ፡ የሚቈይበት ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፪ |
| ፻፲፰ | የሞት ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸም ፡ ስለሚቈይበት ፡ ሁኔታ ። ... .... | ፻፪ |
| ፻፲፱ | የሞት ፡ ፍርድን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። .... .... .... .... .... | ፻፪ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

ክፍል ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፻፹ | መሠረቱ ። | ፺፪ |
| ፻፹—ሀ | ስለ ፡ ግርፋት ። | ፺፫ |
| ፻፹፩ | በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ማስጠንቀቂያ ፤ ተግሣጽ ፤ ወቀሳ ፤ ጥፋተኛው ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ይቅርታ ። | ፺፫ |
| ፻፹፪ | ከመብት ፡ ስለ ፡ መሻር ። | ፺፬ |
| ፻፹፫ | ቅጣቱ ፡ ስለሚቈይበት ፡ ዘመንና ፡ ስለ ፡ አወሳሰኑ ። | ፺፬ |
| ፻፹፬ | የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ስለሚያስገኘው ፡ ውጤት ። | ፺፭ |
| ፻፹፭ | መብትንና ፡ ክብርን ፡ ስለ ፡ መመለስና ፡ ስለ ፡ መሰየም ። | ፺፭ |
| ፻፹፮ | ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ስለ ፡ ማስወገድና ፡ ማዕርግን ፡ ስለ ፡ መግፈፍ ። | ፺፭ |
| ፻፹፯ | ውሳኔው ፡ ስለሚያስገኘው ፡ ውጤት ። | ፺፮ |

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በተለይ ፡ ሁኔታ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱ ፡
ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ጥንቃቄ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ደጋግመው ፡ ወንጀልን ፡ በሚሠሩና ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡
አድርገው ፡ በያዙ ፡ ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ጥንቃቄ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፻፹፰ | ጽኑ ፡ ግዞት ። | ፺፮ |
| ፻፹፱ | የግዞቱ ፡ አፈጻጸም ። | ፺፮ |
| ፻፺ | የግዞቱ ፡ ዘመን ። | ፺፯ |
| ፻፺፩ | በገደብ ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ። | ፺፯ |
| ፻፺፪ | መፈጸም ፡ ስለማይቻልበት ፡ ሁኔታ ። | ፺፯ |

ክፍል ፡ ፪ ።

አላፊነት ፡ በሌላቸውና ፡ አላፊነታቸው ፡ በተቀነሰ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡
ስለሚደረግ ፡ ጥንቃቄ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፻፺፫ | መሠረቱ ። | ፺፰ |
| ፻፺፬ | የጥንቃቄ ፡ ግዞት ። | ፺፰ |
| ፻፺፭ | ስለ ፡ ሕክምናው ። | ፺፰ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፴፮ | ስለ ፡ አጠቃላይ፡ድንጋጌዎች ፤ ውሳኔው ፡ ስለሚቈይበት ፡ ጊዜ ። | ፵፱ |
| ፪፻፴፯ | በቅጣቱና፡በተቀነሰው ፡ ኀላፊነት ፡ መካከል ፡ ስላለው፡ግንኙነት። | ፶ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ።** | |
| | **ስለ ፡ ጥንቃቄና ፡ ስለ ፡ አጠባበቅ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።** | |
| ፪፻፴፰ | መሠረቱ ። | ፶፩ |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ውሳኔዎች ።** | |
| ፪፻፴፱ | የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ዋስ ፡ መሠረቱ ። | ፶፩ |
| ፪፻፵ | ቃል ፡ መግባትን ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ መስጠትን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ። | ፶፪ |
| ፪፻፵፩ | የውሳኔው ፡ ውጤት ። | ፶፪ |
| ፪፻፵፪ | ዋስ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ለመስጠት ፡ ስላለመቻል ። | ፶፪ |
| ፪፻፵፫ | የጥንቃቄውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለ ፡ መደጋገም ። | ፶፫ |
| ፪፻፵፬ | አደገኞች ፡ የሆኑ ፡ ዕቃዎችንና ፡ መሣሪያዎችን ፡ ስለ ፡ መውረስ ። | ፶፫ |
| ፪፻፵፭ | አጠቃላይ ፡ ድንጋጌ ፤ ለጥንቃቄ ፡ የሚደረግ ፡ ጠቅላላ ፡ አፈጻጸም ። | ፶፫ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ሥራን ፡ ስለ ፡ ማገድ ፡ የሚደረግ ፡ ውሳኔ ።** | |
| ፪፻፵፮ | ፈቃድን ፡ ስለ ፡ ማገድና ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ። | ፶፬ |
| ፪፻፵፯ | መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ መከልከልና ፡ ስለ ፡ መዝጋት ። | ፶፬ |
| ፪፻፵፰ | ውሳኔውን ፡ ባለመጠበቅ ፡ ስለሚደርስ ፡ ውጤትና ፡ ቅጣት ። | ፶፭ |
| | **ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **የግል ፡ ነጻነትን ፡ ስለሚቀንሱ ፡ ድንጋጌዎች ።** | |
| ፪፻፵፱ | ጥፋተኛው ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይደርስ ፡ ስለ ፡ መከልከል ። | ፶፭ |
| ፪፻፶ | ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አገር ፡ ከመኖርና ፡ ውሎ ፡ ከማደር ፡ ስለ ፡ መከልከል ። | ፶፭ |
| ፪፻፶፩ | ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፡ ግዴታ ። | ፶፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፶፪ | በተጠባባቂ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። .... .... .... | ፹፮ |
| ፪፻፶፫ | በግልጽ ፡ የተሰጡትን ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ መውሰድ ። ... .... | ፹፮ |
| ፪፻፶፬ | ወንጀለኛው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ እንዳይኖር ፡ ስለ ፡ መከልከልና ፡ ካገር ፡ ስለ ፡ ማስወጣት ። .... .. | ፹፮ |
| ፪፻፶፭ | አፈጻጸሙ ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፹፰ |
| ፪፻፶፮ | የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለሙከራ ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ ማገድ ። .... | ፹፱ |
| ፪፻፶፯ | ስለ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ የተወሰነውን ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ የሚደረግ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ። .... .... .... .... .... .... | ፹፱ |


ክፍል ፡ ፬ ።

የማስታወቂያ ፡ አሰጣጥ ፡ ውሳኔዎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፶፰ | ለደንበኛው ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ። .. .... | ፹፱ |
| ፪፻፶፱ | ፍርድን ፡ ለሕዝብ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። .... .... .... .... ... | ፺ |
| ፪፻፷ | ፍርድን ፡ በግል ፡ የፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ። | ፺ |


ምዕራፍ ፡ ፱ ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ጥንቃቄዎችና ፡ ቅጣቶች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ለአካለ ፡ መጠን ፡ ያልተደረሰበት ፡ ደንበኛ ፡ ዘመን ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

መደበኛ ፡ ድንጋጌዎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፷፩ | መሠረቱ ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፺፩ |
| ፪፻፷፪ | ሕክምና ፡ ለሚደረግበት ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ። .... | ፺፩ |
| ፪፻፷፫ | በበጎ ፡ አስተዳደግና ፡ በትምህርት ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። .... .... | ፺፩ |
| ፪፻፷፬ | ስለ ፡ ተግሣጽና ፡ ስለ ፡ ወቀሳ ። .... .... .... .... .... | ፺፪ |
| ፪፻፷፭ | በትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቤቱ ፡ ስለ ፡ ማገድ ። .... .... | ፺፪ |
| ፪፻፷፮ | ለጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ። .... .... .... | ፺፫ |
| ፪፻፷፯ | ውሳኔው ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ። .... .... .... .... .... | ፺፫ |
| ፪፻፷፰ | ውሳኔዎችን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ። .... .... .... .... .... | ፺፬ |
| ፪፻፷፱ | ሕጋውያን ፡ ውጤቶች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፺፬ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ቅ ጣ ቶ ች ።** | |
| ፯፻ | መሠረቱ ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፶፬ |
| ፯፻፩ | ስለ ፡ መቀጮ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፶፬ |
| ፯፻፪ | የአለንጋ ፡ (የአርጩሜ) ፡ ቅጣት ። .... .... .... .... | ፶፭ |
| ፯፻፫ | ስለ ፡ እስራት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፶፭ |
| | **ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **የወል ፡ ድንጋጌዎች ።** | |
| ፯፻፬ | ስለ ፡ ቀላል ፡ ጥፋት ፤ በሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፶፮ |
| ፯፻፭ | ልዩ ፡ የይርጋ ፡ ደንብ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፶፯ |
| ፯፻፮ | ውሳኔውን ፡ አግዶ ፡ ስለ ፡ ማቈየትና ፡ ተቀጪውን ፡ በሙከራ ፡ ስለ ፡ ማቈየት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፶፯ |
| ፯፻፯ | በሕዝባዊ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። | ፶፯ |
| ፯፻፰ | ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ የጥንቃቄና ፡ የጥበቃ ፡ ውሳኔዎች ። .... .... | ፶፯ |
| ፯፻፱ | የፍርድ ፡ ውሳኔን ፡ ስለ ፡ መግለጽና ፡ በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፶፰ |
| ፯፻፲ | ፍርድን ፡ ስለ ፡ መሰረዝና ፡ ስለ ፡ መሰየም ። .. .... .... .... | ፶፰ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ሕጋዊ ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ዘመን ፡ እስከሚደርስበት ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አማካይ ፡ ዘመን ።** | |
| ፯፻፲፩ | መጠነኛ ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፶፱ |
| ፯፻፲፪ | ልዩ ፡ ሁኔታ ። .... .. .... .... .... .... .... .... .... | ፶፱ |
| | **አንቀጽ ፡ ፪ ።** | |
| | **መወሰን ፤ ለጊዜው ፡ ማቈየት ።** | |
| | **በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ማቈየትና ፡ ቅጣትን ፡ ማስቀረት ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **ቅጣትን ፡ መወሰንና ፡ ለጊዜው ፡ ማቈየት ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **ቅጣትን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።** | |
| ፯፻፲፫ | መሠረቱ ፤ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣንና ፡ የሥልጣን ፡ ወሰን ።.... | ፷ |

ቍጥር ፡ አርእስተ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለልና ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ደንብ ።

፻፹፬ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለል ። ........................ ፹
፻፹፭ በመሰለው ፡ ቅጣትን ፡ ማቅለል ። ........................ ፹፩
፻፹፮ የወል ፡ ድንጋጌዎች ። ........................ ፹፩
፻፹፯ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ ማድረግና ፡ ቅጣትን ፡ መተው ። ........................ ፹፩

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

የቅጣት ፡ ማክበድ ፡ ደንብ ።

፻፹፰ ደንበኛ ፡ የቅጣት ፡ ማክበድ ። ........................ ፹፩
፻፹፱ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ በተደራረበ ፡ ጊዜ ፡ እርግጠኛ ፡ የሆነ ፡ የቅ
ጣት ፡ ማክበድ ፡ ጕዳይ ። ........................ ፹፪
፻፺ ልዩ ፡ ሁኔታ ። ........................ ፹፫
፻፺፩ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተሠራና ፡ የተደራረበ ፡ ወንጀል ፡ ከፍርድ ፡
በኋላ ፡ ስለ ፡ መገለጹ ። ........................ ፹፫
፻፺፪ የሕጋዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መደራረብ ። ........................ ፹፫
፻፺፫ በተደጋገመ ፡ ጥፋት ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ። ........................ ፹፬

ክፍል ፡ ፪ ።

ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቆም ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ቅጣትን ፡ በገደብ ፡ ስለ ፡ ማገድ ።

፻፺፬ መሠረቱ ። ........................ ፹፬
፻፺፭ ለቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፤ ውሳኔውን ፡ ስለ ፡
ማገድ ። ........................ ፹፭
፻፺፮ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ........................ ፹፭
፻፺፯ ቅጣቶችን ፡ ስለ ፡ መደራረብ ፤ ለአፈጻጸማቸው ፡ ጊዜ ፡ መስጠ
ትን ፡ ስለ ፡ መከፋፈል ። ........................ ፹፭
፻፺፰ ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ የማይቻልበት ፡ ሁኔታ ። ........................ ፹፮
፻፺፱ (ማጣራት) ፡ ምርመራ ። ........................ ፹፮
፪፻ የወል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለፈተና ፡ የሚሰጥ ፡ ጊዜ ። ........................ ፹፮
፪፻፩ ፈተና ፡ የሚሰጥባቸው ፡ ሁኔታዎች ። ........................ ፹፮

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፱፻፪ | በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የሚወሰን ፡ የአኗኗር ፡ ደንብ ። | ፹፯ |
| ፱፻፫ | ጥፋተኛውን ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ። | ፹፰ |
| ፱፻፬ | ፈተናው ፡ ፍሬ ፡ ያልሰጠ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ለፈተና ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ። | ፹፱ |
| ፱፻፭ | በመልካም ፡ ውጤት ፡ ፈተናን ፡ ስለ ፡ ማለፍ ። | ፹፱ |


ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለ ፡ መፈታት ።


| | | |
|---|---|---|
| ፱፻፮ | መሠረቱ ። | ፺ |
| ፱፻፯ | የመለቀቁ ፡ ሁኔታዎች ። | ፺ |
| ፱፻፰ | ለጕዳዩ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ አሳብ ። | ፺ |
| ፱፻፱ | የአመክሮ ፡ ጊዜ ፡ ልክ ። | ፺፩ |
| ፱፻፲ | የጠባይ ፡ አመራርና ፡ የአጠባበቅ ፡ ደንብ ። | ፺፩ |
| ፱፻፲፩ | የፈተናው ፡ ውጤት ። | ፺፪ |
| ፱፻፲፪ | በአንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ከመድረስ ፡ የመከልከል ፤ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ታግዶ ፡ የመኖርና ፡ ካገር ፡ የመውጣት ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። | ፺፪ |


ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

ባልደረብነት ።


| | | |
|---|---|---|
| ፱፻፲፫ | መሠረቱ ። | ፺፫ |
| ፱፻፲፬ | የባልደረብነት ፡ ዓላማና ፡ ሥልጣን ። | ፺፬ |
| ፱፻፲፭ | የሥራው ፡ ድርጅት ። | ፺፬ |


ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ክስና ፡ ቅጣት ፡ ስለሚታገድበትና ፡ ስለሚቀርበት ።

ክፍል ፡ ፩ ።

የከሳሽ ፡ ወይም ፡ የተከሳሽ ፡ መታጣት ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

የክስ ፡ ወይም ፡ የአቤቱታ ፡ አለመኖር ።


| | | |
|---|---|---|
| ፱፻፲፮ | በጠቅላላው ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ ወይም ፡ የመክሰስ ፡ መብት ። | ፺፭ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፲፯ | በግል ፡ ከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ስለሚቀርብ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ። | ፺፭ |
| ፪፻፲፰ | የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ ተገቢ ፡ መብት ። | ፺፭ |
| ፪፻፲፱ | በኅብረት ፡ የሚቀርብ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ። | ፺፮ |
| ፪፻፳ | የአቤቱታ ፡ ማቅረቢያ ፡ ጊዜና ፡ ያቀራረቡ ፡ ፎርም ። | ፺፮ |
| ፪፻፳፩ | የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ መተው ። | ፺፮ |
| ፪፻፳፪ | ክስ ፡ የማይከፋፈል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፺፯ |

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

የተከሳሹ ፡ ወይም ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ መሞት ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፳፫ | ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ መሞት ። | ፺፯ |
| ፪፻፳፬ | ከቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መሞት ። | ፺፯ |

ክፍል ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ይርጋ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፳፭ | መሠረቱና ፡ ውጤቱ ። | ፺፯ |
| ፪፻፳፮ | መደበኛው ፡ የክስ ፡ አቀራረብ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ። | ፺፰ |
| ፪፻፳፯ | ልዩ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ። | ፺፰ |
| ፪፻፳፰ | የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ጊዜ ፡ አቈጣጠር ። | ፺፰ |
| ፪፻፳፱ | የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታገድ ። | ፺፱ |
| ፪፻፴ | የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቋረጥ ። | ፺፱ |
| ፪፻፴፩ | ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ። | ፺፱ |
| ፪፻፴፪ | በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ መድረሱ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። | ፻ |

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

የቅጣት ፡ ይርጋ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፴፫ | መሠረቱና ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። | ፻ |
| ፪፻፴፬ | የጊዜው ፡ ውሳኔ ። | ፻፩ |
| ፪፻፴፭ | የቅጣት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ አቈጣጠር ። | ፻፩ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፴፮ | የቅጣቱ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ ታግዶ ፡ የሚቈይበት ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፭ |
| ፪፻፴፯ | የቅጣት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ የሚቋረጥበት ፡ ሁኔታ ። | ፻፮ |
| ፪፻፴፰ | ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የቅጣት ፡ ይርጋ ። .... .... .... .... .... | ፻፮ |

ክፍል ፡ ፫ ።

በተለይ ፡ የሚሰጥ ፡ ምሕረትና ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፴፱ | ምሕረት ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፮ |
| ፪፻፵ | የዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ (አምኒስቲ) ። .... .... .... .... .... | ፻፯ |
| ፪፻፵፩ | በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ስለሚከፈል ፡ ካሣና ፡ ወጪ ። .... | ፻፯ |

ክፍል ፡ ፬ ።

ስለ ፡ መሰየም ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፵፪ | መሠረቱ ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፯ |
| ፪፻፵፫ | ለመሰየም ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሁኔታዎች ። .... .... .... .... | ፻፰ |
| ፪፻፵፬ | ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፰ |
| ፪፻፵፭ | የመሰየም ፡ ውጤት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፱ |
| ፪፻፵፮ | ለመሰየም ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ ስላለመቀበልና ፡ ጥያቄውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ። .... .... .... .... .... | ፻፱ |
| ፪፻፵፯ | የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለ ፡ መሻር ። .... .... .... .... .... | ፻፱ |

## ፪ኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።

## ልዩ ፡ ክፍል ።

### ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ።

### በመንግሥት ፡ ላይ ፤ ባገርና ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

#### አንቀጽ ፡ ፩ ።

#### በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

#### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

#### በመንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ክፍል ፡ ፩ ።

### በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ደንብና ፡ በመንግሥት ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።


| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፹፰ | በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ። .... .... .... .... | ፻፯ |
| ፪፻፹፱ | በዙፋኑ ፡ አወራረስ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፯ |
| ፪፻፺ | በሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በተቋቋሙ ፡ ባለሥል ጣኖች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።.... | ፻፯ |
| ፪፻፺፩ | በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሥልጣን ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ እርምጃ ፡ መሰ ናከል ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .... .... .... | ፻፯ |
| ፪፻፺፪ | የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ሽብር ፡ በማድረግና ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ጦር ነት ፡ በማንሣት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .... .... .... | ፻፯ |
| ፪፻፺፫ | የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ የግዛቱን ፡ ሙሉነት ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።.... | ፻፰ |
| ፪፻፺፬ | የማነሣሣት ፡ ተግባሮችን ፡ ግዙፍ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ማሰናዳት ። | ፻፰ |
| ፪፻፺፭ | የአገርን ፡ ወሰንና ፡ የፖለቲካን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ በመጣስ ፡ ስለ ሚሠራ ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፰ |


### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

### ንጉሠ ፡ ነገሥቱንና ፡ መንግሥቱን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።


| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፺፮ | ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ባለሥልጣ ኖች ፡ በመድፈር ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። . .... .... .... | ፻፱ |
| ፪፻፺፯ | ያገር ፡ ምልክቶች ፡ የሆኑ ፡ ዓላማዎችን ፡ በመድፈር ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፱ |
| ፪፻፺፰ | ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ምልክቶች ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። | ፻፲ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በመንግሥቱ ፡ የውጭ ፡ ኀይልና ፡ በመከላከያው ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፪፻፶፱ | የመንግሥቱን ፡ ነጻነት ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ መንጀል ። | ፻፲ |
| ፪፻፷ | ያገሩን ፡ መከላከያ ፡ ኀይል ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። | ፻፲ |
| ፪፻፷፩ | ከፍ ፡ ያለ ፡ ክዳት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፲፩ |
| ፪፻፷፪ | የዲፕሎማቲክ ፡ ክዳት ። .. .... .... .... .... .... .... | ፻፲፪ |
| ፪፻፷፫ | የኤኮኖሚክ ፡ (የሀብት) ፡ ክዳት ። ... .... .... .... .... | ፻፲፪ |
| ፪፻፷፬ | ከጠላት ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ (ጠላትን ፡ ስለ ፡ መርዳት) ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፲፫ |
| ፪፻፷፭ | ስለላ ። .... .... .. .... .... .... .... .... .... | ፻፲፫ |
| ፪፻፷፮ | ይህ ፡ የጥበቃው ፡ ውሳኔ ፡ ለጦር ፡ ጓደኞች ፡ መንግሥታትም ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። .... .... .... .... .... .... | ፻፲፬ |
| | **ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **የወል ፡ ድንጋጌዎች ።** | |
| ፪፻፷፯ | በዘወርዋራ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ስለሚቈጠር ፡ ማገዝና ፡ መርዳት ። | ፻፲፬ |
| ፪፻፷፰ | በወንጀል ፡ ተካፋይነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ። .... | ፻፲፭ |
| ፪፻፷፱ | ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ። .... .... .... .... | ፻፲፭ |
| ፪፻፸ | ከባድ ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፲፮ |
| ፪፻፸፩ | ተደራራቢ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባሮች ። | ፻፲፮ |
| ፪፻፸፪ | ንብረትን ፡ ስለ ፡ መውረስ ። .... .... .... .... .... .... | ፻፲፯ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፪፻፸፫ | በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የተቃዋሚነት ፡ ሥራ ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፲፯ |
| ፪፻፸፬ | በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... | ፻፲፰ |
| ፪፻፸፭ | የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥትን ፡ ግዛት ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። .... .. .... .... .... .... .... .... .... | ፻፲፰ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፸፮ | የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥትን ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። | ፹፱ |
| ፪፻፸፯ | ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ምልክቶችን ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። | ፹፱ |
| ፪፻፸፰ | በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተቋቋሙትን ፡ ሥራዎች ፡ (እንስቲቱሲዮኖች) ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። | ፹፱ |
| ፪፻፸፱ | የውለታ ፡ መመለስ ፡ ሁኔታ ። | ፹፱ |
| ፪፻፹ | ስለ ፡ ክስ ፡ አቀራረብ ። | ፺ |

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## በሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ። መሠረታውያን ፡ ወንጀሎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪፻፹፩ | ዘርን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ፡ በሰብአዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ። | ፺ |
| ፪፻፹፪ | በብሔራዊ ፡ በሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚ ፈጸም ፡ የጦርነት ፡ ወንጀል ። | ፺፩ |
| ፪፻፹፫ | በቍስለኞች ፡ በበሽተኞችና ፡ በስጥመት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የጦርነት ፡ ወንጀል ። | ፺፪ |
| ፪፻፹፬ | በታሰሩና ፡ በተጋዙ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ የጦርነት ፡ ወንጀሎች ። | ፺፪ |
| ፪፻፹፭ | በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ የዘረፋ ፡ የየብስና ፡ የባሕር ፡ ወንበዴነት ። | ፺፪ |
| ፪፻፹፮ | ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ። | ፺፫ |
| ፪፻፹፯ | ለጠላት ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፺፫ |
| ፪፻፹፰ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆኑ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መታገዝ ። | ፺፫ |
| ፪፻፹፱ | የጦር ፡ ማቆም ፡ ውልን ፡ ወይም ፡ የሰላም ፡ ስምምነት ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ። | ፺፬ |
| ፪፻፺ | የፋኖ ፡ አለቃ ፡ በመሆን ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። | ፺፬ |
| ፪፻፺፩ | በቍስለኞች ፡ በበሽተኞችና ፡ በእስረኞች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጫንና ፡ የሚገባቸውን ፡ ስለ ፡ ማጓደል ። | ፺፬ |
| ፪፻፺፪ | ፍትሕ ፡ ስለ ፡ መከልከል ። | ፺፬ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በበነ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።** | |
| ፱፻፺፫ | በኢንተርናሲዮናል ፡ የበነ ፡ አድራጎት ፡ ሰብአዊ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ተቃዋሚ ፡ ሥራ ። .... .... .... | ፪፻፳፭ |
| ፱፻፺፬ | በኢንተርናሲዮናል ፡ አርማዎችና ፡ ምልክቶች ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። .... .... .... .... .... .... .... | ፪፻፳፭ |
| ፱፻፺፭ | በዕርቅ ፡ መልክተኛ ፡ ላይ ፡ ተቃዋሚ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መፈጸም ። | ፪፻፳፮ |
| | **አንቀጽ ፡ ፫ ።** | |
| | **ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **ስለ ፡ ወታደር ፡ ወንጀል ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በአገልግሎት ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።** | |
| ፱፻፺፮ | የማገልገል ፡ እንቢተኛነት ። .... .... .... .... .... .... | ፪፻፳፮ |
| ፱፻፺፯ | ስለ ፡ መታዘዝ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፪፻፳፮ |
| ፱፻፺፰ | የታዘዘውን ፡ አገልግሎት ፡ ለመፈጸም ፡ እንዳይችል ፡ ስለ ፡ መሆን ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፪፻፳፯ |
| ፱፻፺፱ | ከወታደር ፡ አገልግሎት ፡ ለማምለጥ ፡ የሚሠራ ፡ ማጭበርበር ። | ፪፻፳፯ |
| ፲፻ | ስለ ፡ መክዳት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፪፻፳፯ |
| ፲፻፩ | ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መስረቅ ። .... .... .... .... .... .... | ፪፻፳፯ |
| ፲፻፪ | ሆን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ጦር ፡ ተመልሶ ፡ ስለ ፡ አለመምጣት ። | ፪፻፳፰ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ያገልግሎትን ፡ ሥልጣን ፡ ከመጠን ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ።** | |
| ፲፻፫ | በማይገባ ፡ ከሥራ ፡ እንዲቀር ፡ ስለ ፡ መፍቀድ ። .... .... .... | ፪፻፳፰ |
| ፲፻፬ | የበላይ ፡ ሹም ፡ ስለሚፈጽመው ፡ የሥልጣን ፡ መተላለፍ ። | ፪፻፳፱ |
| ፲፻፭ | በበታች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ዛቻና ፡ የእጅ ፡ እልፊት ። .... | ፪፻፳፱ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ባገልግሎት ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ደንብንና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።


፫፻፮ በጠቅላላው ፡ የአገልግሎት ፡ ትእዛዞችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። .... ፪፻፹፱
፫፻፯ ለሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ጕዳይ ፡ በሚሰጥ ፡ መረጃ ፡ ላይ ፡ ዐውቆ ፡ በማስቀረትና ፡ ያልተካከለ ፡ መረጃ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ... ፪፻፺
፫፻፰ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ስለ ፡ መስከር ። .. .... .... .... .... ፪፻፺
፫፻፱ ከሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (ከዲስፕሊን) ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መሆን ። .... ፪፻፺፩
፫፻፲ በበላይ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የስድብ ፡ የዛቻና ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፩
፫፻፲፩ ለበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ አለመታዘዝ ። . .... .... .... ፪፻፺፪
፫፻፲፪ አድማ ። .... .... . .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፪
፫፻፲፫ ግርግር ፡ ለማንሣት ፡ ስለሚደረግ ፡ አድማ ፡ ወይም ፡ ስምምነት ። ፪፻፺፫
፫፻፲፬ በተካፋይነት ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ። .... .... .... .... ፪፻፺፫
፫፻፲፭ በዘብ ፤ በዘብ ፡ ጠባቂና ፡ በፈታሽ ፡ ዘብ ፡ (ፓትሩይ) ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። . .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፫


### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

### የዘብ ፡ ተረኛንና ፡ ለዘብ ፡ የተሰጠውን ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚመለከት ፡ ወንጀል ።


፫፻፲፮ የዘብ ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፫
፫፻፲፯ የወታደርን ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መጣስ ። .... .... .... ፪፻፺፬
፫፻፲፰ ለዘብ ፡ የተሰጠውን ፡ ምስጢራዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መግለጽና ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ። .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፬


### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

### ታማኝነትን ፡ በማጓደል ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።


፫፻፲፱ በዕቃዎች ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መጠቀምና ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማባከን ። .... ... .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፭

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፷ | የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። | ፪፴፯ |

ክፍል ፡ ፬ ።

በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጸጥታ ፡ (ሞራል) ፡ ሕሊናና ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለሚያደርሱ ፡ ወንጀሎች ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፷፩ | በአደጋ ፡ ጊዜ ፡ የማስጠንቀቅን ፡ ተግባር ፡ ስላለመፈጸም ። | ፪፴፯ |
| ፫፻፷፪ | አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የጸጥታ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላለማድረግ ። | ፪፴፯ |
| ፫፻፷፫ | ሐሰተኛ ፡ የአደጋ ፡ ምልክት ። | ፪፴፯ |
| ፫፻፷፬ | የጦር ፡ ወታደርን ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ማስቈረጥ ። | ፪፴፰ |
| ፫፻፷፭ | ፈሪነት ። | ፪፴፰ |
| ፫፻፷፮ | ለጠላት ፡ እጅን ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ፪፴፰ |
| ፫፻፷፯ | ምንም ፡ ያልጐደላቸውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መተው ። | ፪፴፱ |

ክፍል ፡ ፭ ።

የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፷፰ | የጦር ፡ ምርኮኞችና ፡ ግዞተኞች ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ። | ፪፴፱ |
| ፫፻፷፱ | መኰንኖች ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ በወታደር ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ። | ፪፵ |
| ፫፻፸ | ለከባድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተጨማሪ ፡ ስለሚሆኑ ፡ ቅጣቶች ። | ፪፵ |
| ፫፻፸፩ | የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቅጣቶች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ። | ፪፵ |

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በወታደሮችና ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ክፍል ፡ ፩ ።

በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ወታደሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፸፪ | የአገልግሎቱን ፡ ተግባር ፡ በማይገባ ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ እንዲጥስ ፡ ስለ ፡ ማስገደድ ። | ፪፵፩ |
| ፫፻፸፫ | በሥራ ፡ ላይ ፡ ከሚገኝ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ የጸብ ፡ ግጭት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፪፵፩ |
| ፫፻፸፬ | ከባድ ፡ ሁኔታ ። | ፪፵፩ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በረዳት ፡ ያገልግሎት ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።** | |
| ፫፻፴፭ | የሕግ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ግዴታዎችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፺፪ |
| ፫፻፴፮ | ስለ ፡ ማሰናከል ። | ፺፫ |
| ፫፻፴፯ | በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መነገድ ። | ፺፫ |
| ፫፻፴፰ | የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ መለዮ ፡ ልብስ ፡ ምልክትና ፡ ሽልማት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በፋብሪካ ፡ ስለ ፡ መሥራትና ፡ በንግድ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ። | ፺፫ |
| ፫፻፴፱ | የወታደር ፡ መለዮ ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ የወታደርን ፡ ምልክትና ፡ ሽልማት ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መልበስ ። | ፺፬ |
| ፫፻፵ | ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ የያዙ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባሮችን ፡ ትእዛዝ ፡ ስላለመቀበል ። | ፺፬ |
| ፫፻፵፩ | የወታደር ፡ ትእዛዞች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ወይም ፡ እንዲጣሱ ፡ ለማድረግ ፡ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ማደፋፈር ። | ፺፬ |
| ፫፻፵፪ | አንዳንድ ፡ የወታደር ፡ ስፍራዎችን ፡ ወይም ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የተደረገውን ፡ ክልከላ ፡ ስላለመከተል ። | ፺፭ |
| ፫፻፵፫ | ጠቅላላ ፡ ትእዛዞችና ፡ አመራሮችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። | ፺፭ |
| ፫፻፵፬ | በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በወታደር ፡ ግዴታዎች ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ ስላለመግለጽ ። | ፺፭ |
| ፫፻፵፭ | የወታደርነትን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፺፮ |
| ፫፻፵፮ | የሐሰት ፡ ወይም ፡ የማደናገር ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ፺፮ |
| | **ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **የወል ፡ ድንጋጌዎች ።** | |
| ፫፻፵፯ | በአደጋ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ። | ፺፮ |
| ፫፻፵፰ | ገንዘብን ፡ በመውደድ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ። | ፺፯ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ።** | |
| | **ደንቡ ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።** | |
| ፫፻፵፱ | የአፈጻጸሙ ፡ መሠረት ። | ፺፯ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፶ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፵፱ |
| ፫፻፶፩ | ስለ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፵፱ |
| ፫፻፶፪ | የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባሮች ፡ ወሰን ። | ፪፻፵፱ |
| ፫፻፶፫ | ጐን ፡ ለጐን ፡ የሚሄድ ፡ አፈጻጸም ፡ ተደራራቢ ፡ ቅጣቶችን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ። | ፪፻፵፱ |

አንቀጽ ፡ ፬ ።

በመንግሥቱ ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ገቢዎችና ፡ በጠቅላላ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅሞቹ ፡
ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፶፬ | በልዩ ፡ ደንብ ፡ ወንጀለኛ ፡ ስለ ፡ መባል ። | ፪፻፶ |
| ፫፻፶፭ | የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡ ዐይነታቸውና ፡ መጠናቸው ። | ፪፻፶፩ |
| ፫፻፶፮ | ተደራራቢ ፡ የሆኑ ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ቅጣቶች ። | ፪፻፶፩ |

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፶፯ | በወርቅ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ፡መንገድ ፡ ስለ ፡ መነገድ ። | ፪፻፶፩ |
| ፫፻፶፰ | ባለዋጋ ፡ ማዕድኖችንና ፡ ዕንቆችን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በንግድ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ። | ፪፻፶፪ |
| ፫፻፶፱ | ታማኝነት ፡ ባለው ፡ በመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የተንኰል ፡ አሠራር ። | ፪፻፶፪ |
| ፫፻፷ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የመንግሥትን ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ የመከፈል ፡ እንቢተኛነት ። | ፪፻፶፫ |
| ፫፻፷፩ | ግብር ፡ እንዳይከፈል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ። | ፪፻፶፫ |
| ፫፻፷፪ | በግብርና ፡ በሎሌቹ ፡ የመንግሥት ፡ ቀረጥ ፡ ገቢ ፡ ምንጮች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፪፻፶፬ |
| ፫፻፷፫ | ኬላ ፡ ስለ ፡ መስበር ፡ (ኮንትራቫንድ) ። | ፪፻፶፬ |
| ፫፻፷፬ | በመንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጕዳይና ፡ በሞኖፖል ፡ ረገድ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ። | ፪፻፶፭ |
| ፫፻፷፭ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ። | ፪፻፶፮ |

| ቍጥር ፤ | አርእስት ፤ ነገር ፤ | ገጽ ፤ |
|---|---|---|


## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ገንዘቦች ፡ ማኅተሞች ፡ ቴምብሮችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የሐሰት ፡ ገንዘብ ።

፫፻፷፮ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። ........................ ፪፻፶፮
፫፻፷፯ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ........................ ፪፻፶፮
፫፻፷፰ የገንዘቡን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። ........................ ፪፻፶፯
፫፻፷፱ ገንዘቡ ፡ እንዲዘዋወር ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ........................ ፪፻፶፯
፫፻፸ የሐሰት ፡ ገንዘብን ፡ ባገር ፡ ስለ ፡ ማስገባት ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ለስጦታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ። ........................ ፪፻፶፯

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ማኅተሞችን ፡ ቴምብሮችን ፡ ምልክቶችን ፡ በሕግ ፡ የታወቁትን ፡ ሚዛኖችንና ፡ መለኪያዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

፫፻፸፩ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱን ፡ ማኅተሞች ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ........................ ፪፻፶፰
፫፻፸፪ ሌሎችን ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ያላቸውን ፡ ማኅተሞች ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ........................ ፪፻፶፰
፫፻፸፫ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ምልክቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ፪፻፶፱
፫፻፸፬ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ቴምብሮችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ........................ ፪፻፶፱
፫፻፸፭ መመዘኛዎችንና ፡ መለኪያዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ........................ ፪፻፷
፫፻፸፮ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ማግባትና ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ በአደራ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥና ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ። ........................ ፪፻፷

### ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

፫፻፸፯ የማሳሳት ፡ ዕቅድ ፡ በሌለው ፡ አሳብ ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። ........................ ፪፷፩

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፷፰ | ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ገንዘብ ፡ በባለዋጋ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ማኅተሞች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። .... | ፻፳፩ |
| ፫፻፷፱ | የሐሰት ፡ ነገር ፡ መሥሪያዎችና ፡ መሣሪያዎች ። .... .... .. | ፻፳፪ |
| ፫፻፸ | ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ስለሚደረግለት ፡ ጕዳይ ። .... .... .... | ፻፳፪ |
| ፫፻፸፩ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ጕዳዮችና ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ። | ፻፳፫ |
| ፫፻፸፪ | የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታትን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። | ፻፳፫ |

፬ኛ ፡ መጽሐፍ ።

በሕዝብ ፡ ጥቅሞችና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

በሕዝብ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

በሰነዶች ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

| | | |
|---|---|---|
| ፫፻፸፫ | በግዙፍ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ። .... .... .... .... .... | ፻፳፬ |
| ፫፻፸፬ | በርቀት ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ። .... .... .... .... .... | ፻፳፬ |
| ፫፻፸፭ | ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። .... .... .... .... .... | ፻፳፭ |
| ፫፻፸፮ | በሐሰት ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። .... .... .... .... | ፻፳፭ |
| ፫፻፸፯ | የመንግሥትንና ፡ የወታደራዊን ፡ ሰነዶች ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በመለወጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .... .... .... .... | ፻፳፭ |
| ፫፻፸፰ | ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። .... .... .... .... .... .... | ፻፳፮ |
| ፫፻፸፱ | የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። | ፻፳፮ |
| ፫፻፹ | የንግድ ፡ ሰነዶችንና ፡ የባንክ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። .... .... .... .... | ፻፳፯ |
| ፫፻፹፩ | እንደ ፡ ዋስ ፡ ስለሚቈጠር ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፳፯ |
| ፫፻፹፪ | የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መመላለሻ ፡ ወረቀቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ በነዚሁ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። .... .... .... | ፻፳፯ |

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ።

| | | |
|---|---|---|
| ፫፻፹፫ | ስለ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ። ... .... .... .... .... | ፻፳፰ |
| ፫፻፹፬ | ሐሰተኛ ፡ የሆኑትን ፡ ግልጽ ፡ ምስክርነቶችን ፡ በማጭበርበር ፡ ስለ ፡ ማግኘት ። .... .... .... .... .... | ፻፳፱ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፺፭ | ሐሰተኛ ፡ የሐኪም ፡ ምስክር፡ ወረቀት ። | ፻፸ |
| ፫፻፺፮ | በግልጽ ፡ የታወቁ ፡ ወንጀሎች ። | ፻፸ |
| ፫፻፺፯ | ሥራ ፡ ሰጪዎችና ፡ የማደሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ፡ አሰጣጥና ፡ አመዘጋገብ ። | ፻፸፩ |
| ፫፻፺፰ | ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለመለወጫ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ጥበቦች ። | ፻፸፩ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ።** | |
| | **የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።** | |
| ፫፻፺፱ | የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ ዋጋቸውን ፡ ስለ ፡ ማርከስ ። | ፻፸፪ |
| ፬፻ | የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፻፸፪ |
| ፬፻፩ | የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማስመጣት ፡ ስለ ፡ መግዛትና ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለ ፡ መቀበል ። | ፻፸፪ |
| ፬፻፪ | የማከበድ ፡ ቅጣቶችና ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ። | ፻፸፪ |
| ፬፻፫ | ጤናን ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ ዕቃን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ መለወጥና ፡ ማበላሸት ። | ፻፸፫ |
| | **አንቀጽ ፡ ፪ ።** | |
| | **ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሊደበቅ ፡ የሚገባውን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።** | |
| ፬፻፬ | የወታደርን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፻፸፫ |
| ፬፻፭ | የሥራን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፻፸፬ |
| ፬፻፮ | የተፈቀደ ፡ የምስጢር ፡ መግለጽ ፡ ጉዳይ ። | ፻፸፬ |
| ፬፻፯ | የግል ፡ ሞያን ፡ የሥራ ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፻፸፭ |
| ፬፻፰ | እንዲገለጽ ፡ የተፈቀደ ፡ ምስጢር ። | ፻፸፭ |
| ፬፻፱ | የሳይንስን ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ወይም ፡ የንግድን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፻፸፮ |
| | **አንቀጽ ፡ ፫ ።** | |
| | **በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፬፻፲ | መሠረቱ ። | ፻፸፮ |

| ቍጥር ። | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ ። |
| --- | --- | --- |
| ፬፻፲፩ | ተደራራቢ ፡ የሆኑ ፡ የማስተዳደሪያና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቅጣቶች ። | ፫፻፷፯ |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በአግልግሎት ፡ የሥራ ፡ ግዴታዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።** | |
| ፬፻፲፪ | የሥራ ፡ ግዴታን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፫፻፷፰ |
| ፬፻፲፫ | የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ በማድረግ ፡ የአገልግሎትን ፡ ሥራ ፡ መከናወን ፡ ስለ ፡ ማወክ ። | ፫፻፷፰ |
| ፬፻፲፬ | በሥልጣን ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። | ፫፻፷፰ |
| ፬፻፲፭ | የሰውን ፡ ንብረት ፡ ለመፈተሽ ፡ ለመበርበር ፡ ወይም ፡ ዕቃውን ፡ ለመያዝ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ (መብት) ፡ ከመጠኑ ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ። | ፫፻፷፱ |
| ፬፻፲፮ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ስለ ፡ ማሰር ። | ፫፻፷፱ |
| ፬፻፲፯ | የማይገባ ፡ አሠራር ፡ ስለ ፡ መሥራት ። | ፫፻፷፱ |
| ፬፻፲፰ | እስረኛን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ መፍታትና ፡ እንዲያመልጥ ፡ ስለ ፡ መርዳት ። | ፫፻፸ |
| ፬፻፲፱ | የጦር ፡ ምርኮኞችንና ፡ የወታደር ፡ ግዞተኞችን ፡ ስለ ፡ መፍታትና ፡ እንዲያመልጡ ፡ ስለ ፡ መርዳት ። | ፫፻፸ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በሞያ ፡ ሥራ ፡ ቅንነትና ፡ ታማኝነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፬፻፳ | ለሕዝብ ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፡ የሚከናወኑትን ፡ ሥራዎች ፡ በተንኰል ፡ ዘዴ ፡ ስለ ፡ መምራት ። | ፫፻፸፩ |
| ፬፻፳፩ | በአደራ ፡ በትሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ ማዘዝ ። | ፫፻፸፪ |
| ፬፻፳፪ | በሥራ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የመውሰድና ፡ የመስረቅ ፡ ወንጀል ። | ፫፻፸፪ |
| ፬፻፳፫ | የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበል ። | ፫፻፸፫ |
| ፬፻፳፬ | በግልጽ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መነገድ ። | ፫፻፸፫ |
| ፬፻፳፭ | መደለያ ፡ ስለ ፡ መቀበል ። | ፫፻፸፬ |
| ፬፻፳፮ | በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በማስገደድ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ። | ፫፻፸፬ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ።** | |
| ፬፻፳፯ | ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ማስታወቂያዎችንና ፡ ዐዋጆችን ፡ ስለ ፡ መናቅ ። | ፫፻፸፭ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፲፪፸፰ | የማስመዝገብን ፡ ትእዛዝ ፡ ግዴታ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፪፺፭ |
| ፲፪፸፱ | ክርክሮች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ጕዳዮች ፡ እንዳይገለጹ ፡ የሚከለክለውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፪፺፮ |
| ፲፪፹ | በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድን ፡ የመፈጸም ፡ ተግባር ። | ፪፺፮ |
| ፲፪፹፩ | ሥልጣንን ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መያዝ ። | ፪፺፮ |
| ፲፪፹፪ | እሽጎችን ፡ ስለ ፡ መቅደድና ፡ ስለ ፡ መስበር ፤ በጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ። | ፪፺፯ |
| ፲፪፹፫ | መቃወምና ፡ አለመታዘዝ ። | ፪፺፯ |
| ፲፪፹፬ | የኀይልና ፡ የማስገደድ ፡ ሥራ ። | ፪፺፰ |
| ፲፪፹፭ | በኅብረት ፡ የሚፈጸም ፡ ሥራ ። | ፪፺፰ |
| ፲፪፹፮ | በግል ፡ ወዳጅነት ፡ ስለ ፡ መነገድ ። | ፪፺፱ |
| ፲፪፹፯ | ጉቦ ፡ መስጠት። | ፪፺፱ |

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### በፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፤ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፲፪፹፰ | ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ አለመግለጽ ። | ፪፺፱ |
| ፲፪፹፱ | አንድ ፡ ተከሳሽ ፤ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይቀርብ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ። | ፫፻ |
| ፲፪፺ | የፍርድን ፡ ሥራ ፡ እንዲሳሳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፫፻ |
| ፲፪፺፩ | በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወንጀል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መክሰስ ። | ፫፻ |
| ፲፪፺፪ | ለፍርድ ፡ እርዳታ ፡ መስጠትን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ። | ፫፻፩ |
| ፲፪፺፫ | ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ። | ፫፻፪ |
| ፲፪፺፬ | የፍርድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምስጢርን ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፫፻፪ |
| ፲፪፺፭ | ትክክለኛ ፡ ያልሆኑትን ፡ ወይም ፡ የተከለከሉትን ፡ የሥራ ፡ ማስታወሻዎች ፡ በአደባባይ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። | ፫፻፫ |

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### በፍርድ ፡ ላይ ፡ ሊደረግ ፡ በሚገባው ፡ በእውነተኛነትና ፡ በታማኝነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

| | | |
|---|---|---|
| ፲፪፺፮ | አንዱ ፡ ወገን ፡ ስለሚሰጠው ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ። | ፫፻፫ |

ቍጥር ፤ አርእስተ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡


፬፻፵፯ ሐሰተኛ ፡ ምስክርነት ። ............ ፻፺፬
፬፻፵፰ ቃልን ፡ ስለ ፡ ማቃናትና ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ............ ፻፺፭
፬፻፵፱ ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማግባባት ። ............ ፻፺፭
፬፻፶ በሙግት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማጭበርበር ። ............ ፻፺፭
፬፻፶፩ የፍርድን ፡ ውሳኔ ፡ ለማሳሳት ፡ በተንኰል ፡ ስለሚደረግ ፡ የወሬ ፡ መግለጽ ፡ ሥራ ። ............ ፻፺፮
፬፻፶፪ ባንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የክሕደት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ። ............ ፻፺፮

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

በወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔዎችና ፡ አፈጻጸሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

፬፻፶፫ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችንና ፡ ጠቅላላውንም ፡ የጸጥታ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላለመጠበቅ ። ............ ፻፺፮
፬፻፶፬ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ስለ ፡ ማሰናከል ። ............ ፻፺፮
፬፻፶፭ የእስረኛ ፡ ማምለጥ ። ............ ፻፺፮
፬፻፶፮ እስረኛ ፡ እንዲያመልጥ ፡ ስለ ፡ ማደራጀትና ፡ እርዳታ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ............ ፻፺፯
፬፻፶፯ የጦር ፡ ምርኮኛና ፡ የወታደር ፡ ግዞተኛ ፡ ማምለጥ ። ............ ፻፺፯
፬፻፶፰ የእስረኞች ፡ ግር ፡ ግር ። ............ ፻፺፰
፬፻፶፱ ከግዞት ፡ ቦታ ፡ ስለማምለጥ ። ............ ፻፺፰

አንቀጽ ፡ ፭ ።

ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ የምርጫ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ።

፬፻፷ ለምርጫ ፡ ጉዳይ ፡ የሚደረገውን ፡ ስብሰባና ፡ የሥራ ፡ መከናወን ፡ ስለ ፡ ማወክና ፡ ስለ ፡ ማሰናከል ። ............ ፪፻
፬፻፷፩ የምርጫ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠትን ፡ ወይም ፡ የመምረጥን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መንካት ። ............ ፪፻
፬፻፷፪ በምርጫ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመደለያ ፡ ስጦታ ። ............ ፪፻፩
፬፻፷፫ የማይገባ ፡ አሠራር ። ............ ፪፻፩
፬፻፷፬ ባመዘጋገብ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ የማጭበርበር ፡ ወንጀል ። ............ ፪፻፩
፬፻፷፭ በድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ። ............ ፪፻፪
፬፻፷፮ የተለዩ ፡ ወንጀሎች ። ............ ፪፻፫

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፩፻፷፯ | የድምፅ ፡ መስጠትን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። ···· ···· | ፪፻፫ |
| ፩፻፷፰ | የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶችንና ፡ የመሰብሰቢያቸውን ፡ ማጥን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። ···· | ፪፻፫ |
| ፩፻፷፱ | ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ። ···· ···· ···· ···· ···· ···· ···· | ፪፻፬ |
| ፩፻፸ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ። ···· ···· ·· ···· ···· | ፪፻፬ |

አንቀጽ ፡ ፯ ።

በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ በሕዝብ ፡ ሰላም ፡ በሕዝብ ፡ ረግቶ ፡ መኖር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡

ወንጀሎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ወንጀሎች ፡ እንዲሠሩ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያነሣሡ ፡ ሥራዎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩፻፸፩ | አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ። ···· ···· ···· ···· ···· | ፪፻፬ |
| ፩፻፸፪ | የከፋ ፡ አድራጊዎች ፡ ማኅበረተኛነት ። ···· ···· ···· ···· | ፪፻፭ |
| ፩፻፸፫ | የከፋ ፡ አድራጊዎች ፡ መጠጊያና ፡ ረዳት ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፪፻፮ |
| ፩፻፸፬ | ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ በጅቷል ፡ በማለት ፡ ስለሚደረግ ፡ መቀስቀስ ። ···· ···· ···· ···· | ፪፻፯ |
| ፩፻፸፭ | በተከለከሉ ፡ መሣሪያዎች ፡ መነገድ ። ···· ···· ···· ···· | ፪፻፯ |

ክፍል ፡ ፪ ።

የሕዝብ ፡ ሁከት ፡ እንዲነሣ ፡ የሚያደርጉ ፡ የማነሣሣት ፡ ጠባይ ፡

ያላቸው ፡ ሥራዎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩፻፸፮ | የተከለከሉ ፡ ማኅበሮችና ፡ ስብሰባዎች ። ···· ···· ···· ···· | ፪፻፰ |
| ፩፻፸፯ | ድብቅ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ክፍሎች ። | ፪፻፰ |
| ፩፻፸፰ | የተከለከሉ ፡ ስብሰባዎች ። ···· ···· ···· ···· ···· ···· | ፪፻፰ |
| ፩፻፸፱ | በወሬ ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማሸበር ። ···· ···· ···· ···· ·· | ፪፻፱ |
| ፩፻፹ | የሐሰት ፡ ወሬዎችን ፡ ስለ ፡ ማውራትና ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ። ···· ···· ···· ···· ···· ···· ···· | ፪፻፱ |
| ፩፻፹፩ | የማነሣሣት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሐሳብ ፡ መግለጫዎች ፡ (ማኒፌስታሲዮን) ። ···· ···· ···· ···· ···· ···· ···· | ፪፻፲ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
| --- | --- | --- |
| ፬፻፹፪ | ሽብር ። | ፪፻፲ |
| ፬፻፹፫ | ልዩ ፡ አስተያየት ፡ የሚደረግላቸው ፡ ጕዳዮች ፡ መታዘዝ ። | ፪፻፲ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በሕዝብ ፡ ሰላምና ፡ በሕዝብ ፡ ረግቶ ፡ መኖር ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ወንጀል ።** | |
| ፬፻፹፬ | ስብሰባንና ፡ ጉባኤን ፡ ስለ ፡ መበጥበጥ ። | ፪፻፲፩ |
| ፬፻፹፭ | በጥፋተኛነት ፡ ከኀላፊነት ፡ ውጭ ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠሩ ፡ ተግባሮች ። | ፪፻፲፩ |
| ፬፻፹፮ | የሃይማኖትን፡ ስሜትና ፡ ሰላም ፡ ስለ ፡ መንካት ። | ፪፻፲፪ |
| ፬፻፹፯ | የሙታንን ፡ ሰላምና ፡ ክብር ፡ መንካት ። | ፪፻፲፪ |
| | **አንቀጽ ፡ ፯ ።** | |
| | **በጋራ ፡ ጸጥታ ፡ (ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲቭና) ፡ በመገናኛዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **በጋራ ፡ ጸጥታ ፡ (ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲቭ) ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፬፻፹፰ | የእሳት ፡ ቃጠሎ ። | ፪፻፲፪ |
| ፬፻፹፱ | ፍጥረታውያን ፡ መቅሠፍቶችን ፡ ስለ ፡ መቀስቀስ ። | ፪፻፲፫ |
| ፬፻፺ | የሥራ ፡ ቦታዎችንና ፡ የመጠባበቂያ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለ ፡ መጐዳት ። | ፪፻፲፫ |
| ፬፻፺፩ | ስለ ፡ ማፈንዳት ። | ፪፻፲፫ |
| ፬፻፺፪ | በቸልተኝነት ፡ የሚደረግ ፡ ወንጀል ። | ፪፻፲፫ |
| ፬፻፺፫ | በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ በሚመርዙ ፡ ጋዞች ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። | ፪፻፲፬ |
| ፬፻፺፬ | በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ መሥራት ፡ መግዛት ፡ መሸ ወርና ፡ ማመላለስ ። | ፪፻፲፬ |
| ፬፻፺፭ | የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ደንቦችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፪፻፲፭ |
| ፬፻፺፮ | መጠባበቂያ ፡ የሚሆኑትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ የሚያገ ለግሉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ማጥፋት ፡ ወይም ፡ አለማደራጀት ። | ፪፻፲፭ |
| ፬፻፺፯ | በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሲደርስ ፡ ባለማስታወቅ ፡ የሚ ደረግ ፡ ጥፋት ። | ፪፻፲፮ |
| ፬፻፺፰ | የማይነኩ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፲፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | ምዕራፍ ፡ ፪ ። | |
| | በመገናኛዎች ፡ ጸጥታና ፡ ንጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ። | |
| ፱፻፺፱ | ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ በተቋቋሙ ፡ ሥራዎችና ፡ አገልግሎቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፫፻፲፯ |
| ፲፻ | በመገናኛዎችና ፡ በሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ከባድ ፡ ጉዳትና ፡ መበላሸት ። | ፫፻፲፯ |
| ፲፻፩ | ምልክቶችንና ፡ የእርዳታ ፡ ጥሪዎችን ፡ አላገባብ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ | ፫፻፲፰ |
| ፲፻፪ | ለሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ለሆኑት ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ፫፻፲፰ |
| | አንቀጽ ፡ ፰ ። | |
| | በሕዝብ ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ። | |
| | ምዕራፍ ፡ ፩ ። | |
| | ለጥበቃ ፡ በተደረጉት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ። | |
| ፲፻፫ | የሰውን ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ማባዛት ። | ፫፻፲፱ |
| ፲፻፬ | የከብት ፡ በሽታን ፡ ስለ ፡ ማባዛት ። | ፫፻፲፱ |
| ፲፻፭ | የሰብልን ፡ ወይም ፡ የደንን ፡ ትል ፡ ስለ ፡ መንዛት። | ፫፻፳ |
| ፲፻፮ | ውሃን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። | ፫፻፳ |
| ፲፻፯ | ግጦሽን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። | ፫፻፳ |
| ፲፻፰ | የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፫፻፳ |
| ፲፻፱ | ችግር ፡ ወይም ፡ ረኃብ ፡ እንዲመጣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፫፻፳፩ |
| ፲፻፲ | መርዛም ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ነገሮችን ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፡ መሥራት ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ማድረግ ። | ፫፻፳፩ |
| ፲፻፲፩ | የሚጎዱ ፡ ወይም ፡ የተበላሹ ፡ ምግቦችንና ፡ ዕቃዎችን ፡ መሥራትና ፡ መሸጥ ። | ፫፻፳፪ |
| ፲፻፲፪ | ለከብት ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ድርቆሽና ፡ ሌላም ፡ ምግብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ ማበላሸትና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ። | ፫፻፳፫ |
| ፲፻፲፫ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ። | ፫፻፳፫ |
| ፲፻፲፬ | አልኮል ፡ ወይም ፡ እስፒርቶ ፡ ያለባቸውን ፡ መጠጦች ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ፫፻፳፫ |
| ፲፻፲፭ | አእምሮን ፡ በሚነኩ ፡ ሥራዎች ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፫፻፳፬ |

ቍጥር ፡ አርእስተ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡


፭፻፲፮ ሥራይ ፡ በሚሆኑ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ፪፻፹፬

፭፻፲፯ ከባዶች ፡ ሁኔታዎች ። ፪፻፹፬

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

የሕክምና ፡ ጠባይ ፡ ባላቸው ፡ የመጠበቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

፭፻፲፰ የሕክምናንና ፡ የጤና ፡ አጠባበቅን ፡ ሥራ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። ፪፻፹፬

፭፻፲፱ መርዛምና ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ፪፻፹፭

፭፻፳ የሕክምና ፡ እርዳታን ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መከልከል ። ፪፻፹፭

፭ኛ ፡ መጽሐፍ ።

በሌሎች ፡ ሰዎችና ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

በሰው ፡ ሕይወትና ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ የወንጀል ፡ ሥራዎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

በሕይወት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

መግደልና ፡ አደራረጉ ።

፭፻፳፩ መሠረቱ ። ፪፻፹፮

፭፻፳፪ ከባድ ፡ (የግፍ) ፡ አገዳደል ። ፪፻፹፮

፭፻፳፫ ተራ ፡ የሆነ ፡ አገዳደል ፡ (ግዳይ) ። ፪፻፹፮

፭፻፳፬ የመግደልን ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ ማቅለል ። ፪፻፹፮

፭፻፳፭ ራሱን ፡ እንዲገድል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማገዝ ። ፪፻፹፮

፭፻፳፮ በቸልተኝነት ፡ ስለ ፡ መግደል ። ፪፻፹፯

፭፻፳፯ ሕፃንን ፡ ስለ ፡ መግደል ። ፪፻፹፯

ክፍል ፡ ፪ ።

በፅንስ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ።

ስለ ፡ ማስወረድ ።

፭፻፳፰ መሠረቱ ። ፪፻፹፯

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፵፱ | እናት ፡ የፈጸመችው ፡ የማስወረድ ፡ ትግባር ። | ፱፻፵፱ |
| ፭፻፶ | ሦስተኛ ፤ ሰው ፡ የፈጸመው ፡ የማስወረድ ፡ ትግባር ። | ፱፻፵፱ |
| ፭፻፶፩ | ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ በማድረግ ፡ ፅንስ ፡ ማስወረድን ፡ የማስፈጸም ፡ ተግባር ። | ፱፻፵፱ |
| ፭፻፶፪ | እርግዝና ፡ በሌላት ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ የማስወረድን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ። | ፱፻፶ |
| ፭፻፶፫ | ቅጣትን ፡ ስለሚያቀሉ ፡ ሁኔታዎች ። | ፱፻፶ |
| ፭፻፶፬ | በሕክምና ፡ ፅንስን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ። | ፱፻፶ |
| ፭፻፶፭ | ያለ ፡ ደንብ ፡ የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መቅጣት ። | ፱፻፶፩ |
| ፭፻፶፮ | ስለሚያስቸሥል ፡ ሁኔታ ። | ፱፻፶፩ |


ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በሰው ፡ አካልና ፡ በሰው ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፶፯ | መሠረቱ ። | ፱፻፶፪ |
| ፭፻፶፰ | አስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ። | ፱፻፶፪ |
| ፭፻፶፱ | አስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ቀላል ፡ የአካል ፡ ጉዳት ። | ፱፻፶፪ |
| ፭፻፷ | ካድራጊው ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ የጥፋት ፡ ውጤት ። | ፱፻፶፫ |
| ፭፻፷፩ | የሚያጠራጥሩ ፡ ሁኔታዎች ፡ የዐዋቂ ፡ ምርመራ ። | ፱፻፶፫ |
| ፭፻፷፪ | ቅጣትን ፡ ስለሚያቀሉ ፡ ሁኔታዎች ። | ፱፻፶፫ |
| ፭፻፷፫ | በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሱ ፡ የአካል ፡ ጉዳቶች ። | ፱፻፶፬ |
| ፭፻፷፬ | የእጅ ፡ እልፊት ። | ፱፻፶፬ |


ምዕራፍ ፡ ፫ ።

በሰው ፡ ሕይወት ፤ በሰው ፡ አካል ፤ በሰው ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡
በማድረስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፷፭ | የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ለአደጋ ፡ ማጋለጥ ። | ፱፻፶፭ |
| ፭፻፷፮ | ሰውን ፡ በአደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማጋለጥና ፡ ስለ ፡ መተው ። | ፱፻፶፭ |
| ፭፻፷፯ | አንድ ፡ ሰው ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለመርዳት ። | ፱፻፶፭ |
| ፭፻፷፰ | ልጆችን ፡ ስለ ፡ መጉዳት ። | ፱፻፶፯ |

| ቍጥር ፡ | አርእስቱ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፵፱ | ስለ ፡ አምባጓሮ ። | ፪፻፵፯ |
| ፭፻፶ | የይዋጣልን ፡ ፉክክር ። | ፪፻፵፰ |
| ፭፻፶፩ | የይዋጣልን ፡ ፉክክርን ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ፤ ስለ ፡ ማደፋፈር ፤ በፉክክር ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ መገኘት ። | ፪፻፵፰ |


አንቀጽ ፡ ፪ ።

በሰው ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

በሰው ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።


| ቍጥር ፡ | አርእስቱ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፶፪ | ስለ ፡ ዛቻ ። | ፪፻፵፰ |
| ፭፻፶፫ | የመክሰስ ፡ ወይም ፡ የማዋረድ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ዛቻ ። | ፪፻፵፰ |
| ፭፻፶፬ | ስለ ፡ ማስገደድ ። | ፪፻፵፱ |
| ፭፻፶፭ | የማሰብን ፡ ችሎታ ፡ ስለ ፡ ማሳጣት ። | ፪፻፵፱ |
| ፭፻፶፮ | የተቀላቀሉ ፡ ወንጀሎች ። | ፪፻፵፱ |
| ፭፻፶፯ | ሰውን ፡ በግድ ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ። | ፪፻፶ |
| ፭፻፶፰ | ስለ ፡ መጥለፍ ። | ፪፻፶ |
| ፭፻፶፱ | ክፉና ፡ በጎ ፡ ለይታ ፡ ለማወቅ ፡ የማትችልና ፡ የመከላከል ፡ ዐቅም ፡ የሌላትን ፡ ሴት ፡ ስለ ፡ መጥለፍ ። | ፪፻፶ |
| ፭፻፷ | ሕፃንን ፡ ስለ ፡ መዝረፍ ፡ (ስለ ፡ መንጠቅ) ። | ፪፻፶፩ |
| ፭፻፷፩ | ቅጣቱን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፶፩ |
| ፭፻፷፪ | ሕፃኑን ፡ ስላለማቅረብ ። | ፪፻፶፪ |
| ፭፻፷፫ | ስለ ፡ ወላጆች ፡ የሚደረግ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ። | ፪፻፶፪ |
| ፭፻፷፬ | በፖለቲካ ፡ ምክንያት ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መሰረቅ ። | ፪፻፶፪ |
| ፭፻፷፭ | ሰውን ፡ በማይገባ ፡ አገልጋይ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፪፻፶፫ |
| ፭፻፷፮ | የጥበቃ ፡ ወይም ፡ የመቈጣጠር ፡ ጕድለት ። | ፪፻፶፫ |
| ፭፻፷፯ | በሰዎች ፡ ለመነገድ ፡ የተቋቋሙ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ማኅበሮች ። | ፪፻፶፫ |


ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በሌሎች ፡ የሰው ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስቱ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፷፰ | የብሔራዊ ፡ መብቶችን ፡ ነጻ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መድፈር ። | ፪፻፶፬ |
| ፭፻፷፱ | የነጻ ፡ መዘዋወር ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መድፈር ። | ፪፻፶፬ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፭፻፷ | የሥራ ፡ ነጻነትን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ መድፈር ። | ፱፻፺፬ |
| ፭፻፷፩ | መኖሪያ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ። | ፱፻፺፭ |
| ፭፻፷፪ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ። | ፱፻፺፭ |
| ፭፻፷፫ | ደብዳቤዎችንና ፡ የሚላኩ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ። | ፱፻፺፮ |


## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## በክብር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።


| | | |
|---|---|---|
| ፭፻፷፬ | መሠረቱ ። | ፱፻፺፯ |
| ፭፻፷፭ | የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመበት ፡ ዐይነት ። | ፱፻፺፯ |
| ፭፻፷፮ | ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ሲሆን ፡ ስለሚሰጠው ፡ ቅጣት ። | ፱፻፺፯ |
| ፭፻፷፯ | የገንዘብ ፡ ካሣ ። | ፱፻፺፰ |
| ፭፻፷፰ | የማይደፈር ፡ መብት ። | ፱፻፺፰ |
| ፭፻፷፱ | የማያስቀጣ ፡ ግምት ፡ መስጠትና ፡ ንግግር ። | ፱፻፺፰ |


### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### የተለዩ ፡ ድንጋጌዎች ፤ ክብርን ፡ ስለ ፡ መንካት ።


| | | |
|---|---|---|
| ፭፻፸ | ስምን ፡ ስለ ፡ ማጥፋትና ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወንጀል ። | ፱፻፺፱ |
| ፭፻፸፩ | እውነትንና ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ጥቅሞች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የሚደረገው ፡ ልዩነት ። | ፲፻ |
| ፭፻፸፪ | የግል ፡ አኗኗርን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። | ፲፻ |
| ፭፻፸፫ | ስድብና ፡ ማዋረድ ። | ፲፻ |
| ፭፻፸፬ | ስለ ፡ ጠብ ፡ ማንሣትና ፡ ስለ ፡ ጠቡ ፡ መልስ ። | ፲፻፩ |
| ፭፻፸፭ | ቃልን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። | ፲፻፩ |
| ፭፻፸፮ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። | ፲፻፩ |
| ፭፻፸፯ | መደበኛ ፡ የሆነ ፡ የክስ ፡ አቤቱታና ፡ ክስ ። | ፲፻፪ |
| ፭፻፸፰ | ጠፍተው ፡ የቀሩትን ፡ ወይም ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ መንካት ። | ፲፻፪ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **አንቀጽ ፡ ፲ ።** | |
| | **በመልካም ፡ ጠባይና ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **በመልካም ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።** | |
| ፭፻፹፱ | የመድፈር ፡ ሥራ ። …. …. …. …. …. …. …. | ፪፻፶፫ |
| ፭፻፺ | በንጽሕና ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የኀይል ፡ ተግባር ። | ፪፻፶፫ |
| ፭፻፺፩ | ለመቃወም ፡ በማይችሉ ፡ አእምሮዋቸው ፡ በተበላሸ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ደካማ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ፡ ስለሚደረግ ፡ የድፍረት ፡ በደል ። …. …. …. …. | ፪፻፶፬ |
| ፭፻፺፪ | በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ በተገኙ ፡ ሰዎች ፡ በተጋዙ ፡ ወይም ፡ በታሰሩ ፡ ሰዎች ፡ ክብረ፡ንጽሕና፡ላይ፡ስለሚደረግ፡በደል ። | ፪፻፶፬ |
| ፭፻፺፫ | ከፍ ፡ ያለውን ፡ የሴት ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ ተገዥነትዋን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚደረገው ፡ የማታለል ፡ ሥራ ። | ፪፻፶፬ |
| ፭፻፺፬ | በሕፃናቶች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ በደል ። | ፪፻፶፭ |
| ፭፻፺፭ | ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ እስከ፡ ዐሥራ፡ ስምንት፡ ዓመት፡ ዕድሜ ፡ ባላቸው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ በደል ። …. …. …. | ፪፻፶፭ |
| ፭፻፺፮ | ማሳት ። …. …. …. …. …. …. …. …. | ፪፻፶፮ |
| ፭፻፺፯ | አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ተታላይ ፡ የማይቀጣ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። …. …. …. …. …. …. …. | ፪፻፶፮ |
| ፭፻፺፰ | ከባዶች ፡ ሁኔታዎች ። .. …. …. …. …. …. …. | ፪፻፶፮ |
| ፭፻፺፱ | በደሉ ፡ ጋብቻን ፡ ባስከተለ ፡ ጊዜ ፡ ክስ ፡ ቀሪ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፪፻፶፮ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ስለ ፡ ተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ መበላሸት ።** | |
| ፮፻ | ለተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ። | ፪፻፶፮ |
| ፮፻፩ | ቅጣቱን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ። …. …. …. …. | ፪፻፶፮ |
| ፮፻፪ | ለተፈጥሮ ፡ ተግባር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ። | ፪፻፶፯ |
| ፮፻፫ | የተፈጥሮ ፡ ግብሩ ፡ መበላሸት ፡ ስለ ፡ መታወቁ ። … …. | ፪፻፶፯ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በሌላ ፡ ሰው ፡ አመንዝራነት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።** | |
| ፮፻፬ | የሌላውን ፡ ሰው ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ፡ የዘወትር ፡ መጠቀሚያ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ........................ | ፪፻፸፰ |
| ፮፻፭ | ሴቶችንና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሱትን ፡ በማቃጠር ፡ በማከራየት ፡ ስለ ፡ መነገድ ። ........................ | ፪፻፸፱ |
| ፮፻፮ | ስለ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ። ........................ | ፪፻፸፱ |
| ፮፻፯ | ሴቶችን ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ለዝሙት ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚደረጉት ፡ ዝግጅቶች ። ............ | ፪፻፹ |
| | **ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **መልካም ፡ በሆነው ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፮፻፰ | ክብረ ፡ ንጽሕናንና ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የሚያሳፍር ፡ ሥራን ፡ በአደባባይ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። .... | ፪፻፹ |
| ፮፻፱ | ኀፍረተ ፡ ነገርን ፡ የሚያሳዩ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አሳትሞ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ። | ፪፻፹፩ |
| ፮፻፲ | አሳፋሪ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ስለ ፡ ማሳየት ። ........................ | ፪፻፹፩ |
| ፮፻፲፩ | ስለ ፡ ተፈቀዱ ፡ ሥራዎች ። ........................ | ፪፻፹፪ |
| ፮፻፲፪ | መልካም ፡ ጠባይን ፡ የሚነኩ ፡ ነገሮችን ፡ ለሕዝብ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ። ............ | ፪፻፹፪ |
| ፮፻፲፫ | አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ልጆች ፡ በሕሊና ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ከሚጥሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ሥዕሎች ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። | ፪፻፹፪ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፱ ።** | |
| | **በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፮፻፲፬ | ጋብቻን ፡ በተንኰል ፡ በማታለል ፡ ስለ ፡ መፈጸም ። ........ | ፪፻፹፫ |
| ፮፻፲፭ | በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ መፈጸም ። | ፪፻፹፫ |
| ፮፻፲፮ | በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። .............. | ፪፻፹፫ |

| ቍጥር ፤ | አርእስተ ፡ ነገር ፤ | ገጽ ፤ |
|---|---|---|
| ፯፻፲፯ | የተለየ ፡ ሁኔታ ። | ፰፻፳፪ |
| ፯፻፲፰ | ስለ ፡ ሴሰኝነት ። | ፰፻፳፪ |
| ፯፻፲፱ | የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ መሞት ። | ፰፻፳፪ |
| ፯፻፳ | ቅጣትን ፡ የሚያከብድ ፡ ሁኔታ ። | ፰፻፳፫ |
| | **ክፍል ፤ ፪ ።** | |
| | **በዘመዶች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረግ ፡ የዝሙት ፤ ወንጀል ።** | |
| ፯፻፳፩ | በዘመድ ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የዝሙት ፡ ተግባር ። | ፰፻፳፭ |
| ፯፻፳፪ | በሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ ክብረ ፡ ንጽሕናን ፡ በሚያበላሽ ፤ ተግባር ፡ ስለ ፡ መደፋፈር ። | ፰፻፳፭ |
| | **ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **በክብር ፤ መዝገብና ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፤ ስለሚሠራ ፤ ወንጀል ።** | |
| ፯፻፳፫ | የሕፃኑን ፡ መወለድ ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ። | ፰፻፳፯ |
| ፯፻፳፬ | የሕዝብን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ሕፃኑን ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ከተባለው ፡ መዝገብ ፤ ስለ ፡ መሰረዝ ። | ፰፻፳፯ |
| ፯፻፳፭ | ቀለብ ፡ የመስጠት ፡ ተግባርን ፡ ስላለመፈጸም ። | ፰፻፳፯ |
| ፯፻፳፮ | ልጅን ፡ የማሳደግ ፡ ተግባርን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፰፻፳፰ |

## ፯ኛ ፡ መጽሐፍ ።

### በሀብቶች ፤ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፤ ወንጀሎች ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### በንብረት ፤ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፤ ወንጀል ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፳፯ | መሠረቱ ። | ፰፻፳፯ |
| ፯፻፳፰ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መክበር ። | ፰፻፳፰ |
| ፯፻፳፱ | በቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ በኩል ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፤ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ። | ፰፻፳፰ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **በተንቀሳቃሽ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፮፻፴ | ስለ ፡ ስርቆት ። | ፪፻፷፱ |
| ፮፻፴፩ | የሥራ ፡ ኀይልን ፡ ስለ ፡ መስረቅ ። | ፪፻፸ |
| ፮፻፴፪ | የጋራ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ ስለ ፡ መስረቅ ። | ፪፻፸ |
| ፮፻፴፫ | በሙታን ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ። | ፪፻፸ |
| ፮፻፴፬ | ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት ። | ፪፻፸ |
| ፮፻፴፭ | ከባድ ፡ ስርቆት ። | ፪፻፸ |
| ፮፻፴፮ | ስለ ፡ ወንበዴነት ። | ፪፻፸፪ |
| ፮፻፴፯ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ። | ፪፻፸፪ |
| ፮፻፴፰ | ስለ ፡ ዘረፋ ። | ፪፻፸፫ |
| ፮፻፴፱ | የባሕር ፡ ወንበዴነት ። | ፪፻፸፫ |
| ፮፻፵ | የተጠበቁ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፸፬ |
| ፮፻፵፩ | እምነትን ፡ ስለ ፡ ማጕደል ። | ፪፻፸፬ |
| ፮፻፵፪ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ የእምነት ፡ ማጕደል ። | ፪፻፸፭ |
| ፮፻፵፫ | አግኝቶ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ። | ፪፻፸፭ |
| ፮፻፵፬ | የሌላ ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። | ፪፻፸፮ |
| ፮፻፵፭ | ወድቆ ፡ የተገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ለራስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፪፻፸፮ |
| ፮፻፵፮ | ባለቤት ፡ የሌለውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ። | ፪፻፸፯ |
| ፮፻፵፯ | የመሸሸግ ፡ ወንጀል ። | ፪፻፸፯ |
| ፮፻፵፰ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ የመሸሸግ ፡ ወንጀል ። | ፪፻፸፯ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።** | |
| ፮፻፵፱ | በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ ስዶ ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። | ፪፻፸፰ |
| ፮፻፶ | በሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፪፻፸፱ |
| ፮፻፶፩ | በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። | ፪፻፸፱ |
| ፮፻፶፪ | የወሰን ፡ ምልክቶችን ፡ ከስፍራቸው ፡ ስለ ፡ ማዘዋወርና ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። | ፪፻፸፱ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ክፍል ፡ ፫ ።

### በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።


፯፻፶፫ መደበኛ ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹

፯፻፶፬ ከባድ ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹

፯፻፶፭ የተለዩ ፡ አሠራሮች ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፩


## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### በንብረት ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

### በማታለል ፡ የተመሠረቱ ፡ ወንጀሎች ።


፯፻፶፮ ስለ ፡ አታላይነት ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፩

፯፻፶፯ ልዩ ፡ ሁናቴ ፤ ስንቅ ፡ ሳይኖር ፡ ቼክ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። .... ፪፻፹፪

፯፻፶፰ ስለ ፡ ከባድ ፡ አታላይነት ። .... .... .... .... .... ፪፻፹፪

፯፻፶፱ የኢንሹራንስን ፡ ኩባንያ ፡ ስለ ፡ ማታለል ። .. .... .... ፪፻፹፪

፯፻፷ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ማታለል ። .. .... .... .... .... .... ፪፻፹፫

፯፻፷፩ በሕዝብ ፡ እምነት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ። .. .... .... .... ፪፻፹፫

፯፻፷፪ አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ የማታለል ፡ ሥራዎች ። .... .... .... ፪፻፹፫

፯፻፷፫ በግል ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ አመራር ። ፪፻፹፬

፯፻፷፬ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ተንኰል ፡ ያለበት ፡ የሥራ ፡ አመራር ። .... ፪፻፹፬

፯፻፷፭ ጥቅም ፡ ታገኛለህ ፡ በማለት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በመደለል ፡ ስለ ፡ ማንሣሣት ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፭

፯፻፷፮ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ንብረታቸውን ፡ የሚጎዳ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ስለ ፡ ማንሣሣት ። .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፭


## ክፍል ፡ ፪ ።

### የሕሊናን ፡ ወይም ፡ የሰውነትን ፡ ችግር ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።


፯፻፷፯ አራጣ ። .... .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፯

፯፻፷፰ ስለ ፡ መንጠቅ ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፯

፯፻፷፱ ስለ ፡ ማስፈራራት ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፯

፯፻፸ ከባድ ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፹፯

ቍጥር ፤ አርእስተ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡


አንቀጽ ፡ ፪ ።

በንግድና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ግዙፍ ፡ ባልሆኑ ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

፮፻፶፩ በሌላ ፡ ሰው ፡ ታማኝነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ፪፻፹፯
፮፻፶፪ ጉዳትን ፡ የሚያደርሱ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫዎች ። ..... ፪፻፹፰
፮፻፶፫ የማይገባ ፡ ውድድር ። ... .... .... .... .... .... ፪፻፹፰
፮፻፶፬ የፋብሪካ ፡ ምልክቶችን ፡ (ማርኮችን) ፡ የመጡበትን ፡ ስፍራ ፡ ማመልከቻ ፡ ጽሑፎችን ፤ ሥዕሎችንና ፡ ዐይነቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። .... .... .... .... ፪፻፺
፮፻፶፭ የድርሰት ፡ መጻሕፍትን ፡ ወይም ፡ የጥበብ ፡ ሥራዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። .... .... .... .... ፪፻፺
፮፻፶፮ የተከለከሉትን ፡ ድርሰቶች ፡ ስለ ፡ ማሳየት ፡ ወይም ፡ ማሠራት ። ፪፻፺
፮፻፶፯ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ መብት ። .... .... .... .... .... ፪፻፺
፮፻፶፰ የተለዩ ፡ ወንጀሎች ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፺
፮፻፶፱ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፩

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በክስ ፡ አቀራረብ ፡ በፍርድ ፡ በተያዘ ፡ ነገርና ፡ በአከማሠር ፡ ጕዳይ ፡ አሠራር ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ።

፮፻፷ በአጭበርባሪነት ፡ ዕዳ ፡ ለመክፍል ፡ ስላለመቻል ። .. .... ፪፻፺፩
፮፻፷፩ ስለ ፡ መክሠር ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፩
፮፻፷፪ በአጭበርባሪነት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ፪፻፺፪
፮፻፷፫ በተያዘ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የአጭበርባሪነት ፡ ወንጀል ፡ ስለ ፡ መሥራት ። .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፫
፮፻፷፬ በመያዣ ፡ ስም ፡ የተቀመጡትን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የተያዙትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፤ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። .... .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፫
፮፻፷፭ በፍርድ ፡ የተያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። ... .... .... .... .... ፪፻፺፬
፮፻፷፮ የማይገባ ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ ማስገኘት ። .. .... .... .... ፪፻፺፬
፮፻፷፯ የድምፅ ፡ ብልጫን ፡ ለማግኘት ፡ መደለያ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ፪፻፺፬
፮፻፷፰ የስምምነት ፡ ድምፅ ፡ አጭበርብሮ ፡ ስለ ፡ ማግኘት ። .... ፪፻፺፮

| ቍጥር ፤ | አርእስተ ፡ ነገር ፤ | ገጽ ፤ |
|---|---|---|
| ፮፻፹፱ | በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። | ፪፻፺፭ |
| | **፫ኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።** | |
| | **የደንብ ፡ ትላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ኮንትራቨንሲዮን) ።** | |
| | **፩ኛ ፡ መጽሐፍ ።** | |
| | **ጠቅላላ ፡ ክፍል ።** | |
| | **አንቀጽ ፡ ፩ ።** | |
| | **ተቀጭነትንና ፡ ደንብ ፡ መተላለፍን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **የሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚደርስበት ፡ ወሰን ።** | |
| ፮፻፺ | ጠቅላላዎቹን ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦች ፡ ስለ ፡ መመልከት ። | ፪፻፺፮ |
| ፮፻፺፩ | ስለ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ። | ፪፻፺፮ |
| ፮፻፺፪ | በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡ የሕጉ ፡ ተፈጻሚነት ። | ፪፻፺፮ |
| ፮፻፺፫ | በሰው ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡ የሕጉ ፡ ተፈጻሚነት ። | ፪፻፺፯ |
| ፮፻፺፬ | በቦታ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ የሕጉ ፡ ተፈጻሚነት ። | ፪፻፺፯ |
| ፮፻፺፭ | በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሰጠው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ። | ፪፻፺፰ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **ስለ ፡ ተቀጪነት ።** | |
| ፮፻፺፮ | የሚያስቀጡ ፡ ተግባሮችና ፡ የሚቀጡ ፡ ሰዎች ። | ፪፻፺፰ |
| ፮፻፺፯ | የሚያስቀጡ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፺፱ |
| ፮፻፺፰ | ነገርን ፡ ስለ ፡ ማጣራት ፡ የሚሰጡ ፡ ሁኔታዎች ። | ፪፻፺፱ |
| ፮፻፺፱ | ይቅርታዎችና ፡ ቅጣትን ፡ ማቃለል ። | ፪፻፺፱ |
| ፯፻ | ስሕተት ። | ፫፻ |
| ፯፻፩ | የሚያቀሉና ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ። | ፫፻ |

**አንቀጽ ፡ ፪ ።**

**ቅጣቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ።**

**ምዕራፍ ፡ ፩ ።**

**የሚፈጸሙ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ።**

| ቍጥር ፣ | አርእስተ ፣ ነገር ፣ | ገጽ ፣ |
|---|---|---|
| | **ክፍል ፣ ፩ ።** | |
| | **ዋና ፣ ቅጣቶች ።** | |
| ፯፻፩ | ደንበኛ ፣ በሆኑት ፣ በወንጀል ፣ ቅጣቶች ፣ ስላለመሥራት ። | ፫፻ |
| ፯፻፪ | የማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ። .... .... .... .... .... | ፫፻፩ |
| ፯፻፫ | መደበኛ ፣ የሆነ ፣ ወይም ፣ የፖሊስ ፣ የማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ። | ፫፻፩ |
| ፯፻፬ | በቤቱ ፣ የሚደረግ ፣ የማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ። .... .... .... | ፫፻፪ |
| ፯፻፭ | የቅጣቱ ፣ አፈጻጸም ፤ ስለ ፣ ወታደሮችና ፣ አካለ ፣ መጠን ፣ ስላላደረሱ ፣ ልጆች ፣ ልዩ ፣ ሁኔታ ። .... .... .... .... | ፫፻፪ |
| ፯፻፮ | በማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ፣ ፈንታ ፣ የሚደረግ ፣ የግዴታ ፣ ሥራ ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፫ |
| ፯፻፯ | መቀጫ ፣ — መደበኛ ፣ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... | ፫፻፫ |
| ፯፻፰ | መቀጫን ፣ ስላለመክፈል ፤ በመታገድ ፣ ወይም ፣ በግዴታ ፣ ሥራ ፣ መቀጫን ፣ መለወጥ ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፬ |
| ፯፻፲ | መቀጮን ፣ ስለ ፣ ማስገባት ፣ — ስለ ፣ ወታደሮችና ፣ አካለ ፣ መጠን ፣ ስላላደረሰ ፣ ሕፃን ፣ ልዩ ፣ ሁኔታ ። .... .... .... | ፫፻፬ |
| ፯፻፲፩ | የጉዳት ፣ ካሣ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፭ |
| | **ክፍል ፣ ፪ ።** | |
| | **ተጨማሪና ፣ ተደራቢ ፣ የሆኑ ፣ ቅጣቶች ።** | |
| ፯፻፲፪ | ማስጠንቀቂያና ፣ ወቀሳ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፭ |
| ፯፻፲፫ | ከመብት ፣ የመሻር ፣ ቅጣት ፣ ተፈጻሚ ፣ ስላለመሆኑ ። .... | ፫፻፭ |
| | **ክፍል ፣ ፫ ።** | |
| | **የጸጥታ ፣ ውሳኔ ።** | |
| ፯፻፲፬ | ዋስትና ። .... .... .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፭ |
| ፯፻፲፭ | ስለ ፣ መውረስ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፮ |
| ፯፻፲፮ | የሥራ ፣ ፈቃዶችን ፣ ስለ ፣ መከልከልና ፣ ለጊዜው ፣ ስለ ፣ ማገድ ። | ፫፻፮ |
| ፯፻፲፯ | ዐይነተኞቹ ፣ የአፈጻጸም ፣ ሁኔታዎች ። .... .... .... .... | ፫፻፮ |
| ፯፻፲፰ | የግል ፣ ነጻነትን ፣ ስለ ፣ መከልከልና ፣ ስለ ፣ መቀነስ ። .... | ፫፻፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ክፍል ፡ ፩ ።

### የማስታወቂያ ፡ ውሳኔዎች ።


| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፲፱ | ለባለሥልጣን ፤ ስለ ፡ ማስታወቅና ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ። | ፫፻፹፯ |
| ፯፻፳ | በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ። .... .... .... .... | ፫፻፹፰ |


## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ።


| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፳፩ | ስለ ፡ ክስ ። .... .... .... .... .. .... .... .... | ፫፻፹፰ |
| ፯፻፳፪ | ጊዜ ፡ መስጠት ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። .... .... .... | ፫፻፹፱ |
| ፯፻፳፫ | ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለል ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፹፱ |
| ፯፻፳፬ | መደበኛ ፡ የሆነ ፡ የቅጣት ፡ ማከበጃ ። .... .... .... .... | ፫፻፹፱ |
| ፯፻፳፭ | ጥፋት ፡ ሲደራረብ ፡ ስለሚከብድ ፡ ቅጣት ። .... .... .... | ፫፻፺ |
| ፯፻፳፮ | ጥፋትን ፡ በመደጋገም ፡ ስለሚከብድ ፡ ቅጣት ። .... .... | ፫፻፺ |
| ፯፻፳፯ | ስለ ፡ መደጋገምና ፡ ስለ ፡ መደራረብ ። .... .... .... | ፫፻፺ |


## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማገድና ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።


| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፳፰ | የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የሚቀርብባቸው ፡ ሁኔታዎች ። .... .... | ፫፻፺፩ |
| ፯፻፳፱ | የተከሳሹ ፡ መሞት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፩ |
| ፯፻፴ | የይርጋ ፡ ዘመን ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፩ |
| ፯፻፴፩ | ምሕረትና ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት ። .... .... .... .... | ፫፻፺፩ |
| ፯፻፴፪ | ስለ ፡ መሰየም ። .... .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፩ |


# ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ልዩ ፡ ክፍል ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### በሕዝባዊና ፡ በማኅበራዊ ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።


| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፴፫ | መሠረቱ ፤ ጠቅላላ ፡ ሥርዐት ። .... .... .... .... .... | ፫፻፺፪ |


## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በመንግሥትና ፡ በሕዝብ ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ክፍል ፡ ፩ ።

### በሕዝባዊ ፡ ክብርና ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።


፲፯፻፴፩ ሕጋዊ ፡ ገንዘብን ፡ ስላለመቀበል ። .... .... .... .... ፫፻፺፪
፲፯፻፴፪ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የተለወጠ ፡ ገንዘብ ፡ በእጁ ፡ መኖሩን ፡ ሳያስታ ውቅ ፡ ስለ ፡ መቅረት ። .... .... .... .... .... ፫፻፺፫
፲፯፻፴፫ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆኑ ፡ መስፈሪያዎችና ፡ ሚዛኖች ፡ (ክብደቶች) ፡ መሥራት ። .... .... .... .... .... ፫፻፺፫
፲፯፻፴፬ ውድቅ ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በተለወጡ ፡ የመመ ላለሻ ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ መገልገል ። .... .... .... ፫፻፺፫
፲፯፻፴፭ የማዕርግ ፡ ስምና ፡ የምስክር ፡ ወረቀትን ፡ በማጭበርበር ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ስለ ፡ መገልገል ። .... .... .... ፫፻፺፬
፲፯፻፴፮ ከሕግ ፡ ውጪ ፡ የሲቢል ፡ ኒሻኖችንና ፡ የማዕርግ ፡ ምልክ ቶችን ፡ መሥራት ፤ በነዚህ ፡ መነገድና ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ማድረግ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፬


## ክፍል ፡ ፪ ።

### በቀረጥ ፡ በግብር ፡ ገቢ ፡ በአስተዳደርና ፡ በገንዘብ ፡ (በፊናንስ) ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።


፲፯፻፵ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ መብቶችን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ። ፫፻፺፬
፲፯፻፵፩ ስለ ፡ ከበሩ ፡ ማዕድኖች ፡ አጠባበቅ ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ። .. .... ፫፻፺፭
፲፯፻፵፪ ስለ ፡ ንግድ ፡ ወረቀቶች ፤ ስለባለዋጋ ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ አክ ሲዮኖችና ፡ ስለ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፭
፲፯፻፵፫ ስለ ፡ ባንኮችና ፡ የአደራ ፡ ገንዘብ ፡ ማስቀመጫ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፭
፲፯፻፵፬ ስለ ፡ ዕጣዎች ፤ ስለ ፡ ሎተሪዎች ፡ ስለ ፡ ጨዋታዎችና ፡ ውርር ዶች ፤ ጕዳይ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ። ፫፻፺፮
፲፯፻፵፭ ስለ ፡ ዋጋ ፡ መቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ። ፫፻፺፮
፲፯፻፵፮ የሞያ ፡ ሥራዎችን ፡ አካሄድ ፡ ስለ ፡ ማቋቋምና ፡ ስለ ፡ መቈጣ ጠር ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደ ንብ ፡ መተላለፍ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፮

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ ነገር ፤ | ገጽ ፤ |
|---|---|---|
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **በወታደራዊ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፤ በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፤ የደንብ ፡ መተላለፍ ።** | |
| ፯፻፹፯ | የወታደራዊ ፡ ደንብን ፡ መተላለፍ ፡ የሚለይበት ፤ ሁኔታ ። | ፫፻፲፯ |
| ፯፻፹፰ | የወታደራዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቅጣቶች ። | ፫፻፲፰ |
| ፯፻፹፱ | በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍና ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ። | ፫፻፲፰ |
| ፯፻፺ | ደንቡ ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፫፻፲፰ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ።** | |
| | **በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣንና ፡ በሥራ ፤ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **የሥራ ፡ አፈጻጸምን ፡ ተግባር ፡ የሚመለከት ፡ የደንብ ፤ መተላለፍ ።** | |
| ፯፻፺፩ | ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። | ፫፻፲፱ |
| ፯፻፺፪ | የማስገደድን ፡ መብት ፡ ከመጠኑ ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ። | ፫፻፲፱ |
| ፯፻፺፫ | ሐቀኛነትን ፡ ስለ ፡ ማጓደል ። | ፫፻፲፱ |
| ፯፻፺፬ | የአድልዎ ፡ እርዳታ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ፫፻፳ |
| ፯፻፺፭ | ከባለሥልጣን ፡ የሚሰጡትን ፡ ወረቀቶች ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ ስለ ፤ መስጠት ። | ፫፻፳ |
| ፯፻፺፮ | አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ ጕዳዮች ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (የዲሲፕሊን) ፤ ቅጣቶች ። | ፫፻፳ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።** | |
| ፯፻፺፯ | ግልጾች ፡ የሆኑ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። | ፫፻፳፩ |
| ፯፻፺፰ | ግዴታ ፡ የሆነውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ስላለመስጠትና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ መዝገብ ፡ ስላለመጻፍ ። | ፫፻፳፩ |
| ፯፻፺፱ | ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ማስታወቂያ ። | ፫፻፳፪ |
| ፰፻ | በመብት ፡ አላገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። | ፫፻፳፪ |
| ፰፻፩ | ባለሥልጣንን ፡ የመርዳት ፡ እንቢታ ። | ፫፻፳፪ |
| ፰፻፪ | ትእዛዝ ፡ እንዲፈጽም ፡ ሲጠየቅ ፡ እንቢተኛ ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፫፻፳፪ |

ቍጥር ፡ አርእስት ፡ ነገር ፤ ገጽ ፤

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

### በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ በሰላምና ፡ ያለ ፡ ሥጋት ፡ በሚኖርበት ፤ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

፯፻፷፫ ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያዎችና ፡ ጥይቶች ፡ ጥበቃ ። ........ ፫፻፹፫
፯፻፷፬ የተከለከለ፡የጦር፡መሣሪያን፡ስለ ፡ መያዝና ፡ ስለ ፡ መገልገል ። ፫፻፹፫
፯፻፷፭ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጥበቃ ። ............ ፫፻፹፬
፯፻፷፮ ስምን ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ መጠራት ። ........................ ፫፻፹፬

### ክፍል ፡ ፪ ።

በሕዝብ ፡ ሰላም ፡ ጸጥታና ፡ እርጋታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፤ መተላለፍ ።

፯፻፷፯ የጋዜጣና፡የማስታወቂያ ፡ መታተም ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። ፫፻፹፬
፯፻፷፰ የሚያስደነግጡ ፡ መግለጫዎች ፡ ወሬዎች ፡ ወይም ፡ ጽሑፎች ። ፫፻፹፭
፯፻፷፱ ሐሰተኛ ፡ የአደጋ ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ........ ፫፻፹፭
፯፻፸ በሌላ ፡ ሰው፡ሥራና፡ዕረፍት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ፫፻፹፭
፯፻፸፩ ሃይማኖትን ፡ የመስደብና ፡ የማዋረድ ፡ ንግግር ። ........ ፫፻፹፮
፯፻፸፪ የበዓል ፡ ቀኖችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። ............ ፫፻፹፮
፯፻፸፫ አልኮል ፡ የሚያደርሰውን ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ መጣባበቅ ። ፫፻፹፮
፯፻፸፬ ሰክሮ ፡ ወይም ፡ አእምሮ ፡ የሚያናውጽ ፡ ነገር ፡ ቀምሶ ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማወክ ። ................ ፫፻፹፮
፯፻፸፭ የምግብና ፡ የመጠጥ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ። ........................ ፫፻፹፮
፯፻፸፮ የትያትር ፡ ቤቶችንና፡ የሕዝብ ፡ መደሰቻ ፡ ስፍራዎችን፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ። ........................ ፫፻፹፮
፯፻፸፯ እንስሳትን ፡ በሚያሰቅቅ ፡ ሁኔታ ፡ ስለ ፡ ማንገላታት ። ፫፻፹፯

### ክፍል ፡ ፫ ።

በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የሕግ ፡ መተላለፍ ።

፯፻፸፰ የሰዎችን ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ስለ ፡ መንካት ። .......... ፫፻፹፯
፯፻፸፱ አደገኞች ፡ የሆኑ ፡ የሰዎችን ፡ ወይም ፡ የእንስሶችን ፡ ጥበቃ ፡

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | ስለ ፡ ማጕደል ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፹፱ |
| ፯፻፹ | ስለ ፡ ለሊት ፡ ደንብ ፡ ጥበቃ ። .... .... .... .... | ፫፻፹፱ |
| ፯፻፹፩ | የሕንጻ ፡ ሥራዎችን ፡ አፈጻጸም ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። .... .... | ፫፻፺ |
| ፯፻፹፪ | መንገዶችንና ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስፍራዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺ |
| ፯፻፹፫ | የመገናኛ ፡ ጸጥታን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ። .... .... | ፫፻፺፩ |
| ፯፻፹፬ | የእሳት ፡ አደጋ ፡ የሚፈነዱ ፡ መሣሪያዎችንና ፡ አደገኞች ፡ ነገሮችን ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ። .... .... .... .... | ፫፻፺፩ |

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃና ፡ ስለ ፡ ጽዳት ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፹፭ | ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጽዳትና ፡ ንጽሕና ፡ መቈጣጠር ። .... .... | ፫፻፺፪ |
| ፯፻፹፮ | መርዛምና ፡ አፍዛዥ ፡ የሆኑ ፡ መድኀኒቶችን ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ። | ፫፻፺፪ |
| ፯፻፹፯ | ሕሊና ፡ እንዲያጣ ፡ ወይም ፡ እንዲፈዝ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ፫፻፺፫ |
| ፯፻፹፰ | የምግብ ፡ የመጠጥና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የንግድ ፡ ሸቀጦችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፬ |
| ፯፻፹፱ | የሕክምና ፡ የበሽተኞች ፡ ማስታመም ፡ ዘዴ ፡ ጥበብና ፡ የሆስፒታሎች ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ አስተዳደር ። .... .... ... | ፫፻፺፬ |
| ፯፻፺ | የማስታወቅን ፡ የግዴታ ፡ ተግባር ፡ ስላለመፈጸም ። .... ... | ፫፻፺፭ |
| ፯፻፺፩ | የማከምን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ አለመፈጸም ። .... .... .... .. | ፫፻፺፭ |
| ፯፻፺፪ | ስለ ፡ አቀባበር ፡ ጥበቃ ። .... .... .... .... .... | ፫፻፺፭ |

አንቀጽ ፡ ፪ ።

በሰዎችና ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፺፫ | መሠረቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ። .... .... .... .... .... | ፫፻፺፮ |

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

በሰዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ለሰውነት ፡ ጥበቃ ፡ የተወሰኑትን ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፯፻፺፬ | በሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የእጅ ፡ እልፊትና ፡ ቀላል ፡ የኀይል ፡ ሥራ ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፮ |

ቍጥር ፤ አርእስተ ፤ ነገር ፤ ገጽ ፤


፯፻፺፭ ሬሳ ፤ ስለ ፤ መደበቅ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፹፯
፯፻፺፮ የሰውን ፤ የግል ፤ ነጻነትን ፤ ስለ ፤ መንካት ። .. .... .... ፫፻፹፯
፯፻፺፯ የግል ፤ ምስጢርን ፤ የመጠበቅ ፤ መብት ፤ ስለ ፤ መጣስ ። ፫፻፹፯
፯፻፺፰ በክብር ፤ ላይ ፤ ቀላል ፤ ጉዳት ፤ ስለ ፤ ማድረስ ። .... .... ፫፻፹፯

ክፍል ፤ ፪ ።

መልካም ፤ ባህልን ፤ ስለ ፤ መጠበቅ ፤ ጉዳይ ፤ የተመለከተውን ፤
ደንብ ፤ ስለ ፤ መተላለፍ ።

፯፻፺፱ ሥርዐትንና ፤ መልካም ፤ ባህልን ፤ ስለ ፤ መጠበቅ ። .... .. ፫፻፹፰
፰፻ ስለ ፤ አስነዋሪ ፤ ልመናና ፤ በብልግና ፤ አድራጎት ፤ ሁከት ፤
ስለ ፤ ማንሣት ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፹፰
፰፻፩ ለብልግና ፤ ተግባር ፤ የሚያነሣሣ ፤ ማስታወቂያና ፤ መግለጫ ፤
ስለ ፤ ማውጣት ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፹፰
፰፻፪ ዕንስን ፤ ለመከልከል ፤ ስለሚችል ፤ መግለጫ ። ... .... ፫፻፹፱

ምዕራፍ ፤ ፪ ።

በንብረት ፤ ላይ ፤ ስለሚፈጸም ፤ የደንብ ፤ መተላለፍ ።

ክፍል ፤ ፩ ።

የሀገርን ፤ ንብረት ፤ ስለ ፤ መጠበቅ ።

፰፻፫ ታሪካዊ ፤ ጥበብና ፤ የተፈጥሮ ፤ ሀብቶችን ፤ ስለ ፤ መጠበቅ ። ፫፻፹፱
፰፻፬ ያገር ፤ ተክልንና ፤ እንስሳትን ፤ ስለ ፤ መጠበቅ ። .... .... ... ፫፻፺
ክፍል ፤ ፪ ።

በሀብት ፤ ላይ ፤ ስለሚፈጸም ፤ የደንብ ፤ መተላለፍ ።

፰፻፭ የሕዝብንና ፤ የግል ፤ ንብረትን ፤ ስለ ፤ መጠበቅ ። .... .... ፫፻፺
፰፻፮ ቀላል ፤ ስርቆት ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፩
፰፻፯ የእህልና ፤ የተክል ፤ እሸት ፤ ስለ ፤ መልቀም ። ... .... ፫፻፺፩
፰፻፰ አጠራጣሪ ፤ የሆኑትን ፤ አንዳንድ ፤ ዕቃዎች ፤ ያለ ፤ ምክንያት ፤
ስለ ፤ መያዝ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፪
፰፻፱ በሀብት ፤ ረገድ ፤ ስለሚፈጸም ፤ መግለጫ ፤ ያለ ፤ መስጠትና ፤
የመሰወር ፤ ጉዳይ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፪
፰፻፲ የሰውን ፤ ሀብት ፤ ስለ ፤ ማበላሸት ፤ ስለ ፤ ማራከስ ። .... ... ፫፻፺፪
፰፻፲፩ የሕዝብ ፤ የሆኑትን ፤ ቤቶችና ፤ ሐውልቶች ፤ ስለ ፤ መድፈር ። ፫፻፺፫

| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ክፍል ፡ ፪ ።

### በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በጠቅላላው ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፰፻፲፪ | በተንኰል ፡ መንገድ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መጉዳት ። | ፫፻፺፫ |
| ፰፻፲፫ | ስለ ፡ ወስላታነት ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፫ |
| ፰፻፲፬ | ሌሎችን ፡ አገልግሎቶች ፡ በአጭበርባሪነት ፡ ስለ ፡ ማግኘት ። | ፫፻፺፬ |
| ፰፻፲፭ | ዐውቃለሁ ፡ ባይ ። .... .... .... .... .... .... | ፫፻፺፬ |
| ፰፻፲፮ | ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መሰብሰብ ። ... .... .... | ፫፻፺፬ |


## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### በኤኮኖሚና ፡ በንግድ ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ አስተዳደር ፡ ረገድ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።


| ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፰፻፲፯ | ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገቦችና ፡ ስለ ፡ ሒሳቦች ፡ አያያዝ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ። .... .... .... .... .... | ፫፻፺፭ |
| ፰፻፲፰ | በግዴታ ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ የኪንቢተኛነትን ፡ መልክ ፡ ስለ ፡ ማሳየት ። .... .... .... .... | ፫፻፺፭ |
| ፰፻፲፱ | ስለ ፡ ንግድ ፡ መርከቦች ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ፫፻፺፮ |
| ፰፻፳ | በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠውን ፡ የማኅበር ፡ ሥራ ፡ በማካሄድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።.... | ፫፻፺፮ |

ቍጥር ፡ ፩፻፶፰ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡

# አ ዋ ጅ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ኢትዮጵያ ፡ የደረሰችበትን ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ በመመልከት ፤ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ተሽሮ ፡ አዲስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንዲተካ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየን ፤

በሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፰ና ፡ ፹፱ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፤ ምክር ፡ ቤቶቻችንም ፡ መክረውበት ፡ ያቀረቡትን ፡ ውሳኔ ፡ ተቀብለንና ፡ ፈቅደን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አውጀናል ።

፩ ፤ ይህ ፡ አዋጅ ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አዋጅ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

፪ ፤ ልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ በወጣው ፡ በቍጥር ፡ ፩/ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የታተመው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ ይጸናል ።

፫ ፤ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብና ፡ ለርሱ ፡ ማሻሻያ ፡ ሆነው ፡ የወጡት ፡ አዋጆች ፡ ሁሉ ፡ ጭምር ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተጻፈው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ ተሽረዋል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ተፈራ ፡ ወርቅ ፡

የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።

BACK

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

# የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡፡

## መጀመሪያ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፤

## ጠቅላላ ፡ ክፍል ፡

### ፩ኛ ፡ መጽሐፍ ፤

### የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ስለ ፡ መጣስና ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ አድራጊው ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የሥራው ፡ አፈጻጸም ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የሕጉ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ።

**ቍ ፡ ፩ ። ጕዳዩና ፡ ግቡ ።**

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግብ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ሥርዐትን ፡ ሰላ ምን ፡ የመንግሥትንና ፡ የዜጎችን ፡ ጸጥታ ፡ መጠበቅና ፡ ማረጋገጥ ፡ ነው ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በጠቅላላው ፡ ለወንጀለኞች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በቂ ፡ ባልሆነበት ፡ ጊዜ ፡ የወንጀለኞች ፡ መቅጫ ፡ ማረሚያ ፡ እንዲሁም ፡ ከጥፋትና ፡ ከወንጀል ፡ እንዲወገዱ ፡ ማድረጊያ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ ። የሕግነቱ ፡ መሠረት ።**

(፩) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ ቅጣት ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥፋቶች ፡ እንዲሁም ፡ በአድራጊዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ቅጣቶችና ፡ ጥንቃቄዎች ፡ አስተካክሎ ፡ ይወስናል ።

አስቀድሞ ፡ በሕግ ፡ ያልተመለከተውን ፡ ጥፋት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ መጣስ ፡ ሊቈጥረውና ፡ በሕግም ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ ባልተመለከተ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ቅጣትን ፡ ሊወስን ፡ አይችልም ። በሕጉም ፡ ከተወሰኑት ፡ ቅጣቶችና ፡ ጥንቃቄዎች ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቅጣት ፡ መፈጸም ፡ አይችልም ።

በሕግ ፡ አስቀድሞ ፡ ባልተመለከቱት ፡ አድራጎቶች ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ይመሳሰላል ፡ በማለት ፡ መፍረድ ፡ ክልክል ፡ ነው ።

(፪) የሕግነቱ ፡ መሠረት ፡ የሕግን ፡ ትርጓሜ ፡ አያገድም ።

ሕጉ ፡ የሚያሻማ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ ሰጪው ፡ ሕጉን ፡ ለመስጠት ፡ በፈለገው ፡ ስሜትና ፡ ሊደርስበት ፡ ያሰበውን ፡ ግብ ፡ ለማረጋገጥ፡በሚችልበት ፡ መንገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕጉ ፡ መንፈስ ፡ ሊተረጕመው ፡ ይችላል ።

(፫) ማንም ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አይቀጣም ።

ቍ ፡ ፫ ። ስለ ፡ ልዩና ፡ ስለ ፡ ማሟያ ፡ ሕግ ።

ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የሚሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ደንቦችና ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ የተጠባቂ ፡ ናቸው ።

እነዚህም ፡ የተለዩ፡መሆናቸው ፡ ባልተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ፡ ወንጀለኛ፡መቅጫ፡ ሕግ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

ቍ ፡ ፬ ። በሕግ ፡ ፊት ፡ ትክክል ፡ ስለ ፡ መሆን ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሰውን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ ደረጃ ፡ የዘርን ፡ ወይም፡የሃይማኖትን፡ልዩነት፡ሳያደርግ ፡ በሁሉም ፡ ሰው፡ላይ፡ በትክክል ፡ ይፈጸማል ። ልዩነት ፡ የሚደረገው ፡ ሕጉ ፡ ራሱ ፡ ሲፈቅድና ፡ ይኸውም ፡ ልዩነት ፡ በመንግሥት ፡ ሕግና ፡ በሕገ፡መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የታወቁትን ፡ የማይደፈሩ ፡ መብቶችን ፡ የሚጠቅስ ፡ ሲሆን ፡ የጥፋቱንና ፡ የወንጀሉን ፡ ከባድነት ፡ ለማመዛዘን ፡ ሲሆን ፡ ያድራጊውን ፡ ዕድሜ ፡ ሁናቴ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሁናቴ ፡ በማስተያየት፡በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ ያድራጊው ፡ አደገኛነት ፡ ሲገመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ሕጉ ፡ የሚጸናበት ፡ ወሰን ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ጊዜ ፡ ሁናቴ ።

ቍ ፡ ፭ ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ የማይሠራ፡ስለመሆኑ ።

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሕግን፡የጣሰ፡እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚፈረደው ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ነው ።

BACK



ወንጀል ፡ የተሠራው ፡ የቀድሞ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ይሠራበት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርዱ ፡ የሚፈረደው ፡ በዚያው ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ እንዲጸና ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ የተሠራ ፡ ሥራ ፡ ሲኖርና ፡ ሕግን ፡ እንደ ፡ መጣስ ፡ ያልተቈጠረ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ሊያስቀጣ ፡ አይችልም ። እንዲሁም ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ነገር ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ፀልተጸፈ ፡ ቅጣት ፡ ሊፈረድ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፮ ። ከሕጉ ፡ ስለ ፡ መለየት ፤ የተሻለውን ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ እንዲጸና ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ አድራጊው ፡ ቀድሞ ፡ ባደረገው ፡ ወንጀል ፡ ሲፈረድበት ፡ ወንጀሉን ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ይሠራበት ፡ ከነበረው ፡ ከቀድሞ ፡ ደንብ ፡ ይልቅ ፡ ይኸኛው ፡ ሕግ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያቃልልለት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ለማመዛዘን ፡ ለያንዳንዱ ፡ ነገር ፡ በጠቅላላው ፡ የሚወዳደሩትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መገመት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፯ ። ስለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ።

ሕጉ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ወዲያውኑ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ የጥንቃቄ ፡ ማረጋገጫዎች ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ አጠባበቆችና ፡ የበጎ ፡ አስተዳደግ ፡ ጉዳዮች ፡ ባለፈው ፡ ሕግ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ቢሆኑም ፡ ፍርድ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፰ ። ስለ ፡ ይርጋ ፡ አፈጻጸም ።

(፩) ክስና ፡ ቅጣት ፡ የሚቀርበት ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ድንጋጌ ፡ ሕጉ ፡ ከታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በጠቅላላው ፡ በዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይፈጸማል ።

ስለሆነም ፡ ይህ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ያለፈው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

(፪) በተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ ባለመብት ፡ በሆነው ፡ አቤት፡ባይነትና ፡ ከሳሽነት ፡ ብቻ ፡ በቀድሞ ፡ ሕግ ፡ ያስቀጡ ፡ የነበሩ ፡ ወንጀሎች ፤ አቤት፡ባዩ ፡ ለጊዜው ፡ ባለመከሰሱ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡መከሰስ ፡ በተፈቀደለት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚያስከስሱ ፡ ሆነው ፡ ቢገኙም ፡ ይህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በገል ፡ ከሳሹ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ክስ ፡ ሳይቀርብባቸው ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

6

BACK



## ቍ ፡ ፱ ። አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ በተሰጡት ፡ ፍርዶች ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ፡ አፈጻጸም ።

ፍርዱ ፡ በቀድሞ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አፈጻጸሙ ፡ የሚመራው ፡ ከዚሁ ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ (የተመሳሰለ) ፡ በመሆን ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ነገሮች ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ነው ።

(፩) ቀድሞ ፡ ቅጣት ፡ ተወስኖበት ፡ የነበረው ፡ ተግባር ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የማያስቀጣ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ። ወይም ፡ የተጀመረው ፡ ቅጣት ፡ ወዲያውኑ ፡ ተቋርጦ ፡ ይቀራል ።

ለአንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻና ፡ አላፊ ፡ ለሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ሕግ ፡ የከለከለውን ፤ ወይም ፡ ያደረገውን ፡ ግዴታ ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የዚሁ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ማለፍ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ የተሰጠውን፡ ቅጣት ፡ ሊያቆመው ፡ አይችልም ። ክሱም ፡ ተጀምሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ የተነሣ ፡ የተጀመረው ፡ ክስ ፡ አይታገድም ።

(፪) በፍርድ ፡ የተወሰኑ ፡ ቅጣቶች ፡ አፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ወዲያውኑ ፡ በዚሁ ፡ ሕግ፡ በተመለከተው፡ድንጋጌና ፡ ፎርም ፡ ይፈጸማል ። እንዲሁም ፡ የተጣለውን ፡ መቀጮ ፡ ስለ፡ማስገባትና ፡ አስቀድሞ ፡ በገደብ ፡ ስለ፡መልቀቅ ፤ ነጻነትን ፡ ስለ ፡ መቀነስ ፡ የሚደረገው ፡ የሥርዐቱ ፡ አፈጻጸም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

(፫) ይህ ፡ ሕግ ፡ በጸናበት ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ እስረኛ ፡ ነጻነቱን ፡ በማሳጣት ፡ የሚያስቀጣውን ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ ሳይገለጽበትና ፡ በዚህም ፡ ሳይቀጣበት ፡ የቀረ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርዱን ፡ የሚወስንበት ፡ ፍርድ፡ቤት ፡ ለተቀጪው ፡ ምቹ ፡ የሆነውን ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ፡* መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ስለ ፡ ተደራራቢዎች፡ ወንጀሎች ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች፡‡ መሠረት ፡ ይቀጣዋል ። ቢሆንም ፡ በቀድሞ ፡ ፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ የፈጸመውን ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ጊዜ ፡ ይቀንስለታል ።

[ ቍ ፡* ፻፶፩ ። ‡ ፮ ። ]

## ቍ ፡ ፲ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ መሠረዝና ፡ ስለ ፡ መሰየም ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ አፈጻጸም ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ መሠረዝና ፡ ስለ ፡ መሰየም ፡ ነገር፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረው ፡ ፍርድ ፡ በተሻረው ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ ባገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ እንኳ ፡ ቢሆንም ፡ የሥርዐቱ ፡ አፈጻጸም ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተደነገገው፡ አኳኋን ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ፤
## ስለ ፡ ቦታ ፡ ሁናቴ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤
### ዋናው ፡ አፈጻጸም ።

**ቍ ፡ ፲፩ ። በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።**

**ደንበኛ ፡ ሁናቴ ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ ማናቸውንም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በሠራ ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር፡ማለትም ፡ በመላው፡ስፋቱ ፡ ሁሉ ፡ የየብስ ፡ የባሕር ፡ የአየርም ፡ ወሰን ፡ ጭምር ፡ ነው ። የግዛቱም፡ስፋት፡ በመንግሥቱ ፡ ሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

(፪) ከውጭ ፡ አገር ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ተላኩ ፡ ሰዎች ፡ በኢንተርናሲዮናል፡ሕግ፡ የተደነገጉት ፡ የማይደፈሩ ፡ መብቶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፫) አድራጊው ፡ በሌላ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በራሱ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንዲፈርድበት ፡ ወደ ፡ ግዛቱ ፡ ተገድዶ ፡ እንዲመጣለት ፡ ይጠይቃል ።

**ቍ ፡ ፲፪ ። ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፤ ስለ ፡ መወከል ።**

(፩) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በመሸሹ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀጣ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይልቁንም ፡ የሸሸበት ፡ አገር ፡ የትውልድ ፡ አገሩ ፡ ሆኖ ፡ እንዲመለስ፡ ማድረጉ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ በዚያው ፡ በተጠጋበት ፡ አገር፡እንዲፈረድበት፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለሥልጣን ፡ ይጠይቃል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ወንጀለኛ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በተፈጸመበት ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ተፈርዶበት ፡ በሚገባ ፡ ምሕረት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ፡ሆነ፡ወይም፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ቅጣቱ ፡ ተሠርዞለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ወንጀል ፡ ሁለተኛ ፡ አይቀጣም ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በይርጋ ፡ ቅጣት ፡ የቀረለት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወንጀለኛው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሳይፈጽም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ቢገኝ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረው ፡ እዚሁ ፡ ይፈጸምበታል ።

ምናልባት ፡ በቅጣቱ ፡ ዐይነትና ፡ አፈጻጸም ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የተገኘ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ከተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ይበልጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኘው ፡ ዐይነት ፡ ይፈጸምበታል ።

ቍ ፡ ፲፫ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በ፲ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ና ፡ * ባ፩ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ‡ የተደነገጉትን ፡ በመጣስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ በነጋሚው ፡ በጸጥታው ፤ በአንድነቱ ፤ በሕገጋቱ ፡ አቅዋም ፤ በዋና ፡ ዋና ፡ ጥቅሞቹና ፡ በገንዘቡ ፡ ሕግን ፡ በጣሰ ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [* ቍጥር ፡ ፪፻፵፰ ፡ እስከ ፡ ፪፻፸፪ ፡ ‡ ቍ ፡ ፫፻፴፯ ፡ እስከ ፡ ፫፻፵፪ ። ]

ቍ ፡ ፲፬ ። በውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ ስለሚሠራቸው ፡ ወንጀሎች ።

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የዲፕሎማቲክና ፡ የቆንሲል ፡ አባሎች ፡ የሆኑ ፡ የመንግሥት ፡ መልክተኞች ፤ ወኪሎች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀል ፡ ሠርተው ፡ ስለማይደፈር ፡ መብት ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ በሆነው ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ወንጀሉን ፡ በሠሩበት ፡ አገር ፡ ሊፈረድባቸው ፡ የማይቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሚፈጸምባቸው ፡—

(ሀ) የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ የተሠራ ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፤ እንዲሁም ፡ ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ አገር ፡ ባለው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ስለ ፡ ሆነም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። ወይም ፡

(ለ) ወንጀል ፡ የሠራበትን ፡ የዚያን ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ የተደረገ ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፤ ይኸውም ፡ ወንጀል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) በውጭ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ወንጀሉ ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ የክስ ፡ አቤቱታውን ፡ ካላቀረበ ፡ የማያስቀጣ ፡ ካልሆነና ፡ በሚገባም ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ክሱ ፡ ሊቀጥል ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፭ ። የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆነው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ።

(፩) ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወታደር ፤ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በወል ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በወታደርነቱ ፡ ሳለ ፡ ሕግን ፡ በመጣሱ ፡ ሕግን ፡

በጣሰበት ፡ ስፍራ ፡ ተይዞ ፡ ሲዳኝ ፡ በዚያው ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ በግዛቱ፡ባለው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡* ይፈረድበታል ።

ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ የገባ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ እጁም ፡ ተላልፎ ፡ ያልተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይፈረድበታል ። [ቍ ፡ ፳፩፡(፪)።]

(፪) በልዩ ፡ ክፍል ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ና፡፫፡ * በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመው ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ በእንተርናሲዮናል ፡ ሕግና ፡ በተለይም ፡ በወታደርነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ የሚዳኘው ፡ በዚህ ፡ በራሱ ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወታደር ፡ ፍርድ፡ ቤቶች፡ነው። [ ቍ * ፪፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፫፻፴፩ ። ]

ቍ ፡ ፲፮ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፍርድ ።

(፩) በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር፡ * የሚገኝ ፡ አንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተፈረደበት ፡ ቢሆንም፡ እንኳ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከተገኘ ፡ ወይም ፡ ተላልፎ ፡ ካልተሰጠ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ እንደገና፡ሊከሰስና፡ሊፈረድበት፡ይቻላል ። [ ቍ፡ * ፲፩ ። ፲፫ ። ፲፬ (ሀ) ። ፲፭ ፡ (፪) ]

(፪) እንዲሁም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ከክስ ፡ ውጭ ፡ የመሆኑ ፡ ወይም ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ የመውጣቱ ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደገና ፡ ተከሶ ፡ መቀጣትን ፡ አያስቀርለትም ።

(፫) ተከሳሹ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተፈርዶበትና ፡ ቅጣቱን ፡ በሙሉም ፡ ሆነ፡ በከፊል ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ ቅጣትን ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ የፈጸመውን ፡ ቅጣት ፡ አስቦ ፡ ይቀንስለታል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤

## ተከታይ ፡ አፈጻጸም ።

ቍ ፡ ፲፯ ። በማኅበራዊ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ።

(ሀ) ኢትዮጵያ፡ተስማምታ፡በተቀበለችው፡በኢንተርናሲዮናል፡ ውል ፡ ወይም፡ ስምምነት፡ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ኢንተርናሲዮናል፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ የተቈጠረውን፡በመሥራት፡አጥፊ፡ሆኖ፡የተገኘ ፡እንደ፡ሆነ፤

(ለ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፲—፭፻፲፯ ፡ ፮፻፭ ፡ ፮፻፮ ፡ ፮፻፱ ፡ ወይም ፡ ፮፻፲ ፡ የተመለከተውን ፡ የሕዝብን ፡ ጤንነት ፡ ወይም ፡ የሕዝብን ፡

ሞራል ፡ በመጉዳት ፡ አጥፊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውጭ፡አገር፡ ተከሶ ፡ ካልተቀጣበት ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ በጠቅላ ላዎቹ ፡ ሕጋውያን ፡ ግዴታዎች ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ በኢትዮጵያ፡ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊታይና ፡ ተከሳሹ ፡ ሊቀጣ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ በቍጥር ፡ ፲፫ና ፡ ፲፬ ፡ (፪)፡የተመለከ ቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚቃወም ፡ አይደለም ።

## ቍ ፡ ፲፫ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሠሩ ፡ ሌሎች ፡ ወንጀሎች ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ፡ ሆኖ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገሩት ፡ቍጥሮች ፡ ከተመለከቱት፡ ወንጀሎች ፡ ሌላ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ተግባሩ ፡ በውጭ፡ አገር ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀጣ ፡ በመቅረቱ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ የሚፈጸሙት ፡—

(ሀ) ፍርዱ ፡ የሚወሰንበት ፡ የወንጀል ፡ አድራጎት ፡ ወንጀሉ፡በተሠራበት ፡ አገርና ፤ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የሚያስቀጣ ፡ መሆኑ ፡ የተደገገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የዚሁ ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ከባድነት ፡ ወንጀለኛው ፡ ተይዞ፡ እንዲ ተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣትን ፡ የሚያስፈር ድበት ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ እጁም ፡ ተላልፎ ፡ መስጠቱ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ አድራጊው ፡ እዚሁ ፡ ሊከሰስና ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፲፬ ። ይህ ፡ ሕግ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ፈንታ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈልገው ፡—

(ሀ) ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ፡መሠ ረት ፡ ክሱ ፡ እንዲቀጥልና ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ወይም ፡ እንዲያስታውቁ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆንና ፡ ክሱን ፡ ወይም ፡ ማስ ታወቂያውን ፡ እነዚሁ ፡ አቅርበው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አድራጊው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡ ውስጥ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ ያልተሰጠ ፡ እንደ፡ሆነ፡ወይም፡በዚሁ፡

በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ ተይዞ ፡ በመገደድ ፡ ወደዚህ፡ተላልፎ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ጥፋተኛው ፡ ወንጀሉን ፡ በሠራበት ፡ አገር ፡ በሕግ ፡ አገባብ ፡ ምሕረት ፡ ያላገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ አገር ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በይርጋ ፡ ያልታገደ ፡ እንደ፡ሆነ፡ ነው ።

(፪) ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የክስ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያቀርበው ፡ በጉዳዩ፡ከፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ ጋራ ፡ ከተስማማበት ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፫) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ መንግሥትነቱ ፡ በታወቀለት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ የተፈረደው ፡ ቅጣት ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ወንጀሉ፡በተሠራበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፳ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፍርድ ።

(፩) የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ፈንታ ፡ በሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ * አድራጊው ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከሶ ፡ በሚገባ ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የማያስከስሰው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተለቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንበትም ። [ ቍ ፡ * ፲፭ ፡ (፩) ። ፲፯ ። ፲፰ ። ]

(፪) አድራጊው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተፈርዶበት ፡ ቅጣቱን፡አልፈጸመ፡እንደ፡ሆነ፡ ወይም ፡ የፈጸመው ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቅጣቱ ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ቅጣቱና ፡ ስላፈጻጸሙ ፡ በሕጎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስለዚሁ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት፡ * ሳይፈጽመው፡የቀረው፡ቅጣት፡ሊፈጸም፡ይቻላል። [ ቍ፡ * ፲፪፡(፫) ። ]

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ፤

ቍ ፡ ፳፩ ። አሳልፎ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ማንኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውጭ፡ሆኖ ፡ በወል ፡ ሕግ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ባደረገው ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰ፡ወይም፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ፡ሆነና ፡ ወደ፡ኢትዮጵያ ፡ የገባ ፡ እንደ፡ሆነ፡ ሕጉ ፡ እንደሚያዘው ፡ በመንግሥት ፡ ውል ፡ ስምምነት፡ወይም ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አጥፊው ፡ የሠራው ፡ ወንጀል ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ በቀጥታና ፡ በዋና ፡ ባለጉዳይነት ፡ የማያገባው ፡ ሆኖ ፡ ሲገ

BACK



ኝና ፡ ወንጀሉን ፡ የሠራበት ፡ አገር ፡ መንግሥትም ፡ በግዛቱ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ እንዲፈጽም ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተይዞ ፡ ቅጣቱን ፡ ወደሚፈጽምበት ፡ አገር ፡ እንዲተላለፍ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል። [ ቍ ፡ ፲፫ ። ]

(፪) ጥፋት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ዜጋ ፡ የነበረውን ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ የተደነገገ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለሌላ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ አይቻልም። አሳልፎ ፡ ባልተሰጠም ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣንና ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይፈረድበታል ።

(፫) እጅን ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠትን ፡ ነገር ፡ የሚያመጡ ፡ ወንጀሎች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጥያቄው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሕገጋትና ፡ በሚሠራባቸው ፡ የስምምነት ፡ ውሎች ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

## ቍ ፡ ፳፪ ። የውጭ ፡ አገርን ፡ ፍርዶች ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።

(፩) ቀድሞ ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፡ ውሳኔዎችና ፡ ቅጣትን ፡ ስለሚያከብዱ ፡ ፍርዶች ፤ አመክሮን ፡ ስለ ፡ መስጠትና ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ፤ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ፡ መደጋገምና ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፤ ስለ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ የማረጋገጫ ፡ ደንብ ፤ አጥፊው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፤ ከማዕርግ ፡ ስለ ፡ መሻር ፤ ስለ ፡ መሰየም ፡ ሁኔታ ፤ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ አከፋፈል ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ነክነት ፡ ስላላቸው ፡ ነገሮችና ፡ የተወሰዱ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መመለስ ፤ በዚህም ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተደነገጉትን ፡ ሌሎችን ፡ ፍትሐውያን ፡ ጉዳዮች ፡ በሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠውን ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ማወቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) ይህንንም ፡ ጉዳይ ፡ መቀበል ፡ የሚቻለው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ በልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይሆን ፡ በመደበኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሕገጋት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ መጣስ ፡ በተቈጠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ ላይ ፡ በሚፈረደው ፡ ዐይነት ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ትክክለኛነቱም ፡ ያንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለማወቅ ፡ የሚቻለው ፡ ትክክለኛነቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ የተመሰከረለት ፡ የፍርድ ፡ ቅጂ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ስሌዳ ፤ የዳኝነት ፡ ወይም ፡ ያስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተረጋገጠ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ በሚገባ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።
## ስለ ፡ ወንጀልና ፡ ስለ ፡ አሠራሩ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ።

**ቍ ፡ ፳፫ ። ስለሚያስቀጡ ፡ ወንጀሎች ።**

(፩) ያስቀጣል ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ የተደነገገውን ፡ መሥራት ፡ ወይም፡እንዲሠራ ፡ የታዘዘውን ፡ አለመሥራት ፡ የከባድነቱ ፡ ደረጃ ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት፡ቢሆን ፡ ወንጀል ፡ ነው ።

(፪) በሕግ፡ተደንግገው ፡ የተገለጹትና ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያቋቁሙት ፡ የሞራል ፡ ወይም ፡ የግዙፍ ፡ ተግባር ፡ ጠባዮች ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ፡አድራጎት ፡ ካልተፈጸሙ ፡ በቀር ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ተግባር፡እንደ፡ተሠራ፡አይቈጠርም።

(፫) ያድራጊው ፡ አጥፊነት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ካልተረጋገጠ፡በቀር ፡ አድራጎቱ ፡ አያስቀጣም ።

**ቍ ፡ ፳፬ ። ውጤቱ ፡ ከነገሩ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የሕግ ፡ መጣሱ ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ውጤት ፡ እንደሚያመጣ ፡ የታወቀ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ውጤት ፡ በተደረገው ፡ ወይም ፡ ባል ተደረገው ፡ ተግባር ፡ ምክንያት ፡ ያድራጊው ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ ወንጀሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ አይቈጠርም ።

በምክንያቱና ፡ በውጤቱ ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ አለ ፡ የሚባለውም ፡ በኑሮ ፡ ልማድ ፡ ዕውቀት ፡ በሕግ ፡ የታዘዘውን ፡ ማድረግ፡ወይም ፡ አለማድረግ፡ በተለምዶው ፡ ውጤቱን ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

(፪) ከሌላ ፡ ሰው ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ከፍጥረታዊ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ከአጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ወይም ፡ የተደራረቡ ፡ ምክንያቶች ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ለተከሳሹ ፡ እንግዳ ፡ የሆነው ፡ ምክንያት ፡ ውጤቱን ፡ ለማስከተል ፡ ራሱ ፡ በቂ ፡ ሲሆን ፡ በምክንያቱና ፡ በውጤቱ ፡ መካከል ፡ አለ ፡ የሚባለውን ፡ ግንኙነት ፡ ያስቀረዋል ።

እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የማድረጉ ፡ ወይም ፡ ያለማድረጉ ፡ ጒድለት ፡ ወንጀል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚሁ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

**ቍ ፡ ፳፭ ። ሕግ ፡ መጣስ ፡ ስለ ፡ ተሠራበት ፡ ስፍራና ፡ ጊዜ ።**

(፩) የሕግ ፡ መጣስ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ፡ያህል፡ሆኖ፡የሚቈጠርበት ፡ ስፍራና ፡ ጊዜ ፡ ጥፋተኛው ፡ ወንጀሉን፡የፈጸመበት ፡ ወይም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡

BACK



ሕግ ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያስገድደውን ፡ ተግባር ፡ አድራጊው ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረበት ፡ ስፍራና ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

የሕግ ፡ መጣስ ፡ ሥራ ፡ ሙከራ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ያህል ፡ የሚቈጠርበት፡ ስፍራና ፡ ጊዜ ፡ አድራጊው ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የሚያስገኙትን፡የወንጀሉን ፡ የመጀመሪያ ፡ ሥራዎች ፡ የፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ያልፈጸመበት፡ስፍራና፡ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ሕግ ፡ መጣሱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የማይፈጸም ፡ ሲሆን ፡ ማለት ፡ ሥራውና ፡ ውጤቱ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በማይገኝበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተሠራበት ፡ የሚ ቈጠረው ፡ ሕግ ፡ መጣሱ ፡ በተሠራበት ፡ ወይም ፡ ሊሠራ ፡ የሚገባው ፡ ተግ ባር ፡ ባልተፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ተሠርቶ ፡ የነበረው ፡ ሕግ፡ መጣስ፡ የመጨረሻ ፡ ውጤቱን ፡ ፍጻሜ ፡ ያገኘበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሙከራ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ያህል፡ የሚቈጠ ረው ፡ አድራጊው ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ በሞከረበት ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ በአድራጊው ፡ ዐቅድ ፡ ውጤት ፡ ይገኝበታል ፡ ብሎ ፡ ባሰበበት ፡ ስፍራ፡ ነው ።

ስለ ፡ ክሱ ፡ አቀራረብ ፡ ወንጀሉ ፡ ውጤትን ፡ ያገኘበት ፡ ስፍራ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ወንጀሉ ፡ ለተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምትኩ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።
## የሕግ ፡ መጣስ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ደረጃ ።

### ቍ ፡ ፳፯ ። የመሰናዳት ፡ ተግባሮች ።

የሕግ ፡ መጣስን ፡ ሥራ ፡ ለማሰናዳት ፡ ወይም ፡ ለማድረግ፡እንዲቻል፡ይልቁንም ፡ መሣሪያዎችን ፡ በመሰብሰብ ፡ ወይም ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ሁኔታዎች ፡ እንዲከናወኑ ፡ ለማድረግ ፡ የተደረጉት ፡ ተግባሮች ፡ ማስቀጣት ፡ የሚችሉት ፡—

(ሀ) ተግባሮቹ ፡ ራሳቸው ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ሥራ ፡ ሆነው ፡ የሚያስቀጡ ፡ መሆናቸው ፡ በሕግ ፡ የተደነገገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ከሚያስከትለው ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው፡ በሚ ያደርሰው ፡ አደጋ ፡ መጠን ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ መሆናቸው ፡ በሕግ፡ ተገልጾ ፡ የተነገረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፳፰ ። ስለ ፡ መሞከር ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ ጀምሮ ፡ የወንጀሉን ፡ ተግ ባር፡እስከ፡መጨረሻው፡ያልተከታተለ ፡ ወይም ፡ ለመከታተል ፡ ያልቻለ፡ወይም ፡

የወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሥራውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተከታትሎ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ውጤት ፡ ያላገኘ ፡ ቢሆንም ፡ በመሞከሩ ፡ ብቻ ፡ ጥፋተኛ ፡ ይሆናል ።

የወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ ያህል ፡ የሚቈጠረው ፡ የተፈጸመው ፡ ተግባር ፡ በማያጠራጥር ፡ ሁኔታና ፡ በቀጥታ ፡ ወንጀሉን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ታሰበበት ፡ ግብ ፡ ለማድረስ ፡ የተሠራ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሙከራ ፡ ዘወትር ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ።

ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ የማነሣሣት ፡ ወይም ፡ ያባሪነት ፡ ሙከራ ፡ ብቻ ፡ በሕግ ፡ ተገልጾ ፡ ያስቀጣል ፡ ተብሎ ፡ ካልተደነገገ ፡ በቀር ፡ አያስቀጣም ።

(፫) የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ በመሞከሩ ፤ በመደቡ ፡ ለመፈጸም ፡ በፈለገው ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

የነገሩ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚገቡ ፡ ምክንያቶችን ፡ ሲያስገኙ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሕጉ ፡ በወሰነው ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ ለማቅለል ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፪፻፬ ።]

ቍ ፡ ፳፰ ። ስለ ፡ መተውና ፡ ስለ ፡ መጸጸት ፡ ተግባር ።

(፩) አድራጊው ፡ ሊፈጽመው ፡ የነበረውን ፡ የወንጀል ፡ ሥራውን ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕግ ፡ በተፈቀደው ፡ ወሰን ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ ሊያቀልለት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ቅጣቱን ፡ ሊያቀልለት ፡ ይችላል ። የወንጀል ፡ ሥራውን ፡ የተወው ፡ በሐቀኝነት ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ የሕሊና ፡ ስሜት ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቅጣቱ ፡ ነጻ ፡ ያደርገዋል ። [ቍ ፡ ፪፻፬ ።]

(፪) አድራጊው ፡ የወንጀሉን ፡ አሠራር ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ አድርሶ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ውጤቱ ፡ እንዳይደርስ ፡ የከለከለ ፡ ወይም ፡ እንዳይደርስ ፡ እርዳታ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ሊያቃልልለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፪፻፭ ።]

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ የወንጀሉን ፡ ሥራ ፡ በፈቃዱ ፡ ለተወ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ ውጤት ፡ እንዳያገኝ ፡ ለማገድ ፡ በበኩሉ ፡ የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ ላደረገ ፡ አነሣሽ ፡ ለሆነ ፡ ወንጀለኛ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፴፭ ። ፴፮ ።]

ቍ ፡ ፳፱ ። ሊፈጸም ፡ ስለማይቻል ፡ ወንጀል ።

በማናቸውም ፡ ዘዴና ፡ መሣሪያ ፡ ቢሆን ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ በፍጹም ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ ለሞከረ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ቅጣቱን ፡ ለማቃለል ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፪፻፭ ።]

አድራጊው ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስና ፡ የወንጀል ፡ ውጤት ፡ ለመስጠት ፡ በማይችል ፡ በማናቸውም ፡ ዘዴና ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ በአምልኮ ፡ ሥራ ፡ በሞኝነት ፡ ወይም ፡ በመንፈስ ፡ ልልነት ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሙከራ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቅጣቱ ፡ ነጻ ፡ ያደርገዋል ።

ቍ ፡ ፴ ። የተለየ ፡ የወንጀል ፡ ሙከራ ።

ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ የተደረጉት ፡ የሙከራ ፡ ተግባሮች ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ወንጀል ፡ ሆነው ፡ ከተገኙ ፡ ለዚሁ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

ቍ ፡ ፴፩ ። የዳኛ ፡ ግምት ።

በተተወ ፡ ወይም ፡ ሳይፈጸም ፡ በቀረ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሙከራ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰን ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ቅጣትን ፡ ለማቃለል ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ አንድ ፡ ቅጣት ፡ መወሰንን ፡ ጨርሶ ፡ ለመተው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ መገመትና ፡ ማመዛዘን ፡ ይገባዋል ። በተለይም ፡ የወንጀሉን ፡ ሙከራ ፡ እርምጃ ፡ መጠንና ፡ የተፈጸመውም ፡ ሙከራ ፡ የሚያደርሰውን ፡ የአደጋ ፡ ከባድነት ፡ ደረጃ ፤ ሙከራው ፡ ከፍጻሜ ፡ ሳይደርስ ፡ የቀረበትን ፡ ምክንያት ፡ አድራጊው ፡ ወንጀሉን ፡ መሥራት ፡ የተወበትንና ፡ የተጸጸተበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የጥፋተኛውን ፡ ያለፈ ፡ ጊዜ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩንና ፡ የጠባዩን ፡ አደገኛነት ፡ መመርመርና ፡ መመዘን ፡ አለበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

ቍ ፡ ፴፪ ። ስለ ፡ ዋና ፡ ወንጀል ፡ አድራጊውና ፡ ስለ ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ።

(፩) ወንጀል ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ተቈጥሮ ፡ አድራጊው ፡ በዚሁ ፡ የሚቀጣው ፡—

(ሀ) በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ በተለይም ፡ በእንስሳ ፡ ወይም ፡ በተፈጥሮ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ መሣሪያ ፡ አማካይነት ፡ በእርግጥ ፡ የወንጀልን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ማንም ፡ ሰው ፡ ወንጀሉን ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በቀጥታ ፡ ባይሠራውም ፡ እንኳ ፤ በሙሉ ፡ አሳቡና ፡ አድራጎቱ ፡ በወንጀሉ ፡ ሥራና ፡ በሚሰጠው ፡ ውጤት ፡ ሙሉ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ተግባሩን ፡ የራሱ ፡ ያደረገ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲሠራ ፡ ዐውቆ ፡ በማስገ

ደድ {በሰውም ፡ ሆነ ፡ በእንስሳ ፡ ወይም ፡ በግዙፋዊ ፡ ኃይል ፡ አማካይ ነት ፡ እእምሮ ፡ የሌለውን} አላዋቂ ፡ መሣሪያ ፡ በማድረግ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ ከአድራጊው ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንጀለኛው ፡ የሚቀጣው ፡ በቍጥር ፡ ፶፰ ፡ (፫) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) አድራጊዎች ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመደቡ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ለዚሁ ፡ ጥፋት ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ መሠረት ፡ ይቀጣሉ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሁኔታዎችና ፡ *እንደ ፡ ሰውዬው ፡ ጥፋት ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ *መከተል ፡ አለበት ። [ቍ ፡ *፺ ፡ ፻፲፪ ፡]

ቍ ፡ ፴፫ ። ልዩ ፡ ወንጀል ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

የተለዩ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሊሠሩት ፡ የሚቻል ፡ ወንጀል ፡ ሲያጋጥምና ፡ እንዚህ ንም ፡ ለመሥራት ፡ ወታደር ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፤ የመድፈር ፡ ተግባር ፡ ሲሆን ፡ ወንድ ፡ መሆን ፡ የሚያሻ ፡ ሲሆን ፤ ተከሳሹ ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ልዩነት ፡ ባይኖረ ውም ፡ በሙሉ ፡ ፈቃዱና ፡ ዕውቀቱ ፡ ለወንጀሉ ፡ ሙሉ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በግብረ ፡ አበርነት ፡ ከመከሰስ ፡ አይድንም ።

ቍ ፡ ፴፬ ። የኅብረት ፡ ወንጀል ።

አንድ ፡ ወንጀል ፡ በአንድ ፡ ክፍል ፡ በተመደቡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በኅብረት ፡ በተ ሠራ ፡ ጊዜ ፡ የወንጀሉ ፡ ተካፋይ ፡ አለመሆኑ ፡ የታወቀለት ፡ ሰው ፡ አይቀጣም ።

ቍ ፡ ፴፭ ። ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ።

(፩) የወንጀል ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ አነሣሺ ፡ ተብሎ ፡ የሚቈጠረው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በገዛ ፡ አሳቡ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በማግባባት ፤ ተስፋ ፡ በመ ስጠትና ፡ በገንዘብ ፡ ስጦታ ፤ በማስፈራራት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ወንጀልን ፡ እንዲሠራ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

አነሣሹ ፡ የሚቀጣው ፡ የወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ የተሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) የሚወሰንበትም ፡ ቅጣት ፡ ሊደረግ ፡ በታሰበው ፡ ወንጀል ፡ ላይ ፡ ሕጉ ፡ በደነገ ገው ፡ ቅጣት ፡ ልክ ፡ ነው ። የነገሩም ፡ ሁኔታዎች ፡ ተገቢ ፡ ሆነው ፡ ሲታዩ ፡ ሕግ ፡ በወሰነው ፡ መጠን ፡ ቅጣቱ ፡ ሊቃለል ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፹፱ ፡]

(፫) ወንጀሉን ፡ በእርግጥ ፡ የፈጸመው ፡ ሰው ፡ አነሣሺው ፡ ከፈለገው ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አነሣሺው ፡ የሚቀጣው ፡ እርሱ ፡ በፈለገው ፡ ወይም ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ሊገምተው ፡ በሚችለው ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፶፰ ፡ (፫) ።]

በእርግጥ ፡ ወንጀሉን ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ ለፈጸመው ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፴፮ ። ስለ ፡ አባሪነት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ አባሪ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚቈጠረው ፡ ዋናውን ፡ አድራጊ ፡ ለመርዳት ፡ ወንጀሉን ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፤ ወሬ ፡ በማቀበል ፡ በመምከር ፡ ወንጀል ፡ የሚሠራበትን ፡ ዘዴና ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ድጋፍና ፡ የወንጀል ፡ መሣሪያ ፡ ግዙፍ ፡ እርዳታ ፡ በመስጠት ፡ ዐውቆ ፡ በገዛ ፡ አሳቡ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ሆነ ፡ ብሎ ፡ ለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ አባሪ ፡ መሆን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ።

(፫) ቅጣቱ ፡ ለዚሁ ፡ ለተደረገው ፡ ወይም ፡ ለተሞከረው ፡ ወንጀል ፡ የተደነገገው ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ በማመዛዘን ፡ ሕጉ ፡ ከደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ መሥመር ፡ ሳያልፍ ፡ የአባሪው ፡ ወንጀለኛ ፡ ተግባር ፡ ከአሳቡ ፡ በላይ ፡ ያላለፈ ፡ ከሆነ ፡ *ቅጣቱን ፡ ሊያቀልለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ *፶፰ ፡ (፫) ፻፷፩] ።

ቍ ፡ ፴፯ ። በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መስማማትና ፡ ስለ ፡ ማደም ።

(፩) ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ የተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለግብረ ፡ አበርነት ፡ ወንጀል ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎችና ፡ በዚሁም ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ የቅጣት ፡ ማከበድ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በጠቅላላ ፡ ይፈጸሙባቸዋል ። [ቍ ፡ ፹፩ ፡ (መ) ።]

(፪) ስለሆነም ፡ በመንግሥቱ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጥቅሞች ፡ ላይና ፡ በመከላከያ ፡ ኀይሉ ፡ ስለ ፡ ማደም ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ ስለ ፡ ማቋቋምና ፡ በነዚሁም ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መግባት ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ወይም ፡ በወንበዴዎች ፡ ድርጅት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ክፍል ፡ የተሠሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸማሉ ። [ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ፪፻፹፮ ። ፫፻፲፫ ። ፬፻፸፪ ።]

ቍ ፡ ፴፰ ። የወንጀል ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ።

(፩) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በግልጽ ፡ ካልተደነገገ ፡ በቀር ፡ ወንጀልን ፡ ለመፈጸም ፡ የተደረገውን ፡ ዝግጅት ፤ የተፈጸመውን ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛውን ፡ አለማስታወቅ ፤ በእጅ ፡ አዙር ፡ ወንጀለኛን ፡ መርዳት ፡ ነው ፡ ወይም ፡ አባሪነት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አያስቀጣም ። [ቍ ፡ ፪፻፳፯ና ፡ ፫፻፵፩ ። ]

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ በግልጽ ፡ የተወሰኑትን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ነገሮች ፡ ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ አለማስታወቅ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተዳደር ፡ (አድሚኒስትራሲዮን) ፡ ላይ ፡ የሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ በመሆኑ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡

ስለ ፡ አለማስታወቅ ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፴፰ ፡ የተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) እነዚህም ፡ በሕግ ፡ የጸኑት ፡ ገደቶታዎች ፡ ወሰን ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ፴፱ ። ወንጀለኛን ፡ ስለ ፡ መርዳት ።

ማንም ፡ ሰው ፤ ወንጀል ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ወንጀል ፡ አድራጊውን ፡ ረድቶ ፤ ወንጀለኛው ፡ ከመከሰስና ፡ ከመቀጣት ፡ እንዲያመልጥ ፡ ለማድረግ ፡ የደበቀ ፡ የረዳ ፤ በወንጀል ፡ የተገኘውንም ፡ ዕቃ ፡ የሸሸገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለነዚሁ ፡ አድራጎቶች ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፩፻፴፱ ። ፩፻፶፩ ። ፯፻፵፯ ። ]

## ቍ ፡ ፵ ። የግል ፡ ምክንያቶች ፡ ለሌላ ፡ የማይተላለፉ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዋናነት ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተካፋይነት ፡ አንድ ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ሠርተው ፡ ሲገኙ ፡ እያንዳንዱ ፡ በተካፋይነቱ ፡ ደረጃ ፡ በጥፋቱ ፡ መጠን ፡ ራሱና ፡ ተግባሩ ፡ ሊያስከትለው ፡ በሚችለው ፡ የአደጋ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ እየራሱ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ይቀጣል ።

ከቅጣት ፡ ለማዳን ፤ ቅጣትን ፡ ለማቃለል ፡ ወይም ፡ ለማክበድ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑት ፡ የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፤ የአጥፊው ፡ ልዩ ፡ ጠባዮች ፤ ወይም ፡ የግል ፡ ግንኙነቶች ፡ ለራሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፉ ፡ አይደሉም ። እንዲሁም ፡ ጕዳዩ ፡ በቀጥታ ፡ የሚመለከተውን ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ሊጎዳ ፡ ወይም ፡ ሊጠቅም ፡ አይችልም ።

# ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ታትመው ፡ በሚወጡ ፡ ጽሑፎች ፡ በሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

## ቍ ፡ ፵፩ ። መሠረቱ ።

(፩) ማስታወቂያ ፡ በማውጣት ፡ ወንጀል ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአሳቡንም ፡ መግለጽ ፡ ነጻነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ወዲያውም ፡ ይህ ፡ የነጻነት ፡ መብት ፡ ከመጠኑ ፡ እንዳያልፍ ፡ ለማገድ ፤ ለወንጀል ፡ ተካፋይነት ፡ የተሠራው ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ዐይነት ፡ በከፊል ፡ ተለይቷል ።

(፪) አሳትሞ ፡ በማውጣት ፡ የሚደረጉት ፡ እነዚህ ፡ ወንጀሎችም ፡ በማተም ፡

BACK



በሚለጠፉ ፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ በሥዕሎች ፤ በሲኒማ ፤ በራዲዮ ፤ በቴሌቢዢዮን ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕዝብ ፡ ማስታወቂያ ፡ በሆኑ ፡ ዘዴዎች ፡ የሚደረጉ ፡ ናቸው ።

ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በዚሁ ፡ በሚታተም ፡ ጽሑፍ ፡ ከሆነ ፡ በክብረ ፡ ንክነት ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ በግላዊ ፡ ወይም ፡ በጋራ ፡ ጸጥታ ፡ አደፍራሽነትና፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ተከብሮ ፡ የሚኖረውን ፡ ግናቸውንም ፡ ሕጋዊ፡ መብት ፡ በመንካት ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ።

## ቍ ፡ ፵፪ ። ዋና ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) በጽሑፍ ፤ በማስታወቂያ ፤ በተለጣፊ ፡ ወረቀትና ፡ በሥዕል ፡ እነዚህንም ፡ በመሰሉት ፡ አትሞ ፡ አውጥቶ ፡ ለሕዝብ ፡ በማስታወቅ ፡ ወንጀል ፡ ያደረገ ፡ ጽሑፉን ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ጽሑፍ ፡ የራሱ ፡ ያደረገና፡ እንደ፡ ባለቤት ፡ ሆኖ ፡ በወንጀል ፡ መንፈስ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲገለጽ ፡ ወይም ፡ እንዲበተን ፡ የሰጠ ፤ በመደቡ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በሥራው ፡ በአላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ በዋናነት ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ፡ወንጀል፡ ለሠሩ ፡ ሰዎች ፡ የተሠራው ፡ ጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ ይጸናል ።

## ቍ ፡ ፵፫ ። ታትመው ፡ በሚገለጹ ፡ ጽሑፎች ፡ በሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ ምክትል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ ያደረገው ፡ ሊታወቅ ፡ ባይቻል ፡ ወይም ፡ ደራሲው ፡ ሳያውቅ ፡ ወይም ፡ ሳይፈቅድ ፡ ጽሑፉ ፡ ታትሞ ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ደራሲው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊዳኝ ፡ የማይቻል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለተሠራውና ፡ ለተገለጠው ፡ ጉዳይ ፡ በአድራጊነት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ሊቀጣ ፡ የሚገባው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፤

(ሀ) በየጊዜው ፡ እየታተመ ፡ የሚወጣ ፡ ጽሑፍ ፡ (ጋዜጣ ፡ ወይም ፡ መጽሔት) ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ለተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ በቀጥታ ፡ አላፊ ፡ የሚሆነውን ፡ ደራሲ ፡ ለመግለጽ ፡ ካልፈለገ ፡ በቀር ፡ ለታተመው ፡ ጉዳይ ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቀው ፡ የጋዜጣውና ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጅ ፡ ዲሬክተር ፡ ወይም ፡ ሬዳክተሩ ፡ ነው ።

(ለ) በየጊዜው ፡ እየታተመ ፡ የማይወጣ ፡ ወይም ፡ ለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ አዘጋጁው ፡ (ኤዲተሩ) ፡ እርሱም ፡ ባይኖር ፡ አታሚው ፤ አታሚው ፡ ባይኖር ፡ ሻጪዎቹ ፡ ወይም ፡ አዳዮቹ ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የወንጀለኛው ፡ በደል ፡ የሚገመተው ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጠቅላላዎቹን ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፷፩ ። የጽሑፍን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ ማክበር ።

በጋዜጣ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ እየታተመ ፡ በሚወጣ ፡ ጽሑፍ ፡ ጥፋት፡በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ዲሬክተሩ ፡ ወይም ፡ አላፊው ፡ አዘጋጅ ፡ (ሬዳክተሩ) ፡ የጽሑፉን ፡ ምስጢር፡ የመጠበቅ ፡ መብትን ፡ ድጋፍ ፡ በማድረግ ፡ ደራሲውን ፡ ለመግለጽ ፡ ያልፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጽሑፉን ፡ ደራሲ ፡ ለማወቅ ፡ የተለመዱትን ፡ የምርመራ ፡ ዘዴዎ ችና ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡ የግዴታ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ አይቻልም ።

ይህ ፡ የምርመራ ፡ ዘዴና ፡ የማስገደድ ፡ ሥራ ፡ የሚፈጸመው ፡ ግን ፡ ታትሞ ፡ የተ ገለጸው ፡ ጽሑፍ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ሕግ፡ልዩ፡ክፍል ፡ በ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡*ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ ተደነገገው ፡ በመንግሥቱ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በነጋሢው፡ላይ ፡ ወይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ በተቋቋመው ፡ የመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፤ ወይም ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ የሚያደርስ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ፡* ፪፻፷፰ ፡ እስከ ፡ ፪፻፹፯ ።]

## ቍ ፡ ፷፪ ። በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ወሬን ፡ በመንዛት ፡ ምክትል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በፊልም ፤ በተለጣፊ ፡ ማስታወቂያ ፤ በቲያትር ፤ በራዲዮ ፡ በቴሌቪዚዮንና ፡ በሌላም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ አማካይነት ፡ ሲሆን ፡ በደንቡ ፡ አላፊ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ የጽሑፉ ፡ ደራሲ ፡ ወይም ፡ የሥዕሉ ፡ ሠዓሊ ፡ ባይኖር፡ ፊልም ፡ አንሺው ፡ ወይም ፡ ጽሑፉን ፡ አታሚው ፤ እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ ሥራውን፡ እንዲነዛ ፡ ያደረገው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፤ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ ቢሆን፡አላፊ ፡ ሆኖ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፷፫ ። ሁለተኛ ፡ አላፊነትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።

በሕግ ፡ ላይ ፡ በተደነገገው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ከአላፊዎቹ ፡ አንዱ ፡ ከተቀጣ፡ በዚሁ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ሌሎቹ ፡ ከአላፊነት ፡ ውጪ ፡ ሆነው ፡ ከቅጣት ፡ ይድናሉ ።

## ቍ ፡ ፷፬ ። በጽሑፍ ፡ ጉዳይ ፡ የማይደፈር ፡ መብት ።

በማያጠራጥር ፡ ምክንያት ፡ ለሕዝብ ፡ መገለጻቸው ፡ በሕግ ፡ በቂ ፡ በሆኑ ፡ ምክ ንያቶች ፡ ወይም ፡ ለዚህ ፡ በግልጽ ፡ በሰተጠ ፡ ውሳኔ ፡ በተለይ ፡ የተከለከሉ ፡ ካል ሆኑ ፡ በቀር ፡ ያንድ ፡ ትችት ፡ ውሳኔ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ በታረመ ፡ ፅቅድ ፡ የወጣ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡ መግለጫ ፡ የሕግ፡ አውጪዎችን ፤ ያስተዳዳሪዎችን ፤ የፍ ርድ ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ ያተመ ፡ ያስታወቀ ፡ የገ ለጠ ፡ ደራሲ ፡ ወይም ፡ ጽሑፍ ፡ አታሚ ፡ ወይም ፡ ተናጋሪው ፡ አይቀጣም ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።
## ወንጀል ፡ አድራጊውን ፡ የሚያስቀጡ ፡ ሁኔታዎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### የወንጀል ፡ አላፊነት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።
### መደበኛ ፡ አላፊነት ።

**ቍ ፡ ፵፰ ። ለወንጀል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆንና ፡ ስላለመሆን ።**

(፩) አድራጊው ፡ ለሠራው ፡ ሥራ ፡ አላፊ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተቀጪ ፡ አይሆንም ።

በዕድሜ ፤ በሕመም ፤ በዕውቀት ፡ ባለመጐልመስ ፡ ወይም ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ በአእምሮ ፡ መቃወስ ፡ ምክንያት ፡ ጥፋት ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ የተግባሩን ፡ ዐይነትና ፡ ውጤት ፡ ለመገመት ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ለመራመድ ፡ ያልቻለ ፡ ሲሆን ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ በሕጉ ፡ መንፈስ ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

(፪) ተከሳሹ ፡ የማይቀጣ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ሕክምናዎችን ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የጥበቃ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ እንዲያደርጉለት ፡ ያዛል ። [ቍ ፡ ፻፴፫ ፡ እስከ ፡ ፻፴፭ ።]

**ቍ ፡ ፵፱ ። የተቀነሰ ፡ አላፊነት ።**

(፩) የአእምሮ ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ እድገቱ ፡ የጐደለ ፤ ወይም ፡ ያልተካከለና ፡ በጐደሉ ፡ ሁኔታ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የተግባሩ ፡ ዐይነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አላፊነትን ፡ እንደሚያስከትል ፡ በሙሉ ፡ ለመገመት ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ለመራመድ ፡ ያልቻለ ፡ ሲሆን ፡ ላደረገው ፡ ጥፋት ፡ የተወሰነው ፡ ተገቢው ፡ ቅጣት ፡ በሙሉ ፡ ሊፈጸምበት ፡ አይቻልም ።

ቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ሊያቃልልለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፹፮ ።]

(፪) ከቅጣቱ ፡ ጋራ ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ [1] ያጥፊውን ፡ ቅጣት ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ በሕክምና ፡ መንገድ ፡ እንዲጠበቅ ፤ ከአጥፊነቱ ፡ እንዲታረም ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ልዩ ፡ ጥበቃ ፡ እንዲደረግለትም ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ * ፻፴፫ ፡ እስከ ፡ ፻፴፭ ።]

**ቍ ፡ ፶ ። ከአላፊነት ፡ እድናለሁ ፡ በማለት ፡ ዘዴን ፡ ስለ ፡ መፍጠር ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ አላፊነቱን ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ከአላፊነት ፡ ለመዳን ፡ ሲል ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በአልኮል ፡ መጠጥ ፡ ወይም ፡ አእምሮን ፡ በሚያደነዝዝ ፡ ወይም ፡

BACK



በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አኳኋን ፡ ተደግፎ ፡ ለሠራው ፡ ወንጀል ፡ ቅጣትን ፡ የሚ ቀንሱ ፡ ወይም ፡ ነጻ ፡ የሚያወጡ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አይጸኑለትም ። ጠቅላላዎቹ ፡ የወንጀል ፡ ደንቦች ፡ ይጸኑበታል ።

(፪) አድራጊው ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ለማወቅ ፡ እየቻለ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ እያለ በት ፡ አንድ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ጥፋት ፡ ከአላፊነት ፡ እንዲወጣ ፡ ወይም ፡ አላፊነቱ ፡ እንዲቀነስለት ፡ አድርጎ ፡ ቢገኝ ፤ የተፈጸመ ውም ፡ ወንጀል ፡ በቸልተኛነት ፡ መሠረት ፡ የሚያስቀጣ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋተኛው ፡ ስለ ፡ ቸልተኛነት ፡ በተደነገጉት ፡ በመደበኛዎቹ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ተፈርዶበት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፶፱ ።]

(፫) አድራጊው ፡ ሊሠራው ፡ ያልፈቀደውን ፡ ወይም ፡ ያላሰበውን ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ በጭራሽ ፡ ከአላፊነት ፡ በሚያድን ፡ ሁኔታ ፡ በገዛ ፡ ጥፋቱ ፡ ሠርቶ ፡ ሲገኝ ፡ በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ ስለ ፡ ማድረስ ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፹፭ ። የተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ ይፈጸምበታል ።

**ቍ ፡ ፶፩ ። አጠራጣሪ ፡ ሁናቴ ።**

(፩) በተከሳሹ ፡ አላፊነት ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የጥርጣሬ ፡ ምክ ንያት ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ በተከሳሹ ፡ በቀድሞ ፡ ኑሮዎቹና ፡ ሁኔታዎቹ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ምር መራ ፡ እንዲደረግ ፡ ትእዛዝን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ስለዚሁ ፡ ነገር ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያለውን ፡ ያዋቂ ፡ አሳብ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

ተከሳሹ ፡ የአእምሮ ፡ በሽታ ፡ ያደረበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሚጥል ፡ በሽታ ፡ (ኤፒሌፕሲ) ፡ የሚታወክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በድንቍርናና ፡ በዲ ዳነት ፡ ወይም ፡ በመጠጥ ፡ አዘውታሪነት ፡ በሽታ ፡ የተለከፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚሁ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያለውን ፡ ያዋቂ ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ መጠየቅ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ዐዋቂ ፡ ወይም ፡ ዐዋቂዎች ፡ በተለመ ዱት ፡ ዐይነቶች ፡ የምርመራውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ መርጦ ፡ ያዛቸዋል ። እንዲሁም ፡ የተግባራቸውን ፡ አገባብና ፡ የሚያጣሩዋቸውንም ፡ ጉዳዮች ፡ ገልጾ ፡ ያስታውቃቸዋል ።

በተከሳሹ ፡ ሁኔታ ፤ በማመዛዘንና ፡ በመወሰን ፡ ችሎታው ፡ ላይ ፡ ሁኔታው ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ውጤት ፡ ምርመራው ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ፤ ከዚ ህም ፡ በቀር ፡ ሕክምናና ፡ የሕክምና ፡ ዐይነት ፤ ወይም ፡ ስለ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባ በቅ ፡ የሆኑት ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ጠቃሚ ፡ መሆናቸውን ፡ ለዳኛው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) በዚሁ ፡ በተገኘው ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡

መያዝ ፡ የሚገባው ፡ ልዩ ፡ መርማሪው ፡ በሕግ ፡ ነገር ፡ ረገድ ፡ የሚያቀርብለ
ትን ፡ አሳብ ፡ ሳይሆን ፤ በሲያንስ ፡ (በሥነ ፡ ጥበብ ) ፡ ረገድ ፡ በትክክል ፡ ተጠ
ንቶ ፡ የሚቀርብለትን ፡ ባስረጂው ፡ ውጤት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የተገኘውን ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ጥፋተኞች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ወጣቶች ።

### ቍ ፡ ፶፪ ። ስለ ፡ ሕፃናት ። የዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስላለመፈጸማቸው ።

የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዕድሚያቸው ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ባልሞላ ፡ ሕፃናት ፡
ላይ ፡ አይፈጸሙም ። እነዚህም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ አላፊዎች ፡
ሆነው ፡ አይቈጠሩም ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፡ በነዚህ ፡ ሕፃ
ናት ፡ ልጆች ፡ ላይ ፤ ባለሥልጣን ፡ የሆኑ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቻቸውና ፡ አስተማሪዎቻ
ቸው ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ያደርጉላቸዋል ።

### ቍ ፡ ፶፫ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ።

(፩) ዕድሚያቸው ፡ ከዘጠኝ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሞላቸው ፡ አካለ ፡
መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆችና ፡ ወጣቶች ፡ (ወራዙት) ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡
የሚያስቀጣ ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ ሕጉ ፡ ለይቶ ፡ ከወሰነላቸው ፡ ቅጣቶ
ችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥራዎች ፡ በቀር ፡ አይቀጡም ። [ቍ ፡ ፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፻፸፫ ።]
በግናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ለዐዋቂዎች ፡ ጥፋተኞች ፡ በተመለከቱት ፡ በደንበ
ኞቹ ፡ ቅጣቶች ፡ መሠረት ፡ አይቀጡም ። እንደዚሁም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በእ
ስር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አይደባለቁም ።

(፪) ቅጣት ፡ ወይም ፡ የዲስፕሊን ፡ ሥርዐት ፡ ሊፈጸምባቸው ፡ የሚቻለው ፡ ፍርድ ፡
ቤቱ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አላፊነታቸ
ውን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፻፷፪ ፡ እስከ ፡ ፻፸፫ ።]

### ቍ ፡ ፶፬ ። ስለ ፡ ዳኛ ፡ ግምት ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ የሚደረጉትን ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥራ
ዎች ፡ ሲመርጥ ፡ በአጥፊው ፡ ወጣት ፡ ዕድሜ ፤ በጠባዩ ፤ በአእምሮውና ፡ በግብረ ፡
ገብነቱ ፡ የደረሰበትን ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ እንደዚሁም ፡ የሚፈጸሙበት ፡
የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዓላማ ፡ በመልካም ፡ ጠባይ ፡ ለማሳደግ ፡ እንዲሆን ፡ በማሰብ ፡
መመራት ፡ አለበት ።

በትክክል ፡ ወደ ፡ ግቡ ፡ ለመድረስ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ፡ቤቱ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ማሻሻል ፡ ይገባዋል ። [ቍ ፡ ፻፷፯ ።]

ቍ ፡ ፶፰ ። ስለ ፡ ማጣራት ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ምርመራና ፡ ስለ፡ማናቸውም ፡ ምርመራ ።

(፩) ለሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በታየው ፡ ቍጥር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ ስለ ፡ ወጣቱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ጠባይ ፣ ስለ ፡ አስተዳደጉ ፣ ስለ ፡ ኑሮውና ፡ ስለ፡ሕይወቱ ፡ ሁኔታ ፡ ሊያውቅ ፡ የሚፈልገውን ፡ መረጃ ፡ ይጠይቃል ።

የዘመዶቹን ፣ የትምህርት፡ቤቱን፡ ባለሥልጣኖች ፡ የአሳዳጊዎቹን፡አሳብ፡ መቀበል ፡ ይችላል ። እነዚህም ፡ የትምህርት ፡ ባለሥልጣኖችና፡አሳዳጊዎች፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ወጣትና ፡ በቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ ላይ ፡ የግል ፡ መዝገባቸውን ፡ (ዶሴዩ) ፡ የሐኪሞቹን ፡ የምርመራ ፡ ውጤትና ፡ ስለ፡ማኅበራዊ ፡ ኑሮዋቸው ፡ የሚያውቁትን ፡ ነገር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያቀርባሉ ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር፡ተከሳሹ፡በመላ፡አካሉና ፣ በአእምሮው፡ትክክለኛ፡ጤና፡ ያለውና ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ እንዲችል ፣ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ በሕክምና ፡ እየተጠበቀ ፡ ደንበኛ ፡ አስተዳደግ ፡ ሊያገኝ ፡ በሚችልበት ፡ አማካይ ፡ ስፍራ ፡ ባንድ ፡ የማኅበራዊ ፡ መኖሪያ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ፡ ተገቢነት ፡ ባለው ፡ ቦታ ፡ እንዲኖር ፡ ካደረገው ፡ በኋላ ፡ ልዩ፡ዕውቀት፡ያላቸውን፡ ሰዎች ፡ የምርመራ ፡ አሳብ ፡ መጠየቅ ፡ ይገባዋል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለዚሁ፡ወጣት ፡ ሊደረግለት ፡ የሚገባውን ፡ የማስታመም ፣ በትምህርት ፡ የማሠልጠን ፣ የጠባይን ፡ ማረም ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ፡አጠባበቆችን ፣ ጥንቃቄዎችን ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ይጠይቃል ።

(፫) ሕጋዊን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ የቀረበውን ፡ የመርማሪውን ፡ አስተያየት ፣ የአሳብ ፡ አቀራረቡን ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፶፱ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ከማድረስ ፡ አስቀድሞ ፡ ያለው ፡ መካከለኛ ፡ ጊዜ ።

(፩) አድራጊው ፡ ወንጀል ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ካ፲፭ ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ዕድሜ፡ ኖሮት ፣ ነገር ፡ ግን ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ያልሞላው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚወሰንበት ፡ በሕጉ ፡ ላይ፡በተመለከቱት ፡ በመደበኞቹ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ የሚወስነው ፣ በነገሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታና ፡ ይልቁንም ፡ ቢያንስም ፡ ቢበዛም ፡ የተከሳሹን ፡ የወጣትነት ፡ ዕድሜ ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ስሜቱ፡መጥፎነትና ፡ አደገኛነት ፣ ከብዙ ፡ በጥቂቱ፡ዐመሉ፡ ሊታረምና ፡ ሊሻሻል ፡ የሚችል ፡ ዕድል ፡ የሚያጋጥመው ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ደንበኞቹን ፡ የቅጣት ፡ ማቃለያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡

አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ *ወይም ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱት ፡ ወንጀለኞች ፡ የተመደበውን ፡ የልዩ ፡ ቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ በመከተል ፡ ‡ነው ።[ቍ ፡ *፻፹፪ ፡ ‡ ፻፹፮ ፡ እስከ ፡ ፻፹፰ ።]

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በወንጀል ፡ ሥራ ፡ አጥፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### አሳብ ፤ ቸልተኛነትና ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ።

**ቍ ፡ ፶፯ ። መሠረቱ ፤ የወንጀል ፡ ጥፋትና ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ።**

(፩) በሕጉ ፡ አሳብ ፡ አጥፊነቱ ፡ ተገልጾ ፡ ካልታወቀ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊቀጣ ፡ አይቻልም ።

በሥራው ፡ አላፊ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ካላደረገ ፡ በወንጀለኛነት ፡ ሊፈረድበት ፡ አይቻልም ።

(፪) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ጥፋት ፡ ሳያደርግ ፤ የተሠራው ፡ ጥፋት ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ቢሆንም ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ በድንገተኛነት ፡ ወይም ፡ በአጋጣሚ ፡ አደጋ ፡ የተሠራ ፡ ወይም ፡ የደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሊቀጣ ፡ አይገባውም ።

ከወንጀል ፡ ሥራ ፡ አላፊነት ፡ የተነሣ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ሊኖሩ ፡ የሚችሉትን ፡ የኪሣራ ፡ ጉዳዮች ፡ አያስቀራቸውም ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ቀላል ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛነት ።

**ቍ ፡ ፶፰ ። ዐውቆ ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።**

(፩) ጥፋት ፡ መሆኑን ፡ ሕሊናው ፡ እየተረዳው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የማይገባና ፡ የሚያስቀጣ ፡ ጥፋትን ፡ ፈጽሞ ፡ የዚሁኑ ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ዐውቆ ፡ የሕግ ፡ መጣስን ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ይቈጠራል ።

የአጥፊነት ፡ ተግባር ፡ በራስ ፡ ፈቃድና ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ የሚቈጠረው ፡ ጥፋተኛው ፡ ይህ ፡ ሥራው ፡ በወንጀል ፡ ቅጣትን ፡ እንደሚያመጣበት ፡ እየተረዳ ፡ የሆነው ፡ ይሁን ፡ በማለት ፡ ይህንኑ ፡ የወንጀል ፡ ተግባሩን ፡ ዐውቆ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) በገዛ ፡ ፈቃድ ፡ ታስቦ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ *እንደተመለከተው ፡ በቂና ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ ምክንያትና ፡ ይቅርታ ፡ ለማስጠት ፡ የሚቻልበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ምንጊዜም ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ። [ቍ፡ *፸፮፡እስከ፡፸፱።]

(፫) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ቸልተኝነት ፡ የተደነገጉት ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ባላወቀው ፡ ባልፈለገው ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በአጋጣሚ ፡ ከአሳቡ ፡ በላይ ፡ በሆነው ፡ ሥራ ፡ ሊቀጣ ፡ አይቻልም ።

## ቍ ፡ ፶፱ ። በቸልተኛነት ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥፋት ።

(፩) ተግባሩ ፡ ሊያመጣበት ፡ የሚችለውን ፡ ውጤት ፡ ሳይገምትና ፡ ሳያስብ፡ባለማመዛዘንና ፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ በቸልተኛነት ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ይቈጠራል ።

በግል ፡ ኑሮው ፡ አቀማመጥ ፡ ግምት ፤ በተለይም ፡ በዕድሜውና ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ባለው ፡ የልማድ ፡ ዕውቀት ፡ በትምህርቱ ፡ ደረጃ ፡ በልዩ ፡ ሞያ ፡ በሚፈጽመው ፡ ሥራውና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ ደረጃ ፡ ግምት፡መጠን ፡ ሊያደርጋቸው ፡ የሚገቡትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ያልፈጸመ ፡ ሰው ፡ በአኳኋኑ ፡ ጥፋተኛ ፡ ይባላል ።

(፪) በተደረገው ፡ ጥፋት ፡ ዐይነትና ፡ ከባድነት ፡ ወይም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችለው ፡ አደጋ ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ በሕጉ ፡ ላይ፡በተለይ፡እንደ፡ ወንጀል ፡ ተቈጥሮ ፡ ካልተደነገገ ፡ በቀር ፡ በቸልተኛነት ፡ የተሠራ ፡ ሥራ ፡ አያስቀጣም ።

ሊያስከትልበት ፡ የሚችለውን ፡ በሕሊናው ፡ እየተረዳ ፡ ወይም ፡ ለመረዳት ፡ ሲገባውና ፡ መረዳትና ፡ መገመትም ፡ ሲኖርበት ፡ ካለማመዛዘኑ ፡ የተነሣ ፡ያደረገው ፡ የጥፋት ፡ ደረጃና ፡ የአድራጊውን ፡ አደገኛነት ፡ ጠባይ ፡ በመገመት ፡ ተገቢውን ፡ ቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስንበታል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ወንጀሎች ፡ ወይም ፡ የሕግ፡ድንጋጌዎች፡አንድነት ፡ ሆነው ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለ ፡ ጥፋተኛነት ።

## ቍ ፡ ፷ ። ላንድ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በሕግ ፡ በተጠበቀ ፡ ባንድ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የሚሠሩ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ የተቀላቀሉ ፡ የወንጀል ፡ አድራጎቶች ፡ የተፈጸሙት ፡ ባንድ ፡ የወንጀል፡መሥራት፡ አሳብ ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ፡ሁለት፡ወይም፡ ከሁለት ፡ የበለጡ ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሊወሰንባቸው ፡ አይቻልም ።

(፪) በሕግ ፡ በተጠበቀው ፡ በዚያው ፡ ባንድ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ተደጋግመው ፡ ወይም ፡ ተከታትለው ፡ የተፈጸሙ ፡ የወንጀል ፡ አድራጎቶች ፡ ባንድ ፡ የወንጀል ፡ መሥራት ፡ አሳብ ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ቸልተኛነትና ፡ አንድ ፡ ግብ ፡ ለማግኘት ፡ በተደረጉ፡ጊዜ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ብቻ ፡ ተቈጥረው ፡ አድራጊውም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ተከታትለው ፡ ለተፈጸሙት ፡ አድራጎቶች ፡ ሳይሆን ፡ ለዚሁ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ለተቈጠረው ፡ ወንጀል ፡ ብቻ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፫) አጥፊው ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ወንጀል ፡ የመሥራት ፡ አሳብ ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ በሚገመትበት ፡ ጊዜ ፤ ለምሳሌ ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የማይገባውን ፡ ብልጽግና ፡ ለማግኘት ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ እንዲዘዋወር ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ ተገልግሎበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንጀለኛው ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጥፋቱን ፡ እግቡ ፡ ለማድረስ ፡ ሲል ፡ መሠረታዊ ፡ ከሆነው ፡ ወንጀል ፡ በኋላ ፡ አከታትሎ ፡ የፈጸመው ፡ ተከታይ ፡ ተግባሩ ፡ ከቀድሞው ፡ አሳቡና ፡ ሊደርስበት ፡ ካቀደው ፡ ግቡ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ በመሆን ፡ በዋናው ፡ ወንጀል ፡ ይጠቀለላል ።

ቊ ፡ ፷፩ ። አዲስ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትል ፡ ጥፋትን ፡ የመደጋገም ፡ ሥራ ።

ቢሆንም ፡ አድራጊው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ጠባይ ፡ ከያዙት ፡ ወንጀሎች ፡ አንደኛውን ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፈጸመው ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ቀድሞ ፡ ሠርቶት ፡ ከነበረው ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ በመሆን ፡ በዚያው ፡ ቀድሞ ፡ በድሎት፡ በነበረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ያንኑ ፡ የመሰለ ፡ በደል ፡ ለማድረስ ፡ ወይም ፡ ቀድሞ፡ወንጀል ፡ አድርሶበት ፡ በነበረው ፡ በሕግ፡በተጠበቀው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በፊት፡ ሠርቶት ፡ ከነበረው ፡ ወንጀል ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ፍጹም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ በማግኘት ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ የሠራውም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትል ፡ ጥፋትን ፡ ወይም ፡ የነዘህላልነት ፡ ተግባርን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ፈጽሞ፡ ከተገኘ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ያህል ፡ ተቈጥሮ ፡ ፍርድ፡ቤቱ ፡ ስለ ፡ ተደራረቡ፡ግዙፍ ፡ ጥፋቶች ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ ያጸናበታል ። [ቊ ፡ ፻፶፱ ።]

ቊ ፡ ፷፪ ። የተቀራረበ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ስላለው ፡ ጥፋተኛነት ።

አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ጥፋተኛ ፡ የፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ የሚመለከተው ፡ የሕዝብ ፡ ንብረት ፡ የመድፈርን ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ አካል ፤ በክብር ፤ በሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የማድረግን ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ይህንኑም ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ ያስቀጣል ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነውን ፡ የሌላ ፡ ወንጀል ፡ ውጤት ፡ በማስገኘት ፡ ዐቅድ ፡ ተንሣሥቶ ፡ ወይም ፡ የዚሁኑ ፡ አፈጻጸም ፡ ዘዴ ፡ አቃንቶ ፡ እግቡ ፡ ለማድረስ ፡ በዋናው ፡ ወንጀል ፡ አስታኮ ፡ ሊፈጽም ፡ ያሰበውን ፡ ወንጀል ፡ ሞክሮ ፡ ከተገኘ ፡ ሕጉ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ቅጣት ፡

እንዲወሰንበት ፡ የደነገገና ፡ ይህንኑ ፡ እንደ ፡ ልዩ ፡ ወንጀል ፡ የሚቈጥረው ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ በተደራረቡ ፡ ጥፋቶች ፡ ላይ ፡ ቅጣትን ፡ ለማክበድ ፡ የተመለከተው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ ይፈጸምበታል ። [ቍ ፡ ፻፺ ።]

ቍ ፡ ፷፫ ። የተቀላቀለ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ስላለው ፡ ጥፋተኛነት ።

(፩) በሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለማድረስ፡ይችላል፡ተብሎ፡ የሚገመት ፡ አንድ፡የተወሰነ ፡ ወንጀል ፡ በጦር፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ በሆነ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያና ፡ ዘዴ ፡ በእሳት ፤ በሚፈነዳ ፡ ነገር ፤ በመርዝ ፡ ወይም ፡ በሚያፈዝ ፡ መድኀኒት ፡ አማካይነት፡ሊሠራ ፡ ታስቦ፡የሰውን፡አካል፡ እንደ ፡ መጉዳት ፡ ወይም፡የሰውን ፡ ጤንነት ፡ እንደ፡መንካት ፤ የሰውን ፡ ሕይ ወት ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ ማሳለፍ ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ማጥፋት ፡ ያለውን ፡ የሁለተኛውን ፡ ተጨማሪ ፡ ወንጀል ፡ ጠባይ ፡ የሚያቋ ቁም ፡ በመሆን ፡ ተፈጽሞ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጥፋተኛነትን ፡ ሁኔታና ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰን ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱ ትን ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦች ፡ መከተል ፡ አለበት ።

(ሀ) አድራጊው ፡ ወንጀሉ ፡ የሚያስገኘውንና ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት፡ ቀድሞውንም ፡ በትክክል ፡ አስቦና ፡ ገምቶ ፡ ያቀደው ፡ ጕዳይ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ *አስቦ ፡ በመሥራት ፡ ለተደረጉት ፡ ለሁለቱ፡ወንጀሎች፡አቋም፡ የሚሆኑዋቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ መፈጸማቸውን ፡ በመገመት ፡ ጕዳዩን ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ‡ መሠረት ፡ የተደራረቡና ፡ የከበዱ ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ። [ቍ *፻፹፱ ። ‡ ፻፺፪ ።]

(ለ) የዚህ ፡ ወንጀል ፡ ውጤት ፡ የሚያስከትለው፡አደጋ ፡ ቀድሞውንም ፡ ይህን ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያደርስ ፡ በመገመት፡የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎ ችና ፡ አጋጣሚዎች ፡ በዚሁ ፡ ውጤት ፡ ውስጥ ፡ ሊታሰቡ ፡ የሚችሉና ፡ የሚገባቸው ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ *ታስቦ ፡ የተሠራውን ፡ ዋነኛውን፡ወንጀ ልና ፡ በንዝህላልነት ፡ ተሠርቶ ፡ ውጤት ፡ ያስገኘውን ፡ ወንጀል ፡ የሚ መለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተደራራቢዎች ፡ ስለሚሆኑ ፡ በዚሁ ፡ ምክን ያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ ያከብዳል ። [ቍ ፡ *፶፱ ፡ (፩) ።]

(፪) በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ በሚያደርሱ ፤ ይልቁንም ፡ እንደ፡እሳት ፡ አደጋ ፡ ባሉ፡በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ በመገልገል ፤ በሕዝብ ፡ መገናኛ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ የሚያደርስ ፡ ወንጀል፡ሲሆ ንና ፡ እንዲሁም ፡ ሰዎችን ፡ የማጋለጥ ፡ የማጕላላት ፡ የይዋጣልን ፡ ቶክክር ፡ እርጉዚቱን ፡ ሴት ፡ የማስወረድ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ የሚመለከተው ፡ ወንጀል ፡ የተሠራ ፡ ሲሆን ፡ የቅጣት ፡ ማክበድን ፡ ደንብ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

BACK



## ክፍል ፡ ፪ ።
## በሕግ ፡ የተፈቀደ ፡ አድራጎት ።
## የማያስቀጡና ፡ ይቅርታ ፡ የሚያሰጡ ፡ ሁኔታዎች ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
### በሕግ ፡ የተፈቀደ ፡ አድራጎት ።

**ቍ ፡ ፷፬ ። በሕግ ፡ የታዘዙ ፡ ወይም ፡ የተፈቀዱ ፡ ተግባሮች ።**

በሕግ ፡ የታዘዙ ፡ ወይም ፡ የተፈቀዱ ፡ ተግባሮች ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ የማይቈጠሩና ፡ የማያስቀጡ ፡ ናቸው ። በተለይም ፡

(ሀ) ከሕግ ፡ ወሰን ፡ ሳያልፍ ፡ የተፈጸመውን ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የመንግሥትንና ፡ የወታደርን ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመለከቱ ፡ ተግባሮች ፡ ሲሆኑ ፤

(ለ) ከደንበኛው ፡ ሕሊናዊ ፡ ልምድ ፡ ወሰን ፡ ያልወጡ ፡ የጠባይ፡ማረም ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ማስፈጸም ፡ ሥልጣናዊ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ተግባሮች ፡ ሲሆኑ ፤

(ሐ) ሁኔታዎቹና ፡ ወሰናቹ ፡ ያልተጣሱ ፡ ሆነው ፡ ሕገ፡ ወጥነት ፡ ያለው ፡ የመብት ፡ መነካት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ በምክትልነት ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የተፈቀዱ ፡ የሚገቡ ፡ ተግባሮች ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፷፭ ። የሞያ ፡ ሥራ ፡ ግዴታ ።**

አድራጊው ፡ የሠራው ፤ ሕግ ፡ ከሚያስገድደው ፡ ከሞያ ፡ ሥራው ፡ ደንብና ፡ ልማድ ፡ ውጪ ፡ ሳይሆንና ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ የቸልተኛነት ፡ ጥፋት ፡ የሠራ ፡ ካልሆነ ፡ በሞያ ፡ ሥራው፡ በሕክምና ፡ ሞያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ በሌላ ፡ የሥራ ፡ ግዴታ ፡ ምክንያት ፡ በሠራው ፡ አይቀጣም ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ የካሣና ፡ የኪሣራ ፡ ጉዳዮች ፡ እንደ ፡ ቀጠበቁ ፡ ናቸው ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
### የማያስቀጡና ፡ ይቅርታ ፡ የሚያሰጡ ፡ ሁኔታዎች ።

**ቍ ፡ ፷፮ ። ስለ ፡ ተበዳይ ፡ ፈቃድ ።**

አድራጊው ፡ የሠራው ፡ ተግባር ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ የተከለከለና ፡ የሚያስቀጣ ፡ ከሆነ ፤ ተጎጂው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ የተስማማበት ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ቅጣት ፡ አይቀርለትም ።

## ቊ ፡ ፷፯ ። ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መገደድ ።

ሊያግደው ፡ የማይችለው ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የሰውነት ፡ መገደድ ፡ ደርሶበት ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ በግዴታ ፡ ባደረገው ፡ ጥፋት ፡ አይቀጣም ። አስገዳጁ ፡ ግን ፡ ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ። [ ቊ ፡ ፶፰ ፡ (፩) ፡ (ሐ) ። ]

ግዴታው ፡ የሕሊና ፡ (የሞራል) ፡ ግዴታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ቅጣቱን ፡ ያቀልለታል ፤ ወይም ፡ ከቅጣቱ ፡ በፍጹም ፡ ነጻ ፡ ሊያ ደርገው ፡ ይችላል ። [ ቊ ፡ ፸፱፹፮ ። ]

## ቊ ፡ ፷፰ ። ለማሸነፍ ፡ ስለሚቻል ፡ መገደድ ።

የደረሰበት ፡ መገደድ ፡ ሊታገድ ፡ የሚቻል ፡ ሆኖ ፡ ለማሸነፍ ፡ ወይም ፡ ተግባሩን ፡ ከማድረግ ፡ ለማምለጥ ፡ ችሎታ ፡ እያለው ፡ ጥፋት ፡ ያደረገ ፡ በመደቡ ፡ ይቀጣል ።

ቢሆንም ፡ የነገሩን ፡ አኳኋን ፡ ይልቁንም ፡ የመገደዱን ፡ ዐይነት ፡ የከፍተኛነቱ ንም ፡ መጠን ፡ እንዲሁም ፡ የተገዳጁን ፡ የግል ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ሁኔታና ፡ የዕድሜ ውን ፡ በተለይም ፡ የሁለቱን ፡ የጉልበታቸውን ፡ መጠንና ፡ በተገዳጁና ፡ በአስገዳጁ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የበታችነትና ፡ የበላይነት ፡ አኳኋን ፡ በመገመት ፤ በመገደድ ፡ ባጠፋው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ በመሰለው፡ይወስናል ። [ቊ፡፸፱፹፮ ። [

## ቊ ፡ ፷፱ ። የበላይ ፡ ትእዛዝ ፤ የትእዛዝ ፡ ሰጪው ፡ አላፊነት ።

የማዘዝ ፡ ሥልጣንና ፡ መብት ፡ ካለው ፡ የበላይ ፡ ከሆነ ፡ ያስተዳደር ፡ ወይም ፡ የወ ታደር ፡ ሹም ፡ በተሰጠው ፡ ቊርጠኛ ፡ ትእዛዝ ፡ የበታች ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንጀሉ ፡ ከተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውጭ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ የሚቀጣው ፡ የበላዩ ፡ አዛዥ ፡ ነው ። [ቊ ፡ ፴፪ ። (፫) ። ]

## ቊ ፡ ፸ ። የትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ አላፊነት ።

(፩) ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ እንዲፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ሥራ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ መሆኑ ንና ፡ በተለይም ፡ አዛዡ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የሌለውና ፡ የሚ ፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ወንጀል ፡ መሆኑን ፤ በሕግም ፡ የተከለከለና ፡ የሚያስቀጣ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፤ በተለይም ፡ የተፈጸመው ፡ ተግባር ፡ የነፍስ ፡ መግደል ፡ ወይም ፡ የቃጠሎ ፡ ወይም ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሀብቶች ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በሕዝብ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የደረሰ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሲሆን ፡ በጥፋቱ ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ ይቀጣል ።

ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ የመጠበቅና ፡ የመታዘዝ ፡ ስሜት ፡ አድሮበት ፡ ትእዛዙን ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የትእዛዙን ፡ አስ ገዳጅነት ፡ በመገመት ፡ በመሰለው ፡ የሚወስነውን ፡ ቅጣት ፡ ሊያቃልልለት፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፹፮ ።]

(፪) ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ ጥፋት ፡ ያደረገው ፡ በመንግሥት ፡ ሥራና ፡ የወታደር ፡ ሥርዐት ፡ አፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚያስገድደው ፡ ተግባር ፡ ሆኖ ፡ ትእ ዛዙን ፡ ለመቃወምና ፡ ለመከራከር ፡ ባለመቻሉ ፡ በቀጥታ ፡ ከመፈጸም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የተሻለ ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ ባለመቻል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በግልጽ ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱን ፡ በሙሉ ፡ ሊያስቀርለት ፡ ይችላል ።

(፫) ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ ከተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውጭ ፡ የሆነውን ፡ ጥፋት ፡ ሆን፡ ብሎ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ባደረገው ፡ ጕድለት ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፸፭ ። አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ አድራጎት ፡ መተላለፍ ።

የግል ፡ ጥቅሙን ፡ ወይም ፡ ሊከላከልለት ፡ የሚገባውን ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ከፍ ፡ ካለና ፡ ከበለጠ ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በጥፋተኛነት ፡ የሚያስ ቀጣ ፡ ተግባር ፡ የሠራ ፡ የሚገባውን ፡ መብቱን ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ለማ ዳን ፡ ባለመቻሉ ፡ ምክንያት ፡ በግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖበት ፡ ከነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔ ታዎች ፡ ጋራ ፡ በተመዛዘኑ ፡ መሣሪያዎች ፡ ወንጀል ፡ ቢሠራ ፡ አያስቀጣውም ።

ቍ ፡ ፸፮።አስፈላጊ ፡ ግዴታ ፡ የሆነውን ፡ የመብት ፡ ወሰን ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

በነገሮቹ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኘው ፡ ሀብት፡ መከላከል ፡ ጕዳይ ፡ የሚፈጸመው ፡ መሥዋዕትነት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ሲገመት ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ጕዳት ፡ ካስፈላጊው ፡ መጠን፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አድራጊው ፡ የተገኘበት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገርና ፡ የአደጋ ፡ ሁኔታ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመሰለው ፡ ቅጣቱን ፡ ያቀልለታል ። [ቍ ፡ ፻፹፮ ።]

ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጕዳት፡የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አላፊነት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፸፯ ። ስለ ፡ ወታደራዊ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ።

(፩) በወታደራዊ ፡ አደጋ ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ ያድማ ፡ ግርግር ፡ ሲሆን ፡ ወይም፡ በጦር ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የወታደር ፡ አዛዥ ፡ ወይም ፡ የበላይ ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ በአገልግሎት ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ ለማ

ስከበር ፡ ወይም ፡ ተገቢውን ፡ የታዛዥነት ፡ ተግባር፡ ለማጽናት ፡ በነዚህ ፡ በተ ዘረዘሩት ፡ ጊዜያቶች ፡ አስፈላጊውን ፡ ጸጥታ ፡ ለማስገኘት ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ባለ መገኘቱ ፡ የፈጸመው ፡ አድራጎት ፡ አያስቀጣም ።

(፪) አድራጊው ፡ አስፈላጊው ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ከሚያስገድደው ፡ በላይ ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ሊያቀልለት ፡ ይችላል ። ወይም ፡ አጋጣሚው ፡ ነገር ፡ በተለይ ፡ አስገዳጅ ፡ ሲሆን ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ እስከ ፡ ማድ ረግ ፡ ድረስ ፡ ሊያቃልልለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፹፭ ።]

## ቍ ፡ ፸፬ ። ስለ ፡ ሕጋዊ ፡ መከላከል ፡ ( ስለ ፡ አልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ። )

ራስን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ወይም ፡ የራስን ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ሰውን ፡ ፍትሐዊ ፡ መብት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ከሆነ ፡ ጥቃት ፡ ወይም ፡ በእርግጠኛ ፡ ሊደርስ ፡ ከሚችል ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፤ አደጋው ፡ ወይም ፡ ጥቃቱ ፡ እንዳይደርስ ፡ ለማድረግ ፡ ሌላ ፡ መን ገድ ፡ ሳይኖር ፡ ከሁኔታው ፡ መጠን ፡ ባለማለፍ ፡ ይልቁንም ፡ ያደጋውን ፡ ከባድነ ትና ፡ የተጠቂውን ፡ መብት ፡ ከፍተኛነት ፡ በማመዛዘን ፡ በአልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይ ነት ፡ የተደረገው ፡ መከላከል ፡ አያስቀጣም ።

## ቍ ፡ ፸፭ ። የመከላከልን ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ ከመጠን ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ።

(፩) ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነውን ፡ ጥቃት ፡ ሲከላከልና ፡ የመጣበትን ፡ አደጋ ፡ ለአ ደጋው ፡ ተመዛዛኝ ፡ ባልሆነ ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነ ፡ መጠን ፡ አልፎ ፡ የመከላከልን ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ ወሰን ፡ ባለፈ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመሰለው ፡ ቅጣትን ፡ ለማቃለል ፡ ይችላል ።[ቍ ፡ ፻፹፭ ።]

(፪) ግፈኛን ፡ ለመከላከል ፡ ሲል ፡ ያደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ከመጠኑ ፡ ያለፈበት ፡ ምክንያት ፡ በፍርሀት ፡ ወይም ፡ በድንገተኛ ፡ ድንጋጤ ፤ ወይም ፡ ይቅርታ ፡ ሊያስገኝ ፡ በሚችል ፡ በደም ፡ ፍላት፡ ቍጣ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቅጣቱ ፡ በሙሉ ፡ ነጻ ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ ሊያደርሰው ፡ ይችላል ።

(፫) ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ተገቢ ፡ መከላከል ፡ ሲያደርግ ፡ የመከላከ ሉን ፡ ሁኔታ ፡ ከመጠን ፡ በማሳለፉ ፡ ምክንያት ፡ ስላደረገው ፡ጉዳት ፡ በፍትሐ ብሔር ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፸፮ ። በሁኔታው ፡ ስለ ፡ መሳሳት ።

(፩) አድራጎቱ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለውን ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ በተሳሳተ ፡ መን ገድ ፡ በመገመት ፡ በስሕተት ፡ ስሜት ፡ ተነሣሥቶ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ የሚቀጣው ፡ በዚሁ ፡ በስሕተተኛ ፡ ግምት ፡ በሠራው ፡ ጥፋት ፡ መጠን ፡ ነው ።

ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ አስቦ ፡ ያላደረገው ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ቅጣት ፡ አይደርስበትም ፤ ቢሆንም ፡ የራሱ ፡ የግል ፡ ሁኔታ ፡ የሚያዝዘ

ውን ፡ ተግባራዊ ፡ ግዴታ ፡ በመከተል ፡ ጥንቃቄ ፡ በማድረግ ፡ የነገሩንም ፡ አጋ ጣሚ ፡ ምክንያት ፡ በማመዛዘን ፡ በስሕተት ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ለመሆን ፡ ሲችል ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ * በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ እንዲ ቀጣ ፡ በሕግ ፡ የተመለከተ ፡ ሲሆን ፡ በቸልተኛነት ፡ ይቀጣል ። [ቊ ፡ ፶፱ ።]

(፪) ወንጀል ፡ የሚሆን ፡ ነገርን ፡ በሁኔታ ፡ መሳሳት ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ የፈጸመው ፡ የስሕተት ፡ አድራጎቱ ፡ ሌላ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ አስከትሎ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህኛው ፡ ጉድለቱ ፡ ከቅጣት ፡ አይድንም ።

(፫) በሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ለበደሉ ፡ ምክንያት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተደረ ገው ፡ መሳሳት ፡ ወንጀል ፡ መሆኑን ፡ አያስቀርም ።

ቊ ፡ ፸፯ ። በይመስላል ፡ ብቻ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎም ፡ ቢሆን ፡ የሚያስቀጣ ፡ ጥፋት ፡ በመሳሳት ፡ ያደረገ ፡ ቢመስለው ፡ ማድረጉ ፡ ወይም ፡ አለማድረጉ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሚያ ስቀጣ ፡ ካልሆነ ፡ አይቀጣም ። [ቊ፡ ፪ ፡ (፪) ።]

ቢሆንም ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባው ፡ የመጠበቂያ ፡ ደንብና ፡ በተ ለይም ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ዋስትና ፤ በእጁ ፡ ስለሚገኘው ፡ አደገኛ ፡ ዕቃ ፡ መወረስ ፡ የሚፈጸመው ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ። [ቊ፡፻፴፱ና፡፻፵፩ ።]

ቊ ፡ ፸፰ ። በሕግ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መሳሳትና ፡ ሕግን ፡ ስላለማወቅ ።

(፩) በመደቡ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከጥፋቱ ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ ሕግን፡አለማወቁን ፡ ምክንያት ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

ቢሆንም ፡ በእርግጠኛ ፡ እምነቱ ፡ የሠራው ፡ መስሎትና ፡ ይህን ፡ ያደረገው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መስሎትና ፡ ከመሳሳት ፡ ለመ ድረሱም ፡ በቂና ፡ እርግጠኛ ፡ ምክንያት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣ ቱን ፡ በመሰለው ፡ ያቃልልለታል ። [ቊ ፡ ፻፹፩ ።]

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ የሚወስነው ፡ ከስሕተት ፡ የደረሰበትን ፡ ምክን ያት ፡ በተለይም ፡ የስሕተቱንና ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በመገመት ፡ ነው ።

(፪) የወንጀለኛነቱ ፡ ተግባር ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ያልታየ ፡ ሲሆንና ፡ በቂ ፡ ምክን ያት ፡ ሊገኝበት ፡ በሚችል ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የተደረገ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ ሊያደርሰው ፡ ይችላል ።

(፫) ወንጀለኛው ፡ በፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ስላደረሰው ፡ጉዳት ፡ ካሣ ፡ አከፋፈል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ በአላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ቅጣትን ፡ የሚያቀሉና ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ።

### ቍ ፡ ፸፱ ። ጠቅላላ ፡ የቅጣት ፡ ማቃለያ ፡ ምክንያቶች ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕጉ ፡ ከተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ ሳያልፍ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ቅጣትን ፡ ለማቃለል ፡ የሚችለው ፡— [ቍ ፡ ፻፹፬ ።]

(ሀ) አድራጊው ፡ ወንጀሉን ፡ እስከ ፡ ሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የዘወትር ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ያጠፋውም ፡ በዕውቀቱ ፡ መጕደል ፤ ባለማወቅ ፡ በመንፈስ ፡ ልልነት ፤ ወይም ፡ ባልታሰበና ፡ በድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይኸን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ የተከበረ ፡ ምክንያትን ፡ በመከተል ፤ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባይ ፡ ላለው ፡ ለሃይማኖት ፤ ለሞራልና ፡ ለባህላዊ ፡ እምነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወንጀል ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ የአካል ፡ ወይም ፡ የመንፈስ ፡ ሥቃይ ፡ ደርሶበት ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ የሚያመጣ ፡ ነገር ፡ የተቃጣበት ፡ መስሎት ፡ ወይም ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ፍርሀት ፡ አድሮበት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሊታዘዝለት ፡ የሚገባው ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚተዳደር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) የተበደለው ፡ ሰው ፡ ጠባይ ፡ ከብርቱ ፡ ፈተና ፡ ላይ ፡ ጥሎት ፡ ወይም ፡ ደም ፡ ከሚያፈላ ፡ ንዴት ፡ ወይም ፡ ከሥቃይ ፡ ላይ ፡ አድርሶት ፡ ወይም ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ያደረገው ፡ ጸብ ፡ ቀስቃሽነት ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ በደል ፡ አነሣሥቶት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስገዳጅነት ፡ ያለው ፡ መንፈስን ፡ የሚለውጥ ፡ ስሜት ፡ ወይም ፡ ምክንያት ፡ ባለው ፡ የመንፈስ ፡ ሁከት ፡ ላይ ፡ በመገኘት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) በተለይም ፡ ለተበዳዩ ፡ አስፈላጊውን ፡ እርዳታ ፡ በማድረግ ፡ ጥፋቱን ፡ ዐውቆ ፡ እጁን ፡ ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ በመስጠት ፤ ጥፋቱ ፡ ላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በመካስ ፡ ወንጀሉን ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ ባደረገው ፡ ጥፋት ፡ በእውነት ፡ ተጸጽቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በተለየ ፡ ድንጋጌ ፡ እነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ለሚያደርግለት ፡ ወንጀል ፡ መቋቋሚያ ፤ ወይም ፡ ለቅጣቱ ፡ ማቅለያ ፡ ምክንያቶች ፡ ይሆኑታል ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ የወንጀሉን ፡ ቅጣት ፡ ለማቅለል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ዳግመኛ ፡ ምክንያት ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፹ ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፤ በዝምድና ፡ ወይም ፡ በፍቅር ፡ ወዳጅነት ፡ ስለ ፡ ተሳሰረ ፡ ግንኙነት ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ የተወሰኑትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመጣስ ፡*ጥፋተኛ ፡ የሆነውና ፡ ይልቁንም ፡ ወንጀል ፡ መሥራቱንና ፡ የሠራውን ፡ እያወቀ ፡ ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ማስታወቅ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረው ፡ ወይም ፡ መስጠት ፡ የሚገባውን ፡ የእርዳታ ፡ ተግባር ፡ ያልፈጸመው ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫና ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ምልክት ፡ የሰጠው ፡ ወይም ፡ ሐሰት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ያመለከተው ፡ ወይም ፡ አጥፊው ፡ ከክስ ፡ ወይም ፡ ከቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲያመልጥ ፡ የሸሸገው ፤ ራሱን ፡ እንዳያጋልጥ ፡ ወይም ፡ የሥጋ ፡ ዘመዱን ፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰረ ፡ ወገኑን ፡ በተለይ ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ ወዳጅነት ፡ የተሳሰረውን ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ እንዳይሰጥና ፡ ከወንጀል ፡ ቅጣትና ፡ ከውርደት ፡ ከከባድ ፡ አደጋ ፡ ሊያድነው ፡ በማቀድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመሰለው ፡ ቅጣቱን ፡ ያቀልለታል ። [ቍ ፡* ፮፹፯ ።]

እንዲሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ የቀረቡለትን ፡ የዝምድናና ፡ የፍቅር ፡ ሰፊ ፡ ግንኙነት ፡ በቂ ፡ መሆናቸውን ፡ መመርመርና ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፪) ተከሳሹ ፡ የሚጠየቅበት ፡ ጥፋት ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ያልሆነና ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ በፍቅር ፡ የተሳሰረ ፡ ግንኙነት ፡ እጅግ ፡ ጥብቅ ፡ በመሆኑ ፡ የነገሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስጨንቀው ፡ ስሜት ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊው ፡ ለወደፊቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲያደርግ ፡ በማስጠንቀቅ ፡ በወቀሳ ፡ ብቻ ፡ ሊያሳልፈውና ፡ አስፈላጊም ፡ ከሆነ ፡ ከሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ነጻ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፮፳፩ ።]

(፫) ከባድ ፡ ለሆነ ፡ ወንጀልና ፡ በተለይም ፡ ጠቅላላና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ስለሚያደርስ ፡ ጥፋት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የቅጣት ፡ ማቃለል ፡ ደንብ ፡ የማይጸናበትን ፡ ሁኔታና ፡ ምክንያት ፡ ሕጉ ፡ ባግልጽ ፡ ደንግጎታል ። [ቍ ፡ ፪፻፳፯ ፡ (፩)ና ፡ ፫፻፴፩ ፡ (፫) ። ፮፻፵፯ ፡ (፩) ።]

**ቍ ፡ ፹፩ ። ቅጣትን ፡ ስለሚያከብዱ ፡ ጠቅላላ ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ደንቡ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ቅጣቶችን ፡ ለማክበድ ፡ የሚችለው ፡— [ቍ ፡ ፮፹፰ ።]

(ሀ) አድራጊው ፡ የጥፋቱን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በከሐዲነት ፡ ወይም ፡ በወስላታነት ፤ ወይም ፡ በክፉ ፡ ጠባይና ፡ በመጥፎ ፡ ዐመል ፤ በቂመኛነት ፤

**ቍ ፡ ፹፪ ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥራዎች ፡ መጣመርና ፡ መደጋገም ።**

(፩) ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተለይ ፡ በተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ የወንጀሉ ፡ ቅጣት ፡ የሚከብደው ፡— [ ቍ ፡ ፻፹፱ ፡ እስከ ፡ ፻፺፫ ።]

(ሀ) ወንጀሉ ፡ በተደራረበ ፡ ጊዜ ፡ አድራጊው ፡ አከታትሎ ፡ ብዙ ፡ ወንጀሎችን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወንጀሎቹ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ዐይነቶች ፡ ቢሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ እንደ ፡ አጥፊነቱ ፡ መጠን ፡ ወንጀሉ ፡ በተጣመረ ፡ ጊዜ ፡ ወንጀል ፡ አድራጊው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎቹን ፡ የወንጀል ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የወንጀል ፡ ሥራ ፡ በተደጋገመ ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነለትን ፡ ቅጣት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ከፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ቅጣት ፡ በምሕረት ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ ከተማረበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ አድራጊው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በዚህ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተወሰነውና ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እጅን ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያበቃ ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ወንጀለኛው ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ የወንጀል ፡ ተግባርን ፡ በመደጋገምና ፡ በመደራረብ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ተደራረበው ፡ ወንጀል ፡ ቅጣትን ፡ ይወስናል ፤ ቀጥሎም ፡ ጕዳዩን ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ * የተደጋገመበትን ፡ ሁኔታ ፡ በመገመት ፡ ቅጣትን ፡ ያከብዳል ።

**ቍ ፡ ፹፫ ። ስለ ፡ ሌሎች ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያቶች ።**

ቅጣትን ፡ ለማቅለል ፡ ወይም ፡ ለማከበድ ፡ የሚሆን ፡ በሕግ ፡ በግልጽ ፡ ያልተጻፈ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሲገኝና ፡ ይህንኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀበለው ፡ ሲሆን ፡ ምክንያቱ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተቀበለበትን ፡ አሳብ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ገልጾ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፹፬ ። ቅጣትን ፡ ስለማቃለልና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማከበድ ።**

**አጋጣሚ ፡ በመሆን ፡ የተደራረቡ ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ ጥፋተኛነትን ፡ ለማቃለል ፡ ወይም ፡ ለማከበድ ፡ የሚችሉ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ባጋጠሙት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁለቱን ፡ አስተካክሎ ፡ በማመዛዘን ፡ ቅጣትን ፡ ይወስናል ።

(፪) ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ የሚያቀሉ ፡ ምክንያቶች ፡ በተደራረቡ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስቀድሞ ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ይወስንና ፡ ቀጥሎ ፡ በዚሁ ፡ በሕጋዊው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የማሻሻያ ፡ ደንቦችን ፡ ያጸናል ።

በወራዳነት ፤ አሳቡን ፡ በማነሣሣት ፤ ወይም ፡ በክፉ ፡ ፍላጎትና ፡ ምኞት ፤ መጥፎ ፡ ነገርን ፡ ለመሥራትና ፡ ሰውን ፡ ለመጉዳት ፡ ፍጹም ፡ ፈቃደኛ ፡ በመሆን ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ክፉትና ፡ በጨካኝነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ የችሎታውን ፡ ሥልጣን ፡ ከመጠን ፡ በማሳለፍ ፡ በአኗኗሩ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ በመመካትና ፡ እንዲሁም ፡ በራሱ ፡ በመተማመን ፡ በተሰጠው ፡ በበላይነት ፡ ወይም ፡ በባለሥልጣንነቱ ፡ ተመ ክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ጥፋትን ፡ ሞያ ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፤ የወትሮ ፡ ታሪኩ ፡ በተ ለየ ፡ አደገኛነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የወንጀሉ፡አፈጻጸም ፡ በቦታውና ፡ በጊዜው ፡ ያፈጻጸም ፡ ዘዴዎችን ፡ ይልቁንም ፡ በሌሊት ፡ በመ ሥራት ፡ ሽብርን ፡ ወይም ፡ መዓትን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችንና ፡ ሌሎችንም ፡ አደገኞች ፡ መሣሪያዎችን ፡ በመ ያዝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ጥፋቱን ፡ የፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ ከተባበሩ ፡ ወንበዴዎች ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ ወይም ፡ ሕግን ፡ ለማፍረስ ፡ ከተቋቋሙ ፡ ከወንጀል ፡ ወንበዴዎች ፡ ጋራ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በመሆን ፡ ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ዎች ፤ ሹም ፡ ወይም ፡ አደራጂ ፡ ወይም ፡ መሪ ፡ በመሆን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) በዕድሜው ፤ በጤንነቱ ፤ በኑሮውና ፡ በሥራው ፡ ሁኔታ ፡ ልዩ ፡ የጥበቃ ፡ ድጋፍ ፡ በሚያሻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በተለይም ፡ ለመከላከል ፡ ዐቅም ፡ በሌ ለው ፡ መንፈስ ፡ ደካማ ፡ በሆነ ፡ በበሽተኛ ፡ ወይም ፡ በእስረኛ ፡ ወይም ፡ ወደታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ ወይም ፡ ወደላይ ፡ የሚቈጠር ፡ ወላጅ ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በተቋቋመ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የተወሰነውን፡ሥል ጣን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ ባንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ በሆነ ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ለማድረግ ፡ በማቀድ ፡ ተነሣሥቶ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ ድንጋጌ ፡ እነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ለሚያደርግለት ፡ ወንጀል ፡ መቋቋሚያ ፡ ወይም ፡ የቅጣቱ ፡ ማክበጃ ፡ ምክንያቶች ፡ ይሆኑታል ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ የወንጀሉን ፡ ቅጣት ፡ ለማክበድ ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ዳግመኛ ፡ ምክንያት ፡ ሊያደርገው ፡ አይች ልም ።

**ቍ ፡ ፻፪ ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥራዎች ፡ መጣመርና ፡ መደጋገም ።**

(፩) ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተለይ ፡ በተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ የወንጀሉ ፡ ቅጣት ፡ የሚከብደው ፡— [ ቍ ፡ ፪፻፱ ፡ እስከ ፡ ፪፻፫ ። ]

(ሀ) ወንጀሉ ፡ በተደራረበ ፡ ጊዜ ፡ አድራጊው ፡ አከታትሎ ፡ ብዙ ፡ ወንጀሎ ችን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወንጀሎቹ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ዐይነቶች ፡ ቢሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ እንደ ፡ አጥፊነቱ ፡ መጠን ፡ ወንጀሉ ፡ በተጣመረ ፡ ጊዜ ፡ ወን ጀል ፡ አድራጊው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎቹን ፡ የወንጀል ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ዎች ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የወንጀል ፡ ሥራ ፡ በተደጋገመ ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነለትን ፡ ቅጣት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ከፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ቅጣት ፡ በምሕረት ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ ከተማረበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ አድራጊው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በዚህ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተወሰነውና ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እጅን ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያበቃ ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ወንጀለኛው ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ የወንጀል ፡ ተግባርን ፡ በመደጋገምና ፡ በመደራ ረብ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ተደራረበው ፡ ወንጀል ፡ ቅጣትን ፡ ይወስናል ፤ ቀጥሎም ፡ ጕዳዩን ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የተደጋገመበትን ፡ ሁኔታ ፡ በመገመት ፡ ቅጣትን ፡ ያከብዳል ።

**ቍ ፡ ፻፫ ። ስለ ፡ ሌሎች ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያቶች ።**

ቅጣትን ፡ ለማቅለል ፡ ወይም ፡ ለማክበድ ፡ የሚሆን ፡ በሕግ ፡ በግልጽ ፡ ያልተጻፈ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሲገኝና ፡ ይህንኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀበለው ፡ ሲሆን ፡ ምክንያቱ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተቀበለበትን ፡ አሳብ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ገልጾ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፬ ። ቅጣትን ፡ ስለማቃለልና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማክበድ ።**

**አጋጣሚ ፡ በመሆን ፡ የተደራረቡ ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ ጥፋተኛነትን ፡ ለማቃለል ፡ ወይም ፡ ለማክበድ ፡ የሚችሉ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ባጋጠሙት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁለቱን ፡ አስተካክሎ ፡ በማመዛዘን ፡ ቅጣትን ፡ ይወስናል ።

(፪) ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ የሚያቀሉ ፡ ምክንያቶች ፡ በተደራረቡ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስቀድሞ ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ይወስንና ፡ ቀጥሎ ፡ በዚሁ ፡ በሕጋዊው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የማሻሻያ ፡ ደንቦችን ፡ ያጸናል ።

## ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ወንጀል ፡ የተወሰነ ፡ ቅጣት ፡ በሥራ ፡ እንዲጸና ፡ ስለ ፡ መደረጉ ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ቅጣትና ፡ ስለ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ስለ ፡ አፈጻጸማቸውም ።

#### ቊ ፡ ፹፮ ። መሠረቱ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ውሳኔዎች ፡ በሕጉ ፡ መንፈስና ፡ ሕጉ ፡ ሊደርስበት ፡ ያሰበውን ፡ ዓላማ ፡ ለማረጋገጥ ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ለሰው ፡ ተፈጥሮ ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ አክብሮ ፡ መጠበቅ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።

#### ቊ ፡ ፹፯ ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቶችንና ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ የሚወስነው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በጠቅላላ ፡ ክፍሉና ፡ በልዩ ፡ ክፍሎቹ ፡ የተመለከቱትን ፡ ጥፋቶች፡ እነዚህም ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ቅጣቶች ፡ በመከተል ፡ ነው ።

ቅጣት ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፤ ያጥፊውን ፡ ያደገኛነት ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ በመገመት ፤ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ለማጥፋት ፡ ያነሣሡትን ፡ ምክንያቶችና ፡ ያሳበን ፡ ዓላማ ፤ የግል ፡ ኑሮውን ፡ ሁኔታና ፡ የትምህርቱን ፡ ደረጃ ፤ እንዲሁም ፡ የጥፋቱን ፡ ከባድነትና ፡ ያፈጸጸሙን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመገመት ፡ በራሱ ፡ አጥፊነት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

#### ቊ ፡ ፹፰ ። እጅግ ፡ ቀላል ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ጉዳዮች ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ታስበው ፡ የተደነገጉት ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ በመሆናቸው ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ሁነው ፡ የሚገመቱ ፡ ጥፋቶች ፡ ቢጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ቀላል ፡ ጥፋቶች ፡ ላይ ፡ በወንጀል ፡ ቅጣት ፡ መወሰን ፡ ለእውነተኛ ፡ አስተያየት ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊውን ፡ ለወደፊቱ ፡ ከማስጠንቀቅ ፡ ጋራ ፡ በወቀሳ ፡ ወይም ፡ በተግሣጽ ፡ *ለማሳለፍ ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ በመከተል ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ የተደነገጉትን ፡ ቀላል ፡ ቅጣቶች ፡ በመወሰን ፡ ብቻ ፡ ሊያልፈው ፡ ይችላል ። [ቊ ፡ ፯፻፷፩ ። ]

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ደንበኞች ፡ ቅጣቶች ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ዋና ፡ ቅጣቶች ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### የገንዘብ ፡ ቅጣቶች ።

### ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### መቀጮ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ መውረስና ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።

**ቍ ፡ ፻፹፰ ። መቀጮ ፡ መሠረቱ ።**

በወንጀል ፡ ምክንያት ፡ መቀጮ ፡ የሚከፈለው ፡ በገንዘብ ፡ ነው ። ገቢነቱም ፡ ለመንግሥት ፡ ነው ። ሕጉ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ካልደነገገ ፡ በቀር ፡ መቀጮው ፡ ካንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የመቀጮውን ፡ ልክ ፡ የሚወስነው ፡ የትዳሩን ፡ ሁኔታና ፡ የሀብቱን ፡ ምንጭ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ አስተዳደር ፡ ያለበትን ፡ ሸክም ፡ የሞያ ፡ ሥራውንና ፡ ጥቅሙን ፡ ዕድሜውንና ፡ የጤንነቱን ፡ ሁኔታ ፡ በመገመት ፡ ነው ።

መቀጮውም ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ችግር ፡ በመገመት ፡ በተቻለም ፡ መጠን ፡ ከዐቅሙ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝና ፡ ከፈጸመውም ፡ ጥፋት ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፹፱ ። መቀጮን ፡ ነጻነትን ፡ ከማሳጣት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ መደረብ ።**

የዚህ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ከግል ፡ ነጻነት ፡ የመወሰን ፡ ቅጣትንና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮን ፡ በማረጋገጥ ፡ ደንግጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለወንጀለኛው ፡ ጥፋትና ፡ ለኑሮው ፡ ሁኔታ ፡ የሚበቃ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለቱንም ፡ አጣምሮ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለያንዳንዱ ፡ አጋጣሚ ፡ ጉዳይ ፡ ይህንኑ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ መላልሶ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፺ ። ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ስሜት ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማግኘትና፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ወንጀለኛው ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ የአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ስሜት ፡ አነሣሥቶት ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛነትን ፡ እንደ ፡ ሞያ ፡ ሥራ ፡ በመቍጠር ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ጥቅም ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችልበት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ባጋጠመው ፡ ቍጥር ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተግባሩ ፡ መጠቀምንና ፡ ይህንኑ ፡ እንደ ፡ ጥቅም ፡ ማግኛ ፡ የመደበው ፡ ሆኖ ፡ የኑሮውም ፡ ግዙፍ ፡ ምችትና ፡ በወንጀሉ ፡ ያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ይህንኑ ፡ ተግባሩን ፡ በግልጽ ፡ የሚያሳይ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ቅጣቱን ፡ አሳድጎ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ መደብ ፡ ለማድረስ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

በተለይም ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የቅጣት ፡ መደብ ፡ የሚወስኑት ፡ የልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፤ አድራጊው ፡ በወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ ምክንያት ፡ካገኘው ፡ ጥቅም ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ አይደለም ።

(፪) የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ያነሣሣው ፡ የአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ የአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ መነሾ ፡ የተሠራውን ፡ ውጤት ፡ ያላቋቋመ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥፋት ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ በሚወስኑት ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ያልተመለከተም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚወስንበት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ ከማሳጣት ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ የገንዘብንም ፡ መቀጮ ፡ አጣምሮ ፤ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፺፩ ። የመቀጮ ፡ ገንዘብን ፡ ስለ ፡ ማስገባት ።

(፩) ተቀጪው ፡ የመቀጮውን ፡ ገንዘብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ለገንዘቡ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ቀን ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የተቀጪው ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ ሲሆን ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ መቀጮውን ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እንዲከፍል ፡ ይፈቅድለታል ።

እርግጠኛ ፡ የሆነ ፡ ችሎታውንም ፡ በመገመት ፡ የመክፈያውን ፡ ጊዜያቶችና ፡ የገንዘቡን ፡ ልክ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ። የመጨረሻው ፡ ገንዘብ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፺፪ ። የመቀጮውን ፡ ገንዘብ ፡ በሥራ ፡ ስለ ፡ ማስከፈል ።**

አስፈላጊ ፡ በሆነበትም ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ መቀጮ ፡ የተቀጪው ፡ ሁኔታ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠንና ፡ ጊዜውንም ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ በመስጠት ፡ ለመንግሥት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እየሠራ ፡ በማገልገል ፡ መቀጮውን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲከፍል ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

ለተቀጪውም ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ሊታሰብለት ፡ የሚገባው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ፡ የሚወሰነው ፡ በዘወትር ፡ ሥራው ፡ በቀን ፡ ያገኝ ፡ የነበረውን ፡ መጠነኛ ፡ ሒሳብ ፡ በመገመት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በቀን ፡ ካ፩ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፺፫ ። የግዴታው ፡ ዋስትና ።**

የተወሰነው ፡ መቀጮ ፡ ወዲያው ፡ በማይከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ተቀጪው ፡ የተወሰነበትን ፡ መቀጮ ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመክፈል ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ የሰው ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ መያዣ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

ተቀጪው ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ አሰጣጥ ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚገምተውና ፡ የሚወስነው ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታና ፡ የተቀጪውን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ግምት ፡ የፍትሕንም ፡ ተስማሚነት ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፺፬ ። የመቀጮ ፡ ገንዘብ ፡ ስላለመከፈል ፡ መቀጮውን ፡ ነጻነት ፡ በሚያሳጣ ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ተቀጪው ፡ የመቀጮውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ሳይሆን ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሳይከፍል ፡ በቀረው ፡ የመቀጮ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ሀብቱ ፡ በሕጉ ፡ አገባብ ፡ ይያዝበታል ።

(፪) ተቀጪው ፡ የሚያዝ ፡ ሀብት ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የመቀጮው ፡ አከፋፈል ፡ በሀብቱ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ሲሆን ፡ በኑሮው ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሕይወታዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ጉዳቶች ፡ የሚያስከትልበት ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቀጮው ፡ ወይም ፡ ከመቀጮው ፡ ውስጥ ፡ ያልተከፈለው ፡ ሒሳብ ፡ በእስራት ፡ ተለውጠ ፡ ለመንግሥት ፡ በጉልበት ፡ ማገልገል ፡ እንዲከፍል ፡ ይደረጋል ።

የጠቅላላውን ፡ ኑሮውንና ፡ የተቀጪውን ፡ የግል ፡ ሁኔታ ፡ በተለይም ፡ የዘወትር ፡ ገቢውን ፡ ወይም ፡ የሚያገኘውን ፡ በማሰብ ፡ ላንዱ ፡ የእስራት ፡ ቀን ፡ የሚታሰብለት ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በፍርድ ፡ ይወሰናል ።

በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ መቀጮ ፡ ባለመከፈሉ ፡ ምክንያት ፡ የእስራት ፡

ቅጣት ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራቱ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ለማለፍ፡ አይችልም ።

(፫) ተቀጪው ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ በከፈለ ፡ ጊዜ ፡ ከእስ ራቱ ፡ ይፈታል ።

ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፡ ሲያረጋግጥና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ዋስትና ፡ ሲያቀርብ ፡ ሊፈታ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፺፭ ። ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቆም ።

ቅጣቱ ፡ በተለወጠ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ተቀጪው ፡ የተጣለበትን ፡ መቀጮ ፡ ለመክፈል ፡ ፈቃደኛ ፡ ቢሆን ፤ በድህነቱ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ አስተዳደር ፡ ባለበት ፡ አላፊነት ፡ በጤንነቱ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ለመክ ፈል ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣውን ፡ ቅጣት ፡ አፈጻ ጸም ፡ ለማቆም ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ይቀራሉ ። [ቍ ፡ ፻፺፯ ።]

በዚህ ፡ መካከል ፤ የተቀጪው ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ መሻሻል ፡ ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፡ የሚያስችለው ፡ ሆኖ ፡ እንዲከፍል ፡ ሲጠየቅ ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ የተሰ ጠው ፡ የቅጣት ፡ ማቆም ፡ ትእዛዝ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፺፮ ። መቀጮን ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ተቀጪው ፡ የተወሰነበትን ፡ የመቀጮ ፡ ገንዘብ ፡ ያልከፈለው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቀጮውን ፡ በእስ ራት ፡ በመለወጥ ፡ ፈንታ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባው ፡ የመቀጮ ፡ ገንዘብ ፡ ሒሳብ ፡ እስኪያልቅ ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፪ ፡ ወይም ፡ ፻፫ ።]

ቍ ፡ ፺፯ ። ንብረትን ፡ ስለ ፡ መውረስ ።

(፩) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ታስቦ ፡ የተገለጸ ፡ ውሳኔ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ባለማለፍ ፡ የወንጀለኛው ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲወረስ ፡ ሊፈርድ ፡ ይችላል ።

(፪) በልዩ ፡ ሕግ ፡ በግልጽ ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ የንብረት ፡ መውረስን ፡ ፍርድ፡ ለመስጠት ፡ አይቻልም ።

የንብረትም ፡ መውረስ ፡ ጉዳይ ፤ የተቀጪው ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፤ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በእጅ ፡ አዙር ፤ በወንጀለኛነት ፡ ሥራው ፡ ያፈራውን ፡ ገን ዘብ ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ጠባይና ፡ ተፈጥሮ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ ሀብትና ፡ ከዚህም ፡ ከወንጀል ፡ ሥራው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ የገዛውንና ፡ ያገኘውን ፡ ማናቸ ውንም ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ አጠቃሎ ፡ ሊመለከት ፡ ይችላል ።

BACK



(፫) ውርሱ ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻለው ፡—

(ሀ) ለተቀጪውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ መተዳደሪያ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ፡ ለዘወትር ፡ የቤት ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ቈሳቍሶች ፡ የጥበብ ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሲሆኑ ፤

(ለ) ቢበዛ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታውን ፡ አይቶ ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ለሚገምተው ፡ ምክንያቱ ፡ ለተገለጸና ፡ በቂ ፡ አስተያየት ፡ ሊሰጠው ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ከዚህ ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ለተቀጪው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሕይወትና ፡ ለመተዳደሪያቸው ፡ ፍጹም ፡ አስ ፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የዕለት ፡ ምግብና ፡ ለኑሮዋቸው ፡ መደገፊያ ፡ የሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገቢዎች ፡ ሲሆኑ ፡—

(ሐ) በውርስ ፡ ከዘር ፡ የወረዱ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ዐይነቶች ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፤ ተቀጪው ፡ በስጦታ ፤ በውርስ ፤ በይ ዞታ ፤ በኑዛዜና ፡ በሌላውም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ሊያዝበት ፡ የማይቻል በት ፡ ሀብት ፡ ሆኖ ፡ ለዘር ፡ ትውልድ ፡ የተላለፉ ፡ ንብረቶች ፡ ሲሆኑ ፡—

(መ) ከወንጀሉ ፡ ንጹሓን ፡ የሆኑ ፡ የልጆቹና ፡ የሚስቱ ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ሆኖ ፤ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ወይም ፡ በልማዳዊ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ በባለአ ደራነት ፤ በአስተዳዳሪነት ፤ በሥራ ፡ አስኪያጅነት ፤ በሙሉ ፡ አዛዥነት ፡ ምክንያት ፡ በተቀጪው ፡ ይዞታ ፡ የሚገኙ ፡ ሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፺፰ ። ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ላይ ፡ አድማ ፡ በማድረጉ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ተግባር ፡ በመፈ ጸሙ ፡ ምክንያት ፡ በሌለበት ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚወስንበት ፡ ከማ ንኛውም ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ አጣምሮ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

የንብረት ፡ መያዝ ፡ ፍርድ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፤ በቍጥር ፡ ፺፯ ፡(፫) ፡ የተመለከ ቱት ፡ የአወሳሰን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ወንጀሉ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ሌሎች ፡ የገንዘብ ፡ ውጤቶች ።

ቍ ፡ ፺፱ ። ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ሊሆን ፡ ስለሚገባው ፡ ሀብት ።

(፩) የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለወን ጀል ፡ ሥራ ፡ እንዲነሣሣ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉን ፡ ለመሥራት ፡ እንዲረዳው ፡ ወይም ፡

ወንጀሉን ፡ ለፈጸመበት ፡ ዋጋ ፡ እንዲሆነው ፡ የተሰጠው ፡ የስጦታ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም ፡ ሁሉ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ይሆናል ።

የተባለውም ፡ ንብረት ፡ ዐይነታው ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀባዩ ፡ ዋጋ ውን ፡ ለመንግሥት ፡ ማግባት ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ተላላፊ ፡ በወንጀል ፡ ሥራው ፡ ያገኛቸው ፡ ገን ዘቦችና ፡ ዕቃዎች ፡ ተይዘው ፡ ባለንብረቱ ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በተለመዱት ፡ ደንቦች ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ ባለመብቱ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ጠፉ ፡ ተቈጥሮ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፲ ፱ ። ስለ ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ።

(፩) ወንጀሉ ፡ በተበዳዩ ፡ ወይም ፡ በተበዳዩ ፡ ባለመብቶች ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ባደረሰባቸው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በተለይም ፡ የሞት ፡ አደጋ ፤ ሰውነትን ፡ ወይም ፡ ጤንነትን ፡ የሚያጓድል ፤ ክብርን ፡ የመንካት ፤ ንብረትን ፡ የማፍረስ ፤ ሀብትን ፡ የመጉዳት ፡ አደጋ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በዳዩ ፡ ያደረሰባቸውን ፡ ጉዳት ፡ እንዲክ ሳቸው ፡ ያጠፋውን ፡ ወይም ፡ ያፈረሰውን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲመልስና ፡ እንዲሁም ፡ ለደረሰባቸው ፡ ጉዳት ፡ ተመዛዛኝነት ፡ ያለው ፡ ካሣ ፡ በኪሣራ ፡ ስም ፡ እንዲከፈላቸው ፡ እንዲፈረድበት ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ።

የሆስፒታልና ፡ የመታመሚያ ፡ ወጪ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በመሰከረው ፡ መጠን ፡ እዚሁ ፡ የኪሣራ ፡ ጥያቄ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

(፪) ክስን ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፤ እንዲሁም ፡ የክስ ፡ አሰጣጥ ፡ ሁኔታ ፤ በፍ ትሐ ፡ ብሔር ፡ የሚከፈለው ፡ ኪሣራና ፡ ያመላለሱ ፡ ተገቢነትና ፡ ልክ ፡ በፍ ትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንበኛ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናሉ ።

ነገረተኞቹን ፡ በመስማት ፡ ወይም ፡ ስምምነታቸው ፡ ሕጋዊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተረዳው ፡ መሠረት ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ይወስ ናል ።

አስፈላጊም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈልና ፡ የፈረሰውና ፡ የጠፋው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የመመለሱ ፡ ጉዳይ ፡ ለተቀጪው ፡ ሕይወትና ፡ ኑሮ ፡ ለሞያ ፡ ሥራውም ፡ ማከናወኛ ፡ አስፈላጊ ፡ ካልሆኑት ፡ ሀብቶች ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ በመያዝ ፡ ሊያስከፍል ፡ ይችላል ።

(፫) ተበዳዩና ፡ ስለርሱም ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የጉዳቱን ፡ ኪሣራ ፡ ለማ

ግኘት ፤ ከወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ጋራ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ተጨማሪ ፡ ጠያቂዎች ፤ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

ስለ ፡ አደጋ ፡ ካሣና ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ከወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፤ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ ጉዳይ ፡ ሁኔታ ፡ አሠራርና ፡ ፎርም ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ ተደንግጓል ።

የጉዳዩ ፡ ሁኔታና ፡ የነገሩ ፡ አጋጣሚ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ በተለይም ፡ አስቀ ድሞ ፡ ስለሚደረገው ፡ ደንበኛ ፡ ምርመራ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ምርመራ ፤ አስ ቀድሞ ፡ ግምት ፡ የማድረጉ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያስገድድ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ የሚፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ያጋ ጠመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የወንጀሉ ፡ ክፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የምርመራ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ደንበኛው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ዳኝነት ፡ ክፍል ፡ ሊያስተላልፈው ፡ ይችላል ።

ቍጥር ፡ ፻፩ ። ለተበዳይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ካሣ ።

(፩) ወንጀለኛው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ባለመብቶች ፡ የሆኑት ፡ በኑሮዋቸው ፡ ምክንያት ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ አደጋ ፡ ሊከሱ ፡ የማይችሉ ፡ መሆና ቸው ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፤ ከወንጀለኛው ፡ ላይ ፡ ከተያዘው ፡ ዕቃ ፡ ከሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፤ ወይም ፡ በዋስትናው ፡ መያዣ ፡ ስም ፡ ከአስያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በጉልበት ፡ ሥራው ፡ አገልግሎት ፡ ከሚያገኘው ፡ የደመ ወዝ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከንብረቱ ፡ ውርስ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፤ ለተበ ዳዩ ፡ እንዲከፈል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ባለመብቶቹ ፡ በግልጽ ፡ ካልጠየቁ ፡ በቀር ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚከፈል ፡ የካሣ ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ፤ ልኩም ፡ የሚወሰነው ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ አደጋ ፡ ከባድነት ፡ ተመዛዛኝ ፡ በመሆን ፡ ለተጎጂው ፡ ወይም ፡ ለወገኖቹ ፡ መኖሪያ ፡ አስፈላጊ ፡ በሚሆነው ፡ መጠን ፡ ነው ፤ እጅግም ፡ ቢበዛ ፡ በዳኝነት ፡ ረገድ ፡ ከተገመተው ፡ ወይም ፡ ሁለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ከተስማሙበት ፡ በላይ ፡ እን ዳያልፍ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

(፫) መንግሥት ፡ ለተበዳዩ ፡ በከፈለው ፡ የካሣ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በተበዳዩ ፡ መብት ፡ ተተኪ ፡ ይሆናል ፤ ይኸንንም ፡ ሁኔታው ፡ በሚፈቅድ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳት ፡ ካደረገው ፡ አጥፊ ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ሊጠይቅና ፡ ሊቀበል ፡ ይችላል ።

BACK



## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚቀንሱና ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ።

### ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ የሚያስከፍሉና ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጡ ፡ የተቀላቀሉ ፡ ቅጣቶች ።

**ቍ ፡ ፻፪ ። ከገቢው ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚከፈልለት ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ።**

(፩) ወንጀሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከባድነት ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ የሚያስከትለውም ፡ ቅጣት ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ የማይበልጥ ፡ እስራት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛውም ፡ ሥራ ፡ የሚችል ፡ ( ጤነኛ ) ፡ ሆኖ ፡ አደገኛ ፡ የማይመስል ፡ ሲሆን ፡ የግል ፡ ነጻነቱን ፡ ሳያጣ ፡ በመቈጣጠር ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ ቅጣትን ፡ እንዲፈጽም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ። ግዴታውም ፡ካንድ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ይሆናል ።

(፪) ቅጣቱም ፡ የሚፈጸመው ፡ ተቀጪው ፡ ዘወትር ፡ በሚሠራበት ፡ ቦታና ፡ በሚችለው ፡ ሥራ ፤ ባንድ ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፤ ወይም ፡ ለሕዝባዊ ፡ ጥቅም ፡ በሚ ፈጸም ፡ የሥራ ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

ከተቀጪው ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ፍሬ ፡ ከሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ እስከ ፡ አራት ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ሒሳብ ፡ እየተያዘ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ይደረጋል ።

(፫) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከተቀጪው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ሊያዝ ፡ የሚገባው ፡ የገን ዘብ ፡ ልክ ፡ ሥራው ፡ የሚፈጸምበት ፡ ስፍራና ፡ ቅጣቱ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ የመቈጣጠር ፡ ጥንቃቄ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ይወሰናል።

**ቍ ፡ ፻፫ ። የግል ፡ ነጻነትን ፡ ከመቀነስ ፡ ጋራ ፡ ስለሚወሰን ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ።**

(፩) የነገሩና ፡ የጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ተገቢ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳ ስብ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ በተለይም ፡ ተቀጪው ፤ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ እንዳይገናኝ ፡ ከማናቸውም ፡ ግንኙነትና ፡ ለመጥፎ ፡ ኑሮው ፡ ምቹ ፡ ከሚሆነው ፡ አማካይ ፡ ስፍራ ፡ ለማራቅ ፡ እንዲቻል ፡ የግዴታ ፡ ሥራው ፡ ቅጣት ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ነጻነቱን ፡ ከመቀነስ ፡ ጋራ ፡ ሊፈጸምበት ፡ ይቻላል ።

(፪) ይህንም ፡ የነጻነት ፡ መቀነስ ፡ ቅጣት ፡ ዐይነትና ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ።

ይህም ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ የመፈጸም ፡ ቅጣት ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ሥራ ፡ አሠሪ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የሥራ ፡

ተቋራጭ ፡ ዘንድ ፡ የመቈየትን ፡ ግዴታ ፡ የሚያስከትል ፡ ነው ። ወይም ፡ ከመኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ሳይወጣ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ከሚጠበቅ ፡ ካንድ ፡ ከተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ሳይለይ ፡ የቅጣትን ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

(፫) የተሰጠውን ፡ የግዴታ ፡ ውሳኔ ፡ ጥሶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ በእስራት ፡ ይለወጣል ።

## ቍ ፡ ፻፬ ። ስለ ፡ ድንገተኛ ፡ ሕመም ።

የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የግዴታ ፡ ሥራውን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ የታመመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረውን ፡ የቅጣት ፡ ሥራ ፡ በዳነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈጽም ፡ ይደረጋል ።
የቅጣት ፡ ሥራውንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመቀጠል ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀሪው ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ሊለወጥ ፡ ይችላል ።

## ዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ነጻነትን ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ።

## ቍ ፡ ፻፭ ። ስለ ፡ እስራት ።

(፩) ከባድነቱ ፡ መካከለኛ ፡ የሆነ ፡ ወንጀልን ፡ በሠሩና ፡ ጥፋተኞቹም ፡ እጅግ ፡ አደገኛ ፡ መስለው ፡ ባልታዩ ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰነው ፡ የነጻነት ፡ ማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ እስራት ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ጠቅላላውን ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅና ፡ የተቀጪውንም ፡ ጠባይ ፡ ማረምን ፡ ጒዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

በሕጉ ፡ የተለየ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ አመክሮ ፡ የተደነገገው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ እስራቱ ፡ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ እስራቱ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ።

(፪) ቅጣቱም ፡ የሚፈጸመው ፡ በተለይ ፡ ለዚሁ ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ በተቋቋሙት ፡ እስር ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ ባንዱ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፻፮ ። ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ በሌላ ፡ ስለ ፡ መተካት ።

እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ተመልክቶ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፤ የዚህን ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ ለማስፈጸም ፡ በእስር ፡ ቤቱ ፡ ስፍራ ፡ መጥበብ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡

በሥራው ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ የሚፈጥር ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የተቀጪውንም ፡ ጠባይ ፡ ለማሻሻልና ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ መልሶ ፡ ለማግባት ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ በዚሁ ፡ ለእስራት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ ከመቀነስ ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ በመፈጸም ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ ተከቶ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፪ ። ወይም ፡ ፻፫ ።]

ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጕዳይ ፡ ይህንኑ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ መላልሶ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፻፯ ። ስለ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ።

(፩) የጽኑ ፡ እስራት ፡ (ወይም ፡ የጥብቅ ፡ እስራት) ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ በሠሩኖ ፡ እንዲሁም ፡ በተለይ ፡ አደገኞች ፡ በሆኑት ፡ ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ነው ።

ተቀጪው ፡ እንዲታረምና ፡ የሚቻልም ፡ ቢሆን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲመለስ ፡ ለማድረግ ፡ ሲሆን ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ በተለይ ፡ የመጨቆንና ፡ የመጠበቅ ፡ ግብ ፡ አለው ።

ይህ ፡ ቅጣት ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። በሕጉም ፡ ተገልጾ ፡ የተደነገገ ፡ ሲሆን ፡ ፅዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ። ቢሆንም ፡ ስለ ፡ አመክሮ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፪) የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በተለይ ፡ ለዚሁ ፡ ቅጣት ፡ መፈጸሚያ ፡ እንዲሆኑ ፡ ታስበው ፡ በተሠሩና ፡ ለዚሁ ፡ በተሰናዱ ፡ በዋናዎቹ ፡ ወህኒ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፰ ። የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ የአፈጻጸም ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦች ፡ የሁለቱንም ፡ ዐይነት ፡ የነጻነትን ፡ መቀነስና ፡ የማገድን ፡ ቅጣቶች ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዐት ፡ ደርበው ፡ የያዙ ፡ ናቸው ። የሚመለከቱትም ፡ የቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፡ ውጤት ፡ ሊያስገኝ ፡ የሚችለውን ፡ ግብ ፡ ነው ።

የቅጣቱን ፡ አፈጻጸም ፡ ጠቅላላ ፡ ያስተዳደር ፡ ደንብ ፤ ወደ ፡ እስራት ፡ የማግባትን ፤ የእስረኞችን ፡ መለያየት ፤ ከውጭ ፡ ጐብኙዎች ፡ (ጠያቂዎች) ፡ ጋራ ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ግንኙነት ፤ የውስጣዊውን ፡ ሥርዐትና ፡ የቅጣቱን ፡ አወሳሰን ፤ እንዲሁም ፡ እስረኞች ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚገባቸውን ፡ ትምህርትና ፡ የመንፈሳዊ ፡ እርዳታን ፡ አሰጣጥ ፡ ጕዳይ ፡ የቅጣቶች ፡ አፈጻጸም ፡ ሕግና ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ ለይተው ፡ ይገልጻሉ ።

ቍ ፡ ፶፱ ። በእስር ፡ ቤት ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ ስለ ፡ መለያየትና ፡ በየተወሰኑላቸው ፡ ስፍራ ፡ ነጥሎ ፡ ስለ ፡ ማኖር ።

(፩) ጾታቸው ፡ የተለያየ ፡ ወንጀለኞች ፡ ቅጣታቸውን ፡ የሚፈጽሙት ፡ በተለያየ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ለዚሁም ፡ ጕዳይ ፡ የተለያየ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ያልተዘጋጀ ፡ ሲሆን ፡ በዚያው ፡ ውስጥ ፡ የተለያየ ፡ ክፍል ፡ እንዲኖር ፡ ተደርጎ ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ እንዳይገናኙ ፡ በጥብቅ ፡ ማነጣጠል ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ በጥብቅ ፡ እንዲታሰሩ ፡ ወይም ፡ በወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በልዩ ፡ የቅጣት ፡ ክፍል ፡ ተለይተው ፡ እንዲታሰሩ ፡ የተፈረደባቸው ፡ አደገኞች ፡ ወይም ፡ አዋኪዎች ፡ ወይም ፡ ደጋጋሚ ፡ ወንጀለኞች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ካላደረሱ ፡ ወንጀለኞችና ፡ በመጀመሪያ ፡ ጥፋት ፡ ከተቀጡ ፡ እስረኞች ፡ ጋራ ፡ በፍጹም ፡ እንዳይገናኙ ፡ ይደረጋል ።

(፫) ያልተፈረደባቸው ፡ እስረኞችና ፡ በዕዳ ፡ ምክንያት ፡ የተያዙ ፡ እስረኞች ፡ ከተፈረደባቸው ፡ እስረኞች ፡ ጋራ ፡ አይቀላቀሉም ።

ቍ ፡ ፷ ። ስለ ፡ እስረኛው ፡ የግዴታ ፡ ሥራና ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ዋጋ ።

(፩) በአንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ተቀጪው ፡ በግዴታ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድረግ ፡ ከቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ።

ጤነኛ ፡ የሆነ ፡ ተቀጪ ፡ ከእስር ፡ ቤቱ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የታዘዘውን ፡ ሥራ ፡ መቀበል ፡ አለበት ። ይህም ፡ ሥራ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሁሉ ፡ ከተቀጪው ፡ ችሎታ ፡ ጋራ ፡ የሚስማማና ፡ ጤንነቱን ፡ የማይጐዳ ፡ ጠባይ ፡ ለማረምና ፡ በሥራ ፡ ልማድ ፡ ትምህርትም ፡ አእምሮውን ፡ ለማጐልመስ ፡ የሚረዳው ፡ ሆኖ ፡ ወንጀለኛው ፡ የቅጣቱን ፡ ጊዜ ፡ ሲጨርስ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ተመልሶ ፡ ተፈላጊውን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ለመያዝ ፡ ወደሚያስችለው ፡ ግብ ፡ ሊያደርሰው ፡ የሚችል ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

(፪) ይህን ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ የተገደደ ፡ ማንኛውም ፡ እስረኛ ፡ ሁሉ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ ከሆነና ፡ ጠባዩም ፡ መልካም ፡ ከሆነ ፡ ለሥራ ፡ ችሎታውና ፡ ለሚሰጠውም ፡ አገልግሎት ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ የቀን ፡ የጉልበት ፡ ዋጋ ፡ ይታሰብለታል ።

ሊታሰብለት ፡ የሚገባው ፡ የገንዘብ ፡ ልክና ፡ እንዲሁም ፡ ታስሮ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የገንዘቡ ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ ፤ ከእስራት ፡ ነጻ ፡ በሚለቀቅበት ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ የገንዘብ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥርዐት ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፲፩ ። የተቀጪውን ፡ የእስራቱን ፡ ደረጃ ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።**

ቅጣቱ ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ ያደረሰውን ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ ስሜትና ፡ እስረኛውም ፡ በሚፈታበት ፡ ጊዜ ፡ ደንበኛውን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሕይወት ፡ ለመያዝ ፡ ተገቢ ፡ ለመሆን ፡ መቻሉን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦች ፡ በመከተል ፡ የተቀጪው ፡ የእስር ፡ ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ሁኔታ ፡ በየጊዜው ፡ እየተለዋወጠለት ፡ እንዲሄድ ፡ ይደረጋል ። የዚህም ፡ አፈጻጸም ፤ አሠራርና ፡ ዝርዝር ፡ በቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ሕግና ፡ በእስር ፡ ቤቱ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ይገለጻል ።

(፩) ተቀጪው ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወይም ፡ ቅጣቱን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፤ አስፈላጊና ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ ለማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

የእስር ፡ ቤቱ ፡ የሥራ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቢያስፈልግም ፡ የሕክምናና ፡ የመንፈስ ፡ ጠባይ ፡ ምርመራ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸውን ፡ ሐኪሞች ፡ አሳብ ፡ በመቀበል ፡ ጥንቃቄውንና ፡ የጊዜውን ፡ ልክ ፡ ይወስናል ።

(፪) ዋናው ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸመው ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱና ፡ እንደ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ እንደ ፡ ጊዜውም ፡ ሁኔታ ፡ መጠን ፤ በኅብረት ፡ ወይም ፡ ለብቻ ፡ የሚሠራ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ በመሥራት ፡ ነው ።

ከሥራ ፡ ውጪና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሊት ፡ እስረኛውን ፡ ለብቻው ፡ የመለየት ፡ ጉዳይ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ይከናወናል ።

(፫) እስረኞቹ ፡ ጠባያቸውን ፡ በተሻሻለ ፡ ሁኔታ ፡ በማረማቸውና ፡ የተሻሻሉ ፡ በመሆናቸው ፡ መጠን ፡ ከእስራትም ፡ የመፈታታቸው ፡ ጊዜ ፡ በመቃረቡ ፡ መጠን ፡ የተሻለ ፡ ምግብ ፡ የማግኘት ፤ የጠያቂ ፡ አለመከልከል ፤ የተቃለለ ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፤ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ የመስጠትና ፡ በሌላም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ነገር ፡ የመጠቀም ፡ ሁኔታ ፡ የእስራቱንም ፡ አስተዳደር ፡ የማቃለልና ፡ የማሻሻል ፡ ጥቅም ፡ በእስር ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ሊፈቀድላቸው ፡ ይቻላል ።

ከመጠን ፡ ያለፉ ፡ ወይም ፡ ጠባያቸው ፡ ደስ ፡ ያላሰኘ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተሰጧቸው ፡ ጥቅሞች ፡ ሊቀሩባቸው ፡ ይቻላል ። እንዲሁም ፡ የተቀጪው ፡ የእልከኛነት ፡ ጠባይ ፡ ይህ ፡ እንዲደረግበት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ሲያሳይ ፤ ለተወሰነ ፡ ወይም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ጥቅሞቹን ፡ ለማስቀረት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፻፲፪ ። አስቀድሞ ፡ በአመክሮ ፡ ስለ ፡ መፈታት ።**

(፩) ተቀጪው ፡ ከተወሰነበት ፡ የእስራት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡ ሁለቱን ፡ እጅ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ የተፈ

BACK



ረደበት ፡ ሲሆን ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ የታሰረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተቀጪው ፡ ጠባይና ፡ ሌሎችም ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኙ ፡ ሲሆኑ ፡ ቀዋሚ ፡ ባልሆን ፡ ውሳኔና ፡ በአመክሮ ፡ ስም ፡ ቅጣቱን ፡ በሙሉ ፡ ሳይጨርስ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሊፈታ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፫ ።]

በአመክሮ ፡ ከመለቀቁ ፡ በፊት ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ የቅጣት ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ በማናቸውም ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ እንዲያሳልፍ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) የቅጣቶችን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግና ፡ የእስር ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ደንቦች ፤ የአመክሮውን ፡ አፈጻጸም ፡ አሠራርና ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ ይወስናሉ ።

## ቍ ፡ ፻፲፫ ። ስለ ፡ ወታደር ፡ የእስራት ፡ አስተዳደር ።

ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ በወታደሮች ፡ ላይ ፡ በተወሰነባቸው ፡ ጊዜ ፡ በወታደር ፡ እስር ፡ ቤት ፤ በወታደር ፡ ሰፈር ፤ ወይም ፡ የወታደር ፡ የጦር ፡ ምሽግ ፡ በሚገኝበት ፡ ስፍራ ፤ በወታደር ፡ አስተዳደርና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አፈጻጸም ፡ የተወሰነባቸውን ፡ ቅጣት ፡ የመፈጸም ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ያሠራሩም ፡ አፈጻጸም ፡ በውስጥ ፡ ደንብ ፡ የተወሰነ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፻፲፬ ። ለመጠበቂያ ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መቍጠር ።

ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ፍርድ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡

(፩) የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ ከመወሰኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመጠበቂያ ፡ ተቀጪው ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዋናው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ይቈጥርለታል ።

ቢሆንም ፡ አጥፊው ፡ ወንጀሉን ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ በሚያሳየው ፡ ጠባይ ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ በጥበቃ ፡ እንዲታሰር ፡ ወይም ፡ ይኸው ፡ የእስራቱ ፡ ጊዜ ፡ እንዲረዝምበት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ሳይወሰንበት ፡ ለመጠበቂያ ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ የቈየበት ፡ ጊዜ ፡ አይቈጠርለትም ።

(፪) ለመጠበቂያ ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ የመቈየት ፡ ጉዳይ ፡ ሁኔታ ፤ አሠራርና ፡ አፈጻጸም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ ተደንግጓል ።

## ቍ ፡ ፻፲፭ ። የታመመውን ፡ እስረኛ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማግባትና ፡ የታመመበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መቍጠር ።

(፩) አንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ በመታመሙ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ሕክምና ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ የተዛወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመደቡ ፡ የእስር ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ

BACK



በመታመሚያ ፡ ቦታ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጽመው ፡ ከሚገባው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ያስብለታል ። ቢሆንም ፡ እንዲዛወር ፡ ያስፈለገበት ፡ ከመታሰሩ ፡ በፊት ፡ በደረሰበት ፡ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ የቈየበት ፡ ጊዜ ፡ በቅጣት ፡ ከሚ ፈጽመው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሳይቈጠርለት ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ።

ተቀጪው ፡ በሆስፒታል ፡ ተኝቶ ፡ የመቈየቱን ፡ ወይም ፡ የመታመሙን ፡ ሁኔታ ፡ በማታለል ፡ መንፈስ ፡ ዐውቆ ፡ አምጥቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ያሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጽመው ፡ ከሚገባው ፡ የእስራት ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ አይቀነስለትም ።

(፪) ወንጀለኛው ፡ ቅጣትን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፤ በመላ ፡ መንፈሱ ፡ በበሽታ ፡ የተለከፈ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በሚያደርገውም ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ሊሆን ፡ አለመቻ ሉን ፡ ዐዋቂዎች ፡ ያረጋገጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲቋረጥ ፡ ተደርጎ ፡ ወደ ፡ መታከሚያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ተገቢ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ የማ ስታመሚያ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ ይዛወራል ።

ሕመሙ ፡ የማይድን ፡ ነዋሪ ፡ ሲሆን ፡ ቀሪው ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ አይፈጸም በትም ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

<u>ስለ ፡ ሞት ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ።</u>

<u>ቍ ፡ ፻፲፮ ። መሠረቱ ።</u>

(፩) ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ በሕግ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ተደንግጎ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜና ፡ ለወንጀለኛው ፡ ቅጣትን ፡ የሚያቀልለት ፡ ምክንያት ፡ በታጣ ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊፈረድ ፡ አይቻልም ።

ቅጣቱም ፡ የሚፈጸመው ፡ በመሰቀል ፡ ነው ። ለወታደሮች ፡ ሲሆን ፡ የሞቱ ፡ ፍርድ ፡ በጥይት ፡ እንዲሆን ፡ ሊታዘዝ ፡ ይቻላል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቅጣቱን ፡ አሠራር ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ይወስናል ። ለመቀ ጣጫ ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ የቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ በዐደ ባባይ ፡ እንዲሆን ፡ በግልጽ ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ። በሌላው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚፈጸመው ፡ በወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ነው ።

(፪) የሞት ፡ ፍርድ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ካላጸኑት ፡ በቀር ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ። በምሕረት ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ የተሻረ ፡ ወይም ፡ የተለ

ወጠ ፡ መሆኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ከመመርመሩና ፡ ከመታወቁ ፡ በፊት ፡ ተፈጻሚ ነት ፡ አይኖረውም ።

የሞት ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ሥቃይ ፡ ከባድ ፡ በቀል ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የአካል ፡ ማጉደል ፡ ቅጣት ፡ ሊደርስበት ፡ አይችልም ።

በፍርድ ፡ የተገደለው ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ በቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ጠያቂነት ፡ ተሰ፡ቷ ቸው ፡ በሚገባ ፡ ይቀበራል ።

## ቍ ፡ ፻፲፯ ። ሞት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ እስኪፈጸም ፡ የሚቈይበት ፡ ሁኔታ ።

ሞት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ እስኪጸናና ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ታስሮ ፡ ይቈያል ።

አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ የወህኒ ፡ ቤቱ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ልዩ ፡ የጥንቃቄ ፡ ጥበቃ ፡ ሊያደርግበት ፡ ይችላል ።

እስረኛው ፡ ሲፈልግና ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ በታሰረበት ፡ ቦታ ፡ ተስማሚውን ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ይደረጋል ።

## ቍ ፡ ፻፲፰ ። የሞት ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸም ፡ ስለሚቈይበት ፡ ሁኔታ ።

፲፭ ፡ ዓመት ፡ ባልሞላቸውና ፡ እንዲሁም ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ ሊጠየቁ ፡ አለመ ቻሉ ፡ በታወቀላቸው ፡ ወንጀለኞች ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊፈረድባቸው ፡ አይ ቻልም ።

በጽኑ ፡ በታመሙ ፡ ሰዎችና ፡ ባረገዙ ፡ ሴቶች ፡ ላይ ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እስከ ሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊፈጸምባቸው ፡ አይችልም ። ያረገዘች ፡ ሴት ፡ ስትሆን ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ሲሆንና ፡ እናቲቱ ፡ መመ ገብና ፡ ማሳደግ ፡ ሲኖርባት ፡ ቅጣቱ ፡ በዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ ሊለወጥ ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፻፲፱ ። የሞት ፡ ፍርድን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በምሕረት ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ ሊለወጥ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፪፻፴፱ና ፡ ፪፻፵ ። ]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ።

## ቍ ፡ ፻፳ ። መሠረቱ ።

ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ የሚወሰኑት ፡ ለዋነኛው ፡ ቅጣት ፡ ተደራቢና ፡ ማሟያ ፡ በሚ ሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የቅጣቶችንም ፡ ውሳኔ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በግልጽ ፡ መፍ

BACK



ረድ ፡ አለበት ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ መላልሶ ፡ መግለጽና ፡ አስቀድሞ ፡ ማስታወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ የሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚወስኗቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ሊወሰኑ ፡ ይችላሉ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችን ፡ የሚወስነው ፡ የቅጣቱን ፡ ዓላማና ፡ በተለይም ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ ሊያደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ የጥበቃና ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ ዝንባሌ ፡ በመከተልና ፡ በዚሁ ፡ አሳብ ፡ በመመራት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፹—ሀ—ስለ ፡ ግርፋት ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፴፭ ፡ (፫) እና ፡ በ፯፻፴፯ ፡ (፩) በተመለከተው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚወስንበት ፡ ከዋናው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ አጣምሮ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ፤ የሚገረፍበትንም ፡ ስፍራ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ገልጾ ፡ ያመለክታል ።

(፪) የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከ፲፫ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በሆነ ፡ በወንዶች ፡ ወንጀለኞች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የግርፋቱም ፡ ቍጥር ፡ ከ፳ ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ አጥፊውም ፡ የሚገረፈው ፡ በአለንጋ ፡ ወይም ፡ በጅራፍ ፡ ሆኖ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) አጥፊው ፡ ግርፋትን ፡ የሚችል ፡ ሙሉ ፡ ጤነኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሐኪም ፡ ካልመሰከረ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ ወንጀለኛ ፡ ሊገረፍ ፡ አይችልም ። ሐኪሙ ፡ ግርፋቱ ፡ እንዲቆም ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የተጀመረው ፡ ግርፋት ፡ መቅረት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፹፩ ። በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ማስጠንቀቂያ ፤ ተግሣጽ ፡ ወቀሳ ፡ ጥፋተኛው ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ይቅርታ ።

(፩) የተጠቂውን ፡ ክብር ፡ ጠቅሶ ፡ በማስገንዘብ ፡ በአጥፊው ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ለቅጣቱ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በገመተ ፡ ጊዜ ፡ በችሎትና ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ቍርጠኛ ፡ የሆነ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የመስጠት ፡ የመውቀስና ፡ ወይም ፡ የመገሠጽ ፡ ፍርድ ፡ በግልጽ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ አጥፊው ፡ ስለ ፡ ፈጸመው ፡ የጥፋት ፡ ተግባር ፡ ጥፋቱን ፡ አምኖ ፡ ተበዳዩን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ባለመብቶች ፡ የሆኑትን ፡ በግልጽ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲጠይቅ ፡ ሊያዘው ፡ ይችላል ።

(፪) ጉዳዩ ፡ ቀላል ፡ ሲሆንና ፡ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ይህንኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ባስታወቀ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ቅጣቱን ፡ የሚያቀሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ሲገኙ ፡ *ቅጣቱንም ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ለማቃለል ፡ ሲችል ፡ **ወይም ፡ ቅጣቱ ፡ ከመፈጸሙ ፡ እንዲ

ቈይ ፣ በተደረገ ፣ ጊዜ ፣ ‡ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ለዋናው ፣ ቅጣት ፣ ምትክ ፣ አድርጎ ፣ ይህን ፣ ቅጣት ፣ ለመወሰን ፣ ይችላል ። [ቍ ፣ *፹፱ ። ፺ ። **፻፺፭ ፣ ‡፻፺፯ ።]

## ቍ ፣ ፻፹፪ ። ከመብት ፣ ስለ ፣ መሻር ።

የጥፋቱ ፣ ዐይነትና ፣ ሁኔታ ፣ በቂ ፣ ምክንያት ፣ የሚያስገኝ ፣ ሲሆንና ፣ ወንጀለኛው ፣ የሚገባውን ፣ ባለማድረጉ ፣ የማይገባውን ፣ በማድረጉ ፤ በመብቶቹ ፣ ሊሠራባቸው ፣ ያልተገባ ፣ ሰው ፣ መሆኑ ፣ ሲታወቅ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፦

(ሀ) ከሕዝባዊ ፣ መብቶቹ ፤ ይልቁንም ፣ ከመራጭነት ፣ መብቱ ፤ ባንድ ፣ ምርጫ ፣ ተካፋይ ፣ ከመሆንና ፣ ለሕዝብ ፣ አገልግሎት ፣ ሥራ ፣ ከመመረጥ ፣ ወይም ፣ ለመሾርግ ፣ ከመመረጥ ፤ ለምስክርነት ፣ ከመቈጠር ፤ ወይም ፣ ላንድ ፣ ውል ፣ ወይም ፣ ለስምምነት ፣ ጉዳይ ፣ ለዋስትና ፣ በቂ ፣ ከመሆን ፣ ላንድ ፣ ጉዳይ ፣ መርማሪ ፣ ከመሆን ፣ ወይም ፣ ለፍርድ ፣ ቤት ፣ ነባሪ ፣ ሆኖ ፣ ከመመረጥ ፣ መብት ።

(ለ) በቤተ ፣ ዘመድ ፣ ላይ ፣ ካለው ፣ መብት ፤ ይልቁንም ፣ የአባትነት ፣ ሥልጣንን ፣ ከመያዝ ፣ ችሎታ ፤ ሞግዚት ፣ ወይም ፣ አስተዳዳሪ ፣ (ጠባቂ) ፣ ከመሆን ፣ መብት ።

(ሐ) በባለሥልጣን ፣ ፈቃድ ፣ የሚሰጡትን ፣ የሞያ ፣ ሥራ ፣ ፈቃድ ፣ የእንዱስትሪ ፣ ወይም ፣ የንግድ ፣ ፈቃድ ፣ ከማግኘት ፣ መብት ፤ ሊሽረው ፣ ይችላል ።

## ቍ ፣ ፻፹፫ ። ቅጣቱ ፣ ስለሚቈይበት ፣ ዘመንና ፣ ስለ ፣ አወሳሰኑ ።

(፩) ከመብት ፣ ወይም ፣ ከችሎታ ፤ የመታገድ ፣ ወይም ፣ የመከልከል ፣ ውሳኔዎች ፣ ለጊዜው ፣ ወይም ፣ ለዘወትር ፣ ሊሆኑ ፣ ይችላሉ ፤ ለጊዜው ፣ ብቻ ፣ የሆነ ፣ እንደሆነ ፣ ካንድ ፣ ዓመት ፣ አያንስም ። ካምስት ፣ ዓመት ፣ አይበልጥም ። [ቍ ፣ ፻፹፪ ።]

አጥፊው ፣ የፈጸመውን ፣ የወንጀል ፣ ከባድነት ፤ ያለፈ ፣ የሕይወት ፣ ታሪኩን ፣ የጠባዩን ፣ አደገኛነት ፣ ወይም ፣ መጥፎነት ፣ የተደጋገመ ፣ ወንጀል ፣ ለመሥራት ፣ አሥጊ ፣ መሆን ፣ አለመሆኑን ፤ የውሳኔውን ፣ ተፈላጊነትና ፣ ጠቃሚነት ፣ ወይም ፣ ውሳኔው ፣ በተቀጪው ፣ ላይ ፣ ሊያደርስ ፣ የሚችለውን ፣ ውጤት ፣ እንዲሁም ፣ ማኅበራዊውን ፣ ኑሮ ፣ ለመጠበቅ ፣ አስፈላጊ ፣ የሆነውን ፣ በመገመትና ፣ መሠረት ፣ አድርጎ ፣ በመያዝ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በያንዳንዱ ፣ አጋጣሚ ፣ ሁኔታ ፣ መጠን ፣ ይህ ፣ ቅጣት ፣ የሚቈይበትን ፣ ጊዜ ፣ ይወስናል ።

(፪) የሞት ፣ ወይም ፣ የጽኑ ፣ እስራት ፣ ቅጣት ፣ ፍርድ ፣ ከሕዝባዊ ፣ መብት ፣ የመሻርን ፣ የመሠረዝን ፣ ጉዳይ ፣ በግድ ፣ ማስከተል ፣ አለበት ። ይህም ፣ የሚቈይበትን ፣ ጊዜ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ይወስናል ። የሞት ፣ ፍርድ ፣ ቅጣት ፤ ወይም ፣ የዕድሜ ፣ ልክ ፣ እስራት ፣ በተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ የምሕረት ፣ ማግኘት ፣ መብትና ፣ ከቍጥር ፣

BACK



፻፺፪ ፡ እስከ ፡ ፻፺፯ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የመሻሩ ፡ ጒዳይ ፡ ለዘወትር ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪፻፩ ። የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ስለሚያገኘው ፡ ውጤት ።

(፩) መብትን ፡ መሻር ፤ ማሳጣት ፡ መቀነስ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነታቸውን ፡ የሚያገኙት ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

እንዲህ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ለመከልከል ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠው ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተፈጻሚነቱ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ ተቀጪው ፡ ዋናውን ፡ ቅጣት ፡ ከፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ቅጣቱን ፡ ከተማረበት ፡ ወይም ፡ በይርጋ ፡ ዘመን ፡ ቅጣቱ ፡ ከቀረለት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፪) በወንጀለኛው ፡ ላይ ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበት ፡ ለአመክሮ ፡ ተለቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ አመክሮ ፡ ለጊዜው ፡ ተፈትቶ ፡ በቈየበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ አሳይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሥልጣን ፡ የመሻር ፡ ወይም ፡ ከማናቸውም ፡ መብት ፡ የመሠረዝ ፡ ወይም ፡ የመሻር ፡ ውሳኔ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የሚታሰበው ፡ ለጊዜው ፡ ከእስራቱ ፡ ከተፈታበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ወንጀለኛው ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ ከመሥራት ፡ መብት ፡ ታግዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ * ስለ ፡ አመክሮ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲፈታ ፡ ሲደረግ ፤ ለፈተና ፡ ያህል ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ እንዲቀጥል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ። ‡ [ቊ ፡ * ፪፻፪ ፡ (ሐ) ። ‡ ፻፺፲ ።]

ቊ ፡ ፪፻፪ ። መብትንና ፡ ክብርን ፡ ስለ ፡ መመለስና ፡ ስለ ፡ መሰየም ።

እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በቅጣት ፡ ተሠርዞ ፡ የነበረውን ፡ ማናቸውም ፡ መብት ፡ አጥፊው ፡ በወንጀል ፡ ሥራው ፡ ከመቀጣቱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ሁኔታ ፡ ሊመለስለትና ፡ ሊሰየም ፡ ይችላል ። [ቊ ፡ ፻፺፪ ፡ እስከ ፡ ፻፺፯ ።]

ቊ ፡ ፪፻፫ ። ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ስለ ፡ ማስወገድና ፡ ማዕርግን ፡ ስለ ፡ መግፈፍ ።

(፩) በወታደራዊ ፡ ጒዳይ ፡ ሲሆን ፡ አጥፊው ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚፈርድበት ፡ ከዋነኛው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባነት ፡ የመወገድን ፡ ወይም ፡ ከማዕርግ ፡ የመገፈፍን ፡ ቅጣት ፡ ይፈርድበታል ።

(፪) እነዚህም ፡ ቅጣቶች ፡ የሚወሰኑት ፡ ከክፍሉ ፡ የጦር ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋራ ፡ አስቀድሞ ፡ በመመካከርና ፡ የሚሰጠውንም ፡ ተቀዳሚ ፡ አሳብ ፡ በመረዳት ፡ ነው ።

BACK



እነዚህም ፡ ቅጣቶች ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተመለከቱት ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ የአፈጻጸማቸው ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ ሳይነኩ ፡ ሊወሰኑ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፯፻፯ ። ውሳኔው ፡ ስለሚያስገኘው ፡ ውጤት ።

ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረብነት ፡ የመወገድና ፡ የማዕርግ ፡ መገፈፍ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ የሚጸናውና ፡ ፍርዱ ፡ የሚፈጸመው ፡ በወታደር ፡ አስተዳደር ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በተለይ ፡ ሁኔታ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱ ፡

ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ጥንቃቄ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ደጋግመው ፡ ወንጀልን ፡ በሚሠሩና ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡

አድርገው ፡ በያዙ ፡ ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ጥንቃቄ ።

ቍ ፡ ፯፻፰ ። ጽኑ ፡ ግዞት ።

(፩) አንድ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ የተደጋገመ ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበት ፡ ቅጣቱን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ የአመለኛነት ፡ ዝንባሌ ፡ ስላለው ፡ ጠባዩን ፡ ባለማረም ፡ በሥራ ፡ ፈትነትና ፡ ባልተገባ ፡ ሁኔታ ፡ በመኖር ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ መሥራትን ፡ እንደ ፡ ሞያ ፡ ሥራው ፡ በማድረግ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተደጋገመ ፡ ወንጀል ፡ በሚሠሩት ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመውን ፡ የቅጣት ፡ ማክበድ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ አዲስ ፡ ለሠራው ፡ ጥፋት ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ቅጣት ፡ ይወስንበታል ።

(፪) ቢሆንም ፤ የተደጋገመ ፡ ቅጣት ፡ ተወስኖበት ፡ ቢፈጸምም ፡ ቅጣቱ ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ ያላስገኘ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተገነዘበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አዲስ ፡ የሠራው ፡ ጥፋት ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ባይገኝና ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ከሠራቸው ፡ ጥፋቶች ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይነትና ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ባይኖራቸውም ፡ እንኳ ፡ የቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ጽኑ ፡ ግዞት ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ በመኖር ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፱ ። የግዞቱ ፡ አፈጻጸም ።

(፩) ጽኑ ፡ ግዞት ፡ የሚፈጸመው ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተዘጋጀው ፡ ባንድ ፡ የግዞት ፡ ስፍራ ፤ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ መፈጸሚያ ፡ እንዲሆን ፡ በተዘጋጀ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተግዞ ፡ በመኖር ፡ ነው ። የተፈረደበት ፡ ግዞተኛ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

BACK



(፪) የተወሰነው ፡ የግዞት ፡ መፈጸሚያ ፡ ስፍራ ፡ አስተዳደር ፤ በተቀጪዎቹ ፡ ላይ ፡ የቅጣቱን ፡ አፈጻጸም ፡ ማጥበቅና ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ መቈጣጠርን ፡ የሚፈጽምባቸው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በጠቅላላው ፡ ከሌሎቹ ፡ የቅጣት ፡ መፈጸሚያ ፡ እስር ፡ ቤቶች ፡ ያስተዳደር ፡ ደንብ ፡ *ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። [ቍ ፡ *፪፻፱ ፤ እስከ ፡ ፪፻፲፩ ።]

ያስተዳደሩም ፡ ዝርዝር ፡ ደንብ ፡ በወህኒ ፡ ቤቶች ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፪፻፴ ። የግዞቱ ፡ ዘመን ።

(፩) በአመክሮ ፡ የመፈታት ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በግዞት ፡ የመኖር ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ ከሁለት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ። የዘመኑም ፡ ወሰን ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ አይገለጽም ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተወስኖ ፡ እንዲኖር ፡ የተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ የጥንቃቄና ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅን ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመጠበቂያ ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ የቈየበት ፡ ጊዜ ፡ አይታሰብለትም ። [ቍ ፡ ፪፻፲፬ ።]

(፪) ተቀጪው ፡ በግዞት ፡ እንዲቀመጥ ፡ ከተወሰነበት ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የክፍሉን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ አሳብ ፡ ተቀብሎ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፲፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በአመክሮ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፴፩ ። በገደብ ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።

(፩) የፈተናው ፡ ጊዜም ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ያነሰ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ለጊዜው ፡ ነጻ ፡ ለተለቀቀው ፡ ጥፋተኛ ፡ ሊከተል ፡ የሚገባውን ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ የጠባይ ፡ ማሻሻል ፡ ሥርዐት ፡ ሊወስንለትና ፡ ባንድ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እንዲኖር ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፪፻፲፫ ።]

(፪) ተፈቺው ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በመልካም ፡ ጠባይ ፡ የተመራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መለቀቁ ፡ ለመጨረሻ ፡ ይሆናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ያላሳየ ፡ እንደሆነና ፡ በሕጉ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ *የአመክሮ ፡ መስጠትን ፡ ከሚያስቀሩ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተለቀቀው ፡ እስረኛ ፡ ወደ ፡ ግዞቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ያዛል ። [ቍ ፡ ፪፻፲፩ ።]

በዚህ ፡ በግዞት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አመክሮ ፡ ከመፈቀዱ ፡ በፊት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ መቈየት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፴፪ ። መፈጸም ፡ ስለማይቻልበት ፡ ሁኔታ ።

ጥፋተኛው ፡ ከተፈረደበት ፡ ጀምሮ ፡ ግዞቱን ፡ ሳይፈጽም ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡

BACK



እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቅጣቱ ፡ ወይም ፡ ከግዞቱ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባውን ፡ አንደኛውን ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

ቅጣቱ ፡ በይርጋ ፡ ዘመን ፡ ተሠርዞለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግዞቱ ፡ በተቀጪው ፡ ላይ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## አላፊነት ፡ በሌላቸውና ፡ አላፊነታቸው ፡ በተቀነሰ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥንቃቄ ።

### ቍ ፡ ፻፴፫ ። መሠረቱ ።

ደንበኛውን ፡ ምርመራና ፡ ልዩ ፡ ምርመራ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ *አድራጊው ፡ በሕጉ ፡ ስሜት ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ አላፊነት ፡ የሌለው ፡ **ወይም ፡ አላፊነቱ ፡ የተቀነሰ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ፡ ፤ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አኳኋንና ፡ እንደ፡ ሌላው ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይወስናል ። [ቍ ፡ *፶፩ ። **፵፰ ። ፵፱ ።]

### ቍ ፡ ፻፴፬ ። የጥንቃቄ ፡ ግዞት ።

(፩) የአድራጊው ፡ ሁኔታ ፡ በጸጥታ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ ሁከትን ፡ የሚያደርስ ፡ መስሎ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በአካባቢው ፡ ላይ ፡ አደገኛ ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ በክልል ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ በመታከሚያ ፡ ቤት ፡ ተወስኖ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያዝዛል ።

(፪) በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ አድራጊው ፡ ሕክምና ፡ የሚያስፈልገው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅና ፡ ሕክምናውን ፡ በዚያው ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ መስጠት ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ እዚያው ፡ ሆኖ ፡ እንዲታከም ፡ ወይም ፡ የማይቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አጠባበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የማረጋገጫ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ በቍጥር ፡ ፻፴፭ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ በተገቢ ፡ ስፍራ ፡ እንዲታከም ፡ ለማዛወር ፡ ይቻላል ።

### ቍ ፡ ፻፴፭ ። ስለ ፡ ሕክምናው ።

(፩) አድራጊው ፡ በበሽታ ፡ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ ጕድለት ፡ የተነካ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ድዳ ፡ ደንቆሮ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ኤፒሌፕሲ ፡ (የሚጥል ፡ በሽታ) ፡ አድሮበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመጠጥ ፡ በመመረዝ ፡ ነዋሪ ፡ በሽታ ፡ አድሮበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ዕፀዋትን ፡ በማብዛት ፡ የተመረዘ ፡

BACK



እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ በማናቸውም ፡ በሽታ ፡ የተነካ ፡ ሆኖ ፡ በሆስፒታል ፡ ወይም ፡ ለጤና ፡ ጥበቃ ፡ በተቋቋመ ፡ መታከሚያ ፡ ቤት ፡ እንዲታከም ፡ ወይም ፡ እዚያ ፡ እንዲቀመጥ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ወንጀለኛ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ደንበኛ ፡ በሆነ ፡ ክፍል ፡ ገብቶ ፡ እንዲታከም ፡ ያዛል ።

(፪) ልዩ ፡ መርማሪው ፡ እንዳቀረበው ፡ አሳብ ፡ ወንጀለኛው ፡ አደገኛ ፡ እንዳልሆነና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሆስፒታል ፡ መታከሙ ፡ አስፈላጊ ፡ አለመሆኑ ፡ በተለይ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተመላላሽነት ፡ ብቻ ፡ እንዲታከም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ ጥንቃቄ ፡ ዳኛው ፡ በየጊዜው ፡ ራፖር ፡ ሊጠየቅ ፡ በሚችለው ፡ ሰዎችን ፡ በሚያከመው ፡ ሐኪም ፡ ወይም ፡ የጥበቃ ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጣቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ባልደረቦች ፡ ጥበቃ ፡ መቈጣጠር ፡ ውስጥ ፡ ነው ። አጠባበቁም ፡ የተረጋገጠ ፡ ካልሆነና ፤ መልካም ፡ ውጤት ፡ የማያስገኝ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሚሻር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፴፮ ። ስለ ፡ አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ፤ ውሳኔው ፡ ስለሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) አድራጊው ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ እንዲገባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ የሚፈጽመው ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ነው ።

ጥንቃቄውም ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ መጠን ፡ ነው ። በመደቡ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ ውሳኔ ፡ ሳያደርግ ፡ ጥንቃቄው ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ይበልጥ ፡ ሊቈይ ፡ አይችልም ።

ውሳኔ ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ መጥፋቱን ፡ ልዩ ፡ መርማሪው ፡ ባረጋገጠ ፡ ጊዜ ፡ ያስተዳደሩ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካመለከተና ፡ ትእዛዝ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ታዞ ፡ የነበረውን ፡ የጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፡ ያስቀርለታል ።

(፪) ጥንቃቄው ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ጥንቃቄው ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ በመላው ፡ ያልጠፋ ፡ ሆኖ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ ለአመክሮ ፡ ያህል ፡ በነጻ ፡ ሊለቀቅ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂው ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጒዳዩን ፡ የሚመለከተው ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ያቀረበለትን ፡ ራፖር ፡ በመከተል ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የታዘዘውን ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸም ፡ ወይም ፡ በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ የመታከሙ ፡ ጒዳይ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲቋረጥ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ተለቃቂ ፡ የጠባቂነት ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ባንድ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሥልጣን ፡ (ባልደረባ) ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ ጊዜ ፡ እንዲጠበቅና ፡ አስፈላጊው ፡ መቈጣጠር ፡ እንዲደረግበት ፤ ማስገደድና ፡ ጠባዩንም ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ መምራት ፡ እንደሚገባ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። [ ቍ ፡ ፪፻፲ ። ]

(፫) ጠቅላላውን ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ወይም ፡ የተለቃቂውን ፡ የጤንነት ፡ ሁኔታ ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊው ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ተመልሶ ፡ እንዲገባ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ የጥንቃቄ ፡ መፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ይቀርለታል ። እንዲሁም ፡ ባንድ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሥልጣን ፡ (ባልደረባ) ፡ ጥበቃ ፡ የመኖሩ ፡ ወይም ፡ የመጠበቁና ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ አመራር ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ይሠረዝለታል ።

ቍ ፡ ፪፺፯ ። በቅጣቱና ፡ በተቀነሰው ፡ አላፊነት ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

(፩) የተቀነሰ ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ አጥፊው ፡ ሲሆን ፡ በመደቡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመሰለው ፡ ሊያቀል ፡ የሚችለውን ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ ይፈርዳል ። [ቍ፡፺፱።]

ባለፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ በበደለኛው ፡ ላይ ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅ ፡ ወይም ፡ የመታከም ፡ ሥርዐት ፡ እንዲፈጸምበት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ለጊዜው ፡ አግዶ ፡ ለጥንቃቄ ፡ መፈጸሚያ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ እንዲቈይ ፡ ወይም ፡ ሆስፒታል ፡ እንዲገባ ፡ ያዛል ።

(፪) ለጥንቃቄ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ የክፍሉ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅና ፡ የመጠበቅ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ባለሥልጣን ፡ (ባልደረባ) ፡ ያቀረቡት ፡ ራፖር ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ ቅጣት ፡ አሁንም ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አጥፊው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ለጥንቃቄ ፡ መፈጸም ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ የቈየበት ፤ ወይም ፡ በሕክምና ፡ ያሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ሊፈጸምበት ፡ ከሚገባው ፡ ለጊዜው ፡ ታግዶለት ፡ ከነበረው ፡ ቅጣት ፡ ላይ ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ ታስቦ ፡ ሊቀነስለት ፡ እንደሚገባው ፡ ይወስናል ።

ይህንንም ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ የሚከተለው ፡ አድራጊው ፡ የፈጸመውን ፡ የወንጀል ፡ ከባድነት ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩንና ፡ የጠባዩን ፡ ሁኔታ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጽም ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ የመቈየቱ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የተደረገለት ፡ ሕክምና ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ስሜት ፡ እንዳደረሰበት ፡ እንዲሁም ፡ አጥፊው ፡ ለወደፊቱ ፡ ጠባዩን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ ሰላማዊ ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ የሚሰጠውን ፡ ዋስትና ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

(፫) የቅጣቱ ፡ መፈጸም ፡ ከመጥቀሙ ፡ ይልቅ ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑ ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቅጣቱን ፡ መፈጸም ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ጥንቃቄና ፡ ስለ ፡ አጠባበቅ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።

### ቍ ፡ ፻፴፰ ። መሠረቱ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ታስበው ፡ የተመለከቱት ፡ የጥንቃቄና ፡ የአጠባበቅ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ጠቃሚና ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ከዋናው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ በመሆን ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ በመጣመር ፡ ሊወሰኑ ፡ ይችላሉ ።

የዚህ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ነገሩ ፡ ባጋጠመው ፡ ቍጥር ፡ እየመላለሰ ፡ ሳይገልጸው ፡ ቢቀር ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ለመወሰን ፡ ተገቢ ፡ የሆኑት ፡ የፍትሕ ፡ ጕዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ተሟልተው ፡ መፈጸማቸው ፡ ከታወቀ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ውሳኔዎች ።

### ቍ ፡ ፻፴፱ ። የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ዋስ ። መሠረቱ ።

(፩) የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ ማሰቡን ፡ ሲገልጽ ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ እንደሚሠራም ፡ በእርግጥ ፡ የሚያሠጋ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በተለይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስበው ፡ በተገለጸ ፡ ጠላትነት ፡ ወይም ፡ በዛቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ወንጀለኛ ፡ በመልካም ፡ ጠባይ ፡ እንዲመራ ፡ ማረጋገጫ ፡ ቃል ፡ እንዲገባና ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ዋስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ የግዴታ ፡ ቃል ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

የማረጋገጫውም ፡ ግዴታ ፡ የሚሰጠው ፡ በመያዣ ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ዋስትና ፡ ነው ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቃል ፡ መግባቱን ፡ ጊዜና ፡ ለመያዝ ፡ የሚገባውንም ፡ የጥንቃቄ ፡ ከፍተኛነት ፡ የሚወስነው ፡ የዛቻውን ፡ ዐይነት ፡ ከባድነትና ፡ አደገኛነቱን ፡ እንዲሁም ፡ የአድራጊውን ፡ ወይም ፡ የዋሶቹን ፡ የግል ፡ ኑሮ ፡ ደረጃና ፡ የሀብት ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ነው ።

ለማረጋገጫው ፡ የገባበት ፡ ቃልና ፡ የተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ይጻፋል ።

ቍ ፡ ፻፶ ። ቃል ፡ መግባትን ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ መስጠትን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ።

(፩) ወንጀል ፡ ይሠራል ፡ ተብሎ ፡ አሥጊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ እንዲሰጥ ፡ የተጠየቀውን ፡ የማረጋገጫ ፡ ግዴታ ፡ ለመስጠት ፡ ያልፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመጥፎ ፡ አሳብና ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ላይ ፡ በመመሥረት ፡ ዋስ ፡ ያላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊውን ፡ የማረጋገጫ ፡ መያዣ ፡ ያላስቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተለመደው ፡ የፖሊስ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ እንዲቈይ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

(፪) ወዲያውም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ጥፋተኛ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ። አጥፊው ፡ ዛቻውን ፡ በመደጋገም ፡ ካላደሰና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጠባዩንም ፡ የማያሻሽል ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ መጥፎ ፡ አሳቡን ፡ ካልቀጠለና ፡ ይህንንም ፡ የመሳሰለ ፡ ልዩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ካላደረሰ ፡ በቀር ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ይበልጥ ፡ የተራዘመ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

በቂ ፡ ለሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ የጊዜውን ፡ ውሳኔ ፡ እንዲያራዝም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ መጠየቅ ፡ ይቻላል ። በእንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ጊዜ ፡ ተቀጪው ፡ በዐይነ ፡ ቍራኛ ፡ እየተጠበቀ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲፈታ ፡* ወይም ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቁን ፡ ጕዳይ ፡ ማጠንከር ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ሲታየው ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የእስራቱ ፡ ውሳኔ ፡ ታድሶ ፡ እንዲፈጸም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ የመታደሱ ፡ ጊዜ ፡ በድምሩ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ሊያልፍ ፡ አይችልም ። [ቍ ፡* ፻፶፪ ።]

(፫) በዚሁ ፡ መካከል ፡ ጥፋተኛው ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ማረጋገጫ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይለቀቃል ።

ቍ ፡ ፻፶፩ ። የውሳኔው ፡ ውጤት ።

ለፈተናው ፡ በተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ጥፋተኛው ፡ ወንጀሉን ፡ ሳይሠራ ፡ ያሳለፈ ፤ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገባበት ፡ የማረጋገጫው ፡ ቃል ፡ ይቀርለታል ፤ የዋሶችም ፡ ዋስትና ፡ ይወርድላቸዋል ። ስለ ፡ ዋስትና ፡ ያስቀመጠው ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ይመለስለታል ። ወንጀሉ ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ የዋስትናው ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ዋሱ ፡ ይገደዳል ፤ ቢሆንም ፡ የሠራው ፡ ጥፋት ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ደንበኞቹ ፡ ቅጣቶችና ፡ ጥንቃቄዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፶፪ ። ዋስ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ለመስጠት ፡ ስላለመቻል ።

ወንጀል ፡ ይሠራል ፡ ተብሎ ፡ አሥጊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ለመታመኛ ፡ እንዲያሲዝ ፡ የሚ

ጠየቀውን ፡ የገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ ዋስ ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሆኖ ፡ በማጣት ፡ ብቻ ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንጀለኛው ፡ ነጻ ፡ ሆኖ ፡ እን ዲጠበቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ። [ቍ ፡ ፻፺፪ ።]

ቍ ፡ ፻፹፫ ። የጥንቃቄውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለ ፡ መደጋገም ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በአካባቢዎች ፡ ሁኔታ ዎች ፡ በተለይም ፡ በአዲስ ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ በአዲስ ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ የተገባ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ሰውዬው ፡ እንደገና ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አይታገድም ።

(፪) ስለሆነም ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነውን ፡ በቍጥር ፡ ፻፹ ፡ (፪) የተመለከተውን ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነውን ፡ የ፮ ፡ ወር ፡ የመገደጃ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ የፈጸመ ፡ ሲሆን ፡ ለወደፊቱ ፡ ቃል ፡ እንዲገባ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ተጠ ይቆ ፡ በመጥፎ ፡ አሳብ ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲታሰር ፡ ሳይደረግ ፡ በተ ጠባባቂ ፡* ውስጥ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡* ፻፺፱ ።]

ቍ ፡ ፻፹፬ ። አደገኞች ፡ የሆኑ ፡ ዕቃዎችንና ፡ መሣሪያዎችን ፡ ስለ ፡ መውረስ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ ሊያገለግሉ ፡ የሚችሉት ፡ ወይም ፡ ለወ ንጀል ፡ ሥራ ፡ ያገለገሉት ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ፍሬ ፡ የሆኑት ፡ ማንኛዎ ቹም ፡ መሣሪያዎችና ፡ ዕቃዎች ፡ የሕዝብን ፡ ሰላማዊ ፡ የኑሮ ፡ ጸጥታ ፡ የሰላማ ዊውን ፡ ደንበኛ ፡ የኑሮ ፡ ጸጥታ ፡ ጤናን ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ሊጎዱ ፡ የሚችሉ ፡ ሲሆኑ ፡ እንዲወረሱ ፡ ይፈርዳል ።

የተወረሱት ፡ ዕቃዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ እንዲጠፉ ፤ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆኑ ፤ ወይም ፡ ለምሳሌ ፤ ለፖሊስ ፡ ወይም ፡ ለወንጀል ፡ ምርመራ ፡ ክፍል ፡ እንዲሰጡ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ስሜት ፤ ወደ ፡ አደጋ ፡ የማያደርሱ ፡ መሆና ቸው ፡ በተገለጸና ፡ በዐይነታቸውም ፡ ምክንያት ፡ የተከለከሉ ፡ ባልሆኑት ፡ ዕቃ ዎች ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያዎች ፡ ላይ ፡ ለወንጀሉ ፡ ባዕድ ፡ የሆኑት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በተለይም ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የተታለለው ፡ የዕቃው ፡ ባለሀብት ፡ ከእነርሱ ፡ በተውሶ ፡ በተወሰዱት ፡ ወይም ፡ በተሠረቁት ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፹፭ ። አጠቃላይ ፡ ድንጋጌ ፤ ለጥንቃቄ ፡ የሚደረግ ፡ ጠቅላላ ፡ አፈጻጸም ።

(፩) ፍርድ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ የቀረበበት ፡ ክስ ፡ በፍርድ ፡ በመመር መር ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜም ፡ ቢሆንና ፡ በኅብረታዊ ፡ ወይም ፡ በግል ፡ የሰ ላም ፡ አኗኗር ፤ ወይም ፡ በጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ ዛቻ ፡ ባደ

ረገ ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጥያቄ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ አስቀድሞ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ፡ ደንብ ፡ ሊጸናበት ፡ ይችላል።

እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ አደገኛ ፡ የሆኑት ፡ ዕቃዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊከሰስ ፡ ወይም ፡ ሊፈረድበት ፡ ባይቻልም ፡ እንኳ ፡ እንዲወርስ ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ጥንቃቄ ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ባለሥልጣን ፡ በሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አመራር ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ይገለጻል።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ሥራን ፡ ስለ ፡ ማገድ ፡ የሚደረግ ፡ ውሳኔ ።

### ቍ ፡ ፻፳፪ ። ፈቃድን ፡ ስለ ፡ ማገድና ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።

ተሽከርካሪ ፡ መኪና ፡ ለመንዳትም ፡ ሆነ ፡ በመኪናው ፡ ለመዘዋወር ፡ ለማደን ፡ ወይም ፡ ዓሣ ፡ ለማጥመድ ፡ በቲያትር ፡ በዳንስ ፡ በምግብ ፡ መስጫ ፡ ቤትና ፡ ስፍራ ፡ እየነገደ ፡ በፍሬው ፡ እንዲጠቀም ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ንግድና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ እንዲጠቀም ፡ በግልጽ ፡ በተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ የሚጠቀም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስ ፡ ወይም ፡ የተደጋገመ ፡ ከፍተኛ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዋነኛው ፡ ወንጀሉ ፡ ምክንያት ፡ ከሚወስንበት ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፡ ይህ ፡ በግልጽ ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለማድረስ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያዝበት ፡ ለመበየን ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ ወንጀለኛ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተደጋገመ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ የፈቃዱ ፡ ወረቀት ፡ እስከ ፡ ጭራሹ ፡ እንዲወሰድበት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። እንዲያውም ፡ አንድ ፡ ሥራን ፡ ከማከናወን ፡ መብት ፡ የመሻር ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፻፳፩ ፡ (ሐ) ።]

### ቍ ፡ ፻፳፫ ። መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ መከልከልና ፡ ስለ ፡ መዝጋት ።

የወንጀሉን ፡ ሥራ ፡ ባደረገው ፡ ወይም ፡ ባደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከሚወስንባቸው ፡ ቅጣትም ፡ በቀር ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ከባድነትና ፡ ዐይነቱ ፡ ታይቶ ፡ ውሳኔው ፡ ለሕዝብ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያገለገሉ ፡ ወይም ፡ የረዱ ፤ የንግድ ፡ ወይም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ የሃይማኖት ፡ የፖለቲካ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የተቋቋሙ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ እንዲዘጉና ፡ እንዲከለከሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

እንዲሁም ፡ የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በበለጠ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ ፡ ሥራዎችና ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲፈርሱ ፡ ንብረታቸውም ፡ እንዲጣራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

## ቊ ፤ ፻፵፮ ። ውሳኔውን ፡ ባለመጠበቅ ፡ ስለሚደረስ ፡ ውጤትና ፡ ቅጣት ።

(፩) የመዝጋቱ ፡ የማገዱ ፤ ወይም ፡ የመከልከሉ ፡ ትእዛዞች ፡ ጠቅላላና ፡ የመጨረሻ ፡ ሊሆኑ ፡ ወይም ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለተለየ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ለተለየ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ በፍርዱ ፡ ውስጥ ፡ ሊወሰኑ ፡ ይችላሉ ።

እርሱ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰውም ፡ ስም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ ስም ፡ በመለወጥ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አመራር ፡ በማካሄድ ፡ ዘዴም ፡ ቢሆን ፡ የተከለከለውን ፡ ሥራ ፡ እንዳይቀጥል ፡ ያግዱታል ።

(፪) የክልከላውን ፡ ውሳኔ ፡ መተላለፍ ፡ በሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ያስቀጣል ። [ቊ ፡ ፩፻፵፫ ።]

የተከፈተውም ፡ የንግድ ፡ ወይም ፡ የእንዱስትሪ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይዘጋል፤ አዲሱም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ማኅበር ፡ ይፈርሳል ። ንብረታቸውም ፡ በፍርድ ፤ ባለሥልጣን ፡ ይጣራል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የግል ፡ ነጻነትን ፡ ስለሚቀንሱ ፡ ድንጋጌዎች ።

## ቊ ፤ ፻፵፯ ። ጥፋተኛው ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይደርስ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በጥፋቱ ፡ ከሚወስንበት ፡ ከዋነኛው ፡ ቅጣት ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ ለጥፋቱ ፡ መፈጸሚያ ፡ ምክንያት ፡ ከሆነው ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ጥፋት ፡ ለመሥራት ፡ ከሚረዳው ፡ ካንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ በተለይም ፡ ከመሸታ ፡ ቤት ፡ ከሆቴል ፡ ቤት ፡ በጨዋታ ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ ከሆኑ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቤቶች ፡ ከገበያዎች ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ከሆኑ ፡ ከማንኛዎቹም ፡ ስፍራዎች ፡ እንዳይደርስ ፡ የሚከለክል ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣትንም ፡ ሊውስንበት ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ የተከለከለውን ፡ ስፍራ ፡ ክልልና ፡ ክልከላውም ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ። ይህም ፡ የክልከላ ፡ ጊዜ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

## ቊ ፤ ፻፵፰ ። ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አገር ፡ ከመኖርና ፡ ውሎ ፡ ከማደር ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

(፩) እንዲሁም ፡ ለጥበቃው ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ተመሳሳይ ፡ ምክንያት ፡ ሲገኝ ፡ ይህ ፡ የመከልከል ፡ ጉዳይ ፡ ወንጀለኛው ፡ ባንድ ፡ ከተማ ፡ ባንድ ፡ መንደር ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አውራጃ ፡ እንዳይኖር ፡ ወይም ፡ ውሎ ፡ እንዳያድር ፡ የማገድንም ፡ ውሳኔ ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ከባድነት ፡ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡

ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ለዘወትር ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሚቈይ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሚደረገው ፡ ክልከላ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተከለከለውን ፡ አገር ፡ ክልልና ፡ ክልከላውም ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ምክንያቱን ፡ ገልጾ ፡ ይወስናል ።

**ቊ ፡ ፻፶፩ ። ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፡ ግዴታ ።**

(፩) የተገለጹና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያላቸው ፡ ጕዳዮች ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ ወንጀለኛው ፡ ሁከት ፡ የሚያደርግ ፡ መሆኑ ፡ ሲገለጽና ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ መገኘት ፡ በቂም ፡ በበቀል ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ በመሥራት ፡ አደጋ ፡ የሚያስከትል ፡ ጕዳት ፡ የሚያደርስ ፡ መሆኑ ፡ በእርግጥ ፡ የሚያሥጋ ፡ ሲሆን ፤ ተቀጪው ፡ በግዴታ ፡ ተለይቶ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ርቆ ፡ እንዲኖር ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስንለት ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አውራጃ ፡ ተወስኖ ፡ እንዲኖር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ ተቀጪ ፡ የሚኖርበትን ፡ የወረዳ ፡ ክልል ፡ ስፍራውንና ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖሩ ፡ ቅጣት ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ፤ ይህም ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ሊያንስ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

(፫) በተቀጪው ፡ ዐመል ፡ መሻሻልና ፡ በነገሩም ፡ ሁኔታ ፡ ግምት ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ አመራር ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ * ወንጀለኛውን ፡ ለመጠበቅ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የጥበቃውን ፡ ውሳኔ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አድርጎ ፡ ይፈጽምበታል ። [ቊ ፡ *፻፴፱ ።]

**ቊ ፡ ፻፶፪ ። በቅጠባባቂ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) አጥፊው ፡ በተጠባባቂ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከእስራት ፡ የተለቀቀው ፡ ወይም ፡ ከእስራት ፡ ነጻ ፡ የወጣው ፡ ወንጀለኛ ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነው ፡ ክፍል ፡ ተጠባባቂ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ካልተመለከተ ፡ በተለይም ፡ በቍጥር ፡ ፻፵፫ ፡ በተመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ጥፋተኛውም ፡ መላልሶ ፡ በሠራቸው ፡ ተግባሮች ፤ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ከባድነት ፡ በተለይ ፡ አደገኛ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፤ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ በጥቂቱ ፡ ያንድ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ የተፈረደበት ፡ ካልሆነ ፤ ወይም ፡ የተደጋገመ ፡ ወንጀል ፡ በመሥራቱ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ መፈጸሚያ ፡ በሆነ ፡ የግዞት ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፡ ፍርድ ፡ የተወሰነበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ አይፈጸምበትም ።

BACK



(፪) በተጠባባቂ ፡ የመጠበቅ ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ያነሰ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። እንዲያውም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊራዘም ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ።

የመጠባበቅ ፡ ሥርዐት ፤ ተጠባቂውን ፡ በግል ፡ ተግባሩ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ መጠነኛ ፡ ኑሮውን ፡ ለመያዝ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የማኅበራዊ ፡ ደረጃ ፡ ለማግኘት ፡ በሚችልበት ፡ እርምጃ ፡ ሳያስቸግረው ፡ በስውር ፡ ሊፈጸም ፡ ይገባዋል ።

በተጠባባቂ ፡ የሚጠበቀው ፡ ሰው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የዘወትር ፡ መቈጣጠር ፡ በሚደረግበት ፡ በየጊዜው ፡ ወይም ፡ በተጠራ ፡ ቍጥር ፡ ካንድ ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ዘንድ ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚያስገድድ ፡ ትእዛዝ ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ ሊወሰንበት ፡ ይቻላል ።

(፫) የነገሩን ፡ ሁኔታና ፡ የተቀጪውንም ፡ የዐመል ፡ ሁኔታ ፡ በመገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያዝ ፡ የሚገባውንም ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥርዐት ፡ አፈጻጸም ፡ ጕዳይ ፡ መሠረት ፡ በማድራግ ፡* በተቀጪው ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ የተጠባባቂነት ፡ ጥበቃ ፡ ባንድ ፡ የመጠበቅ ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ባልደረባ ፡ ብቻ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚበቃ ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህንኑ ፡ ብቻ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ * ፩፻፲፫ ።]

ቍ ፡ ፻፴፫ ። በግልጽ ፡ የተሰጡትን ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።

ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ሲገኙ ፡ በተለይም ፡ ለጥበቃና ፡ ለጸጥታ ፡ ጕዳይ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ ስለ ፡ መቀነስ ፡ ለተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀጪውን ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ ፓስፖርት ፡ ለጊዜው ፡ እንዲያዙበት ፡ ወይም ፡ እንዲወሰዱበት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

የፍርዱም ፡ ውሳኔ ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ የተበየነበትን ፡ ምክንያትና ፡ ቅጣቱም ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ገልጾ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፴፬ ። ወንጀለኛው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ እንዳይኖር ፡ ስለ ፡ መከልከልና ፡ ካገር ፡ ስለ ፡ ማስወጣት ።

(፩) ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ተቀጪው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በተለይም ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡ የማያስፈልግ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ወንጀለኛ ፡ ለጊዜው ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ጭራሹ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እንዲወጣ ፡ በፍርድ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የሚጸናው ፡ የሠራው ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡

BACK



እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በክፋት ፡ መንፈስ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ በዚህም ፡ ወን ጀል ፡ በጥቂቱ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ በተፈረደበት ፤ ወይም ፡ የዘወትር ፡ ዐመፀኛ ፡ በመሆኑ ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥራ ፡ መፈጸሚያ ፡ በሆነ ፡ የግዞት ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፡ ፍርድ ፡ በተወሰነበት ፡ በማናቸውም ፡ ወንጀለኛ ፤ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ዐዋቂው ፡ ምርመራ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡ በሠራው ፡ ጥፋት ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ በማይጠየቅ ፡ ወይም ፡ አላፊነቱ ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ በሆነው ፡ አደገኛነቱም ፡ በተገለጸ ፡ በማናቸውም ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ እንዳይኖር ፡ የመከልከሉ ፡ ውሳኔ ፡ የሚጸናበትን ፡ ጊዜ ፡ ይገልጻል ።

(፪) ይህን ፡ ዐይነት ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ የፖ ለቲካ ፡ መምሪያና ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍሎችን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አሳብ ፡ አስቀድሞ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

ይህን ፡ ስለመሳሰለው ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ገብቶ ፡ በሚቀመጥበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ባገር ፡ መኖር ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

(፫) ካገር ፡ የማስወጣት ፡ ውሳኔ ፡ ሌላውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ አያስቀርም ።

## ቍ ፡ ፻፶፭ ። አፈጻጸሙ ።

(፩) ውሳኔው ፡ የሚፈጸመው ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ክፍል ፡ በሆነው ፡ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ አማካይነትና ፡ ስለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ባስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ደንብ ፡ በሚወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ጥፋተኛው ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካገር ፡ የመውጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ የሚፈጸምበት ፡ የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ከፈጸመ ፡ ወይም ፡ አጋጣሚው ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከቅጣቱ ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፫) ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የሚመለከተው ፡ አላፊነቱ ፡ የተወሰነውን ፡ ጥፋተኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ ሲሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ቅጣቱ ፡ ይፈ ጸምበታል ። ካገር ፡ የመውጣቱም ፡ ውሳኔ ፡ በመታከም ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ በጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፡ በተለመደው ፡ ደንብ ፡ ይለወጥለታል ። [ቍ ፡ ፻፴፬ ፡ እና ፡ ፻፴፭ ።]

እንዲሁም ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ በማይጠየቅ ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ከክሱ ፡ ውጭ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ በሙሉ ፡ ነጻ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ካገር ፡ የመውጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ በዚሁ ፡ በጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፶፯ ። የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለሙከራ ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ ማገድ ።**

ወንጀለኛው ፡ ከግል ፡ ነጻነት ፡ የመታገድ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የግዞት ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበትና ፡ ለአመክሮ ፡ ተለቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ከመድረስ ፡ የመከልከል ፤ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፤ ወይም ፡ ካገር ፡ የመውጣት ፡ ውሳኔ ፡ ለሙከራና ፡ ውሳኔውንም ፡ የመሻር ፡ መብት፡ ሳይነካ ፡ በጠቅላላው ፡ ሁኔታዎችና ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ ዋስትና ፡ መሠረት ፡ ለጊዜው ፡ ታግዶ ፡ እንዲቈይ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፪፻፲፪ ።]

**ቍ ፡ ፻፶፰ ። ስለ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ የተወሰነውን ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ የሚደረግ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ።**

ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ እንዳይደርስ ፡ ባንዳንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ እንዳይኖር ፤ ወይም ፡ ውሎ ፡ እንዳያድር ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አገር ፡ ርቆ ፡ በግዴታ ፡ እንዲቀመጥ ፤ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ የተጠባባቂ ፡ መከታተል ፡ እንዲደረግበት ፤ ካንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ዘንድ ፡ በየጊዜው ፡ ወይም ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀርብ ፡ የተሰጠውን ፡ የግዴታ ፡ ትእዛዝ ፡ ባለመፈጸም ፤ እንዲሁ ፡ ካገር ፡ እንዲወጣ ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡እንዳይገባ ፡ የተወሰነበትን ፡ የክልከላ ፡ ፍርድ ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ የሚቀጣው ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፩፻፶፫ና ፩፻፶፬ ።]

## ክፍል ፡ ፬ ።

## የማስታወቂያ ፡ አሰጣጥ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቍ ፡ ፻፶፱ ። ለደንበኛው ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።**

ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ተቀዳሚ ፡ ጥንቃቄና ፡ የአጠባበቅን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ ያለውን ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዲያውቀው ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ቍጥር ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ተፈጻሚነቱን ፡ እንዲያገኝና ፡ መጠበቁን ፡ ለመቈጣጠር ፡ እንዲቻል ፤ ባለጉዳይ ፡ ለሆኑት ፡ ለአስተዳደር ፡ ለብሔራዊ ፡ (ለባላገር) ፡ ለወታደር ፤ ለፖሊስ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሳይዘገይ ፡ ያስታውቃል ።

የተወሰነውም ፡ ቅጣት ፡ ፍሬ ፡ ማግኘቱን ፡ ለማረጋገጥ ፡ እንዲችል ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አግጣጫ ፡ ሁኔታ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲገለጽ ፡ ማስፈለጉንም ፡ ጭምር ፡ ይገልጻል ።

## ቍ ፡ ፻፶፱ ። ፍርድን ፡ ለሕዝብ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) የፍርድ ፡ ለሕዝብ ፡ መገለጽ ፡ ለጠቅላላው ፡ ለሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ ለተከሳሹና ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲገለጽ ፡ ያዛል ።

የዚህም ፡ ፍርድ ፡ መገለጽ ፡ ለጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀጥታ ፡ እንዲገለጽ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ። ጠቃሚነቱ ፡ ለግል ፡ ባለጉዳይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ባለጉዳዩ ፡ በጽሑፍ ፡ ካላመለከተ ፡ በቀር ፡ እንዲገለጽ ፡ አይደረግም ።

ተከሳሹ ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፍርዱን ፡ ውሳኔ ፡ ማስታወቂያ ፡ ዋጋ ፡ የሚከፍለው ፡ ራሱ ፡ ነው ። ከፍርዱም ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማስታወቂያውን ፡ ዋጋ ፡ የሚከፍሉት ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ ወይም ፡ ወንጀዩ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ መንግሥት ፡ ይከፍላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተለመደውን ፡ የማስታወቂያ ፡ አወጣጥ ፡ ሥርዐት ፡ በመከተል ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ መጠን ፡ የፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚገለጽበትን ፡ ዐይነትና ፡ የመገለጫውንም ፡ ጽሑፍ ፡ ብዛት ፡ ይወስናል ።

ማስታወቂያውም ፡ ሕዝብ ፡ በሚሰበሰብበት ፡ አደባባይ ፡ በመለጠፍ ፡ ወይም ፡ በድምፅ ፡ በመልፈፍ ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ በባለግል ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ በመታተም ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፷ ። ፍርድን ፡ በግል ፡ የፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።

(፩) በፍርድ ፡ የተሰጡ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ውሳኔዎች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ታስቦ ፡ የተደነገገው ፡ ጉዳይ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜና ፡ ስለዚሁ ፡ የፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ጉዳይ ፡ በተቋቋመው ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ይመዘገባሉ ።

ፍርዱ ፡ ተመዝግቦ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜና ፡ የአመዘጋገቡን ፡ መጠን ፡ ባለመብት ፡ ለሆነውም ፡ የሚገለጽበትን ፡ ልክ ፡ እንዲሁም ፡ የወንጀሉን ፡ መፋቅና ፡ የወንጀለኛውን ፡ መሰየም ፡ ሁኔታና ፡ ውጤት ፡ የደንቡ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይወስናሉ ።

(፪) በጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ (ሥርዐት) ፡ የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡ በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የሚመዘገቡት ፡ የፍርድ ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተቀጪውን ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ለማወቅ ፡ እንዲረዳቸው ፡ ነው ። ተቀጪው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ ሊመደብ ፡ የሚችልበትን ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ እንዳያስናክሉበት ፡ በማሰብ ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ላልሆኑት ፡ ወይም ፡ በጉዳዩ ፡ ለማያገባቸው ፡ ባዕዶች ፡ ሰዎች ፡ ሊገለጹ ፡ አይገባቸውም ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፩ ።
## አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ጥንቃቄዎችና ፡ ቅጣቶች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።
### ለአካለ ፡ መጠን ፡ ያልተደረሰበት ፡ ደንበኛ ፡ ዘመን ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
### መደበኛ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቁ ፡ ፻፷፩ ። መሠረቱ ።**

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከቱት ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ተግባሮች ፡ አንዱን ፤ ከ፱ ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሠርቶ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ * ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሕጉን ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመከተልና ፡ * * ከነገሩም ፡ ልዩ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ነገሩን ፡ ለመረዳት ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ፡ ካዘዘ፡ በኋላ፡ ከዚህ ፡ በታች፡ ከተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ አንዱን ፡ ያዛል ። * [ቁ፡ * ፶፫። * ፶፬።፶፭።]

**ቁ ፡ ፻፷፪ ። ሕክምና ፡ ለሚደረግበት ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።**

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁኔታ ፡ ሕክምና ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲሆን ፡ በተለይም ፡ የአእምሮ ፡ ደካማ ፡ የሆነ ፤ ዕውቀቱ ፡ ሙሉ ፡ ከመሆን ፡ የዘገየ ፤ አእምሮው ፡ የተበላሸ ፤ ዕውር ፡ ዲዳ ፡ ደንቆሮ ፡ የሚጥል ፡ (ኤፒሌፕቲክ) ፡ በሽታ ፡ ያለበት ፤ በመጠጥ ፡ የተሸነፈ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ተገቢ ፡ በሆነው ፡ መታከሚያ ፡ ቦታ ፡ እንዲታከም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ።

ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የትምህርትና ፡ የበጎ ፡ አስተዳደግ ፡ ጥንቃቄ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ይሰጠዋል ።

**ቁ ፡ ፻፷፫ ። በበጎ ፡ አስተዳደግና ፡ በትምህርት ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።**

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወንጀለኛ ፡ በበጎ ፡ አስተዳደግ ፡ ያላደገ ፤ በነዘኅላልነት ፡ የተተወ ፤ ጠባዩ ፡ ወደ ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ያዘነበለ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ የሚያዘነብል ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ በተጠባባቂ ፡ እንዲማርና ፡ በጎ ፡ አስተዳደግ ፡ እንዲያገኝ ፡ ይታዘዝለታል ።

ተጠባባቂ ፡ የሚሆኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ዘመዶች ፡ የሌሉትና ፡ ቢኖሩም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ ታማኝነት ፡ ላለው ፡ ራሱን ፡ ለቻለ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ምግዚት ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ አልማጅ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፤ ሕፃናትን ፡ ለመጠበቅ ፡ ለማስተማር ፡ ለቆመ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ እንዲሰጥ ፡ ይታዘዛል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡የተዘረዘሩትም ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ተጠባባቂዎች ፡

በአደራ ፡ የተሰጣቸውን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ ሁኔታ ፡ ስለ ፡ መከታተላቸው ፡ ከዳኛው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ አላፊነታቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ ያረጋግጣሉ ።

በክፍሉ ፡ የባልደረብነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡* የመጠበቁን ፡ ሥራ ፡ ይቈጣጠራል ።[ቍ ፡* ፪፻፲፫ ።]

(፪) ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በደንብ ፡ እንዲሄድ ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራን ፡ እንዲለምድ ፡ ካንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከመገናኘት ፡ ወይም ፡ ካንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ከመድረስ ፡ እንዲከለከል ፡ በተወሰኑ ፡ ጊዜያቶች ፡ ከጠባቂዎች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ እንዲቀርብ ፡ ወይም ፡ ራፖር ፡ እንዲያደርግ ፡ ይህንኑም ፡ የመሳሰሉትን ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ሊታዘዙበት ፡ ይቻላል ።

እንደ ፡ ነገሩ ፡ አኳኋንና ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ግብ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰው ፡ አጥፊ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ ዋስ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እነዚህ ፡ ትእዛዞች ፡ ሊሰጡ ፡ ይቻላል ።

(፫) አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ዳኛው ፡ ወይም ፡ ተጠባባቂው ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ ዋስ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ሊያስገነዝባቸውና ፡ ሊወቅሳቸው ፡ ይችላል ።

ተጠባባቂዎች ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የተጠባባቂነት ፡ የማሳደግ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ሊወስድባቸው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፷፩ ። ስለ ፡ ተግሣጽና ፡ ስለ ፡ ወቀሳ ።

(፩) እንዲህ ፡ ያለው ፡ አሠራር ፡ ተገቢና ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ የሚሰጥ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥፋታቸውን ፡ በተግሣጽና ፡ በወቀሳ ፡ ያልፈዋል ።

ለወደፊቱ ፡ የበጎ ፡ ተግባር ፡ ስሜትና ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ፍላጎት ፡ እንዲኖረውና ፡ ተግባሩም ፡ የሚያመጣበትን ፡ ለሕሊናው ፡ እንዲረዳው ፡ አድርጎ ፡ ያስጠነቅቀዋል ።

(፪) ስለ ፡ ነገሩ ፡ ቀላልነት ፡ ወይም ፡ ባሠራሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያቶችና ፡ ሥራውን ፡ ሊረዳው ፡ የሚችል ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ጥፋተኛ ፡ ለማረም ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲገምት ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ብቻውን ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

ጠቃሚ ፡ በሚሆንበትም ፡ ጊዜ ፡ ከማንኛዎቹም ፡ ሌሎች ፡ ውሳኔዎችና ፡ ቅጣቶች ፡ ጋራ ፡ በመጣመር ፡ ሊሠራበት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፻፷፮ ። በትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቤቱ ፡ ስለ ፡ ማገድ ።

ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውም ፡ ጥፋተኛ ፡ በቀላሉ ፡ የሚታረም ፡ መሆኑ ፡ ሲታይ ፡ ለዕድሜውና ፡ ለኑሮው ፡ የሚስማማ ፡ የተወሰነ ፡

ሥራ ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቤቱ ፡ ተቀምጦ ፡ በዕረፍት ፡ ሰዓቱ ፡ ወይም ፡ በዕረፍት ፡ ቀኖቹ ፡ በግዴታ ፡ እንዲሠራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ።

እንደ ፡ ነገሩ ፡ አኳኋንና ፡ እንደ ፡ ሥራውም ፡ ጥፋት ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ ተገድዶ ፡ የሚሠራበትን ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ።

በተጠባባቂ ፡ ሆኖ ፡ ውሳኔው ፡ በጥብቅ ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዋስትና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይቀበላል ።

ቍ ፡ ፻፸፮ ። ለጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ የማይበቃ ፡ ወይም ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይልቁንም ፡ የተፈጸመውን ፡ ወንጀል ፡ ከፍተኛነትና ፡ ያፈጸመውን ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ የወጣቱን ፡ ወንጀለኛ ፡ ጠባይ ፡ ያለፈ ፡ ታሪኩን ፡ የተፈጥሮውን ፡ አደገኛነት ፡ በመገንዘብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ በተዘጋጀው ፡ ልዩ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፤ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እየተጠበቀ ፡ ጠቅላላ ፡ ያስተዳደግ ፡ ትምህርትን ፡ ግብረ ፡ ገብነትንና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ የሚይዝበትን ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ (የሥራ ፡ መልመጃ) ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ሕይወት ፡ እንዲመደብና ፡ በቅንነት ፡ እየሠራ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲማር ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፻፸፯ ። ውሳኔው ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) **የሕክምናና ፡ እየተጠበቁ ፡** የመማር ፡ ውሳኔ ፡ በመደቡ ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈየው ፤ **የሕክምና ፡ ወይም** ፡ የጥበቃ ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ያስፈልጋል ፡ በማለት ፡ ወስኖ ፡ ባቀረበው ፡ ጊዜ ፡ ልክና ፡ ተቀጪውም ፡ በሕግ ፡ የተወሰነለት ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላው ፡ ድረስ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። [ቍ፡ ፻፸፱ ። ፻፸፫ ።]

ይህም ፡ ውሳኔ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ወደ ፡ ማስገኘት ፡ ግብ ፡ የደረሰ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀና ፡ የክፍሉም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የደጋፊነት ፡ አሳባቸውን ፡ ካቀረቡ ፡ ውሳኔው ፡ ይቀራል ።

(፪) ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ክፍል ፡ የመላክ ፡ ውሳኔ ፡ *የሚታዘዘው ፡ በመደቡ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ቢበዛ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚደርስ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ በደለኛው ፡ በሕግ ፡ የተወሰነለትን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ከሚያደርስበት ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ አያልፍም ። [ቍ ፡ *፻፸፯ ።]

BACK



የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠ ፡ ቍጥር ፤ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

ተቀጪው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ አንስተኛውን ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ግዴታዎች ፡ መሠረት ፡* በፍርድ ፡ የተወሰነበት ፡ የሙከራ ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ሊከተላቸውና ፡ ሊፈጽማቸው ፡ የሚገባውን ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንቦች ፡ እንዲጠብቅና ፡ ‡ በጥበቃ ፡ ባለሥልጣን ፡ ባልደረባ ፡ ጥገኛነት ፡ ውስጥ ፡ እንዲቈይ ፡ ተደርጎ ፡ የተወሰነበት ፡ ሙሉ ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ለፈተና ፡ በአመክሮ ፡ ሊለቀቅ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ * ፪፻፲ ፡ ‡ ፪፻፲፫ ።]

ቍ ፡ ፪፻፷ ። ውሳኔዎችን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

ሁኔታዎችና ፡ በተለይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠው ፡ ፍሬና ፡ የጠባዩ ፡ ወይም ፡ የሁኔታው ፡ መለዋወጥ ፡ የሚያስገድድ ፡ ሲሆን ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ መኖሪያ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ በተጠባባቂው ፡ ባለሥልጣን ፡ ራፖር ፡ መሠረት ፤ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጥቅምና ፡ ጠባዩን ፡ ለማሻሻል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመለወጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። ሕጋውያን ፡ ውጤቶች ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ጥፋተኞች ፡ የሕክምና ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ የአስተዳደግ ፡ ቅጣቶች ፡ ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ ቢወሰንባቸው ፡ በወንጀለኛነት ፡ እንደ ፡ ተቀጡ ፡ ሆነው ፡ አይቈጠሩም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ቅ ጣ ቶ ች ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። መሠረቱ ።

ከቍጥር ፡ ፪፻፶፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፶፯ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተሰጥተው ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ ሳያስገኙ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስፈላጊው ፡ ምርመራ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ አንዱን ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። ስለ ፡ መቀጮ ።

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ መቀጮ ፡ መክፈሉ ፡ ቅጣት ፡ ሆኖ ፡ የሚሰማው ፡ የሚያሠለጥነውና ፡ ከጥፋቱ ፡ የሚመልሰው ፡ መስሎ ፡ ሲታየውና ፡ ራሱ ፡

መቀጮውን ፡ የሚከፍል ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድነትና ፡ እንደ ፡ ችሎታው ፡ መጠን ፡ መቀጮውን ፡ እንዲከፍል ፡ ይፈርድበታል ። መቀጮውም ፡ ከሌሎቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ጋራ ፡ በመደመር ፡ የሚወሰን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) መቀጮን ፡ ስለ ፡ መክፈልና ፡ መቀጮውንም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ልጆች ፡ አይፈጸምባቸውም ። [ቊ ፡ ፶፪ ፡ እስከ ፡ ፶፬ ።]

ትእዛዝ ፡ በማቃለል ፡ ወይም ፡ በመለገም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ መቀጮውን ፡ በተሰጠው ፡ አስፈላጊ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ *ቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚቈርጠው ፡ ልክ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ሊለውጠው ፡ ይችላል ፡ [ቊ ፡ *፩፻፺፭ ።]

ቊ ፡ ፩፻፷፪ ። የአለንጋ ፡ (የአርጩሜ) ፡ ቅጣት ።

(፩) ወጣቱ ፡ ወንጀለኛ ፡ እንቢተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የአለንጋ ፡ ቅጣት ፡ ቢፈጽምበት ፤ ይህ ፡ ቅጣት ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ መንፈስ ፡ የሚመልሰው ፡ ጠባዩን ፡ የሚያሻሽልለት ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአለንጋ ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአርጩሜ ፡ በአለንጋ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሊበልጥ ፡ አይገባውም ። የሚገረፈውም ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ሙሉ ፡ ጤነኛ ፡ የሆኑት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቅጣቱን ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚወስነው ፡ የተቀጪውን ፡ ዕድሜ ፡ አስተዳደጉንና ፡ ዐቅሙን ፡ የሰውነቱን ፡ ጥንካሬ ፤ ቢያንስም ፡ ቢያድግም ፡ የወጣቱን ፡ ወንጀለኛ ፡ የጠባዩን ፡ እልከኛነት ፤ እንዲሁም ፡ ያደረገውን ፡ ጥፋት ፡ ከፍተኛነት ፡ መጠን ፡ በመገመትና ፡ ይህንኑ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፩፻፷፫ ። ስለ ፡ እስራት ።

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመትና ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡—

(ሀ) የጸጥታ ፡ ማረጋገጫ ፤ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ የመኖር ፤ ወይም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሆኑት ፡ ጥንቃቄዎች ፡ *ለጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ በዚሁ ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ሊፈጸሙ ፡ ወደሚቻልበት ፡ ልዩ ፡ መቅጫ ፡ ቦታ ፡ እንዲገባ ፡ [ቊ ፡ *፩፻፺፯ ።]

(ለ) ወንጀለኛው ፡ አደገኛና ፡ ሰላምን ፡ የሚያውክ ፡ ወይም ፡ ጸጥታን ፡ የሚበጠ

BACK



ብጥና ፡ ለሌሎችም ፡ መጥፎ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ መሆኑን ፡ በተረዳው ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡ የማኖርን ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ በመያዝ ፡ በቀጥታ ፡ የቅጣት ፡ መፈጸሚያ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ ያዛል ። [ቍ ፡ ፻፱ ፡ (፪) ።]

(፪) ወንጀለኛው ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ጥፋት ፡ ከባድነት ፡ መጠንና ፡ ጥፋቱንም ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የዕድሜ ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመገመት ፡ ታስሮ ፡ የሚቈይበትን ፡ የጊዜ ፡ ልክ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ። ጊዜውም ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ሳያንስ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

ጥፋተኛው ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ መቀጫ ፡ቦታ ፡ ተልኮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጠባዩ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ የመሆን ፡ ግምትን ፡ ያሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ በሞላው ፡ ጊዜ ፤ የተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ ከዚህ ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚያሳስር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ ይሆናል ።

እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ ጥፋተኛ ፡ ታስሮ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ለመወሰን ፤ ወንጀለኛው ፡ በልዩ ፡ የመቀጫ ፡ ቦታ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ በግምት ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ የማሻሻል ፡ ውጤት ፡ እንዳስገኘ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ይገምታል ።

(፫) በወህኒ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ የመቈየቱ ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በቀላል ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ደንብ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የጥፋተኛው ፡ ጠባይ ፡ የተሻሻለ ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ በተለመደውና ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡‡ አስቀድሞ ፡ የመፈታት ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡* ፻፭ ። ‡ ፻፲፪ ።]

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

### ቍ ፡ ፻፸፩ ። ስለ ፡ ቀላል ፡ ጥፋት ፤ በሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።

ሕግን ፡ የመጣስ ፡ ሥራ ፡ ከተሠራ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ የጥንቃቄ ፡ ጥበቃ ፡ ወይም ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዲፈጸሙበት ፡ አስፈላጊ ፡ ወይም ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ያልታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጥንቃቄው ፡ ጥበቃ ፡ ወይም ፡ የቅጣቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዳይፈጸሙበት ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

ይልቁንም ፡ እንደዚሁ ፡ የማሠልጠን ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊዎቹ ፡ ቅጣቶች ፡ በአባት ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሥልጣን ፡ አስቀድሞ ፡ ተፈጽሞ ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ የያዘና ፡ የታረመ ፡

መስሎ ፡ ሲታይ ፡ የመደጋገም ፡ አደጋ ፡ የማያሳይ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ቅጣቱን ፡ ሊያስቀርለት ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፸፭ ። ልዩ ፡ የይርጋ ፡ ደንብ ።

(፩) ወንጀሉ ፡ ከተሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ አቀራረብ ፡ የተወሰነው ፡ ደንበኛው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ ፡ ካለፈ ፡ የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፻፸፬ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማናቸውንም ፡ የጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባርና ፡ ማናቸውንም ፡ ቅጣት ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ *፯፻፺፯ ።]

(፪) ለክስ ፡ ማቅረብና ፡ ለቅጣት ፡ የተደነገገው ፡ ጠቅላላ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ደንብ ፡ የይርጋውን ፡ ደንበኛና ፡ ፍጹም ፡ የሆነውን ፡ ጊዜ ፡ በግማሽ ፡ ለመቀነስ ፡ የተወሰነው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በከባዶቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ላይ ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

## ቍ ፡ ፻፸፮ ። ውሳኔውን ፡ አግዶ ፡ ስለ ፡ ማቈየትና ፡ ተቀጪውን ፡ በሙከራ ፡ ስለ ፡ ማቈየት ።

ክስ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፻፸፬ ፡ ከተመለከቱት ፡ ከባዶች ፡ ወንጀሎች ፡ አንዱን ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ የተደነገጉት ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኙ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተፈጽመው ፡ ሲገኙ ፡ በተጠባባቂ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በፈተና ፡ ቈይቶ ፡ የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ መፈጸም ፡ ለማገድ ፡ የተሠሩት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመደቡ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፻፺፬ ፡ እስከ ፯፻፺፭ ።]

የፈተናውም ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰነው ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፻፸፯ ። በሕዝባዊ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

በቍጥር ፡ ፻፸፬ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ በተለይ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነው ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ ቅጣት ፡ መወሰን ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በግልጽ ፡ ተረድቶ ፡ ካልገመተ ፡ በቀር ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅ ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸምና ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ቅጣት ፡ በዚህ ፡ በወጣቱ ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ የሕዝባዊ ፡ መብቱን ፡ የማጣት ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ለወደፊቱ ፡ ሊያስከትል ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፻፸፰ ። ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ የጥንቃቄና ፡ የጥበቃ ፡ ውሳኔዎች ።

አደገኞች ፡ ዕቃዎችን ፡ (መሣሪያዎችን) ፡ ስለ ፡ መውረስና ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ለመሆን ፡ ስለሚገባው ፡ ሀብት ፡ *እንዲሁም ፡ አንዳንድ ፡ ስፍራዎችን ፡ ከማዘውተር ፡

ስለ ፡ መከልከል ፡ ‡የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ጥፋ ተኞች ፡ ላይ ፡ ይፈጸማሉ ። [ቊ ፡ ፺፱ ። ፻፵፩ ። ፻፵፱ ።]

እንዲሁም ፡ ጠባዩን ፡ ለማሻሻል ፡ የማይችልና ፡ ለማኅበራዊውም ፡ ኑሮ ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ወንጀ ለኛ ፡ የተወሰነበትን ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ የመቈ የትን ፡ ቅጣት ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ካገር ፡ እንዲወጣ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይች ላል ። [ቊ ፡ ፻፸፮ ።]

አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣትና ፡ የተደረ ገባቸው ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ለክፍሉ ፡ የሞግዚትነት ፡ ባለሥ ልጣኖች ፡ መገለጽ ፡ አለበት ። [ቊ ፡ ፻፸፰ ።]

## ቊ ፡ ፻፸፱ ። የፍርድ ፡ ውሳኔን ፡ ስለ ፡ መግለጽና ፡ በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በግልጽ ፡ በማስታወቂያ ፡ አይወጣም ። [ቊ ፡ *፻፸፱ ።]

የተወሰነባቸውም ፡ ቅጣትና ፡ የጥንቃቄ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ውሳኔ ፡ በፍርዱ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የሚመዘገበው ፡ ‡ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ለመንግሥት ፡ አስተዳደርና ፡ ለፍርድ ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አስፈላጊውን ፡ መረጃ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲያገለ ግል ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ የዚህን ፡ የመዝገብ ፡ ቅጂ ፡ ለነገሩ ፡ ባዕድ ፡ ለሆኑ ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መግለጽ ፡ በፍጹም ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። [ቊ ፡ *፻፸፰ ።]

## ቊ ፡ ፻፹ ። ፍርድን ፡ ስለ ፡ መሠረዝና ፡ ስለ ፡ መሰየም ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ባለመብቶቹ ፡ ሲጠይቁ ፡ ከእስራት ፡ ቅጣቱ ፡ በቀር ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ የተወሰኑት ፡ የጥንቃቄና ፡ የሌላ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ ከተፈጸሙ ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡* ተገቢው ፡ ባለሥልጣን ፡ ውሳኔዎቹ ፡ ከፍርዱ ፡ ሰሌዳ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠረዙ ፡ ለማ ዘዝ ፡ ይችላል ። [ቊ ፡ ፪፻፵፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፵፯ ።]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ሕጋዊ ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ዘመን ፡ እስከሚደርስበት ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አማካይ ፡ ዘመን ።

### ቍ ፡ ፻፸፩ ። መጠነኛ ፡ ሁኔታ ።

በ፲፭ና ፡ በ፲፰ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ ወጣት ፡ ወንጀል ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጠነኛውን ፡ (የተለመደውን) ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ሲወስን ፡ *የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ቅጣትን ፡ ሊያቀልለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ *፶፮ ። ፻፸፰ ።]

በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ወንጀሉን ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ባልሞላው ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ፡ ሊፈጸምበት ፡ አይቻልም ። [ቍ ፡ ፻፲፰ ።]

ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ (የእስራት) ፡ ቅጣት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ካደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ተለይቶ ፡ የመታሰር ፡ ደንብ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ እስኪያደርሱ ፡ ድረስ ፡ በጥብቅ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ። [ቍ ፡ ፻፱ ፡ (፪) ።]

### ቍ ፡ ፻፸፪ ። ልዩ ፡ ሁኔታ ።

(፩) ወንጀለኛው ፡ በሰውነቱና ፡ በአእምሮው ፡ መጐልመስ ፡ ገና ፡ ካ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ያልራቀ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ እንዳልሆነ ፡ ልዩ ፡ መርማሪውም ፡ እንዳቀረበው ፡ አሳብ ፡ ለታናናሾች ፡ በደለኞች ፡ ለተመደበው ፡ ለሕክምና ፡ ለትምህርት ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፡ ለጠባይ ፡ ማረም ፡ ጕዳይ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ *ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባለፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ በማቅለል ፡ ፈንታ ፡ ከነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ አንዱ ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ይልቁንም ፡ ወደ ፡ መታከሚያ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ እንዲላክ ፡ ወይም ፡ በአለንጋ ፡ እንዲገረፍ ፡ ግልጽ ፡ በሆነና ፡ በቂነት ፡ ባለው ፡ ምክንያት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ የማሳከሙ ፡ በትምህርት ፡ የማሠልጠኑ ፡ ወይም ፡ በጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ስፍራ ፡ የማቈየቱ ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ ከሆነው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ከማድረስ ፡ ጊዜ ፡ ለማለፍ ፡ አይችልም ። [ቍ ፡ ፻፷፯ ።]

ይህ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይልቁንም ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሚቈጠረውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ በመመልከት ፡ ከጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ እንዲተላለፍ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፸፫ ። (፩) ።]

## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## መወሰን ፤ ለጊዜው ፡ ማቈየት ።

## በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ማቈየትና ፡ ቅጣትን ፡ ማስቀረት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ቅጣትን ፡ መወሰንና ፡ ለጊዜው ፡ ማቈየት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ቅጣትን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

**ቍ ፡ ፻፹፫ ። ቅጣትን ፡ የማቅለልና ፤ የማክበድ ፡ ሕጋዊ ፡ አወሳሰን ።**

በጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ከተጻፈው ፡ በላይ ፡ * በሕጉም ፡ ትእዛዝ ፡ ደንበኛውን ፡ ቅጣት ፡ ማቅለል ፡ ወይም ፡ ማክበድ ፡ የሚቻል ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመከተል ፡ ይወስናል ። [ቍ ፡ ፹፮ ።]

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለልና ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ደንብ ።

**ቍ ፡ ፻፹፬ ። ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለል ።**

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ ለማቅለል ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ በተደነገገ ፡ ጊዜ ፤ ሁሉ ፡ ቅጣቱን ፡ ለማቅለል ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወስነው ፡—

(ሀ) የሞት ፡ ፍርድን ፡ ከሓያ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሆነ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ።

(ለ) የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራትን ፡ ካሥር ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ዓመት ፡ በሆነ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ።

(ሐ) የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ መነሻ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተለይ ፡ የታዘዘውን ፤ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ የሆነ ፡ አነስተኛ ፡ የእስራት ፡ ቅጣትን ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ።

(መ) ጽኑ ፡ የሆነውን ፡ እስራት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሆነ ፡ እስራት ።

(ሠ) በተለይ ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ መነሻ ፡ አነስተኛ ፡ የሆነውን ፤ በጠቅላላው ፡ ለአነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ መነሻ ፡ የሆነውን ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ እስራት ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ።

(ረ) የእስራት ፡ ቅጣትን ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፻፹፭ ፡፡ በመሰለው ፡ ቅጣትን ፡ ማቅለል ፡፡

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመሰለው ፡ ቅጣትን ፡ ማቅለል ፡ የሚገባው ፡ ወይም ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ ተነግሮ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰን ፡ መብት ፡ አለው ፡፡

(ሀ) ስለሚፈረድበት ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የተደነገገውን ፡ ልዩ ፡ ቅጣትና ፡ እንዲሁም ፡ ለነገሩ ፡ አነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ እንዲሆን ፡ የታዘዘውን ፡ ድንጋጌ ፡ ለመከተል ፡ ብቻ ፡ ሳይገደድ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሊቀጣ ፡ ይችላል ፡፡ ወይም ፡ በአነስተኛው ፡ ቅጣት ፡ ሌላ ፡ ቀላል ፡ ቅጣት ፡ ተክቶ ፡ ለመወሰን ፡ መብቱ ፡ ነው ፡፡

(ለ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍል ፡ ከተመለከተው ፡ ከጠቅላላው ፡ ዝቅተኛ ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ በቀር ፡ ለሚፈረደው ፡ ለማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ለዚሁ ፡ በተወሰነው ፡ በአነስተኛው ፡ ቅጣት ፡ ወሰን ፡ አይገደድም ፡፡ [ቍ ፡ ፹፱ ፡ እስከ ፡ ፻፺ ፡፡]

### ቍ ፡ ፻፹፮ ፡፡ የወል ፡ ድንጋጌዎች ፡፡

ደንቡ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ ለማቅለል ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አጥፊነት ፡ በጠቅላላ ፡ የተመለከተውን ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የቅጣቱን ፡ ልክ ፡ ይወስናል ፡፡ [ቍ ፡ ፶፺ ፡፡]

እንደ ፡ ደንቡ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ቅጣትን ፡ በሚያቀልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ካሣ ፡ መክፈልን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ፡፡ *እንዲሁም ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችን ፡ አጣምሮ ፡ ስለ ፡ ጥበቃ ፡ የሚታዘዙትን ፡ ውሳኔዎችና ፡ ** ጠባይ ፡ ማረምን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ተመልክተው ፡ ከሚገኙት ፡ ውሳኔዎች ፡ ‡አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ፡፡ [ቍ ፡ *፻ ፡፡ ** ፻፳፩ ፡ እስከ ፡ ፻፳፯ ፡፡ ‡፻፴፰ ፡ እስከ ፡ ፻፶፯ ፡፡]

### ቍ ፡ ፻፹፯ ፡፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ ማድረግና ፡ ቅጣትን ፡ መተው ፡፡

በሕጉ ፡ ላይ ፡ በትክክል ፡ ተነግሮ ፡ የተመለከተ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከማናቸውም ፡ ቅጣት ፡ ጥፋተኛውን ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ፡፡

እንዲሁም ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ቅጣትን ፡ የመተው ፡ ሥልጣንን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያገኘው ፡ ሕጉ ፡ በትክክል ፡ ያዘዘለት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡፡
## የቅጣት ፡ ማክበድ ፡ ደንብ ፡፡

### ቍ ፡ ፻፹፰ ፡፡ ደንበኛ ፡ የቅጣት ፡ ማክበድ ፡፡

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ቅጣትን ፡ ማክበድ ፡ ታዞ ፡ ሲገኝ ፡ *ቅጣቱን ፡ የሚያከብደውን ፡ ምክንያት ፤ የነገሩን ፡ ዐይነትና ፡ ብዛት ፤ ወንጀለኛውም ፡ ያደረገውን ፡ ጥፋት ፡ ትልቅነት ፡

በማመዛዘን ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ከተወሰነው ፡ ሳያልፍ ፡ ቢያስፈልግም ፡ እስከ ፡ ከፍተኛው ፡ ቅጣት ፡ በመድረስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ይወስናል ። [ቍ ፡ *፹፩ ። ፲

**ቍ ፡ ፻፹፱ ። የወንጀል ፡ ተግባር ፡ በተደራረበ ፡ ጊዜ ፡ እርግጠኛ ፡ የሆነ ፡ የቅጣት ፡ ማክበድ ፡ ጉዳይ ።**

(፩) ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ የጥፋት ፡ መደራረብ ፡ ጉዳይ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ *ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ለማክበድ ፡ የወንጀለኛውን ፡ ተግባር ፡ ከባድነት ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ በመገመትና ፡ ቅጣቱን ፡ የሚቈርጠው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ደንቦች ፡ በመከተል ፡ ነው ። [ቍ ፡ *፹፪ ። (ሀ) ።]

(ሀ) ተደራራቢ ፡ ከሆኑት ፡ ነጻነትን ፡ ከሚያሳጡት ፡ ጥፋቶች ፡ ባንደኛው ፡ ምክንያት ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰን ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ስለ ፡ ሌሎቹ ፡ ተደራራቢ ፡ ጥፋቶች ፡ የሚወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ ሁሉ ፡ አጠቃሎ ፡ (ደርቦ) ፡ ይይዛል ።

(ለ) ነጻነትን ፡ የሚአሳጡ ፡ ቅጣቶች ፡ ተደራርበው ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ የሚወስነው ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ከባድ ፡ ለሆነው ፡ ጥፋት ፡ የተወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ ነው ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ በተደራራቢነት ፡ በተፈጸሙት ፡ ጥፋቶች ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ በተሠራው ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ ማሳደግ ፡ አለበት ። አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝም ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ለያዘው ፡ ጥፋት ፡ በተወሰነው ፡ ከፍተኛ ፡ የቅጣት ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ የዚሁ ፡ የቅጣቱ ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ ፡ እስኪሆነው ፡ ድረስ ፡ በመጨመር ፡ ማሳደግ ፡ ይችላል ። ቢሆንም ፡ በሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ዐይነት ፡ በሕጉ ፡ ከተወሰነው ፡ ከጠቅላላው ፡ ከፍተኛ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ ለመቅጣት ፡ አይችልም ።

(ሐ) ነጻነትን ፡ የመቀነስና ፡ የገንዘብን ፡ ቅጣት ፡ በሚያስከትሉ ፡ ወንጀሎች ፡ መካከል ፡ የተደራረቡ ፡ ጥፋቶች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ ተላላፊነትን ፡ መደራረብ ፡ ሁኔታ ፡ በመገንዘብ ፡ ሊወሰኑ ፡ የሚገባቸውን ፡ ሁለቱንም ፡ ቅጣቶች ለማጣመር ፡ ይችላል ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ከተመደበው ፡ ለእንዳንዱ ፡ ቅጣት ፡ ሊወሰን ፡ ከሚገባው ፡ ከጠቅላላው ፡ ከፍተኛ ፡ የቅጣት ፡ ወሰን ለማለፍ ፡ አይችልም ።

(መ) ብዙ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ቅጣቶች ፡ በሚወሰኑበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ መቀጮ ፡ ይወስናል ፤ ወንጀለኛው ፡ የጥፋቱን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ በመጓጓት ፡ መንፈስ ፡ ካልሆነ በቀር ፡ ይህ ፡ መቀጮ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጥፋት ፡ ለየብቻው ፡ ሊወሰን ፡ ከሚገባው ድምር ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ከከፍተኛው ፡ የመቀጮ ፡ መደብ ለማለፍ ፡ አይችልም ። [ቍ ፡ ፺ ።]

BACK



(ሠ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀጪው ፡ ንብረት ፡ እንዲወረስ ፡ ፍርድ ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተደራረበ ፡ ጥፋት ፡ ቢያጋጥመው ፡ እንኳ ፡ በዋና ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ በተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊወሰንበት ፡ አይችልም ።

(፪) ማናቸውም ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት ፤ ወይም ፡ የጥበቃ ፡ ወይም ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ ወይም ፡ የጸጥታ ፡ ውሳኔ ፡ ሁሉ ፡ ባንዱ ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ተደራርቦ ፡ ከተደረገው ፡ ላንዱ ፡ ወንጀል ፡ ተወስኖ ፡ ቢገኝም ፡ እንኳ ፡ በጠቅላላው ፡ ቅጣት ፡ ላይ ፡ እንዲጸና ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፹፯ ። ልዩ ፡ ሁኔታ ።

(፩) የወንጀል ፡ ተግባር ፡ መደራረብ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ከተደራረቡ ፡ ወንጀሎችም ፡ ያንደኛው ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ የተደራራቢውን ፡ ወንጀል ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጽም ፡ ለማድረግ ፡ ለመደገፍ ፡ ወይም ፡ ላንደኛው ፡ ከለላ ፡ እንዲሆን ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ እስከ ፡ ከፍተኛው ፡ መደብ ፡ ድረስ ፡ አክብዶ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወንጀሉን ፡ ለይተው ፡ የሚያመለክቱት ፡ በተለይም ፡ የነፍስ ፡ ግዳይና ፡ የወንበዴነት ፡ ወንጀል ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ የተወሰኑት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፹፰ ። ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ የተሠራና ፡ የተደራረበ ፡ ወንጀል ፡ ከፍርድ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መገለጹ ።

(፩) አንድ ፡ ወንጀል ፡ በገቢር ፡ ካንድ ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ወንጀሎች ፡ ጋራ ፡ ተደራርቦ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሲገኝና ፡ ወንጀለኛው ፡ የተቀጣው ፡ በተገለጸው ፡ ወንጀሉ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ከተፈረደበት ፡ በኋላ ፤ ሌላ ፡ ወንጀል ፡ መሥራቱ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚፈርደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጣቱን ፡ የሚወስነው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ በመከተል ፡ ወንጀለኛው ፡ በፊት ፡ በፈጸማቸው ፡ በተደራረቡት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀሎች ፡ ምክንያት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢፈረድበት ፡ ኖሮ ፡ ከሚደርስበት ፡ ቅጣት ፡ የሚበልጥ ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ እንዳይደርስበት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ አንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣትን ፡ ይወስናል ።

በዚሁም ፡ መሠረት ፡ በፊተኛው ፡ ፍርድ ፡ የተፈጸመው ፡ ቅጣት ፡ በጠቅላላ ፡ ከተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ይታሰብለታል ።

ቍ ፡ ፹፱ ። የሕጋዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መደራረብ ።

ወንጀለኛው ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በሆነ ፡ ተግባርና ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አደራርቦ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስቀጡትን ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጥሶ ፡ የተ

ገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በግብር ፡ የሚሠራ ፡ የወንጀል ፡ መደራረብ ፡ የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታና ፡ ይልቁንም ፡ በተለይ ፡ የተገለጸው ፡ አድራጎትና ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በአሳብ ፡ የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ የሆነው ፡ የወንጀለኛው ፡ መጥፎነት ፡ ጉዳይ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በገመተው ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፻፹፱ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ አክብዶ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። በሕግም ፡ በግልጽ ፡ ተወስኖ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ማክበድ ፡ አለበት ። [ቍ ፡ ፹፯ ፡ (ሀ) ። ፳፫ ፡ (፪) ።]

በሌላው ፡ ሁኔታ ፡ ግን ፡ በሕጉ ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባውን ፡ የቅጣት ፡ መደብ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ እስከ ፡ ከፍተኛው ፡ የቅጣት ፡ መደብ ፡ በማድረስ ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፻፺፫ ። በተደጋገመ ፡ ጥፋት ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ።

(፩) የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ተወስኖ ፡ ፍርዱ ፡ ተፈጻሚነትን ፡ ካገኘ ፡ በኋላና ፡ ተቀጪውም ፡ የተወሰነበትን ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በሕግ ፡ የተመለከተ ፡ የተደጋገመ ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ሠርቶ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ለወንጀሉ ፡ የተመለከተውን ፡ ከፍተኛ ፡ የቅጣት ፡ መደብ ፡ ሳይከተል ፡ ~~ቅጣቱን ፡ ሊ~~ያከብድበት ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ በጥፋት ፡ መደጋገም ፡ ሁኔታ ፡ በወንጀለኛው ፡ ጥፋተኛነትና ፡ በሥራው ፡ አደገኛነት ፡ መጠን ፡ ከፍተኛውን ፡ የቅጣት ፡ መደብ ፡ ለማለፍ ፡ ስለሚችል ፡ የሚገደደው ፡ በጥፋቱ ፡ ዐይነት ፡ ከሚወሰነው ፡ ከጠቅላላው ፡ የከባድ ፡ ቅጣት ፡ ባለማለፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፹፯ ፡ (ለ) ።]

(፪) ወንጀለኛው ፡ ደጋጋሚና ፡ ቅጣት ፡ የማይመልሰው ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ጽኑ ፡ ግዞት ፡ እንዲላክ ፡ የሚያዝዙት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። ቍ ፡ [፻፳፰]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቆም ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ቅጣትን ፡ በገደብ ፡ ስለ ፡ ማገድ ።

ቍ ፡ ፻፺፬ ። መሠረቱ ።

ለጥፋቱ ፡ መነሻ ፡ የሆኑትን ፡ ምክንያቶች ፡ በጠቅላላው ፡ በመመልከት ፡ በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ለጊዜው ፡ ባንድ ፡ ገደብ ፡ እንዲታገድ ፡ ማድረግ ፡ የወንጀለኛውን ፡ ጠባይ ፡ ለማረምና ፡ ለማሻሻል ፡ ወደ ፡ ደንበኛው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡

ለመመደብ ፣ ጠቃሚ ፣ ሊሆን ፣ የሚችል ፣ ስለ ፣ መሆኑ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የተረጋገጠ ፣ መሠረት ፣ ያለው ፣ እምነት ፣ ያገኘ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ከዚህ ፣ ቀጥሎ ፣ ባሉት ፣ ያሠራር ፣ ዐይነቶችና ፣ በሚከተሉት ፣ ሁኔታዎች ፣ ያንደኛውን ፣ ሥርዐት ፣ ለመከተል ፣ ይችላል።

እነዚህም ፣ ድንጋጌዎች ፣ ከወንጀለኛው ፣ የመታረምን ፣ መልካም ፣ ፈቃድና ፣ እርዳታውን ፣ የሚፈልጉ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ የሚሰጡት ፣ በሚቀር ፣ አኳኋንና ፣ ፈተና ውም ፣ መልካም ፣ ውጤትን ፣ ለመስጠት ፣ አለመቻሉ ፣ ሲታወቅ ፣ በማናቸውም ፣ ጊዜ ፣ የሚሻሩ ፣ ናቸው ።

ቍ ፣ ፻፺፮ ። ለቅጣት ፣ ውሳኔ ፣ ጊዜ ፣ ስለ ፣ መስጠት ፣ ውሳኔውን ፣ ስለ ፣ ማገድ ።

ወንጀለኛው ፣ ቀድሞ ፣ ያልተቀጣ ፣ ሆኖ ፣ ጠባዩም ፣ አደገኛነት ፣ እንደሌለው ፣ የሚገመት ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነና ፣ ጥፋቱ ፣ የገንዘብን ፣ መቀጮ ፣ * የግዴታ ፣ ሥራን ፣ * ወይም ፣ ከሦስት ፣ ዓመት ፣ የማያልፍ ፣ የእስራት ፣ ቅጣትን ፣ ብቻ ፣ የሚያስከትል ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ‡ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጥፋተኛነቱን ፣ ካረጋገጠ ፣ በኋላ ፣ ለወደፊቱ ፣ ጠባይን ፣ ለማረም ፣ እን ደሚችል ፣ እምነት ፣ ሊጣልበት ፣ የሚገባው ፣ መሆኑንና ፣ በዚሁ ፣ ውሳኔ ፣ ብቻ ፣ እስከ ፣ መጨረሻው ፣ ሊሻሻል ፣ የሚችል ፣ መሆኑን ፣ የገመተ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ የተወሰ ነበትን ፣ ፍርድ ፣ ለጊዜው ፣ አግዶ ፣ የተወሰነ ፣ የፈተና ፣ ጊዜ ፣ ሊሰጠው ፣ ይችላል ። [ቍ ፣ * ፹፰ ፩ * * ፻፸ና ፣ ፻፫ ። ‡ ፻፷ ።]

በርግጥም ፣ እንደዚህ ፣ ሆኖ ፣ በተገኘ ፣ ጊዜ ፣ ፍርዱ ፣ እንዳልነበረና ፣ ጥፋተኛ ውም ፣ እንዳልተቀጣ ፣ ያህል ፣ ይቈጠራል ።

ቍ ፣ ፻፺፯ ። ቅጣት ፣ እንዳይፈጸም ፣ ጊዜ ፣ ስለ ፣ መስጠት ።

ጥፋተኛው ፣ በቀድሞ ፣ ጊዜ ፣ የተፈረደበት ፣ ቢሆን ፣ ወይም ፣ ባይሆን ፣ የተፈረደበ ትን ፣ ቅጣት ፣ ከመፈጸሙ ፣ በፊት ፣ ለተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ ቅጣቱ ፣ ታግዶለት ፣ አመሉ ፣ ቢፈ ተን ፣ ሁለተኛ ፣ ጥፋት ፣ ከማድረግ ፣ የሚታገድ ፣ መሆኑንና ፣ ስለ ፣ ጠባዩም ፣ መሻሻል ፣ አንድ ፣ ጽኑ ፣ ማስጠንቀቂያ ፣ ብቻ ፣ የሚበቃ ፣ መሆኑን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የገመተ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ የቅጣቱን ፣ ውሳኔ ፣ ብቻ ፣ ይፈርድበታል ። ነገር ፣ ግን ፣ ቅጣቱ ፣ ሳይ ፈጸም ፣ በተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ ታግዶ ፣ እንዲቈይ ፣ ለማዘዝ ፣ ይችላል ።

ፈተናው ፣ መልካም ፣ ፍሬ ፣ ያስገኘ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ወንጀለኛው ፣ የተወሰነበትን ፣ ፍርድ ፣ መፈጸም ፣ የለበትም ፤ የፍርዱ ፣ ውሳኔ ፣ ግን ፣ በፍርድ ፣ ሰሌዳ ፣ ላይ ፣ ተመ ዝግቦ ፣ ከሌላው ፣ ውጤት ፣ ጋራ ፣ ነዋሪ ፣ ይሆናል ።

ቍ ፣ ፻፺፰ ። ቅጣቶችን ፣ ስለ ፣ መደራረብ ፤ ለአፈጻጸማቸው ፣ ጊዜ ፣ መስጠትን ፣ ስለ ፣ መከፋፈል ።

የተደራረበ ፣ የቅጣት ፣ ውሳኔ ፣ ሲኖር ፣ ይልቁንም ፣ ተጨማሪ ፣ ቅጣት ፣ በሚሰጥበት ፣

BACK



ጊዜ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲያገኝ ፡ ቅጣቱ ፡ እንዲፈጸም ፡ በሚያዝበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥበቃና ፡ ጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ በማየት ፡ የቅጣቱን ፡ መፈጸም ፡ መታገድና ፡ የጊዜ ፡ መስጠትን ፡ ነገር ፡ ላንዳንዶቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ሊተወው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፺፰ ። ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ የማይቻልበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ጊዜ ፡ የመስጠት ፡ ውሳኔ ፡ የሚቀረው ፡ ወንጀለኛው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በተደጋገመ ፡ ወንጀለኛነት ፡ ባንድ ፡ የጽኑ ፡ ግዞት ፡ ስፍራ ፡ እንዲታሰር ፡ ተወስኖበት ፡ እንደሆነና ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ በሚፈረድበት ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ ከነዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣቶች ፡ አንዱ ፡ የሚወሰንበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ እንዲታገድ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ ባንደኛው ፡ ምክንያት ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የሚወሰንበት ፡ ነገር ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ ይህም ፡ ጥፋት ፡ የተሠራው ፡ አስቀድሞ ፡ ሆኖ ፡ የተገለጸው ፡ ግን ፡ ከፍርድ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ያለፈውን ፡ ጥፋት ፡ ባለማወቅ ፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረው ፡ የፍርድ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሻራል ።

እንደዚሁም ፡ ሥራው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በተገለጸው ፡ ጥፋት ፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረው ፡ የቅጣት ፡ ማቆም ፡ ተገቢ ፡ አለመሆኑንና ፡ ፍሬ ፡ የሚያስገኝ ፡ አለመሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተረዳው ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ማገዱን ፡ ውሳኔ ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ።

(፫) ለጥንቃቄ ፡ የሚሰጡ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁልጊዜ ፡ አስፈላጊነታቸው ፡ ስለሚታወቅና ፡ የሚወሰኑትም ፡ ባስፈላጊነታቸው ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የፍርድ ፡ ማገድን ፡ ጉዳይ ፡ ሊያስከትሉ ፡ አይችሉም ። [ቍ ፡ ፻፳፰ ፡ እስከ ፡ ፻፶፯።]

ቍ ፡ ፻፺፱ ። (ማጣራት) ፤ ምርመራ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለውሳኔው ፡ አስቀድሞ ፡ ምርመራ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በገመተ ፡ ቍጥር ፡ ፍርድ ፡ እንዲታገድለት ፡ የሚጠይቀውን ፡ ተከሳሽ ፡ (ተቀጪ) ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩ ፤ የነበረው ፡ ጠባይ ፤ ያኗኗሩና ፡ የሥራው ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በተረጋገጠ ፡ አኳኋን ፡ ምርመራ ፡ ተደርጎ ፡ የተጣራ ፡ መረጃ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ የምርመራ ፡ ሥራ ፡ እምነት ፡ ላለው ፡ ላንድ ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂ ፡ ባልደረባ ፡ ወይም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ረዳት ፡ ለሆነ ፡ ላንድ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪፻ ። የወል ፡ ድንጋጌዎች ፤ ለፈተና ፡ የሚሰጥ ፡ ጊዜ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ የፍርድ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ፡አሰጣጥ ፡

BACK



ደንቦች ፡ መካከል ፡ አንደኛውን ፡ ሲመርጥ ፤ ጕዳዩን ፡ በተረጋገጠ ፡ ሁኔታ ፡ የተረዳበትንና ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ ደንብ ፡ የመረጠበትን ፡ ዋነኛ ፡ ምክንያት ፡ በውሳኔው ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

የተከሳሹ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፤ ጠባዩና ፡ የአመሉ ፡ አካሄድ ፡ ጊዜ ፡ መስጠቱም ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ መስሎ ፡ ካልታየ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ ሳይወሰን ፡ ወይም ፡ ሳይፈጸም ፡ እንዲቈይ ፡ ጊዜ ፡ የመስጠት ፡ ትእዛዝን ፡ ለመወሰን ፡ አይችልም ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለጥፋተኛው ፡ የሚሰጠውን ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ የሚወስነው ፡ የጥፋቱን ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፤ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ መደጋገም ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፤ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ሊጣልበት ፡ የሚችለውን ፡ የእምነት ፡ መጠን ፡ በመገመት ፡ ነው ።

የፈተናው ፡ ጊዜ ፡ ቢያንስ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ቢበዛ ፡ ካምስት ፡ ዓመት ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ። የሚታሰበው ፤ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፻፺፭ ። ፈተና ፡ የሚሰጥባቸው ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸምበት ፡ ፍርድን ፡ የሚያግድለት ፤ ወንጀለኛው ፡ በመልካም ፡ ጠባይ ፡ እንዲመራ ፤ እንዲፈጽም ፡ የተሰጠውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲቀበልና ፡ እንዲሁም ፡ በሚቻለው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ በጥፋቱ ፡ ያደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ እንዲክስ ፡ ወይም ፡ ለተበዳዩ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍልና ፡ *ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሆነውን ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ወጪ ፡ እንዲከፍል ፡ ካረጋገጠለት ፡ በኋላ ፡ ነው ። [ቍ ፡ *፪ ።]

(፪) እንዲሁ ፡ ለገባበት ፡ ግዴታ ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ መተማመኛ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ያስገድደዋል ። ይህም ፡ መተማመኛ ፡ በሰው ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ በንብረትና ፡ በገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ሊፈጸም ፡ ይቻላል ። ሊሰጥ ፡ የሚገባውንም ፡ የመተማመኛ ፡ መያዣ ፡ ልክ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወስነው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታና ፡ እንደ ፡ ሰውዬው ፡ ችሎታ ፡ መጠን ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፻፺፮ ። በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የሚወሰን ፡ የአኗኗር ፡ ደንብ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ ያመራርን ፡ የአጠባበቆችንና ፡ የመቈጣጠርን ፡ አፈጻጸም ፡ ደንቦች ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ይወስናል ።

ይህም ፡ የጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንብ ፡ በተለይ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበብ ፡ የመማርን ፤ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ የመቀመጥን ፡ የመሥራትንና ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ የመኖርን ፡ ግዴታ ፡ ባንዳንድ ፡ በተወሰኑ ፡ ስፍራዎች ፡ ከመድረስ ፡ የመታገድን ፡ ወይም ፡ አልኮል ፡ ያለባቸውን ፡ መጠጦች ፡ ከመጠጣት ፡ የመወሰንን ፤ በሥራ ፡ ከሚያገኘው ፡

በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለቤተ ፡ ሰብ ፡ ለሞግዚት ፡ ወይም ፡ ለአሳዳሪው ፡ መስጠትን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የሕክምና ፡ ጥበቃ ፡ መፈጸምን ፡ ወይም ፡ የሙከራውን ፡ ውጤት ፡ ፍሬ ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችል ፡ ለዚሁ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሌላውን ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ አመራርን ፡ ደንብ ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ የተመለከተበት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) የጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አኳኋንና ፡ ጥፋቱ ፡ ባደረሰው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ ጥፋተኛው ፡ ጠባዩን ፡ ለማሻሻል ፡ ወደ ፡ ታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ የሚያስችል ፡ በሚሆን ፡ መንገድ ፡ ከተቀጪው ፡ ዐቅም ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በመሆን ፡ በትክክል ፡ መመረጥ ፡ ይገባቸዋል ።

የአመራሩ ፡ ደንብ ፡ ግብ ፡ ከፍርድ ፡ ማገድ ፡ ግብ ፡ ልዩ ፡ ሊሆንና ፡ ከሕጉም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ግዴታዎችን ፡ ሊያመጣ ፡ አይገባም ።

(፫) የተወሰነው ፡ የጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንብ ፡ በጊዜው ፡ አዲስ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፤ ወይም ፡ የነገሩን ፡ እርምጃ ፡ የመለወጥ ፡ መልክ ፡ በማሳየቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑንና ፡ ተገቢነቱን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ መንገድ ፡ ያስገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርዱ ፡ በታገደለት ፡ ሰው ፡ በባልደረባው ፡ በሞግዚቱ ፡ ወይም ፡ በዋሱ ፡ አመልካችነት ፡ ወይም ፡ በጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ጠያቂነት ፡ ሊለወጥ ፡ ይቻላል ።

ቊ ፡ ፪፻፫ ። ጥፋተኛውን ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባንድ ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ እንዲታገድ ፡ ሲያደርግ ፤ ይህ ፡ የፍርድ ፡ መታገድ ፡ ጉዳይ ፡ በሚገባ ፡ በተገለጸ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የተሻረ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፍርዱ ፡ የታገደለት ፡ ጥፋተኛ ፡ ባንድ ፡ አሳዳሪ ፡ ሞግዚት ፤ በጠባይ ፡ ማሻሻል ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኛ ፤ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ የጠባቂነት ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ባልደረባ ፡ ተጠባባቂነት ፡ ውስጥ ፡ እንዲሆን ፡ ያደርጋል ። [ቊ ፡ ፪፻፲፫ ።]

ባልደረባው ፡ ወይም ፡ ተጠባባቂው ፡ ፍርዱ ፡ ከታገደለት ፡ ጥፋተኛ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ እያደረገ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ሊጐበኘው ፤ የዕረፍቱንም ፡ ጊዜ ፡ ሊቈጣጠረው ፤ በተቻለም ፡ መጠን ፡ ሁሉ ፡ በቅንነት ፡ ለመኖር ፡ እንዲችልና ፡ ጠባዩንም ፡ እንዲያሻሽል ፡ አስፈላጊውን ፡ የመሪነት ፡ እርዳታ ፡ ሊያደርግለት ፡ ይገባዋል ።

ፍርዱ ፡ በታገደለት ፡ ተቀጪ ፡ ላይም ፡ ስውር ፡ የሆነ ፡ ደንበኛ ፡ መቈጣጠር ፡ ይፈጸምበታል ። ባለሥልጣን ፡ ለሆነውም ፡ የጠባይ ፡ መሻሻል ፡ ጥበቃ ፡ ኮሚሲዮን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በየሦስቱ ፡ ወርና ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ራፖር ፡ ያቀርባል ።

(፪) የጥበቃ ፡ ሠራተኞችና ፡ የኮሚሲዮኖች ፡ ሥራ ፡ አቋቋም ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ሕግና ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በሚወጣው ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ይወሰናል ።

BACK



## ቍ ፡ ፪፻፬ ። ፈተናው ፡ ፍሬ ፡ ያልሰጠ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፤ ለፈተና ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፤

### ስለ ፡ ማስቀረት ።

(፩) ፍርዱ ፡ የታገደለት ፡ ጥፋተኛ ፡ ለፈተና ፡ በተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በግዴታ ፡ እንዲከተላቸው ፡ ከተሰጡት ፡ የጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንቦች ፡ አንዱን ፡ የጣሰ ፤ ከቶ ጠባባቂው ፡ ጥበቃ ፡ ወይም ፡ ከባልደረባው ፡ ሥልጣን ፡ ለማምለጥ ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ አጥፊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማና ቸውም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ የተጣለበትን ፡ እምነት ፡ ለማሳሳት ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቍርጠኛ ፡ የሆነ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ይነግረዋል ።

አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ በሕጉ ፡ ዐቅድና ፡ ወሰን ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በፊት ፡ ተወስኖ ፡ የነበረውን ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ ከማራዘም ፡ ጋራ ፡ አዲስ ፡ የጠ ባይ ፡ አመራር ፡ ደንብ ፡ እንዲከተል ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ቍርጠኛ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ቢሰጠው ፡ እንኳ ፡ ለጊዜው ፡ ፍርዱ ፡ የታገ ደለት ፡ ጥፋተኛ ፡ በዚሁ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ አመራር ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለፈተና ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ ዐውቆ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርዱን ፡ ማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሽርበታል ። አስቀድሞ ፡ ግን ፡ ፍርዱ ፡ የታገደለት ፡ ጥፋተኛ ፡ የሚያቀርበው ፡ ነገር ፡ መሰ ማት ፡ አለበት ።

ጥፋተኛው ፡ ለፈተና ፡ በተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳግመኛ ፡ የፍርድ ፡ ማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ።

(፫) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አግዶት ፡ የነበረውን ፡ ቅጣት ፡ እንዲ ፈጸም ፡ ያዝዛል ። ወይም ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ያደ ርጋል ። ፍርዱም ፡ ደንበኛ ፡ ተፈጻሚነትን ፡ ያገኛል ።

የቅጣቱን ፡ ማገድ ፡ የሚያሽር ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ መደጋገም ፡ የተመሠረተውን ፡ ደንብ ፡ በመከተል ፡ ያዲሱ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ከቀድሞ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፪፻፫።]

## ቍ ፡ ፪፻፭ ። በመልካም ፡ ውጤት ፡ ፈተናን ፡ ስለ ፡ ማለፍ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሳይሆን ፡ ፈተናው ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ግቡ ፡ ድረስ ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ የታለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የመ ታገድ ፡ ትእዛዝ ፡ የሌለባቸው ፡ የተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባ በቅ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱ ፡ ከፍርድ ፡ ሰሌ ዳው ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠረዝለት ፡ ያዛል ።

BACK



## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡፡

## ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለ ፡ መፈታት ፡፡

**ቍ ፡ ፻፲፪ ፡፡ መሠረቱ ፡፡**

በዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተደነገገው ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ነጻ ነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ ውሳኔ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ የተወሰነው ፡ የአፈ ጻጸም ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስና ፡ ጠቅላላውም ፡ ሁኔታ ፡ ተሟልቶ ፡ ሲገኝ ፡ ጥፋተኛውን ፡ ለአመክሮ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመልቀቅ ፡ ይቻላል ፡፡

ለአመክሮ ፡ የመልቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የተቀጪ ውን ፡ ጠባይ ፡ ማሻሻያ ፤ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ መመለሻ ፡ ሆኖ ፡ መቈ ጠር ፡ ይገባዋል ፡፡ ይህም ፡ የሚፈጸምለት ፡ ተቀጪ ፡ ለዚሁ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ መባሉና ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ አፈጻጸም ፡ እርግጠኛ ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑ ፡ ካልታ መነ ፡ በቀር ፡ ሊፈቀድ ፡ አይቻልም ፡፡

**ቍ ፡ ፻፲፫ ፡፡ የመለቀቁ ፡ ሁኔታዎች ፡፡**

በእስር ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ አሳሳቢነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለአመክሮ ፡ እንዲለ ቀቅ ፡ ለመፍረድ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የቅጣት ፡ ወይም ፡ ነጻነትን ፡ የመቀነስ ፡ የጥንቃቄ ፡ አፈ ጻጸም ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ወንጀለኛው ፡ በሥራውና ፡ በአረማመዱ ፡ የተረጋገጠ ፡ የመሻሻል ፡ ማስረጃ ፡ አሳይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ራሱ ፡ ዐውቶ ፡ ሊፈጽመው ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ በሚገባ ፡ በተገመተው ፡ መጠን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተወሰነውን ፡ ወይም ፡ ከተበዳዩ ፡ ጋራ ፡ የተስማማበትን ፡ ካሣ ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ዐመሉና ፡ የጠባዩ ፡ አረማመድ ፤ እንዲሁም ፡ ነጻ ፡ በተለቀቀ ፡ ጊዜ ፡ የሚተዳ ደርበት ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፤ በተፈታ ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ አኗኗር ፡ ለመተዳደር የሚያስችለውና ፡ ይህም ፡ ውሳኔ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችላል ተብሎ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፻፲፬ ፡፡ ለጕዳዩ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ አሳብ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡፡**

(፩) ተቀጪዎቹ ፡ በሚፈረድባቸው ፡ ጊዜና ፡ እንዲሁም ፡ ወደሚላኩበት ፡ እስር ቤት ፡ በሚገቡበት ፡ ጊዜ ፤ የተወሰነባቸው ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፤ ቀደም

ብለው ፡ ሊለቀቁ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ይህንንም ፡ ዕድል ፡ ለማግኘት ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ እንደሚገባቸው ፡ እንዲያውቁት ፡ ሊገለጽላቸው ፡ ይገባል ።

(፪) ለጊዜው ፡ በአመክሮ ፡ ስለ ፡ መፈታት ፡ የታዘዙት ፡ ግዴታዎች ፡ የተፈጸሙ ፡ መሆናቸው ፡ በተረጋገጠ ፡ ጊዜ ፡ የእስር ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፤ እስረኛው ፡ በአመክሮ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ራሱ ፡ አሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ወይም ፡ በአመክሮ ፡ ልለቀቅ ፡ ብሎ ፡ እስረኛው ፡ ያቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀብሎ ፡ የደጋፊነት ፡ አሳቡንም ፡ ጨምሮ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሆነው ፡ ለክፍሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስተላለፍ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪፻፱ ። የአመክሮ ፡ ጊዜ ፡ ልክ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአመክሮ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ ወዲያውም ፡ ተፈቺው ፡ በአመክሮ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ፤ ይህም ፡ የአመክሮ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈየው ፡ በጠቅላላው ፡ ደንብ ፤ ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸም ፡ ውሳኔ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

የዚህም ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፤ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ያነሰ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ፤ እንዲሁም ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ ካምስት ፡ ዓመት ፡ ለመብለጥ ፡ አይችልም ። በጽኑ ፡ ግዞት ፡ ስፍራ ፡ ተወስኖ ፡ እንዲኖር ፡ የተወሰነበት ፡ ደጋጋሚ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሲሆን ፡ የአመክሮው ፡ ጊዜ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ሊያንስ ፡ አይችልም ። * የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የተወሰነበት ፡ ወንጀለኛ ፡ ሲሆን ፡ የአመክሮው ፡ ጊዜ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ አይወርድም ። [ቍ ፡ ፪፳፰ ፡ ፪፯ ።]

## ቍ ፡ ፪፻፲ ። የጠባይ ፡ አመራርና ፡ የአጠባበቅ ፡ ደንብ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የተለቀቀው ፡ አጥፊ ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ የጠባይ ፡ አመራር ፡ ሥርዐት ፡ እንዲከተል ፡ ይወሰንበታል ። [ቍ ፡ ፪፻፪ ።]

የእነዚህም ፡ የጠባይ ፡ አመራር ፡ ሥርዐቶች ፡ አወሳሰን ፡ በተለይ ፡ የሚመለከቱት ፡ የተለቃቂውን ፡ የዕድሜ ፡ መጠንና ፡ የአመሉን ፡ ሁኔታ ፡ በግምት ፡ ወይም ፡ በትክክል ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ አደጋ ፡ መጠን ፤ እንዲሁ ፡ ከእስር ፡ ቤቱ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ መተዳደሪያ ፡ ሊሆነው ፡ የሚችለውን ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ሁኔታ ፤ የሞያ ፡ ሥራውንና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮውን ፡ ተለዋዋጭ ፡ ወይም ፡ እርግጠኛ ፡ አኳኋን ፡ በመገመት ፡ ነው ።

የሚቻልም ፡ ቢሆን ፡ እነዚህ ፡ ለተለቃቂው ፡ መተዳደሪያ ፡ የሚሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ተቀጪው ፡ ከመለቀቁ ፡ በፊት ፡ በእስር ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ መምሪያ ፡ ክፍልና ፡ ያስ

ተዳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጣቸው ፡ የጥበቃ ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ባልደረቦች ፡ በሞግዚት ፡ ወይም ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበሮች ፡ ድጋፍ ፡ መዘጋጀት ፡ አለባቸው ።

(፪) በጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ ተለቃቂው ፡ ባንድ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የጠባቂነት ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ አስተዳዳሪ ፡ (ባልደረባ) ፡ ተቈጣጣሪነትና ፡ መሪነት ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡ ይደረጋል ። * ይህ ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥርዐት ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻልበት ፡ ምክንያት ፡ ካጋጠመና ፡ ጠቃሚነት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፤ ተለቃቂው ፡ ከዚህ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ውጭ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፲ ።]

## ቍ ፡ ፻፲፩ ። የፈተናው ፡ ውጤት ።

የፈተናው ፡ ሁኔታ ፤ ተሰጥቶ ፡ የነበረውን ፡ ችሮታ ፡ መሻር ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፻፬ ።]

(፩) በአመክሮ ፡ የመለቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሻር ፡ ተለቃቂው ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ተመልሶ ፡ እንዲገባ ፡ ይደረጋል ።

ለአመክሮ ፡ ተለቆ ፡ ያሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ መፈጸሚያ ፡ ከተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ጋራ ፡ አይታሰብለትም ።

በመካከሉ ፡ አዲስ ፡ የጥፋት ፡ ተግባር ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቅጣቱ ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ውሳኔ ፡ የሚፈጸመው ፡ በደንበኛው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ተለቃቂው ፡ ለአመክሮ ፡ የተወሰነለትን ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ አመራር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ነጻነቱን ፡ አግኝቶ ፡ ቅጣቱ ፡ በሙሉ ፡ ይቀርለታል ።

## ቍ ፡ ፻፲፪ ። ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ከመድረስ ፡ የመከልከል ፤ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ታግዶ ፡ የመኖርና ፡ካገር ፡ የመውጣት ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) ነጻነትን ፡ ከሚያሳጣ ፡ ወይም ፡ ከግዞት ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ከማከናወን ፡ የመታገድ ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ከመድረስ ፡ ወይም ፡ ውሎ ፡ ከማደር ፡ የመከልከል ፡ ወይም ፡ በሩቀ ፡ ስፍራ ፡ ታግዶ ፡ የመኖር ፡ ወይም ፡ ከአገር ፡ የመውጣት ፡ ቅጣት ፡ በተጨማሪነት ፡ ተወስኖ ፡ እንደሆነና ፡ በአመክሮ ፡ የመለቀቅም ፡ ጕዳይ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ከነገሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ውሳኔው ፡ ጠቃሚና ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ ሲታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አፈጻጸሙን ፡ ለሙከራ ፡ እንዲታገድ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። * [ቍ ፡ * ፻፳፪ ፡ (ሐ) ። ፻፵፱ ፡ እስከ ፻፶፩ና፻፶፬ ።]

ይህንም ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፤ በተለይ ፡ የተለቃቂውን ፡ የመሻሻል ፡ ሁኔታ ፡ ደረጃ ፤ የአደገኛ ፡ ጠባዩን ፡ መጥፋት ፤ ወይም ፡ መቀነስ ፡ ሁኔታ ፤ ይህም ፡ የቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ለጊዜው ፡ የማገድ ፡ ጕዳይ ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ መደቡ ፡

ስለ ፡ መመለስ ፡ ሊያስገኝ ፡ የሚችለውን ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ በማመዛዘን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ የሚወስነው ፤ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ በቂ ፡ ምርመራ ፡ ካደረገ ፡ በኋላና ፡ የቅጣት ፡ ማስፈጸሚያን ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣንና ፡ ጕዳዩ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ የስፍራውን ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተቀዳሚ ፡ አሳብ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ለፈተና ፡ በመለቀቁ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመው ፤ ደንብ ፡ በሚፈቅደው ፡ ዐይነት ፡ ተለቃቂው ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ግዴታ ፡ የሚከለክለውን ፡ ነገርና ፡ ወይም ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፡ የመተማመኛ ፡ ዋስ ፡ (ማረጋገጫ) ፡ ሌላውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ይወስናል ።

(፫) በአመክሮ ፡ የተለቀቀው ፡ ተቀጪ ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ በመልካም ፡ እርምጃ ፡ ተመርቶ ፡ እንዳችም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወቀሳ ፡ ያላገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠባዩም ፡ የተሻሻለ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ነጻነትን ፡ የመቀነስ ፡ ወይም ፡ ካገር ፡ የመውጣቱ ፡ ቅጣት ፡ ያስከተለበትን ፡ ጥፋት ፡ ሁለተኛ ፡ እንደ ማይሠራ ፡ የሚታመን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተወስኖበት ፡ የነበረው ፡ ቅጣት ፡ አይፈጸምበትም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## ባልደረብነት ።

### ቍ ፡ ፪፻፲፫ ። መሠረቱ ።

የጥበቃ ፡ ባልደረባ ፡ ማለት ፡ የቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ውሳኔዎች ፡ የነዚሁም ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዐት ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ እንዲያስገኝ ፡ የሚረዳ ፡ ዋነኛ ፡ የሆነ ፡ አስፈላጊ ፡ ድርጅት ፡ ነው ።

ሕጉ ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጥፋተኛ ፡ በጥበቃ ፡ ባልደረባ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

የቅጣት ፡ ፍርዱ ፡ የታገደለት ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ ነጻ ፡ የተለቀቀ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁሉ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በሌላም ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያቶች ፡ ቢሆን ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ለጠባዩ ፡ መልካም ፡ አመራር ፡ የጥበቃ ፡ ባልደረባ ፡ ድጋፍና ፡ እርዳታ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። እነዚህም ፡ የባልደረባ ፡ ድርጅቶች ፡ ለጥፋተኛው ፡ የእርዳታ ፡ ድጋፍ ፡ እንዲያደርጉለት ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፪፻፲፬ ። የባልደረብነት ፡ ዓላማና ፡ ሥልጣን ።

(፩) የጥበቃው ፡ ባልደረባ ፡ ዋና ፡ ሥራው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲለምዱ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ወንጀለኞች ፡ ቅጣታቸው ፡ በታገደላቸው ፡ ጊዜም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአመክሮ ፡ ከተለቀቁም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ነጻነትን ፡ ከሚያሳጣ ፡ ውሳኔ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተመደበው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንዲያደርሱና ፡ ዳግመው ፡ ወንጀል ፡ እንዳይሠሩ ፡ ምክር ፡ መስጠት ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ መምራት ፡ የመልካም ፡ ጠባይና ፡ የተጨበጠ ፡ እርዳታ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

በተለይም ፡ ባልደረብነት ፡ የተሰጠው ፡ ባለሥልጣን ፡ ተጠባቂዎቹን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውላቸው ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ሊሰጣቸው ፤ ወይም ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ አሠሪ ፡ ወይም ፡ መኖሪያ ፡ ወይም ፡ እርዳታ ፡ እንዲያገኙ ፡ ሊያግዛቸው ፡ በሥራቸው ፡ የሚያገኙትን ፡ ደመወዝና ፡ ጥቅም ፡ ለተገቢ ፡ ጉዳያቸው ፡ እንዲያውሉትና ፡ በጠቅላላውም ፡ በጨዋነት ፡ ለመኖር ፡ የሚችሉበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ድጋፍና ፡ እርዳታ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ዘወትር ፡ በተጠባባቂ ፡ ያስጠብቃቸዋል ። በተጠባባቂ ፡ የመጠበቁና ፡ የመቈጣጠሩ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መሻሻል ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የያዙትን ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ እንዳያሰናክላቸውና ፡ እንዳያሠጋቸው ፡ በስውር ፡ ሊፈጸም ፡ ይገባዋል ። አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ቍጥርም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱና ፡ በጠቅላላም ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በየጊዜው ፡ ራፖር ፡ ያቀርባል ።

ቍ ፡ ፪፻፲፭ ። የሥራው ፡ ድርጅት ።

(፩) ባልደረብነቱ ፡ የሚቋቋመው ፡ በመንግሥት ፡ ድጋፍና ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ሆነው ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ በተመደቡ ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ በሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ ነው ።

ይህም ፡ ሥራ ፡ በየጊዜው ፡ ለሚመረጥ ፡ እምነቱ ፡ ለተፈተነና ፡ ለዚሁ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑ ፡ ለታወቀ ፡ የጠባይ ፡ ማሻሻል ፡ ጠባቂ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

በጠቅላላው ፡ ሥርዐትና ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ለማካሄድ ፡ ከተቻለ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የጥበቃ ፡ ሥራ ፡ ለፖሊስ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አይሰጥም ።

(፪) የሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ዝርዝር ፡ በቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ሕግና ፡ ጉዳዩን ፡ በሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ ይገልጻል ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።
## ክስና ፡ ቅጣት ፡ ስለሚታገድበትና ፡ ስለሚቀርበት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።
### የከሳሽ ፡ ወይም ፡ የተከሳሽ ፡ መታጣት ።

#### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
#### የክስ ፡ ወይም ፡ የአቤቱታ ፡ አለመኖር ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፮ ። በጠቅላላው ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ ወይም ፡ የመክሰስ ፡ መብት ።**

ፍርዱ ፡ እንዲሰጥና ፡ ቅጣት ፡ እንዲወሰን ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ የተመለከተ ፡ ተቃራኒ ፡ ደንብ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ በኩል ፡ ነው ።

በሕግ ፡ አስከባሪው ፡ አማካይነት ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ በግልጽ ፡ አነጋገር ፤ ተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ ሆነው ፡ የመክሰስ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ ማቅረብን ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ መሠራቱን ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጠቅላላ ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ ጕዳይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ አያስቀርም ፡ (አያግደውም) ።

እነዚህ ፡ ማስታወቂያ ፡ የማቅረብ ፡ ጠባያትን ፡ የያዙ ፡ ሥርዐቶች ፡ ለክሱ ፡ መነሻ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የክሱ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ ክሱን ፡ ለሚቀጥልበት ፡ ነገር ፡ ግዴታ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደሉም ። አሠራራቸውም ፡ በወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ተወስኗል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፯ ። በግል ፡ ከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ስለሚቀርብ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ።**

በዚህ ፡ የወንጀል ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ የመቅጫ ፡ ድንጋጌ ፡ የግል ፡ ጠባይ ፡ በያዙትና ፡ ይህንኑ ፡ አጠቃለው ፡ በሚመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻ ፡ ካልቀረበ ፡ ወይም ፡ ተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ ሆኖ ፡ የመክሰስ ፡ መብት ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ በኩል ፡ አቤቱታ ፡ በማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቻልባቸውን ፡ ወንጀሎች ፡ ዐይነት ፡ ሕጉ ፡ በወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ተቀዳሚ ፡ ግዴታ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይፈጸም ፡ ከቀረ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣት ፡ ሊወስን ፡ ወይም ፡ ፍርድን ፡ ሊያይ ፡ አይገደድም ።

የመክሰስ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ክሱን ፡ ለመቀጠልና ፡ ሥረ ፡ ነገሩን ፡ ለመነጋገር ፡ እንዲችል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ አቀራረብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፰ ። የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ ተገቢ ፡ መብት ።**

ባንድ ፡ ጥፋት ፡ የተበደለና ፡ ዕድሜው ፡ በጥቂቱ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ የማወቅም ፡

BACK



ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ተገቢነት ፡ አለው ። ተበዳዩ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ወይም ፡ አእምሮው ፡ የጐደለ ፡ በመሆኑ ፡ ከባላጋራው ፡ ጋራ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ለመቋቋም ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክስ ፡ አቤቱታውን ፡ የማቅረብ ፡ ጉዳይ ፡ የሕጋዊ ፡ ወኪሉ ፡ መብት ፡ ይሆናል ።

ተበዳዩ ፡ የክስ ፡ አቤቱታውን ፡ ሳያቀርብና ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አለመፈለጉን ፡ በግልጽ ፡ ሳይናገር ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የክስ ፡ ማቅረቡ ፡ መብት ፡ ለቅርብ ፡ ዘመዶቹ ፡ ይሆናል ። ቢሆንም ፡ የተግባሩን ፡ ውጤት ፡ ለይቶ ፡ ሲረዳው ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አለመፍቀዱን ፡ ገልጾ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አለመፈለጉ ፡ የመጨረሻ ፡ ቃል ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፲፱ ፡ በኅብረት ፡ የሚቀርብ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ።

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ጥፋት ፡ የተበደሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የክስ፡አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ይህም ፡ መብት ፡ በየራሳቸው ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፳ ። የአቤቱታ ፡ ማቅረቢያ ፡ ጊዜና ፡ ያቀራረቡ ፡ ፎርም ።

(፩) በወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ የክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ተበዳዩ ፡ የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነው ።
ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለው ፡ ጉልህ ፤ በሆነ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ በማያስችል ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ ክስ ፤ ለማቅረብ ፡ እንዳልፈለገ ፡ ይቈጠራል ። ክሱንም ፡ ለመቀበል ፡ አይቻልም ።
ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ላለመቻሉ ፡ ማስረጃ ፡ የተገኘለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክስ ፡ ማቅረቢያ ፡ የሚያልፍበት ፡ የሦስት ፡ ወሩ ፡ ውሳኔ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ያጋጠመው ፡ ችግር ፡ ከተቃለለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) የክስ ፡ አቀራረብ ፡ ደንብ ፡ ፎርም ፡ በወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ይገለጻል ።

ቍ ፡ ፪፻፳፩ ። የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ስለመተው ።

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ ክሱን ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክሱ ፡ መቀጠል ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

ፍርድ ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ ክስን ፡ መተው ፡ ይቻላል ። ክሱን ፡ ለመተው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከሳሹ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ጉዳዩ ፡ በሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ የክስ ፡ መተው ፤ ፍጻሜ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። ክሱንም ፡ እንደገና ፡ ለማደስ ፡ አይቻልም ።

BACK



## ቍ ፡ ፪፻፳፫ ። ክስ ፡ የማይከፋፈል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ባንድ ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ተካፋዮች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ፡ እንጂ ፡ ሊለያይ ፡ አይችልም ።

በተሠራው ፡ ወንጀል ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ባለመብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ከተባባሪዎቹ ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ ያቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ሁሉንም ፡ ያስከስሳቸዋል ።

ክሱን ፡ የሚከታተለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከተባባሪዎቹ ፡ ወንጀለኞች ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ መተው ፡ የሌሎችንም ፡ ክስ ፡ ጨምሮ ፡ ያስቀራል ። ቢሆንም ፡ ከተከሳሾቹ ፡ አንዱ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጠኝ ፡ እንጂ ፡ ክሱ ፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ የተቃወመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አያግደውም ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
### የተከሳሹ ፡ ወይም ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ መሞት ።

## ቍ ፡ ፪፻፳፬ ። ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ መሞቱ ።

ፍርዱ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ ወንጀለኛው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክሱ ፡ አይከፈትም፡ ወይም ፡ የክሱ ፡ በዳኝነት ፡ መታየት ፡ አይቀጥልም ። እንዲሁም ፡ ብይኑ ፡ በፍርድ ፡ አይገለጽም ። የተከሳሹ ፡ መሞት ፡ ክሱን ፡ አስቀርቶ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ያደርገዋል ።

## ቍ ፡ ፪፻፳፭ ። ከቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መሞት ።

ጥፋተኛው ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሞቱ ፡ ተወስኖበት ፡ የነበረውን ፡ የቅጣትንና ፡ የጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፤ የገንዘብ ፡ መቀጮውንም ፡ ውሳኔ ፡ ያስቀራል ።

ስለ ፡ ሆነም ፡ የተቀጪው ፡ የወራሽነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ከውርሱ ፡ በሚያገኙት ፡ ንብረት ፡ መጠን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የጉዳት ፡ካሣ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ይገደዳሉ ።

### ክፍል ፡ ፪ ።
### ስለ ፡ ይርጋ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ።

## ቍ ፡ ፪፻፳፮ ። መሠረቱና ፡ ውጤቱ ።

(፩) ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከተው ፡ ሕጋዊ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ አቤቱታና ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ አቤቱታን ፡

BACK



ወይም ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ለመቀበልና ፡ በፍርድ ፡ ለመመርመር ፡ አይቻልም ።

የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ ማለፍ ፡ በማናቸውም ፡ ጥፋተኛ ፡ ለተሠራው ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ቅጣትን ፡ ያስቀራል ። ለይርጋ ፡ የተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

(፪) የክሱን ፡ በይርጋ ፡ መታገድና ፡ ለመቀበል ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ ባለጉዳዩ ፡ ሳያመለክት ፡ ሲቀር ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማንሣት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፳፯ ። መደበኛው ፡ የክስ ፡ አቀራረብ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ።**

በወንጀል ፡ ተግባር ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ የሚጸናው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(ሀ) የሞት ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ለሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ።

(ለ) ከዐሥር ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡

(ሐ) ካምስት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ።

(መ) እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ለሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ።

(ሠ) ካንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ በእስራት ፡ ለሚያስቀጡ ፡ ወንጀሎች ፡ አምስት ፡ ዓመት ።

(ረ) እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በእስራት ፡ ለሚያስቀጡ ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ብቻ ፡ ለሚያስቀጡ ፡ ወንጀሎች ፡ ሦስት ፡ ዓመት ።

**ቍ ፡ ፪፻፳፰ ። ልዩ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ።**

ግለኝነት ፡ ያላቸው ፡ ወንጀሎች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜና ፡ የሚያስቀጡትም ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ በተለይ ፡ አቤቱታ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሲሆንና ፡ ° ነገሩም ፡ ይበልጥ ፡ የሚነካው ፡ የግል ፡ ጥቅምን ፡ ሲሆን ፡ ይልቁንም ፡ ቀላል ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ክብርን ፡ መንካትና ፡ በሰዎች ፡ ነጻነትና ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ጉዳት ፡ ቀላል ፡ ሲሆን ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ° ፪፻፲፯ ።]

**ቍ ፡ ፪፻፳፱ ። የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ጊዜ ፡ አቈጣጠር ።**

(፩) የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ የሚታሰበው ፡ የቅጣት ፡ ማክበድን ፡ ወይም ፡ የማቅለልን ፡ ደንብ ፡ ባለመመልከት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ እንደ፡ ተደነገገው ፡ ሊወሰን ፡ የተቃጣውን ፡ የከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ መደብ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ሕጉ ፡ ለዚህ ፡ ጥፋት ፡ ተከታይ ፡ ወይም ፡ ተደራራቢ ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰን ፡

BACK



በቃጣ ፡ ጊዜ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ የሚታሰበው ፡ ከሁሉም ፡ ከባድ ፡ ለሆነው ፡ ቅጣት ፡ በተወሰነው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ነው ።

(፪) የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ጥፋተኛው ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ተግባሩን ፡ ከፈጸመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተደጋገመ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጊዜው ፡ የመጨረሻው ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ይታሰባል ። ተግባሩም ፡ ተራዝሞ ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚጸናበት ፡ ቀን ፡ የሚታሰበው ፡ የወንጀል ፡ ሥራው ፡ ከቆመበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ወንጀሉ ፡ ተደርጓል ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፡ ከጠባዮቹ ፡ አንዱ ፡ ጠባይ ፡ የወንጀሉ ፡ ውጤት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይርጋው ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ የሚጀመረው ፡ ወንጀሉ ፡ ውጤቱን ፡ ካገኘበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፳፱ ። የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታገድ ።

(፩) ክሱ ፡ እንዳይጀመር ፡ ወይም ፡ እንዳይቀጥል ፡ ጥፋተኛው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በሚያደርገው ፡ ተግባር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሕጋዊ ፡ ወይም ፡ ተግባራዊ ፡ መሰናክል ፡ እስከሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ ለጊዜው ፡ ታግዶ ፡ ይቈያል ።

እንዲሁም ፡ በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ነገሩ ፡ በዳኝነት ፡ በመታየት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የይርጋው ፡ መቈጠር ፡ ታግዶ ፡ ይቈያል ።

መሰናክሉም ፡ እንደ ፡ ተወገደ ፡ ወዲያውኑ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ መቈጠር ፡ ይቀጥላል ።

(፪) ስለ ፡ ክሱ ፡ መከታተል ፡ አቤቱታ ፡ እንዲቀርብ ፡ ማስፈለጉ ፡ በሕግ ፡ ተመልክቶ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ አቤቱታ ፡ አለመቅረቡ ፡ የይርጋውን ፡ መቈጠር ፡ አያግደውም ።

ቍ ፡ ፻፴ ። የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቋረጥ ።

ማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛው ፡ እንዲፈለግ ፡ የሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፤ ወይም ፡ መጥሪያ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉን ፡ ካደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ምርመራ ፡ ሁሉ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑን ፡ መታሰብ ፡ ያቋርጣል ።

የይርጋ ፡ ዘመን ፡ በተቋረጠ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መቈጠር ፡ ይጀምራል ።

የይርጋው ፡ ዘመን ፡ መቋረጥ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ አለው ፤ ለወንጀሉ ፡ ተካፋይ ፡ መሆናቸው ፡ ለታወቁት ፡ ላልታወቁትም ፡ ሁሉ ፡ መቋረጡ ፡ ይጸናባቸዋል ።

ቍ ፡ ፻፴፩ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ።

በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የደንበኛው ፡ ሕጋዊ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ አጠፌታ ፡ ባለፈ ፡

ጊዜና ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ሲሆን ፡ የዚሁ ፡ ግማሽ ፡ አልፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ‡ በወንጀሉ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የሚደረገው ፡ መከታተል ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ። ‡ [ቍ ፡ ፪፻፳፯ና ፡ ፪፻፳፰ ። ]

ቍ ፡ ፪፻፳፱ ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ መጽናት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

ስለ ፡ ጉዳት ፡ ማሻሻያ ፡ ካሣ ፡ አከፋፈል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ እንዲጸና ፡ የሚታሰበውን ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ የሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ከወንጀል ፡ ክስ ፡ ጋራ ፡ ቢቀርብም ፡ ባይቀርብም ፡ ይጸናል ፡ በሚያሰኝበት ፡ ሥርዐትና ፡ የጊዜው ፡ ውሳኔም ፡ ሆነ ፡ የይርጋው ፡ መጽናት ፡ በሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የጉዳይ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመራው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንበኛ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ክስ ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ሳይሆን ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ማቅረቢያ ፡ ጊዜ ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ ቀርቦ ፡ ሊታይ ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ችሎት ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ሊታይ ፡ ይገባዋል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## የቅጣት ፡ ይርጋ ።

ቍ ፡ ፪፻፴ ። መሠረቱና ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) የተወሰነው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተወሰኑት ፡ ጊዜያቶች ፡ ውስጥ ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱን ፡ የማስፈጸም ፡ መብት ፡ ስለሚቀር ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀለኛው ፡ ላይ ፡ ሊፈጸም ፡ አይቻልም ።

ለዋነኛው ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ለተጨማሪ ፡ ቅጣቶችና ፡ ለጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸም ፡ ጉዳዮችም ፡ ጭምር ፡ ይረጋል ።

(፪) የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ደንብ ፡ ለሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ የተወሰነ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በባለሥልጣን ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በአፈጻጸም ፡ ክፍል ፡ በማናቸውም ፡ ሹማምቶች ፡ ሁሉ ፡ ተከብሮ ፡ መጠበቅ ፡ ይገባዋል ።

የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ በይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ መጠቀስ ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸም ፡ ቢቀርም ፡ በተቀጪው ፡ የፍርድ ፡ ስሌዳ ፡ ላይ ፡ ተመዝግቦ ፡ መኖር ፡ አለበት ።

BACK



(፫) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነክ ፡ ለሆኑት ፡ ነገሮች ፡ የጠፋውን ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ መመለስን ፤ የጉዳትን ፡ ካሣና ፡ ኪሣራን ፡ የዳኝነትን ፡ ወጪ ፡ የሚመለከቱ ፡ ነገሮች ፡ በይርጋ ፡ የሚጸኑት ፡ የጊዜው ፡ ውሳኔ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፴፬ ። የጊዜው ፡ ውሳኔ ።

የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ውሳኔ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

(ሀ) ለሞት ፡ ፍርድ ፤ ለዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ለጠቅላላ ፡ ውርስ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ።

(ለ) ካሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ነጻነትን ፡ ለማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ ሓያ ፡ ዓመት ።

(ሐ) ካንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ነጻነትን ፡ ለመቀነስ ፡ ቅጣት ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ።

(መ) ለማንኛዎቹም ፡ ለሌሎች ፡ ቅጣቶች ፡ ሁሉ ፡ አምስት ፡ ዓመት ።

ቍ ፡ ፪፻፴፭ ። የቅጣት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ አቈጣጠር ።

(፩) ይርጋ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ መታሰብ ፡ የሚጀመረው ፡ ፍርድ ፡ የተወሰነበት ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚነቱን ፡ ካገኘበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ መፈጸም ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀጪው ፡ ይኸው ፡ ፍርድ ፡ እንዳይፈጸምበት ፡ ካመለጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ተቀጪው ፡ በፍርዱ ፡ መታገድ ፡ እንዲጠቀም ፡ ተደርጎለት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህም ፡ የፍርድ ፡ መታገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይርጋው ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ የሚታሰበው ፡ የቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲቀጥል ፡ ከታዘዘበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፪) ተደራራቢው ፡ ቅጣት ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ይርጋው ፡ ጊዜ ፡ አቈጣጠር ፡ ከሁሉም ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ ቅጣት ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ ይያዛል ። ቀላል ፡ የሆኑትም ፡ ቅጣቶች ፡ የይርጋ ፡ አቈጣጠር ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ በአንድነት ፡ ይታሰባል ።

ቍ ፡ ፪፻፴፮ ፡ የቅጣቱ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ ታግዶ ፡ የሚቈይበት ፡ ሁኔታ ።

የቅጣቱ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ ታግዶ ፡ የሚቈየው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(ሀ) የቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ሊፈጸም ፡ ወይም ፡ አፈጻጸሙ ፡ ሊቀጥል ፡ ባልቻለ ፡ ጊዜና ፡ ይኸውም ፡ መሰናከል ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፤

(ለ) ተቀጪው ፡ የፍርዱ ፡ መታገድ ፡ ጥቅም ፤ የአመክሮ ፡ ወይም ፡ የዕዳ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ተወስኖለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ እስካለቀ ፡ ድረስ ፤

BACK



(ሐ) ነጻነትን ፡ በማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ በማስፈጸም ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የግዞት ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ በመኖር ፡ ቅጣት ፡ ታስሮ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፪፴፯ ። የቅጣት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ የሚቋረጥበት ፡ ሁኔታ ።

የቅጣት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መታሰብ ፡ የሚቋረጠው ፡ የማስፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ በተሰጠው ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚደረግ ፡ ማናቸውም ፡ የቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያዘነብል ፡ ተግባር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ከተጀመረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፪፴፰ ። ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የቅጣት ፡ ይርጋ ።

ለመደበኛው ፡ ሕጋዊ ፡ ቅጣት ፡ ከተወሰነው ፡ የይርጋ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ የዚሁ ፡ የይርጋው ፡ ጊዜ ፡ አጋማሽ ፡ ተጨምሮበት ፡ ካለፈ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ የቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸም ፡ ውሳኔ ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ የሚሆነው ፡ ወንጀል ፡ አድራጊው ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚያስፈርድ ፡ ወንጀል ፡ በመሥራት ፡ አደገኛ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፻፪፴፬ ።]

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በተለይ ፡ የሚሰጥ ፡ ምሕረትና ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት ።

ቍ ፡ ፻፪፴፱ ፡ ምሕረት ።

(፩) በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ቅጣት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ምሕረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ። ወይም ፡ የቅጣቱ ፡ አፈጻጸምና ፡ ዐይነት ፡ በቀላል ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሊለወጥ ፡ ይቻላል ።
ምሕረት ፡ የመስጠቱ ፡ መብት ፡ አኳኋን ፡ በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ እንደተደነገገው ፡ ነው ።

(፪) ተፈጻሚ ፡ ለሚሆኑ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸሞች ፡ ሁሉ ፡ ለዋነኛና ፡ ለተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ለማናቸውም ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ ቢሆን ፡ ምሕረት ፡ ሊሰጥባቸው ፡ ይቻላል ። ምሕረት ፡ የሚሰጥበትም ፡ ድንጋጌ ፡ የአሰጣጡን ፡ ደንብና ፡ የሚጸናበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ።
ምሕረት ፡ ሲሰጥ ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ፍርድ ፡ አይፍቀውም ። ፍርዱም ፡ ከሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ጋራ ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ተመዝግቦ ፡ ይኖራል ።

BACK



ቍ ፡ ፻፱ ። የዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ (አምኒስቲ) ።

(፩) በዐዋጅ ፡ የሚሰጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምሕረት ፡ የጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ አስፈላጊነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ሲሆን ፡ ላንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀሎች ፡ ወይም ፡ ላንዳንድ ፡ ክፍል ፡ ወንጀለኞች ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ ግዴታ ፡ በዐዋጅ ፡ ጠቅላላ ፡ ምሕረት ፡ ለመስጠት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊፈቀድ ፡ ይቻላል ።

የአሰጣጡም ፡ ደንብ ፡ በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተደነገገው ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ዐይነት ፡ ምሕረት ፡ የሚሰጠው ፡ ሕግ ፡ በተወሰነ ፡ አኳኋን ፡ የምሕረትን ፡ ጉዳይ ፡ የሚጠቀሙበትን ፡ ሰዎችና ፡ የሚደርስበትን ፡ መጠን ፡ ይገልጻል ።

(፪) የወንጀልን ፡ ክስና ፡ ቅጣት ፡ የሚደመስሰው ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ወዲያውኑ ፤ በክስ ፡ የመከታተልን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ይሠርዛል ፡ ወይም ፡ ያቋርጣል ።

የቅጣቱ ፤ ፍርድ ፡ ተበይኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የወንጀሉ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትለው ፡ ነገር ፡ በምሕረቱ ፡ ይደመሰሳል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ፍርዱ ፡ እንዳልነበረ ፡ ተቈጥሮ ፡ ከወንጀል ፡ የፍርድ ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ይሠረዛል ።

ቍ ፡ ፻፱፩ ። በፍትሐ ፤ ብሔር ፡ በኩል ፡ ስለሚከፈል ፡ ካሣና ፡ ወጪ ።

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ የጠፋውን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የመመለስና ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የሚከፈለው ፡ ካሣና ፡ ኪሣራ ፡ በምሕረትና ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ አይነካም ።

(፪) የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ጉዳይ ፡ በሚፈቅዱት ፡ ሕጋዊዎች ፡ ዐዋጆች ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ የተደነገገ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ገና ፡ የሚከፈሉና ፡ ለመንግሥት ፡ የሚገቡ ፡ ኪሣራዎች ፡ በምሕረትና ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ ይሠረዛሉ ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ መሰየም ።

ቍ ፡ ፻፱፪ ። መሠረቱ ።

(፩) የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ ቅጣቱ ፡ በይርጋ ፡ የተወሰነለት ፡ ወይም ፡ በምሕረት ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ የቀረለት ፡ ተቀጪ ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሕጋውያን ፡ ግዴታዎች ፡ ከፈጸመ ፡ (ከሞላ) ፡ ከመቅጣቱ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ንጹሕ ፡ ስም ፡ እንዲመለስለትና ፡ እንዲሰየም ፡ የተወሰነበትም ፡ ፍርድ ፡ እንዲደመሰስለት ፡ ራሱ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

BACK



መሰየም ፡ የሚገኘው ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በይገባኛል ፡ መብት ፡ አይደለም ።

(፪) ተቀጪው ፡ ከመቀጣቱ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ንጹሕ ፡ ስም ፡ ለመመለስና ፡ ለመሰየም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ኖሮት ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪሉ ፡ ወይም ፡ ከዘመዶቹ ፡ አንዱ ፡ ጥያቄውን ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፶፫ ። ለመሰየም ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሁኔታዎች ።

መሰየምን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚፈቅደው ፡

(ሀ) ቅጣቱ ፡ የሚመለከተው ፡ ጽኑ ፡ እስራትንና ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ልማደኛነት ፡ በተደጋገመ ፡ ጥፋት ፡ ቅጣቱ ፡ ባንድ ፡ ጽኑ ፡ ግዞት ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ በመኖር ፡ የተለወጠ ፡ ቅጣትን ፤ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ከአገር ፡ የመውጣትን ፡ ወይም ፡ የጠቅላላ ፡ መወረስን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀጪው ፡ የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ ከፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ከተፈታበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በጥቂቱ ፡ ያሥር ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሌላው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ በጥቂቱ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነጻ ፡ የተለቀቀው ፡ ተቀጪ ፡ በመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተመርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በማናቸውም ፡ ጥፋት ፡ ሳይከሰስና ፡ አቤቱታም ፡ ሳይቀርብበት ፡ ቈይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችንም ፡ የሚመለከተውን ፡ ፍርድ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ነጻ ፡ የወጣው ፡ ተቀጪ ፡ የራሱ ፡ ችሎታና ፡ የጊዜው ፡ ምቾት ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠንና ፡ ራሱም ፡ ሊፈጽመው ፡ ይገባዋል ፡ ተብሎ ፡ በሚገመትበት ፡ ሁኔታ ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነበትን ፡ ካሣና ፡ ዳኝነት ፡ ማናቸውንም ፡ ኪሣራ ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ አጠናቆ ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፻፶፬ ። ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ፍርዱ ፡ ተፈጻሚነቱን ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ወዲያውኑ ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ቅጣቱ ፡ በይርጋ ፡ የታገደለት ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸምበት ፡ የቀረው ፡ የቅጣት ፡ ዘመን ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ንጹሕ ፡ ስም ፡ የመመለስ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

(፪) አንድ ፡ ተቀጪ ፡ የተወሰነበትን ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ በአመክሮ ፡ ተለቆ ፡ የተሰጠውን ፡ የአመክሮ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ በመልካም ፡ ጠባይ ፡ የዘለቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቅጣት ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ንጹሕ ፡ ስም ፡ ለማግኘት ፡ የጥያቄ ፡

BACK



ማቅረቡ ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ በአመክሮ ፡ ከተለቀቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፫) ስሙ ፡ እንዲታደስለት ፡ የሚጠይቀው ፡ ተቀጪ ፡ ሰብአዊ ፡ ክብርን ፤ ወታደራዊ ፡ ወይም ፡ ማኅበራዊ ፡ ሞያን ፡ በሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎቱ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ በደንቡ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ መሰየሙ ፡ ሊፈቀድለት ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፻፺፭ ። የመሰየም ፡ ውጤት ።

የተበየነውን ፡ ፍርድ ፡ የሚደመስስ ፡ የመሰየም ፡ ጕዳይ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ ነገሮች ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ።

(ሀ) ተቀጥቶ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ከተሰየመበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ወደፊት ፡ ተወስኖበት ፡ ከነበረው ፡ የመብትና ፡ የወግ ፡ የማዕርግ ፡ ማጣት ፡ ፍርድ ፡ ከተወሰነበት ፡ የችሎታ ፡ ማጣትና ፡ ከማዕርግ ፡ የመሻር ፡ ብይን ፡ ነጻ ፡ ሆኖ ፡ ሕዝባዊ ፡ መብቱን ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አስተዳዳሪነቱንና ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመያዝ ፡ ችሎታ ፡ ይኖረዋል ።

(ለ) የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ ከፍርድ ፡ የግል ፡ ሰሌዳ ፡ ይፋቅለታል ፤ ለወደፊትም ፡ እንዳልተፈረደበት ፡ ይቈጠራል ።

(ሐ) በጠላትነት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ያለፈውን፡ ቅጣት ፡ እንሥቶ ፡ መውቀስ ፡ ለሕዝባዊ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ለመርታት ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ወቃሹን ፡ በስም ፡ ማጥፋት ፡ ወንጀለኛነት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፻፺፮ ። ለመሰየም ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ ስላለመቀበልና ፡ ጥያቄውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

ለመሰየም ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ በቂ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጥያቄ ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም ።

## ቍ ፡ ፻፺፯ ። የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለ ፡ መሻር ።

ከተፈረደበት ፡ በኋላ ፡ እንዲሰየም ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ ተወስኖበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዲሰየም ፡ ሊፈቀድለት ፡ አይቻልም ።

## ፪ኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።
## ልዩ ፡ ክፍል ።

## ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ።
## በመንግሥት ፡ ላይ ፤ ባገርና ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፤

### አንቀጽ ፡ ፩ ።
### በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፤

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### በመንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፤

### ክፍል ፡ ፩ ።
### በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ደንብና ፡ በመንግሥቱ፡ያገር ፡ ውስጥ ፡ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
### በንጉሠ ፡ ነገሥቱ፡በሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፰ ። በንጉሠ፡ነገሥቱና ፡ በንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በእቴጌ ዪቱ ፡ ወይም ፡ በልጆቻቸው ፡ ነጻነት ፡ ወይም ፡ ጸጥታ ፡ ወይም ፡ በሰውነታቸው ፡ ወይም ፡ በጤንነታቸው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የጣለ ፡ ወይም ፡ ለመጣል ፡ ያቀደ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤—ካምስት ፡ እስከ፡ሓያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ፡በሚችል፡ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ይሀ ፡ በሰውነት ፡ ወይም ፡ በጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የመጣል ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀለኛው ፡ አሳብ ፡ በነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታና ፡ በተገለገለበት ፡ ዘዴ ፡ ዐይነት ፡ ከባድና ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጽኑ ፡ እስራቱ ፡ ቅጣት ፡ ካሥር ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ይደርሳል ።

(፪) አደጋ ፡ የመጣሉ ፡ ጉዳይ ፡ የታቀደው ፡ በሕይወታቸው ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

BACK



### ቍ ፡ ፪፻፵፱ ። በዙፋኑ ፡ አወራረስ ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ በመጣል ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፤ በዛቻ ፤ በመዶለት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የዙፋኑን ፡ አወራረስ ፡ ተርታ ፡ ለማፋለስ ፤ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ያቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

ካምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፤ ወይም ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ሲሆን ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፪፻፶ ። በሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በተቋቋሙ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በአድማ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፤

(ሀ) የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዐት ፡ ያፈረሰ ፡ ወይም ፡ ለማፍረስ ፡ የፈለገ ፡ ወይም ፡ ለማገድ ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) መንግሥቱን ፡ ወይም ፡ የተቋቋሙትን ፡ የሕግ ፡ አውጪ ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ ወይም ፡ የፍርድን ፡ ሥልጣን ፡ ያፈረሰ ፡ ወይም ፡ ለማፍረስ ፡ የፈለገና ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሆነ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፪፻፶፩ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሥልጣን ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ እርምጃ ፡ መሰናከል ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ የሕግ ፡ አውጪ ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሥራቸውን ፡ እንዳያከናውኑ ፡ የከለከለ ፡ ወይም ፡ ለመከልከልና ፡ ለማስገደድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ፡ ለመንጠቅ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፪፻፶፪ ። የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ሽብር ፡ በማድረግና ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጦርነት ፡ በማንሣት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ።

(ሀ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ላይ ፤ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፤ ወይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተቋቋሙት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ላይ ፡ ሕዝቡ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ እንዲነሣ ፡

በማድረግ ፡ ሁከት ፡ በማንሣት ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ሽፍቶች ፡ በማስነሣት ፡ ሽብር ፡ ያነሣ ፡ ወይም ፡ ለማንሣት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ያገር ፡ ተወላጆችን ፡ ወይም ፡ በአገር ፡ ነዋሪ ፡ የሆኑትን፡መሣሪያ ፡ በማስያዝ ፡ ወይም ፡ መሣሪያውን ፡ ይዞ ፡ እንዲነሣ ፡ በማደፋፈር ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ እንዲነሣ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ለማድረግ ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካ፭ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሚደርስ ፡ በጽኑ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ እንደዚህ ፡ ላለው ፡ ሽብር ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ የተባበረ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፫ ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ የግዛቱን ፡ ሙሉነት ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የሕዝቡን ፡ ያንድነት ፡ ኅብረት ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚያደርግ ፡ ተግባር ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ተከፍሎ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዐት ፡ ተነጥሎ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥርዐት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ተግባር ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፬ ። የማነሣሣት ፡ ተግባሮችን ፡ ግዙፍ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ማሰናዳት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ አንዱን ፡ ለመፈጸም ፡ የጦር ፡ ወታደሮችን ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ ሴረኞችን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ወይም ፡ ጥይቶችን ፡ ሥንቅን ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ ያዘጋጀ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ያስገባ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ግዙፍ ፡ የሆኑ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ያከማቸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፭ ። ያገርን ፡ ወሰንና ፡ የፖለቲካን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ —

(ሀ) ባገር ፡ ውስጥ ፡ ለመኖር ፡ የተደረጉትን ፡ስምምነቶች ፤ ወይም ፡ ያሉትን ፡ የደንብ ፡ አጠባበቅ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ማናቸውንም ፡ የማነሣሣትን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ሲል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ተደብቆ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ለመረዳዳት ፡ ወይም ፡ ለመተባበር ፡ የተደረጉትን ፡ የስምምነት ፡ ውሎች ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፤ ወይም ፡ ከደንበኞች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፈቃድ ፡ ሳይሰጠው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ለሆነ ፡ ድርጅት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ በሆነው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ በተለይም ፡ የምርመራ ፡ የብርበራ ፡ የሰውና ፡ የዕቃ ፡ መያዝ ፡ ወይም ፡ ያስተዳደርና ፡ የፍርድ ፡ አሠራር ፡ በሆነው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲሠራ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱንና ፡ መንግሥቱን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

ቍ ፡ ፪፻፶፮ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በመድፈር ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ።

(፩) የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የአልጋ ፡ ወራሹን ፡ ክብር ፡ የነካ ፡ የደፈረ ፡ ስማቸውን ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በማያንስ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተደረገው ፡ በመንግሥቱ ፡ ወይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በተቋቋመው ፡ በሕግ ፡ አውጪ ፡ በሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፫) ደፈረ ፤ ክብር ፡ ነካ ፤ ስም ፡ አጠፋ ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፤ ስለ ፡ ክብር ፡ መንካት ፡ የተወሰኑትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመመልከት ፡ ነው ። [ቍ፡፭፻፹ ፤ ፭፻፹፫ ።]

ቍ ፡ ፪፻፶፯ ። ያገር ፡ ምልክቶች ፡ የሆኑ ፡ ዓላማዎችን ፡ በመድፈር ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በንቀትና ፡ በማቃለል ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ስሜት ፡ በግልጽ ፡ የታወቀውን ፡ አንድ ፡ ያገር ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ምልክት ፡ ያሉትን ፡

እንዲሁም ፡ የየጠቅላይ ፡ ግዛቶቹን ፡ ምልክቶች ፡ አርማዎች ፡ በአደባባይ ፡ የነቀለ ፡ ያጠፋ ፡ ያዋረደ ፤ የደፈረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፰ ። ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ምልክቶች ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።**

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ለማናቸውም ፡ አገልግሎት ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ወይም ፡ ምልክት ፡ የተገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በመንግሥቱ ፡ የውጭ ፡ ኀይልና ፡ በመከላከያው ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፱ ። የመንግሥቱን ፡ ነጻነት ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ መንገድና ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡

(ሀ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስ ፡ ወይም ፡ ነጻነቱን ፡ የሚያጠፋ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ጕዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በገሩ ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ በሚያደርስ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ እንዲረዳ ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ እንዲቀላቀል ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

(ሐ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጸብ ፡ እንዲያነሣ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ በጸብ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ የሳበ ፤ አገሩ ፡ በጦር ፡ እንዲከበብ ፡ ወይም ፡ በጠላት ፡ እንዲያዝ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷ ። ያገሩን ፡ መከላከያ ፡ ኀይል ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ የሚያገለግለውን ፡ ወይም ፡ ለሀገሩ ፡ መከላከያ ፡ የሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ፤ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ስፍራዎችን ፤ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ መስጫ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ሁሉ ፤ የመመላለሻ ፡ መንገዶችን ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ማመላለሻ ፡ ተሽከርካሪ ፡ መኪናዎችን ፡ ማንኛዎችንም ፡ ጥበባዊ ፡ ሥራዎችን ፡ ወይም ፡ የተቋቋሙ ፡ ፋብሪካዎችን ፡ ማከማቻዎችን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ሁሉ ፡ ያለገባብ ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠትና ፡

BACK



በማፍረስ ፡ በማሰናከል ፡ ወይም ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እንዳያገለግሉ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ እን ዲያገለግሉ ፡ ወታደሮችን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ ወታደሮችን ፡ በመቅጠር ፡ ወይም ፡ ለጠላት ፡ መንግሥት ፡ እንዲቀጠሩ ፡ መንገድ ፡ በመፈለግ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ችሎታ ፡ እንዳለው ፡ ለጠላት ፡ የመንግሥት ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ በመቅጠር ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የጦር ፡ ወታደሩ ፡ የጦር ፡ አገልግሎቱን ፡ ከመፈጸም ፡ እንቢተኛ ፡ እንዲ ሆን ፡ ሽብር ፡ እንዲያነሣ ፡ ወይም ፡ እንዲከዳ ፡ በግልጽ ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ወይም ፡ የጦር ፡ ወታደርነት ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ከነዚህ ፡ ወንጀሎች ፡ አንደኛውን ፡ እንዲሠራ ፡ በማደፋፈር ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ የተንኰል ፡ መንገድ ፡ ላገሩ ፡ መከ ላከያ ፡ የተመደበውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ የጥንቃቄ ፡ ድርጅት ፡ ያሰናከለ ፡ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ ያፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስ ራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ሲሆን ፡ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ አሥጊ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ክዳት ።

ማናቸውም ፡ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋነት ፡ የተ ሰጠው ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያከናውን ፡ በግልጽ ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፤

(ሀ) የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በመያዝ ፡ ወይም ፤ በጸብ ፡ ሥራ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የተቃ ወመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ከሚያደርግ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ጥቅም ፡ ከሚሠራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ከተቋቋመ ፡ ክፍል ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ የስለላ ፡ ሥራዎችን ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ምስጢራዊ ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ጠላት ፡ እንዲመቸውና ፡ እንዲ ቀናው ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ዕቃዎችን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ፕላኖችን ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑ ፎችን ፡ ወይም ፡ ላገሩ ፡ መከላከያ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ነገ ሮች ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ለጠላት ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ ብአገልግሎቶችና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ ለጠላት ፡ በማቅ ረቢ ፡ ጠላትን ፡ የደገፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከአምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። የዲፕሎማቲክ ፡ ክዳት ።

(፩) ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፤ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ በግልጽ ፡ እንዲያከናውን ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ጥቅም ፡ በምስጢር ፡ እንዲጠበቅና ፡ እንዳይገለጽ ፡ የተደረገውን ፡ ማናቸውንም ፡ ምስጢር ፤ ሰነድ ፡ የመላላክ ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ለሕዝብ ፡ ላንድ ፡ መንግሥት ፡ ላንድ ፡ ወገን ፡ ላንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ የገለጸ ፤ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ ወሬውን ፡ ያስተላለፈ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ እንዲነገር ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ መልክተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ እንዲፈጽም ፡ የተላከበትንና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጥቅም ፡ ሊከራከርበትና ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ጉዳይ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ፀይነት ፡ እንዲሰናከል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ጸጥታውን ፡ ወይም ፡ ዋናኛ ፡ ጥቅሞቹን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ማስረጃዎች ፡ ሰነዶችንና ፡ ወይም ፡ ለእስረጂነት ፡ መሣሪያ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ያበላሸ ፡ ያጠፋ ፤ የደበቀ ፤ እንዲጠፋ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡—

እስከ ፡ ዐሥራ፡አምስት፡ዓመት ፡ ሊደርስ፡በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ አድራጎት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ አኗኗርና ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ፡ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

(፫) ጥፋተኛው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ቢያንስ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። የኤኮኖሚ ፡ የሀብት ፡ ክዳት ።

(፩) ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያከናውን ፡ በግልጽ ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፤—

(ሀ) ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ መከላከያ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥቅም ፡ በምስጢር ፡ የሚጠበቁትን ፡ የኤኮኖሚክ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውን ፡ የመላላክ ፡ ግንኙነቶች ፤ ውሳኔዎች ፡ የተደረጉ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ማስረጃዎች ፡ ሰነዶች ፡ ለሕዝብ ፡ ወይም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እንዲገለጹ ፡ ያደረገ ፤ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ወሬውን ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

BACK



(ለ) የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ተካባቾች ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ የሚያደርግ ፡ መንግሥት ፡ ባወጣው ፡ የብድር ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ወይም ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጽኑ ፡ እስራቱ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

(፪) ጥፋተኛው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። ከጠላት ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ( ጠላትን ፡ ስለ ፡ መርዳት ) ።

ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ እንዲጠብቅ ፡ ( ለኢትዮጵያ ፡ እንዲሠራ ) ፡ በኦፊሲየል ፡ የተሾመ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በተነሣ ፡ የጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመላው ፡ ወይም ፡ ከግዛትዋ ፡ ክፍል ፡ አንዱ ፡ በጠላት ፡ በተወረረበት ፡ ጊዜ ፡ የጠላትን ፡ አሳብ ፡ ለማቃናት ፡ በማቀድ ፡ በምክርም ፡ ሆነ ፡ በሥራ ፡ ጠላትን ፡ የደገፈ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በተለይም ፤

(ሀ) የሲቢል ፡ ወይም ፡ የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ሥራ ፡ በፍርድ ፡ በፖሊስ ፡ ወይም ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ በዘብ ፡ ጥበቃ ፡ በዕቃ ፡ ማመላለሻ ፤ ወይም ፡ በሌላ ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ክፍሎች ፡ በማከናወን ፡—

(ለ) ከጠላት ፡ ግዴታ ፡ ለማምለጥ ፡ የሚፈልጉትን ፡ አርበኞችና ፡ ስደተኞች ፡ በማጋለጥና ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፤

(ሐ) በፕሮፓጋንድ ፡ በጋዜጣና ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ክፍል ፡ በማገልገል ፡ የጠላት ፡ አሳብ ፡ እንዲቃና ፡ በመርዳት ፡ ያገለገለ ፤

(መ) በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ አብሮ ፡ በመሥራት ፡ የወራሪው ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሥራ ፡ እንዲቃናለት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። ስለላ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ላንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ላንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ክፍል ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥትና ፡ በድርጅቶች ፡ በክፍሎች ፡ ወይም ፡ በዜጎች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያደርስ ፡ ሁኔታ ፡—

(ሀ) የፖለቲካ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ የወታደር ፡ ወይም ፡ የኤኮኖሚ ፡ ስለላ ፡ ሥራ ፡ አገልግሎት ፡ አቋቁሞ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ እንዲያገለግል ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ አገልግሎት ፡ ሌላውን ፡ ቀጥሮ ፡ ያሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህንኑ ፡ የስለላ ፡ ጉዳይ ፡ የሰበሰበ ፤ ያስተላለፈ ፤ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፤ ወይም ፡ በምስጢር ፡ የሚጠበቀውንና ፡ በግልጽ ፡ እንዳይነገር ፡ የተደረገውን ፡ መረጃ ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በግል ፡ በተቋቋሙ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ለወኪሎቻቸው ፡ እንዲገለጽ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ስለላው ፡ የተደረገው ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያመጣ ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ወይም ፡ ስለላው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ የግል ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በግል ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የመንግሥቱን ፡ የውስጥና ፡ የውጭ ፡ ጸጥታ ፡ በቀጥታ ፡ በመጉዳት ፡ የተደረገ ፡ ስለላ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።—

ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ በሚያሠጋበት ፡ ጊዜ ፡ የፖለቲካ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ስለላ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ። እንዲያውም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ በሕይወታዊ ፡ ጥቅሙ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ይወሰንበታል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። ይህ ፡ የዋበቃው ፡ ውሳኔ ፡ ለጦር ፡ ጓደኞች ፡ መንግሥታትም ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ አንደኛው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ በተባበሩ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ክፍል ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸማሉ ። ይህም ፡ የሚፈጸመው ፡ ይህንኑ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ ለሚያደርግ ፡ መንግሥት ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። በዘወርዋራ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ስለሚቈጠር ፡ ማገዝና ፡ መርዳት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በእቴጌዪቱ ፡ ወይም ፡ በአልጋ ፡ ወራሹ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በመከላከያ ፡ ኀይሉ ፡ አቋቋም ፡ ወይም ፡ በመንግሥቱ ፡ የውስጥና ፡ የውጭ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የመጣል ፡ ዐቅድ ፡

BACK



ወይም ፡ ተግባር ፡ መዘጋጀቱን ፡ ሰምቶ ፡ ለባለሥልጣን ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አደጋው ፡ እንዳይደርስ ፡ አድራጊው ፡ ወይም ፡ አድራጊዎቹ ፡ እንዲያዙ ፡ የሚቻለውን ፡ ያላደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ያልቻለ ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እነዚህ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ለባለሥልጣን ፡ ለማስታወቅ ፡ ካለበት ፡ ግዴታ ፡ ውጭ ፡ ለመሆን ፡ ሲል ፡ የሥራውን ፡ ወዓም ፡ የሞያውን ፡ ምስጢር ፡ ሰበብ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

(፫) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በአገሩ ፡ የውስጥና ፡ የውጭ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ የማይበልጥ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፬) ያደጋውን ፡ መጣል ፡ ሙከራ ፡ ዝግጅት ፡ የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ ካጥፊው ፡ ወይም ፡ ካጥፊዎቹ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ የዝምድና ፡ ወይም ፡ የጠበቀ ፡ የፍቅር ፡ ግንኙነት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ ጉዳዮች ፡ ምክንያት ፡ ሊሆነው ፡ አይችልም ።
[ቁ ፡ ፹ ።]

<u>ቁ ፡ ፪፻፷፰ ። በወንጀል ፡ ተካፋይነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ የማነሣሣት ፡ ያባሪነትና ፡ የመርዳት ፡ ሙከራ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ። [ቁ ፡ ፷፯ ፡ (፪) ።]

<u>ቁ ፡ ፪፻፷፱ ። ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ምዕራፎች ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉት ፡ ሥራዎች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለማድረግ ፡ በመርዳት ፡ ወይም ፡ በመደገፍ ፡—

(ሀ) በንግግር ፡ በሥዕል ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ አማካይነት ፡ በግልጽ ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አንድ ፡ ክፍል ፡ ወንበዴዎች ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ካገር ፡ ውጪም ፡ ቢሆን ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ ያቋቋመ ፡ ከነዚህም ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ያደመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) እንደዚህ ፡ ባሉት ፡ ሽፍቶች ፡ ውስጥ ፡ በመግባት ፡ ወይም ፡ የነዚሁ ፡ ክፍል ፡ ከሆኑት ፡ ጋራ ፡ በመደባለቅ ፡ በሥራቸው ፡ የተባበረ ፡ ወይም ፡ ትእዛዛቸውን ፡ የተከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ካንድ ፡ ዝግጅት ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ወኪሎች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በምስጢር ፡ ግንኙነት ፡ የተሳሰረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) ሕዝቡን ፡ ለማሸበር ፡ እምነቱን ፡ ወይም ፡ ኀይሉን ፡ ለማፍረስ ፡ በሚችል ፡ ሁኔታ ፡ ያልተረጋገጡ ፡ የወሬ ፡ ምንጮችን ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆኑ ፡ የውስጠ ፡ ዘዴ ፡ ንግግሮችን ፡ በተደራጀና ፡ በታሰበ ፡ ዐይነት ፡ በንግግር ፡ በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በሥዕል ፡ የበተነ ፡ ወይም ፡ ያስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካንድ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ አድራጎት ፡ ሊያስከትል ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ አደጋ ፡ በተለይ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፰ ። ከባድ ፡ ሁኔታ ።

በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፤ በዙፋኑ ፡ አወራረስ ፤ ወይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አሠራር ፤ በነገሩ ፡ በውስጣዊውና ፡ በውጭ ፡ ጸጥታው ፤ በግዛቱ ፡ ሙሉነትና ፡ በፖለቲካ ፡ ሥልጣኑ ፡ ባገሩ ፡ የመከላከያ ፡ ጦር ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራው ፡ ወንጀልና ፡ ይህን ፡ ስለመሳሰለውም ፡ ጉዳይ ፡ ሕጉ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ የሚወስን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ የሚወስነው ፡—

(ሀ) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ የሽብር ፡ ሁከት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሁከትና ፡ ሽብር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ ጦርነት ፡ በሚያሠጋበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ በነገሩ ፡ በሚቀላቀልበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በጸጥታ ፡ መታወክ ፡ ምክንያት ፡ ዐዋጅ ፡ በተነገረበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ መኖራቸው ፡ በግልጽ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አድራጎቶቹ ፡ የታቀዱትና ፡ የተፈጸሙት ፡ ከአድማ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በያዙ ፡ ክፍሎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወንጀለኛው ፡ ወይም ፡ ወንጀለኞቹ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የፖሊቲካ ፡ ክፍሎች ፡ ባገኙት ፡ ሀብት ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በሚያገኙት ፡ እርዳታ ፡ ወይም ፡ ድጋፍ ፡ ወንጀሉን ፡ ሠርተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፡ በቦንብ ፡ በዲናሚት ፡ በሚፈነዳ ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችል ፡ ይህንኑ ፡ በመሳሰለ ፡ በማሸበሪያ ፡ መሣሪያና ፡ ዘዴ ፡ ሠርተውት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፱ ። ተደራራቢ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባሮች ።

(፩) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜና ፡ ጥፋቱም ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚያስፈርድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ወንጀለኛው ፡ የተሾመ ፡ ወይም ፡ የመሪነት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሆኖ ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ስሜት ፡ በግብዝነት ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ በመነሣሣት ፡

የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚሁ ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ በማጣመር ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ጥፋቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ እስከ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚያስወስን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ዳኛው ፡ ጥፋተኛውን ፡ ከሕዝባዊ ፡ መብቱ ፡ እንዲሻር ፡ ሊፈርድበት ፡ ይቻላል ።

(፫) እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ቅጣቱ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ይኸውም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ለወንጀሉ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ሁሉ ፡ ካገር ፡ እንዲወጣ ፡ ይወሰንበታል ።

(፬) የመከዳት ፡ የሰላይነት ፡ ወይም ፡ ምስጢር ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠት ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ መፈጸሚያ ፡ የሆኑት ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ መሣሪያዎች ፤ ዕቃዎች ፤ የመልክት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ወይም ፡ ማስረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ይወረሳሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። ንብረትን ፡ ስለ ፡ መውረስ ።

ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያከናውን ፡ በግልጽ ፡ የታዘዘ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ በመጣል ፡ ወይም ፡ አደጋን ፡ ለመጣል ፡ በመሞከር ፤

(ለ) ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ የዙፋኑን ፡ አወራረስ ፡ ተርታ ፡ ለማፋለስ ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ በማቀድ ፤

(ሐ) በቍጥር ፡ ፪፻፶፪ ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፶፱ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷፬ ፡ በተጻፉት ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ አንዱን ፡ በመሥራት ፤

ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚፈርደው ፡ ከዋናው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ አጣምሮ ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ በሕግ ፡ በተፈቀደው ፡ መጠን ፡ እንዲወረስ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺፯ ።]

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የተቃዋሚነት ፡ ሥራ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ሰላማዊ ፡ ግንኙነት ፡ ለማበላሸት ፡ በሚቻል ፡ አኳኋን ።

(ሀ) የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ውስጣዊ ፡ ፖለቲካ ፡ ሥርዐት ፤ ወይም ፡ የውስጥ ፡ ጸጥታው ፡ እንዲናወጽ ፡ በመሞከር ፡ አፍራሽ ፡ በሆነ ፡ ንቅናቄ ፡ በሐሰት ፡ በመወንጀል ፡ በጥላቻ ፡ ስብከት ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ ለማደፍረስ ፡ የሞከረ ፤

(ለ) በሚዋጉ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማትገባ ፡ ስለ ፡ መሆኑዋ ፡ የሚገልጽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚገባ ፡ የታወጀውን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ደንብ ፡ የተገለጸውን ፡ የመንግሥት ፡ ድንጋጌ ፡ የጣሰ ።

(ሐ) ጦርነት ፡ በሚያደርግ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የሁከት ፡ ሥራ ፡ ያነሣሣ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤—

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ይፈረድበታል ። ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለ ሚሠራ ፡ ወንጀል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ሰላማዊ ፡ የሆነ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ባለው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ገዢ ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ወይም ፡ ከወዳጅ ፡ መንግሥት ፡ ተልኮ ፡ የመልክት ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ ያንድ ፡ ሚሲዮን ፡ ሹም ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ በነጻነቱ ፡ በጸጥታው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የጣለ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አደጋ ፡ የመጣሉ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በሕይወቱ ፡ በሰውነቱ ፡ በጤናው ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጽኑ ፡ እስራቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥትን ፡ ግዛት ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የሰው ፡ ልጆችን ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ያሉትን ፡ የስምምነት ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በሆነ ፡ ውስጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ሁከት ፡ የማነሣሣት ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ሲል ፡ የገባ ፤

(ለ) ወይም ፡ በዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ የዚሁ ፡ መንግሥት ፡

ሥልጣን ፡ በሆነ ፡ ሕዝባዊ ፡ መብት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ያላገባብ ፡ በሆነ ፡ አድ ራጎት ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቊ ፡ ፪፻፷፯ ። የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥትን ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በመልክተኛነት ፡ ካሉት ፡ ከወኪሎቻቸው ፡ ባንዱ ፡ ወይም ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ መልክተኞች ፡ ከሆኑት ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ በተጠሪዎቹ ፡ ወይም ፡ በወኪሎቹ ፡ ሰውነት ፡ አማካይነት ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ወዳጅ ፡ የሆነውን ፡ መንግሥት ፡ በአደባባይ ፡ የሰደበ ፤ ስም ፡ ያጠፋ ፤ በሐሰት ፡ የወነጀለ ፡ ያዋረደ ፡ የደፈረ ፡ ወይም ፡ በንግግር ፡ ወይም ፡ በአድራጎት ፡ የበደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ነገሩም ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ በሐሰት ፡ የመወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሲሆን ፡ እስራቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ይሆናል ።

ቊ ፡ ፪፻፷፰ ። ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ምልክቶችን ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በጸብ ፡ ስሜት ፡ በጥላቻ ፡ መንፈስ ፤ በንቀት ፡ (በነቀፌታ) ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ በማናቸውም ፡ ስሜት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ሰላማዊ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ዓላማዎች ፡ (ምልክቶች) ፡ ይልቁንም ፡ የዚሁ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ በግልጽ ፡ ይዟቸው ፡ የሚሄደውን ፡ ዓላማዎች ፡ አርማዎች ፡ የቀደደ ፤ ያዋረደ ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቊ ፡ ፪፻፷፱ ። በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተቋቋሙትን ፡ ሥራዎች ፡ (እንስቲቱሲዮኖች ፡) ስለ ፡ ማዋረድ ።

ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነችበትን ፤ በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ በግልጽ ፡ የተቋቋመውን ፡ ድርጅት ፡ እንደራሴዎች ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ምልክታቸውን ፡ በአደባባይ ፡ የሚያዋርድ ፡ (የሚደፍር) ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቊ ፡ ፪፻፸ ። የውለታ ፡ መመለስ ፡ ሁኔታ ።

የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታትን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ለኢትዮጵያ ፤ ለንጉሠ ፡ ነገሥትዋ ፡ ከነዚህም ፡ ጋራ ፡ ላላቸው ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ በሕጋቸው ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ የጥበቃ ፡ አድራጎት ፡ ለሚያደርጉት ፡ መንግሥታት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ይህ ፡ የጥበቃ ፡ አድራጎት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የጦር ፡ ጓደኞች ፡ ወይም ፡ የተባበሩ ፡ ለሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ እንዲፈጸም ፡ ሲባል ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ፡ [ቍ ፡ ፪፻፸፯ ። ]

**ቍ ፡ ፪፻፹ ። ስለ ፡ ክስ ፡ አቀራረብ ።**

በዚህም ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ ወንጀል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ አሳሳቢነት ፡ መንግሥት ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ ተበደልሁ ፡ የሚለው ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ድርጅቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር ፡ ክስ ፡ አይቀርብበትም ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## በሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ መሠረታውያን ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፩ ። ዘርን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ፤ በሰብአዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በሰላም ፡ ጊዜም ፡ ሆነ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በቋንቋና ፡ በልማድ ፡ አንድ ፡ የሆነውን ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በፖለቲካ ፡ ተሳስሮ ፡ የተቋቋመውን ፡ የኅብረ ፡ ብሔርን ፡ ማኅበራዊ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለማጥፋት ፡ በማቀድ ፡ የጥፋቱን ፡ ሥራ ፡ በማቋቋም ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ አድራጎት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡—

(ሀ) ነፍስ ፡ የገደለ ፡ አካል ፡ ያቈሰለ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ክፍል ፡ አባሎች ፡ በአንደኛው ፡ አፍአዊና ፡ ውሳጣዊ ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እነዚሁ ፡ አባሎች ፡ በዘር ፡ እንዳይራቡ ፡ ወይም ፡ በሕይወት ፡ እንዳይኖሩ ፡ ለማገድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ዘዴ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ሕዝቡን ፡ ወይም ፡ ሕፃናቱን ፡ በኀይል ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ በማዛወር ፡ ወይም ፡ በመበተን ፤ ወይም ፡ ዝርያቸው ፡ እንዲበተን ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ እንዲጠፉ ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ በሚያደርስባቸው ፡ ሁኔታ ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ በግዞት ፡ በማስቀመጥ ፡ ማኅበራዊ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

BACK



## ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። በብሔራዊ ፡ በሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የጦርነት ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ጾብ ፡ ወይም ፡ በጠላት ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ መብትና ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ስምምነት ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ የሰብአዊ ፡ መብትን ፡ አጠባበቅ ፡ ሕግጋት ፡ ተቃዋሚ ፡ በመሆን ፡ በሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ሥራ ፡ በማዘጋጀት ፡ እንዲዘጋጅ ፡ በማዘዝ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ድርጅት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡—

(ሀ) የነፍስ ፡ መግደል ፤ ሰውን ፡ የማሠቃየት ፡ ተግባሮች ፡ ወይም ፡ ሰውን ፡ ርኀራኄ ፡ በሌለው ፡ ሁኔታ ፡ በማጉላላት ፡ የሕዋሳትን ፡ ሁኔታ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ለማጥናት ፡ በሚያደርገው ፡ ሥራ ፡ ጭምር ፡ ወይም ፡ በሰዎች ፡ መላ ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በጤንነታቸው ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአእምሮ ፡ ሥቃይ ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችል ፡ ሁኔታ ፡ ሰላማዊውን ፡ ሕዝብ ፡ የበደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሆን ፡ ብሎ ፡ ሕዝብን ፡ ችጋር ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ እንዳያገኝ ፡ ባለዋጋነቱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ በማክሠር ፤ ሐሰተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በማተም ፡ ወይም ፡ በተደራጀ ፡ ዐቅድ ፡ ገንዘብን ፡ በማዋረድ ፡ ሕዝብን ፡ በጠቅላላ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ በመጣል ፡ ኑሮውን ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ሕዝቡ ፡ በግድ ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ እንዲዛወር ፡ ወይም ፡ እንዲበተን ፡ በአፈሳ ፡ ከአገሩ ፡ አስወጥቶ ፡ በመውሰድ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ግዞት ፡ ስፍራ ፡ በመላክ ፡ ወይም ፡ በማሰር ፡ ዐውቆ ፡ በተደራጀ ፡ ዐቅድ ፡ ሰብስቦ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ያሰረና ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ያሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) በስለላ ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ በአስተዳደር ፡ በአድሚኒስትራሲዮን ፡ መሥሪያ ፡ ክፍሉ ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ተቀጥሮ ፡ እንዲያገለግል ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) በግዴታ ፡ ከትውልድ ፡ አገሩ ፡ ዜግነት ፡ ወደ ፡ ባዕድ ፡ አገር ፡ ጥገኝነት ፡ እንዲዛወር ፡ ወይም ፡ ሃይማኖቱን ፡ እንዲክድ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ረ) በአመንዝራነት ፡ ተግባር ፡ በብልግና ፡ ሥራ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ድፍረት ፡ እንዲባልግ ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሰ) በማስፈራራት ፡ ወይም ፡ በማስደንገጥ ፡ ወጀ ፡ በመያዝ ፡ የአፈሳ ፡ ቅጣት ፡ የጣለና ፡ የበቀል ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ቀ) ንብረቱን ፡ የወረሰ ፤ ሀብቱን ፡ ያፈረሰ ፤ ወይም ፡ ለራሱ ፡ ያደረገ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መብትና ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ላልሆኑ ፡ ጕዳዮች ፡ ሕዝቡ ፡ ለጠላት ፡ የሀብት ፡ እርዳታ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከመብቱ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሀብትን ፡ በመውሰድ ፡ ግፍ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡

ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፹፫ ፡ በቍስለኞች ፤ በበሽተኞችና ፡ በስጥመት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የጦርነት ፡ ወንጀል ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ —

(ሀ) ቍስለኞችን ፡ ሕመምተኞችንና ፡ የስጥመት ፡ አደጋ ፡ የደረሰባቸውን ፡ ወይም ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ረዳት ፡ ሠራተኞችን ፡ የነፍስ ፡ መግደል ፤ የማሠቃየት ፡ ተግባሮች ፡ ወይም ፡ ርኅራኄ ፡ በሌለው ፡ ሁኔታ ፡ ሰውን ፡ የመበደል ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ በአፍአዊና ፡ በውስጣዊ ፡ ሕዋሳታቸው ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥቃይ ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለጤና ፡ ጥበቃ ፡ ወይም ፡ ለእርዳታ ፡ መስጫ ፡ ክፍል ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ያፈረሰ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ዕቃዎቹን ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶቹን ፡ ሕግን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ለጦር ፡ ወታደሩ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነው ፡ ውጪ ፡ እነዚህን ፡ መጣሪያዎችና ፡ ዕቃዎች ፡ ያላገባብ ፡ የወሰደ ፡ ወይም ፡ ዝግጅቱ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፤ በተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። በታሠሩና ፡ በተጋዙ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ የጦርነት ፡ ወንጀሎች ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡—

(ሀ) በጦር ፡ ምርኮኛነት ፡ በታሰሩ ፡ ወይም ፡ በግዞት ፡ ቦታ ፡ በተቀመጡ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የነፍስ ፡ መግደል ፤ የማሠቃየት ፡ ተግባሮች ፡ ወይም ፡ ከሰብአዊ ፡ ፍጥረት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የሥቃይ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጸምባቸው ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ሥቃይና ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስባቸው ፡ የማድረግ ፡ ሥራ ፡ ያዘጋጀ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ያዘዘ ፤ ወይም ፡ ዝግጅቱን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በጠላት ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወይም ፡ የመረጃ ፡ ስለላ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ባስተዳደር ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፡ በተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፹፭ ። በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ የዘረፋ ፡ የየብስና ፡ የባሕር ፡ ወንበዴነት ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ ለጦር ፡ ወታደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሰበብ ፡ በማድረግ ፡ የየብስና ፡ የባሕር ፡ ወንበዴነትን ፡ የዘረፋን ፡ የገፋፊነትን ፡ የማፍረስን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ የንዋዮች ፡ መውሰድን ፡ ሥራ ፡ ያዘጋጀ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ያዘዘ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ አድራጎት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፤ በተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፯ ። ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ተግባሮች ፡ እንደኛውን ፡ ለመፈጸም ፤ እንዲፈጸም ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ አፈጻጸማቸውን ፡ ለመርዳት ፡—

(ሀ) በንግግር ፡ በሥዕል ፡ ወይም ፡ በጽሕፈት ፡ ሕዝቡን ፡ በአደባባይ ፡ ያነሣሣ ፡ ያደፋፈረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አንድ ፡ የወንበዴ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጓድ ፡ እንዲቋቋም ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ያደመ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ወይም ፡ የሥራው ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ አመራር ፡ ተደራቢ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝን ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፰ ። ለጠላት ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መጣስ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜና ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ መብትና ፡ ስለ ፡ ሰብአዊ ፡ መብት ፡ አጠባበቅ ፡ ተጠብቆ ፡ የቈየውን ፡ ደንብ ፡ ተቃዋሚ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡—

(ሀ) የተማረከውን ፤ መሣሪያውን ፡ ለምርኮ ፡ ያስረከበውን ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ለመከላከል ፡ የተሳነውን ፤ ወይም ፡ የመከላከሉን ፡ ተግባር ፡ በፈቃዱ ፡ የተወውን ፡ ጠላት ፡ የገደለ ፡ ወይም ፡ ያቈሰለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የሙት ፡ አካል ፡ ያጐደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ የጠላት ፡ ቍስለኛ ፡ በሽተኛ ፡ ወይም ፡ ሬሳ ፡ ላይ ፡ ለመስረቅ ፡ ወይም ፡ ለመግፈፍ ፡ የኀይል ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ከነዚሀ ፡ ተግባሮች ፡ አንዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያዘዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ፤ ወይም ፡ የወንጀሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆኑ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መታገዝ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በታወቁት ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ደንብ ፡ በግልጽ ፡ በተከለከሉ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ የውጊያ ፡ ሥራዎች ፡ ጠላትን ፡ የወጋ ፡ ወይም ፡ በነዚህ ፡ መሣሪያዎች ፡ ጠላት ፡ እንዲወጋ ፡ ትእዛዝ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከሦስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ አድራጎቱ ፡ ከባድነት ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፱ ። የጦር ፡ ማቆም ፡ ውልን ፡ ወይም ፡ የሰላም ፡ ስምምነትን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ የጦር ፡ ማቆም ፡ ወይም ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ በሚገባ ፡ መፈረሙን ፡ በግልጽ ፡ እያወቀና ፡ ትእዛዝ ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላ ፡ ውጊያው ፡ እንዲቀጥል ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አድራጎት ፡ የውሉን ፡ ስምምነት ፡ በመቃወም ፡ ዐውቆ ፡ ያፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ፤ ወይም ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺ ። የፋኖ ፡ አለቃ ፡ በመሆን ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜና ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ መብት ፡ በሚቃወም ፡ ሁኔታ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የጦር ፡ ሠራዊትነቱ ፡ ወይም ፡ (የተጨማሪ) ፡ የተደራቢ ፡ ጦር ፡ ባልደረባነቱ ፡ ሳይታወቅለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ ባገልግሎት ፡ ሥራዎቹ ፡ በዕቃ ፡ ማመላለሻ ፡ መሣሪያዎቹ ፡ ወይም ፡ በመገናኛ ፡ መሣሪያዎቹ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ተግባሩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፩ ። በቍስለኞች ፤ በበሽተኞችና ፡ በእስረኞች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጨከንና ፡ የሚገባቸውን ፡ ስለ ፡ ማጓደል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ መብት ፡ ሥርዐት ፡ በመጣስ ፡ የጦር ፡ ምርኮኛ ፡ ሆኖ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በግዞት ፡ የሚገኘውን ፡ በሽተኛ ፡ ቍስለኛ ፡ በጨካኝነት ፡ ያሠቃየ ፡ በሰውነቱም ፡ ላይ ፡ የማሠቃየት ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የተረጋገጡለትን ፡ መብቶቹን ፡ እንዳይጠቀምባቸው ፡ የከለከለ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፪ ። ፍትሕን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በጦርነት ፡ ወይም ፡ በወረራ ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ መብት ፡ አጠባበቅ ፡ ሥርዐት ፡ በመጣስ ፡ ብሔራዊ ፡ (ሰላማዊ) ፡ ሰው ፡ ቍስለኛ ፡ እስረኛ ፡ ወይም ፤ የጦር ፡ ምርኮኛ ፡ የሆነ ፡ ግዞተኛ ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ የዳኝነት ፡ ሥርዐትና ፡ ሚዛናዊ ፡ ፍርድን ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚያስችለውንና ፡ በሰብአዊ ፡ አስተዳደር ፡ እንዲኖር ፡ የሚ

BACK



ያደርገውን ፡ የራሱን ፡ መከላከያ ፡ መብት ፡ የሚያሳጣውን ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ ፍርድ ፡ እንዲያጣ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ እንዲከለከል ፡ ያዘዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። በኢንተርናሲዮናል ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሰብአዊ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ተቃዋሚ ፡ ሥራ ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ለሰብአዊ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ በተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ላይና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ የጨረቃ ፡ የአንበሳ ፡ ወይም ፡ የቀይ ፡ ፀሐይ ፡ ምልክት ፡ ባላቸው ፡ የእርዳታ ፡ መስጫ ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ማኅበሮች ፡ ሠራተኞች ፡ (ባልደረቦች) ፡ ወይም ፡ በነዚሁ ፡ ጥገኝነት ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ፡የተቃዋሚነት ፡ ሥራ ፡ የኀይል ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ በደል ፡ ያደረሰባቸው ፡ ወይም ፡ ያዋረዳቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ማኅበር ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ የጥገኞቹ ፡ ንብረት ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ መጓጓዣዎች ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ተካባቾች ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያፈረሰ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ የጣለባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። በኢንተርናሲዮናል ፡ አርማዎችና ፡ ምልክቶች ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ የሰብአዊ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበር ፡ ዓላማዎች ፡ ወይም ፡ ምልክቶች ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ የሰቀለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ዓላማ ፡ ወይም ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ በማንኛቸውም ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ ሕግ ፡ በታወቁ ፡ የመጠበቂያ ፡ ምልክቶች ፡ ይልቁንም ፡ የማሸበር ፡ ተግባሮችን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወይም ፡ ለማከናወን ፡ በነጭ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ያላገባብ ፡ የታገዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፪፻፺፭ ፡፡ በዕርቅ ፡ መልከተኛ ፡ ላይ ፡ ተቃዋሚ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መፈጸም ፡፡**

ማንም ፡ ሰው ፡ ከጠላት ፡ ወገን ፡ የዕርቅ ፡ መልክተኛ ፡ ወይም ፡ የዕርቅ ፡ ድርድር ፡ አሳብ ፡ አቅራቢ ፡ ሆኖ ፡ የሚመጣውን ፡ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ያጕሳሳ ፡ ያዋረደ ፡ (የበደለ) ፡ ወይም ፡ ያላገባብ ፡ በእስር ፡ ስም ፡ ይዞ ፡ ያስቀረ ፡ እንደሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ፡፡

## አንቀጽ ፡ ፫ ፡፡

## ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ወንጀሎች ፡፡

## በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡፡

### ምዕራፍ ፡ ፩ ፡፡

### ስለ ፡ ወታደር ፡ ወንጀል ፡፡

### ክፍል ፡ ፩ ፡፡

### በአገልግሎት ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡፡

**ቍ ፡ ፪፻፺፮ ፡፡ የማገልገል ፡ እንቢተኛነት ፡፡**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ የሚገደድበትን ፡ ለወታደርነት ፡ የመቀጠር ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ወታደር ፡ ውስጥ ፡ የማገልገል ፡ ተግባሩን ፡ ከመፈጸም ፡ ለማምለጥ ፡ ሲል ፡ በሚገባ ፡ የታዘዘውን ፡ ጥሪ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ወታደርነት ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በእንቢተኛነት ፡ ያልፈጸመ ፡ ወይም ፡ በየግንባሩ ፡ ቀርቤ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ አባል ፡ እንዲሆን ፡ በተነገረ ፡ በአደባባይ ፡ በተለጠፈ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ የተገለጸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ፡፡

(፪) ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በተነገረበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፪፻፺፯ ፡፡ ስለ ፡ አለመታዘዝ ፡፡**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በወታደርነት ፡ መመልመልን ፤ ወይም ፡ በጦር ፡ ወታደርነት ፡ ማገልገልን ፡ ባለመፈለግ ፡ ሳይሆን ፡ የጥሪ ፡ ትእዛዝን ፡ ያልፈጸመ ፤ ይልቁንም ፡ ወታደር ፡ ለመመልመል ፡ የሚደረገውን ፡ ጕብኝት ፡ የወታደር ፡ ፍተሻ ፡ የወታደርነት ፡ መለማመጃ ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ወታደር ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ ማናቸውንም ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ አለመታዘዝ ፡ የተፈጸመው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፺፰ ። የታዘዘውን ፡ አገልግሎት ፡ ለመፈጸም ፡ እንዳይችል ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በመላ ፡ ሰውነቱ ፡ ወይም ፡ በጤንነቱ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችል ፡ ሁኔታ ፡ አካሉን ፡ በማጕደል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ጥበብ ፡ በራሱም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አድራጎት ፡ ለጊዜው ፡ ወይም ፡ ለዘወትር ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ አገልግሎት ፡ እንዳይችል ፡ በሚያደርገው ፡ ሁኔታ ፡ አካሉን ፡ አጕድሎ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተነገረው ፡ ጕዳይ ፡ በባለጕዳዩ ፡ ፈቃድ ፡ በተመለከተው ፡ አድራጎት ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ላገልግሎት ፡ እንዳይችል ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ።

(፫) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። ከወታደር ፡ አገልግሎት ፡ ለማምለጥ ፡ የሚሠራ ፡ ማጭበርበር ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ለዘወትር ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ ከወታደር ፡ አገልግሎት ፡ ለማምለጥ ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሆኑትን ፡ የብሔራዊ ፡ (የሰላማዊ)፡ ወይም ፡ የወታደራዊ ፡ ሹማምቶችን ፡ የማታለል ፡ ዘዴ ፡ በመሥራት ፡ ይልቁንም ፡ ሐሰተኛ ፡ በሆነ ፡ ምስክርነት ፡ ወይም ፡ በሐሰተኛ ፡ ስም ፡ በመታገዝ ፡ ወይም ፡ በሽተኛና ፡ ሕመምተኛ ፡ በመምሰል ፡ ያታለለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በተነገረበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻ ። ስለ ፡ መክዳት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ያገልግሎት ፡ ተግባሩን ፡ እንዳይፈጽም ፡ ለማምለጥ ፡ በማሰብ ፡ የጦር ፡ ክፍሉን ፡ (የጦር ፡ ሰፈሩን ፡ ) ወይም ፡ የወታደርነት ፡ አገልግሎት ፡ ሥራውን ፡ ያለፈቃድ ፡ ትቶ ፡ የሄደ ፡ ወይም ፡ በፈቃድ ፡ ተለይቶ ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ያልተመለሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በተነገረበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
የጽኑ ፡ እስራቱ ፡ ቅጣት ፡ መነሻ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ። ወይም ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፩ ። ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መቅረት ።</u>

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ከወታደር ፡ አገልግሎቱ ፡ ለማምለጥ ፡ በማቀድ ፡ ሳይሆን ፡—
(ሀ) ያለፈቃድ ፡ ወይም ፡ አስገዳጅ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ የወታደር ፡ ክፍሉን ፡ ትቶ ፡ የሄደ ፡ ወይም ፡ ከወታደርነት ፡ ሥራው ፡ የራቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
(ለ) ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ ባልሆነ ፡ በማይበቃ ፡ ምክንያት ፡ ከተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።
(፪) በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስራቱ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ለመ ድረስ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፪ ። ሆነ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ጦር ፡ ተመልሶ ፡ ስላለመምጣት ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡—
(ሀ) ከክፍሉ ፡ ጦር ፡ ተቋርጦ ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ ወይም ፡ ባቅራቢያው ፡ ወደሚገኘው ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ሳይቀላቀል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
(ለ) ወይም ፡ ከተማረከ ፡ በኋላ ፡ የምርኮው ፡ እስራት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ወዲያውኑ ፡ ላንድ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ የወታደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ቀርቦ ፡ ሳያመለክት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ መደቡ ፡ ከመድረስ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ይቀጣል ፤ ወይም ፡ ይህን ፡ ጕድለት ፡ የፈጸመው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ለዘወትር ፡ ከመደቡ ፡ ለመለየት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

<u>ያገልግሎትን ፡ ሥልጣን ፡ ከመጠን ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ።</u>

<u>ቍ ፡ ፫፻፫ ። በማይገባ ፡ ከሥራ ፡ እንዲቀር ፡ ስለ ፡ መፍቀድ ።</u>

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የሥራ ፡ አገልግሎትን ፡ ወይም ፡ የተሰጠውን ፡ የሥራ ፡ መብት ፡ ከመጠኑ ፡ በላይ ፡ በማሳለፍ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ያገልግሎቱን ፡ ሥራ ፡ እንዲፈ ጽም ፡ ግዴታ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ከሥራው ፡ ተለይቶ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህም ፡ የሥልጣኑ ፡ ከመጠን ፡ ማለፍ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፤ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በተነገረበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

<u>ቁ ፡ ፫፻፬</u> ። የበላይ ፡ ሹም ፡ ስለሚፈጽመው ፡ የሥልጣን ፡ መተላለፍ ።

በጦር ፡ ወታደርነቱ ፡ ሁኔታ ፡ የተሰጠውን ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣን ፡ ከመጠን ፡ በማሳለፍ ፡ የተገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሹመቱ ፡ በማይፈቅድለት ፡ ሥልጣን ፤ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በጠቅላላው ፡ የመቀጫ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ አድራጎቱ ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ ካላስከተለ ፡ በቀር ፡ በወታደር ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

<u>ቁ ፡ ፫፻፭</u> ። በበታች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ዛቻና ፡ የእጅ ፡ እልፊት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ታዛዡን ፡ ወይም ፡ የበታቹን ፡ የዛተበት ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ እልፊት ፡ የመታው ፡ ወይም ፡ የማሠቅየትና ፡ የኀይል ፡ ተግባር ፡ የፈጸመበት ፤ ወይም ፡ በሚያዋርድ ፡ ሁኔታ ፡ ያጕላላው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ ይህን ፡ ለመፈጸም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ሠርቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራት ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## <u>በገልግሎት ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።</u>

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### <u>ደንብንና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።</u>

<u>ቁ ፡ ፫፻፮ ። በጠቅላላው ፡ ያገልግሎት ፡ ትእዛዞችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።</u>

(፩) በየብስ ፡ በባሕርና ፡ በአየር ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ደንብ ፡ ላይ ፤ ከተመለከተው ፡ ውጪ ፡ ደንቦችን ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ያገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ትእዛዞችን ፡ ባለመጠበቅና ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በመጣስ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ [ ቁ ፡ ፯፻፵፯ ። ]

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፤ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታወጀ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

(፫) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በቸልተኛነት ፡ ሲሆን ፡ በመጀመሪያው ፡ መሥመር ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አድራጊው ፡ የሚቀጣው ፡ በሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (በዲስፕሊን ፤) ነው ። በሁለተኛው ፡ መሥመር ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፯ ። ለሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ጕዳይ ፡ በሚሰጥ ፡ መረጃ ፡ ላይ ፡ ዐውቆ ፡ በማስ ቀረትና ፡ ያልተካከለ ፡ መረጃ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በሥራው ፡ ደረጃ ፡ ወይም ፡ በወታደራዊ ፡ አገልግሎቱ ፡ በትክክል ፡ መግለጽ ፡ ተግባሩ ፡ በመሆኑ ፡ በሚያቀርበው ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ በሆነው ፡ ራፖር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ጕዳይ ፡ የሆነ ፡ ሰነድ ፡ በመመዝገብ ፡ ጕዳይ ፡—

(ሀ) የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ እውነተኛውን ፡ ጕዳይ ፡ ዐውቆ ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ ሳይገልጽ ፡ የቀረ ፤ ወይም ፡ የርሱ ፡ መተማመኛ ፡ ፊርማ ፡ እንደ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሊያገለግል ፡ በሚችልበት ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ቍጥር ፡ ሳይሞላ ፡ ዐውቆ ፡ በነጭ ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የማድረግ ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ ዘንግቶ ፡ ቅጣትን ፡ በሚያስከትል ፡ ቸልተኛነት ፡ የሥራ ፡ ጕዳይ ፡ መግለጫውን ፡ ራፖሩን ፡ ወይም ፡ የማረጋገጫ ፡ መግለጫውን ፡ ሳይጽፍ ፡ ወይም ፡ ሳይልክ ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የተሰጠውን ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ ለማራዘም ፡ በማሰብ ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሆነው ፡ ሹም ፡ እውነቱን ፡ የደበቀ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ ማረጋገጫ ፡ ቃል ፡ የሰጠ ፡ ወታደር ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ይህ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህም ፡ ጥፋት ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራቱ ፡ ውሳኔ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፰ ። በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ስለ ፡ መስከር ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በጦር ፡ ወታደርነት ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ እየደጋገመ ፡ የሰከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) ወይም ፡ ሰክሮ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐቱን ፡ ያደፈረሰ ፡ ወይም ፡ ሕዝቡን ፡ የበጠበጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የሰከረ ፡ ሰው ፡ በስካሩ ፡ ምክንያት ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ዎቹ ፡ የዛተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

በራሱ ፡ ጕድለት ፡ ባመጣው ፡ ጥፋት ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ በማያስጠይቅ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያቈሰለ ፡ ወይም ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠቅላላው ፡ የቅ ጣት ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈረድበታል ። [ቍ ፡ ፶ ። ]

## ቍ ፡ ፫፻፱ ። ከሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (ከዲስፕሊን) ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ያለፈቃድ ፡ ከጦር ፡ ሰፈሩ ፡ ከወታደር ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ከወታ ደር ፡ ምሽግ ፡ የሄደ ፡ የሸሸ ፡ ወይም ፡ ያለትእዛዝና ፡ ያለፈቃድ ፡ እንዳይደርስ ፡ እተከለከለበት ፡ ስፍራ ፡ የተገኘ ፡ ወይም ፡ ከተፈቀደለት ፡ ሰፈር ፡ ወሰን ፡ ውጭ ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በጸብ ፡ በድብድብ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ አድርራጎት ፡ እንዲ ተው ፡ አንድ ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ወይም ፡ ሹም ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በእንቢ ተኛነት ፡ የተቃወመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በሆስፒታል ፡ በተመላላሽ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ሁኔታውን ፡ ለማባስ ፡ በሚችል ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ የመታከሚ ያው ፡ ጊዜ ፡ የተራዘመ ፡ እንዲሆን ፡ ሲል ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ያልጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ በንግግር ፡ በንቀት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በአድራጎት ፡ የወታደርን ፡ መልካም ፡ አስተዳደር ፡ ደንብና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያበላሽ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፲ ። በበላይ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የስድብ ፡ የዛቻና ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ወንጀል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ አንዱን ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ የሰደበው ፡ የዛተበት ፡ ያዋላላው ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ እልፊት ፡ የመታው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ዛቻውና ፡ የእጅ ፡ እልፊቱ ፡ ከኀይል ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ተደራቢ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣ

ሪያ ፡ አደገኛ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ መሣሪያ ፡ አማካይነት ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተደረገው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በመጀመሪያው ፡ ሁኔታ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እስራቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፤ በሁለተኛው ፡ ሁኔታ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ጽኑ ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፲፩ ። ለበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ አለመታዘዝ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የወታደር ፡ ሹም ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ያልፈጸመ ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ አገልግሎቱን ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ትእዛዝ ፡ ከመፈጸም ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝም ፡ በቃል ፤ በጽሑፍ ፡ በምልክት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ በቀጥታም ፡ ለራሱ ፡ ቢሰጥ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ለሚገኝበት ፡ ክፍለ ፡ ጦርም ፡ ቢሰጥ ፡ በእንቢተኛነት ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ የክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንቢተኛውም ፡ ቍርጠኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

ወንጀሉም ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ የተደረገውም ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፲፪ ። አድማ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ከሌሎች ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ በመሰብሰብ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ባንድ ፡ ሹም ፡ ባንድ ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ የወታደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ ዛቻ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ የግርግር ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የግርግሩም ፡ ውጤት ፡ አለመታዘዝን ፡ ሽብርን ፡ ያስከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ግርግሩ ፡ የተፈጸመው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በተነገረበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡

እስራት ፡ ነው ። ወይም ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ነው ።

(፫) የግርግሩ ፡ መሪዎች ፡ ወይም ፡ የሥራው ፡ አደራጆች ፡ በተለይ ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምባቸዋል ። [ቍ ፡ ፹፩ ፡ (መ) ።]

**ቍ ፡ ፫፻፲፫ ። ግርግር ፡ ለማንሣት ፡ ስለሚደረግ ፡ አድማ ፡ ወይም ፡ስምምነት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ግርግር ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወይም ፡ የሽብር ፡ ንቅናቄ ፡ ለማንሣት ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ በመደረብ ፡ የተደለቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፬ ። በተካፋይነት ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ።**

ያደጋ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ ዐዋጅ ፡ ወይም ፡ ጦርነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ግርግር ፡ የማነሣሣትና ፡ የግብረ ፡ አበርነት ፡ ሙከራ ፡ ያስቀጣል ። [ ቍ ፡ ፳፯ ፡ (፪) ። ]

**ቍ ፡ ፫፻፲፭ ። በዘብ ፤ በዘብ ፡ ጠባቂና ፡ በፈታሽ ፡ ዘብ ፡ (ፓትሩይ) ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።**

ሥራውን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ ዘብ ፡ በዘብ ፡ ጠባቂ ፡ በፈታሽ ፡ ዘብ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ያለመታዘዝ ፤ ስድብ ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ዘብ ፤ በዘብ ፡ ጠባቂ ፡ በፈታሽ ፡ ዘብ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ የኀይል ፡ ሥራና ፡ የግርግር ፡ ተግባሮች ፡ ቅጣት ፡ ባንድ ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የበላይ ፡ አዛዥ ፡ በሆነ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ያስቀጣል ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

### የዘብ ፡ ተረኛንና ፡ ለዘብ ፡ የተሰጠውን ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚመለከት ፡ ወንጀል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፮ ። የዘብ ፡ ወንጀል ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በራሱ ፡ ፈቃድም ፡ ሆነ ፡ በቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ በሚያስቀጣ ፡ አለመጠንቀቅ ፡ በስካር ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ የዘብ ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ በማያስችለው ፡ ሁኔታ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) ወይም ፡ የዘብ ፡ ሥራውን ፡ ያለፈቃድ ፡ የተወ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ተረኛ ፡ ሳይ ተካለት ፡ ከሥራው ፡ ላይ ፡ የታጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ሆኖ ፡ ዐውቆ ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ <u>፫፻፲፯</u> ። የወታደርን ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ለመደበኛ ፡ ዘብ ፤ ዘብ ፡ ለቆመ ፡ ወታደር ፤ ለዘብ ፡ ፍተሻ ፡ ጓድ ፡ ወታደሮች ፡ ለአጃቢ ፡ ወታደሮች ፡ ወይም ፡ ለማናቸውም ፡ ይሀን ፡ ለመሳ ሰለ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የተሰጠውን ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ተግ ባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቢሆንም ፡ ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፤

(ሀ) የኤሌክትሪክን ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ መብራትን ፡ የመስጠት ፡ ድርጅት ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ በግድብ ፡ በውሃ ፡ ማገጃ ፡ በውሃ ፡ መከተሪያ ፡ በመርከብ ፡ መጠጊያ ፡ በወደብ ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ ክፍል ፡ ባሉ ፡ በመጠባበቂያ ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ በድልድዮች ፡ በሸለቆ ፡ መሸጋገሪያዎች ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ባላቸው ፡ መተላለፊያዎች ፡ ፊት ፡ ሲሆን ፤

(ለ) መርከቦች ፡ መልሕቆችን ፡ ጥለው ፡ በሚቆሙበት ፡ ቦታ ፡ በሞተር ፡ በሚን ቀሳቀሱ ፡ መሣሪያዎች ፡ በባቡሮች ፡ ወይም ፡ በተሽከርካሪዎች ፡ ማከማቻ ፡ በጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ጥይት ፡ የሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ ነዳጆች ፡ ወይም ፡ የስንቅ ፡ ዕቃዎች ፡ በሚከማቹበት ፡ ቦታ ፡ ፊት ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ወይም ፡ ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ ጠረፍ ፡ ጠባቂ ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ እስራቱ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ ይሆናል ።

(፫) ነገሩ ፡ ከባድ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚ ችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ። ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አም ስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

ቍ ፡ <u>፫፻፲፰</u> ። ለዘብ ፡ የተሰጠውን ፡ ምስጢራዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መግለጽና ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በአገልግሎት ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በክዳት ፡ አሠራር ፡ ሳይሆን ፡

BACK



(ሀ) የልፍ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የምስጢራዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ቃሎችን ፡ ሊነግረው ፡ ተገቢ ፡ ላልሆነ ፡ ሰው ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ምስጢሩ ፡ ሊገለጽለት ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ከተቀበለው ፡ የልፍ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የምስጢራዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ቃሎች ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰለውን ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ቃል ፡ ዐውቆ ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚቀጣው ፡ በሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አግባብ ፡ ነው ።

(፫) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ ያደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አፈጻጸሙ ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ዐውቆ ፡ ሕግን ፡ በመጣስ ፡ ተሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## ታማኝነትን ፡ በማጓደል ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፫፻፲፱ ። በዕቃዎች ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መጠቀምና ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማባከን ።

(፩) ማንም ሰው ፡—

(ሀ) ከመጠኑ ፡ ባለፈ ፡ ሁኔታ ፡ በዕቃዎች ፡ የተገለገለ ፡ ያዋሰ ፡ የሸጠ ፡ ለሌላ ፡ ያሳለፈ ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ያስያዘ ፤

(ለ) የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ጥይቶችን ፡ የወታደር ፡ ትጥቆችን ፡ ዕቃዎችን ፡ ወይም ፡ መሣሪያዎችን ፡ ተሽከርካሪ ፡ መኪናዎችን ፡ እንስሶችን ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ የተሰጡትን ፡ ወይም ፡ የተረከባቸውን ፡ ወይም ፡ በሥራውና ፡ በወታደርነት ፡ ሹመቱ ፡ ምክንያት ፡ ሊያገኛቸው ፡ የሚችላቸውን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ሀብቶች ፡ ያጠፋ ፡ የጣለ ፤ አደጋ ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ያደረገ ፡ ያባከነ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

አንድ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ድንጋጌ ፡ የማይፈጸምበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የወታደር ፡ አገልግሎት ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ የሹመቱ ፡ ጊዜ ፡ ያለፈም ፡ ቢሆን ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጽኑ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ። ነገሩም ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጽኑ ፡ እስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፫፻፳ ። የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የወታደርን ፡ ሥንቅ ፡ ማከማቻ ፡ ማጋዘን ፡ የመጠበቅ ፡ ሥራውን ፡ የመምራት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ ወይም ፡ የሥንቅ ፡ የገንዘብ ፡ የዕቃ ፡ ወይም ፡ የማናቸውም ፡ ሀብት ፡ አከፋፋይነት ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቶት ፡—

(ሀ) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ያለመብቱ ፡ የተጠቀመበትን ፡ ሀብቱን ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ያሳለፈና ፡ የደበቀ ፡ ያጐደለ ፡ ወይም ፡ ዋጋውን ፡ የቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ማናቸውንም ፡ ጥቅም ፡ የሚቀበል ፡ ወይም ፡ እንዲሰጠው ፡ የሚያስገድድ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ባንድ ፡ የወታደር ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ሰፈር ፡ የሰፈር ፡ ሆቴል ፡ በወታደሮች ፡ መሰብሰቢያ ፡ ወይም ፡ በወታደር ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጠውን ፡ ማናቸውንም ፡ ምግብ ፡ ሥንቅ ፡ የወታደር ፡ ትጥቅ ፡ የሺያጭ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ በመግዛት ፡ በመሸጥ ፡ ወይም ፡ በማከፋፈል ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ በማይገባ ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

አድራጎቱ ፡ እንደ ፡ እምነት ፡ ማጕደል ፡ በተንኰል ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፤ እንደ ፡ ጉቦ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በማስገደድ ፡ እንደ ፡ መጠቀም ፡ ሆኖ ፡ ለነዚሁ ፡ በተደነገጉት ፡ ሌላ ፡ የመቀጮ ፡ ውሳኔ ፡ የማይቀጣ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሁኔታውም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የጽኑ ፡ እስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጸጥታ ፡ (ሞራል) ፡ ሕሊናና ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለሚያደርሱ ፡ ወንጀሎች ።

ቊ ፡ ፫፻፳፩ ። በአደጋ ፡ ጊዜ ፡ የማስጠንቀቅን ፡ ተግባር ፡ ስላለመፈጸም ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ያደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ፈጣን ፡ የሆነ ፡ የወታደር ፡ ጥንቃቄ ፡ ሊደረግበት ፡ የሚገባው ፡ አደጋ ፡ ሊደርስ ፡ መቃረቡን ፡ እያወቀ ፡ ላለቃው ፡ ላንድ ፡ የወታደር ፡ የበላይ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ክፍል ፡ የወታደር ፡ አዛዥ ፡ ሳያስታውቅ ፡ ሳያስጠነቅቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የመከዳትን ፡ የስለላን ፡ የወታደርን ፡ ግርግር ፡ ወይም ፡ የመኮብለልን ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ አደጋው ፡ መታቀዱን ፡ አለማስታወቅ ፡ ለዚሁ ፡ ጕድለት ፡ በተደነገገው ፤ ጠቅላላ ፡ ውሳኔ ፡ ያስቀጣል ። [ ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። ]

ቍ ፡ ፫፻፳፪ ። አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የጸጥታ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላለማድረግ ።

(፩) በጦር ፡ ሠራዊት ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ወይም ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በወታደር ፡ ሥራ ፡ መለማመጃ ፡ ወይም ፡ ያገልግሎት ፡ ጕዳይ ፡ በሚመለከት ፡ በማናቸውም ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የሰዎችንና ፡ የእንስሳትን ፡ ሕይወት ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ አላፊነት ፡ እንዲጠበቁ ፡ ባደራ ፡ የተሰጡትን ፡ የዕቃ ፡ ማከማቻዎች ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰፈሮች ፡ የተቋቋሙ ፡ ሥራዎች ፡ የሥራ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ በሚገባ ፤ እንዲጠበቁ ፡ አስፈላጊውን ፡ የጥንቃቄ ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያስብበት ፡ የሚገባውን ፡ የመልካም ፡ አጠባበቅ ፡ ሥርዐት ፡ ሳያዘጋጅ ፡ በመቅረቱ ፤ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ አደጋ ፡ እንደሚደርስባቸው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አጥፊው ፡ ያደረገው ፡ በቸልተኛነት ፡ በነዘኅላልነት ፡ ወይም ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተግባሩ ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (የዲስፕሊን) ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፤ ይቀጣል ።

(፫) ወንጀሉ ፡ የተደረገው ፡ ያደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፤ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያላስጠነቀቀውም ፡ ሆነ ፤ ብሎ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፳፫ ። ሐሰተኛ ፡ ያደጋ ፡ ምልክት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በጦር ፡ ወታደር ፡ ጕዞ ፡ ወይም ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ወይም ፡ በሰፈር ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በአይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይልቁንም ፤ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ በመምዘዝ ፡ ወይም ፡ በመተኰስ ፡ ከበሮ ፡ በመምታት ፤ ወይም ፡ ጥሩምባ ፡ በመንፋት ፡ በምልክቶች ፡ በጩኸቶች ፡ በንቅናቄዎች ፡ ወይም ፤ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ በመገልገል ፡ ሐሰተኛ ፡ ያደጋ ፡ ምልክት ፡ የሰጠ ፤ እንደ ፡ ሆነ ፤
በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ ያደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የተደረገ ውም ፡ ለከዳት ፡ ተግባር ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስወስን ፡ ጉዳይ ፡ የሌለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራት ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

(፫) ያደጋው ፡ ምልክት ፡ የተሰጠው ፡ በቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ቅጣት ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችል ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለመጀመሪያው ፡ ጉዳይ ፡ እስራቱ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለሁለተኛው ፡ ጉዳይ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፫፻፳፩ ። የጦር ፡ ወታደርን ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ማስቈረጥ ።

(፩) የወታደር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ በውጊያ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከውጊያ ፡ ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ሁኔታ ፡ ይልቁንም ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይ ነት ፡ ግንባሩን ፡ በማጠፍ ፡ (በመሸሽ) ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ የጦር ፡ ትጥቁን ፡ ወይም ፡ ጥይቶቹን ፡ በመጣል ፡ በተዋጊው ፡ ጦር ፡ መካከል ፡ ፍርሀትን ፡ በማሰራ ጨት ፡ ወይም ፡ ብጥብጥንና ፡ ሁከትን ፡ በማስነሣት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ መጥፎ ፡ ውጤት ፡ እንዳይኖረው ፡ ለማገድ ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቅበትን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሳያ ደርግ ፡ ወይም ፡ እንዲሻሻል ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ ሳይዝ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉና ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደሚሆን ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፫፻፳፪ ። ፈሪነት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ፊት ፡ ሆኖ ፡ በመፍራት ፡—

(ሀ) የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ለማንሣት ፡ ወይም ፡ በመሣሪያው ፡ ሊሠራበት ፡ ያልፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የተደበቀ ፤ የሸሸ ፡ ወይም ፡ የተሰጠውን ፡ የውጊያ ፡ ቦታ ፡ ያለፈቃድ ፡ የለ ቀቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ጓደኞቹ ፡ ወይም ፡ ጭፍሮቹ ፡ የሱን ፡ ምሳሌ ፡ እንዲከተሉ ፡ ያነሣሣ ፡ እንደሆነ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊደርስ ፡ በሚ ችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፳፫ ። ለጠላት ፡ እጅን ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ማናቸውም ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ አዛዥ ፡—

(ሀ) በውጊያ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ፊት ፡ በጦር ፡ ወታደር ፡ ተግባሩ ፡

ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ ሳያደርግ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎቹን ፡ ያስረከበ ፡ የዕርቅ ፡ ድርድር ፡ መልክተኛ ፡ የላከ ፡ ወይም ፡ ለመማረክ ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማን ፡ ያንጠለጠለ ፡ ወይም ፡ ከጭፍሮቹ ፡ ጋራ ፡ ለጠላት ፡ እጁን ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሊድን ፡ የሚችለበትን ፡ መንገድ ፡ ፈልጎ ፡ የተቻለውን ፡ ተግባር ፡ ሳይፈጽም ፡ በአላፊነቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መርከብ ፡ አይሮፕላን ፡ የመዋጊያ ፡ ታንክ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለጠላት ፡ ትቶ ፡ የሄደ ፡ የለቀቀ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ ለጠላት ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የተቻለውን ፡ ያህል ፡ የመከላከል ፡ ጉልበቱን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሳያደርስ ፡ ትልቅ ፡ ምሽግ ፡ የጦሩን ፡ ስፍራ ፡ እርዱን ፡ የውጊያውን ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ የተመሸገውን ፡ የውጊያ ፡ ስፍራ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ የአይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ለጠላት ፡ የለቀቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። ምንም ፡ ያልጐደላቸውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) ማንም ፡ ወታደር ፤ ወይም ፡ የወታደር ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ለጠላት ፡ እንዳያገለግሉ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለውን ፡ ተግባር ፡ ሳይፈጽም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ዕቃ ፡ ቤቶችን ፡ ቤቶችን ፡ የወታደር ፡ ሰፈርን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ማረፊያ ፡ ቤቶችን ፤ ጥይቶችን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ወይም ፡ ለጦርነት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ ድልድዮችን ፡ የሽቦ ፡ መሸጋገሪያ ፡ የብረት ፡ መንገዶችን ፡ ሀዲዶችን ፡ ወይም ፡ ሳገቱ ፡ መከላከያ ፡ የሆኑትን ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያላቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ሳያፈርስ ፡ ሳያቃጥል ፡ ሳያጠፉ ፡ ወይም ፡ ካገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ሳያደርግ ፡ ለጠላት ፡ የተወ ፤

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እሥራት ፡ ቢያንስ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

## የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። የጦር ፡ ምርኮኞችና ፡ ግዞተኞች ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ።

(፩) በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ወይም ፡ የባሕሩ ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞችና ፡ ግዞተኞች ፡ ባለፈው ፡ አንቀጽ ፡

በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ (አንቀጽ ፡ ፪ ፤) በሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ለተሠሩት ፡ ወንጀሎች ፡ አላፊ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ ወንጀሎችን ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተጸፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

ከንብረትና ፡ ከገንዘብ ፡ ቅጣቶች ፡ በቀር ፡ የዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ እንዲሁም ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መደበኛ ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የወታደራዊ ፡ ወንጀሎች ፡ ብቻ ፡ ያልሆኑትን ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ካመለጡ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ወንጀል ፡ ከሠሩ ፡ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ዐይነት ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በጠቅላላው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

## ቍ ፡ ፫፻፵፱ ። መኰንኖች ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ በወታደር ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ።

በማገልገል ፡ ግዴታ ፡ በሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (በዲስፕሊን) ፡ በወታደር ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ተግባርና ፡ በጠቅላላው ፡ በወታደር ፡ ግዴታዎች ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ማናቸውም ፡ ማዕርግ ፡ ያላቸው ፡ መኰንኖችና ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ ባጠፉት ፡ ጥፋት ፡ መጠንና ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ መሠረት ፡ ከፍ ፡ ብለና ፡ አርኣያ ፡ በሚሆን ፡ አኳኋን ፡ ይቀጣሉ ።

## ቍ ፡ ፫፻፶ ። ለከባድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተጨማሪ ፡ ስለሚሆኑ ፡ ቅጣቶች ።

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የጽኑ ፡ እስራትን ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትሉ ፡ ጕዳዮች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ በገንዘብ ፡ ፍላጎት ፡ ወይም ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ሲሆንና ፡ አድራጊው ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፤ ሹም ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፤

አጥፊው ፡ አገልግሎቱን ፡ ለመቀጠል ፡ ወይም ፡ በማዕርጉ ፡ ለመኖር ፡ የማይገባ ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከማዕርግ ፡ የመገፈፍን ፡ ወይም ፡ ከጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ የመወገድን ፡ ቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቅጣቶች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ያገልግሎትን ፡ ትእዛዝና ፡ ድንጋጌዎችን ፡ በመጣስ ፤ በድንገተኛ ፡ ስካር ፤ ባለመታዘዝ ፡ ወይም ፡ ደንቡን ፡ ባለመከተል ፡ ወይም ፡ ያለመጠን ፡ በመገልገል ፡ ቀላል ፡ የሆኑ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለመቅጣት ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (ዲስፕሊን) ፡ ደንቦች ፡ ሊፈጸሙበት ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፹፯ ። ፯፻፵፰ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በወታደሮችና ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ወታደሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፪ ። ያገልግሎቱን ፡ ተግባር ፡ በማይገባ ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ እንዲጥስ ፡ ስለ ፡ ማስገደድ ።**

አንድ ፡ ወታደር ፡ ያገልግሎት ፡ ተግባሩን ፡ ያላገባብ ፡ እንዲፈጽም ፤ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ አገልግሎት ፡ እንዳይፈጽም ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ የሚያስገድድ ፡ ወይም ፡ የሚያግድ ፡ ሰው ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፫ ። በሥራ ፡ ላይ ፡ ከሚገኝ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ የጸብ ፡ ግጭት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ወታደር ፡ ሳይደርስበት ፡ የዛተበት ፡ ያጠቃው ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ያደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ ተበዳዩን ፡ በዚሀ ፡ ዝቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ በተበዳዩ ፡ ያካል ፡ ማቍሰል ፡ ወይም ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ የጤንነት ፡ ማጕደል ፡ ጕዳት ፡ አድርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስራቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ይሆናል ።
ማጥቃቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአካል ፡ ጕዳት ፡ ፣ አድርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከአካባቢው ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ እንደሚደርስ ፡ ሊታወቅ ፡ የሚቻለውን ፡ ሞትን ፡ አስከትሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲሀ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለነዚሁ ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ የተጻፈው ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፣ ፭፻፴፰ ። ፭፻፵ ።]

**ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። ከባድ ፡ ሁኔታ ።**

ከዚሀ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፪ና ፡ ፫፻፴፫ ፡ የተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ የተፈጸሙት ፦—

(ሀ) ሥራውን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ ባንድ ፡ ዘብ ፤ ላንድ ፡ ዘብ ፡ በቆመ ፡ ወታደር ፡ በዘብ ፡ ፍተሻ ፡ ጓድ ፡ ወታደሮች ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፖሊስ ፡ አባል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፤

(ለ) ባንድ ፡ መኰንን ፤ ወይም ፡ በሥራው ፡ ወይም ፡ በማዕርጉ ፡ ምልክት ፡ ሊለይ ፡ በሚቻል ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የአካል ፡ መጕደል ፡ ወይም ፡ ሊደርስ ፡ እንደሚችል ፡ የታወቀ ፡ ሞት ፡ ሲደርስ ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰንና ፡ ለማክበድ ፡ የተጸፈው ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ ያለጦር ፡ መሣሪያ ፡ የማጥቃት ፡ ሥራ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜና ፡ ለአካል ፡ ወይም ፡ ለጤና ፡ ማናቸውንም ፡ ጉዳት ፡ ያላደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ቢያንስ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይሆናል ። የማጥቃቱ ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመው ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሲሆን ፡ ቅጣቱ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፭፻ ።]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በረዳት ፡ ያገልግሎት ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፫፻፵፭ ። የሕግ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ግዴታዎችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ለወታደሮቹ ፡ ወይም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ አገልግሎት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ እንስሳት ፡ ተሽከርካሪዎች ፤ ምግቦች ፤ ወይም ፡ ለጦሩ ፡ ለማቅረብ ፡ በሕጋዊ ፡ ውል ፡ የተዋዋለበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ በማናቸውም ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳያስረክብ ፡ ሳይሰጥ ፤ ሳያቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ክፍል ፡ ለሆነው ፤ የሥራ ፡ አገልግሎትን ፡ ሊሰጥ ፡ ወይም ፡ ሊያቀርብ ፡ በውል ፡ ግዴታ ፡ የገባበትን ፡ የሥንቅ ፡ መስጠት ፡ ማስረከብ ፡ ወይም ፡ የማቅረቡን ፡ ሥራ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ትጥቅ ፡ የዕቃ ፡ ወይም ፡ የማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ በቤት ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራዎችን ፡ የሕንጻ ፡ ሥራዎችን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ተዋውሎ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፤ አገልግሎቱን ፡ ወይም ፡ አላፊነቱ ፡ የሚመለከተውን ፡ የዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ ተግባሩን ፤ የሚፈጽመውን ፡ ወይም ፡ ሊያቀርብ ፡ የሚገባውን ፡ ዕቃ ፡ ትክክለኛነት ፡ የመረመረው ፡ ያስረከበው ፡ ወይም ፡ የተቀበለው ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ የሕሊና ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ ካለመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ያፈጻጸም ፡ መዘግየት ፡ አድርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። ነገሩም ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

(፪) አድራጊው ፡ የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፫፻፴፯ ። ስለ ፡ ማሰናከል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ክፍል ፡ የሚያገለግሉትን ፡ የተቋቋሙ ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ድርጅቶችን ፡ ዕቃዎችን ፡ ወይም ፡ መጓጓዣዎችን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ነገሮች ፡ ያፈረሰ ፤ ያበላሸ ፤ ወይም ፡ ካገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ የማገልገል ፡ ሥራቸውን ፡ እንዳይቀጥሉ ፡ ባለሥልጣናችን ፡ ወይም ፡ ሠራተኞችን ፡ የሚያሰናክል ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ያወከ ፡ ወይም ፡ ችግር ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

(፫) በመንግሥት ፡ የመከላከያ ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ የወንጀል ፡ ተግባሮችን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህን ፡ በሚመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፪፻፳፰ ።]

## ቍ ፡ ፫፻፴፰ ። በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መነገድ ።

በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ (አድሚኒስትራሲዮን) ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ተወርሰው ፡ ወይም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ከሕዝብ ፡ ተወስደው ፡ በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ዕቃዎች ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፤ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሰጠ ፤ የሸጠ ፤ የገዛ ፤ ያዋሰ ፤ ወይም ፡ በዕዳ ፡ ያስያዘ ፤ በብድር ፡ በተውሶ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለ ፤ የጨረሰ ፤ ወይም ፡ ያጠፋ ፤ ያፈረሰ ፤ ወይም ፡ ካገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ያደረገ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፴፱ ። የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ መለዮ ፡ ልብስ ፡ ምልክትና ፡ ሽልማት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በፋብሪካ ፡ ስለ ፡ መሥራትና ፡ በንግድ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ።

የጦር ፡ ወታደርን ፡ መለዮ ፡ ልብስ ፤ ምልክት ፡ ወይም ፡ የሽልማት ፡ ኒሻን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡

በሆን ፡ አኳኋን ፡ በፋብሪካ ፡ የሥራ ፤ በተካባችነት ፡ ያስቀመጠ ፤ ያቀረበ ፡ ወይም ፡ የሸጠ ፤ የገዛ ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ ያገኘ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቊ ፡ ፫፻፴፱ ። የወታደር ፡ መለዮ ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ የወታደርን ፡ ምልክትና ፡ ሽል ማት ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መልበስ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የማይገባውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መለዮ ፡ የሆነውን ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ሽልማት ፤ ወይም ፡ ሌላ ፡ ምልክት ፡ ለብሶ ፡ ወይም ፡ ምልክቱን ፡ አድርጎ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፫፻ ፡ ብር ፡ በሚደ ርስ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቊ ፡ ፫፻፵ ። ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ የያዙ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባሮችን ፡ ትእዛዝ ፡ ስላለመቀበል ።

(፩) የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ አስፈላጊ ፡ ጥቅም ፡ ለመጠበቅ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የክ ፍሉ ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ባለሥልጣን ፡ የሰጠውን ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈረሰ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፤ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ በተለይ ፡ እንዲደርስበት ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ አልተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ፫፻ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቊ ፡ ፫፻፵፩ ። የወታደር ፡ ትእዛዞች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ወይም ፡ እንዲጣሱ ፡ ለማድረግ ፡ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ማደፋፈር ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የወታደር ፡ ትእዛዞች ፡ እንዳይፈጸሙ ፤ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንዳይከበር ፡ ወይም ፡ ወታደራዊ ፡ ግዴታ ፡ እንዲጣስ ፡ በግልጽ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ሌሎችን ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ ያደፋፈረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህንኑ ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ጓድ ፡ አንድ ፡ ንቅናቄ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ስብሰባ ፡ ያቋቋመና ፡ በድርጅቱ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሥራው ፡ አረማመድ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ወይም ፡ ማኅበረተኛ ፡ በመሆን ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

BACK



ቍ ፡ ፫፻፵፱ ። አንዳንድ ፡ የወታደር ፡ ስፍራዎችን ፡ ወይም ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የተደረገውን ፡ ክልከላ ፡ ስላለመከተል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡

(ሀ) በወታደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወይም ፡ በወታደራዊ ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ በተከለከሉ ፡ የጦር ፡ ስፍራዎች ፡ በወታደራዊ ፡ የጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ስፍራ ፡ ገብቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የጦር ፡ ስፍራዎች ፡ እንዲሁም ፡ በውስጣቸው ፡ የሚገኙትን ፡ ስፍራዎች ፡ ወይም ፡ ቦታዎች ፡ እንዲሁም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ ያሉበትን ፤ የጦር ፡ ዕቃዎች ፡ ፕላናቸውን ፡ ንድፋቸውን ፡ ፎቶግራፋቸውን ፡ ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ የምሥላቸውን ፡ ሥዕል ፡ የወሰደ ፤ ያባዛ ፡ የገለጸ ፤ ወይም ፡ ወሬውን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። ጠቅላላ ፡ ትእዛዞችንና ፡ አመራሮችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ለወታደርነት ፡ የመመልመል ፤ ወይም ፡ በወታደርነት ፡ ውስጥ ፡ የማገልገል ፡ ወይም ፡ ለወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ዕቃ ፡ እንዲቀርብ ፡ የተሰጠውን ፡ የትእዛዝ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ለወታደርነት ፡ ለመመልመል ፡ ዕድሜያቸው ፡ የፈቀደላቸው ፡ ያገር ፡ ተወላጆች ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ሊያገለግሉ ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታና ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተውን ፡ ሰነድ ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የጻፈ ፡ ያጠፋ ፡ ወይም ፡ እንዲጠፋ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህንኑ ፡ ዐይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ መምሪያ ፡ በሐሰተኛነት ፡ ወይም ፡ በመለወጥ ፡ አሠራር ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህን ፡ ማስረጃ ፡ ያፈረሰው ፡ የሠረዘው ፡ ወይም ፡ የተገለገለበት ፡ ቅጣትን ፡ በሚያስከትል ፡ አለመጠንቀቅ ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በወታደር ፡ ግዴታዎች ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ ስላለመግለጽ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የመከዳት ፡ የስለላ ፡ የማሸበር ፡ ወይም ፡ የመኮብለል ፡ ወንጀል ፡

ዐቅድ ፡ ወይም ፡ ተግባር ፡ መዘጋጀቱን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ እያወቀ ፡ ያልገለጸ ፡ ወይም ፡ እንዳይፈጸም ፡ ለማገድ ፡ ያልፈለገ ፡ ወይም ፡ አድራጊዎቹን ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ወንጀሉ ፡ የተሠራ ፡ ወይም ፡ ሊሠራ ፡ የተሞከረ ፡ ከሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ። ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የተሠራውን ፡ ወንጀል ፡ ለባለሥልጣን ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታን ፡ አለመፈጸም ፡ የሞያ ፡ ሥራንና ፡ የግል ፡ ሥራን ፡ ምስጢር ፡ መብት ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ለመጥቀስ ፡ አይቻልም ። የአደጋ ፡ ምልክት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የክተት ፡ ዐዋጅ ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜና ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሥጋ ፡ ዝምድናንና ፡ በፍቅር ፡ ወዳጅነት ፡ የተሳሰረ ፡ ግንኙነትን ፡ በመጥቀስ ፡ ከቅጣት ፡ ለመዳን ፡ የይቅርታ ፡ ማግኛ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ። [ቍ ፡ ፹ ።]

(፫) የከሕደትንና ፡ የወታደር ፡ ስለላን ፡ ወንጀል ፡ የአለመግለጽ ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ አገር ፡ ጸጥታና ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ የመከላከያ ፡ ኀይል ፡ አጠባበቅ ፡ ጉዳይ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ያስቀጣል ። [ቍ ፡ ፪፻፸፯ ።]

ቍ ፡ ፪፻፶፰ ። የወታደርነትን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፶፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፶፭ ፡ ከተደነገጉትና ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ ከሚያስከትሉት ፡ የከዳት ፡ ወይም ፡ የስለላ ፡ ወንጀል ፡ ከሆኑት ፡ ጥፋቶች ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በጠቅላላው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ባደባባይ ፡ ያልታወቁትንና ፡ ባይነታቸውና ፡ ከፍተኛ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ በመያዛቸው ፡ ምክንያት ፡ ላልተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ እንዳይገለጹ ፡ በምስጢር ፡ የሚጠበቁትን ፡ የወታደርነት ፡ ምስጢር ፡ ያላቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ መረጃዎች ፡ ላልተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ወሬውን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የሚመለከተው ፡ በተለይ ፡ የተጠበቁትን ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ መረጃዎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ የሠራው ፡ በነዚሁ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ ልማድ ፡ ያለውና ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ የተመረጠ ፡ ወይም ፡ አደራ ፡ የተቀበለው ፡ ሠራተኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ያስከተለ ፡ ወይም ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ አደጋ ፡ ያደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ ጉዳይ ፡ አምጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፫) አድራጊው ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) እንደ ፡

ተመለከተው ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) እንደተመለከተው ፡ አደጋው ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፮ ። የሐሰት ፡ ወይም ፡ የማደናገር ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ማንም ፡ ሰው ፤ ወታደሮች ፡ በጦር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ወይም ፡ ያገልግሎት ፡ ተግባራቸውን ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ትክክል ፡ አለመሆናቸውን ፡ ወይም ፡ የሚያደናግሩ ፡ መሆናቸውን ፡ እያወቀ ፡ ለወታደራዊው ፡ ጥቅም ፡ ተብሎ ፡ የተያዘውን ፡ የጥንቃቄ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ ለማሰናከል ፡ ወይም ፡ ለማገድ ፡ በማሰብ ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ንቅናቄዎች ፡ ወይም ፡ የውጊያ ፡ ዕቅዶች ፡ ለማሰናከል ። ወይም ፡ የሚያሰናክል ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ለማድረግ ፡ በማሰብ ፡ ወይም ፡ ወታደሮቹ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆኑ ፡ ወይም ፡ እንዳይታዘዙ ፡ ለማነሣሣት ፡ ወይም ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ሽብርና ፡ ብጥብጥ ፡ እንዲነሣ ፡ ለማበረታታት ፡ አስቦ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እያወቀ ፡ ትክክለኞች ፡ አለመሆናቸውንና ፡ የሚያደናግሩ ፡ መሆናቸውን ፡ እያወቀ ፡ የሐሰት ፡ ወሬዎችን ፡ የነዛ ፡ ወይም ፡ የሰበከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፫፻፵፯ ፡ በአደጋ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ።

(፩) በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ከሚያስቀጡት ፡ ወንጀሎች ፡ አንዱ ፡ ወንጀል ፡ ባንዱ ፡ ወታደር ፡ ላይ ፡ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ክፍል ፡ በሆነው ፡ ተደራቢ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ በወታደርነት ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ተፈጽሞ ፡ የተደረገውም ፡ የአደጋ ፡ ምልክት ፡ ጠቅላላ ፡ የጦር ፡ ክተት ፡ በታዘዘበት ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ቅጣቱን ፡ የሚያከብድ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡

(ሀ) በእስራት ፡ ፈንታ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ።

(ለ) ቅጣቱ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተደነገገውን ፡ ከፍተኛ ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ እጠፌታ ፡ ድረስ ፡ ለመፍረድ ፡ ይቻላል ። ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ የመጣልን ፤ ሽብር ፡ የማስነሣትን ፡ ወይም ፡ የመክዳትን ፡ ዐቅድ ፡ ወይም ፡ ተግ

ባር ፡ ያለ ፡ መግለጽ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፫፻፺፬ ።]

(፪) ስለ ፡ ቸልተኛነትና ፡ ቅጣትን ፡ ስለሚያስከትል ፡ ያለመጠንቀቅ ፡ ጥፋት ፡ የሚ ወሰነው ፡ ቅጣት ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተደንግጎ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡—

(ሀ) ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከፍተኛውን ፡ የእስራት ፡ መደብ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለማድረስ ፡ ይችላል ።

(ለ) የቅጣቱም ፡ ልዩ ፡ ከፍተኛ ፡ መደብ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ያነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ አድርሶ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ የፈረደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተፈጻሚ ፡ በሆነው ፡ ድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ መቀጮ ፡ እስከ ፡ አጠፌታ ፡ ድረስ ፡ ለመወ ሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፰ ። ገንዘብን ፡ በመውደድ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

የጽኑ ፡ እስራትን ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትሉ ፡ ጥፋቶች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋ ተኛው ፡ የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በወራዳነት ፡ መንፈስና ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ እንደ ፡ አድራጊው ፡ ሀብት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡— ከዋናው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፡ አጣምሮ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ደንቡ ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ቍ ፡ ፫፻፺፱ ። የአፈጻጸሙ ፡ መሠረት ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በሁለት ፡ ምዕራፎች ፡ ውስጥ ፡ ቅጣትን ፡ ያስከትላሉ ፡ ተብሎ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ አንዱን ፡ የመንግሥቱ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ለመሥራት ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሥ ራው ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አባል ፡ ላይ ፡ የተፈጸመበት ፡ ወይም ፡ የተሞከረበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ወንጀል ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ቅጣትን ፡ የማያስከትል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፪፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ፫፻፺፯ ።]

ቁ ፡ ፫፻፺ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ ግርግር ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ የአደጋ ፡ ምልክት ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ዐመፅ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ በተነሣበት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወታደራዊ ፡ ረገድ ፡ ጉዳዩን ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ ሲወስን ፡ ለቅጣት ፡ ማክበጃ ፡ የሚሆኑትን ፡ ምክንያቶች ፡ ከግምት ፡ በማግባት ፡ ነው ። [ቁ ፡ ፫፻፵፮።]

(፪) እንዲሁም ፡ ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ ገንዘብ ፡ በመውደድ ፡ ስሜት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተውን ፡ የሕጉን ፡ ቍጥር ፡ በመጥቀስ ፡ ቅጣቱን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፫፻፵፰ ።]

ቍ ፡ ፫፻፺፩ ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

የወታደርንና ፡ የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ አኗኗርና ፡ ሕይወት ፡ የሚመለከቱት ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ሲያደርግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ በሚታየው ፡ ረገድ ፡ ሁሉ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ልዩ ፡ አስተዳደር ፡ ለሥራው ፡ አቋቋምና ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ በማግባት ፡ ነው ።

ቁ ፡ ፫፻፺፪ ። የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባሮች ፡ ወሰን ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ በተደነገጉት ፡ በሥራ ፡ አቋቋሞች ፡ በአገልግሎት ፡ ተግባሮችና ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊትን ፡ ኀይል ፡ ለመጠበቅ ፡ የተቋቋሙትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመጣስ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ቅጣቶች ፡ ከሚወስኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በቀር ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባሎች ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ለተቋቋመው ፡ ድርጅት ፡ ሠራተኛ ፡ በመሆናቸው ፡ ይህንኑም ፡ ተግባራቸውን ፡ ሲፈጽሙ ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ጉድለት ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎችና ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።
[ከቍ ፡ ፬፻፲ ፡ እስከ ፡ ፬፻፳፯ ።]

ቍ ፡ ፫፻፺፫ ። ጐን ፡ ለጐን ፡ የሚሄድ ፡ አፈጻጸም ፡ ተደራራቢ ፡ ቅጣቶችን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።

የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎትን ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የአመራር ፡ ጉዳይ ፡ ከሚመለከቱት ፡ ጋራ ፡ ይልቁንም ፡ በጠቅላላው ፡ የአገልግሎትን ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፡ መጣስን ፡ ከሚመለከቱት ፡ ጋራ ፡ [ቍ ፡ ፫፻፮ና ፡ ፬፻፲፪) ] ። ሥልጣንን ፡ ከመጠኑ ፡ ማሳለፍን ፤ ]ቍ ፡ ፫፻፬ና ፡ ፬፻፲፬፡] ወይም ፡ ያላገባብ ፡ ማግኘትን ፡ ያላገባብ ፡ ማጥፋትን ፡ ወይም ፡ በተንኮል ፡ ዘዴ ፡ መምራትን ፡ [ቍ ፡ ፫፻፲፱ ፤ ፫፻፳ና ፡ ፬፻፳ ፡እስከ ፡ ፬፻፳፯ ።] የሥራ ፡ ምስጢር ፡ መግለጽን ፡ [ቍ ፡ ፫፻፵፰ ፤ ፬፻፬ና፡፬፻፰ ]።

BACK



ከሚመለከቱት ፡ ጋራ ፡ የተገናኙ ፡ (የተገጣጠሙ) ፡ ሲሆን ፡ የወታደርን ፡ ጠባይ ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ ከሰላማዊ ፡ አስተዳደር ፡ ጋራ ፡ የሚጠጋ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ በተለይ ፡ ክስ ፡ የቀረበበትን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ድንጋጌዎቹንም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ አጣምሮ ፡ መፍረድ ፡ አይቻልም ።

## አንቀጽ ፡ ፱ ።

## በመንግሥቱ ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ገቢዎችና ፡ በጠቅላላ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅሞቹ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፫፻፶፬ ። በልዩ ፡ ደንብ ፡ ወንጀለኛ ፡ ስለ ፡ መባል ።

(፩) አንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ወይም ፡ የማስፈጸሚያ ፡ ክፍል ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የመንግሥቱን ፡ ጥኖፖል ፡ ሥራ ፡ ለማቋቋም ፤ ሥራውን ፡ ለማካሄድ ፡ ለመምራት ፡ ለመቈጣጠር ፡ ለመጠበቅ ፡ ግብርንና ፡ ታክስን ፡ ለመወሰንና ፡ ለመቀበል ፡ ካገር ፡ የሚወጣውንና ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገባውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወጪና ፡ ገቢ ፡ የንግድ ፡ ዕቃና ፡ ያገርን ፡ ሀብት ፡ አወጣጥ ፡ ለመወሰን ፡ ለመቈጣጠር ፡ የገበያ ፡ ዋጋዎችን ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ በመንግሥቱ ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግብርና ፡ ቀረጥ ፡ ገቢ ፡ የፊናንስንና ፡ የኤኮኖሚክን ፡ ጉዳይ ፡ ለሚመለከተው ፡ ጠቅላላ ፡ ድርጅት ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊውን ፡ ድንጋጌ ፡ በሚገባ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አትሞ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ መጣስ ፡ የሚወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብና ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

(፪) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱት ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ በሆኑና ፡ ባልሆኑ ፡ በጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ በሚያገዙ ፡ ወይም ፡ በሚከለክሉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ያልሞላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ የወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

BACK



ቍ ፡ ፫፻፶፭ ። የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡ ዐይነታቸውና ፡ መጠናቸው ።

(፩) ጕዳዩን ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ትእዛዞችና ፡ ድንጋጌዎች ፡ በግልጽ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ታወቀ ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ተመለከቱት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ባመሩ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረትና ፡ መጠን ፡ አድራጊውም ፡ ጥፋቱን ፡ የሠራው ፡ በጥቅም ፡ ፍላጎት ፡ ወይም ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ሲሆን ፡ መቀጮውን ፡ ከማከበድ ፡ ጋራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስራትን ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡መቀጮን፡ይፈርዳል ። [ቍ ፡ ፹፰ ፡ እስከ ፡ ፺ ። ፪፭ና ፡ ፪፮ ።]

(፪) እንደዚህ ፡ ባለው ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ወንጀሉና ፡ የጥፋተኛነቱ ፡ ሁኔታ ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ የተሰነዘረውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ባለው ፡ በባለዋጋ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በከፍተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ አነጋገር ፤ ወንጀለኛው ፡ ይህን ፡ ተግባሩን ፡ እንደ ፡ ሞያ ፡ ሥራው ፡ አድርጎ ፡ የሚጠቀምበት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ የተገኘው ፡ ዕቃና ፡ ገንዘብ ፡ እንዲወረስ ፡ ከማድረጉ ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺ ።]

(፫) የጥበቃ ፡ ቅጣቶችና ፡ የመጠባበቂያ ፡ የመከልከል ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ የማገድ ፡ እንዲሁም ፡ በተጨማሪነት ፡ የሚታዘዙ ፡ የመግለጫና ፡ የማስታወቂያ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚጠቀሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በገመተ ፡ ጊዜ ፡ ተጨማሪ ፡ አድርጎ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፮ ። ተደራራቢ ፡ የሆኑ ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ቅጣቶች ።

በቀረጥና ፡ በግብር ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሰው ፡ ጥፋት ፡ በወንጀል ፡ በኩል ፡ የሚወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ የሚፈጸሙት ፡ እንደዚህ ፡ ስላለው ፡ ጕዳይ ፡ ባስተዳደር ፡ (በአድሚኒስትራሲዮን) ፡ ክፍል ፡ በወጡት ፡ ደንቦች ፡ በመቀጮው ፡ አወሳሰን ፡ በኩልም ፡ ሆነ ፡ በተሰረቁት ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ገቢዎች ፡ በኩል ፡ የሚፈጸመውን ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ ሳያስቀሩ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፫፻፶፯ ። በወርቅ ፤ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ መነገድ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ የሚሠራውን ፡ ወንጀለኛ ፡ ስለ ፡ መቅጣት ፡

BACK



በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ድንጋጌ ፡ (ከዚህ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ባምስተኛው ፡ አንቀጽ) ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ያገር ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሀብት ፡ የሆነውንና ፡ የንግዱ ፡ ወይም ፡ የምንዛሬው ፡ ጉዳይ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ሕጋዊ ፡ መሥመር ፡ ውስጥ ፡ የሚጠበቀውን ፡ ወይም ፡ የመቈጣጠር ፡ የመከልከልና ፡ የልዩ ፡ ጥበቃ ፡ ሥርዐት ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ ወይም ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረውና ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ወርቅና ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ያገር ፡ ገንዘብ ፡ የገዛ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ያመጣ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ያገባ ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ተቀብሎ ፡ ያስቀመጠ ፡ የለወጠ ፡ የመነዘረ ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ለሽያጭ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠራበትን ፡ ሀብት ፡ የመወረሱ ፡ ደንብ ፡ የሚጸናበት ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። ባለዋጋ ፡ ማዕድኖችንና ፡ ዕንቁዎችን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በንግድ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ።

እንዲሁም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉትን ፡ ባለዋጋ ፡ ማዕድኖች ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ብር ፡ እንደ ፡ ፕላቲን ፡ እንደ ፡ ኡራኒዮም ፡ የሆኑትንና ፡ ሌሎችንም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ማዕድኖችን ፡ እንዲሁም ፡ ባለዋጋ ፡ የሆኑ ፡ ዕንቁዎችንና ፡ ሚኒራሎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፤ ወንጀል ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፶፪ ፡ የተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፶፬ ። ታማኝነት ፡ ባለው ፡ በመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የተንኰል ፡ አሠራር ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በመንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ በማቀድ ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፤

(ሀ) ያገሩን ፡ ገንዘብ ፡ ምንዛሬ ፡ እንዲረክስ ፡ ለማድረግ ፡ ከሕዝብ ፡ የገንዘብ ፡ ማከማቻ ፡ ሣጥን ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲወጣ ፡ ወይም ፡ ገንዘባቸውን ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ የቊጠባ ፡ ገንዘብ ፡ ማከማቻ ፡ ሣጥን ፡ እንዲያገቡ ፡ በሕግ ፡ የተቋቋሙት ፡ ድርጅቶች ፡ ያገቡትን ፡ ገንዘብ ፡ አውጥተው ፡ እንዲወስዱ ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ የገቢና ፡ የወለድ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኙትን ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ያወጣቸውን ፡ ሌሎች ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ በጅምላ ፡ በመሸጡ ፡ ዋጋቸው ፡ ዝቅ ፡ እንዲል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እነዚህንም ፡ ገንዘቦች ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ወረቀቶች ፡ ሰው ፡ እንዳይገዛቸው ፡ ያሰናከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የመንግሥትን ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ የመክፈል ፡ እንቢተኛነት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውንና ፡ በደንበኛው ፡ የክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በደንብ ፡ የተቈረጠውን ፡ በዐይነታቸው ፡ የሚከፈለውን ፡ ከመሬት ፡ ከርስት ፡ ከሀብት ፡ ከንብረት ፡ ወይም ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ገቢ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚከፈለው ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ የመንግሥት ፡ ቀረጥና ፡ ታክስ ፤ እንዲከፍል ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ሲጠየቅ ፡ ለመክፈል ፡ መቻሉ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆኖ ፡ የሚገባውን ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ ለመቃወም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ እንቢተኛነቱ ፡ ዛቻን ፡ የኀይል ፡ ሥራን ፡ ድብደባን ፡ (የእጅ ፡ እልፊት) ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ የመገልገልና ፡ መሣሪያ ፡ አንሥቶ ፡ የመቃጣትን ፡ የሁከትንና ፡ የሸፍትነትን ፡ ሥራዎች ፡ አስከትሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጕዳዩን ፡ በሚመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተደነገገው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ተጣምሮ ፡ ይፈጸምበታል ።
[ቍ ፡ ፺፪ ።[

ቍ ፡ ፫፻፷፩ ። ግብር ፡ እንዳይከፈል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ባድራጎት ፡ በስጦታ ፤ በንግግር ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አኳኋን ፡ በሕግ ፡ የተደነገገው ፡ ታክስና ፡ ግብር ፡ እንዳይከፈል ፡ ያነሣሣ ፡ ለማነሣሣት ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በነገሩ ፡ መስፋፋትና ፡ ትልቅ ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ በተፈጠረው ፡ ዘዴ ፡ ሁኔታው ፡ ከባድና ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስራቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመትና ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ወንጀል ፡ የተባለው ፡ ተግባር ፡ ሸብር ፡ ማነሣሣትን ፡ በባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ ማመጽንና ፡ ባለሥልጣን ፡ መገልበጥን ፡ ለመሳሰሉት ፡ በተወሰኑት ፡ ከፍ ፡ ባሉት ፡ ቅጣቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ በተጣመሩ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቶችን ፡ የማከበድ ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፺፪ ።]

BACK



ቍ ፡ ፫፻፷፪ ። በግብርና ፡ በሌሎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ቀረጥ ፡ ገቢ ፡ ምንጮች ፡ ላይ ፡ ጕዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፤ በሕግ ፡ የተወሰነውንና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ገቢ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ ታክስ ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ እንዳይከፍል ፡ ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ወይም ፡ ማኅበራዊ ፡ የሆነውን ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ እንዳይከፍል ፡ ለማድረግ ፡ ዐቅዶ ፦—

(ሀ) ግብርና ፡ ታክስ ፡ ሊወሰንባቸው ፡ በሚገባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ሀብቶች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ በሚያስገኙት ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ግብሩንና ፡ ታክሱን ፡ ለመወሰን ፡ በሚጠቅሙት ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ እያወቀ ፡ ለመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ሐሰተኛ ፡ መረጃ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎትና ፡ ዘዴ ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ከስሕተት ፡ ላይ ፡ እንዲወድቁ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ እውነቱን ፡ በሐሰት ፡ በመለወጥ ፡ ነገሩን ፡ በመሰወር ፡ የማስመሰል ፡ ዘዴ ፡ በመፍጠር ፤ በማንኛውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ አድራጎት ፡ ያሳሳተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ ይህን፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ የማታለልንና ፡ የማጭበርበርን ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ አኳኋን ፡ ያደረገ ፡ መሆኑ ፡ ሲገለጽ ፡ ለነዚህ ፡ አድራጎቶች ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጣምረው ፡ ይፈጸሙበታል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፫ ። ኬላ ፡ ስለ ፡ መስበር ፡ (ኮንትራባንድ) ።

(፩) ማንም ፡ ሰው፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነው ፡ ግብር ፡ ቀረጥ ፡ ወይም ፡ ታክስ ፡ ያልተከፈለበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሀብት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የፋብሪካና ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ የሚያፈራውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ያስገባ ፡ ወይም ፡ ከግዛቱ ፡ ያስወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ወንጀሉ ፡ የተሠራባቸው ፡ መጓጓዣዎችና ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ መወረስ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ሳይቀሩና ፡ ለወንጀሉም ፡ በፍጹም ፡ ባዕድ ፡ የሆኑት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፤

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ። [ ቍ ፡ ፻፵፩ ። ]

(፪) በጉምሩክ ፡ ውስጥ ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ በድንገት ፡ በሚፈጸሙ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ የሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ ደንብ ፡ ተላላፊዎች ፡ መቅጫ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፯፻፱ ። ]

ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። በመንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጉዳይና ፡ በሞኖፖል ፡ ረገድ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተለይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ደግሞም ፡ ባስተዳደር ፡ አቋቋምና ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ በምርመራ ፡ በመቈጣጠርና ፡ በደንብ ፡ ተላላፊዎች ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ። [ቍ ፡ ፯፻፱ ፡ እስከ ፡ ፯፻፵፮ ። ]

(ሀ) ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ከፋብሪካ ፡ ወይም ፡ ከመሬት ፡ ስለሚወጡ ፡ ሀብቶች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ማስመጣትና ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ መላክ ፤ ስለ ፡ ማስቀመጥ ፤ ስለ ፡ ማመላለስ ፡ የተከለከሉትን ፤ ወይም ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ መቈጣጠር ፤ ወይም ፡ ቀረጥ ፡ መክፈል ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ደንቦች ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ካገሩ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሀብት ፡ በሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ ለመጠቀም ፡ በኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ መገልገል ፡ በውሃዎች ፡ በደኖች ፡ በማዕድኖች ፡ በዱር ፡ አራዊቶችና ፡ ለማዳ ፡ ባልሆኑ ፡ እንስሳዎች ፡ ሀብትና ፡ በሚሰጡት ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ የወጣውን ፡ የክልከላ ፡ ደንብ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በመንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ የተቋቋመውን ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ የሚቈጣጠረውን ፡ ሞኖፖል ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ በመቃወም ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፤ የአልኮልን ፤ የትምባሆን ፤ የክብሪትንና ፡ የሌላውንም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በተቋቋሙት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እየተመሩ ፡ እንዲከናወኑ ፡ የተመደቡትን ፡ የመገናኛ ፡ የመላላኪያ ፤ የፖስታ ፤ የቴሌፎን ፤ የቴሌግራፍና ፡ የማመላለሻ ፡ አገልግሎት ፡ ደንቦችን ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) የባንክ ፡ አቋቋምን ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ክፍሎችን ፡ የኮንሴሲዮን ፡ አሰጣጥ ፡ ወይም ፡ በባንክ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ ፍሬ ፡ የመጠቀምንና ፡ የመጠባበቅን ፡ የንግድን ፡ ወይም ፡ የእንዱስትሪን ፡ የፋብሪካን ፡ የወፍጮን ፡ የሆቴሎችን ፡ ወይም ፡ የሌሎች ፡ ድርጅቶችን ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የተቋቋሙትን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ይህ ፡ ተግባሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ በሚያስወስን ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመለከተ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ በመገኘቱ ፡ አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ወንጀል ፡ የሠራበት ፡ ንብረት ፡ የሚወረስበት ፡

የንግድ ፡ ፈቃዱና ፡ የሥራ ፡ ምስክር ፡ ወረቀቶቹ ፡ የሚወሰዱበት ፡ የእንዱስ
ትሪ ፡ ሥራውን ፡ እንዳይቀጥል ፡ የሚታገድበት ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ቤቱ ፡ የሚዘጋ
በት ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡
እንደ ፡ ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታና ፡ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ እጅግ ፡
ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፭ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ።

የተከለከለ ፡ ዕቃ ፡ የማስተላለፍ ፡ ያልተገባ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ የተደረገ ፡ ሕገ ፡
ወጥ ፡ ንግድ ፡ ወይም ፡ ኮንትራባንድ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ባለው ፡ ገን
ዘብ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛው ፡ ይህን ፡ የመ
ሳሰለውን ፡ የማስተላለፍና ፡ በሕግ ፡ በተከለከለ ፡ ነገር ፡ መሥራትን ፡ የዘወትር ፡
የሞያ ፡ ሥራው ፡ ያደረገ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የሚወሰንበት ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡
ሺሕ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ መቀጮና ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣትም ፡
እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

አንቀጽ ፡ ፳ ።

ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ገንዘቦች ፡ ማኅተሞች ፡ ቴምብሮችና ፡ መሠሪያዎች ፡ ላይ ፡

ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የሐሰት ፡ ገንዘብ ።

ቍ ፡ ፫፻፷፮ ። ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡
ሕጋዊ ፡ መገበያያ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ አድርጎ ፡ መገበያያ ፡
ለማድረግ ፡ በማቀድ ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ አስመስሎ ፡ የሠራና ፡ በሕዝብ ፡
እጅ ፡ እንዲገቡ ፡ (መገበያያ ፡ እንዲሆኑ) ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ካምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡
ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፯ ። ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡
በውጭ ፡ አገር ፡ መልካቸውን ፡ በመለወጥ ፡ በእውነተኛው ፡ መልካቸው ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡

ነገርን ፡ በመጨመር ፤ ቀለማቸውን ፡ በመለወጥ ፡ ወይም ፡ በማስመሰል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ ሕጋዊ ፡ መገበያያ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ የወረቀት ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ባንክ ፡ ኖቶች ፡ ከእርግጠኛ ፡ ዋጋቸው ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ መገበያያ ፡ እንዲሆኑ ፡ በማቀድ ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጣቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፷፰ ። የገንዘቡን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በሜካኒካዊ ፡ በፊዚክስ ፡ ወይም ፡ በኬሚስትሪ ፡ ጥበብና ፡ በማናቸውም ፡ በሌላ ፡ ጥበባዊ ፡ ዘዴ ፡ የገንዘቦችን ፡ ባለዋጋነት ፡ ያዋረደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። ገንዘቡ ፡ እንዲዘዋወር ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ዋናው ፡ ወንጀል ፡ አድራጊው ፡ ሳይሆን ፡ ወይም ፡ በወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ ሳይተባበር ፤—

(ሀ) እያወቀ ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆኑትን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የተለወጡትን ፡ ገንዘቦች ፡ ባንክ ፡ ኖቶች ፡ እንደ ፡ እርግጠኛ ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ ከተወሰነው ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ እንዳላቸው ፡ አስመስሎ ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ዋጋቸው ፡ የተቀነሰውን ፡ ገንዘቦች ፡ ሙሉ ፡ ዋጋቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ አድርጎ ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በ (ሀ) ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ጥፋት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ በ(ለ) ላይ ፡ ስለ ፡ ተመለከተው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀለኛው ፡ ወኪሉ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ገንዘቡ ፡ ባንክ ፡ ኖቱ ፡ ወይም ፡ የባንኩ ፡ ወረቀት ፡ ሐሰተኛ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ መቀነሱን ፡ እያወቁ ፡ ኪሣራ ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ አድርገው ፡ ወይም ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አስመስለው ፡ በመገበያያ ፡ እንዲዘዋወር ፡ አድረገውት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የተገለገሉበትም ፡ በገንዘብ ፡ በባንክ ፡ ኖት ፡ ወይም ፡ በሐሰተኛና ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በተለወጠ ፡ የወረቀት ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስራት ፡ ሊወስንባቸው ፡ ይችላል ። ወይም ፡ ዋጋው ፡ የተቀነሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ በማስመሰል ፡ ተገልግለውበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊወስንባቸው ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፫፻፸ ። የሐሰት ፡ ገንዘብን ፡ ባገር ፡ ስለ ፡ ማስገባት ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ለስጦታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የተለወጡ ፡ ገን

ዘቦችን ፡ የወረቀት ፡ ገንዘቦችን ፡ ባንክ ፡ ኖቶችን ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ ሆነው ፡ በመገበያያ ፡ እንዲዘወዋሩ ፡ ወይም ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ እንዳላቸው ፡ ለማድረግ ፡ በማቀድ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ያስገባ ፡ የገዛ ፡ ወይም ፡ ካሉበት ፡ ፈልጎ ፡ የወሰደ ፡ በባለአደራነት ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ያስቀመጠ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ በስጦታና ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ ቀላል ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ወይም ፡ የገንዘቡ ፡ ብዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የማይሰጠው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስራት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ማኅተሞችን ፡ ቴምብሮችን ፡ ምልክቶችን ፡ በሕግ ፡ የታወቁትን ፡ሚዛኖችንና ፡ መለኪያዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፩ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱን ፡ ማኅተሞች ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ለመንግሥቱ ፡ የሥራ ፡ ጕዳዮች ፡ ለማገልገል ፡ ብቻ ፡ የሚታተሙባቸውን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ የመንግሥቱን ፡ ወይም ፡ ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያንዱን ፡ ማኅተም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ አስመስሎ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በተለወጠው ፤ መስሎ ፡ በተሠራው ፡ ማኅተም ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ በእውነተኛው ፡ ማኅተም ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ ባገሩ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ባገሩ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያደርስ ፡ ታውቆ ፡ ይኸውም ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፪ ። ሌሎችን ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ያላቸውን ፡ ማኅተሞች ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የሕዝብ ፡ ጕዳይ ፡ ማከናወኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሆነውን ፡ ሌላ ፡ ማኅተም ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) ወይም ፡ እውነተኛ ፡ በሆነው ፡ ማኅተም ፡ ያለመብቱ ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል።

(፪) ከፍተኛ ፡ ጉዳት ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደ ርስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፫ ። ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ምልክቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ —

(ሀ) እንደ ፡ እውነተኛ ፡ ወይም ፡ እንዳልተነኩ ፡ አድርጎ ፡ ያላገባብ ፡ ሊሠራባ ቸው ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ እንዲሠሩባቸው ፡ በማቀድና ፡ በማሰብ ፡ ያመጣጣቸ ውን ፡ ሥረ ፡ መሠረት ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ የታወቀውን ፡ የመለያ ፡ ምል ክት ፡ የመመርመሪያ ፡ ወይም ፡ የጥሩነታቸውን ፡ ማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ ምልክት ፤ ይልቁንም ፡ በጉምሩክና ፡ በዕቃ ፡ ማመላለስ ፡ ጉዳይ ፡ የሚሰጠውን ፡ የመለያ ፡ ምልክት ፡ የወርቅን ፡ የብርን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ብረታ ፡ ብረት ፡ ክቡር ፡ ማዕድኖችን ፡ የዕንጨትን ፡ የቆዳን ፡ ወይም ፡ ሌሎችን ፡ የፋ ብሪካ ፡ ፍሬ ፡ ምልክቶችን ፡ የምግብ ፡ ዕቃዎችን ፡ የመድኀኒቶችን ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፤ ይህ ፡ አድራጎት ፡ የሚመለከተው ፡ ማኅተሞችን ፡ በመሰርሰሪያ ፡ ማኅተም ፡ የሚሠሩ ፡ ምልክቶ ችን ፡ እርጥብ ፡ ማኅተሞችን ፡ (ኤቲኬት) ፡ ምልክቶችን ፡ ወይም ፡ ማንኛዎቹ ንም ፡ ሌሎች ፡ ምልክቶች ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ የሠራ ፤ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ አስመስሎ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እነዚህኑ ፡ ምልክቶች ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ሆኑና ፡ እንዳልተነኩ ፡ እንዳልተለወጡ ፡ በማስመሰል ፡ እያወቀ ፡ የሠራባቸው ፡ ወይም ፡ በመሰል ፡ በተለወጡት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በተለወጡት ፡ የሠራባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሦስት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፬ ። ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ቴምብሮችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ —

(ሀ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ዐቅድ ፡ እግቡ ፡ ለማድረስ ፡ ሲል ፡ በግ ልጽ ፡ የታወቁ ፡ ባለዋጋ ፡ የሆኑ ፡ ቴምብሮችን ፡ በተለይም ፡ የገንዘብ ፡ መክ ፈያ ፡ ምልክት ፡ የሆኑትን ፡ ማኅተሞች ፤ ቴምብርነት ፡ ያላቸውን ፡ ወረቀቶች ፡ የፖስታ ፡ ወይም ፡ የቀረጥ ፡ ቴምብሮችን ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ የሠራ ፡ የለ ወጠ ፡ ወይም ፡ ያስመሰለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) ቴምብሮቹ ፡ ከተሠራባቸው ፡ ወይም ፡ ከተደመሰሱ ፡ በኋላ ፡ ገና ፡ ዋጋ ፡ እንዳላቸው ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ያሉ ፡ አስመስሎ ፡ ሊሠራባቸውና ፡ ሊያሠራባቸው ፡ ቴምብሮችን ፡ የማስመሰል ፡ መልክ ፡ የሰጣቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ሲገመት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ነገሩ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ ቀድሞ ፡ የተሠራባቸውና ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በተለወጡ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ በሆኑ ፡ የፖስታ ፡ ወይም ፡ የቀረጥ ፡ ቴምብሮች ፡ በድንገት ፡ ተገልግሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ብቻ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፸፩ ። መመዘኛዎችንና ፡ መለኪያዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሌሎችን ፡ ለማታለል ፡ በማሰብ ፡—

(ሀ) ክብደቶችን ፡ ሚዛኖችን ፡ መለኪያዎችን ፡ ወይም ፡ ለንግድና ፡ ለመለዋወጫ ፡ የተመደቡትን ፡ ሌሎች ፡ መሣሪያዎችን ፡ በሐሰት ፡ የለዋወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) መብት ፡ ሳይኖረው ፡ በግልጽ ፡ የታወቁትን ፡ የመመርመሪያ ፡ ወይም ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትናነት ፡ ያላቸውን ፡ የመለያ ፡ ምልክቶች ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ምልክቶችን ፡ በነዚህ ፡ መሣሪያዎች ፡ ላይ ፡ ያተመ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በነዚህ ፡ በሐሰተኞች ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በተለወጡት ፡ እያወቀ ፡ የሠራባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስራትና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፸፪ ። ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ማግባትና ፡ ስለ ፡ መግዛት ፤ በአደራ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥና ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ሐሰተኛ ፡ መሆናቸውን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ መለወጣቸውን ፡ እያወቀ ፡ ቴምብሮችን ፡ ወረቀቶችን ፡ ምልክቶችን ፡ በግልጽ ፡ የታወቁትን ፡ መመዘኛዎችን ፡ ሚዛኖችን ፡ መለኪያዎችን ፡ አምጥቶ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ያገባ ፤ የገዛ ፤ ወይም ፡ ፈልጎ ፡ ያገኘ ፡ በባለአደራነት ፡ ለማስቀመጥ ፡ የተቀበለ ፤ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ለሽያጭና ፡ ለስጦታ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፯ ። የማሳሳት ፡ ዐቅድ ፡ በሌለው ፡ አሳብ ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የማሳሳት ፡ አሳብ ፡ ሳይኖረው ፡—

(ሀ) ባንክ ፡ ኖቶችን ፤ ገንዘቦችን ፤ ባለዋጋ ፡ የሆኑትን ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ቴምብሮችን ፤ ያስመሰለ ፡ ይልቁንም ፡ ለማስታወቂያ ፡ ሲል ፡ ያወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ አምሳያ ፡ አድርጎ ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ በማድረግ ፡ የስሕተት ፡ ጉዳት ፡ የሚፈጥር ፡ ወይም ፡ ለመፍጠር ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ በአምሳያ ፡ የተሠራውን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ያስገባ ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስም ፡ የተቀበለ ፡ ለሽያጭና ፡ ለስጦታ ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ያቀረበ ፡ ወይም ፡ እንዲዘዋወር ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ ለማሳሳት ፡ ወይም ፡ ለማታለል ፡ እጅግ ፡ የሚያሠጋ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) በግልጽ ፡ በሚነገሩ ፡ ጉዳዮች ፡ ለኪነ ፡ ጥበብ ፡ ወይም ፡ ለወሬ ፡ ማቀባበያና ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለሚያገለግሉ ፡ ነገሮች ፤ ይህንኑ ፡ ከሚሠሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠበት ፡ ከሆነ ፡ ማናቸውንም ፡ ቅጣት ፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፰ ። ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ገንዘብ ፡ በባለዋጋ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ማኅተሞች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ደንበኛ ፡ የሆነው ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ሳያዘው ፡ ወይም ፡ ሳይፈቅድለት ፡—

(ሀ) ገንዘብ ፡ ለማተሚያ ፡ ወይም ፡ ለፖስታ ፡ ቴምብሮች ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ ለሆኑ ፤ ሰነዶችና ፡ ማኅተሞች ፡ መሥሪያ ፡ የሆኑትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ፎርሞች ፡ ከውሮች ፡ ወረቀቶች ፡ ዐይነቶች ፡ ወይም ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ሌሎች ፡ ዐይነቶች ፡ ዕቃዎችንና ፡ መሣሪያዎችን ፡ የሠራ ፡ ከእጁ ፡ እንዲገባ ፡ ያደረገ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያገባ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ያቀረበ ፡ ወይም ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ማኅተሞችን ፡ ወይም ፡ ሰነዶችን ፡ ወይም ፡ ቴምብሮችን ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ወረቀቶችን ፡ ወይም ፡ ገንዘቦችን ፡ እንዲወጡ ፡ የሚላኩትን ፡ ትእዛዞች ፡ የተቀበለ ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ ያስፈጸመ ፡ ወይም ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ ያሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። የሐሰት ፡ ነገር ፡ መሥሪያዎችና ፡ መሣሪያዎች ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ መብቱና ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ሊሠራበት ፡ በማሰብ ፡ ሐሰተኛ ፡ የገንዘብ ፡ ወረቀቶችን ፡ ገንዘቦችን ፡ የባንክ ፡ ወረቀቶችን ፡ ማኅተሞችን ፡ በግልጽ ፡ የታወቁ ፡ ምልክቶችን ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚሆን ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የመሳሰለውን ፡ መሥሪያ ፡ የሚሆን ፡ ወረቀት ፡ ለገንዘብ ፡ የሚሆን ፡ ማዕድን ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የመሳሰለ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ ሊያገለግል ፡ የሚችለውን ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ የሠራ ፡ ያገኘ ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ የማቅለጫና ፡ የማተሚያ ፡ መሣሪያ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) መሥሪያዎቹና ፡ መሣሪያዎቹ ፡ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱን ፡ ወይም ፡ የሕዝቡን ፡ ባለሥልጣን ፡ ማኅተም ፡ በሐሰት ፡ ለመሥራት ፡ የሚያገለግሉ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፸ ። ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ስለሚደረግለት ፡ ጉዳይ ።

(፩) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ አንደኛውን ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ በማዘጋጀቱ ፡ ጉዳይ ፡ ተካፋይ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ለማቅለል ፡ እንዲያውም ፡ ከማናቸውም ፡ ቅጣት ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ የሚችለው ፡— [ቍ ፡ ፫፻፸፭ ።]

(ሀ) እነዚህን ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለመለወጥ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ነገሮች ፡ በሥራ ፡ ከመዋላቸው ፡ በፊት ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ ያጠፋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ባለሥልጣኖች ፡ ከማወቃቸው ፡ አስቀድሞ ፡ በሕዝብ ፡ እጅ ፡ እንዳይዘዋወሩ ፡ እንዳያገለግሉ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ እንዳያደርሱ ፡ ለማገድ ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ የነዚህን ፡ መሣሪያዎችና ፡ ፋብሪካዎች ፡ መኖር ፡ ወይም ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ወንጀለኞችን ፡ ገልጾ ፡ እንዲታሰሩ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ አድራጎቶቹ ፡ ምክንያት ፡ ከቅጣት ፡ የዳነም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ ለወደፊት ፡ አደጋ ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችልና ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጥንቃቄና ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ተግባር ፡ ሊፈጸምበት ፡ እንዲችል ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ማረጋገጫ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ሙሉ ፡ የግል ፡ ነጻነቱ ፡ ተወስኖ ፡ በጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቈይ ፡ ለማድረግ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፻፴፱ ፡ ፻፵፱ ፡ እስከ ፡ ፻፶፭ ።]

BACK



(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በሁለት ፡ ምዕራፎች ፡ እንደተመለከተው ፡ ሐሰተኛ ፡ ነገር ፡ የመሥራቱ ፡ ወይ ፡ ሐሰተኛ ፡ የመለወጡ ፡ ዋጋውን ፡ የማዋረዱና ፡ ወይም ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ የመሥራቱ ፡ ወንጀል ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ በመንግሥትና ፡ በጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የማያደርስ ፡ መሆኑ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕጋዊው ፡ ወሰን ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱን ፡ ያቃልላል ። [ቍ ፡ ፻፹፬ ። ]

ቍ ፡ ፫፻፹፮ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ጉዳዮችና ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተመከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ በሚያጋጥሙበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቅጣት ፡ ማክበድን ፡ ድንጋጌ ፡ ከሐሳቡ ፡ ሳይለይ ፡ ይህንኑ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ የሚከተለው ፡ የወንጀሉ ፡ ተግባርና ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከተው ፡ ልማዳዊ ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ የተያዘ ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ስለዚሁ ፡ ወንጀል ፡ የተባበሩ ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ ወንበዴዎች ፡ ተቋቁመው ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ማኅበረተኞች ፡ በመሆን ፡ የተግባሩን ፡ ድርጅት ፡ አዘጋጅተው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ እንዲሁም ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ስሜት ፡ በሚያነሣሣ ፡ ወንጀለኛነት ፡ የተሠራ ፡ ተግባር ፡ መሆኑን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፹፩ ፡ (መ) ፡ ፺ ። ]

(፪) ወንጀሉ ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ስሜት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ሐሰተኛ ፡ ገንዘብ ፡ የመሥራት ፡ ወንጀል ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ ኀምሳ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ይደርሳል ።

(፫) በማናቸውም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ ጸጥታው ፡ ማረጋገጫ ፡ የመውረስን ፡ ደንብ ፡ የሚመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ መሣሪያዎችና ፡ የመሥሪያ ፡ ዕቃዎችን ፡ የማፍረስና ፡ የማጥፋት ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፻፵፬ ። ]

ቍ ፡ ፫፻፹፯ ። የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታትን ፡ ጥቅሞች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ የሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ገንዘብን ፡ የወረቀት ፡ ገንዘብን ፤ ባንክ ፡ ኖቶችን ፤ ማኅተሞችን ፡ ቴምብሮችን ፡ የመጓዣ ፡ ሰነዶችን ፡ ምልክቶችን ፡ በግልጽ ፡ የታወቁ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መመዘኛዎችን ፡ መለኪያዎችንና ፡ መስፈሪያዎችን ፡ በማሳሳትና ፡ በመለወጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ተሠርተው ፡ ስለሚገኙትም ፡ ልዩ ፡ልዩ ፡ ወንጀሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገ ፡ስምምነት ፡ ሲኖር ፡ ወይም ፡ ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ የሚሠራው ፡ ተለዋዋጭ ፡ የውለታ ፡ መመላለስ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ፬ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## በሕዝብ ፡ ጥቅሞችና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### በሕዝብ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በሰነዶች ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፫ ። በግዙፍ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የጉዳት ፡ አደጋ ፡ ለማድረስ ፡ በማቀድ ፡ ወይም ፡ ለራሱም ፡ ሆነ ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘትና ፡ ለማስገኘት ፡ በማሰብ ፡ —

(ሀ) በሐሰት ፡ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ ግንኙነት ፡ ማናቸውንም ፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ የሰነድነት ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ጽሑፍና ፡ መሣሪያ ፡ አሳስቶ ፡ በመፍጠር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ማስረጃ ፡ ሊመስል ፡ የሚችል ፡ ሰነድን ፡ በሐሰት ፡ የፈጠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የይምሰል ፡ ማስረጃ ፡ ለመፍጠር ፡ በማኅተም ፡ ወይም ፡ በፊርማ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ በተደረገ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ የጣት ፡ ፊርማ ፡ ያታለለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ይልቁንም ፡ እውነተኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ በመለወጥና ፡ በመደለዝ ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ በሐሰተኛ ፡ ፊርማ ፡ በእጁ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ በአሻራ ፡ ፊርማ ፡ በመተካት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ ለአድራጊው ፡ ምስክርነት ፡ የሚያገለግለውን ፡ ሰነድ ፡ በሌላ ፡ ፊርማ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በመፈረም ፡ ያሳሳተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ ያሳሳተ ፡ ይልቁንም ፡ የሠራውን ፡ ወይም ፡ የፈረመውን ፡ ሰው ፡ ስሙን ፡ ወይም ፡ ፊርማውን ፡ በመለወጥ ፡ በማሻሻል ፡ በከፊልም ፡ ቢሆን ፡ ቃሉን ፡ በመቀነስ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ በመጨመር ፡ አኀዞችን ፡ ቃላቶችን ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታና ፡ መግለጫ ፡ በመለወጥ ፡ ያሳሳተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፬ ። በርቀት ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ዐቅዶች ፡ ለማከናወን ፡ ሲል ፡ ሰነዱ ፡ በሚጻፍበት ፡ ጊዜ ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆኑ ፡ ቃላትን ፡ ጣልቃ ፡ በማግባት ፡ የጻፈ ፡ ወይም ፡ እንዲጻፉ ፡ ያደረገ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤ ይህም ፡ ጽሑፍ ፡ በሕጋዊ ፡ ጕዳይ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይፈረድበታል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፭ ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ የወንጀል ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ በማቀድ ፡ —

(ሀ) አንድ ፡ ሰው ፡ በሐሳቡ ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፍቺ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ መስሎት ፡ ተሳስቶ ፡ እንዲፈርም ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ፈቃዱ ፡ ባልሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሰነድ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፮ ። በሐሰት ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የሐሰት ፡ ነገርን ፡ በመፍጠር ፡ ወንጀል ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ በፈጠረው ፡ ሐሰተኛ ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ በተለወጠ ፡ ሰነድ ፡ እያወቀ ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ስለ ፡ ማሳሳት ፡ ወንጀል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ልክ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፯ ። የመንግሥትንና ፡ የወታደራዊን ፡ ሰነዶች ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በመለወጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

(፩) ሰነዶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛ ፡ የመለወጡ ፡ ወንጀል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አድራጎት ፡ ረገድ ፡ የተፈጸመው ፡ ወይም ፡ የተገለገለበት ፡—

(ሀ) ባንድ ፡ የመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ በተደረገ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ በሚወጣ ፡ ባለዋጋ ፡ በሆነ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ የሕዝብን ፡ ጥቅም ፡ በሚመለከት ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ በገባ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ሟቹ ፡ ራሱ ፡ በእጁ ፡ በጻፈው ፡ ኑዛዜ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ያገር ፡ መከላከያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ አቋቋሙንና ፡ ድርጅቱን ፡ የሥራ ፡ ተግባሩንና ፡ ቀጥተኛ ፡ ጥቅሙን ፡ በሚመለከቱት ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፪) ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ትን ፡ ሰነዶችና ፡ መዝገቦች እንዲያቋቁም ፡ ወይም ፡ እንዲመዘግብ ፡ እንዲጠብቅና ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቅጂዎች ፡ እንዲሰጥ ፡ የታዘዘ ፡ ወይም ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ አንድ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፹፰ ። ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍ ፡ ፫፻፹፫ ፡ በተመለከቱት ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ዐቅዶች ፡ መሠረት ፡ ሊያዝበት ፡ መብት ፡ በሌለው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሰነድ ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፤ የቀደደ ፡ ያጠፋ ፡ የሠረዘ ፤ ወይም ፡ ወስዶ ፡ የደበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ወይም ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህን ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በዘመዱ ፡ ላይ ፡ የቅርብ ፡ ዝምድና ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከወንጀለኛው ፡ ጋራ ፡ በጥቅምና ፡ በኑሮ ፡ ኅብረት ፡ በሚኖር ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስላ ፡ ተበዳዩ ፡ ሆነው ፡ ለመክሰስ ፡ መብተኛ ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አቤቱታ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ የክሱን ፡ ጉዳይ ፡ መከታተል ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፫፻፹፱ ። የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ በሆነ ፡ ሰነድ ፤ መዝገብ ፤ ወይም ፡ ባንድ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ጥፋቱም ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይወስናል ።

(፪) ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ ሹም ፤ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፤ አንድ ፡ ወታደር ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሰነድና ፡ መዝገብ ፡ እንዲጠብቅ ፡ እንዲሠራበት ፤ እንዲያስቀምጥና ፡ እንዲሰጥ ፡ በግልጽ ፡ የተሾመ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

BACK



(፫) ጥፋተኛው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የሚ ደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይፈርድበታል ።

**ቍ ፡ ፫፻፺ ። የንግድ ፡ ሰነዶችንና፡ የባንክ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።**

(፩) ሰነድን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የመለወጡ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ የመገልገሉ ፡ ወንጀል ፡ የተደረገው ፡—

(ሀ) በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ ቼክ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ የማዘዣ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፤ በገንዘብ ፡ ማከማቻ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ለባንክ ፡ ማስረከቢያ ፡ በሆነ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ማስቀመጫና ፡ በማበደሪያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በእንዱስትሪ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ማኅበር ፡ አክሲዮኖች ፡ ወይም ፡ በግ ዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

(፪) የተደረገው ፡ ወንጀል ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ የማጥ ፋት ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስራት ፡ ነው ።

የተፈጸመውም ፡ በወንጀለኛው ፡ ቸልተኛነት ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገ ንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይወስናል ።—

**ቍ ፡ ፫፻፺፩ ። እንደ ፡ ዋና ፡ ስለሚቈጠር ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ።**

ትክክለኛነታቸው ፡ በባለሥልጣን ፡ የተረጋገጠላቸው ፡ ወይም ፡ የዋናው ፡ ትክ ክለኛ ፡ ግልባጮች ፡ መሆናቸው ፡ የተመሰከረላቸው ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ አግባብና ፡ ሥርዐት ፡ በዋናው ፡ ሰነድ ፡ ምትክ ፡ የሚሆኑ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዋናው ፡ ማስረጃ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፪ ። የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መመላለሻ ፡ ወረቀቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ በነዚሁ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።**

(፩) ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡—

(ሀ) በየብስ ፤ በባሕር ፡ ወይም ፡ በአየር ፡ መንገድ ፡ ለሰዎች ፤ ለከብቶች ፡ ወይም ፡ ለዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ለሸቀጦች ፡ መመላለሻ ፡ የሆኑትን ፡ የትራንስፖርር ፡ ወረቀቶች ፡ ቲኬቶች ፡ ወይም ፡ የመጓዣ ፡ ሰነዶች ፡ መብት ፡ ሳይሰጠው ፡ የሠራ ፤ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ እውነተኛ ፡ እንዲመስሉ ፡ አድርጎ ፡ የለዋወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እውነተኛ ፡ የሆኑትን ፡ እነዚህን ፡ ወረቀቶች ፡ ከተሠረዙ ፡ ወይም ፡ ከተበሱ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሊገለገልባቸው ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ እንዲገለገልባቸው ፡ ለማድረግ ፡ የእውነተኛውን ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ የቲኬት ፡ መልክ ፡ የሰጣቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ በመቀጮ ፡ ይቀጣል ። ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ማንም ፡ ሰው ፡ እያወቀ ፡ እነዚሁኑ ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛ ፡ የተለወጡትን ፡ ወይም ፡ ያገለገሉትን ፡ ወረቀቶች ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ አድርጎ ፡ የሠራባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፯፻፴፯ ።]

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

<u>በምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ።</u>

<u>ቍ ፡ ፫፻፺፫ ። ስለ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ።</u>

(፩) ማንም ፡ ሰው ፤ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ የተሻሻለ ፡ የሥራ ፡ ደረጃ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡—

(ሀ) ተገቢ ፡ መብት ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችሉ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወይም ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃዎችን ፡ ወይም ፡ የምስክርነት ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነዶችን ፤ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ጽሑፎችና ፡ ሰነዶችም ፡ ቢሆኑ ፤ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሰነዶች ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ የያዙትን ፡ ጽሑፎች ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ በማይገባ ፡ መንገድ ፡ እንዲገለገልበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የተለወጠውን ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሰነዱ ፡ ትክክለኛ ፡ ሆኖ ፡ ለራሱ ፡ ያልተሰጠ ፡ ወይም ፡ እርሱን ፡ የማይመለከተው ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ያላገባብ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ይህ ፡ ሰነድ ፡ የግል ፡ ጕዳይን ፡ ብቻ ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡
የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ነው ። ወይም ፡ ሰነዱ ፡ የሕዝብ ፡ ጕዳይን ፡ የሚመለከት ፡
ሆኖ ፡ እንደ ፡ መለያ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ያመጣጡን ፡ መሠረት ፡ የሚ
ገልጽ ፤ የችግረኛነት ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ማረጋገጫ ፡ ምስክርነት ፡ የችሎታ ፡
ወይም ፡ ችሎታ ፡ የማጣት ፡ ያንድ ፡ መዝገብ ፡ ቅጂ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ (በኦፊ
ሲየል) ፡ የተደረገ ፡ የምርመራ ፡ ሰነድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡
ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፪) ይህን ፡ ወንጀል ፡ የፈጸመው ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለ
ሥልጣን ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፤ የሕዝብ ፡ ወይም ፡ የወታደ
ራዊ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ
ውም ፡ ይህንኑ ፡ ሰነድና ፡ መዝገብ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ እንዲመዘግብ ፡ እንዲጠብቅ ፡
እንዲያስቀምጥና ፡ እንዲሠራበት ፡ የታዘዘ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
ይህንንም ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ በተለየ ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለመለወጥ ፡ ሳያቅድ ፡ ሠር
ቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡
አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።
[ቍ ፡ ፫፻፹፫ ።]

አድራጊው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡
ቤቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡
ይፈርዳል ።

## ቍ ፡ ፫፻፺፬ ። ሐሰተኛ ፡ የሆኑትን ፡ ግልጽ ፡ ምስክርነቶችን ፡ በማጭበርበር ፡ ስለ ፡ ማግኘት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማ
ስገኘት ፡ ወይም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ ዐቅዶ ፡—

(ሀ) አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሹምን ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛን ፡ ወይም ፡
አንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኛን ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ያለ
ውን ፡ ሥራ ፡ ለመመልከት ፡ ወይም ፡ ለማደራጀት ፡ ተገቢ ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡
ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ በማታለል ፤ ያንድ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረትን ፡ ትክክለኛነት ፡
ያንድ ፡ ማስረጃን ፡ (ሰነድ) ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ፊርማን ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ግል
ባጭን ፡ ትክክለኛነት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ነገር ፡
በሐሰት ፡ እንዲያረጋግጥ ፡ እንዲመሰክር ፡ ያግባባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ሌሎቹን ፡ ለማሳሳት ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሰነድ ፡ እያወቀ ፡ የተ
ገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፭ ። ሐሰተኛ ፡ የሐኪም ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ።

(፩) ማናቸውም ፡ ሐኪም ፡ የጥርስ ፡ ሐኪም ፡ መድኀኒት ፡ ሻጭ ፡ (ቀማሚ) ፡ ወይም ፡ የከብት ፡ ሐኪም ፤ አዋላጅ ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ የሐኪም ፡ ምስክርነት ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማንኛዎቹም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ሰዎች ፡ በማስረጃ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ለመቅረብ ፡ የተዘጋጀና ፡ ለተቀባዩ ፡ ሰው ፡ የማይገባ ፡ ጥቅም ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ የሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ መብታዊ ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፤ ሐሰተኛ ፡ የሆነ ፡ የሕክምና ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ የጻፉ ፡ ወይም ፡ የሰጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ ወንጀለኛነቱ ፡ በተደጋገመ ፡ ጊዜ ፡ የሞያውን ፡ ሥራ ፡ በሚመለከተው ፡ ጥፋት ፡ የሚወሰነው ፡ የቅጣት ፡ ደንብ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፪፻፶፪ ፡ (ሐ) ።]

(፪) ሐሰተኛውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የመስጠት ፡ ጕዳይ ፡ የተከናወነው ፡ የማይገባ ፡ ስጦታ ፡ በመሰጠት ፡ ወይም ፡ በመስጠት ፡ ተስፋ ፡ በማባበል ፡ በመደለል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራት ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ከገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ጋራ ፡ ይጣመራል ። [ቍ ፡ ፺ ።]

(፫) ሐሰተኛውን ፡ ምስክርነት ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የሰላማዊ ፡ የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ወይም ፡ የወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የማስተዳደር ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ ባልደረባ ፡ ሆኖ ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ በዚሁ ፡ ባገኘው ፡ ሥልጣን ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ፡ ለተመለከተው ፡ ጥፋቱ ፡ የሚወሰንበት ፡ ቅጣት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ነው ። ወይም ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) ፡ ለተመለከተው ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፬) እንዲሁም ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለማታለል ፡ ሲል ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሐሰተኛ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ የተገለገለ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፮ ። በግልጽ ፡ የታወቁ ፡ ወንጀሎች ።

ሐሰተኛውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፤ ወይም ፡ የሐሰት ፡ ማስረጃ ፤ ወይም ፡ ለራሱ ፡ ያልተሰጠውን ፡ ወይም ፡ እርሱን ፡ የማይመለከተውን ፡ ትክክለኛ ፡ የምስክር ፡ ወረ

BACK



ቀት ፡ ተቀብሎ ፡ የተጠቀመው ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ መነሻ ፡ አድርጎ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀል ፡ ለመሥሪያ ፡ የተገለገለበት ፡ ሲሆን ፤ ይልቁንም ፡ እምነት ፡ ማጓደልን ፡ ወይም ፡ የማታለልን ፡ የመሳሰለ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህም ፡ ወንጀሉ ፡ ሊሠራ ፡ ተሞክሮም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠቅላላውን ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ መደራረብ ፡ የቅጣት ፡ ማከበድን ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመከተል ፡ ቅጣት ፡ ይወስንበታል ። [ቍ ፡ ፹፪ ።]

ቍ ፡ ፫፻፺፯ ። ሥራ ፡ ሰጪዎችና ፡ የማደሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ፡ አሰጣጥና ፡ አመዘጋገብ ።

(፩) ሥራ ፡ ሰጪዎች ፤ የማደሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፤ ባለሆቴሎች ፤ የእንግዳ ፡ ማደሪያ ፡ ባለቤቶች ፤ ወይም ፡ በሕግ ፡ አግባብና ፡ በልዩ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ለባለሥልጣኖች ፡ መቈጣጠሪያ ፡ እንዲሆን ፡ መዝገብን ፡ የሚይዙ ፡ ወይም ፡ የሰዎችን ፡ ስም ፡ የሚጽፉ ፡ ሰዎች ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ በመጣስ ፡—

(ሀ) እያወቁ ፡ እውነተኛ ፡ ያልሆነውን ፡ ወይም ፡ ከእውነተኛ ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰለውን ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የሰውና ፡ የዕቃ ፡ መግለጫዎችን ፡ የመዘገቡ ፡ ያስመዘገቡ ፡ ወይም ፡ እንዲመዘገብ ፡ የፈቀዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በእውነተኛው ፡ መሠረት ፡ ሳይመዘግቡ ፡ የተዉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) አድራጊው ፡ ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ በጥቅም ፡ ፍላጎት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ እስራቱ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጮ ፡ እስከ ፡ ደንበኛው ፡ ከፍተኛ ፡ መቀጮ ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፺፰ ። ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለመለወጫ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ጥበቦች ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ለመሥሪያ ፡ እንዲሆኑ ፡ አስቦ ፡ ጽሑፎችን ፤ የምስክር ፡ ወረቀቶችን ፡ ዲፕሎሞችን ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶችን ፤ ለመሥሪያ ፡ የሚሆኑትን ፡ መሣሪያዎችና ፡ ጥበቦች ፡ የሠራ ፤ ፈልጎ ፡ ያገኘ ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ ያስቀመጠ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ለሺያጭና ፡ ለስጦታ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እነዚህን ፡ መሣሪያዎች ፡ ማናቸውንም ፡ አገልግሎት ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ያጠፋቸውን ፡ ሰው ፡ ከማናቸውም ፡ ቅጣት ፡ ለማዳን ፡ ይቻላል ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

### ቍ ፡ ፫፻፺፱ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ ዋጋቸውን ፡ ስለ ፡ ማርከስ ።

ማንም ፡ ሰው ፤ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ በንግዱ ፡ ለማታለል ፡ በማቀድ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፤ አስመስሎ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ዋጋቸውን ፡ ያረከሰ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፬፻ ። የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ በማቀድ ፡ አስመስሎ ፡ የተሠሩትን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የተለወጡትን ፡ ወይም ፡ ዋጋቸው ፡ የተዋረደውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ ወይም ፡ እንዳልተበላሹና ፡ እንዳሉ ፡ በማስመሰል ፡ ለሺያጭ ፡ ያቀረበ ፡ ወይም ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ እጅ ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፤ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ትጋት ፡ ወይም ፡ ጥንቃቄ ፡ የማድረግ ፡ ተግባር ፡ ያለበት ፡ ሲሆንና ፡ በተለይም ፡ በነጋዴነቱ ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በቸልተኛነቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስበት ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፬፻፩ ። የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማስመጣት ፡ ስለ ፡ መግዛትና ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የተለወጡትን ፤ ሐሰተኛ ፡ የሆኑትን ፡ የተበላሹትን ፡ ወይም ፡ ዋጋቸው ፡ የረከሰውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ዐይነታቸው ፡ ይህ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ሌሎቹን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ሰዎች ፡ በንግድ ፡ ለማታለል ፡ በማቀድ ፡ ያስመጣ ፤ የገዛ ፤ የተቀበለ ፡ በአደራ ፡ ያስቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።—

### ቍ ፡ ፬፻፪ ። የማከበድ ፡ ቅጣቶችና ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ።

(፩) አድራጊው ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ተግባር ፡ ሞያው ፡ አድርጎ ፡ ይዞት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ እንደ ፡ ነገሩም ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

(፪) ዕቃውን ፡ የመውረስና ፡ ፍርድን ፡ በግልጽ ፡ የማውጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በማና ቸውም ፡ ጊዜ ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪፻፫ ። ጤናን ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ ዕቃን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ መለወጥና ፡ ማበላሸት ።

ጤናን ፡ ለመጉዳት ፡ የሚችሉ ፡ ምግቦችን ፤ ሸቀጦችን ፡ ወይም ፡ የተበላሹ ፡ ዕቃዎ ችን ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ ማበላሸትና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌ ዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፭፻፲፩ ።]

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሊደበቅ ፡ የሚገባውን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

ቍ ፡ ፪፻፬ ። የወታደርን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ወታደር ፤ ወይም ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ የሚ ገኝ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ክዳትና ፡ ስለ ፡ ስለላ ፡ ጉዳይ ፡ ለዚሁ ፡ የተመደበውን ፡ ቅጣት ፡ ከሚያስወስንበት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ በተፈጥሮዋቸው ፡ ምስጢር ፡ የሆኑ ትን ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ምስጢር ፡ ሆነው ፡ እንዲጠበቁ ፡ የተደረጉትን ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ጉዳዮች ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ወሬያ ቸውን ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ እነዚህ ፡ ማስረጃዎችና ፡ ሰነዶች ፡ ለሕዝብ ፡ ሊገለጹ ፡ ያልተመደቡ ፡ ሆነው ፡ በሥራው ፡ ወይም ፡ በወታደራዊ ፡ ሥልጣኑ ፡ ሊያውቃቸው ፡ የቻለውን ፡ ለሕዝብ ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፪፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷፭ ።]

የምስጢሩ ፡ መጠበቅ ፡ ጊዜ ፡ ያለፈም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፤ እነዚህ ፡ የተባሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ለሕዝብ ፡ ግልጽ ፡ የሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ካልደረሰ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱም ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚ ሆነው ፡—

(ሀ) በቍጥር ፡ ቃል ፡ የገባ ፡ ምስጢራዊ ፡ መረጃ ፡ ወይም ፡ ሰነድ ፡ እንደሆነና ፡ ጉዳዩም ፡ በተለይ ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲጠብቅ ፡ በአደራ ፡ የተ ሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛው ፡ ይህን ፡ ምስጢር ፡ እንዳይገልጽ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ይህ ፡ ምስጢር ፡ በመገለጹ ፡ ምክንያት ፡ በተለይ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥቅም ፡ ባላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ አድርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

BACK



(፫) የምስጢር ፡ መግለጹ ፡ ጉዳይ ፡ በቸልተኛነት ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከላይ ፡ በ(ሀ) ለተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ። በ(ለ) ለተመለከተው ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ ደግሞ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፬፻፰ ። የሥራን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) የጦር ፡ መኰንኖች ፤ የጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኞች ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችና ፡ በጠቅላላውም ፡ እንደ ፡ መንግሥት ፡ ሹማምትና ፡ ሠራተኞች ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡ (ቍ ፡ ፬፻፲) ፡ በማናቸውም ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ቢሆን ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፱ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አነጋገር ፡ ምስጢር ፡ ሆነው ፡ ሊጠበቁ ፡ የሚገባቸውን ፡ መረጃዎች ፡ ሰነዶችና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ በሹመታቸው ፤ በሥራቸው ፡ በሠራተኛነታቸው ፡ ምክንያት ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ የተገለጸላቸውን ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ያወቁትን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ምስጢራዊ ፡ ሰነድና ፡ መረጃ ፡ በሥራቸውና ፡ በሹመታቸው ፡ ላይ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሹመታቸው ፡ ከቀረበት ፡ ጊዜ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ምስጢር ፡ የገለጹ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ምስጢር ፡ በመጠበቅ ፡ ግዴታቸው ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የሚመለከታቸውን ፡ አላፊነትና ፡ ግዴታ ፡ በሚገባ ፡ ባለመጠበቅ ፡ የፈጸሙት ፡ የምስጢር ፡ መግለጽ ፡ ወንጀል ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ተግባራቸውን ፡ ካለመጠበቃቸውም ፡ የተነሣ ፤ የምስጢር ፡ መግለጻቸው ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

(፫) የምስጢር ፡ መግለጹ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፬፻፱ ። የተፈቀደ ፡ የምስጢር ፡ መግለጽ ፡ ጉዳይ ።

የክፍሉ ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ከሆነው ፡ ከፍተኛ ፡ የክፍል ፡ ሹም ፡ ከብሔራዊ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ካስተዳደርና ፡ ከወታደር ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ሹማምቶች ፡

የጽሑፍ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጥቶ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ይህንኑ ፡ ለመሥራት ፡ በተፈቀደላቸው ፡ የምርመራ ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ የተደረገ ፡ የምጢስር ፡ መግለጽ ፡ ጉዳይ ፡ አያስቀጣም ።

ቍ ፡ ፬፻፯ ። የግል ፡ ሞያን ፡ የሥራ ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበባቸው ፡ ጊዜ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ የሚቀጡት ፡—

(ሀ) የማናቸውም ፡ ሃይማኖት ፡ የሆኑት ፡ ቀሳውስት ፡ ወይም ፡ ካህናት ፤

(ለ) ጠበቆች ፡ የሕግ ፡ አማካሪዎች ፡ የፍርድ ፡ እንደራሴዎች ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ (ኤክስፐርቶች) ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ የሰጡ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ እማኞች ፤ ነባሪዎች ፡ ተርጓሚዎችና ፡ አስተርጓሚዎች ፤

(ሐ) ውል ፡ አዋዋዮች ፤ ባለባንኮች ፡ ዲሬክተሮች ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ፤ ሥራ ፡ መርማሪዎች ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተሰጣቸውን ፡ ምስጢር ፡ በእምነት ፡ መጠበቅ ፡ የሚገባቸው ፡ ያንድ ፡ ግላዊ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞች ።

(መ) ሐኪሞች ፤ የጥርስ ፡ ሐኪሞች ፡ መድኀኒት ፡ ሻጪዎችና ፡ ቀማሚዎች ፤ አዋላጅ ፡ ሴቶች ፡ አስታማሚዎችና ፡ ረዳቶቻቸው ፤

በግል ፡ ሞያ ፡ ሥራቸው ፡ ምክንያት ፡ ለማወቅ ፡ የቻሉትን ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ የተነገራቸውን ፡ ምስጢር ፡ በሞያ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ ሳሉም ፡ ሆነ ፡ ሥራቸውን ፡ ከለቀቁ ፡ በኋላ ፡ የገለጹ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በሞያ ፡ ሥራ ፡ መለማመድ ፡ ትምህርታቸው ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ሊያውቁ ፡ የቻሉትን ፡ ወይም ፡ የተሰጣቸውን ፡ የጥበባዊ ፡ ሥራ ፡ ምስጢር ፡ የገለጹ ፡ ተማሪዎች ፤ የጥበብ ፡ ሥራ ፡ መለማመጃ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ተለማማጆች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይደርስባቸዋል ።

(፫) የምስጢር ፡ መግለጹ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፬፻፰ ። እንዲገለጽ ፡ የተፈቀደ ፡ ምስጢር ።

(፩) በተለይ ፡ በፍርድ ፡ ችሎት ፡ ወይም ፡ በኢንሹራንስና ፡ በኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ክርክር ፡ ምስጢር ፡ መግለጽ ፡ የማያስቀጣው ፡—

(ሀ) ምስጢሩን ፡ ለመጠበቅ ፡ ጥቅም ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ምስጢሩን ፡ በያዘው ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ አቅራቢነትና ፡ ጠያቂነት ፡ የበላይ ፡ የሆነ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የጥበቃ ፡ ክፍል ፡ የሆነ ፡ የክፍሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣን ፤ የጽሑፍ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጉዳይ ፡ ባንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ተሰጥቶ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ምስጢሩ ፡ በግልጽ ፡ እንዲነገር ፡ የታዘዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፡ ደግሞ ፡ ለሕዝባዊ ፡ ተግባር ፡ ሲባል ፡ በፍርድ ፡ ችሎት ፡ እንዲመሰክር ፡ ወይም ፡ ላንዱ ፡ ባለሥልጣን ፡ መግለጫ ፡ እንዲሰጥበት ፡ የሕጉ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚፈቅዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በሕግ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ከደንበኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ በተሰጠ ፡ ግልጽ ፡ ውሳኔ ፡ ምስጢር ፡ እንዲገለጽ ፡ የታዘዘ ፡ ሲሆን ፡ የምስጢሩ ፡ ባለቤት ፡ የምስጢር ፡ መጠበቅ ፡ ተግባሩን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ መረጃ ፡ ከመስጠት ፡ ለመዳን ፡ አይችልም ።

ይህም ፡ ሲሆን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የምስጢረ ፡ ንስሓ ፡ ኑዛዜ ፡ እንዲገለጽ ፡ ማድረግ ፡ የማይገባ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፱ ። የሳይንስን ፤ የኢንዱስትሪን ፡ ወይም ፡ የንግድን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በያዘው ፡ የሥራ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ በሠራተኛነቱ ፡ ወይም ፡ በሁኔታው ፡ ምክንያት ፡ የተገለጸለትን ፡ ወይም ፡ ለማወቅ ፡ የቻለውን ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ወይም ፡ የንግድን ፡ የሲያንስን ፡ (ሥነ ፡ ጥበብ) ፡ ምስጢር ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፡ ጥበባዊ ፡ ዘዴ ፤ ባለቤቱን ፡ ወይም ፡ ባለይዞታውን ፡ ለመጉዳት ፡ ወይም ፡ ለራሱም ፡ ሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ አስቦ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ምስጢር ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፤ ይህ ፡ ጥፋቱ ፡ የግል ፡ ሞያን ፡ ወይም ፡ የሠራተኛነትን ፡ ምስጢር ፡ መግለጽ ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ ወንጀል ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፡ በሚገባው ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ቅጣት ፡ የማያስቀጣው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ላገር ፡ መከላከያ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ የሲያንስ ፡ (ሥነ ፡ ጥበብ) ፡ ምስጢርን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክሱን ፡ የሚያቀርበው ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሆኖ ፡ የቅጣት ፡ ማከበጃው ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፬፻፩ ።]

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፬፻፲ ። መሠረቱ ።**

(፩) የሕዝብን ፡ ጒዳይ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹማምትና ፡ ሠራተኞች ፤ የሕዝብ ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ሹማምትና ፡ ሠራተኞች ፤ በጠቅላላውም ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ የመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ ኀይል ፡ የተሰጣቸው ፡ ሁሉ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ እንዲሁም ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ኀይል ፡ አባሎች ፡ ሁነው ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ እነርሱን ፡ በተለየ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከተጻፈው ፡ አንዱን ፡ ወንጀል ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

(፪) የተከሰሱበት ፤ በወንጀለኛነት ፡ የፈጸሙት ፡ ወይም ፡ ሳይፈጽሙ ፡ በግድፈት ፡ የተዉት ፡ ተግባር ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ተግባራቸውም ፡ የወል ፡ ሕግ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ሆኖ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ በመሆናቸውና ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ከተጣለው ፡ እምነት ፡ የተነሣ ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ በመጣስ ፡ ቅጣታቸው ፡ የሚከብድ ፡ ሲሆን ፡ በዚሁ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ የተደነገጉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፩ ። ተደራራቢ ፡ የሆኑ ፡ የማስተዳደሪያና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቅጣቶች ።**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተጻፉት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለማድረግ ፡ የሚወሰኑት ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ ሳያስቀሩ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ አድራጊው ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ በደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ የሚፈጸምበት ፡ የካሣ ፡ አከፋፈል ፡ ደንብም ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በመንግሥትና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፩ ።

## በአገልግሎት ፡ የሥራ ፡ ግዴታዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፬፻፲፱ ። የሥራ ፡ ግዴታን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምቶችና ፡ ሠራተኞች ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሹመት ፤ ሥልጣን ፡ ሥራና ፡ ተግባር ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጽሙት ፡ በሚገባቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ተግባራቸው ፡ ወይም ፡ ለአገልግሎት ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ፡ የተመለከተውን ፡ ሥርዐት ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ የሠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህም ፡ አድራጎታቸው ፡ በሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በአገር ፡ ተወላጆች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ አድርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ። ወይም ፡ ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠሩት ፡ በተለይ ፡ በሚያስነቅፍና ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ከዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ በሕዝብ ፡ ወይም ፡ በግል ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስራቱና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮው ፡ በሕግ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ድረስ ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፬፻፳ ። የሥራ ፡ ማቆም ፤ አድማ ፡ በማድረግ ፤ የአገልግሎትን ፡ ሥራ ፡ መከናወን ፡ ስለ ፡ ማወክ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የሕዝብን ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱን ፡ የሥራ ፡ አከናወን ፡ መልካም ፡ እርምጃ ፡ ለማሰናከልና ፡ ለማወክ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ እንዲነሣ ፡ የገፋፋ ፡ ወይም ፡ የሞያውንና ፡ የሥራ ፡ ደንቡን ፡ ግዴታ ፡ በመጣስ ፡ በፈቃዱ ፡ ከአድማ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፲፱ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

### ቍ ፡ ፬፻፳፩ ፡ በሥልጣን ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ሠራተኞች ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ ለራሳቸው ፡ ለማግኘት ፤ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ በማሰብ ፡—

(ሀ) ከዚህ ፡ በታች ፡ በተለይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ በተሰጣቸው ፡ የሥልጣን ፡ ችሎታ ፡ ከመጠን ፡ አሳልፎ ፡ በመገልገል ፡ በግልጽ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የሥልጣን ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ በሹመታቸው ፡ ማዕርግ ፡ በመመካት ፤ በግልጽ ፡ ተግባርም ፡ ሆነ ፡ ቅጣትን ፡ በሚያስከትል ፡ ግድፈት ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ከመጠን ፡ በማሳለፍ ፡ የሠሩበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በግልጽ ፡ ከተሰጣቸው ፡ የሥልጣን ፡ ችሎታ ፡ በላይ ፡ አልፈው ፡ የሠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በሥልጣን ፡ ያልተሰጣቸውን ፡ ወይም ፡ የሥልጣናቸው ፡ ችሎታ ፡ የማይ ፈቅድላቸውንና ፡ መብታቸው ፡ ያልሆነውን ፡ ጕዳይ ፡ ይልቁንም ፡ ሥልጣና ቸው ፡ በማይፈቅድላቸው ፡ ጊዜና ፡ ከሥራ ፡ ከታገዱ ፡ ከተዛወሩ ፡ ከተሻሩና ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ከተዉ ፡ በኋላ ፡ የሠሩበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የሚወሰን ፡ በተለይ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነው ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌ ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ሆኖ ፡ በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ይህ ፡ አድራጎት ፡ በሕዝብ ፤ ወይም ፡ በግል ፡ ጥቅም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚ ያደርስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አም ስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፲፭ ። የሰውን ፡ ንብረት ፡ ለመፈተሽ ፡ ለመበርበር ፤ ወይም ፡ ዕቃውን ፡ ለመ ያዝ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ (መብት) ፡ ከመጠኑ ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ።

የሰውን ፡ ቤትና ፡ ንብረት ፡ እንዲፈትሹ ፡ እንዲበረበሩ ፡ ሀብቱን ፡ እንዲይዙ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ሥልጣንና ፡ መብት ፡ የተሰጣቸውም ፡ ቢሆኑ ፡ እንኳ ፤ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ከተ ፈቀደው ፡ ሥርዐት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፤ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደላቸውን ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ሥርዐት ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ያላግባብ ፡ የሚመረምሩ ፡ የሚበረብሩ ፤ ወይም ፡ የሚፈትሹ ፡ ሹማምቶች ፡ የመንግሥት ፡ ባለ ሥልጣኖችና ፡ ሠራተኞች ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ መኰንኖችና ፡ ዘበኞች ።

ይህ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ አድራጎታቸው ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ በሚያስ ወስን ፡ በልዩ ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፲፮ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ስለ ፡ ማሰር ።

የመንግሥት ፡ ሹም ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ ከተገለጸው ፡ ሥርዐት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያሰረ ፡ ወይም ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀ ጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፲፯ ። የማይገባ ፡ አሠራር ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ የተገደደውን ፡ ተይዞ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ የተቀመጠውን ፡ ወይም ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ተገድዶ ፡ እንዲቀመጥ ፡ የተፈረደበትን ፡ ሰው ፡ የሚጠብቁ ፡ ሹማምቶችና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የተሰጣቸውን ፡ የሹ መት ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ መግለጫ ፡ እንዲሰጣቸውም ፡

BACK



ሆነ ፡ ወይም ፡ ጥፋቱን ፡ እንዲያምን ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ነገር ፡ እንዲገልጽላቸው ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ያልታረመ ፡ የሆነ ፡ የጭከና ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ክብርና ፡ ለተሰጠው ፡ የሥራ ፡ ሥልጣን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ይልቁንም ፡ የድብደባ ፡ የማሠቃየትና ፡ የማጕላላት ፡ ተግባር ፡ የፈጸሙበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ይህ ፡ አድራጎታቸው ፡ ሊያስከትልባቸው ፡ የሚችለው ፡ የከባድ ፡ ቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

## ቍ ፡ ፬፻፲፰ ። እስረኛን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ መፍታትና ፡ እንዲያመልጥ ፡ ስለ ፡ መርዳት ።

(፩) የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ዘበኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ሕግን ፡ ወይም ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የታሰረውን ፤ የተያዘውን ፤ ወይም ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ተገድዶ ፡ እንዲኖር ፡ ተደርጎ ፡ እርሱ ፡ እንዲጠብቀው ፡ የተሰጠውን ፡ እስረኛ ፡ የፈታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የዚሁኑ ፡ ዐይነት ፡ ሰው ፡ እንዲያመልጥ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ያስደረገ ፤ ወይም ፡ በማምለጡ ፡ ጕዳይ ፡ የረዳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በእስረኛው ፡ የማምለጫ ፡ መንገድና ፡ ዘዴ ፡ በአጠፋፉ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ በመፍታቱ ፡ ጕዳይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ወንጀል ፡ ያደረሰው ፡ ከባድ ፡ ጕዳት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የታሰረበት ፡ ነገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ በመሆኑ ፡ መጠን ፤ ወይም ፡ በእስረኛው ፡ ወይም ፡ በግዞተኛው ፡ ጠባይ ፡ አደገኛነት ፡ መጠን ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ መደበኛው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ለመድረስና ፤ የእስራቱም ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

(፫) አድራጊው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፤ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፬፻፲፱ ። የጦር ፡ ምርኮኞችንና ፡ የወታደር ፡ ግዞተኞችን ፡ ስለ ፡ መፍታትና ፡ እንዲያመልጡ ፡ ስለ ፡ መርዳት ።

(፩) የጦር ፡ ምርኮኞችን ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ግዞተኞችን ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ፈትቶ ፡ የመልቀቅ ፡ ወይም ፡ እንዲያመልጡ ፡ የመርዳት ፡ ወንጀል ፡

በሠራ ፡ ጊዜና ፡ ይህንንም ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እነዚህን ፡ እስረኞች ፡ እንዲጠብቅ ፡ የታዘዘ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ጠባቂ ፡ ዘበኛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) አድራጊው ፡ ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በሞያ ፡ ሥራ ፡ ቅንነትና ፡ ታማኝነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ቍ ፡ ፬፻፳ ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፡ የሚከናወኑትን ፡ ሥራዎች ፡ በተን ኰል ፡ ዘዴ ፡ ስለ ፡ መምራት ።

(፩) የታወቀ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለራሱም ፡ ሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡—

(ሀ) ባንድ ፡ የሥራ ፡ ጕዳይ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ መቋረጥ ፡ ውል ፡ ጕዳይ ፡ ውስጥ ፡ በግገር ፡ ወይም ፡ በሽያጭ ፡ ጕዳይ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ መረጣ ፡ ጨረታ ፡ ጕዳይ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ የራሱን ፡ የሥራ ፡ ሥልጣን ፡ በሚ መለከት ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ በሚሠራው ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ የሚሆኑ ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ዐይነት ፡ ትርፎች ፡ የወሰደ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ የፈጠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በክፍሉ ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ የዕቃ ፡ ማቅረብ ፤ ያንድ ፡ ሥራ ፡ መቋረጥ ፡ ወይም ፡ የማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በጠቅላላው ፤ በሥራው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ በአደራ ፡ የተሰጠ ውን ፡ ወይም ፡ ሊጠብቀውና ፡ ሊከላከልለት ፡ የሚገባውን ፡ የሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚጐዳ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ቅጣትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣው ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፬፻፳፩ ። በአደራ ፡ በተሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ ማዘዝ ።

(፩) የታወቀ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሳይ ፈቀድለት ፡ ንብረቱን ፡ ለራሱ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ሳይሆን ፤

(ሀ) ታሽጎ ፡ የተረከበውን ፤ ጥቅል ፡ አምቦሎፕ ፤ ማስረጃ ፤ ባለዋጋ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ የማንኛዎቹንም ፡ ዕቃዎች ፡ እሽግ ፡ የከፈተ ፤ ያስከፈተ ፤ የወሰደ ፡ ወይም ፡ ያስወሰደ ፤ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ወሬውን ፡ ወይም ፡ ዕቃ ውን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ የተገለገለ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲገለገልባቸው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

እንዲህም ፡ የሚሆነው ፡ በፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ከፍተኛነት ፡ መጠን ፡ ሊፈረ ድበት ፡ የሚገባው ፡ ልዩ ፡ የሆነው ፡ የከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ድንጋጌ ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ የዐመፅ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ በማቀድ ፡ ስሜት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

(፫) ጥፋቱ ፡ የተፈጸመው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፳፪ ። በሥራ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የመውሰድና ፡ የመስረቅ ፡ ወንጀል ።

የታወቀ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሹም ፤ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለራ ሱም ፡ ሆነ ፡ ለሌላው ፡ የማይገባውን ፡ የቅርስ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስ ገኘት ፡ በማሰብ ፡—

(ሀ) በውርስ ፤ በብርበራ ፤ በመያዣ ፤ በመወረስ ፡ ሥርዐት ፤ በሐራጅ ፡ ሽያጭ ፤ በሕግ ፡ ውርስ ፤ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸም ፡ በመወሰኑ ፡ የሚደረገው ፡ የሀብት ፡ መያዝ ፡ ጉዳይ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃዎችን ፡ ሰነዶችን ፤ ባለዋጋ ፡ ነገሮችን ፤ ዝርዝር ፡ ገንዘቦችን ፤ ተንቀሳቃሽ ፤ ወይም ፡ አላቂ ፡ ሀብቶችን ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ በአደራ ፡ የተረከባቸውን ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ አጋጣሚና ፡ ምክንያት ፡ በእጁ ፡ ሊገቡ ፡ የቻሉትን ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ባለዋጋ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ የሰወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፬፻፳፫ ። የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ለማዋል ፡ ሲል ፡ ይህን ፡ ላደርግልህ ፡ እችላለሁ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ ይህንንም ፡ የመሳሰለ ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጠው ፡ የጠየቀ ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ከባለጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ የተቀበለ ፡ ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፺ ።]

(፪) እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዐዋቂዎች ፡ (ኤክስፔርቶች) ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ የሰጡ ፡ የፍርድ ፡ ነባሪዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ለማካሄድ ፡ በባለሥልጣን ፡ የተሾሙ ፡ ተርጓሚዎችና ፡ አስተርጓሚዎች ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

## ቍ ፡ ፬፻፳፬ ። በግልጽ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መነገድ ።

የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ በግልጽ ፡ የተሾመ ፡ ሰው ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ የብሔራዊም ፡ ሆነ ፡ የወታደራዊ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡—

(ሀ) የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ የሆነውን ፡ የሥራ ፡ ደረጃ ፡ የሹመት ፡ ሥራ ፡ የማዕርግ ፡ መለያ ፡ ሽልማት ፡ ያገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ችሮታ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲሰጥ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በርሱ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣንነት ፡ ውስጥ ፡ የሚተዳደረውንና ፡ የሚመራውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ከተቋቋመው ፡ ካስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሆነውን ፡ ውል ፡ የመገበያያ ፡ ስምምነት ፡ የሥራ ፡ ጨረታ ፡ ውል ፡ የዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጥቅም ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ አደራረግ ፡ ከሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ከመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ካስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሆነውን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ እንዲያገኝ ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ በሚሰጠው ፡ ወይም ፡ ይሰጠዋል ፡ ከሚባለው ፡ ሥልጣን ፡ የተነሣ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ጥቅም ፡ ከባለጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ እንዲሰጠው ፡ ተስፋ ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራትና ፡ እንደ ፡ ነገሩም ፡ ከባድነት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፳፭ ። መደለያ ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) በግልጽ ፡ የታወቁ ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምቶች ፤ ሥራ ፡ መሪዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሥራቸው ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ያላፈነት ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ ወይም ፡ የሥራቸው ፡ ተግባር ፡ የሚያስገድዳቸውን ፡ አፈጻጸም ፡ በመደገፍ ፤ ሊቀበሉ ፡ ወይም ፡ ሊያገኙ ፡ መብት ፡ የሌላቸውን ፡ ስጦታና ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ጥቅም ፡ የጠየቁ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ተስፋ ፡ «ቃል» ፡ የተቀበሉ ፡ ወይም ፡ የቀረበላቸውን ፡ የወሰዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) እንዲጣስ ፡ የተጠየቀው ፡ ጉዳይ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ሊቈጠር ፡ በሚችለው ፡ ገንዘብና ፡ ስጦታ ፡ መጠን ፡ የተደለለው ፡ ሰው ፡ ባለው ፡ የሹመት ፡ ማዕርግና ፡ የችሎታ ፡ ሥልጣን ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ በመደለል ፡ የተሠራው ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ተግባር ፡ ከፍተኛ ፡ ሆኖ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

መቀጮውም ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ይሆናል ።

(፫) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ «ኤክስፔርቶች» ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ የሰጡ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ነባሪዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ለማካሄድ ፡ በባለሥልጣን ፡ የተሾሙ ፡ ተርጓሚዎች ፡ አስተርጓሚዎችም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

ቍ ፡ ፬፻፳፮ ። በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በማስገደድ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

(፩) የተሾሙ ፡ ሰዎች ፤ ያንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፡ ሹማምቶች ፤ የማይገባቸውን ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ዐቅደውና ፡ ጥቅሙን ፡ ለራሳቸው ፡ ለማዋል ፡ አስበው ፡ ሊከፈል ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ ታሪፍ ፡ በላይ ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፡ ቀረጥ ፡ ታክስ ፡ ግብር ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገቢ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የገቢ ፡ ጥቅም ፤ ምንዳ ፤ ደመወዝ ፡ ኪራ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ወጪ ፡ የወሰዱ ፤ እንዲከፈል ፡ ያዘዙ ፡ ወይም ፡ ያስከፈሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የወሰዱትን ፡ እንዲመልሱ ፡ መደረጉ ፡ ሳይቀር ፡ በእስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ጥፋቱ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በወንጀሉ ፡ ያገኙት ፡ ጥቅም ፡ የመወረሱ ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጮ ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺፪ ፡ (፪) ።[

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፪ ። ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ማስታወቂያዎችንና ፡ ዐዋጆችን ፡ ስለ ፡ መናቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ማናቸውም ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በደባባይ ፡ የለጠፉዋቸውን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ዐዋጆች ፤ ውሳኔዎች ፡ ከስፍራቸው ፤ ያነሣ ፡ ያበላሸ ፤ የቀደደ ፡ ወይም ፡ እንዳይነበቡ ፡ ያደረጋቸው ፡ እንደ ፡ ሆን ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፫ ። የማስመዝገብን ፡ ትእዛዝ ፡ ግዴታ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የታዘዘውን ፡ የመዝገብ ፡ ማስገባት ፡ ጉዳይ ፡ ሳይፈጽም ፡ በሕዝብ ፡ ቈጠራና ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብ ፡ ስሙን ፡ ሳያጽፍ ፡ የሀብት ፡ ማስመዝገብን ፡ የንግድና ፡ የሌላውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ መዝገብ ፡ እንዲገባ ፡ በደንብ ፡ የታዘዘውን ፡ የሰዎችን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ መግለጫ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሚመለከት ፡ ስምምነት ፡ የማኅበርን ፡ ፍሬ ፡ አሰጣጥ ፡ ወይም ፡ የማቋቋሙን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያመለክት ፡ ወይም ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ይህን፡ የመሳሰሉ ፡ ግዴታዎችን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤

መዝገብ ፡ ሳይገባ ፡ የተቋቋመው ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ውል ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲፈጸም ፡ የታዘዘ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ውሉ ፡ ፈራሽነትን ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የዚህን ፡ ዐይነት ፡ መግለጫ ፡ ያለመስጠቱ ፡ ጉዳይ ፡ ተደጋግሞና ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ የተያዘ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ወይም ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ በተለይ ፡ የሰጠውን ፡ ሕጋዊ ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ።

(፫) ልጅ ፡ መውለድን ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ፡ የሚመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፯፻፳፫ ።]

ቍ ፡ ፬፻፳፱ ። ክርክሮች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ጕዳዮች ፡ እንዳይገለጹ ፡ የሚከለ ክለውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ግልጽ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ ሊጠበቅ ፡ የሚገባውን ፤ በሕዝብ ፡ ጕዳይ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የተደረገውን ፡ ቃል ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔና ፡ ስምምነት ፡ ለጋዜጣና ፡ ለማስታወቂያ ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፴ ። በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድን ፡ የመፈጸም ፡ ተግባር ።

ማንም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ሕግን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡—

(ሀ) በመያዣ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ያስረከበውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መያዣ ፡ በእጁ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሳይፈቅድለት ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ዕቃ ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ ቀርቦበት ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ ተጀምሮበት ፡ ሳለ ፡ ያለፍርድ ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ክፍያ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፤ የባለዕዳው ፡ ንብረት ፡ የሆነውን ፡ አንድ ፡ ዕቃ ፡ ያለፍርድ ፡ የወሰደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በጠቅላላ ፡ ሁኔታ ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ በመቍጠር ፡ መብቱን ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሳይችል ፡ በግፈኛነት ፡ አንድ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ተግባር ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፴፩ ። ሥልጣንን ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መያዝ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ ዐቅድ ፤ ወይም ፡ ለራስም ፡ ሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ በማሰብ ፤ ያንድ ፡ ሥልጣን ፡ ስም ፡ የሥልጣን ፡ ምልክቶች ፡ ማዕርግ ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ሥራ ፡ ሥልጣን ፡ ያለ ፡ መብቱ ፡ በመያዝ ፡ በዚሁ ፡ ሥልጣን ፡ የተገለገለ ፤ ወይም ፡ ግልጽ ፡ (ኦፊሲያል) ፡ የሆኑ ፡ ትእዛዞች ፡ በመስጠት ፡ መብት ፡ የተገለገለ ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ይህን ፡ ሥልጣናዊ ፡ መብት ፡ ለመያዝ ፡ የደፈረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፤ ወይም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ ያላገባብ ፡ ሥልጣን ፡ የመያዙ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለመበደል ፤ ወይም ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስበት ፡ ለማድረግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ በሕግ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፬፻፴፪ ። እሽጎችን ፡ ስለ ፡ መቅደድና ፡ ስለ ፡ መስበር ፤ በጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ትእዛዝ ፡ ምክንያት ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ የሥራ ፤ አግባብ ፡ ሳይኖረው ፡ ዐውቆ ፡—

(ሀ) አንድ ፡ ዕቃ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ (ማስረጃ) ፡ ለመጠበቅ ፤ ወይም ፡ ለማስቀመጥ ፤ ለመለየት ፤ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አሽገው ፡ ያስቀመጡት ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይደረስበት ፤ አንድ ፡ ቤት ፡ እንዳይገባበት ፡ ለመከልከል ፡ የተደረገውን ፡ እሽግ ፡ ግልጽ ፡ (የኦፊሲየል) ፡ ምልክት ፤ ወይም ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፤ ያነሣ ፡ ያበላሸ ፤ ወይም ፡ የሰበረ ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ውጤት ፡ እንዳያገኝ ፡ ያሰናከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የተያዙ ፡ የተወረሱ ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ባንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የገቡ ፤ ወይም ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ የተሰጡ ፤ ዕቃዎችን ፤ ጽሑፎችን ፡ ወይም ፡ ማስረጃዎችን ፡ የሰረቀ ፡ ያበላሸ ፤ ወይም ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፴፫ ። መቃወምና ፡ አለመታዘዝ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡—

(ሀ) በሥራቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚገባውን ፡ አገሎግልት ፡ የሚፈጽሙትን ፡ ከመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ አባሎች ፡ አንዱን ፤ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፤ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ከሚያከናውኑ ፡ ሠራተኞች ፡ አንዱን ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ያሰናከለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ብሔራዊ ፡ ሆነ ፡ ወታደራዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራው ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ስብሰባ ፡ ውስጥ ፡ እንዲበተን ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ከተከለከለ ፡ ስፍራ ፡ እንዲሄድ ፡ ወይም ፡ በቃጠሎ ፡ በማዕበል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ሌላ ፡

አደጋ ፡ በኅብረት ፡ እርዳታ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንዲሠራ ፡ በሕግ ፡ ስም ፡ ሲጠ
ይቀውና ፡ ሲያዝዘው ፡ አልታዘዝም ፡ ያለ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በሚገባ ፡ ሊያዝዘው ፡ የሚችለው ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነውን ፡ ሹም ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ ወይም ፡ ለትእዛዙ ፡ ተገዢ ፡ ባለመሆን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ደንብ ፡ በማስጠንቀቅ ፡ አዞት ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንቢታው ፡ ወይም ፡ ያለመታዘዙ ፡ አድራጎት ፡ የተፈጸመው ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ አማካይነት ፡ ሆኖ ፡ ዛቻን ፤ መቃጣትን ፤ ድፍረትን ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ እልፊትን ፡ አስከትሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፷፩ ፡ የተመለከተው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፬፻፷፩ ። የኀይልና ፡ የማስገደድ ፡ ሥራ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ አንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባል ፡ የሥራው ፡ ሥልጣን ፡ የሚፈቅድለትን ፡ ያገልግሎት ፡ ጉዳይ ፡ በዛቻ ፤ በግዴታ ፤ ወይም ፡ በኀይል ፡ ያሰናከለ ፡ ወይም ፡ እንዲሠራ ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እነዚሁን ፡ ሠራተኞች ፡ ወይም ፡ የሚረዱዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ የደበደበ ፡ ወይም ፡ የማስገደድና ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ የፈጸመባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድነት ፡ መጠንና ፡ እንደ ፡ ተበዳዩም ፡ የሥራ ፡ ደረጃ ፡ ተበዳዩ ፡ ባንድ ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ አማካይነት ፡ ተዝቶበት ፡ ተገድዶ ፡ ወይም ፡ ተደብድቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የእስራቱ ፡ ቅጣትና ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጮ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ከፍተኛ ፡ መደብ ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

(፫) በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የአካል ፡ መቍሰል ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ለማክበድ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፬፻፷፪ ። በኅብረት ፡ የሚፈጸም ፡ ሥራ ።

ይህን ፡ የድፍረት ፡ የማስገደድና ፡ የማንገላታት ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ወይም ፡ ሸብር ፡ ያነሡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተደራቢነት ፡ ይፈጸማሉ ። [ቍ ፡ ፬፻፹፰ ፡ ፬፻፹፱ ።]

**ቍ ፡ ፬፻፴፯ ። በግል ፡ ወዳጅነት ፡ ስለ ፡ መነገድ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ባለመሆኑ ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ የተደነገገው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ የማይፈጸም ፡ ሲሆን ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሆነው ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ የሚሰጠውን ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ካለው ፡ ወይም ፡ አለው ፡ ከሚባለው ፡ ወዳጅነት ፡ የተነሣ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የጠየቀ ፡ ወይም ፡ እንዲሰጠው ፡ ተስፋ ፡ ያገኘ ፤ ወይም ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፬፻፳፩ ።]

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፰ ። ጉቦ ፡ መስጠት ።**

ማንም ፡ ሰው ፤ አንዱን ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ አባል ፤ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ ሠራተኛ ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የወታደራዊ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ በማባበል ፡ ያላፈነቱን ፡ ወይም ፡ የሥራውን ፡ ተግባር ፡ እንዲጥስ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ የሰጠ ፤ ለስጦታ ፡ ያቀረበ ፡ የስጦታ ፡ ተስፋ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ በኩል ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስጦታ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደረገ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ ከእነዚህ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የሚጠበቀው ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፡ ከተፈጸመም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ጉቦ ፡ የሰጠው ፡ ወይም ፡ ሊሰጥ ፡ ያቀረበው ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ስጦታ ፡ ቢሆን ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**አንቀጽ ፡ ፬ ።**

**በፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።**

**ምዕራፍ ፡ ፩ ።**

**በፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።**

**ቍ ፡ ፬፻፴፱ ። ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስላለመግለጽ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የሚያከራክር ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡—

(ሀ) የሞት ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚያስከትል ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ መፈጸሙን ፡ ወይም ፡ አድራጊውን ፡ ወንጀለኛ ፡ እያወቀ ፤

(ለ) ወይም ፡ በሕጉ ፡ ወይም ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ ደንቦች ፡ ለሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ወይም ፡ ሰላም ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ለባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ለፍትሕ ፡ አንዳንድ ፡ ወንጀሎችን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ከባድ ፡ ሥራዎችን ፡ በተ

ለይ ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ግዴታ ፡ ኢያለበት ፡ ይህን ፡ የማስታወቅ ፡ ተግባሩን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ለመንግሥት ፡ ወይም ፡ ላገር ፡ ጥቅም ፡ መከላከያ ፡ በሆኑት ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ የወንጀል ፡ ተግባሮች ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ፡ ቀጥተኛ ፡ ባል ሆነ ፡ እንደ ፡ እጅ ፡ አዙር ፡ በሚቈጠር ፡ ዘዴ ፡ የወንጀል ፡ ግብረ ፡ አበር ፡ ወይም ፡ ረዳት ፡ በመሆን ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ ጕዳይ ፤ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፯ ፡ እና ፡ ፫፻፶፩ ፡ የተደነገጉት ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፵፱ ። አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይቀርብ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ እያወቀ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቅጣት ፡ የሚደርስበትንና ፡ የሚከሰሰውን ፡ ወንጀለኛ ፡ አስቀድሞ ፡ በማስጠንቀቅም ፡ ሆነ ፡ በመደበቅ ፡ የወንጀሉን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመበትን ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ሰነድ ፡ ዱካውን ፡ በመሸሸግም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማጥፋት ፡ የፍለጋውን ፡ መንገድ ፡ በማሰናከልም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አድራጎት ፡ ወንጀለኛው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ ቀርቦ ፡ እንዳይከሰስ ፡ ወይም ፡ እንዳይቀጣ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፶ ። የፍርድን ፡ ሥራ ፡ እንዲሳሳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ያልተሠራ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ተሠርቷል ፡ ብሎ ፡ ለባለ ሥልጣኖች ፡ ክስ ፡ ያቀረበ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ራሱ ፡ ያልሠራውን ፡ ወንጀል ፡ ሠርቻለሁ ፡ በማለት ፡ ራሱን ፡ በማጋለጥ ፡ በሐሰት ፡ ራሱን ፡ የከሰሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የመከታተል ፡ ተግባር ፡ እንዳይከናወን ፡ በማሰብ ፡ ትክክል ፡ ያልሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ለባለሥልጣኖች ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፶፩ ። በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወንጀል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መክሰስ ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ወንጀል ፡ አለመሥራቱን ፡ ወይም ፡ ንጽሕናውን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ባልሠ

BACK



ራው ፡ ወንጀል ፡ እንዲቀጣ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በባለሥልጣን ፡ ዘንድ ፡ የወንጀለ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የከሰሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፤ ይልቁንም ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራ ፡ በማስመሰል ፡ ወይም ፡ የወንጀዩ ፡ ስም ፡ ባልተገለጸ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ትክክለኛ ፡ ባልሆነ ፡ ውንጀላ ፡ ንጹሕ ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አነሣሥቶ ፡ ፀልሠራው ፡ ወንጀል ፡ እንዲከሰስ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ወይም ፡ ያቀረበው ፡ ውንጀላ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ የሚያስፈርድበት ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፵፪ ። ለፍርድ ፡ እርዳታ ፡ መስጠትን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ።</u>

(፩) በፍርድ ፡ ቤትና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ነክነት ፡ ያለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሚፈጽመው ፡ ጕዳይ ፡ እንዲጠየቅ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ በምስክረነት ፡ እንዲሰማ ፤ በልዩ ፡ ዐዋቂነት ፡ ወይም ፡ በተርጓሚነት ፡ እንዲሰማ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ በነባሪነት ፡ ወይም ፡ በትቺ ፡ እንዲረዳ ፡ በሥርዐት ፡ የተጠራ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ በእንቢተኛነት ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ቀርቦ ፡ ሕግን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ለተጠየቀው ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዳዘዘው ፡ ከመፈጸም ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ደጋጋሚ ፡ እልከኛ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አጥፊው ፤ ሰው ፡ መልስ ፡ ስላለመስጠቱና ፡ ስለ ፡ እንቢታው ፡ ያቀረበው ፡ ምክንያት ፡ ሐሰተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የእስራትና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይፈርድበታል ።

(፫) ይህም ፡ ሰው ፡ በማጭበርበር ፡ ዘዴው ፡ በመገልገል ፡ ከግዴታው ፡ የወጣው ፡ ሐሰተኛ ፡ ምክንያትን ፡ በማቅረብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፈጸመው ፡ የአጭበርባሪነት ፡ ወንጀል ፡ ሊደርስበት ፡ የሚገባው ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፤ ይልቁንም ፡ ሐሰት ፡ በሆነ ፡ ማስረጃ ፡ በተገለገለ ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰነው ፡ የቅጣት ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ጠቅላላው ፡ ሕጋዊ ፡ የቅጣት ፡ ደንብ ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፵፫ ። ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ምርመራ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፤ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ ወይም ፡ በችሎት ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱንና ፡ ዳኛውን ፡ የደፈረ ፡ የሰደበ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱና ፡ በዳኛው ፡ ወይም ፡ ከአባሎቹ ፡ በአንደኛው ፡ ላይ ፡ ያፌዘ ፤ የዛተ ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ የሥራውን ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ በማሰናከል ፡ ሁከት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ቀጠሮ ፡ ሳያደርግ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ወዲያውኑ ፡ ቅጣቱን ፡ ይወስናል ።

(፪) ይህ ፡ ድፍረት ፡ የተፈጸመው ፡ በግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ ከችሎቱ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አፈጻጸሙ ፡ ከባድ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ፭፻ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

(፫) የድፍረቱ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በችሎት ፡ ላይ ፡ በተቀመጠ ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ በፍትሐዊ ፡ ጕዳይ ፡ በተደረገ ፡ የምክር ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ የፍርድ ፡ ጉባኤን ፡ በማወክ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚሁ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፬፻፴፱ ። ]

ቍ ፡ ፬፻፵፬ ። የፍርድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምስጢርን ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ፈቃድና ፡ መብታዊ ፡ የሆነ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ በሁኔታው ፡ ምስጢር ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ ጕዳዩ ፡ የቀረበለት ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ማስፈለጉን ፡ የገለጸበትን ፡ በወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አፈጻጸም ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ለማወቅ ፡ የቻለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ምስጢራዊ ፡ ጕዳይ ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ ይህን ፡ የሕግ ፡ መጣስ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስቀጣውን ፡ የግል ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ ወይም ፡ በሠራተኛነት ፡ ምክንያት ፡ ያገኘውን ፡ ምስጢር ፡ በመግለጽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙበታል ። [ቍ ፡ ፬፻፳ና ፡ ፬፻፯ ። ]

**ቍ ፡ ፬፻፵፭ ። ትክክለኛ ፡ ያልሆኑትን ፡ ወይም ፡ የተከለከሉትን ፤ የሥራ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ባደባባይ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያልተረጋገጡትን ፡ (ያልተካከሉትን) ፡ ያልታረሙትን ፡ ወይም ፡ የተዘባረቁትን ፡ የወሬ ፡ ምንጮች ፡ ማስታወሻዎች ፡ በምርመራ ፡ የተጣሩ ፡ ጉዳዮች ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ መግለጫዎች ፡ ባደባባይ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ የነዛ ፤ ለፍርድ ፡ የተዘጋጁ ፡ ወይም ፡ የተፈረዱትን ፡ ጉዳዮች ፡ ያዘባረቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። ወይም ፡ አድራጎቱ ፡ በሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ የሚያደርስ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ጉዳትን ፡ የሚያደርስ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) በሕጋዊ ፡ ድንጋጌ ፡ ወይም ፡ የክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነው ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተከለከለና ፡ ቅጣትን ፡ የሚያስከትል ፡ ጉዳይ ፡ ባደባባይ ፡ የመግለጽ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣቱ ፡ የሚወሰነው ፡ ተፈጻሚ ፡ በሚሆነው ፡ በጠቅላላው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፬፻፳፱ ።]

ባደባባይ ፡ የመግለጹ ፡ ጉዳይ ፡ ትክክለኛና ፡ እርግጠኛ ፡ አለመሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ፈ፦ሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ጥፋት ፡ መደራረብ ፡ በተደነገገው ፡ ደን ፡ መሠረት ፡ ጽኑ ፡ የሆነውን ፡ ቅጣት ፡ ይወስናል ። [ቍ ፡ ፹፪ ።]

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### በፍርድ ፡ ላይ ፡ ሊደረግ ፡ በሚገባው ፡ በእውነተኛነትና ፡ በታማኝነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፮ ። አንዱ ፡ ወገን ፡ ስለሚሰጠው ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ።**

(፩) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የሥነ ፡ ሥዐርት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ነክነት ፡ ባለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እውነተኛውን ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ አዞት ፡ ጉዳዩን ፡ በሚመለከተው ፡ ነገርና ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ በሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ፍትሐዊውን ፡ ሥርዐት ፡ ሊያሳምን ፡ የሚችል ፡ ሐሰተኛ ፡ መረጃ ፡ ወይም ፡ እውነት ፡ ያልሆነ ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ያሰበው ፡ ዐቅድ ፡ እግቡ ፡ ደርሶ ፡ ውጤት ፡ ሳያስገኝም ፡ ቢቀር ፡ እንኳ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የሐሰት ፡ ቃል ፡ የሰጠው ፡ የወንጀል ፡

BACK



ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ደንብ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ያስከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ሐሰተኛ ፡ ቃል ፡ ሰጪው ፤ ሐሰት ፡ እንዳይናገር ፡ ምሎ ፡ ወይም ፡ እውነተኛውን ፡ ለማስረዳት ፡ በግልጽ ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አካበቢ ፡ ሁኔታና ፡ ይልቁንም ፡ በከፊልም ፡ ቢሆን ፡ ሐሰቱ ፡ ውጤት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፫) አንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ የሚከራከርበት ፡ መብቱን ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ የሰጠው ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ ቃል ፡ አሰጣጥ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ቅጣት ፡ አያስከትልም ።

## ቍ ፡ ፬፻፵፯ ። ሐሰተኛ ፡ ምስክርነት ።

(፩) ምስክር ፡ ሆኖ ፡ የቀረበ ፡ ሰው ፡ ያስተዳደር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ የዳኝነት ፡ ወይም ፡ የዳኝነት ፡ ነክነት ፡ ያለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ለክርክሩ ፡ ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሐሰተኛ ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህ ፡ የሐሰት ፡ ተግባሩ ፡ አንዱን ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ለመጥቀም ፡ ወይም ፡ ለመጉዳት ፡ ተሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ያቀደው ፡ ዐቅድ ፡ እግቡ ፡ ባይደርስም ፡ እንኳ ፡ በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ በከፍተኛነት ፡ የሚገመት ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) መስካሪው ፡ ሐሰት ፡ እንዳይናገር ፡ ምሎ ፡ ወይም ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ለማስረዳት ፡ በግልጽ ፡ የእምነት ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታና ፡ ይልቁንም ፡ የሐሰቱ ፡ ሥራ ፡ በከፊልም ፡ ቢሆን ፡ የታሰበውን ፡ ውጤት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ በመስካሪው ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሹ ፡ በስሕተት ፡ ተፈርዶበት ፡ ከመስካሪው ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ ደርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሐሰተኛነቱ ፡ በማሳሳቱ ፡ ባስፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ልክ ፡ ሊቀጣ ፡ ይቻላል ።

(፫) እንዲሁም ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ነክነት ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ጉዳዩን ፡ በሚመለከት ፡ በግልጽ ፡ በታወቀ ፡ ሁኔታ ፡ አሰተኛ ፡ ትርጉም ፡ የሚሰጥ ፡ ማንኛውም ፡ ተርጓሚና ፡ አስተርጓሚ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ።

(፬) ሐሰተኛነቱን ፡ እያወቀ ፡ ያደረገው ፡ የቃል ፡ አሰጣጡ ፡ የምርመራው ፡ አስተያ

BACK



የት ፡ ወይም ፡ የማመልከቻው ፡ ወይም ፡ የትርጕሙ ፡ አቀራረብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ሳያሳምነው ፡ ቀርቶ ፡ አንዳችም ፡ የተሳሳተ ፡ ፍርድ ፡ አላስወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፬፻፵፭ ። ቃልን ፡ ስለ ፡ ማቃናትና ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

አጥፊው ፤ ሐሰተኛ ፡ ምስክርነቱ ፡ ማስታወቂያው ፤ የምርመራ ፡ አስተያየቱ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ ትርጕሙ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ከማድረሱ ፡ በፊትና ፡ የመጨረሻ ውም ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ቃሉን ፡ አቃንቶ ፡ ወይም ፡ የፈጸመውን ፡ ተግባር ፡ ለውጦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተወሰነበ ትን ፡ ቅጣት ፡ በመሰለው ፡ ሊያቃልልለት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፹፭ ። ]

የተፈጸመው ፡ አድራጎት ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ ወይም ፡ አደጋው ፡ እጅግ ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሐሰቱንም ፡ ነገር ፡ የማቃናቱና ፡ የማሻሻሉ ፡ ጕዳይ ፡ በቅንነት ፡ መንገድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊው ፡ ለወደፊቱ ፡ እንዲጠነቀቅ ፡ በማድረግና ፡ በመገሠጽ ፡ ብቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከማናቸውም ፡ ቅጣት ፡ ነጻ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፬፻፵፮ ። ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማግባባት ።

ማንም ፡ ሰው ፤ በስጦታ ፡ በተስፋ ፤ በዛቻ ፤ በተንኰል ፡ ወይም ፡ በማታለል ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ በማግባባት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በሐሰት ፡ እንዲወነጀል ፤ በሐሰት ፡ እንዲመሰክር ፤ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ አስተ ያየት ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሐሰተኛ ፡ ትርጕም ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ ማመልከቻ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ያግባባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ያቀደው ፡ ተግባር ፡ ያልተፈጸመም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የአደራረጉ ፡ ሁኔታና ፡ ጠባዩ ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ አነሣሽነት ፡ በተወሰነው ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በጽኑ ፡ ቅጣት ፡ የማያስቀጣው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፴፭ ። ]

## ቍ ፡ ፬፻፵፯ ። በሙግት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማጭበርበር ።

ማንም ፡ ሰው ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ጕዳዮች ፡ በቀር ፡ በዳኝነት ፡ ወይም ፡ የዳኝነት ፡ ነክ ፡ በሆነ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ጕዳይ ፡ ዳኛውን ፡ ለማሳሳት ፡ በማሰብ ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረቡን ፡ ጕዳይ ፡ ለማሰናከል ፡ ወይም ፡ የፍርዱን ፡ ትክክ ለኛ ፡ መንገድ ፡ ለማሳሳት ፡ ግዙፍ ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ በማ ሰብ፡ ወይም ፡ በሚደግፍና ፡ በማይደግፍ፡ ሁኔታ ፡ ውሳኔ ፡ ለማሰጠት ፡ በማግባባት ፡ ስሜት ፡ —

(ሀ) የሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ አንድ ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ማሳመኛ ፡ የሆነውን ፡ አስረጅ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የመርቻ ፡

BACK



ነገር ፡ የደበቀ ፤ የሰረቀ ፤ የሰወረ ፤ ያጠፋ ፤ ያበላሸ ፤ ወይም ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በመላው ፡ የማያገለግል ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ዕቃዎቹን ፡ ወይም ፡ ሰዎቹን ፡ የደበቀ ፡ የስፍራውን ፡ ሁኔታ ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የሠራው ፡ ወንጀል ፡ በተለይ ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ በሚያስቀጡ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚጥለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፬፻፶፩ ። የፍርድን ፡ ውሳኔ ፡ ለማሳሳት ፡ በተንኰል ፡ ስለሚደረግ ፡ የወሬ ፡ መግለጽ ፡ ሥራ ።

ማንም ፡ ሰው ፤ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፤ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በመስጠት ፡ ጕዳይ ፡ ሊፈረድ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ በተጀመረው ፡ ክርክር ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለማግባባት ፡ ለማሳሳት ፡ በማሰብ ፡ ተከሳሹን ፡ ወይም ፡ ግብረ ፡ አበሮቹን ፤ በማስጠንቀቅም ፡ ሆነ ፡ በዳኛው ፤ በእማኞቹ ፤ በምስክሮቹ ፤ በልዩ ፡ አዋቂዎች ፤ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ረዳቶች ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ የመሳሳትን ፡ ስሜት ፡ ለማሳደር ፡ እያወቀ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆኑና ፡ የሚያሳስቱ ፡ ማመልከቻዎች ፡ የወሬ ፡ ምንጮች ፡ ማስታወሻዎች ፡ ምርመራዎች ፡ የመንቀፍ ፡ ሐተታዎች ፤ መግለጫዎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጽሑፎች ፡ በደባባይ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ በወሬ ፡ የነዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፬፻፶፪ ። ባንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የክሕደት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ።

(፩) ማንኛውም ፡ ጠበቃ ፤ ነገረ ፡ ፈጅ ፤ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ እያወቀ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በባለጕዳዩ ፡ ወካይነት ፤ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ክርክር ፡ ያለበትን ፡ ጕዳይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲከራከር ፡ የተወከለበትን ፡ መብቱንም ፡ እንዲከላከልበት ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ የተቀበለበትን ፡ ጕዳይ ፡ የወካዩን ፡ ወገን ፡ ክርክር ፡ በማበላሸት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ነገር ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ተከራካሪዎች ፡ ጕዳይ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሁለቱንም ፡ አጣምሮ ፡ በመሥራት ፡ ነገሩን ፡ ያሰናከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ቅጣትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ ከተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ያነሰ ፡ ሊሆን ፡ አይች

ልም ። በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ስሜት ፡ በመነሣሣት ፡ ወይም ፡ ተጨባጭ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

የከዳተኛነቱ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ በሚአስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ በተከሰሰ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያስከትል ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡ ጽኑ ፡ ሆኖ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስራቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔዎችና ፡ አፈጻጸሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቊ ፡ ፬፻፶፫ ። ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችንና ፡ ጠቅላላውንም ፡ የጸጥታ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላለመጠበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፻፳፪ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ወይም ፡ ከማዕርግ ፡ የመሻር ፡ ቅጣት ፡ አንደኛው ፡ ተወስኖበት ፡ ወይም ፡ ከ፻፵፯ ፡ እስከ ፡ ፻፶፯ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ከተወሰነበት ፡ ከተቀዳሚ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ቅጣት ፡ ለማምለጥ ፡ እያወቀ ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ በመጣስ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የተቈረጠበትን ፡ ክልከላ ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ያፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ልዩ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ እንዲወሰንበት ፡ ያልተገለጸ ፡ ከሆነ ፡ ይልቁንም ፡ ከግዞት ፡ ቦታ ፡ ባመለጠ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ጥፋት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፬፻፶፱ ።]

### ቊ ፡ ፬፻፶፬ ። የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ስለ ፡ ማሰናከል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ተሰጥቶ ፡ የተወሰነበት ፡ ቅጣትና ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲፈጸምበት ፡ የተደረገውን ፡ ተቀጪ ፡ በመደበቅ ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸምበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቊ ፡ ፬፻፶፭ ። የእስረኛ ፡ ማምለጥ ።

በፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ተፈርዶበት ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ተይዞ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ የተደረገ ፡ ሰው ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በሀብት ፡ ላይ ፡

BACK



የኀይል ፡ ወይም ፡ የዛቻ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ያመለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ይህም ፡ ቅጣት ፡ ቀድሞ ፡ ተፈርዶ ፡ በነበረው ፡ በደንበኛው ፡ ቅጣት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚፈረደው ፡ ቅጣት ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ የሚወሰን ፡ ነው ፤ የሚፈጸመውም ፡ ቀድሞ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፶፯ ። እስረኛ ፡ እንዲያመልጥ ፡ ስለ ፡ ማደራጀትና ፡ እርዳታ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ግዴታ ፡ ስለ ፡ መጣስ ፡ ከተመለከተው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ በኀይል ፡ በአስገዳጅነት ፡ በዛቻ ፡ በተንኰል ፡ በግል ፡ ሥልጣኑ ፡ ደረጃ ፡ ያለመጠን ፡ በመገልገል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ አንድ ፡ እስረኛ ፡ እንዲያመልጥ ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ ያዘጋጀ ፡ ወይም ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፬፻፲፭ ።]
በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከፍተኛነት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፦

(ሀ) እስረኛው ፡ እንዲያመልጥ ፡ የማድረጉ ፡ የመርዳቱ ፡ የመተባበሩ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራው ፡ ወይም ፡ የተሞከረው ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ የሚያገለግል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ ለእስረኛው ፡ በማስገባት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እንዲያመልጥ ፡ እርዳታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ብሔራዊ ፡ ወይም ፡ ወታደር ፡ ቢሆንም ፡ የሐያ ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ የተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) እነዚህ ፡ ወንጀለኞች ፡ እስረኛው ፡ እንዲያመልጥ ፡ ያዘጋጁት ፡ ዐቅዳቸው ፡ እንዲከናወን ፡ ሽብር ፡ አስነሥተው ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በሀብት ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሠራተኞቹን ፡ ወይም ፡ ዘበኞቹን ፡ ደል ለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ተደራራቢና ፡ የተያያዘ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀል ፡ ሠርተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተነባበረ ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ ማክበድ ፡ የተደነገገው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፷፪ ። ፷፫ ።]

ቍ ፡ ፬፻፶፰ ። የጦር ፡ ምርኮኛና ፡ የወታደር ፡ ግዞተኛ ፡ ማምለጥ ።

በተለይ ፡ በተሰናዱት ፡ የወታደር ፡ ግዞት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የጦር ፡ ምርኮኞችና ፡ የወታደር ፡ ግዞተኞች ፡ ምንም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ ቅጣት ፡ የተያዙ ፡ ባይሆኑም ፡ እንኳ ፡ ሁኔታው ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፺፭ ፡ እና ፡ ፩፻፺፮ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባ ቸዋል ። በቍጥር ፡ ፩፻፲፱ ፡ የተመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ድንጊጋዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

### ቍ ፡ ፩፻፺፰ ። የእስረኞች ፡ ግርግር ።

(፩) በፍርድ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ተወስኖባቸው ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ለመጠበቅ ፡ የተያዙ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ለማድረግ ፡ በማቀድ ፡—

(ሀ) ዲሬክተሩን ፡ ወይም ፡ የእስር ፡ ቤቱን ፡ ሹማምቶች ፡ ወይም ፡ የወህኒ ፡ ቤቱን ፡ ዘበኞች ፡ ወይም ፡ የእስር ፡ ቤቱን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩትንና ፡ የሚያካሂዱትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ በማስገደድ ፡ ተግባር ፡ በግድ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ የሚገባቸውን ፡ የግዴታ ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲተዉ ፤ ለማድረግ ፤

(ለ) ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ተግባሩን ፡ ሲፈጽም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፤

(ሐ) ለማምለጥ ፡ ሲሉ ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በሀብት ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ለመ ሥራት ፡ አድማ ፡ በማንሣት ፡ የተባበሩና ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመስማማት ፡ ግርግር ፡ ያነሣሡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ሊወሰንባቸው ፡ ከሚገባው ፡ ወይም ፡ ተወስኖባቸው ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ ተደራቢ ፡ የሚሆን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ግርግሩን ፡ ያዘጋጀው ፡ ወይም ፡ የመራው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ተግ ባር ፡ ውስጥ ፡ የማስገደድ ፡ ወይም ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ አልፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ። ይህም ፡ የማስገደድና ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ እንዲ ወሰን ፡ የተደነገገው ፡ የከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

(፫) በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ በተ ደረገ ፡ ጊዜ ፡ ወንጀሎች ፡ ሲቀላቀሉ ፡ ወይም ፡ ሲያያዙ ፡ የማከበድ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፷፪ ፡ ፷፫ ።]

### ቍ ፡ ፩፻፺፱ ። ከግዞት ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ማምለጥ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በግዞት ፡ ስፍራ ፡ እንዲኖር ፡ ባንድ ፡ አውራጃ ፡ ከመኖር ፡ የመከ ልከል ፤ የመታገድ ፤ ወይም ፡ ካገር ፡ የመውጣት ፡ ፍርድ ፡ ተወሰኖበት ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ውሳኔውን ፡ በመጣሱ ፡ ከግል ፡ ነጻነት ፡ የመወሰን ፡ ፍርድ ፡ ተወስኖበት ፡ የነበረውን ፡ ቅጣት ፡ ከፍ ፡ የማድረግ ፡ ደንብ ፡ ሳይቀር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ የሚቈይበት ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ ከመወሰን ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ አይታሰብም ።

## አንቀጽ ፡ ፭ ።

## ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ የምርጫ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፬፻፷ ። ለምርጫ ፡ ጕዳይ ፡ የሚደረገውን ፡ ስብሰባና ፡ የሥራ ፡ መከናወን ፡ ስለ ፡ ማወክና ፡ ስለ ፡ ማሰናከል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደውን ፡ ሕዝባዊ ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ የምርጫ ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ በባለሥልጣኖቹ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ በደንብ ፡ የሚደረገውን ፡ የድምፅ ፡ ብልጫና ፡ የምርጫ ፡ አሠራሮች ፡ ያወከ ፡ ወይም ፡ ያላገባብ ፡ ያቋረጠ ፡ ወይም ፡ ያላገባብ ፡ አፈጻጸማቸውን ፡ ያሰናከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፬፻፹፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

(፪) በሰዎችና ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርሱ ፡ የኀይል ፡ ሥራዎች ፡ ተፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የአድማ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሁከቶች ፡ ወይም ፡ እምባጓሮዎች ፡ ተፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ የተመለከቱት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጣምረው ፡ ይወሰናሉ ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፩ ። የምርጫ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠትን ፡ ወይም ፡ የመምረጥን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መንካት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በዛቻ ፡ በማስገደድ ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ ያላገባብ ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በማጭበርበርና ፡ ይልቁንም ፡ ስምን ፡ በመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ በመደበቅ ፡ ወይም ፡ ጥሪን ፡ በማስቀረት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ብልሀትና ፡ ዘዴ ፡—

(ሀ) አንዱ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ እንዳይሠራበት የከለከለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ይህንኑ ፡ በመሳሰለ ፡ ዘዴ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ዐይነት ፡ ድምፅ ፡ በመስጠት ፡ መብቱ ፡ እንዲሠራበት ፡ ወይም ፡ እንዳይሠራበት ፡ ያግባባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሕግ ፡ በታወቀለት ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብቱ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ዐይነት ፡ የሠራውን ፡ ወይም ፡ ሳይሠራ ፡ የቀረውን ፡ ሰው ፡ በደል ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰበት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፩፻፷፪ ። በምርጫ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመደለያ ፡ ስጦታ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ እርሱ ፡ በፈለገው ፡ ዐይነት ፡ እንዲመርጥ ፡ ወይም ፡ የመምረጥ ፡ መብቱን ፡ እንዲተው ፡ ለማድረግ ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ጥቅም ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ያሰጠ ፡ ወይም ፡ እሰጥሃለሁ ፡ በማለት ፡ የደለለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫውን ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ዐይነት ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ ላለመስጠት ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጥቅም ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፩፻፷፫ ። የማይገባ ፡ አሠራር ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፤ ድምፅ ፡ የተሰጠበትን ፡ ሰነድ ፡ የወሰደ ፤ በዚሁ ፡ ሰነድ ፡ ያላግባብ ፡ የተገለገለበት ፡ ወይም ፡ ሰነዱን ፡ ወስዶ ፡ የደበቀ ፡ ይህንንም ፡ የፈጸመው ፡—

(ሀ) ሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ በማስወራት ፡ ዘዴ ፤ ወይም ፡ በድምፅና ፡ በጽሑፍ ፡ መልክት ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ድምፅ ፡ በመንዛት ፤ በራሪ ፡ ጽሑፎችን ፡ በመበተን ፤ በጋዜጣ ፡ በራዲዮ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የወሬ ፡ መስጫ ፡ ዘዴ ፤

(ለ) ወይም ፡ ባልተካከሉና ፡ እውነተኛ ፡ ባልሆኑ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ያሠራር ፡ ዘዴዎች ፡ አማካይነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፩፻፷፬ ። ባመዘጋገብ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ የማጭበርበር ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በምርጫ ፡ ዝርዝር ፡ ወይም ፡ በመመረጫ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ስሙን ፡

BACK



ወይም ፡ የማዕርጉን ፡ ዐይነት ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለውጦ ፡ በማጻፍ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የችሎታ ፡ ማጣት ፡ ሁኔታ ፡ በመደበቅ ፡ ያስ መዘገበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ መዛግብትና ፡ ዝርዝሮች ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ ያጻፈ ፡ ወይም ፡ ያላገባብ ፡ ብዙ ፡ የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶ ችን ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ እንዲሰጠው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ያላገባብ ፡ በሕይወት ፡ ያሉትን ፡ የሞቱትን ፡ የጠፉትን ፡ ወይም ፡ የሌሉትን ፡ ሰዎች ፡ ያስመዘገበ ፡ ወይም ፡ በእነርሱ ፡ ስም ፡ የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀት ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፬፻፷፭ ። በድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ምርጫ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ በሥራው ፡ ተግባር ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ በፈጸመው ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አሠራር ፡ የምርጫውን ፡ ደንበኛ ፡ ውጤት ፡ ያሳሳተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተለይም ፡—

(ሀ) የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መመዝገቢያ ፡ የሆነውን ፡ ደብተር ፡ ወይም ፡ የተሞሉ ትን ፡ የምርጫ ፡ ዝርዝር ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ የገቡትን ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ወረቀቶች ፡ በመለወጥ ፤ ሐሰተኛ ፡ በማድረግ ፡ በማበላሸት ፡ ወይም ፡ እንዳይ ነበብ ፡ በማድረግ ፤ በማስቀረት ፡ በማጥፋት ፡ ወይም ፡ እንዲሰወሩ ፡ በማድረግ ፡

(ለ) ባንድ ፡ የምርጫ ፡ አሠራር ፡ ጊዜ ፡ በድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብቱ ፡ መላልሶ ፡ በመሥራት ፤

(ሐ) የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶች ፡ በሚገቡበት ፡ ሣጥን ፡ ወረቀቶችን ፡ አብ ልጦ ፡ በመጨመር ፡ ወይም ፡ በማጕደል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ምርጫ ፡ ከሚደረግበት ፡ ቀበሌ ፡ ውጭ ፡ የሆኑትን ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውን ፡ ወይም ፡ የሞቱትን ፡ ወይም ፡ የሌ ሉትን ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ እንዲሰጡ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ በማስመረጥ ፡ ወይም ፡ እያወቀ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውን ፡ ወይም ፡ ሐሰ ተኛ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የተለወጡትን ፡ የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶችን ፡ በሣጥኑ ፡ በማግባት ፡ ወይም ፡ እንዲገቡ ፡ በመፍቀድ ።

(መ) ትክክለኛ ፡ ባልሆነ ፡ ዐይነት ፡ በመቍጠር ፡ ወይም ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የሚሰጥባቸውን ፡ ወረቀቶች ፡ የመራጮቹን ፡ ፊርማ ፡ የተመራጮቹን ፡ ስም ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በመተው ፡ ወይም ፡ ከተጻፉት ፡ ፊርማዎች ፡ ወይም ፡ ስሞች ፡

ሐቁ ፡ በማገባበ ፡ ወይም ፡ በፕሮሴ ፡ ቬርባሎችና ፡ አሠራሩ ፡ በግልጽ ፡ በሚቀርቡ ፡ ራፖርቶች ፡ ላይ ፡ ሊገለጽ ፡ የሚገባውን ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡ ሐሰተኛውን ፡ ተክቶ ፡ በመግለጽና ፡ በማቅረብ ፤

(መ) የምርጫ ፡ ራፖርቶችን ፡ ወይም ፡ ጽሑፎችን ፡ ይዞ ፡ በማስቀረት ፡ በመሸሸግ ፡ በመለዋወጥ ፤ ወይም ፡ በማጥፋት ፡ ወይም ፡ እነዚህኑ ፡ ሊቀበሏቸው ፡ ሥልጣን ፡ ለሌላቸው ፡ ሰዎች ፤ ያለ ፡ አገባብ ፡ በመስጠት ፡ አጥፊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። የተለዩ ፡ ወንጀሎች ።

የተፈጸመው ፡ የማጭበርበር ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የመለወጥ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራው ፡ በታወቀ ፡ በረቂቅ ፡ ወይም ፡ በግዙፍ ፡ ዘዴ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ በተጨማሪነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፫፻፹፫ ። ፫፻፹፬ ።]

## ቍ ፡ ፬፻፷፰ ። የድምፅ ፡ መስጠትን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ መራጮች ፡ ያላቸውን ፡ መብታቸውን ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተገለገሉበት ፡ ወይም ፡ ድምፃቸውን ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ ለማወቅ ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

(ለ) ወይም ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ በድንገት ፡ በማወቅ ፡ በቃልም ፡ ሆነ ፡ በጋዜጣ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ለሕዝብ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ወሬውን ፡ የነዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፬፻፷፱ ። የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶችንና ፡ የመሰብሰቢያቸውን ፡ ሣጥን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መግለጫ ፡ የሆኑትን ፡ ጥቅል ፡ ወረቀቶችና ፡ ገና ፡ ያልተገለጹትን ፡ ወረቀቶች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ የነዚሁ ፡ መሰብሰቢያ ፡ የሆነውን ፡ ሣጥን ፡ የወሰደ ፤ እንዲሰወሩ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በተባበሩ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለቆቹና ፡ ለመሪዎቹ ፡ የቅጣቱ ፡ መክበድ ፡ ሳይቀር ።

ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፹፩ ። (መ) ።]

(፫) በምርጫው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ የሚደረጉ ፡ የኀይል ፡ ወይም ፡ የማስገደድ ፡ ሥራዎች ፡ መደበኛ ፡ በሆኑት ፡ ድን ጋጌዎች ፡ ያስቀጣሉ ። [ቍ ፡ ካ፬፻፵፪ ፡ እስከ ፡ ፬፻፵፰ ።]

## ቍ ፡ ፬፻፷፱ ። ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ።

ከግል ፡ ነጻነት ፡ የመታገድ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያስከትል ፡ የምርጫን ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለ ከት ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሕዝባዊ ፡ መብት ፡ የመታገድን ፡ ቅጣት ፡ በተደራቢነት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። (ሀ) ።]

## ቍ ፡ ፬፻፸ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ በሥል ጣኑ ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ የመምረጫ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሥልጣን ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ወይም ፡ የሥራን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ፡ (ቍ ፡ ፬፻፳) ። በተደነገጉት ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ የተመለከቱትን ፡ ቅጣቶች ፡ አሠራሩ ፡ የሚያስከትል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ያ፩ ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ ለጥፋቱ ፡ ከተመደበው ፡ ቅጣት ፡ አጋማሹ ፡ የሚጨ መርበት ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፬፻፲፬ ።]

ነገሩም ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ተደጋግሞ ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነጻ ነት ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣትንና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ አጣምሮ ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ።

# አንቀጽ ፡ ፮ ።

# በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ በሕዝብ ፡ ሰላም ፡ በሕዝብ ፡ ረግቶ ፡ መኖር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ወንጀሎች ፡ እንዲሠሩ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያነሣሡ ፡ ሥራዎች ።

## ቍ ፡ ፬፻፸፩ ። አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ።

(፩) ሙሉ ፡ አካል ፡ እያለው ፡ መኖሪያ ፤ የተለምዶ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ምግብ ፡ ለማግኘት ፡ የተረጋገጡ ፡ ወይም ፡ አሉ ፡ ለመባል ፡ የሚችሉ ፡ ለዚሁ ፡

BACK



እንዲሠሩት ፡ የሚረዱ ፡ ነገሮች ፡ ሳይኖሩት ፡ ሠርቶ ፡ ሊያገኝበት ፡ የሚችለውን ፡ ሥራ ፡ አልቀበልም ፡ በማለት ፡ የሥራ ፡ ፈትነትን ፤ የመጥፎ ፡ አካሄድ ፡ ዐመልን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ነቀፌታ ፡ ያለበትን ፡ የመጥፎ ፡ ዘዴ ፡ ወይም ፡ የለማኝነትን ፡ ኑሮ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ የያዘና ፡ በዚህም ፡ ኑሮው ፡ ለሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ሰው ፤

የነጻነት ፡ መወሰን ፡ ባለበት ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።
[ቍ ፡ ፻፫ ።]

(፪) የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ባሠራራቸው ፡ የወንጀልን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያገለግሉትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ይዞ ፡ የተገኘ ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ የማስገደድ ፡ ተግባርን ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ያጥቂነትን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ ለመፈጸም ፡ የሞከረ ፡ ሲሆን ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ መደራረብ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ደንበኛው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

(፫) አኳኋኑ ፡ የሚጠቅም ፡ ሆኖ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለመጠበቂያ ፡ የሆኑትን ፡ የነጻነት ፡ መቀነስ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ከዋናው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ አጣምሮ ፡ ለመፍረድ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፻፵፰ ፡ እስከ ፡ ፻፶፫ ።]

(፬) በወንጀል ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ በአደገኛ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ፡ ወይም ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በተሠራ ፡ በሌላ ፡ ወንጀል ፡ ተፈርዶበት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተባለው ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ በመጠበቂያ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ተወስኖ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ይፈርድበታል ። [ቍ ፡ ፻፳፰ ።]

ቍ ፡ ፬፻፸፪ ። የከፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ማኅበረተኛነት ።

(፩) ወንጀል ፡ ሠሪዎችን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወይም ፡ ለመሥራት ፡ ከአንድ ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በማደም ፡ አንድ ፡ ስምምነት ፡ ያበጀ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ማኅበረኛነት ፡ አንድ ፡ ጭፍራ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጓድ ፡ ያቋቋመ ፤ ወይም ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ለዚሁ ፡ ተጨማሪ ፡ እንዲሆን ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ተጨማሪ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የገባ ፡ ሰው ፤ አድማው ፡ የተገለጸ ፡ ሲሆን ፤ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በዚሁ ፡ አድማ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተባበሩ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ወይም ፡ የወንጀሎችን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያገለግሉ ፡ ሌሎች ፡ መሣሪያዎች ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እነዚሁ ፡ አድመኞች ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡

ሌሎችንም ፡ ለዚህ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሆኑትን ፡ መጣሪያዎች ፡ ይዘው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የሺሕ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

(፫) ይህ ፡ አድማ ፡ በሰው ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ አካል ፤ ወይም ፡ በጋራ ፡ ጸጥታ ፡ (ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲቭ) ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ተከታትሎ ፡ የተሠራ ፡ ፩ ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ያልሆነ ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መጣሪያ ፡ ወይም ፡ በአፍዛዥ ፡ መድኀኒቶች ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ስለ ፡ መነገድ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሚያስቀጡ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ በመሥራት ፡ በተለይ ፡ አደገኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ የማደራረብ ፡ ድንጋጌን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በሕግ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነውን ፡ የወንጀሉን ፡ ቅጣት ፡ ይፈርዳል ። [ቁ ፡ ፷፪ና ፡ ፷፫ ።]

ቁ ፡ ፬፻፹፫ ። የከፋ ፡ አድራጊዎች ፡ መጠጊያና ፡ ረዳት ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ከሚያስቀጡት ፡ የተባባሪነት ፡ ሥራዎች ፡ ሌላ ፡ [ቁ ፡ ፴፯ ።]

(ሀ) በሕዝብና ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ የወንጀል ፡ ተግባሮችን ፡ ለመፈጸም ፡ ለተቋቋሙት ፡ ጓዶች ፡ ወይም ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሳይገደድ ፡ ዐውቆ ፡ መጠጊያ ፡ ቀለብ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቦታ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሳይገደድ ፡ የነዚህን ፡ ጓዶች ፡ ወይም ፡ ማኅበረተኞች ፡ መኖራቸውን ፡ ዐቅዳቸውን ፡ ወይም ፡ መኖሪያቸውን ፡ ወይም ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቦታቸውን ፡ እያወቀ ፡ ለባለሥልጣን ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የወንበዴው ፡ ጓድ ፡ በጣም ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ መጠጊያና ፡ እርዳታ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ልማደኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ የማያንስ ፡ ይሆናል ።

(፫) ለተከሳሹ ፡ ጥፋት ፡ አደራረግ ፡ ይቅርታን ፡ የሚያሰጠው ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ ጥብቅ ፡ ወዳጅነት ፡ ሲኖር ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለል ፡ ወይም ፡ ከቅጣቱ ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ የተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ። [ቁ ፹ ።]

**ቍ ፡ ፬፻፹፬ ። ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ በጅቷል ፡ በማለት ፡ ስለሚደረግ ፡ መቀስቀስ ።**

በቃል ፤ በጽሑፍ ፤ ሥዕልን ፡ በመሥራት ፡ በአኳኋን ፡ በማመልከት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አድራጎት ፡—

(ሀ) የግፍ ፡ ተግባሮች ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ወንጀል ፡ በማኅበር ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ የሚቀሰቅስ ፤

(ለ) የተሠራውን ፡ ወንጀል ፡ በጅቷል ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛውን ፡ የሚያመሰግን ፤

(ሐ) ከተቀጣው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በመሆን ፡ የጥፋተኛውን ፡ ሥራ ፡ የራሱ ፡ አድርጎ ፡ በመቍጠር ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣኑን ፡ በመንቀፍ ፡ አሳብ ፡ ባንድ ፡ ደንበኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በገንዘብ ፡ እንዲቀጣ ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማዋጣት ፡ የሚጠይቅ ፡ ወይም ፡ መዋጮ ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰበስብ ፡ ወይም ፡ እያወቀ ፡ በዚሁ ፡ ሥራ ፡ የሚሳተፍ ፡ ሰው ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። በተከለከሉ ፡ መሣሪያዎች ፡ መነገድ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) መንግሥትን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጣል ፤ ከቆወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሠራር ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ሕግንና ፡ ደንቦችን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ የሆኑትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ጥይቶች ፡ የሠራ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ያስገባ ፡ ያስመጣ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የላከ ፡ ወይም ፡ ያመላለሰ ፡ (የጫነ) ፡ የገዛ ፡ የተቀበለ ፡ በአደራ ፡ ያስቀመጠ ፤ ወይም ፡ የደበቀ ፡ ወይም ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ያደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፪፻፶፬ ።]

(ለ) ወይም ፡ በመሣሪያ ፡ መነገድ ፡ ከተባለው ፡ አድራጎት ፡ ውጭ ፡ ቢሆንም ፡ ለሚጠረጠሩ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እያወቀ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሸጠ ፡ ያስረከበ ፡ ወይም ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ያደረገው ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ሐሳብ ፡ ሲሆን ፡ የሚደርስበት ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮና ፡ የተባሉትም ፡ ዕቃዎች ፡ መወረስ ፡ ሳይቀር ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ የመጣስና ፡ እንዲሁም ፡ የተከለከሉትን ፡ መሣሪያዎች ፡ የመያዝና ፡ በነዚሁም ፡ የመገልገል ፡ ተግባሮች ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ያስቀጣሉ ። [ቍ ፡ ፯፻፷፫ና ፡ ፯፻፷፬ ።]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የሕዝብ ፡ ሁከት ፡ እንዲነሣ ፡ የሚያደርጉ ፡ የማነሣሣት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሥራዎች ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፯ ። የተከለከሉ ፡ ማኅበሮችና ፡ ስብሰባዎች ።**

ማንኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡—

(ሀ) በሕግ ፤ በመንግሥት ፤ ወይም ፡ በደንበኛ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በጠቅላላው ፡ ወይም ፡ በአጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ የተከለከለውን ፡ ማኅበር ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ ጉባኤ ፡ ያቋቋሙ ፡ ያደራጁ ፡ ወይም ፡ የመሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እያወቁ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ለነዚሁ ፡ ለተከለከሉ ፤ ማኅበሮች ፡ ስብሰባዎች ፡ ጉባኤዎች ፡ የነርሱ ፡ የሆኑትን ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ቦታዎች ፡ እያወቁ ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲገለገሉባቸው ፡ ያደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

መሪ ፤ አዘጋጅ ፡ ወይም ፡ አነሣሽ ፡ የሆኑት ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፭፻ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፰ ። ድብቅ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፤ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ክፍሎች ።**

የማኅበሩ ፡ ሥራና ፡ ስብሰባ ፡ በድብቅ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ማኅበሮችና ፡ ክፍሎች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ የወታደር ፡ የዒላማ ፡ የጨዋታ ፡ ስብሰባዎች ፡ ናቸው ፡ በሚባል ፡ ስም ፡ ሲሆኑ ፡ ለነዚሁ ፡ ለተከለከሉት ፡ ማኅበሮችና ፡ ስብሰባዎች ፡ ሥራ ፡ አዘጋጂዎች ፡ ወይም ፡ መሪዎች ፡ ወይም ፡ እውነተኛ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እስከ ፡ መደበኛው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በእስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፱ ። የተከለከሉ ፡ ስብሰባዎች ።**

(፩) በሕዝብ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉትን ፡ የግርግር ፡ ስብሰባዎች ፡ የሚያደራጁ ፡ የሚያቋቁሙ ፡ ወይም ፡ የሚመሩ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ በፈቃዳቸው ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ።

አነሣሺዎቹ ፡ አዘጋጂዎቹ ፡ መሪዎቹ ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ይህ ፡ ስብሰባ ፡ መሣሪያ ፡ በመያዝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራቱ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ይሆናል ። ደግሞም ፡ በአነሣሺዎቹ ፡ በአዘጋጇዎቹ ፡ በመሪዎቹና ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ በተገኙት ፡ ወይም ፡ መሣሪያ ፡ መያዙን ፡ በተረዱት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፤ እስከ ፡ ደንበኛው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። በወሬ ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማሸበር ።</u>

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ለሕዝብ ፡ ወይም ፡ ለሕይወት ፡ ለጤና ፡ ወይም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ንብረቶች ፡ አሥጊ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ መጣ ፡ በማለት ፡ በሚደረግ ፡ ማስፈራራት ፡ ይልቁንም ፡ ወራሪ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መጣ ፤ ቃጠሎ ፡ ተነሣ ፤ አገር ፡ መውደሙ ፡ ወይም ፡ መዘረፉ ፡ ነው ፡ በማለት ።

(ለ) ወይም ፡ እንደዚሁ ፡ ያሉትን ፡ ሥራዎች ፡ ብጥብጦችን ፡ ምስቅልን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ መጡ ፡ በማለት ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የሐሰትን ፡ ወሬዎች ፡ በመንዛት ፡ ሕዝብን ፡ ያሸበረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አስፈላጊ ፡ ሲሆን፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ቅጣቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ብጥብጥን ፤ ወይም ፡ ትልልቅ ፡ ምስቅልቅሎችን ፡ ለማምጣት ፡ የሚችሉ ፡ ወይም ፡ ያመጡ ፡ ነገሮች ፡ ሲሆኑ ፡ የሚፈረደው ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ እስራት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። የሐሰት ፡ ወሬዎችን ፡ ስለ ፡ ማውራትና ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፤ በመንግሥት ፡ ባገር ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ሲሠራ ፡ ከሚፈጸሙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ። [ቍ ፡ ፪፻፶፪ ። ፪፻፷፬ ፡ (ሠ) ። ፭፻ ፡ (ሀ) ።]

(ሀ) በመንግሥት ፡ በሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወይም ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ወሬዎችን ፡ ጥርጣሪዎችን ፡ ወይም ፡ የሐሰት ፡ ሐሜታዎችን ፡ የሚጥል፡ወይም ፡ የሚነዛ ፡ ሰው ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሕዝብን ፡ አሳብ ፡ ያናወጠ ፡ የቀሰቀሰ ፡ ወይም ፡ ለማናወጥ ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ማሳጣት ፤ ወይም ፡ ጥርጣሪ ፡ በሚያሳድሩ ፡ ነገሮች ፤ በውስጠ ፡ ነገር ፤ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ አድራጎቶች ፡ በፖለቲካ ፡ ጉዳይ ፤ በዘር ፡ ወይም ፡ በሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ለመለያየት ፡ ለጥል ፡ ለፍጅት ፡

ወይም ፡ ለብጥብጥ ፡ የሚገፋፋ ፡ ወይም ፡ የሚቀሰቅስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። የማነሣሣት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሐሳብ ፡ መግለጫዎች ፡ (ማኒፌስታሲዮን)።**

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ስብሰባ ፤ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ በሆነ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የሚያነሣሣ ፡ ወይም ፡ ዛቻ ፡ የሆነ ፡ ንግግር ፡ የተናገረ ፤ ጩኸት ፡ ያሰማ ፤ ሥዕል ፡ ወይም ፡ የሥዕል ፡ ንድፍ ፡ የበተነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተሰጡትን ፡ ትእዛዞች ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ በዐዋጅ ፡ ለወጣው ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ መታዘዝ ፡ እንዳይኖር ፡ ለማድረግ ፡ በግልጽ ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ የቀሰቀሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ፭፻ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። ሽብር ።**

(፩) ብዙ ፡ በመሆን ፡ በሰዎች ፡ በርስቶችና ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ የፍጅት ፡ ሥራ ፡ በተደረገበት ፡ ስብሰባ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፤ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ሽብሩን ፡ ያደራጁት ፡ የቀሰቀሱት ፡ ወይም ፡ የመሩት ፡ ሰዎች ፡ በገንዘብ ፡ ከመቀጣታቸው ፡ በላይ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

(፫) እያንዳንዳቸው ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ የግፍን ፡ ተግባሮች ፡ የሚፈጽሙ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የሠሩት ፡ ወንጀል ፡ በተለይ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ የማያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። ልዩ ፡ አስተያየት ፡ የሚደረግላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ መታዘዝ ።**

የኀይል ፡ ሥራ ፡ ሳይሠሩ ፡ ወይም ፡ እንዲሠሩ ፡ ሳያነሣሡ ፡ ክልክል ፡ ከሆነው ፡ ጉባኤ ፤ ከሐሳብ ፡ መግለጫ ፡ ቦታ ፤ ከስብሰባ ፤ ሽብር ፡ ግርግር ፡ ከሚደረግበት ፡ ስፍራ ፤ ወይም ፡ ሽብሩ ፡ ሲጀመር ፡ ዐውቀው ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ ሲያዛቸው ፡ ከነዚህ ፡ ተለይተው ፡ ወጥተው ፡ በሄዱት ፡ ተካፋዮች ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነ ፡ ወቀሳና ፡ ተግሣጽ ፡ ከተደረገባቸው ፡ በኋላ ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ እንዲወጡ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፻፳፩ ።]

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በሕዝብ ፡ ሰላምና ፡ በሕዝብ ፡ ረግቶ ፡ መኖር ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፬፻፹፬ ። ስብሰባንና ፡ ጉባኤን ፡ ስለ ፡ መበጥበጥ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ ያለውንና ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደውን ፣ ስብሰባ ፣ ወይም ፡ ጉባኤ ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በማስፈራራት ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ በጉልበት ፣ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አደራረግ ፡ በማይገባ ፡ አኳኋን ፡ የሚበጠብጥ ፤ (የሚያውክ) ፡ የሚከለክል ፡ ወይም ፡ የሚበታትን ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፤ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በሕዝብ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተፈቀደ ፡ በግልጽ ፡ የታዘዘ ፡ የመማከርቶች ፡ ወይም ፣ የኮሚሲዮን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ምርጫ ፡ የተደረገ ፤ በአደባባይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሐራጅ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ስለ ፡ ተፈቀደው ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ የሕዝብ ፡ ሥራ ፡ የማከናወን ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገ ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ ጉባኤ ፡ ሲሆን ፤ ለፖለቲካ ፡ ወይም ፡ ለአስተዳደር ፡ ለሕግ ፡ አስፈጻሚነት ፡ ወይም ፡ ለዳኝነት ፡ ረገድ ፡ የተደረገም ፡ ቢሆን ፡ እስራቱ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ ሆኖ ፡ መቅጫውም ፡ ጭምር ፡ ከፍተኛ ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ እስከተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ድረስ ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ።

(፫) ብጥብጥ ፡ አንሺው ፡ ወይም ፡ አንሺዎቹ ፣ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ይሆን ፡ የኀይል ፡ ሥራቸውን ፡ የመደገፍ ፡ ዐይነት ፡ ያላቸውን ፡ መሣሪያዎች ፡ በመያዝ ፡ የመበጥበጥ ፡ ሥራቸውን ፡ ፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ የመበጥበጥ ፤ ወይም ፡ የመከልከል ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በብዙ ፡ ጭፍራ ፡ በብዙ ፡ ሰው ፣ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነጻነትን ፡ የመከልከሉ ፡ ቅጣት ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ለመሆንና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባለውም ፡ ጥፋት ፡ የተፈጸመው ፡ በሕዝብ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ ይህን ፡ ጽኑ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለማስረዘም ፡ ይቻላል ።

### ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። በጥፋተኛነት ፡ ከኀላፊነት ፡ ውጭ ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠሩ ፡ ተግባሮች ።

ሆነ ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ሆኖ ፡ በሚቈጠር ፡ ቸልተኛነት ፡ ሰክሮ ፡ ወይም ፤ ተመርዞ ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፤ ከአላፊነት ፡ በሚያድን ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ያንድ ፡ ዓመት ፤ እስራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሥራ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እንደ ፡ ተፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ከባድነትና ፡ እንደ ፡ አደገኛነቱ ፣ ማደግ ፡ ወይም ፣ ማነስ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚ ችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። የሃይማኖትን ፡ ስሜትና ፡ ሰላም ፡ ስለ ፡ መንካት ።**

ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ።

(ሀ) የተፈቀደውን ፡ የሃይማኖት ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ተግባር ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚከለክል ፡ የሚያውክ ፡ ወይም ፡ የሚያስተሐቅር ፤

(ለ) ላንድ ፡ አምልኮት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ የተመረጡትን ፡ ያንድ ፡ ሃይማኖት ፡ የግል ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሥዕል ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትን ፡ የሚያረክስ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። የሙታንን ፡ ሰላምና ፡ ክብር ፡ መንካት ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የሬሳን ፡ አጀብ ፡ ወይም ፡ የቀብሩን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ያወከ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አንድ ፡ ሙት ፡ ሰው ፡ ያረፈበትን ፡ ቦታ ፡ የሚደፍር ፡ የሚያረክስ ፡ የመቃብሩን ፡ ሐውልት ፡ የሚያፈርስ ፡ ወይም ፡ የሚያረክስ ፡ ወይም ፡ የተቀበረውን ፡ ወይም ፡ ያልተቀበረውን ፡ ምውት ፡ ሰው ፡ ያረከሰ ፡ ወይም ፡ አካሉን ፡ የቈረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በግልጽ ፡ የሰውን ፡ሬሳ ፡ ያዋረደ ፡ ወይም ፡ የመታ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሬሳን ፡ እንዲጠፋ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ሬሳን ፡ ወይም ፡ ያሬሳውን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ነጣጥሎ ፡ ያጠፋ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ።

## አንቀጽ ፡ ፯ ።

## በጋራ ፡ ጸጥታ ፡ (ሴኩሪቲ) ፡ ኮሌክቲቭና ፡ በመገናኛዎች ፡ ላይ ።

## ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በጋራ ፡ ጸጥታ ፡ (ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲቭ) ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፰ ። ዳእሳት ፡ ቃጠሎ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ ዐቅዶ ፡ ወይም ፡ የኅብረት ፡ አደጋ ፡ ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ ሕንጻዎችን ፡ ወይም ፡ እነዚ

ህን ፡ የመሰሉትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ዐይነቶች ፡ ሥራዎች ፡ ሰብሉችን ፡ ወይም ፡ የግብርና ፡ ፍሬዎችን ፡ ደኖችን ፡ ዛፎችን ፡ ወይም ፡ ሌሎችን ፡ ዕቃዎች ፡ በእሳት ፡ ያያያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስ ራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደገኛ ፡ በሚሆንበት ፡ ወይም ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብ ረቶች ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ የጉዳት ፡ አደጋ ፡ በጣም ፡ የተስፋፋ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ በሕዝብ ፡ ሕንጻዎች ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በሚጠቅሙ ፡ ሕንጻዎች ፡ ተቀማጭ ፡ ሰው ፡ ባለባቸው ፡ ወይም ፡ ለመኖሪያነት ፡ በሚያገለግሉ ፡ ቤቶች ፡ በሥራ ፡ ቦታዎች ፡ በምግብ ፡ ማከማቻዎች ፡ በነዳጆች ፡ ወይም ፡ በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ በጫካዎች ፡ በመዓድኖች ፡ በቤንዚን ፡ ማውጫ ፡ ጕድጓዶች ፡ ወይም ፡ በማጣሪያዎች ፡ በመርከቦች ፡ ወይም ፡ በአይሮፕ ላኖች ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ለአደጋ ፡ ምቹ ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተወሰነው ፡ መጠን ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እኳ ኋን ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፬፻፹፱ ። ፍጥረታውያን ፡ መቅሠፍቶችን ፡ ስለ ፡ መቀስቀስ ።

ይህንኑ ፡ ዐቅዶና ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ ለማ ምጣት ፡ የውሃ ፡ ማጥለቅለቅ ፡ ወይም ፡ ማስጠም ፡ እንዲነሣ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲ ፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲናድ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ መቅሠፍት ፡ እንዲደርስ ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፯ ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፺ ። የሥራ ፡ ቦታዎችንና ፡ የመጠባበቂያ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለ ፡ መጉዳት ።

ይህንኑ ፡ ዐቅዶና ፡ አስቦ ፡ በኤሌክትሪክ ፡ በውሃዎች ፡ የሚካሄዱትን ፡ ወይም ፡ ለተፈጥሮ ፡ ኀይል ፡ ለመጠባበቂያ ፡ የሆኑትን ፡ የሥራ ፡ ቦታዎችን ፡ ይልቁንም ፡ ቧንቧዎችን ፡ ቦዮችን ፡ ማጠራቀሚያዎችን ፡ ማገጃዎችን ፡ የውሃ ፡ ማገጃና ፡ መል ቀቂያዎችን ፡ ወይም ፡ ማዕበል ፡ መከልከያዎችን ፡ የሚያበላሽ ፡ ወይም ፡ የሚያፈ ርስ ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ የሚያደ ርስ ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፯ ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። ስለ ፡ ማፈንዳት ።

እንዲሁም ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስ ፡ በማሰብ ፡ ይህ ንኑ ፡ ዐቅዶ ፡ ጋዝ ፡ ቤንዚን ፡ ባሩድ ፡ ዲናሚት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ አደገኛ ፡ ነገር ፡ እንዲፈነዳ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፯ ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። በቸልተኛነት ፡ የሚደረግ ፡ ወንጀል ።

አጥፊነትን ፡ በሚያስከትል ፡ ቸልተኛነት ፡ የእሳት ፡ ቃጠሎን ፡ የተፈጥሮ ፡ መቅሠፍ ትን ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ በተቋቋሙ ፡ የሥራ ፡ ሕንጻዎችና ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ያደ ረሰ ፡ ወይም ፡ ከቍጥር ፡ ፬፻፹፯ ፡ እስከ ፡ ፬፻፺፩ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ የሚፈነዳ ፡

BACK



ነገር ፡ ያስነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ ሁኔታ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስራትን ፡ የሚፈርደው ፡ አጥፊው ፡ በራሱ ፡ አሠራር ፡ ምክንያት ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ አድርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህም ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስ ፡ ለማወቅ ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፭፻፳፫ ። በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ በሚመርዙ ፡ ጋዞች ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በኅብረት ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ ለማድረስ ፡ በማቀድ ፡ በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ዐውቀው ፡ በቀላሉ ፡ በሚቃጠሉ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ በሚመርዙ ፡ ጋዞች ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ የሰውን ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ የሰዎችን ፡ የአካል ፡ ሙሉነት ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ የጣለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። በወንጀል ፡ የተከሰሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ የጣለው ፡ ንብረትን ፡ ብቻ ፡ ሲሆንና ፡ ያደረሰውም ፡ ጉዳት ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የማይባል ፡ ወይም ፡ ዋና ፡ ጉዳት ፡ ተብሎ ፡ የማይቈጠር ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ እስራት ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ።

(፪) በኅብረት ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ ለማድረስ ፡ በማቀድ ፡ ሳይሆን ፡ ሆነ ፡ ብሎም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ ሙሉነት ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ ለመጣል ፡ እስከሚችል ፡ ድረስ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በእስራት ፡ ፋንታ ፡ ቅጣቱን ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፭፻፳፬ ። በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ መሥራት ፡ መግዛት ፡ መሰወርና ፡ ማመላለስ ።**

(፩) ለአጥፊነት ፡ መሠራታቸውን ፡ እያወቀ ፡ የሚፈነዱ ፡ የሚያቀጣጥሉ ፡ ወይም ፡ መርዝ ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ ወይም ፡ የሚመርዙ ፡ ጋዞችን ፡ የሠራ ፡ ሠርቶ ፡ የሚያወጣ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ የአጥፊነት ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ለዚሁ ፡ ሰው ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ሠርቶ ፡ ለማውጣት ፡ የሚያገለግሉትን ፡ መሣሪያዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ወይም ፡ የሚያመለክት ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፤ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ለአጥፊነት ፡ ተግባር ፡ የሚውሉ ፡ መሆናቸውን ፡ እያወቀ ፡ የሚፈነዱ ፡ የሚያቃጥሉ ፡ ነገሮችን ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሚመርዙ ፡ ጋዞችን ፡ የሚሠሩባቸውንም ፡ ቅመሞች ፡ የሚያስመጣ ፡ የሚገዛ ፡ ወይም ፡ ፈልጎ ፡ የሚያገኛቸው ፡ ወይም ፡ እጁ ፡ እንዲገቡ ፡ የሚያደርግ ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ የሚቀበል ፡ ወይም ፡ አደራ ፡ የሚያስቀምጥ ፡ የሚሰውር ፡ ወይም ፡ የሚያመላልስ ፡ ሰው ፡ በዋጋ ፡ ወይም ፡ ያለዋጋ ፡ ቢሆን ፤ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፶፭ ። የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ኪን ፡ ጥበብ ፡ ደንቦችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ የሕንጻን ፡ ሥራ ፡ በመምራት ፡ ወይም ፡ በመፈጸም ፡ ወይም ፡ በማፍረስ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ የልምድና ፡ የጥንቃቄ ፡ ደንቦችን ፡ የሚጥስ ፡ በዚሁም ፡ ሥራው ፡ ዐውቆ ፡ የጋራ ፡ ጸጥታን ፡ (ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲቭን ፡) ኑሮ ፤ የሰዎችን ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ሙሉነትን ፡ ወይም ፡ የንብረቶችን ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ሰውን ፡ ንብረት ፡ ጸጥታ ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ የሚጥል ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተለይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተወሰነው ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆነ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፭፻፶፮ ። መጠባበቂያ ፡ የሚሆኑትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ማጥፋት ፡ ወይም ፡ አለማደራጀት ።

(፩) አስቦ ፡—

(ሀ) ባንድ ፡ የሕዝብ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የግል ፡ ፋብሪካ ፡ ቤት ፡ ባንድ ፡ የማዕድን ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ በሚወጣበት ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስ ፡ ለመጠበቂያ ፡ የተደረገውን ፡ መሣሪያ ፡ የሚያጠፋ ፡ ወይም ፡ የሚያስቀር ፤ ወይም ፡ የሚያበላሽ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ እንዲቀር ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ የሚያደርግ ፤

(ለ) ግዴታው ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ችሎታ ፡ ባለው ፡ ሥልጣን ፡ የታዘዘ ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፡ ለመጠበቂያ ፡ የሚያገለግል ፡ የሥራ ፡ መሣሪያ ፡ ማቋቋምን ፡ የተወና ፡ በዚሁም ፡ የተነሣ ፡ እያወቀ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ጸጥታ ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ የጣለ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

በእስራትና ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አጥፊው ፡ በቸልተኛነት ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከነዚሁ ፡ ቅጣቶች ፡ አንዱን ፡ ይፈርዳል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፯ ። በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሲደርስ ፡ ባለማስታወቅ ፡ የሚደረግ ፡ ጥፋት ።**

በእርሱም ፡ በሌሎችም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሳይመጣ ፡ ለማስታወቅ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ቃጠሎ ፡ መፈንዳት ፡ የውኃ ፡ ማጥለቅለቅ ፡ ወይም ፡ በተፈጥሮ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ያልሆነ ፡ አንድ ፡ መቅሠፍት ፡ በሰው ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያመጣውን ፡ አደጋ ፡ ለባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የጥበቃ ፡ ችሎታ ፡ ላላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ያላስታወቀ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ለመከላከል ፡ በጊዜው ፡ አስፈላጊዎቹን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ያላደረገ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፰ ። የማይነኩ ፡ ሁኔታዎች ።**

ለአገር ፡ መከላከያና ፡ ለወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ የቆሙ ፡ የሥራ ፡ ቦታዎችንና ፡ ሥራዎችን ፡ በጉዳት ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ወይም ፡ በማበላሸት ፡ በተለይም ፡ በማፍረስ ፡ ወይም ፡ በማሰናከል ፡ በጉዳት ፡ ላይ ፡ የማዋልን ፡ ነገሮች ፡ የፈጸሙ ፡ ሰዎች ፡ ስለነዚሁ ፡ ጉዳቶች ፡ በተወሰኑት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣሉ ። [ቍ ፡ *፬፻፷ ። ፫፻፳ና ፡ ፫፻፳፪ ። ፫፻፴፯ ፡ (ሀ) ።]

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በመገናኛዎች ፡ ጸጥታና ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፱ ። ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ በተቋቋሙ ፡ ሥራዎችና ፡ አገልግሎቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሆኑትን ፡ የማመላለሻ ፡ የምድር ፡ የወንዝ ፡ የባሕር ፡ ወይም ፡ የአየር ፡ መገናኛዎችን ፡ እንዲሁም ፡ ለዚሁ ፡ መርጃ ፡ የሆኑትን ፡ በማደሻ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የሚሠሩትን ፡ የመጠባበቂያ ፡ ቦታዎች ፡ አገልግሎትን ፤

(ለ) ወይም ፡ የሥራ ፡ ቦታዎችን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ፖስታ ፡ ማስ

BACK



ተላለፍ ፡ ቴሌግራፍ ፡ ቴሌፎን ፡ ወይም ፡ በጠቅላላ ፡ ስለ ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ሥራዎች ፡ የሚመለከቱትን ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የውሃ ፡ የመብራት ፡ የጋዝ ፡ የኀይል ፡ ወይም ፡ የሙቀት ፡ መመላለሻ ፡ ወይም ፡ ማካፈያ ፡ ደንበኛ ፡ አሠራራቸውን ።

የከለከለ ፡ ያወከ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህን ፡ በማሰብ ፡ የተደረገውን ፡ ጉዳት ፡ በሕግ ፡ በውል ፡ በኅብረት ፡ ወይም ፡ በግል ፤ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይልቁንም ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ ግዴታዎቹ ፡ የተቋረጡት ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ ባልሆነ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ከተፈቀዱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የተደነገጉት ፡ የኪሣራዎች ፡ መክፈል ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ፩ ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

(፫) ጥፋቱ ፡ የተደረገው ፡ በቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያልፍ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፭፻ ። በመገናኛዎችና ፡ በሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ከባድ ፡ ጉዳትና ፡ መበላሸት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በመንገድም ፡ ሆነ ፡ በምድር ፡ ባቡር ፡ በውሃም ፡ ሆነ ። በአየር ፡ ላይ ፡ መጋጨትን ፡ መስጠምን ፡ ከሐዲድ ፡ መውጣትን ፡ ወይም ፡ በሰውና ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ አደጋና ፡ መቅሠፍት ፡ ሊያመጣ ፡ በሚችል ፡ አኳኋን ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ባለመሥራት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይልቁንም ፡—

(ሀ) ድልድዮችን ፡ ግድቦችን ፡ የተቋቋሙ ፡ መሥሪያዎችን ፡ ለመመላለሻ ፡ አገልግሎት ፡ የሚረዱ ፡ ነገሮችን ፡ መዛሪያዎችን ፡ ወይም ፡ የመጠባበቂያን ፡ የመቈጣጠሪያን ፡ የማሳያን ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ የማመላለሻ ፡ ድርጅቶችን ፡ በማበላሸት ፡ ከቦታው ፡ በማዛወር ፡ በማፍረስ ፡ ወይም ፡ እንዳያገለግሉ ፡ በማድረግ ፤

(ለ) በሚሄዱበት ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ ሐዲድ ፡ ወይም ፡ ትልቅ ፡ ቦይ ፡ (ካናል) ፡ ወይም ፡ በማንኛዎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ ለማምጣት ፡ የሚችሉትን ፡ ክንውኖች ፡ ወይም ፡ ሥራዎች ፡ በማካሄድ ፡ ወይም ፡ መሰናክሎችን ፡ በማድረግ ፤

(ሐ) የሐሰት ፡ ትእዛዞችን ፡ ማመልከቻዎችን ፡ ወይም ፡ ምልክቶችን ፡ በመስጠት ፤

(መ) ግዴታዎችን ፡ ደንቦችን ፡ ወይም ፡ ለጥንቃቄ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በመጣስ ፤

BACK



የሕዝብ ፡ ማመላለሻዎችን ፡ ያቆመ ፡ ያሰናከለ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡ ጥፋተኛው ፡ እያወቀ ፤

(ሀ) ያለበትን ፡ የውሉን ፡ ወይም ፡ የሞያውን ፡ ግዴታ ፡ የጣሰ ፤

ለ) ሕይወትን ፡ የአካልን ፡ ሙሉነት ፡ ወይም ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ጤና ፡ በጉዳት ፡ ላይ ፡ ያዋለ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የንብረትን ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ጥፋቱን ፡ ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ ቅጣት ፡ ይፈርድበታል ።

በእስራት ፡ ሊቀጣ ፡ የሚገባው ፡ ባንድ ፡ የሞያ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ወይም ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ሲችል ፡ ቸል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፩ ። ምልክቶችንና ፡ የእርዳታ ፡ ጥሪዎችን ፡ አላግባብ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

በክፋት ፡ ወይም ፡ አንድም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ሳይኖረው ፡ በመገናኛዎች ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ እንዲሆን ፡ ወይም ፡ መገናኛ ፡ እንዲቋረጥ ፡ በማቀድ ፡ የአደጋ ፡ ምልክቶችን ፡ ያሳየ ፡ ያሰማ ፡ ወይም ፡ የተለመደውን ፡ የእርዳታ ፡ ጥሪ ፡ ወይም ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ የታወቀውን ፡ ምልክት ፡ የሰጠ ፤ የጸጥታን ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ የማስጠንቀቂያን ፡ ምልክት ፡ የሠራበት ፡ ወይም ፡ ለአደጋ ፡ ጊዜ ፡ የሚሆነውን ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ምልክት ፡ በማይገባ ፡ የሠራበት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

በገንዘብ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፪ ። ለሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ለሆኑት ፤ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ትራፊክ ፡ አጠባበቅ ፡ የወጡትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ባለመጠበቅ ፡ ሰዎችን ፡ ወይም ፡ ንብረቶችን ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ ለመጣል ፡ ወይም ፡ ለመጉዳት ፡ ሳያስብ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በሆነ ፡ በምድር ፡ በአየር ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡ ማመላለሻ ፡ የሚቃጠሉ ፡ የሚፈነዱ ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ መርዝ ፡ የሚሆኑ ፡ ወይም ፡ በመነካካት ፡ ወይም ፡ በሙብነን ፡ ወይም ፡ በመበተን ፡ የሚያበላሹና ፡ የሚያጠፉ ፡ ነገሮችን ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ይዞ ፡ የተሳፈረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## በሕዝብ ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ለጥበቃ ፡ በተደረጉት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፭፻፫ ። የሰውን ፡ በሽታ ፡ ማባዛት ።**

(፩) አስቦ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ያባዛ ፡ ወይም ፡ ያስተላለፈ ፡ ሰው ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ከገንዘቡ ፡ መቀጮ ፡ ጋራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ለመፍረድ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) በጥላቻ ፤ በመበቀል ፡ መንፈስ ፡ ወይም ፡ በቂም ፡ በክፋት ፡ ወይም ፡ በወራዳነት ፡ ጠባይ ፡ ከባድ ፡ በሽታ ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ያልሆነ ፡ ወረርሺኝ ፡ (ኤፒዴሚ) ፡ ተላላፊ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ በሽታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ያደረገው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚሆን ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፭፻፬ ።የከብት ፡ በሽታን ፡ ስለ ፡ ማባዛት ።**

(፩) በቤት ፡ እንስሶች ፡ ወይም ፡ በዶሮ ፡ ቤት ፤ በሚበላ ፡ የዱር ፡ እንስሳ ፡ በዓሣ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዐይነታቸው ፡ በሕግ ፡ የተጠበቁ ፡ የዱር ፡ አውሬዎች ፡ መካከል ፡ የከብት ፡ በሽታን ፡ የነዛ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ቀጣት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ወርና ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) አጥፊው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከቱት ፡ ከዝቅተኛ ፡ ምክንያቶች ፡ በንዱ ፡ ተገፋፍቶ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ አስቦ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፭፻፭ ። የሰብልን ፡ ወይም ፡ የደንን ፡ ትል ፡ ስለ ፡ መንዛት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ በእርሻ ፡ ሰብል ፡ ወይም ፡ በደን ፡ አሥጊ ፡ የሆነ ፡ የትል ፡ ርቢን ፡ ያባዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ።

ቍ ፡ ፭፻፮ ። ውሃን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ።

(፩) አስቦ ፡ ለሰው ፡ ወይም ፡ ለእንስሳዎች ፡ ባስፈላጊነት ፡ የሚያገለግለውን ፡ የሚጠጣ ፡ ውሃ ፡ ጥሩነት ፡ ለጤና ፡ ጎጂ ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ የሚያበላሽ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ።

እንደ ፡ ነገሩ ፡ አኳኋን ፡ አስቦና ፡ ፈቅዶ ፡ እንዳደረገው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አስቦ ፡ የውሃ ፡ ጕድጓዶችን ፡ ወይም ፡ ማጠራቀሚያዎችን ፡ ምንጮችን ፡ የውሃ ፡ መነሻዎች ፤ ወንዞችን ፡ ወይም ፡ ሐይቆችን ፡ የመረዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጽኑ ፡ እስራቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፫) ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፯ ። ግጦሽን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ።

(፩) አስቦና ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ የእንስሳዎችን ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ጤና ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ በመጣል ፡ አኳኋን ፡ መርዛም ፡ ወይም ፡ ጎጂ ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ግጦሽን ፡ ወይም ፡ መስኮችን ፡ ያበላሸ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፰ ። የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) የሰውን ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ለማስወገድ ፡ ወይም ፡ ለማቆም ፡ በሕግ ፡ በደንብ ፡ በባለሥልጣን ፡ የተሰጡትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የጣሰ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስራቱ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወርና ፤ መቀጮውም ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

(፪) የከብት ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ የትል ፡ ርቢ ፡ ወይም ፡ የሰብል ፡ ወይም ፡ የደን ፡ ትልን ፡

ማባዛት ፡ ለማስወገድ ፡ ወይም ፡ ለማቆም ፡ የተሰጡ ፡ ውሳኔዎች ፡ ወይም ፡ ደንቦች ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በተጣሰ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ያደረገው ፡ በቸልተኛነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፭፻፱ ። ችግር ፡ ወይም ፡ ረኃብ ፡ እንዲመጣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ሆን ፡ ብሎ ፡ የማይገባውን ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ባለመሥራት ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ባገር ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ መከራ ፤ ችግር ፤ ረኃብ ፤ ተላላፊ ፡ በሽታ ፤ የከብት ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ኀዘን ፡ እንዲመጣ ፡ ያደረገ ፤ በተለይም ፡ በመደበቅ ፡ ወይም ፡ ያላገባብ ፡ በማከማቸት ፡ በማጥፋት ፡ ወይም ፡ ለሰው ፡ ወይም ፡ ለእንስሳ ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ጤና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የእህልን ፡ የምግብን ፡ የቀለብን ፡ የመድኀኒትን ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ ማመላለስንና ፡ ማከፋፈልን ፡ የከለከለ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

እሥራት ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ምግብ ፡ መድኀኒት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የችግር ፡ ሁኔታ ፡ እንዳይደርስ ፡ ለማድረግ ፡ ሌሎችን ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ለማቅረብ ፡ በአቅራቢነት ፡ በአማካይነት ፡ በሁለተኛ ፡ ተዋዋይነት ፡ በአመላላሽነት ፡ በእንደራሴነት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ስም ፡ የገባውን ፡ ግዴታዎችና ፡ ውለታዎች ፤ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ሳይሆን ፡ ያልፈጸመ ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ ያልሠራ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ይህን ፡ ያደረገው ፡ በማይገባ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሦስት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ተጣምሮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፲ ። መርዛም ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ነገሮችን ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፡ መሥራት ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ማድረግ ።

(፩) ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ መርዛም ፡ ነገሮችን ፡ ወይም ፡ መድኀኒቶችን ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙትን ፡ አብነቶች ፡ ያወጣ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ የለዋወጠ ፡ ያስመጣ ፡ ወይም ፡ የላከ ፡ ወይም ፡ ያመላለሰ ፡ የገዛ ፡ ወይም ፡ የተቀበለ ፡ ያኖረ ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ያዘዋወረ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሰጠ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

BACK



እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) መርዝ ፡ የሚሆኑ ፡ መድኀኒቶች ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ነገሮች ፡ የሚደረግባቸውን ፡ ቤቶች ፡ በግል ፡ አኳኋንም ፡ ቢሆን ፡ እያወቀ ፡ ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመቅጣት ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) ይኸው ፡ ጥፋት ፡ የተደረገው ፡ በብዙ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ንግድ ፡ በተደራጀ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ሞያው ፡ አድርጎ ፡ በሚሠራ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ወይም ፡ ጥቅምን ፡ በመፈለግ ፡ መንፈስ ፡ ወይም ፡ ራስን ፡ በመውደድ ፡ ወይም ፡ በወራዳነት ፤ የተከለከለውን ፡ መርዛም ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ እያወቀ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ በሽታ ፡ ሁኔታ ፡ ላደረበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ መድኀኒቱን ፡ ከልክ ፡ ለሚያሳልፍ ፡ ሰው ፡ የሰጠና ፡ የፈቀደ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፲፩ ። የሚጎዱ ፡ ወይም ፡ የተበላሹ ፡ ምግቦችንና ፡ ዕቃዎችን ፡ መሥራትና ፡ መሸጥ ።

(፩) ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ዐይነታቸው ፡ ጎጂ ፡ የሆኑትን ፡ ወይም ፡ ጎጂ ፡ ከሆኑት ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ከቀበላሹ ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ ምግቦችን ፡ ቀለቦችን ፡ የሚሠራ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ጕዳት ፡ ለማድረግ ፡ በሚችል ፡ አኳኋን ፡ የሚያበላሻቸው ።

(ለ) ወይም ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ጎጂ ፡ ነገሮች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ያስመጣ ፡ የተቀበለ ፡ ያስቀመጠ ፡ ወይም ፡ ያከፋፈለ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱ ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሚሆነው ፡ —

(ሀ) አድራጊው ፡ የመንግሥት ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ ከመንግሥት ፡ በተሰጠ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ በተቋቋመ ፡ ድርጅት ፡ የመጠባበቅና ፡ የመመርመር ፡ ልዩ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤

(ለ) ጤናን ፡ የሚጠብቁ ፡ ወይም ፡ የሚያበረቱ ፤ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ መርዝነት ፡ የሌላቸው ፤ ያለ ፡ ሐኪም ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መድኀኒቶች ፡ በመጥፎ ፡ አሠራራቸው ፡ ወይም ፡ በመጥፎ ፡ አለዋወጣቸው ፡ የታወቀ ፡ ጕዳት ፡ የሚያመጡ ፡ መሆናቸው ፡ ሲታወቅ ፡ ለማወቅ ፡ ሲቻል ፡ እነዚህን ፡

መድኀኒቶች ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የሚሠራ ፡ የሚለዋውጥ ፡ የሚሸጥ ፡ የሚያድል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

(፪) ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፭፻፲፪ ። ለከብት ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ድርቆሽና ፡ ሌላም ፡ ምግብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ ማበላሸትና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ —

(ሀ) ድርቆሽን ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ምግቦችን ፡ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ በቤት ፡ እንስሳዎች ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ ዐይነታቸው ፡ ጎጂ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እነዚህን ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጡ ፡ ድርቆሽንና ፡ ሌሎችንም ፡ ምግቦች ፡ ያመጣ ፡ ወይም ፡ ያስቀመጠ ፤ የሸጠ ፡ ወይም ፡ እንዲዘዋወር ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ያደረገው ፡ በቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፭፻፲፫ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።

አድራጊው ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ ሞያው ፡ አድርጎ ፡ የሠራ ፡ ሲሆንና ፡ የወንጀል ፤ ሥራዎቹ ፡ ብዛታቸው ፡ ከፍ ፡ ባሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ የደረሰውም ፡ ጉዳት ፡ ከባድ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ በከፍተኛ ፡ ግምት ፡ እስራቱ ፡ ይፈረዳል ። መቀጮውም ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺ ። ፭፻፲፩ና ፡ ፭፻፲፪ ።]

ቍ ፡ ፭፻፲፬ ። አልኮል ፡ ወይም ፡ እስፒርቶ ፡ ያለባቸውን ፡ መጠጦች ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

የመጠጦቹ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ብዛት ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑ ፡ እርግጠኛ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ ሊጎዳ ፡ የሚችለውን ፡ አልኮል ፡ ወይም ፡ እስፒርቶ ፡ ያለባቸውን ፡ መጠጦች ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ወይም ፡ ከልክ ፡ አሳልፎ ፡ የጠጣ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ለታወቀው ፡ ሰው ፡ ባለማሰብ ፡ ዐውቆ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ እንዲሰጥ ፡ በማድረግ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ያደረሰ ፡ ሰው ፤

አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ይህንኑ ፡ ጥፋት ፡ ደጋግሞ ፡ ሲሠራ ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ መከልከሉ ፡ ሳይቀር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፭ ። አእምሮን ፡ በሚነኩ ፡ ሥራዎች ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

በማስተኛት ፡ ሁኔታ ፡ በማንዘፍዘፍ ፡ በማደንዘዝ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ማበላሸት ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ችሎታን ፡ በማጥፋት ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ለሰው ፡ ባለማሰብ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ያደረገ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፲፬ ፡ የተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፮ ። ሥራይ ፡ በሚሆኑ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለማድረስ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ጠባያቸው ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለውን ፡ አደጋና ፡ ጉዳት ፡ እያወቀ ፡ ጤንነትን ፡ ሊጎዱ ፡ የሚችሉ ፡ ብናኝ ፡ ዱቄቶችን ፡ የሥራይ ፡ በሽታ ፡ የሚያመጡ ፡ ቅመሞችን ፤ መጠጦችን ፤ ወይም ፡ ሌሎችን ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ያሰናዳ ፡ የሰጠ ፡ የሸጠ ፡ ያከፋፈለ ፡ ወይም ፡ ያጠጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፲፬ ፡ በተመከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፯ ፡ ከባዶች ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ተከሳሹ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ከተጠቀሰው ፡ አድራጎት ፡ አንደኛውን ፡ እንደ ፡ ሞያ ፡ ሥራው ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ (ቍ ፡ ፭፻፲፭ና ፡ ፭፻፲፮) ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ መቀጮ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተጣምሮ ፡ ይወሰናል ።

(፪) ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ ተበዳዩ ፡ ሳይፈቅድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ ስለ ፡ መንካት ፡ የተወሰነ ፡ ድንጋጌ ፡ በተደራቢነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። ]ቍ ፡ ፭፻፶፭ ። ]

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የሕክምና ፡ ጠባይ ፡ ባላቸው ፡ የመጠበቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፤ ፭፻፲፰ ። የሕክምናንና ፡ የጤና ፡ አጠባበቅን ፡ ሥራ ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።**

(፩) የተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ችሎታ ፡ ሳይኖረውና ፡ በሚገባው ፡ ባለሥልጣን ፡ ሳይመረመር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ እንዲሠራ ፡ በግልጽ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በሽተኞችን ፡ በማከም ፡ ወይም ፡ መድኃኒቶችን ፡ በመሸጥ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የሕክምና ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውን ፡ ሥራዎች ፡ በመሥራት ፡ ገንዘብ ፡ የሚቀበል ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ —

በእስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ለከብት ፡ ሐኪሞች ፡ ወይም ፡ ከብትን ፡ የማከም ፡ ተግባር ፡ ለሚሠራ ፡ ይኸው ፡ ድንጋጌ ፡ ይጸናል ።

(፫) በችግር ፡ ምክንያት ፡ በድግነት ፡ አለዋጋ ፡ አንድ ፡ ምክር ፡ አንድ ፡ እርዳታ ፡ ወይም ፡ በሚያስቸኩል ፡ ሁኔታ ፡ በአጋጣሚ ፡ ወይም ፡ በአስፈላጊነት ፡ የሕክምና ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፤ እንዲሁም ፡ በነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ የተፈቀዱትንና ፡ አደገኛ ፡ ያልሆኑትን ፡ የተፈጥሮ ፡ ወይም ፡ የተለመዱትን ፡ መድኀኒቶች ፡ የሠራ ፡ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ በተደነገገው ፡ አይቀጣም ።

(፬) በወገኖቻቸው ፡ መካከል ፡ የዚህን ፡ ሥራ ፡ የቈየው ፡ ልማድ ፡ በሚያጸድቀው ፡ መጠን ፡ ዕውቀት ፡ ከሥራ ፡ ልምድ ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀላቸው ፡ ሰዎች ፡ በሀገሬው ፡ ዘዴ ፡ መድኀኒት ፡ ቢያደርጉ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚያግዳቸው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ወገኖቹ ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሕክምና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ወይም ፡ ጤንነት ፡ ወይም ፡ ሕይወትን ፡ የሚጎዳ ፡ ነገር ፡ እንዲሠራ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ አለመፈቀዱን ፡ ሲረዳው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፲፬ ። መርዛምና ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አላገባብ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ሐኪም ፡ መድኀኒት ፡ ቀማሚ ፡ የጥርስ ፡ ሐኪም ፡ ወይም ፡ የከብት ፡ ሐኪም ፤ አስታማሚ ፡ ወይም ፡ መርዛምና ፡ የሚያፈዙ ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ ለጤና ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ በሚያመጡ ፡ ነገሮች ፡ ሕክምና ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ እነዚህኑ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ የታፈቀደለት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የሕክምና ፡ ረገድ ፡ አከናወን ፡ ከሚፈቅዳቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭና ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ የሠራባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ፤ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። ይህን ፡ ያደረገው ፡ ጥቅም ፡ በማግኘት ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፭፻፲፭ ። የሕክምና ፡ እርዳታን ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

(፩) ሐኪም ፤ መድኀኒት ፡ ቀማሚ ፤ የጥርስ ፡ ሐኪም ፡ ወይም ፡ የከብት ፡ ሐኪም ፡ አዋላጅ ፡ ሴት ፡ አስታማሚ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሕክምና ፡ ለመስጠት ፡ ተግባሩ ፡ የሆነ ፡ በደንብ ፡ የታወቀ ፡ ሰው ፡ በተግባሩ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆንና ፡ ባልተገባ ፡ ምክንያት ፡ በእውነት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ አላደርግም ፡ በማለት ፡ በምን ቸገረኝ ፡ ራስን ፡ በመውደድ ፡ ወይም ፡ ሀብትን ፡ አለመጠን ፡ በመፈለግ ፡ በቂም ፡

በንቀት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ተመሳሳይ ፡ ምክንያት ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአሠራሩ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ የሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። ነገሩም ፡ በተደጋገመ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ባንድ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ወይም ፡ በሰውነቱ ፡ ወይም ፡ በጤናው ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ የሚደርስበት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ እርዳታ ፡ ማድረግን ፡ የተወ ፡ ሰው ፡ የሚቀጣበት ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፭፻፵፯ ፡ (፪) ።]

## ፭ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## በሌሎች ፡ ሰዎችና ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## በሰው ፡ ሕይወትና ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ የወንጀል ፡ ሥራዎች ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## በሕይወት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## መግደልና ፡ አደራረጉ ።

### ቍ ፡ ፭፻፳፩ ። መሠረቱ ።

(፩) በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አስቦ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ ነው ።

አስቦ ፡ ነፍስን ፡ በመግደል ፡ ጥፋተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አገዳደሉ ፡ ቀላል ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሚቀል ፡ ቢሆንም ፡ በቀላሉ ፡ ወይም ፡ በከባዱ ፡ ይቀጣል ።

አስቦ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ የገደለ ፡ ሁሉ ፡ ሕጋውያን ፡ በሆኑ ፡ የፍርድ ፡ መንገዶችና ፡ በውሳኔዎቻቸው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ የሚቀጣ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፭፻፳፪ ። ከባድ ፡ (የግፍ) ፡ አገዳደል ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ አገዳደል ።

(ሀ) አስቀድሞ ፡ በማሰብ ፤ ወይም ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ መሣሪያ ፡ እንዳገዳደሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ በጠቅላላ ፡ በሚያከብድ ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ባለው ፡ በተለይ ፡ ጨካኝ ፡ ነውረኛ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ መሆኑን ፡

የሚገልጽ ፡ ሲሆን ። [ቍ ፡ ፹፩ ። ፹፫ ።]

(ለ) ለመግደል ፡ ወይም ፡ ለመወንበድ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ግፍን ፡ ለመፈጸም ፡ ከተደራጀ ፡ ስብሰባ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ሌላ ፡ ወንጀልን ፡ ለመሥራት ፡ እንዲመቸው ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ እንዳይገለጽ ፡ ለማድረግ ፡ ሲሆን ፤

ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ ወንጀለኛ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ እንዲታሰር ፡ ከተፈረደ ፡ በኋላ ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመጨረሻ ፡ የተነገረው ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

<u>ቍ ፤ ፭፻፳፫ ። ተራ ፡ የሆነ ፡ አገዳደል ፤ ግዳይ ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፪ ፡ (፩) የተጻፉት ፡ የቅጣቶች ፡ ማክበድ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፬ ፡ የተጻፉት ፡ የቅጣት ፡ ማቅለል ፡ ምክንያቶች ፡ ሳይኖሩ ፡ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ወንጀለኛ ።

ካምስት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ ከሐያ ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፭፻፳፬ ። [

<u>ቍ ፡ ፭፻፳፬ ። የመግደልን ፤ ቅጣት ፤ ስለ ፤ ማቅለል ።</u>

ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ባልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ሳይሆን ፡ ወይም ፡ ያስፈላጊነት ፡ ግዴታ ፡ ሳይኖረው ፤ በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ባጥሩ ፡ ግቢ ፡ ባሉት ፡ ቤቶች ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ በተንኰል ፡ የገባውን ፡ ሰው ፡ ለማስወገድ ፡ ሲል ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ [ቍ ፡ ፸፩ና ፡ ፸፬ ።]

(ለ) ወይም በፍ ፡ ባለ ፡ ደም ፡ በሚያፈላ ፡ ምክንያት ወይም ፡ ሁኔታዎቹ ፡ በአሳምሮ ፡ ግምት ፡ ይህን ፡ ከመምራጥ ፡ የሚያደርሱ ፡ ሆነው ፡ ሲታዩና ፡ አሠራሩም ፡ በከፊል ፡ ይቅርታን ፡ የሚያሰጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በድንገት ፡ ወይም ፡ በስሜት ፡ ወይም ፡ ከብርቱ ፡ ዝንባሌ ፡ የተነሣ ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፤ ፭፻፳፭ ። ራሱን ፡ እንዲገድል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማገዝ ።</u>

(፩) ራስን ፡ ብቻ ፡ በመውደድ ፡ ወይም ፡ በወራዳነት ፡ መንፈስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ እንዲገድል ፡ የሚያነሣሣ ፡ ወይም ፡ የሚረዳ ፡ ሰው ፡—

ራስን ፡ የመግደሉ ፡ ተግባር ፡ ተሞክሮ ፡ ያልተከናወነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ። ራስን ፡ የመግደሉ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

BACK



(፪) ራሱን ፡ የገደለው ፡ ሰው ፡ ሙሉ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ እንዲያደርግ ፡ ያነ ማሣውና ፡ የረዳው ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፭፻፳፮ ። በቸልተኛነት ፡ ስለ ፡ መግደል ።

(፩) ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ቸልተኛነት ፡ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ሰው ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ወንጀለኛው ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ ወይም፡ ጤና ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈ ላጊ ፡ ጥንቃቄ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ አስተዋይነት ፡ እንዲያደርግ ፡ የሞያ ፡ ተግባሩ ፡ የሚያስገድደው ፡ ሲሆን ፡ ከባድ ፡ ቸልተኛነት ፡ በማድረግ ፡ ሰው ፡ የሞተበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፳፯ ። ሕፃንን ፡ ስለ ፡ መግደል ።

(፩) ለመውለድ ፡ ምጥ ፡ በተያዘች ፡ ጊዜና ፡ ወይም ፡ የምጥ ፡ ስሜት ፡ ሳያልፍ ፡ ሆነ ፡ ብላ ፡ ልጅዋን ፡ የገደለች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ ካምስት ፡ ዓመት ፡ በማይ በልጥ ፡ እስራት ፡ ትቀጣለች ።

በአገዳደሉ ፡ ተግባር ፡ ሙከራ ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ጉዳት ፡ ያልደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ በፈቃዱ ፡ ሊያቃልልላት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፹፩ ።]

(፪) ከነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ብላ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ልጅዋን ፡ የገደለች ፡ እናት ፡ መደበኛ ፡ በሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈረድባታል ።

(፫) ሕፃኑን ፡ ለገደሉት ፤ ወይም ፡ ለመግደሉ ፡ አባሪ ፡ ተባባሪዎች ፡ ወይም ፡ ግብረ ፡ አበሮች ፡ ለሆኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሕጉ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ አይደረግላቸ ውም ። እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታና ፡ እንደ ፡ ጥፋታቸው ፡ ስለ ፡ ነፍስ ፡ ገዳይና ፡ ስለ ፡ መግደል ፡ በተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይፈረድባቸዋል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

በፅንስ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ።

ስለ ፡ ማስወረድ ።

ቍ ፡ ፭፻፳፰ ። መሠረቱ ።

(፩) አስገዳጅ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ይህን ፡ ድንጋጌ ፡ የሚያፈርስ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ የርግዝና ፡ ደረጃ ፡ የሚገኘውን፡ ፅንስ ፡ በማናቸውም ፡

BACK



ዐይነት ፡ መሣሪያ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እንዳይጸና ፡ ያደረገ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፭፻፴፬ ። ]

ሆነ ፡ ተብሎ ፡ የሚደረግ ፡ የማስወረድ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በእናቲቱ ፡ ወይም ፡ በሦስተኛው ፡ ወገን ፡ መሆኑን ፡ በማስተያየትና ፤ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እናቲቱ ፡ ፈቅዳ ፡ ወይም ፡ ሳትፈቅድ ፡ መሆኑን ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

በቸልተኝነት ፡ ወይም ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ የሚደርስ ፡ የፅንስ ፡ መቋረጥ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ አይደለም ።

(፪) የማስወረድን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ምቹ ፡ የሆኑትንና ፡ ፅንስ ፡ እንዳይደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ማስታወቅ ፡ ጕዳዩን ፡ በሚመለከተው ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ያስቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፴፩ ። እናት ፡ የፈጸመችው ፡ የማስወረድ ፡ ተግባር ።</u>

(፩) የማስወረድ ፡ ተግባርን ፡ የምትፈጽም ፡ እርጉዝ ፡ ሴት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስና ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ትቀጣለች ።

(፪) መሣሪያን ፡ የሚሰጣት ፡ ወይም ፡ ለማስወረጃ ፡ የሚረዳት ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ አባሪ ፡ ወይም ፡ ግብረ ፡ አበር ፡ በመሆን ፡ ስለ ፡ ተካፋይነት ፡ በተወሰኑት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ ካ፩ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፴፪ ። ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ የፈጸመው ፡ የማስወረድ ፡ ተግባር ።</u>

(፩) በፀነሰች ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ የማስወረድን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ወይም ፡ አስወራጅን ፡ የማስወረድ ፡ ተግባር ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ የረዳ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የተባለችው ፡ ሴት ፡ ለማስወረድ ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠት ፡ ያልቻለች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ፈቃዷ ፡ የተገኘው ፡ በዛቻ ፡ በማስገደድ ፡ በማታለል ፡ ወይም ፡ ሥራዎቹ ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ውጤቶች ፡ ለመለየት ፡ የማትችል ፡ በሆነችበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አድራጎቱ ፡ ያለፈቃድዋ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ይህ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፴፫ ። ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ በማድረግ ፡ ፅንስ ፡ ማስወረድን ፡ የማስፈጸም ፡ ተግባር ።</u>

(፩) ይህን ፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ በቍጥር ፡ ፺ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሀብትን ፡ በመፈለግ ፡ ወይም ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛው ፡ የማስወረድን ፡

ተግባር ፡ ሥራው ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተወሰነው ፡ የገንዘብ ፡ ቅጣት ፡ ሁልጊዜ ፡ ነጻነትን ፡ ከሚያሳጣው ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ የሚጣመር ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህን ፡ ጥፋት ፡ የፈጸመው ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ ያለ ፡ መጠን ፡ መመኪያ ፡ በማድረግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተለይም ፡ ሐኪም ፡ መድኀኒት ፡ ሻጭ ፡ ወይም ፡ የምታዋልድ ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ አስታማሚ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከሞያ ፡ ሥራው ፡ እንዲታገድ ፡ ይፈረድበታል ፤ ወይም ፡ የወንጀሉን ፡ ሥራ ፡ የደጋገመ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዘወትር ፡ በመታገድ ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፯፭፪ ።]

ይኸውም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተወሰነው ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ማከበጃ ፡ ውሳኔ ፡ ሳይነካ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፴፪ ። እርግዝና ፡ በሌላት ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ የማስወረድን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ።

ባንዲት ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ እርግዝና ፡ ሳይኖራት ፡ እርጉዝ ፡ ናት ፡ በማለት ፡ የማስወረድ ፡ ሥራ ፡ ሙከራ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊደረግ ፡ ስለማይቻል ፡ ወንጀል ፡ የተደነገጉ ፡ የጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ፡ ደንቦች ፡ ይፈጸማሉ ። [ቍ ፡ ፭፱ ።]

ቍ ፡ ፭፻፴፫ ። ቅጣትን ፡ ስለሚያቀሉ ፡ ሁኔታዎች ።

ቅጣትን ፡ ለማቅለል ፡ ከሚፈቅዱት ፡ ተራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ ፅንሱ ፡ ግዙፍ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ከባድ ፡ የሕሊና ፡ ችግር ፡ በተለይም ፡ በመደፈር ፡ ወይም ፡ ከቅርብ ፡ ዘመድ ፡ በተደረገ ፡ የሥጋ ፡ ግብር ፡ ግንኙነት ፡ ወይም ፡ ጥልቅና ፡ የሚቈይ ፡ በሆነ ፡ የኑሮ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ የተቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህንን ፡ ቅጣት ፡ በነጻ ፡ ለማቃለል ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፸፱ ። ፯፻፳፭ ።]

ቍ ፡ ፭፻፴፬ ። በሕክምና ፡ ፅንስን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ።

(፩) ፅንስን ፡ የማቋረጥ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ ለሴቲቱ ፡ ሕይወት ፡ ከሚያሠጋውና ፡ በጤናዋ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስባት ፡ ለማድረግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ በኩልም ፡ ለማዳን ፡ የማይቻል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የተሠራ ፡ ከሆነ ፡ አያስቀጣም ።

(፪) የማይቻል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የፀነሰችው ፡ ሴት ፡ ጤና ፡ ከተመረመረ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠራ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሐኪም ፡ ያወቀውና ፡ በጽሑፍ ፡ የመሰከረለት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) ፅንሱን ፡ ለማቋረጥ ፡ የሚቻለው ፡—

(ሀ) ካረገዘችው ፡ ሴት ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ በመባሉና ፡ በጠቅላላውም ፡ ወይም ፡ በያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊውን ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጥ ፡ በደንበኛው ፡ ባለሥልጣን ፡ የተፈቀደለት ፡ ሌላ ፡ ሐኪም ፡ አስፈላጊ ፡

ሲሆን ፡ ለምርመራ ፡ ሴቲቱን ፡ ካዬየ ፡ በኋላ ፡ ባገኘውና ፡ በሚሰጠው ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ባረገዘችው ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሰውነትዋ ፡ ወይም ፡ በአእምሮዋ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ በሆኑ ፡ ዘመዶችዋ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ ወኪል ፡ ፈቃደኛነትዋ ፡ በሚገባ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ፡፡

(፪) ፅንሱን ፡ የማቋረጡን ፡ ተግባር ፡ የሚያደርገው ፡ ሐኪም ፡ የሞያ ፡ ሥራዬ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ እነዚህን ፡ ሁኔታዎች ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ፡፡ የሥራውንም ፡ አፈጻጸም ፡ ሕጋውያን ፡ ከሆኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ማስወረድ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙበታል ፡፡ [ቍ ፡ ፭፭ ፡፡]

<u>ቍ ፡ ፭፻፴፭</u> ፡፡ ያለ ፡ ደንብ ፡ የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መቅጣት ፡፡

(፩) እርግዝናው ፡ እንዲቋረጥ ፡ ያረጋገጠና ፡ የፈቀደ ፡ ሐኪም ፡ ስላደረጋቸው ፡ ምርመራዎችና ፡ ውሳኔ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ለሆነው ፡ ባለሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ ሁለት ፡ ኮፒ ፡ ማኖር ፡ አለበት ፡፡ የእርግዝናውን ፡ ማቋረጥ ፡ ተግባር ፡ ያደረገው ፡ ሐኪም ፡ ሳይዘገይ ፡ ለዚሁ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ፡፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ሲገጥመው ፡ ሐኪሙ ፡ የሞያ ፡ ሥራን ፡ ምስጢር ፡ መከላከያ ፡ አድርጎ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ፡፡ [ቍ ፡ ፩፻፯ ፡፡]

(፪) እነዚህ ፡ አስገዳጅ ፡ የሆኑት ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ የአመራር ፡ ደንቦች ፡ ያልተፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚሁ ፡ የተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ፡፡ [ቍ፯፻፯ ፡፡]

ጥፋቱ ፡ በመደጋገም ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛው ፡ ሐኪም ፡ ለጊዜው ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ ከመሥራት ፡ ሊታገድ ፡ ይቻላል ፡፡ [ቍ ፡ ፪፭፪ ፡፡]

<u>ቍ ፡ ፭፻፴፮</u> ፡፡ ስለሚያስቸኩል ፡ ሁኔታ ፡፡

(፩) በፍጥነት ፡ በሚደረግ ፡ በሕክምና ፡ ሥራ ፡ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊወገድ ፡ የማይቻል ፡ ከባድና ፡ የተቃረበ ፡ አደጋ ፡ በሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ፡፡ [ቍ ፡ ፭፩ ፡፡]

(፪) የሴቲቱን ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ ለመፍቀድ ፡ የማትችል ፡ ሲሆን ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶቿን ፡ ወይም ፡ የሕጋዊውን ፡ እንደራሴዋን ፡ ፈቃድ ፡ አስቀድሞ ፡ ማግኘትና ፡ ለሚገባው ፡ ባለሥልጣን ፡ ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ ሳይደረግ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸማሉ ፡፡

BACK

## ምዕራፍ ፩ ።

## በሰው ፡ አካልና ፡ በሰው ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

### ቍ ፡ ፭፻፴፯ ። መሠረቱ ።

(፩) አስቦ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ አካል ፡ የጎዳ ፡ ወይም ፡ ጤናውን ፡ ያወከ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ማንኛዎችንም ፡ በሰውነት ፡ ላይ ፡ የሚደርሱትን ፡ የኀይል ፡ ሥራዎችን ፤ መምታትን ፤ ማቍሰልን ፤ የአካል ፡ ማጕደልን ፤ ጕዳቶችን ፡ ወይም ፡ አደጋዎችን ፡ እንዲሁም ፡ በሰው ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ አእምሮ ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ጕዳት ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። ይኸውም ፡ የጥፋቶቹ ፡ ምክንያቶች ፡ ውጤትና ፡ አጥፊው ፡ ያደረገው ፡ የጕዳት ፡ ሥራ ፡ ግንኙነት ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፳፬ ። ]

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለተበደለው ፡ ካሣውን ፡ የሚቈርጠው ፡ በዚሁ ፡ ነገር ፡ የተጻፈውን ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ፡ በመከተል ፡ የጕዳቱን ፡ ከባድነትና ፡ የነገረተኞቹን ፡ ሁኔታ ፡ ተመልክቶ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፺ ። ]

### ቍ ፡ ፭፻፴፰ ። አስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ ጕዳት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ —

(ሀ) ለተጎጂው ፡ ሕይወት ፡ በሚያሠጋ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በሰውነቱም ፡ ሆነ ፡ በአእምሮው ፡ ላይ ፡ ለዘወትር ፡ ጠንቅ ፡ በሚያተርፍ ፡ ዐይነት ፡ ሰውን ፡ ያቈሰለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አካላቱን ፡ ያጐደለ ፤ ከሕዋሳቶቹ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ ብልቶቹ ፡ አንዱን ፡ ያጐደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለሥራቸው ፡ እንዳያገለግሉ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሚያስቅቅ ፡ ዐይነት ፡ መልኩን ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ነዋሪ ፡ የሆኑትን ፡ ሕመምተኛነትን ፡ በሽተኛነትን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፭፻፴፱ ። አስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ቀላል ፡ የአካል ፡ ጕዳት ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፴፰ ፡ በተጻፈው ፡ ከሚያስቀጡት ፡ በቀር ፡ በሰው ፡ አካልና ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ጕዳት ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፤

BACK



የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ውጤቱ ፡ ከባድ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ እስ ራት ፡ ለመሆን ፡ የሚችለውና ፡ ክሱም ፡ በደንበኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚቀርበው ፡—

(ሀ) አድራጊው ፡ በመርዝ ፡ በማናቸውም ፡ መሣሪያ ፡ ቢሆን ፡ የተሠሩት ፡ ለማ ቍሰል ፡ ወይም ፡ ለመግደል ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ በተፈጥሮዋቸው ፡ ወይም ፡ በሚሠራባቸው ፡ አገልግሎት ፡ አደገኛ ፡ በሆኑና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ በሚችሉ ፡ መሣሪያ ዎች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በተለይ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ የሞያውን ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ተግባር ፡ በመጣስ ፡ የሰውነትን ፡ ጉድለት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ተጎ ጂው ፡ ደካማ ፡ በሽተኛ ፡ ሕመምተኛ ፡ ወይም ፡ ለመከላከል ፡ የማይችል ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፵ ። ከአድራጊው ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ የጥፋት ፡ ውጤት ።

(፩) አድራጊው ፡ ቀላል ፡ ጉዳት ፡ ለመፈጸም ፡ አስቦ ፡ ሳለ ፤ ከባዶች ፡ ጉዳቶች ፡ የፈ ጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከባዶች ፡ ውጤቶችን ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ችሎታ ፡ የነበረው ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደ ርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፵፩ ። የሚያጠራጥሩ ፡ ሁኔታዎች ፤ ያዋቂ ፡ ምርመራ ።

በተፈጥሮዋቸው ፡ በሚያስከትሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ በከባድነታቸው ፡ የሚያጠ ራጥሩ ፡ ሲሆን ፡ ውሳኔውን ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መግለጫዎች ፡ ለማግ ኘት ፡ ሕጋዊ ፡ የሕክምና ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄ ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፭፻፵፪ ። ቅጣትን ፡ ስለሚያቀሉ ፡ ሁኔታዎች ።

ማንም ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡—

(ሀ) መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ በተንኰል ፡ በመደፈሩ ፡ ሲከላከል ፤

(ለ) ጉዳቱ ፡ የተደረገው ፡ በመቀስቀስ ፡ በድንጋጤ ፡ ወይም ፡ በመፍራት ፡ — ወይም ፡ በዝንባሌ ፡ ሲሆንና ፡ የነገሩም ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስደርግ ፡ መስሎ ፡ ሲታ ይና ፡ በከፊልም ፡ ይቅርታን ፡ የሚያሰጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ።

(ሐ) የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ወይም ፡ ጉዳቱ ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ (ሞራል) ፡ የሚነካ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ተጎጂው ፡ የጉዳዩን ፡ ውጤት ፡ ለመ

ገመት ፡ ችሎታ ፡ ያለውና ፡ ወይም ፡ የተጎዳው ፡ ሰው ፡ ፈቅዶ ፡ እንዲደረግ ፡ የጠየቀ ፡ ሲሆን ፤

በሌላው ፡ አካል ፡ ወይም ፡ በጤናው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በ(ሐ) እንደ ፡ ተመለከተው ፤ ተጎጂው ፡ በዕድሜ ፡ ወይም ፡ በሁኔታው ፡ ምክንያት ፡ ጥያቄው ፡ ወይም ፡ እሺታው ፡ የሚያስከትለውን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ለመረዳት ፡ ያልቻለ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ በጥፋተኛው ፡ ላይ ፡ የሚፈረደው ፡ ነጻነትን ፡ የመወሰን ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፭፻፵፫ ። በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሱ ፡ የአካል ፡ ጉዳቶች ።

(፩) ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ቸልተኝነት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሰውነት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ ሰው ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ከባድነትና ፡ የጥፋተኛውንም ፡ በደለኛነት ፡ በማመዛዘን ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በሌላ ፡ ሰው ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ በመቻሉና ፡ አድራጊው ፡ የመጠንቀቅ ፡ የመጠበቅ ፡ ወይም ፡ የተለየ ፡ የማስተዋል ፡ ግዴታ ፡ ሲኖርበት ፡ የሞያውን ፡ ሥራ ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ጉዳቱን ፡ ያደረሰው ፡ በከባድ ፡ ቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የማያንስ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

(፫) ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ ጉዳቱ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተጎጂው ፡ በኩል ፡ ነው ። ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፭፻፵፬ ። የእጅ ፡ እልፊት ።

(፩) በሰውነት ፡ ላይ ፡ እርግጠኛ ፡ ጉዳትን ፡ ሳያደርስ ፡ ወይም ፡ ጤንነትን ፡ ሳይነካ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ወይም ፡ የመጋፋት ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፤ የከስ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ ሲሆን ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቀላል ፡ የሆኑ ፡ ሰንበሮች ፡ የደም ፡ መቋጠር ፡ ምልክቶች ፡ ወይም ፡ በቶሎ ፡ የሚያልፉ ፡ ሥቃዮች ፡ የአካል ፡ ጉድለት ፡ የጤና ፡ ጉዳት ፡ ተብለው ፡ ስለማይጠሩ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ መሠረት ፡ ያስቀጣሉ ። [ቍ ፡ ፯፻፺፩ ። ]

(፫) ተበዳዩ ፡ የደረሰበትን ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ተግባር ፡ በእጅ ፡ እልፊት ፡ የመለሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ መላሹን ፡ ቢያስፈልግም ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ቅጣት ፡ በመወሰን ፡ ፋንታ ፡ በመገሠጽ ፡ ወይም ፡ በማስጠንቀቅ ፡ ሊያልፋቸው ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በሰው ፡ ሕይወት ፤ በሰው ፡ አካል ፤ በሰው ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ በማድረስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ቍ ፡ ፭፻፴፭ ። የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ለአደጋ ፡ ማጋለጥ ።

(፩) አስቦ ፡ ያለ ፡ ይሉኝታ ፡ ሰውን ፡ በሚያሠጋ ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ያጋለጠ ፤ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፭፻፴፮ ። ሰውን ፡ በአደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማጋለጥና ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በጤናው ፤ በዕድሜው ፤ በሁኔታው ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ በጠባቂነትም ፡ ሆነ ፡ በአላፊነት ፡ ለማኖር ፡ የተቀበለውን ፡ ራሱን ፡ ለመጠበቅ ፡ የማይችለውን ፡ ሰው ፡—

(ሀ) አስቦ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ለሕይወቱ ፡ ወይም ፡ ለጤናው ፡ አሥጊ ፡ ከሆነ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ያደረሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይኸን ፡ በመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ጥሎት ፡ የሄደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(፪) አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ መብቱ ፡ የሚወገድ ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፭፻፴፯ ። አንድ ፡ ሰው ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለመርዳት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፤ በሰውነቱ ፡ ወይም ፡ በጤንነቱ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሊደርስበት ፡ የተቃረበውን ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ አደጋ ፡ የማያመጣ ፡ ሲሆን ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ሊረዳ ፡ ሲችል ፡ ዐውቆ ፡ ሳይረዳ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እስራቱ ፡ ከገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ጋራ ፡ የሚጨመረውና ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ የማያንስና ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) አድራጊው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታና ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ ራሱ ፡ ያቈሰለው ፡ ሲሆን ፤

(ለ) አድራጊው ፡ በሕክምና ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አድራጎት ፡ በሚሆን ፡ ሥራ ፡

ለማገገ፤ ፡ ወይም ፡ ለመርዳት ፡ የሞያ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፴፰ ። ልጆችን ፡ ስለ ፡ መጉዳት ።

(፩) ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላውን ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ የሚጠብቅ ፡ ወይም ፡ በአላፊነት ፡ የሚያሳድግ ፡ ሰው ፡ የልጁን ፡ ሰውነት ፡ ወይም ፡ አእምሮውን ፡ ወይም ፡ የጤናውን ፡ እርምጃ ፡ እስከ ፡ ማበላሸት ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋ ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ያሠራ ፡ ልጁን ፡ ችላ ፡ ያለ ፡ የጎዳ ፡ ወይም ፡ የመታ ፡ ሰው ፤

አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ መብቱ ፡ የሚወገድ ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ሕጋዊና ፡ ልከኛ ፡ የሆነ ፡ የመቅጣት ፡ መብት ፡ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ አያስቀጣም ፡ ። [ቍ ፡ ፭፬ ።]

ቍ ፡ ፭፻፴፱ ። ስለ ፡ አምባጓሮ ።

(፩) ከሦስት ፡ በማያንሱ ፡ ሰዎች ፡ አምባጓሮ ፡ ወይም ፡ ጠብ ፡ በሰውነት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በጤንነት ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ ወይም ፡ ሞትን ፡ በሚያስከትል ፡ አምባጓሮ ፡ ወይም ፡ ጠብ ፡ አስቦ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

እንዲህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ የተነሣውን ፡ ጠብ ፡ ለመመለስ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ በመከላከል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጠበኞችን ፡ በመገላገል ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይቀጣም ።

(፪) ሰውን ፡ ለማቍሰል ፡ ወይም ፡ ለመግደል ፡ የተሠራውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ የጠብ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በማያንስና ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ከሁኔታው ፡ የተነሣ ፡ አምባጓሮው ፡ ከባድ ፡ ውጤት ፡ ያስከተለ ፡ ሲሆንና ፡ በተለይም ፡ አምባጓሮ ፡ ባነሡት ፡ ጠበኞች ፡ መካከል ፡ በነበረው ፡ ቂም ፡ ወይም ፡ የጠብ ፡ ማጫር ፡ ወይም ፡ ስካር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ድንጋይ ፡ ወይም ፡ የሚገድል ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ እንዳላቸው ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ሲታወቅ ፡ በአምባጓሮው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የቈሰለ ፡ ወይም ፡ የተገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ቅጣቶች ፡ በደንበኛው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ተብሎ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላሉ ።

(፬) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳትን ፡ ወይም ፡ ሞትን ፡ ያደረሱ ፡ ሰዎች ፡ ሊታወቁ ፡

የተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኞች ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ወንጀልን ፡ ስለ ፡ ማጣመር ፤ የተደነገጉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ። [ቍ ፡ ፷፫ ።]

## ቍ ፡ ፭፻፵ ። የይዋጣልን ፡ ፉክክር ።

(፩) የተፎካካሪዎችን ፡ ሕይወት ፤ ጤና ፤ ወይም ፡ አካል ፡ ከአደጋ ፡ ላይ ፡ ለመጣል ፡ በሚችል ፡ አኳኋን ፡ በሁለት ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ አስቀድሞ ፡ የተወሰነ ፡ የይዋጣልን ፡ ፉክክር ፡ ለመዋጋት ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቢቈስሉም ፡ ባይቈስሉም ፡ ቅጣቱ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) የሞት ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባሮች ፡ ተደርገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ የማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ የማይበልጥ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይፈርዳል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የይዋጣልን ፡ ፉክክር ፡ ከተወዳዳሪዎቹ ፡ አንዳቸው ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ይቀጥላል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ሞትም ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ነጻነትን ፡ የመቀነሱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

(፫) ተወዳዳሪው ፡ ልዩዎች ፡ ደንቦችን ፡ ወይም ፡ የይዋጣልን ፡ ፉክክር ፡ ልዩ ፡ ደንቦችን ፡ ወይም ፡ ልማዶችን ፡ ዐውቆ ፡ የጣሰና ፡ በዚሁ ፡ ያላገባብ ፡ በተፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ተፎካካሪውን ፡ ያቈሰለ ፡ ወይም ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሰውን ፡ ስለ ፡ መግደልና ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መጉዳት ፡ በተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፭፻፵፩ ። የይዋጣልን ፡ ፉክክርን ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ፡ ስለ ፡ ማደፋፈር ፡ በፉክክርም ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ መገኘት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ይዋጣልን ፡ ብሎ ፡ ያነሣሣ ፤ ወይም ፡ የማነሣሣት ፡ ተግባር ፡ ያስተላለፈ ፡ ወይም ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ይህ ፡ ሰው ፡ የተባለውን ፡ ሥራ ፡ የደጋገመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚደርስ ፡ እስራት ፡ ሊፈርድ ፡ ይችላል ።

ከባላጋራዎቹ ፡ አንዱ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ የይዋጣልን ፡ ፉክክር ፡ ትግልን ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ እንዳይደረግ ፡ ያገደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተለይ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ ባላጋራዎች ፡ ከቅጣት ፡ ነጻ ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመበየን ፡ ይችላል ።

(፪) ማንም ፡ ሰው ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በማደፋፈር ፡ ንቀቱን ፡ በመግለጽ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ከሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡

የይዋጣልን ፡ ፉክክር ፡ ትግል ፡ እንዲያደርግ ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፫) የይዋጣልኙን ፡ ትክክለኛነት ፡ እንዲያረጋግጡና ፡ ግጥሚያውም ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶችን ፡ እንዲያሻሽሉ ፡ ለመጠባበቅ ፤ የይዋጣልን ፡ ፉክክር ፡ በሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ ምስክሮች ፡ ነባሪዎች ፡ የፉክክር ፡ እማኞች ፡ ረዳቶች ፡ ወይም ፡ ሐኪሞች ፡ ይዋጣልን ፡ የተባባሉ ፡ ባላጋራዎች ፡ እንዲደባደቡ ፡ ያላበረታቱ ፡ ወይም ፡ ያላነሣሡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገሩት ፡ ቅጣቶች ፡ አይቀጡም ።

ስለ ፡ አባሪነት ፡ የተደነገጉትም ፡ ውሳኔዎች ፡ አይፈጸሙባቸውም ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## በሰው ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በሰው ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ቍ ፡ ፭፻፹፱ ። ስለ ፡ ዛቻ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ድንጋጤንና ፡ ሽብርን ፡ (ፍርሀትን) ፡ በሚያደርስበት ፡ ሁኔታ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የዛተበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በተበዳዩ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ዛቻው ፡ እርግጠኛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ መወሰኑ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፤ ለወደፊቱ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ በመስጠት ፡ የእጅ ጠብቅ ፡ ዋስ ፡ እንዲሰጥ ፡ የማድረግ ፡ ደንብ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ሊያግደው ፤ አይችልም ። [ቍ ፡ ፯፻፵፰ ። ]

ቍ ፡ ፭፻፺ ። የመክሰስ ፡ ወይም ፡ የማዋረድ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ዛቻ ።

ማንም ፡ ሰው ፤ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የሰውዬውን ፡ ክብርና ፡ መልካም ፡ ስሙን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ እገልጽብሃለሁ ፡ በማለት ፡ ተበዳዩን ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ በዛቻ ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ እንዲገባ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ የሞከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በተበዳዩ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢነት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፶፪ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፭፻፶፯ ። ስለ ፡ ማስገደድ ።

ማንም ፡ ሰው ፤ በኀይል ፡ ሥራ ፡ በመገልገል ፡ ወይም ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ የሚገመት ፡ አደጋ ፡ ለማድረስ ፤ በመዛት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ በቅርብ ፡ የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ግንኙነት ፡ የተሳሰረ ፡ ወገኑ ፡ በማናቸውም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በተፈጥሮ ፡ ነጻነቱ ፡ እንዳይሠራበት ፡ በማሰናከል ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ እንዲደረግ ፡ እንዲፈቅድ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ተግባር ፡ ሲደረግ ፡ እንዳይከለክል ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ ተግባር ፡ መፈጸምን ፡ እንዲተው ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥፋት ፡ ከዚህ ፡ የበለጠውን ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ በሚወስኑት ፡ ከባድ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ ሳይመለከት ፡ የቀረ ፡ ሲሆን ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፭፻፶፰ ። የማሰብን ፡ ችሎታ ፡ ስለ ፡ ማሳጣት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፤ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ያለፈቃዱ ፡ በምትሐት ፡ በማፍዘዝ ፡ (በማደንገዝ) ፡ ሆነ ፡ አልኮል ፡ ወይም ፡ የሚያፈዝ ፡ መድኀኒት ፡ (ቅመም) ፡ በመስጠት ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ አፍዝዞ ፡ በሙሉ ፡ ሕሊናው ፡ ማሰብ ፡ እንዲሳነው ፡ በትክክለኛ ፡ አእምሮው ፡ የፈለገውን ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ ማድረግ ፡ (መወሰን) ፡ ወይም ፡ ሰብአዊ ፡ ተግባሩን ፡ መፈጸም ፡ እንዲያቅተው ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በተበዳዩ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢነት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አስፈላጊም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፲፯ ፡ ከተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ጋር ፡ ተጣምሮ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፭፻፶፱ ። የተቀላቀሉ ፡ ወንጀሎች ።

በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ የማድረግን ፡ ችሎታ ፡ የማሳጣቱ ፡ ተግባር ፡ የዛቻው ፤ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የማስገደድ ፡ ተግባር ፡ የተደረገው ፡ አንድ ፡ የታወቀ ፡ ወንጀል ፡ ለማስፈጸም ፡ በማሰብ ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህም ፡ አድራጎት ፡ ለወንጀሉ ፡ አንደኛው ፡ መሠረታዊ ፡ ጠባዩ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይኸውም ፡ ውንብድና ፡ ወይም ፡ ነጣቂነት ፡ ወይም ፡ አስፈራሪነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጕዳዩ ፡ የተወሰነው ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፭፻፶፯ ፡ ሰውን ፡ በግድ ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሕግን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ ሹም ፡ ሳያዘው ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በመያዝ ፡ በማሰር ፡ ወይም ፡ በእስረኛነት ፡ ስም ፡ ይዞ ፡ በማስቀመጥ ፡ ነጻነቱን ፡ ያሳጣው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አኳኋን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ የመሄድ ፡ የነጻነት ፡ መብቱን ፡ ያገደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚሆነው ፤ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ያሰረው ፤ ይዞ ፡ በግዴታ ፡ ያስቀመጠው ፡ ወይም ፡ ያስያዘውና ፡ ተገዶ ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያደረገው ፡ በሐሰት ፡ ሰውዬው ፡ አእምሮው ፡ ተበላሽቷል ፡ ወይም ፡ በአደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ ይዞ ፡ የማስቀመጡ ፡ ተግባር ፤ ከ፯ ፡ ቀን ፡ በልጦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ወኪል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለነርሱ ፡ የተሠራው ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈጸምባቸዋል ። [ቍ ፡ ፬፻፲፮ ።]

ቍ ፡ ፭፻፶፰ ። ስለ ፡ መጥለፍ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፤ በኀይል ፤ ወይም ፡ በዛቻ ፡ በተንኰል ፡ ወይም ፤ በማታለል ፤ ፈቃደኛ ፡ እንድትሆን ፡ በማድረግ ፡ እንዲ[illegible]ሴት ፡ ጠልፎ ፡ በኀይል ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ክሱና ፡ በጎ ፡ ለይታ ፡ ለማወቅ ፡ የምትችለው ፡ የተጠለፈችው ፡ ሴት ፡ ጠላፊውን ፡ ፈቅዳ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ ጋብቻ ፡ አግብታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጋብቻው ፡ የሚፈርስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፶፱ ። ክፉና ፡ በጎ ፡ ለይታ ፡ ለማወቅ ፡ የማትችልና ፡ የመከላከል ፡ ዐቅም ፡ የሌላትን ፡ ሴት ፡ ስለ ፡ መጥለፍ ።

ማንም ፡ ሰው ፤ ሴትዮዋ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፤ የምትገኝ ፡ መሆኗን ፡ እያወቀ ፤ ያበደች ፡ የአእምሮ ፡ ጕድለት ፡ ያለባት ፡ መንፈስ ፡ ደካማ ፡ የሆነች ፡ ሕሊናዋን ፡ የሚያውክና ፡ የሚያበላሽ ፡ ሕመም ፡ ያለባት ፤ ወይም ፡ ዐቅም ፡ የሌላትና ፡ ልትከላከል ፡ በማትችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ የምትገኝ ፡ ወይም ፡ የደረሰባትን ፡ አደጋ ፡ ለመመለስ ፡ የማትችል ፡ የሆነችዋን ፡ ሴት ፡ የጠለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፳፰ ። ሕፃንን ፡ ስለ ፡ መዝረፍ ፡ (ስለ ፡ መንጠቅ) ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሕፃን ፡ ለማስተዳደር ፡ ሰመጠበቅ ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ለመሰወር ፡ ሲል ፡ የዘረፈ ፤ የደበቀ ፤ ወይም ፡ በማይገባ ፡ ይዞ ፡ ያስቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱ ፡ ቢበዛ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ የሚሆነው ፡ አድራጊው ፡ ሕፃኑን ፡ በወሰደ ፡ በሠላሳ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ፡ ከመፈጸማቸው ፡ በፊት ፡ ለናት ፡ ለአባቱ ፡ ወይም ፡ ሕፃኑን ፡ ለመጠበቅ ፡ በአደራ ፡ ለተቀበሉ ፡ አሳዳጊዎች ፡ የመለሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቍ ፡ ፭፻፳፱ ። ቅጣቱን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) የማሰብን ፡ ችሎታ ፡ ማሳጣቱ ፤ ዛቻው ፤ ማስገደዱ ፡ በግድ ፡ ይዞ ፡ ማስቀመጡ ፡ ወይም ፡ ሕፃንን ፡ የመዝረፉ ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመው ፦

(ሀ) ተጎጂውን ፡ ለመድፈር ፡ ወይም ፡ እንዲደፈር ፡ ለማድረግ ፤ ለጊዜውም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ለግልሙትና ፡ ወይም ፡ ለአመንዝራነት ፡ ተግባር ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ በማቀድ ፤

(ለ) በተጎጂው ፡ ለመጠቀም ፡ ወይም ፡ ወጆ ፡ ለማግኘት ።

(ሐ) ወይም ፡ በተለይ ፡ በጭካ ማጉላላት ፡ ሲሆን ፤

ወንጀሉ ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ ቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወስናል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚፈርደው ፡ ቅጣት ፦

(ሀ) አድራጊው ፡ የዛቻ ፡ ወይም ፡ የማስገደድ ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ከ፭፻፶፪ እስከ ፡ ፭፻፶፬ ።]

(ለ) የማሰብ ፡ ችሎታን ፡ የማሳጣት ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ ይዞ ፡ የማስቀመጥ ፡ ሥራ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ * ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፤ የመጥለፍ ፡ ተግባር ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ‡ ጽኑ ፡ እስራት ፤ ዕውቀት ፡ የሌላትና ፡ ለመከላከል ፡ የማትችል ፡ ሴት ፡ የመጥለፍ ፡ ተግባር ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ** ጽኑ ፡ እስራት ፡ ነው ። [ቍ * ፭፻፶፭ ፡ ፭፻፶፮ ። ‡ ፭፻፶፰ ፡ ** ፭፻፶፱ ።]

ሕፃንን ፡ የመዝረፍ ፡ ተግባር ፡ ሲሆን ፡ ጽኑ ፡ እስራቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፭፻፳፰ ።]

BACK



## ቍ ፡ ፭፻፳፪ ። ሕፃኑን ፡ ስላለማቅረብ ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሕፃንን ፡ እንዲጠብቅ ፡ አደራ ፡ የተቀበለ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፤ በሕጉ ፡ መሠረትም ፡ ሆነ ፡ ለጊዜው ፡ ወይም ፡ የመጨረሻ ፡ ሆኖ ፡ በተሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ሕፃን ፡ እንዲወስድ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ድርጅት ፡ እንዲያቀርብለት ፡ ወይም ፡ እንዲያስረክበው ፡ ሲጠይቀው ፡ አላቀርብም ፡ በማለት ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል።

## ቍ ፡ ፭፻፳፫ ። ስለ ፡ ወላጆች ፡ የሚደረግ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ።

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሕፃን ፡ የዘረፈው ፡ የሰረቀው ፤ የደበቀው ፤ የሸሸገው ፡ ወይም ፡ ባለመብት ፡ ለሆነው ፡ ጠያቂ ፡ ከማቅረብ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነው ፡ ወላጅ ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ የጉዲፈቻ ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ እናቱ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ አያት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህንንም ፡ የፈጸመው ፡ ጠባቂነቱን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ የክብር ፡ ስሜት ፡ በመነሣሣት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፩፻ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ የተደረገው ፡ ተግባር ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ሕፃኑም ፡ የተሰረቀው ፡ ከሚያምንበት ፡ ሃይማኖትና ፡ ጥልቅ ፡ ለሆነው ፡ ስሜቱ ፡ ባዕድ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ አርቆ ፡ ለማኖር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክሱን ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚያቀርበው ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስራቱ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መደበኛ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፭፻፳፬ ። በፖለቲካ ፡ ምክንያት ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መስረቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በዛቻ ፡ በተንኰል ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ በማስገደድ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ሰርቆ ፡ ላንድ ፡ ባለሥልጣን ፤ ላንድ ፡ ማኅበር ፤ ላንድ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ የፖለቲካ ፡ ወገን ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ በሕይወቱ ፡ በመላ ፡ ሰውነቱ ፡ ወይም ፡ በነጻነቱ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስበት ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የወሰደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህንን ፡ ስርቆት ፡ ያዘዘና ፡ ያሰናዳ ፡ ወይም ፡ እያወቀ ፡ እርዳታውን ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

BACK



ቍ ፡ ፭፻፷፭ ። ሰውን ፡ በማይገባ ፡ አገልጋይ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ሌላውን ፡ ሰው ፡ በተገዥነት ፡ ስም ፡ አስገድዶ ፡ ይዞ ፡ የሸጠው ፤ በገንዘብ ፡ ያስተላለፈ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ ስም ፡ አሳልፎ ፡ ለሌላ ፡ የሰጠ ፤ በገንዘብ ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ የነገደበት ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ ያዘዋወረው ፡ ወይም ፡ በጉልበት ፡ በሚሰጠው ፡ ፍሬ ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በተሸፈነ ፡ አኳኋንም ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ የያዘውና ፡ ያቈየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ካ፭ ፡ እስከ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የዚሁም ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ በየብስም ፡ ሆነ ፡ በባሕርና ፡ በአየር ፤ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሰዎች ፡ አሳፍረው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ በወሰዱና ፡ ሆን ፡ ብለው ፡ የወንጀሉን ፡ አፈጻጸም ፡ በረዱ ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ ይጸናባቸዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፷፮ ። የጥበቃ ፡ ወይም ፡ የመቈጣጠር ፡ ጒድለት ።

የክፍል ፡ ሀገሩ ፡ ገዥ ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ከተማ ፤ ያንድ ፡ መንደር ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ነገድ ፤ አስተዳዳሪ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሹም ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ ወይም ፡ በሚያስተዳድረው ፡ ከተማ ፡ ወይም ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የጥበቃና ፡ የምርመራ ፡ ጒድለት ፡ በማድረጉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ የሰው ፡ መሸጥ ፡ ንግድ ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ የማስተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህንን ፡ የመቈጣጠርና ፡ የመጠበቅ ፡ ተግባሩን ፡ በቸልተኝነት ፡ ያሳለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተደነገገው ፡ ልዩ ፡ ለሆነው ፡ ከፍተኛ ፡ የቅጣት ፡ መደብ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፷፯ ። በሰዎች ፡ ለመነገድ ፡ የተቋቋሙ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ማኅበሮች ።

የሰውን ፡ ነጻነት ፡ መንካት ፡ የተደረገው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጻፉት ፡ ብንዱ ፡ አሠራር ፡ በዛቻ ፤ በተንኰል ፡ ወይም ፡ በማስገደድ ፡ ወይም ፡ በመፈንገል ፤ በመያዝ ፤ በግድ ፡ አጋልጋይ ፡ በማድረግ ፤ በመሸጥና ፡ በማዛወር ፡ የሰውን ፡ ነጻነት ፡ የነካ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ በሰዎች ፡ ለመነገድ ፡ ተቋቁመው ፡ በሚገኙ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ተባባሪዎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ድርጅቱ ፡ ፈርሶ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ይህም ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ አድራጊው ፡ ወይም ፡ አድራጊዎቹ ፡ በየራሳቸው ፡ በፈጸሙት ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ምክንያት ፡ በየራሳቸው ፡ የሚደርስባቸውን ፡ ቅጣት ፡ አያስቀረውም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በሌሎች ፡ የሰው ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

### ቍ ፡ ፭፻፷፰ ። የብሔራዊ ፡ መብቶችን ፡ ነጻ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

በዛቻ ፡ በኀይል ፡ በማታለል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ በሕግ ፡ በተከለከለ ፡ ዐይነት ፡—

(ሀ) በብሔራዊ ፡ መብቶች ፡ በተለይም ፡ በአባትነት ፡ ወይም ፡ በሞግዚትነት ፡ ወይም ፡ ለመከሰስና ፡ ለፍርድ ፡ በመቅረብ ፡ መብቶች ፡ እንዳይሠራባቸው ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ የከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የሕዝባዊንና ፡ የፖለቲካን ፡ ነጻ ፡ ተግባር ፡ የመንካት ፡ ወንጀሎች ፡ ይልቁንም ፡ ድምፅ ፡ የመስጠትንና ፡ የመምረጥን ፡ መብቶች ፡ የመንካት ፡ ወንጀሎች ፡ ተሠርተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተለይ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፬፻፷፩ ።]

### ቍ ፡ ፭፻፷፱ ። የነጻ ፡ መዘዋወርን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

(፩) የሹመት ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሌላውን ፡ እንዳይዘዋወር ፡ የከለከለ ፡ ሰው ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጊው ፡ በደንብ ፡ የተሾመ ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሥልጣን ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ በተወሰኑት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፬፻፲፬ ።]

### ቍ ፡ ፭፻፸ ። የሥራ ፡ ነጻነትን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

(፩) ለብቻው ፡ ወይም ፡ በመተባበር ፡ ተግባር ፡ በዛቻ ፡ በኀይል ፡ በማታለል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ በሕግ ፡ በተከለከለ ፡ አኳኋን ፡—

(ሀ) አንዱን ፡ ሰው ፡ ሥራን ፡ ወይም ፡ የተወሰኑ ፡ የሥራ ፡ ውለታዎችን ፡ እንዲቀበል ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ጠቅላላ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ እንዲቀበል ፡ ወይም ፡ እንዲለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ ሥራውን ፡ እንቢ ፡ እንዲል ፡ ወይም ፡ እንዲያቆም ፡ ያስገደደ ፡ ሰው ፤

(ለ) ግቡ ፡ እነዚህን ፡ የማስገደድ ፡ ተግባሮችን ፡ ለመፈጸም ፡ በቆመ ፡ ባንድ ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ ያደረገ ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ፈለገው ፡ መውጣትን ፡ የከለከለ ፡ ሰው ፤

BACK



የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ሁከት ፡ ያደረገው ፡ አጥፊ ፡ ወይም ፡ ያደረጉት ፡ አጥፊዎች ፡ የዛቻ ፡ ወይም ፡ የኀይል ፡ ተግባራቸውን ፡ ለመደገፍ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መሣሪያዎችን ፡ የያዙ ፡ ሲሆኑ ፡ ወይም ፡ መከልከሉ ፡ ወይም ፡ ማስገደዱ ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስብሰባ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጮና ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ ይጣመራሉ ።

ቍ ፡ ፭፻፹፩ ። መኖሪያ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ያለአግባብና ፡ ሕግን ፡ ተቃራኒ ፤ በመሆን ፤—

(ሀ) ባለመብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ እንዳይገባበት ፡ ሲከለክለው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የቤት ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ ለመኖሪያ ፡ ወደሚያገለግል ፡ ወደ ፡ ማናቸውም ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከቤት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ተያያዘ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ወይም ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የርሱም ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሰውም ፡ ባይኖርባቸው ፡ የሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ የማኅበር ፡ ቤትን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠውን ፡ የድርጅት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶችን ፤ ማከማቻ ፡ ስፍራዎችን ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ቦታዎችን ፡ የደፈረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ባለመብቱ ፡ ሳይቃወም ፡ ወይም ፡ ፈቅዶለት ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ በሕግ ፡ ከተጠበቀው ፡ ቦታ ውጣ ፡ ሲለውና ፡ ሲያስጠነቅቀው ፡ አልወጣም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የቤቱን ፡ መድፈር ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ እንዲህ ፡ ለማድረግ ፡ ሳይገባው ፤ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተደነገገውን ፡ አሠራርና ፡ ጥበቃ ፡ ሳይከተል ፤ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ የጸጥታ ፡ ጠባቂ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ልዩ ፤ የሆነው ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈጸምበታል ። [ቍ ፡ ፬፻፲፭።]

ቍ ፡ ፭፻፹፪ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።

የተጠበቁ ፡ ቦታዎች ፡ በተጣሱ ፡ ጊዜ ፤ ቅጣቱ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚሆነውና ፡ እስከ ፤ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፤—

(ሀ) ወንጀለኛው ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ከባድ ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ የኀይል ፤ ተግባር ፤ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የቤቱን ፡ መድፈር ፡ የፈጸሙት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፤ ወይም ፤ ስምምነት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ሐ) ይኸውም ፡ የተፈጸመው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ጸጥታ ፡ ጠባቂ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፭፻፸፱ ፡፡ ደብዳቤዎችንና ፡ የሚላኩ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥና ፡ ወደሌላ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ፡፡**

ማንም ፡ ሰው ፡—

(፩) በሕግ ፡ ሳይፈቀድለት ፡—

(ሀ) አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ወይም ፡ የተዘጋ ፡ መልክት ፤ ይኸውም ፡ የመጻጻፍ ፡ የቴሌ ግራም ፡ የጕዳይ ፡ ደብዳቤዎች ፤ ወይም ፡ የግል ፡ ግንኙነቶች ፤ ወይም ፡ እን ዲሁ ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፤ አንድ ፡ ኮሊ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የተላከ ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ የከፈተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የርሱ ፡ ያልሆነውን ፡ በስሕተትም ፡ ሆነ ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ ወይም ፡ በቸልተ ኝነት ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ወይም ፡ የተዘጋ ፡ ኮሊ ፡ በመክፈት ፡ አንዳንድ ፡ ነገ ሮችን ፡ ዐውቆ ፡ በከፋት ፡ አሳብ ፡ ሳይሆን ፡ እነዚሁን ፡ ነገሮች ፡ ያወጣ ፡ ወይም ፡ የተጠቀመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ፡፡

(፪) ይህ ፡ ሥራ ፡ የበለጠ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያስከትል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አስቦ ፡ በማ ድረግና ፡ ያለመብት ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ወይም ፡ መላካቸውን ፡ ከሚሄዱበት ፡ ያቋ ረጠ ፤ የያዘ ፡ ወይም ፡ ያዛወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ፡፡

(፫) የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ምስጢርን ፡ ባወጡ ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ወይም ፡ የሚላኩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በያዙዋቸው ፡ ወይም ፡ ከእ ጃቸው ፡ ባገቡዋቸው ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸሙባቸው ፡ ጥብቅ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ፡፡ [ቍ ፡ ፬፻፳፫ ፡ ፬፻፳፩ና ፡ ፬፻፳፪ ፡፡]

## አንቀጽ ፡ ፫ ፡፡

## በክብር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡፡

### ምዕራፍ ፡ ፩ ፡፡

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡፡

**ቍ ፡ ፭፻፹ ፡፡ መሠረቱ ፡፡**

(፩) የበዳዩ ፡ ወይም ፡ የተበዳዩ ፡ ማናቸውም ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ወይም ፡ ማዕርግ ፡

ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ባሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ባንዱ ፡ በክብርና ፡ በስም ፡ ወይም ፡ በመልካም ፡ ግምት ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የሚ ፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ የሚያስቀጡ ፡ ይሆናሉ ።

እነዚህም ፡ ወንጀሎች ፡ ሰዎችን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣ ቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችንና ፡ የተቋቋሙ ፡ ድርጅቶችን ፡ ሊነኩ ፡ ይችላሉ ።

ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ በሕይወት ፡ ያሉትንም ፡ ጠፉ ፡ የተባሉትንም ፡ ወይም ፡ የሞቱትንም ፡ ለመንካት ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ።

(፪) የበደሉን ፡ አነስተኛነት ፡ ወይም ፡ ከባድነት ፡ ጠባይ ፤ የተበደለውን ፡ ሰውና ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ሁኔታ ፡ በመገመት ፤ እንዲሁም ፡ የበደሉ ፡ ወሬ ፡ በሰፊ ፡ ወይም ፡ በአነስተኛ ፡ የተነዛ ፡ ወይም ፡ የተባዛ ፡ መሆኑን ፡ በማመዛዘን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀሎችን ፡ ቅጣት ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመበት ፡ ዐይነት ።

በቃል ፤ በድምፅ ፤ በጽሑፍ ፤ በሥዕል ፤ በንድፍ ፤ በምልክት ፤ በጥቅሻ ፤ ወይም ፡ በሰውነት ፡ አያያዝ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሌላ ፡ አደራረግ ፡ በሚሆን ፡ ተመሳሳይ ፡ ማሳየት ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ የሚደረግ ፡ ክብርን ፡ የመንካት ፡ ሥራ ፡ ያስቀጣል ።

በማናቸውም ፡ በማስመዝገብ ፤ በማብዛት ፡ በማስተላለፍ ፤ በማስታወቅ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፤ በማሳየት ፡ በመጻፍ ፤ በሚታይ ፡ ወይም ፡ በሚሰማ ፡ በማናቸውም ፡ አኳ ኋን ፡ በቀጥታ ፡ ሳይሆን ፡ የሚደረጉ ፡ በደሎች ፡ ወይም ፡ የነገር ፡ መንዛት ፡ በቀጥ ታና ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደ ፡ ተሠሩት ፡ በደሎች ፡ ሁነው ፡ ይቈጠራሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ሲሆን ፡ ስለሚሰጠው ፡ ቅጣት ።

(፩) ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ አንድ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፤ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተቋቋመ ፡ ድርጅት ፡ ሲሆን ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ መቀጮ ፡ ይጣልበታል ።

ቅጣቱም ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በፍርድ ፡ በያንዳንዱ ፡ ነገር ፡ በሚወሰን ፡ በማኅበሩ ፡ በመታገድ ፤ በመከልከል ፡ ወይም ፡ በመፍረስ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፻፵፯ ።]

(፪) የማኅበሩ ፡ ክፍሎች ፡ በኅብረት ፡ ሳይታወቁ ፡ ወይም ፡ ስማቸው ፡ ተለይቶ ፡ ሳይታወቅ ፤ የሰውን ፡ ክብር ፡ ነክተው ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ዝናውን ፡ አጥፍ ተው ፡ ከመገኘታቸው ፡ የተነሣ ፡ ባንድ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ የተፈረደው ፡ ቅጣት ፡ በበኩላቸው ። እንደዚሁ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ የበደል ፡ ተግባር ፡ በየራሳቸው ፡ የፈ

ጸሙ ፡ ለመሆናቸው ፡ የተረቱ ፡ የማኅበሩ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ አባ ሎች ፡ የሆኑት ፡ መሪዎች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ የግል ፡ ቅጣት ፡ እን ዳያገኛቸው ፡ አይከለክልም ።

ቍ ፡ ፭፻፸፯ ። የገንዘብ ፡ ካሣ ።

(፩) የበደሉን ፡ ከባድነትና ፡ መስፋፋት ፡ እንዲሁም ፡ የበዳዩንና ፡ የተበዳዩን ፡ ሁኔታ ፡ በመገመት ፤ በጠቅላላው ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተወሰኑት ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ላገኘው ፡ የሕሊና ፡ በደል ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚሰጠውን ፡ የገንዘብ ፡ ካሣ ፡ ይወስናል ። [ቍ ፡ ፻ ።]

(፪) የሕሊና ፡ በደል ፡ (የሞራል) ፡ ካሣ ፡ ሲታዘዝ ፡ ይልቁንም ፡ ፍርዱን ፡ ወይም ፡ ከፍርዱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ውሳኔውን ፡ በማስታወቂያ ፡ የማውጣት ፡ ጕዳይ ፡ ሲሆን ፤ ለያንዳንዱ ፡ ጕዳይ ፡ ጥበቃ ፡ አስፈላጊ ፡ በሚሆነው ፡ መጠንና ፡ በነዚህ ፡ በተነገሩት ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦች ፡ መንፈስ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ ይሰጣል ። [ቍ ፡ ፻፵፱ ።]

ይኸውም ፡ የሕሊና ፡ በደል ፡ ካሣ ፡ ሲነገር ፡ ክብርን ፡ ለመንካት ፡ ባገለገሉት ፡ አደራረጎች ፤ በተነገሩበት ፡ ልክና ፡ ክብርን ፡ የመንካት ፡ ሥራ ፡ በተፈጸመባቸው ፡ ወይም ፡ የክብሩ ፡ መነካት ፡ በተስፋፋባቸው ፡ በተለይም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ በማሳተም ፡ ማስታወቂያ ፡ በመለጠፍ ፡ ወይም ፡ በሲኒማ ፤ በራዲዮ ፤ በቴ ሌቢዚዮን ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ የወሬ ፡ መስፋፋት ፡ ዘዴዎች ፡ ክብር ፡ በተ ነካባቸው ፡ ቦታዎች ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፭፻፸፰ ። የማይደፈር ፡ መብት ።

በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተቋቋሙት ፡ የሕግ ፡ አውጭ ፤ የሕግ ፡ አስፈጻሚና ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደራሴዎች ፤ በተግባራቸው ፡ መሠረትና ፡ ደንበኛ ፡ ባላደራነታቸ ውን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፤ በአሠራራቸው ፡ (በፎርማቸው) ፡ ትክክለኛ ፡ ሆነው ፡ በሚሰጧቸው ፡ መግለጫዎች ፡ ወይም ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ንግግሮች ፡ ክብር ፡ ነክተ ዋል ፡ በማለት ፡ ሊከሰሱ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፭፻፸፱ ። የማያስቀጣ ፡ ግምት ፡ መስጠትና ፡ ንግግር ።

ክብር ፡ እንደ ፡ መንካት ፡ ሆነው ፡ የማያስቀጡት ፡—

(ሀ) በማይገባና ፡ ከመጠኑ ፡ ባለፈ ፡ ሁኔታ ፡ ሳይሆን ፡ በተሰጥዎ ፡ ወይም ፡ በች ሎታ ፡ ላይ ፡ የሞያ ፡ ወይም ፡ የማኅበር ፡ ሆነው ፡ በተሠሩት ፡ ወይም ፡ በወ ጡት ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ በሊቅነት ፡ ድርሰቶች ፡ በሳይንስ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ በምክንያት ፡ የሚደረጉ ፡ ነቀፌታዎች ፡ ሲሆኑ ፡—

(ለ) አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የጸጥታ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሹም ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ወኪል ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ምስ

BACK



ክር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የጋዜጣ ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በመን ግሥት ፡ የተፈቀደለትን ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፤ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለሚናገረው ፡ ለሚገልጠውና ፡ ግምት ፡ ለሚሰጥበት ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ የሰማ ውን ፡ ደግሞ ፡ ለሚናገረውና ፡ የሚናገራቸውም ፡ ነገሮች ፡ በሥራው ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ እርሱም ፡ ከዚሁ ፡ ሥራ ፡ ውጭ ፡ ሳይሆንና ፡ የተነገሩትም ፡ በግልጽ ፡ ክብርን ፡ ለማዋረድ ፡ ያልተደረጉ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የተለዩ ፡ ድንጋጌዎች ፤ ክብርን ፡ ስለ ፡ መንካት ።

### ቍ ፡ ፭፻፹፫ ። ስምን ፡ ስለ ፡ ማጥፋትና ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወንጀል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የሰውን ፡ ክብር ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ዝናውን ፡ የሚነካ ፡ ተግ ባሩን ፡ እገሌ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ሠርቷል ፤ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አድርጓል ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ላንድ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በማስታወቅ ፡ ስም ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በስም ፡ አጥፊነት ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ይህም ፡ ወንጀል ፡ ተደርጓል ፡ የሚባለው ፡ በሐሰት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አድርጓል ፡ በማለት ፤ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ በመክሰስ ፡ እንዲሁም ፡ የሐሰትን ፡ ወሬ ፡ በመንዛት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ደግሞ ፡ በደንብ ፡ በፍርድ ፡ ተቀጥቶ ፡ የፈጸመውን ፡ ወይም ፡ የተማረበትን ፡ ወንጀል ፡ ጠቅሶ ፡ ስም ፡ ያጠፋ ፡ ሰው ፤ ስለ ፡ ስም ፡ ማጥፋት ፡ በዚሁ ፡ በተደነገ ገው ፡ ውሳኔ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የሰውን ፡ ክብር ፡ ለመንካት ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ዝናውን ፡ ለማጥፋት ፡ የተነ ገሩት ፡ ወይም ፡ የተወሩት ፡ ነገሮች ፡ ሐሰት ፡ መሆናቸው ፡ እየታወቀ ፡ ተነግረው ፡ ወይም ፡ ወሬያቸው ፡ ተነዝቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጥፊው ፡ በስም ፡ ማጥፋት ፡ ወን ጀሉ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ሐሜቱ ፡ የዚህን ፡ የታማውን ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ ዝና ፡ ለማጥፋት ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ ተነግሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እስራቱ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ ይሆናል ።

(፫) ሰውን ፡ በሐሰት ፡ ወንጀል ፡ በፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ የከሰሰ ፡ ወይም ፡ ያስታወቀ ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተለይ ፡ በተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ የተመለከተ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ መደራረብ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የለ ውም ። [ቍ ፡ ፩፻፵፩ ።]

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፹፫ ። እውነትንና ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ጥቅሞች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የሚደረገው ፡ ልዩነት ።**

(፩) ስም ፡ በማጥፋት ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ ለመጉዳት ፡ ብዬ ፡ አልተናገርኩም ፡ ቢልም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ ያወራውን ፤ ባያምነውም ፡ እንኳ ፡ እርሱም ፡ በበኩሉ ፡ ያንኑ ፡ የሰማውን ፡ መልሶ ፡ በማውራት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ እንዲያው ፡ በጥርጣሬ ፡ ወይም ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ በማለት ፡ የተወራውን ፡ በመንዛት ፡ ብቻ ፡ የተሠራም ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለነገሩ ፡ ልዩነት ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ።

(፪) በስም ፡ አጥፊነት ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ የማይቀጣው ፡—

(ሀ) የሌላውን ፡ ሰው ፡ ክብር ፡ የሚነኩ ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ዝናውን ፡ የሚያጠፉ ፡ ናቸው ፡ በመባል ፡ የተገመቱት ፡ ወሬዎች ፡ እውነት ፡ ሆነው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ እነዚህን ፡ ወሬዎች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እውነት ፡ አድርጎ ፡ ለመያዝ ፡ ትክክለኛና ፡ በቂም ፡ ነገር ፡ የሚቈጠር ፡ ምክንያት ፡ ኖሮት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ተገቢ ፡ ለሆነ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ ጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ላንድ ፡ የሕሊና ፡ ወይም ፡ የተግባር ፡ ስሜት ፡ ሲል ፡ አድርጎት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

እውነትንና ፡ ቅን ፡ ልቡናን ፡ በሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ በተፈቀዱት ፡ በማንኛዎቹም ፡ ማስረጃዎች ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

(፫) አድራጊው ፡ በሐሰት ፡ የወነጀለ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ ከሆነ ፡ በሕግ ፡ በተፈቀደው ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ጥቅም ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ የሠራሁት ፡ የሚል ፡ አንዳች ፡ የአስረጂ ፡ ሁኔታ ፡ በማምጣት ፡ ከአጥፊነት ፡ ለማምለጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፬ ። የግል ፡ አኗኗርን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።**

በስም ፡ አጥፊነት ፡ ተከሳሽ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ የተናገራቸው ፡ የስም ፡ አጥፊነት ፡ ወሬዎች ፡ በተለይና ፡ ዐይነተኛ ፡ ዓላማ ፡ በማድረግ ፡ ግለኛ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ ሕይወት ፡ አኗኗር ፡ ተመልክተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ደግሞም ፡ በሕግ ፡ በተፈቀዱትና ፡ ብልጫ ፡ ያላቸውን ፡ ጥቅሞች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የተሠሩ ፡ ሳይሆን ፡ ከሁሉም ፡ አስቀድሞ ፡ የራስን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሐሜት ፡ ወይም ፡ ለመጉዳት ፡ ፍላጎት ፡ ወይም ፡ ለመበቀል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ስሜት ፡ መንፈስ ፡ በመመራት ፡ የተነገሩ ፡ ሲሆኑ ፤ ጥፋተኛው ፡ የተናገረው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለመሆኑ ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ እንዲያስረዳ ፡ አይፈቀድለትም ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፭ ። ስድብና ፡ ማዋረድ ።**

(፩) ተበዳዩን ፡ በቀጥታ ፡ በመናገር ፡ ወይም ፡ በአሽሙር ፡ የሰደበ ፡ ወይም ፡ ያዋ

BACK



ረዳ ፡ ለማዋረድ ፡ ምልክት ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ የቃጣ ፡ ወይም ፡ ያንገላታ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አደራረግ ፡ የተበዳዩን ፡ ክብር ፡ በመንካት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፤

በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሳይታይ ፤ አድራጎቱ ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ መቀጣቱ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሳይታይ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፫፻ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚ ችል ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፯፻፺፰ ። ]

ቍ ፡ ፭፻፹፬ ። ስለ ፡ ጠብ ፡ ማንሣትና ፡ ስለ ፡ ጠቡ ፡ መልስ ።

(፩) በመሳደብ ፡ ወይም ፡ በማዋረድ ፡ የተከሰሰውን ፡ ሰው ፤ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ አኳ ኋን ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ይቅርታ ፡ ሊያሰጡት ፡ የሚችሉ ፡ መስለው ፡ በሚ ታዩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሚደረጉ ፡ ለ፫ኛ ፡ ወገኖችም ፡ ቢሆን ፡ አስቀያሚ ፡ አና ዳጅ ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ ሊነቀፉ ፡ በሚገባቸው ፡ ሥራዎች ፡ ተቀስቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከማናቸውም ፡ ቅጣት ፡ ነጻ ፡ ሊያወጣው ፡ ይችላል ።

(፪) ተበደልኩ ፡ ባዩ ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ ለደረሰበት ፡ ስድብ ፡ ወይም ፡ ውርደት ፡ በዚያው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በተፈጸመው ፡ አደራረግ ፡ ዐይነት ፡ ወዲያ ውኑ ፡ መልሶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ በማመዛ ዘን ፡ ሁለቱንም ፡ ጥፋተኞች ፡ ወይም ፡ መላሹን ፡ በነጻ ፡ ለማሰናበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፭፻፹፭ ፡ ቃልን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) ክብርን ፡ በመንካት ፡ ተከሳሽ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ሙግቱ ፡ ባዳኛው ፡ ፊት ፡ በጽ ሑፍ ፡ ወይም ፡ በቃል ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ምስክሮቹ ፡ ነገሩን ፡ በሚ መሰክሩበት ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ ነው ፡ የተናገርሁት ፡ ሲል ፡ ጸጸቱን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ ለማቅለል ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺፹፩ ። ]

(፪) በሌሎች ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ ዳኛው ፤ ለተከሳሹ ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሚሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ አጥፊው ፡ አጠፋሁ ፡ ሲል ፡ ቃሉን ፡ ያስተባበለበትን ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ይሰጠዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፹፮ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) የስም ፡ ማጥፋት ፡ ወይም ፡ ብሐሰት ፡ የመወንጀል ፡ ወይም ፡ የማዋረድ ፡ ወይም ፡ የስድብ ፡ ሥራ ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ የተደረገው ፡ በአደራ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ አባል ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፤ ወይም ፡ የጸጥታ ፡ ጠባቂ ፡ ወይም ፡ ወታደር ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አድራጊው ፡—

(ሀ) የስድብ ፡ ወይም ፡ የማዋረድ ፡ ተግባር ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፭፻ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(ለ) የስም ፡ ማጥፋት ፡ ሲሆን ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(ሐ) በሐሰት ፡ የመወንጀል ፡ ተግባር ፡ ሲሆን ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ዝናን ፡ ለማዋረድ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የተሠራ ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) በነጋሚውና ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተቋቋሙትን ፡ የባለሥልጣኖች ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ መንካት ፡ በውጭ ፡ አገሮች ፡ መንግሥታትና ፡ በመንግሥቶች ፡ የታወቁትን ፡ ድርጅቶች ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ፤ የበላይን ፡ የወታደር ፡ ሹም ፡ ስለ ፡ መስደብ ፡ እንደዚሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ፡ የተደነገጉት ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፪፻፶፮ ። ፪፻፹፯ ። ፪፻፹፰ ። ፫፻፲ ። ፬፻፵፫ ።]

**ቍ ፡ ፭፻፹ ። መደበኛ ፡ የሆነ ፡ የክስ ፡ አቤቱታና ፡ ክስ ።**

ሰዳቢውና ፡ ወይም ፡ አዋራጁ ፡ ወይም ፡ አጥፊውና ፡ በሐሰት ፡ ወንጃዩ ፡ የሚከሰሰውና ፡ የሚቀጣው ፡ ተበዳዩ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ማኅበር ፤ ወይም ፡ ድርጅት ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርብበት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፩ ። ጠፍተው ፡ የቀሩትን ፡ ወይም ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ መንካት ።**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የሚያስቀጡት ፡ የክብር ፡ መንካት ፡ ተግባሮች ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ አለመኖሩ ፡ በታወቀ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የክስ ፡ አቤቱታን ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ ልጆቹ ፤ ባል ፡ ስለ ሚስቱ ፡ ሚስት ፡ ስለ ፡ ባሏ ፤ እነዚህም ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ ወላጆች ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡ ናቸው ።

(፪) ክብርን ፡ ስለ ፡ መንካት ፡ የክስ ፡ ማቅረቢያ ፡ ጊዜ ፡ ይርጋ ፡ በመደበኛው ፡ የይርጋ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራል ።

የሰውዬውን ፡ መታሰቢያ ፡ ክብር ፡ የሚነኩ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉት ፡ አድራጎቶች ፡ ሁሉ ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ የሕዝብ ፤ አስተዳዳሪነትን ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ታሪክን ፡ ወይም ፡ ኪነ ፡ ጥበብን ፡ ወይም ፡ ድርሰትን ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲሆን ፤ በነገሩ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ሰውዬው ፡ ከሞተ ፡ ወይም ፡ ጠፍቷል ፡ ከተባለ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ካለፈው ፡ የክሱን ፡ አቤቱታ ፡ መቀበል ፡ አይገባም ።

## አንቀጽ ፡ ፬ ።

## በመልካም ፡ ጠባይና ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በመልካም ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፱ ። የመድፈር ፡ ሥራ ።**

(፩) በኀይል ፡ ወይም ፡ በብርቱ ፡ ዛቻ ፡ ወይም ፡ ለመቃወም ፡ በማትችልበት ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ እንድትገኝ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ በጋብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የግብረ ፡ ሥጋን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ሴትን ፡ የሚያስገድድ ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ሥራው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተዘረዘሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ባልሞላት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ወይም ፡ በፊት ፡ በተከሳሹ ፡ ተጠባባቂነት ፡ በርሱ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ሆና ፡ በሆስፒታል ፡ በመጠሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመማጠኛ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ወይም ፡ በጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በግዞት ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ባለች ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተባባሪነት ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፺ ። በንጽሕና ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የኀይል ፡ ተግባር ።**

በኀይል ፡ ወይም ፡ በብርቱ ፡ ማስፈራራት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ አመጣጥ፤ለመቃወም ፡ ከማይቻልበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ከጣለው ፡ በኋላ ፡ ግብረ ፡ ሥጋን ፡ በመሰለ ፡ ወይም ፡ ለንጽሕና ፡ ክብር ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ጾታው ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ ለመገናኘት ፡ የሚያስገድድ ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፩ ። ለመቃወም ፡ በማይችሉ ፡ አእምሮዋቸው ፡ በተበላሸ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ደካማ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የድፍረት ፡ በደል ።**

(፩) የተበዳዩን ፡ ሁኔታ ፡ እያወቀ ፡ አእምሮውን ፡ ካጣ ፤ የአእምሮ ፡ ደካማ ፡ ከሆነ ፡ ከእብድ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ የሥራዎቹን ፡ መጠን ፡ ለይቶ ፤ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ ሥራዎቹን ፡ አስቦ ፡ ለመፈጸም ፡ ችሎታ ፡ ከሌለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በኀይል ፡ ሳያስገድድና ፡ ሳይዝት ፡ በመገናኘት ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ ግንኙነት ፡ ግብረ ፡ ሥጋን ፡ የመሰለ ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡—

እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከባድነት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ከተበደለው ፡ ሰው ፡ ስሕተት ፡ የተነሣ ፡ ተግባሩን ፡ የፈጸመው ፡ ለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፡ አድራጊው ፡ እነዚሁ ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፪ ። በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ በተኙ ፡ ሰዎች ፡ በተጋዙ ፡ ወይም ፡ በታሰሩ ፡ ሰዎች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ በደል ።**

በበዳዩ ፡ መሪነት ፤ በርሱ ፡ ተጠባባቂነት ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚተዳደር ፡ ሆኖ ፡ በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ከገባ ፡ ሰው ፤ በመጦሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመማጠኛ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ በሚሰጥበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በግዞት ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ አኗኗሩን ፡ የተሰጠውን ፡ ሹመቱን ፡ ወይም ፡ ሁኔታውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ የተገናኘ ፡ ሰው ፤

እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከባድነት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፫ ። ከፍ ፡ ያለውን ፡ የሴት ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ ተገዥነትዋን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚደረገው ፡ የማታለል ፡ ሥራ ።**

በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሳይሆን ፡ ባንዲት ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ኀዘን ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በርስዋ ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑ ፡ የሚሰጠውን ፡ አኗኗር ፤ ሹመቱን ፤ ጌታዋ ፡ መሆኑን ፤ አሳዳጊነቱን ፤ አስተማሪነቱን ፤ ወይም ፡ አሠሪነቱን ፡ ወይም ፤ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ አታሎ ፡ ከተባለችው ፡ ሴት ፡

ጋራ ፡ የግብረ ፡ ሥጋን ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡—

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፭፻፺፬ ። በሕፃናቶች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ በደል ።

(፩) ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ባልሞላት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ [ቍ ፡ ፭፻ ፺፪[ ፡ የግብረ ፡ ሥጋን ፡ ወይም ፡ ግብረ ፡ ሥጋን ፡ የመሰለ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ ግንኙነት ፡ ተግባር ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡—

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) በተባለው ፡ ዕድሜ ፡ ላይ ፡ በምትገኘው ፡ ልጅ ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ሌላ ፡ ተግባር ፡ የሚፈጽም ፡ የተባለችው ፡ ልጅ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ተግባር ፡ እንድትፈጽም ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ አስቦ ፡ በእርስዋ ፡ ፊት ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ተግባር ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡—

እንደ ፡ ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ምክንያቶች ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ተበዳይዋ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከተው ፡ አኗኗር ፡ የምትገኝ ፡ ሲሆን ፡ ቅጣቱ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) የጥፋተኛው ፡ ተማሪ ፤ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ተማሪ ፤ አዳሪ ፡ ተማሪ ፡ ወይም ፡ አሽከር ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ በተገዥነት ፡ በገረድነት ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ የበታችነት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ የሕግ ፡ ልጁ ፡ የእንጀራ ፡ ልጁ ፡ በሞግዚትነት ፡ ያሳደገው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ እንዲጠብቀው ፡ ወይም ፡ አስፈላጊውን ፡ እንዲያደርግለት ፡ በአደራ ፡ የተቀበለው ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፭፻፺፭ ። ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ባላቸው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ በደል ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ዕድሜው ፡ ካ፲፭ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ከሆነው ፡ ከራሱ ፡ ጾታ ፡ ልዩነት ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የሚመስል ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የበደለኛው ፡ የማደጎ ፡ ልጅ ፡ የሚስቱ ፡ ወይም ፡ የባሏ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በደለኛው ፡ የሚያሳድገው ፡ የሚያስተምረው ፡ ሥራ ፡ የሚያስለምደው ፡ በመጋቢነት ፡ በቤቱ ፡ የሚያኖረው ፡ ወይም ፡ አሽከሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጠባቂነት ፡ ወይም ፡ በአካሚነት ፡ በአደራ ፡ የተ

ቀበለው ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ በሱ ፡ ተገዥ ንት ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ ሥራ ፡ የሚገኝ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ እስራት ፡ ነው ።

(፪) በዚሁ ፡ ጥፋት ፡ የተከሰሰው ፡ በደለኛ ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ውን ፡ ሌላ ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጽም ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፯ ። ማሳት ።**

የዓለምን ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ አለማወቋን ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያላትን ፡ እምነት ፡ አይቶ ፡ ዕድሜዋ ፡ ከ፲፭ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ የሆነውን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረ ሰችውን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አገባሻለሁ ፡ የማለትን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ በመስጠት ፡ በተን ኰል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ብልሀት ፡ የግብረ ፡ ሥጋን ፡ ተግባር ፡ እንድትፈጽም ፡ ያደ ረገ ፡ ሰው ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፰ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ተታላይ ፡ የማይቀጣ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የግብረ ፡ ሥጋ ፡ በደሎች ፡ በሚፈጸሙባቸው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ተከሳሹ ፡ ባደረ ገው ፡ ሥራ ፡ የተታለለው ፡ ወይም ፡ የተበደለው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አይቀጣም ። ተስማሚ ፡ የሆኑት ፡ የመልካም ፡ አስተዳደግና ፡ የጥበቃ ፡ ውሳኔዎች ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሊፈጸሙበት ፡ ይችላሉ ።

(፪) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ሰው ፡ አደራረግ ፤ ይህን ፡ በደል ፡ እንዲሠራ ፡ ተከሳሹን ፡ አደፋፍሮት ፡ ወይም ፡ ቀስቃሽ ፡ ሆኖት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጉዳዩ ፡ ቅጣ ቱን ፡ የሚያቀል ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፷፱ ። (መ)]

**ቍ ፡ ፭፻፺፱ ። ከባዶች ፡ ሁኔታዎች ።**

ወንጀል ፡ ሆነው ፡ ለሚገኙት ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ተግባሮች ፡ ቅጣቱን ፡ የሚወስነው ፡ ድንጋጌ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ ካልወሰነ ፡ በቀር ፡ ከሦስት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ የሚያስቀጡት ፡—

(ሀ) ወንጀለኛው ፡ በኀይል ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በማስገደድ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዘዴ ፡ የዝሙት ፡ ተግባሩን ፡ የፈጸመበትን ፡ ሰው ፡ ለመከላከል ፡ በማይችልበት ፡ ሁናቴ ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የጭካኔ ፡ ወይም ፡ የከፋት ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፭፻፹፱ ፡ እስከ ፡ ፭፻፺፮ ።]

(ለ) አስረግዟት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሽታ ፡ የያዘው ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የሚተላለፈውን ፡ በሽታ ፡ ያስያዛት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ተግባሩ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ተበዳይ ፡ በኀዘን ፡ በኀፍረት ፡ ወይም ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ራሱን ፡ ለመግደል ፡ ያደረሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፺፱ ። በደሉ ፡ ጋብቻን ፡ ባስከተለ ፡ ጊዜ ፡ ክስ ፡ ቀሪ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

በማሳሳት ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ በደረሰባት ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፤ ወይም ፡ የሰው ፡ ተገዥ ፡ በመሆኗና ፡ የተደፈረችው ፡ ክብረ ፡ ንጽሕናዋ ፡ የተገሠሠው ፡ ሴት ፡ ጥፋተኛውን ፡ ወዳ ፡ በነጻ ፡ ያገባች ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ጋብቻው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ካልተባለ ፡ አንዳች ፡ ክስ ፡ አይቀርብበትም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ መበላሸት ።

**ቍ ፡ ፮፻ ። ለተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ፆታ ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ ግንኙነትን ፡ የመሰለ ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ በደል ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይኸው ፡ ልጅ ፡ አይቀጣም ፤ እርሱንም ፡ የሚመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈጸምበታል ። (ቍ ፡ ፭፻፺፯ ። )

**ቍ ፡ ፮፻፩ ። ቅጣቱን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲያጋጥሙ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ኀዘን ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በተባለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑ ፡ የሚሰጠውን ፡ የበላይነቱን ፡ ሹመቱን ፤ አለቅነቱን ፤ ያስተዳደግ ፡ ትምርህት ፡ ሰጪነቱን ፤ ወይም ፡ ሞግዚትነቱን ፡ ባለቤትነቱን ፤ አስተማሪነቱን ፤ ወይም ፡ አሠሪነቱን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሁኔታውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ተግባር ፡ እንዲሠራ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ እንዲሠራበት ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በሕጉ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ሞያ ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፺ ።]

(፪) ጽኑ ፡ እስራቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡ አድራጊው ፡—

(ሀ) የኀይል ፡ የዛቻ ፡ ወይም ፡ የማስገደድ ፡ ወይም ፡ የተንኰል ፡ ወይም ፡ የማታለል ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ተበዳዩ ፡ ለመቃወምና ፡ ለመከ

BACK



ላከል ፡ አለመቻሉን ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ደካማነቱን ፡ ሰውነቱን ፡ አለማወ ቁን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ሠርቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚያስቀይም ፡ የጭካኔ ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንዳለበት ፡ የሚያውቀውን ፡ የአባለ ፡ ዘር ፡ ደዌ ፡ ያጋባ በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ተግባሩን ፡ የፈጸመው ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ በሆነ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ተበዳዩ ፡ በዚሁ ፡ በደረሰበት ፡ ነገር ፡ በማዘን ፡ በማፈር ፡ ወይም ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ራሱን ፡ ለመግደል ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፮፻፪ ። ለተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የግብረ ፡ ሥጋን ፡ ተግባር ፡ በእንስሳ ፡ ላይ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፫ ። የተፈጥሮ ፡ ግብሩ ፡ መበላሸት ፡ ስለ ፡ መታወቁ ።

የነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አሠራር ፡ በበሽታ ፡ ምክንያት ፡ መሆናቸው ፡ በልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ሲረጋገጥ ፡ አላፊነትን ፡ ለመቀነስና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የሕክምና ፡ የጥበቃ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚያስከትሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፻፴፬ና ፡ ፻፴፰ ። ]

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በሌላ ፡ ሰው ፡ አመንዝራነት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

ቍ ፡ ፮፻፬ ። የሌላውን ፡ ሰው ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ፡ የዘወትር ፡ መጠቀሚያ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ በማቀድ ፡ ይህንን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ በአቃጣሪነት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ግልሙትና ፡ ወይም ፡ አመን ዝራነት ፡ ጥቅም ፡ ለመኖር ፡ ሰብስቦ ፡ በማከራየትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለያንዳንዳ ቸው ፡ አቃጣሪ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፰ ። ሴቶችንና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ በማቃጠር ፤ በማከራየት ፡ ስለ ፡ መነገድ ።**

(፩) ለጥቅም ፡ ሲል ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ሰውን ፡ ፍትወት ፡ ለማስፈጸም ፡—

(ሀ) በፈቃዳቸውም ፡ ቢሆን ፤ የዝሙት ፡ ሥራን ፡ በማሳሰብ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ በማነሣሣት ፡ ወስዶ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ በመቅጠር ፡ ሴቶችን ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ የማቃጠር ፡ ንግድ ፡ የያዘ ፤

(ለ) ወይም ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ቤት ፡ ውስጥም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለዘማዊነት ፡ ለመስጠት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ወይም ፡ ሴቶችን ፡ የሚያስቀምጥ ፡ ሰው ፤

በተለይም ፡ በግድ ፡ ይ። ፡ የማስቀመጡ ፡ ሥራ ፡ በአንድነት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ከባዶች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፱ ። ስለ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ።**

ሞያ ፡ ተብሎ ፡ በተያዘው ፡ አቃጣሪነትና ፡ ሴቶችን ፡ ለዝሙት ፡ ማቅረብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚከተሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚፈረደው ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ከሦስት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመትና ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጫም ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) በደል ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የጥፋተኛው ፡ ሚስቱ ፤ ወይም ፡ ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ወይም ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጁ ፡ ወይም ፡ የእንጀራ ፡ ልጁ ፡ ወይም ፡ ወንድሙ ፡ ወይም ፡ እኅቱ ፡ የሞግዚትነት ፡ ልጁ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ እንዲጠብቃት ፡ በአደራ ፡ የተሰጠችው ፡ እንደ ፡ ሆነች ፤

(ሐ) ለዝሙት ፡ የተሰጠችው ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ኀዘን ፡ ያለባት ፡ በመሆንዋ ፡ ወይም ፡ ጌታዋ ፡ ወይም ፡ አሠሪዋ ፡ ወይም ፡ አስተማሪዋ ፡ ወይም ፡ አኗሪዋ ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ጥፋተኛው ፡ አታሏት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) የተንኰልን ፡ የማታለልን ፡ (የሸንገላን) ፡ የኀይልን ፡ የማስፈራራትን ፡ የአስገዳጅነትን ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ በማስፈራራት ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) ማቃጠርን ፡ ሞያ ፡ አድርጎ ፡ ለያዘ ፡ ሰው ፡ ሴቲቱን ፡ እንድትሰጥ ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ ሰጥቷት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ተወስዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሄደችበት ፡ ዱካ ፡ ወይም ፡ የምትኖርበት ፡ ቦታ ፡ ሊገኝ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ረ) በኀፍረት ፡ ወይም ፡ በኀዘን ፡ ወይም ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ራሷን ፡ ለመግደል ፡ ደርሳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፭፻፯ ። ሴቶችን ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሱትን ፡ ለዝሙት ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ዝግጅቶች ።

በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ አደራረግ ፡ ቢሆን ፤ ሴቶችን ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ለዝሙት ፡ ስለ ፡ ማሳሰብ ፡ ዝግጅቶችን ፡ ወይም ፡ ድርጅቶችን ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡—

ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ሞያ ፡ ብሎ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በብዙዎች ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያደርስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ሲሆን ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ። ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ ከ፭፻ ፡ ብር ፡ በማያንስ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## መልካም ፡ በሆነው ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ቍ ፡ ፭፻፰ ። ክብረ ፡ ንጽሕናንና ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የሚያሳፍር ፡ ሥራን ፡ በአደባባይ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ባንድ ፡ የአደባባይ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ እያየ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ተግባርን ፡ ኀፍረት ፡ ነገርን ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ በብርቱ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ የርኵሰት ፡ ተግባር ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ በተግባሩ ፡ ወይም ፡ በአኳኋኑ ፡ ያሳየ ፡ ሰው ፤

እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አጥፊው ፡ ዐውቆ ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ በሆነ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ፊት ፡ የተባለውን ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ መደበኛው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፮፻፱ ። ኀፍረተ ፡ ነገርን ፡ የሚያሳዩ ፤ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አሳትሞ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕናና ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ለመነገድ ፡ ወይም ፡ ለመጠቀም ፡ ጽሑፎችን ፤ ሥዕሎችን ፡ የሚለጠፉ ፡ ነገሮችን ፡ ፊልሞችን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ዕቃዎችን ፡ ሠርቶ ፡ ያወጣ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ያስመጣ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የላከ ፤ ያመላለሰ ፡ የተቀበለ ፤ ያስቀመጠ ፡ በአደባባይ ፡ የዘረጋና ፡ ያሳየ ፤ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማከራየት ፡ ያቀረበ ፤ ያደለ ፤ ወይም ፡ በያለበት ፡ የነዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ እንደ፡ ምን ፡ ወይም ፡ ከምን ፡ ሊገኙ ፡ እንደሚችሉ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ሊገኝባቸው ፡ እንደሚችሉ ፡ በማናቸውም ፡ ብልሀት ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ያስታወቀ ፡ ያመለከተ ፡ እንዲታወቅ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የተከሰሰባቸው ፡ ነገሮች ፡ መወረሳቸው ፡ ወይም ፡ እንዲጠፉ ፡ መደረጋቸው ፡ ሳይቀር ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ቅጣቱ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ለመድረስ ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) አጥፊው ፡ የዚህን ፡ የንግድ ፡ ጥቅም ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እንደዚሁ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፤ ዕድሜ ፡ ላለው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ዐውቆ ፡ ያሳየ ፡ ወይም ፡ ያስረከበ ፡ ወይም ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፲ ። አሳፋሪ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ስለ ፡ ማሳየት ።**

ክብረ ፡ ንጽሕናንና ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ በብርቱ ፡ የሚቃወሙትን ፡ በትያትር ፡ በሲኒማ ፡ በራዲዮ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ማስተላለፊያ ፡ ያደራጀ ፡ ያሰማ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲታይ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፩ ። ስለ ፡ ተፈቀዱ ፡ ሥራዎች ።**

የማይገባውን ፡ ፍቅርን ፡ ወይም ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋን ፡ በቀጥታ ፡ ለማነሣሣት ፡ ሳይሆን ፡ የጥበብ ፡ የድርሰት ፡ የጠራ ፡ ጠባይ ፡ ብቻ ፡ ያላቸው ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ርኵሰት ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ እንደ ፡ ነኩ ፡ ሆነው ፡ አይቈጠሩም ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፪ ። መልካም ፡ ጠባይን ፡ የሚነኩ ፡ ነገሮችን ፡ ለሕዝብ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

ክብረ ፡ ንጽሕናንና ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ የሚነኩ ፡ ነገሮችን ፤ ዕቃዎችን ፤ መድኀኒቶችን ፤ ጽሑፎችን ፡ ለሕዝብ ፡ ያስታወቀ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ ላልጠየቁ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለሞያ ፡ ሥራቸው ፡ ጠቃሚነት ፡ ለሌላቸው ፡ ወደ ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ የላከ ፡ ሰው ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፫ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ልጆች ፡ በሕሊና ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ከሚጥሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ሥዕሎች ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።**

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በክፋት ፡ ወይም ፡ በማነሣሣት ፡—

(ሀ) የግብረ ፡ ሥጋን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዝንባሌን ፡ ከመጠኑ ፡ በላይ ፡ የማነሣሣት ፡ የማበላሸት ፡ የማሳሳት ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ ከቤተ ፡ ሰብአዊ ፡ ወይም ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ የብልግናዎች ፡ ወይም ፡ የጭካኔዎች ፡ የተፈጥሮ ፡ ስሜቶች ፡ የማሳደር ፡ ወይም ፡ ከመጠኑ ፡ በላይ ፡ የማነሣሣት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውን ፡ ጽሑፎችን ፡ ወይም ፡ ሥዕሎችን ፡ ወይም ፡ ነገሮችን ፡ ባንድ ፡ መስተዋት ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ በሚተላለፍበት ፡ ቦታ ፡ ዘርግቶ ፡ ያሳየ ፡ ወይም ፡ በማንኛዎቹም ፡ ከውጭ ፡ ለመታየት ፡ በሚችሉ ፡ ስፍራዎች ፡ አድርጎ ፡ ለሕዝብ ፡ የገለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ እነዚህኑ ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮችን ፡ ሥዕሎችን ፡ ጽሑፎችን ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ላልሞላው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላልደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ያቀረበ ፡ ያበደረ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ የሸጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ የዕቃው ፡ መወረስ ፡ ሳይቀር ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በቤተ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### በጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፩ ። ጋብቻን ፡ በተንኰል ፡ በማታለል ፡ ስለ ፡ መፈጸም ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዐት ፡ ሲዋዋል ፡ ወይም ፡ ለመዋዋል ፡ ሲል ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ወይም ፡ እንዳይጸና ፡ ለማድረግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በአንደኛው ፡ ውስጥ ፡ የሚከለከል ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ ዐውቆ ፡ የደበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የጋብቻው ፡ ሥርዐት ፡ ካልፈረሰ ፡ በቀር ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፫) በማታለል ፤ በማባበል ፤ በማሳሳት ፤ በማጭበርበር ፡ ዘዴ ፡ ጋብቻን ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፪ ። በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ መፈጸም ።**

በሕግ ፡ የተከለከለውን ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለውን ፡ ወይም ፡ የማይጸናውን ፡ ጋብቻ ፡ በዓለማዊ ፡ ወይም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥርዐት ፡ ያስፈጸመ ፡ ሰው ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፫ ። በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) ሕግ ፡ በሚያጸናው ፡ ዐይነት ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ግዴታ ፡ ታስሮ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ የፊተኛው ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ሳይፈርስ ፡ ወይም ፡ ሳይሻር ፡ ከሌላ ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ብሎ ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዐት ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ በተለይም ፡ አድራጊው ፡ እውነተኛውን ፡ ሁኔታ ፡ በመሰወር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አዲሱን ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ የምትፈጽመውን ፡ ሴት ፡ በማታለል ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ሚስት ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ግዴታ ፡ ታስራ ፡ የምትገኝ ፡ ሴት ፡ መሆንዋን ፡ እያወቀ ፡ ከዚችው ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ከሁለቱ ፡ ጋብቻ ፡ አንዱ ፡ እስከ ፡ ፈረሰ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ተሻረ ፡ ድረስ ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፮፻፲፯ ። የተለየ ፡ ሁኔታ ።

በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደሚፈቅደው ፡ አኗኗር ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ አይፈጸምበትም ።

ቍ ፡ ፮፻፲፰ ። ስለ ፡ ሴሰኝነት ።

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በታወቀ ፡ ጋብቻ ፡ ተጋብተው ፡ ከሚኖሩ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንደኛውና ፡ ከነሱም ፡ ጋራ ፡ የሴሰኝነት ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፤ ተበዳዩ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

አቤት ፡ ባዩ ፡ የሴሰኝነት ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጸም ፡ የተስማማ ፡ ወይም ፡ ያነሣሣ ፡ ይቅርታ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በተፈጸመው ፡ ሴሰኝነት ፡ ጥቅምን ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክሱ ፡ ውጤት ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ።

(፪) የሴሰኝነት ፡ ሥራ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ አንድነት ፡ መኖራቸው ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ ራሱ ፡ የሴሰኝነት ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ለመፋታት ፡ ወይም ፡ ተለይቶ ፡ ለመኖር ፡ የሚያበቃ ፡ ምክንያት ፡ ተገኝቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ መሰለው ፡ ቅጣቱን ፡ ለማቃለል ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፹፭ ።]

(፫) ተከሳሹ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ሳይፋታ ፡ ሳይለያይ ፡ ወይም ፡ ሚስቱ ፡ ጥላው ፡ ሳትሄድ ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ዕቁባት ፡ ያስቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፲፱ ። የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ መሞት ።

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ መሞት ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ያስቀራል ፤ ክሱ ፡ ቀርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የቅጣቱም ፡ ፍርድ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎችና ፡ በተለይም ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ደጋፊነት ፡ ግዴታዎች ፡ ያሉበት ፡ መሆኑ ፡ ለዚሁ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡ እንዲቀርለት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፮፻፳ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብድ ፡ ሁኔታ ።

የሴሰኝነት ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ ካ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ ከሆነ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ካላደረሰ ፡ ሕፃን ፡ ጋራ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሕፃናቶችን ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ በተደራቢነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፭፻፺፬ ።]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በዘመዶች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረግ ፡ የዝሙት ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፮፻፳፩ ። በዘመድ ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የዝሙት ፡ ተግባር ።

(፩) በወላጆችና ፡ በተወላጆች ፡ ወይም ፡ በወንድማማቾችና ፡ በእኅትማማቾች ፡ ወይም ፡ የሥጋ ፡ ልደት ፡ የደም ፡ ጥልቀት ፡ ዝምድና ፡ ባላቸውና ፡ ጋብቻቸው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በተከለከለ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የተደረገ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፤

እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ያስቀጣል ። ይኸውም ፡ ከአባትነት ፡ ሥልጣን ፡ የመሻሩ ፡ ቅጣት ፡ ሳይቀር ፡ ነው ።

(፪) ጥፋተኛው ፡ ወይም ፡ ጥፋተኞቹ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ የተገናኙት ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ከሆነችው ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ካልሞላት ፡ ልጃገረድ ፡ ወይም ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች ፡ የወንጀሉን ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱት ፡ አታላይነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ በእነዚህ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አይፈጸምባቸውም ።

አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የጥበቃ ፡ የትምህርት ፡ የመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ውሳኔዎች ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

### ቍ ፡ ፮፻፳፪ ። በሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ ክብረ ፡ ንጽሕናን ፡ በሚያበላሽ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መደፋፈር ።

በወላጅና ፡ በልጅ ፤ በልጅ ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ በወንድማማቾችና ፡ በእኅትማማቾች ፡ መካከል ፡ ከተሠሩ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ ከመሰሉ ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ ከሆኑት ፡ ሥራዎች ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ በተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ካላደረሰው ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የተሠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ጥፋት ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ አስነቃፊ ፡ የሆነ ፡ ነገርን ፡ የፈጠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ያስቀጣሉ ፤ ወይም ፡ ጥፋቶቹ ፡ ከባዶች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ያስቀጣሉ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በክብር ፡ መዝገብና ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፮፻፳፫ ። የሕፃኑን ፡ መወለድ ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ።

(፩) ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሕፃኑን ፡ መወለድ ፡ ያላስታወቁ ፡ ወላጆች ፤ ሐኪሞች ፤ አዋላጆች ፡ ሴቶች ፡ ወይም ፡ አዋላጅ ፡ ወንዶች ፡ ዲሬክተሮች ፡ ወይም ፡ የሕክምና ፡ ወይም ፡ የክሊኒክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ።

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ይህ ፡ ቅጣት ፡ አንድ ፡ የተጣለ ፡ ሕፃን ፡ አግኝቶ ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ ባላስታወቀ ፡ ሰው ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፮፻፳፬ ። የሕዝብን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፤ ሕፃኑን ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ከተባለው ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መሠረዝ ።

የሌላውን ፡ ሰው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ያጠፋ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የለዋወጠ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በተለይም ፡—

(ሀ) የሕፃኑ ፡ እናት ፡ ያልሆነችውን ፡ እናቱ ፡ ነች ፡ ብሎ ፡ አስመስሎ ፡ የነገረ ፤ ወይም ፡ ለሕፃኑ ፡ ልደት ፡ ጉዳይ ፡ ሐሰተኛ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

(ለ) ወይም ፡ አንዱን ፡ ሕፃን ፡ በሌላ ፡ ሕፃን ፡ የለወጠ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ፤ ወይም ፡ በተለይ ፡ የማለዋወጡ ፡ ተግባር ፡ ከባድ ፡ ውጤቶችን ፡ ያስከተለ ፡ ወይም ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊታወቅ ፡ የሚችል ፡ የነበረ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፮፻፳፭ ። ቀለብ ፡ የመስጠት ፡ ተግባርን ፡ ስለ ፡ አለመፈጸም ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡—

(ሀ) በቤት ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለወላጆቹ ፡ ወይም ፡ ለተወላጆቹ ፤ የፈታትም ፡ ብትሆን ፡ ለሚስቱ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ እርዳታዎች ፡ ምግቦችን ፤ ወይም ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፡ ቀለብ ፡ አልሰጥም ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ መስጠትን ፡ ያስታጐለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ ላስረገዛት ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ለዲቃላ ፡ ልጁ ፡ በሕግ ፤ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ውሳኔ ፤ ወይም ፡ ባንድ ፡ በተገለጠ ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡

እንዲሰጥ ፡ የታዘዘውን ፡ ገንዘብ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታዎችን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ተበዳዩ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርብ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፳፮ ። ልጅን ፡ የማሳደግ ፡ ተግባርን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

(፩) ወላጆች ፡ ወይም ፡ የአባትነት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጥቅምን ፡ በመፈለግና ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ በመናቅ ።

(ሀ) እንዲጠብቁዋቸው ፡ የተሰጧቸውን ፡ ልጆች ፡ በቸልተኝነት ፡ በከባድ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ የተዉና ፡ አስፈላጊውን ፡ ያላደረጉ ፡ ወይም ፡ በሕሊና ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ በአኗኗር ፡ በኩል ፡ በቸልተኝነት ፡ የጣሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ልጁ ፡ በአኗኗር ፡ በሕሊና ፡ ኑሮ ፡ ረገድ ፡ የሚጣልበት ፡ ወይም ፡ የሚጎዳበት ፡ ቦታ ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ማወቅ ፡ ሲችሉ ፡ ለተራዘመ ፡ ጊዜ ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የላኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣሉ ። የሕጉም ፡ መጣስ ፡ ከባድ ፡ ወይም ፡ የተደጋገመ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ከአባትነት ፡ ሥልጣን ፡ የመሻሩ ፡ ቅጣት ፡ ሳይቀር ፡ ነው ።

(፪) የጠባይ ፡ ማረምን ፡ መብት ፡ በመተላለፍ ፡ ወይም ፡ በክፉ ፡ ከማንገላታት ፡ የተነሣ ፡ አስቀድሞ ፡ የታሰበ ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የተሠራ ፡ ጉዳት ፡ በልጅ ፡ ላይ ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተመሳሳይ ፡ ውሳኔዎች ፡ ስለዚሁ ፡ ጥፋት ፡ ከተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ ጋራ ፡ በመጣመር ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይፈጸሙበታል ። [ቍ ፡ ፮፻፲፫ ።]

## ፭ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## በሀብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

#### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

#### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፮፻፳፯ ። መሠረቱ ።

(፩) ንብረትና ፡ የገንዘብ ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ሊገመቱ ፡ በሚችሉት ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ የሀብቱ ፡ ክፍሎች ፡ በሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ለሚፈጸመው ፡ ወን

ጀል ፡ ጉዳቱ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ እንዳልሆነ ፡ የሚቈጠር ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ስለ ፡ ደንብ ፡ ተላላፊዎች ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ የተወሰነውን ፡ ድንጋጌ ፡ የማይመለከት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰኑ ፡ ደንብ ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የመንግሥትም ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ እንዳይደርስበት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ አነጋገር ፡ ንብረቱ ፡ ተጎዳ ፡ የሚባለው ፡ ወንጀሉ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የንብረቱን ፡ ሁኔታ ፡ የሚለውጥ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፮፻፭፰ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መክበር ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ እንዳይከብር ፡ የሚከለክል ፡ ደንብ ፡ በሕግ ፡ ተወስኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ አድራጎት ፡ ወንጀል ፡ ሠርቷል ፡ የሚያሰኘው ፡ አድራጊው ፡ የማይገባውን ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ከግልጽ ፡ አሠራር ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የመበልጸግ ፡ ልዩ ፡ ፍላጎት ፡ መኖሩ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ይህንኑ ፡ ለመፈጸም ፡ የታቀደው ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ የሚሰጠውን ፡ ውጤት ፡ ያላስገኘ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ወንጀሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የተወሰደውን ፡ ሀብት ፡ የመመለስ ፡ ወይም ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ማሻሻያ ፡ ካሣ ፡ አስቀድሞ ፡ የመክፈሉ ፡ ጉዳይ ፡ በአድራጊው ፡ ፈቃደኛነት ፡ የተፈጸመ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ የወንጀሉን ፡ አፈጻጸም ፡ አይሰርዘውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ አድራጎት ፡ ለመገንዘብ ፡ ይችላል ። [ቊ ፡ ፸፱ ፡ (ሠ) ። ]

ቊ ፡ ፮፻፭፱ ። በቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ በኩል ፡ ወንጀል ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።

(፩) በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ የኀይል ፡ ሥራን ፤ ወይም ፡ የወንበዴነትን ፡ ተግባር ፡ በመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ የማስገደድን ፡ በግፍ ፡ የመንጠቅን ፡ ወይም ፡ በዛቻ ፡ የማስፈራራትን ፡ አፈጻጸም ፡ ከሚመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤

(ሀ) ወላጅ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ ተወላጅ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ አሳዳጊ ፡ አባት፡ ወይም ፡ የማደጎ ፡ ልጅ ፡ ባልተለያዩ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በአሳዳጊ ፡ ወይም ፡ የአባትነት ፡

ሥልጣን ፡ በያዘ ፡ ፀለአደራ ፡ ወይም ፡ በማደጎ ፡ ልጅ ፡ የእናት ፡ የአባት ፡ ልጆች ፡ በሆኑ ፡ ወንድማማቾች ፡ ወይም ፡ እትማማቾች ፡ ወይም ፡ በእናት ፡ ብቻ ፡ በሚገናኙ ፡ ወንድማማችና ፡ እኅትማማች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ደግሞ ፡ በተበዳዩ ፡ ቤት ፡ በሚኖሩ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ በሆኑ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ተበዳዩ ፡ ወገን ፡ ክስ ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ የተፈጸመውን ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ በዳኝነት ፡ ለመከታተል ፡ ወይም ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰን ፡ አይቻልም ።

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ የሚወስነው ፡ በጠቅላላዎቹ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የጕዳዩን ፡ አካባቢ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝና ፡ ቢያንስም ፡ ቢያድግም ፡ የወንጀለኛውን ፡ ጥፋት ፡ ከባድነት ፡ በመገመት ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቸው ፡ አንጋገር ፡ ተበዳዩ ፡ ዘመድ ፡ የክስ ፡ አቤቱታን ፡ ሳያቀርብ ፡ መቅረቱ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቃሚ ፡ ባል ሆኑ ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ የዝምድና ፡ ግንኙነት ፡ በሌላቸው ፡ ለወንጀሉ ፡ ተካፋይ ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚቀርብባቸውን ፡ ክስ ፡ በዳኝነት ፡ እንዳይታይ ፡ አያግደውም ። [ቍ ፡ ፵ ።]

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

## በተንቀሳቃሽ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ቍ ፡ ፮፻፴ ። ስለ ፡ ስርቆት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የማይገባውን ፡ ብልጽግና ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ አንድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ከማይንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተነጠለ ፡ ዕቃ ፡ ከማይንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በማንሣት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመውሰድ ፡ በቀጥታ ፡ የራሱ ፡ ሀብት ፡ ያደረገው ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ዘዴ ፡ ከራሱ ፡ ንብረት ፡ ጋራ ፡ እንዲቀላቀል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ቅጣት ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፮፻፴፭ ። የሥራ ፡ ኀይልን ፡ ስለ ፡ መስረቅ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በማይገባው ፡ ለማበልጸግ ፡ ዐቅዶ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አገልግሎት ፡ ከተቋቋመው ፡ ከጋዝ ፡ ከእንፋሎቶች ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ኀይል ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ በድብቅ ፡ ወስዶ ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በሌብነት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፮ ። የጋራ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ ስለ ፡ መስረቅ ።**

(፩) በኅብረት ፡ ባለሀብትነት ፡ ማኅበረተኛነት ፡ በወራሽነትም ፡ ቢሆን ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ የጋራ ፡ የሆነ ፡ ዕቃ ፡ ያለው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የጋራ ፡ የሆነውን ፡ ዕቃ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ለመበልጸግ ፡ ዐቅዶ ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በተበዳዩ ፡ ከሳሽነት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ የወሰደው ፡ የሚያልቅ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ አወሳሰዱም ፡ ለራሱ ፡ ከሚገባው ፡ ድርሻ ፡ ያልበለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣት ፡ አይደርስበትም ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፯ ። በሙታን ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ያላገባብ ፡ ለመበልጸግ ፡ ዐቅዶ ፡ ከሬሳ ፡ ጋራ ፡ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በመቃብር ፡ ቤት ፡ የተቀበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በሌብነት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፰ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት ።**

በቀላል ፡ አኳኋን ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ዕቃ ፡ የሰረቀ ፡ በተለይም ፡ ፍራፍሬዎች ፡ እሸትና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሲሆን ፡ ስለ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ከ፰፻፶፯ ፡ እስከ ፡ ፰፻፶፯ ። ]

**ቍ ፡ ፮፻፴፱ ። ከባድ ፡ ስርቆት ።**

እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ከፍተኛነት ፡ መጠንና ፡ በተሰረቀው ፡ ዕቃ ፡ ዐይነት ፡ በሌባው ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ሁኔታና ፡ በአሰራረቁ ፡ ዐይነት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ የቅጣት ፡ ማክበድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲያጋጥሙ ፡ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚሆነው ፡ የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣትም ፡ የሚያስወስን ፡ ጕዳይ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ የሚችለው ፡—

(፩) ወንጀሉ ፡ የሚመለከታቸው ፡—

(ሀ) የተሰረቁት ፡ ዕቃዎች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሚገኙ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ በአንቲካ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ በሆኑ ፡ ለሕዝብ ፡ በተከፈቱ ፡ ሕንጻዎች ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የዕውቀት ፡ የኪን ፡ ጥበብ ፡ ወይም ፡ የታሪክ ፡ ባለዋጋነት ፡ ያላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የተለየ ፡ ጠባቂ ፡ የሌላቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ ዕቃዎች ፡ እንስሳዎች ፤ ወይም ፡ ሰብሎች ፡ ወይም ፡ ለዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ላንድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በተለይም ፡ ለፖስታ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ለማመላለሻ ፡ ድርጅት ፡ እንዲቀመጡ ፡ ወይም ፡ እንዲላኩ ፡ የተሰጡ ፡ ሸቀጦች ፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡—

(ሀ) ወታደር ፡ ሆኖ ፡ ሌብነቱ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ በቤታቸው ፡ ባረፈባቸው ፡ ወይም ፡ በማደሪያቸው ፡ በሰፈረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በጓደኞቹ ፡ ወይም ፡ በአለቆቹ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ የሚያገለግለውን ፡ ወይም ፡ እንዲያገለግል ፡ የተመደበውን ፡ ዕቃ ፡ በመስረቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የስርቆቱን ፡ ወንጀል ፡ የሠሩት ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ መኰንን ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የንግድና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውን ፡ የባንክ ፡ ሠራተኛ ፡ ጠበቃ ፡ ውል ፡ አዋዋይ ፡ የወኪልነት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምክንያት ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ የንግድ ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የሆነ ፡ በተለይ ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ ምክንያት ፡ በእጃቸው ፡ የገባውን ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) በሆቴል ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በማደሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ መሪ ፤ በዕቃ ፡ አመላላሽ ፡ (ኮሚሲዮኔር) ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂዱ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ስርቆቱን ፡ የፈጸሙት ፡ በደንበኞቻቸው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያደርስ ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፤

(መ) ወይም ፡ የቤት ፡ አሽከር ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ለማጅ ፡ በሥራው ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በጌታው ፡ ወይም ፡ በአሳዳሪው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ አድርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) አድራጊው ፡—

(ሀ) ስርቆትን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ወንጀሎችን ፡ ሥራው ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የነዚህን ፡ ዐይነት ፡ ወንጀሎች ፡ ለመሥራት ፡ በተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ አባልነት ፡ ሰርቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ የስርቆቱን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ሆኖ ፡ የአደገኛነትን ፡ ጠባይ ፡ በሚያሳይ ፡ አድራጎት ፡ ይልቁንም ፡ መሣሪያና ፡ የመሰርሰርያ ፡ ምሣር ፡ የማጥቂያ ፡ ወይም ፡ የመከላከያ ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኛ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ወንበዴዎች ፡ ጋራ ፡ በመሆን ፡ በሌሊት ፡ ቅጥር ፡ ጥሶ ፡ አጥር ፡ ዘሎ ፡ በር ፡ ሰብሮ ፡ ወይም ፡ ግድግዳ ፡ ሰርስሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በሽብር ፡ በግርግር ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ አደጋ ፡ ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ቃጠሎ ፤ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ እንደ ፡ ማዕበል ፡ ባለ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ መቅሠፍት ፡ ተጠግቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፮፻፴፮ ። ስለ ፡ ወንበዴነት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ አስቦ ፡ ወይም ፡ በስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ተይዞ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በስርቆት ፡ ያገኘውን ፡ ነገር ፡ ለመሰወር ፡ በማሰብ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የማንገላታት ፡ ተግባር ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ተበዳዩ ፡ ለመከላከል ፡ እንዳይችል ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ በኀይል ፡ ያስወገደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፮፻፴፯ ። ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ በአንደኛው ፡ በወንበዴነት ፡ ተግባር ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ የወንበዴነቱን ፡ ተግባር ፡ የሠራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ አድራጎቶች ፡ አንደኛውን ፡ ለመፈጸም ፡ ዐቅዶ ፡—

(ሀ) በሰዎች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሀብት ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በተቋቋሙ ፡ በወንበዴ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በልማደኛ ፡ ሌብነት ፡ ወይም ፡ በወንበዴነት ፡ ወይም ፡ ከግፍ ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ ሀብትን ፡ ወይም ፡ የመተዳደሪያ ፡ ቅርስን ፡ ለማግኘት ፡ በሕጉ ፡ አነጋገር ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎቶች ፡ መሆናቸው ፡ የተመለከቱትን ፡ ተግባሮች ፡ በመፈጸም ።

BACK



(ሐ) ተበዳዩን ፡ ይዞ ፡ በቀጥታ ፡ እገድልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ እርግጠኛ ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ሊያደርስበት ፡ ቃጥቶ ፡ ይልቁንም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ አደገኛ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ መሣሪያ ፡ አስፈራርቶ ፡ ወይም ፡ ሥቃይ ፡ በሚያደርስ ፡ ሁኔታ ፡ አንገላቶ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ አድርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ በተለይ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስ ፡ መሆኑን ፡ አሳይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ሓያ ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ።

(፪) የወንበዴነትን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ ሰው ፡ ካንድ ፡ ክፍል ፡ ወንበዴዎች ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣሪያና ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አደገኛ ፡ መሣሪያዎች ፡ በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በሚያደርስ ፡ ዘዴ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ የጭከናው ፡ አሠራር ፡ ወይም ፡ የተፈጸመው ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ነዋሪ ፡ የሆነ ፡ የአካለ ፡ ጐደሎነት ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ሞትን ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ ጉዳት ፡ አድርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ የወንበዴነት ፡ ወንጀል ፡ መሥራትና ፡ ወንበዴዎቹም ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ የተቋቋሙ ፡ የውንብድና ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ወንጀላቸው ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ የሚያስከትል ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፯፻፶፫ ። ስለ ፡ ዘረፋ ።

እንዲሁም ፡ የዘረፋ ፡ ወንጀል ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡—

(ሀ) ለሕዝብ ፡ ምቾት ፡ ላገሩ ፡ መስፋፋትና ፡ ሀብት ፡ (ኤኮኖሚ) ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑት ፡ ሥንቆች ፡ የምግብ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ለሥንቅ ፡ የቀረቡ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ለነዋሪው ፡ ሕዝብ ፡ ሕይወት ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለ ዋጋነት ፡ ያላቸው ፡ መኪናዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ዕቃዎች ፡ ሲሆኑ ፤

(ለ) ወይም ፡ በመሬት ፡ በባሕር ፡ ወይም ፡ በአየር ፡ በሚመጣ ፡ ከፍተኛ ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ መጋጨት ፡ እንደ ፡ አይሮፕላን ፡ ድንገተኛ ፡ ማረፍ ፡ መገደድ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ መርከብ ፡ መስጠም ፡ ያለውን ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ሲሆን ፤

ለቀላል ፡ ወይም ፡ ለከባድ ፡ ወንበዴነት ፡ በተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።
[ቍ ፡ ፯፻፶፮ ፡ ፯፻፶፯ ።]

ቍ ፡ ፯፻፶፬ ። የባሕር ፡ ወንበዴነት ።

እንዲሁም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የውንብድና ፡ ተግባር ፡ የሚፈጽሙ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡

18

በተመለከቱት ፤ ሁኔታዎች ፤ መሠረት ፤ የቀላል ፤ ወይም ፤ የከባድ ፤ ወንበዴነት ፤ ቅጣት ፤ ይፈጸምባቸዋል ። [ቍ ፤ ፮፻፴፯ ፤ ፮፻፴፰ ።]

ቍ ፤ ፮፻፴ ። የተጠበቁ ፤ ሁኔታዎች ።

በጦርነት ፤ ጊዜ ፤ የሰዎችን ፤ መብት ፤ ተቃራኒ ፤ በሆነ ፤ አኳኋን ፤ የውንብድና ፤ የዘረፋ ፤ ወይም ፤ የባሕር ፤ ውንብድና ፤ የሚሠሩ ፤ ሰዎች ፤ ለነዚሁ ፤ በተለይ ፤ በተወሰኑት ፤ ድንጋጌዎች ፤ መሠረት ፤ ይቀጣሉ ። [ቍ ፤ ፪፻፹፭ ።]

ቍ ፤ ፮፻፴፩ ። እምነትን ፤ ስለ ፤ ማጒደል ።

(፩) ማንም ፤ ሰው ፤ ተገቢ ፤ ያልሆነ ፤ ብልጽግና ፤ ለራሱ ፤ ለማግኘት ፤ ወይም ፤ ለሌላው ፤ ሰው ፤ ለማስገኘት ፤ ዐቅዶ ፤—

(ሀ) የሌላው ፤ ሰው ፤ የሆነውንና ፤ ላንድ ፤ ለተወሰነ ፤ አገልግሎት ፤ በእምነት ፤ የተሰጠውን ፤ ነገር ፤ በሙሉ ፤ ወይም ፤ በከፊል ፤ ለራሱ ፤ ያደረገ ፤ እንደ ፤ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፤ በአደራ ፤ አስቀማጭነት ፤ የተረከበውን ፤ አንድ ፤ የተወሰነ ፤ ቊጥር ፤ ያለውን ፤ ጥሬ ፤ ገንዘብ ፤ ወይም ፤ ዐይነቱ ፤ ያልተለየ ፤ አላቂ ፤ ነገር ፤ ፈሳሽ ፤ እህል ፤ ዕንጨትና ፤ ይህንን ፤ የመሳሰለ ፤ ማናቸውንም ፤ ሌላ ፤ ዐይነት ፤ ነገር ፤ ቢሆንም ፤ መብት ፤ ሳይኖረው ፤ ለግል ፤ ጥቅሙ ፤ የተገለገለበት ፤ ወይም ፤ ሌላ ፤ ሰው ፤ እንዲጠቀምበት ፤ ያደረገ ፤ እንደ ፤ ሆነ ፤

በእስራት ፤ ወይም ፤ እንደ ፤ ወንጀሉ ፤ ከባድነት ፤ መጠን ፤ እስከ ፤ አምስት ፤ ዓመት ፤ ለመድረስ ፤ በሚችል ፤ ጽኑ ፤ እስራት ፤ ይቀጣል ።

(፪) ተከሳሹ ፤ በእምነት ፤ የተሰጠውን ፤ ዕቃ ፤ ሸጦ ፤ ያገኘው ፤ ገንዘብ ፤ ወይም ፤ በሌላ ፤ ነገር ፤ ለውጦ ፤ የወሰደው ፤ ልውጫ ፤ ወይም ፤ ለሌላ ፤ ለተወሰነ ፤ ጒዳይ ፤ የሚያገለግልና ፤ ወይም ፤ በዚሁ ፤ በአደራ ፤ ተቀብሎት ፤ በነበረው ፤ ነገር ፤ ሽያጭ ፤ የገዛውም ፤ የተካውም ፤ ሌላ ፤ ዐይነት ፤ ዕቃ ፤ ሁሉ ፤ እንደ ፤ ሌላ ፤ ሰው ፤ ዕቃ ፤ ይቈጠራል ።

(፫) ተከሳሹ ፤ የተቀበለውን ፤ ዕቃ ፤ ወይም ፤ የገንዘቡን ፤ ንብረትነት ፤ ወደ ፤ ራሱ ፤ ለማዛወር ፤ ያሰበበትን ፤ ወይም ፤ ባለይዞታነቱን ፤ ለራሱ ፤ ያደረገበትን ፤ ሁኔታ ፤ ወይም ፤ ይኸው ፤ በአደራ ፤ የተቀበለው ፤ ገንዘብ ፤ ወይም ፤ ዕቃ ፤ መኖር ፤ አለመኖሩን ፤ ፍርድ ፤ ቤቱ ፤ ለማረጋገጥ ፤ የሚችለውና ፤ እንዲመልስም ፤ በተጠየቀ ፤ ጊዜ ፤ ለመመለስ ፤ ወይም ፤ ለመክፈል ፤ ያልቻለ ፤ መሆኑን ፤ ወይም ፤ የዕቃውን ፤ ሁኔታ ፤ እንዲያስረዳ ፤ ወይም ፤ ለባለቤቱ ፤ እንዲያሳይ ፤ ሲጠየቅ ፤ ይህን ፤ ለመፈጸም ፤ አለመቻሉን ፤ ሲገነዘበው ፤ ይህን ፤ በእምነት ፤ የተቀበለውን ፤ ዕቃ ፤ ለግል ፤ ጥቅሙ ፤ ያዋለው ፤ መሆኑን ፤ ሊረዳው ፤ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፪ ። ከባድ ፡ የሆነ ፡ የእምነት ፡ ማጕደል ።**

ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የጽኑ ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) አድራጊው ፡ በእምነት ፡ በተቀበለው ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አካሄድ ፡ ጕዳይ ፡ በነጭ ፡ ወረቀት ፡ ግርጌ ፡ ፊርሞና ፡ አትሞ ፡ ባስረከበው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ አደራ ፡ ሰጪ ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ በማስመሰል ፡ የገንዘብ ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ግዴታ ፡ ቃል ፡ አስመስሎ ፡ በመጻፍ ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀበያ ፡ ሰነድ ፡ በማስመሰል ፡ ወይም ፡ በፈራሚው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያደርስ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ ሠርቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የእምነት ፡ ሥራውን ፡ ያጓደለው ፡ በልዩ ፡ ሥራው ፡ ባገኘው ፡ ሥልጣን ፡ ምክንያት ፡ ይልቁንም ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ወይም ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ ሞግዚትና ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ (ረዳት) ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ የሕግ ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ (የፊናንስ) ፡ አማካሪ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ የመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ የንብረቶች ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ከሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተፈቅዶለት ፡ ልዩ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውን ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ይህ ፡ ወንጀል ፡ የተሠራው ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥሪ ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ለባንክ ፡ ለንግድ ፡ ወይም ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ድርጅት ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ነገሮች ፡ በአደራ ፡ እንዲሰጡ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወንጀለኛው ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ወታደር ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ የጠቅላላው ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ እንዲያገለግል ፡ የተመደበውን ፡ ገንዘብ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጥይት ፡ ጠቃሚና ፡ ዋነኛ ፡ ዕቃዎች ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ የምግብ ፡ (የሥንቅ) ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ለአገር ፡ ጥቅም ፡ ለተቋቋመ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ በእምነት ፡ ተሰጥተውት ፡ የነበሩትን ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ የሰረቀ ፡ ወይም ፡ ያባከነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፫ ። አግኝቶ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ የማይገባውን ፡ ብልጽግና ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ ሲል ፡—

(ሀ) የሌላ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሆኖ ፡ በስሕተት ፡ ባልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡

BACK



ነገር ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ማዕበልና ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ባለ ፡ በተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ በመጣ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ ከባለሀብቱ ፡ ፈቃድ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፤ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ከባለቤቱ ፡ እጅ ፡ ወጥቶ ፡ በእጁ ፡ የገባውን ፡ ነገር ፡ (ዕቃ) ፡ ለራሱ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህም ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ የሆነ ፡ እንስሳ ፡ ሆኖ ፡ ወደዚህ ኛው ፡ ቤት ፡ ሸሽቶ ፡ በመጠጋት ፡ ለራሱ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይፈረድበታል ።

## ቍ ፡ ፮፻፴፬ ። የሌላ ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ ሀብት ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ያላገባብ ፡ ለማበልጸግ ፡ በማሰብ ፡ መንፈስ ፡ ሳይሆን ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ እንዲያጣ ፡ ይልቁንም ፡ የሚገባውን ፡ እንዳያገኝ ፡ እንዳይገለገልበት ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ነገር ፡ ራሱን ፡ ለመጥቀም ፡ ወይም ፡ ለጊዜውም ፡ ቢሆን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲጠቀምበት ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ከባለቤቱ ፡ ላይ ፡ ወስዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፮፻፴፭ ። ወድቆ ፡ የተገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ለራስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የጠፋ ፡ ነገር ፡ አግኝቶ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ማግኘቱ ፡ ለባለሥልጣን ፡ ሳያስታውቅ ፡ ወይም ፡ ባለመብቱ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ሳያደርግ ፡ ቀርቶ ፡ ወድቆ ፡ ያገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ለራሱ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ከባድነት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የተደበቀ ፡ ወይም ፡ የተቀበረ ፡ ገንዘብ ፡ አግኝቶ ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ የሚሆንበትን ፡ ወይም ፡ ሀብቱ ፡ የተገኘበት ፡ የቦታ ፡ ባለቤት ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፡ የክፍያ ፡ ድርሻ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳያደርግ ፡ ለራሱ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፮ ። ባለቤት ፡ የሌለውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብትን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።**

(፩) ባለቤት ፡ የሌላቸውን ፡ ነገሮች ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብትን ፡ የሚመለከተው ፡ የሀብትነት ፡ ጕዳይ ፤ እንዲሁም ፡ በየብስ ፡ በአየር ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡ የሚገኙትን ፤ በነጻ ፡ ያሉትን ፤ የማንም ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ያልሆኑትን ፡ አራዊቶች ፡ የመያዝ ፡ ጕዳይ ፡ ይህንኑ ፡ በሚመለከተው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚመሩ ፡ ናቸው ። [ቍ፡ ፳፻፫ ። ፳፻፬ ።]

(፪) ገንዘብነታቸው ፡ የመንግሥት ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ የታሪክ ፡ የአርኪዎሎጂና ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ በሆኑት ፡ ዕቃዎች ፡ በማይገባ ፡ ለመበልጸግ ፡ በማቀድ ፡ እነዚህን ፡ ዕቃዎች ፡ ለራስ ፡ ማድረግን ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ማጕደልን ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚያስቀጣ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፯ ። የመሸሸግ ፡ ወንጀል ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ዕቃው ፡ የተገኘው ፡ ባንድ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፤ በወንጀል ፡ የተገኘውን ፡ ዕቃ ፡ በመግዛትም ፡ ሆነ ፡ በተውሶ ፡ በስጦታ ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ሌላ ፡ አኳኋን ፡ የወሰደ ፤ የተገለገለ ፡ ያስቀመጠ ፤ ወይም ፡ የደበቀ ፡ አሳልፎ ፡ የሸጠ ፤ ወይም ፡ በመሸጥና ፡ በመለወጥ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ አገናኝ ፡ ሆኖ ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ ባስገኘው ፡ ፍሬ ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ በተሰረቀው ፡ ዕቃ ፡ ምትክ ፡ በልዋጭ ፡ የተገኘውን ፡ ወይም ፡ በሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ የተገዛውን ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የደበቀ ፤ የሸሸገ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ዕቃውን ፡ በሸሸገው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚወሰነው ፡ ቅጣት ፤ መጀመሪያ ፡ ወንጀሉን ፡ ባደረገው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ግንኙነት ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፬) በሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ በወዳጅነት ፡ ፍቅር ፡ ግንኙነት ፡ በመተሳሰር ፡ ወንጀለኛውን ፡ ከቅጣት ፡ ለማዳን ፡ ስለሚደረገው ፡ ተግባር ፡ ይቅርታ ፡ የማግኘት ፡ ደንብ ፤ የተሰረቀ ፡ ዕቃ ፡ ደባቂ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ አይጸናለትም ። [ቍ ፡ ፹ ።]

**ቍ ፡ ፮፻፵፰ ። ከባድ ፡ የሆነ ፡ የመሸሸግ ፡ ወንጀል ።**

የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ የሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስ

ራትና ፣ የገንዘቡም ፣ መቀጮ ፣ እስከ ፣ ዐሥር ፣ ሺሕ ፣ ብር ፣ ለመድረስ ፣ የሚችለው ፣ ተከሳሹ ፣ የተሰረቀ ፣ ዕቃ ፣ የመደበቁን ፣ ወንጀል ፣ የሠራው ፡—

(ሀ) በሰዎች ፣ ላይ ፣ ወይም ፣ በንብረት ፣ ላይ ፣ አደጋ ፣ ለመጣል ፣ በተቋቋሙ ፣ ወንበዴዎች ፣ ወይም ፣ ለክፉ ፣ አድራጎት ፣ በተደራጁ ፣ ማኅበረተኞች ፣ ውስጥ ፣ ተካፋይ ፣ ማኅበረተኛ ፣ በመሆን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፣ የተሰረቀ ፣ ዕቃ ፣ መሸሸግን ፣ ልዩ ፣ ሞያ ፣ አድርጎ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፣ ከሕዝብ ፣ አገልግሎት ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ባለሥልጣኖች ፣ ዘንድ ፣ በተሰጠው ፣ የሥራ ፣ ፈቃድ ፣ ምክንያት ፣ ባገኘው ፣ ሥልጣን ፣ በመገልገል ፣ ይህንኑ ፣ የተፈቀደለትን ፣ ሥራ ፣ አስታኮ ፣ የተሰረቀ ፣ ዕቃ ፣ ደባቂነትን ፣ ሞያ ፣ አድርጎ ፣ በመያዝ ፣ ሠርቶበት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤

(መ) ወይም ፣ ደግሞ ፣ ይህን ፣ የተሰረቀ ፣ ዕቃ ፣ የመደበቅ ፣ ተግባሩን ፣ የፈጸመው ፣ በዘራፊነት ፣ በወንበዴነት ፣ ወይም ፣ በባሕር ፣ ወንበዴነት ፣ በቀማኛነት ፣ በዛቻ ፣ በማስፈራራት ፣ የተገኘ ፣ መሆኑን ፣ በሚያውቀው ፣ ነገር ፣ ላይ ፣ ወይም ፣ ይህ ፣ ዕቃ ፣ በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ አድራጎት ፣ የተገኘው ፣ ከጦር ፣ ሠራዊት ፣ ንብረት ፣ ከአገር ፣ ጥቅም ፣ (ኤኮኖሚ) ፣ ወይም ፣ በጠቅላላው ፣ ካንድ ፣ አገር ፣ የአስተዳደር ፣ ክፍል ፣ ሀብት ፣ ውስጥ ፣ የተገኘ ፣ መሆኑን ፣ እያወቀ ፣ ይህን ፣ የመሸሸግ ፣ (የመደበቅ) ፣ ተግባሩ ፣ የፈጸመ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ነው ።

ክፍል ፣ ፪ ።

<u>በማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ላይ ፣ ስለሚሠሩ ፣ ወንጀሎች ።</u>

<u>ቍ ፣ ፯፻፺፱ ። በሰው ፣ ርስት ፣ ላይ ፣ የከብት ፣ መንጋ ፣ ሰዶ ፣ ስለ ፣ ማበላሸት ።</u>

(፩) ማንም ፣ ሰው ፣ ሆነ ፣ ብሎና ፣ መብት ፣ ሳይኖረው ፣ በሌላ ፣ ሰው ፣ ርስት ፣ ላይ ፣ የሚገኘውን ፣ ማር ፣ ግጦሽ ፣ የእርሻ ፣ ስፍራም ፣ ሆነ ፣ ደን ፣ የአትክልት ፣ ቦታም ፣ ሆነ ፣ በማናቸውም ፣ ሌላ ፣ ዐይነት ፣ ሁኔታ ፣ በሚገኝ ፣ ርስቱ ፣ ላይ ፣ መንጋዎችን ፣ አሰማርቶ ፣ ያስጋጠ ፣ ወደዚሁ ፣ ስፍራ ፣ የወሰደ ፣ ወይም ፣ እንዲዘዋወሩ ፣ የለቀቀ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤

የክስ ፣ አቤቱታ ፣ በቀረበበት ፣ ጊዜ ፣ እስከ ፣ አምስት ፣ መቶ ፣ ብር ፣ በሚደርስ ፣ መቀጮ ፣ ወይም ፣ እስከ ፣ አንድ ፣ ዓመት ፣ ሊደርስ ፣ በሚችል ፣ እስራት ፣ ይቀጣል ።

(፪) ሁኔታዎቹ ፣ ቀላል ፣ በሆኑ ፣ ጊዜና ፣ አድራጎቱንም ፣ የፈጸመው ፣ በቸልተኛነት ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በተለይም ፣ በሚበቃ ፣ ባለመጠበቅ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ድንጋጌዎች ፣ ይፈጸሙበታል ። [ቍ ፣ ፰፻፭ ። (ለ)]

ቍ ፡ ፮፻፶ ። በሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው አንድ ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡—

(ሀ) የሌላ ፡ ሰው ፡ የሆነውን ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ ሕንጻ ፡ የወረረ ፡ ወይም ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አድራጎት ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ (ባለቤትነት) ፡ በሰላማዊ ፡ ይዞታ ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ክሱ ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የሚቀርበውና ፡ ቅጣቱም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ ጽኑ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ የሚሆነው ፡ የሁከቱ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተባባሪነት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ መሣሪያ ፡ በያዙ ፡ ቍጥራቸው ፡ በርከት ፡ ባለ ፡ ሰዎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፮፻፶፩ ። በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ በማሰብ ፡—

(ሀ) የሌላውን ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ ወይም ፡ የመሬት ፡ ሁኔታ ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የሆነውን ፡ የውሃዎች ፡ አወራረድ ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፮፻፶፪ ። የወሰን ፡ ምልክቶችን ፡ ከስፍራቸው ፡ ስለ ፡ ማዛወርና ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መብትና ፡ በሀብቱ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ በማሰብ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነውን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ጥቅም ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡ የሕዝብን ፡ ወይም ፡ የግልን ፡ ንብረት ፡ ወሰን ፡ ለመለየት ፡ ለምልክት ፡ የተተከለውን ፡ መካለያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ምልክት ፡ ከስፍራው ፡ ያነሣ ፡ ያዘዋወረ ፡ ወይም ፡ በሐሰተኛ ፡ ስፍራ ፡ የተከለ ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ ምልክቱ ፡ እንዳይታወቅ ፡ አድርጎ ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ ሲሆን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ተግባሩ ፡ የተፈጸመው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐቅድ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

### ቍ ፡ ፮፻፶፫ ። መደበኛ ፡ ሁኔታ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ ዕቃ ፤ መሣሪያ ፤ እንስሳ ፡ ዛፍ ፤ ሰብል ፤ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ መሬትና ፡ ቤት ፡ ያፈረሰ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያሳጣ ፤ ወይም ፡ እንዳይገለግሉ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፮፻፵፱ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፮፻፶፬ ። ከባድ ፡ ሁኔታ ።

ክሱ ፡ በሕግ ፡ አስከባሪ ፡ በኩል ፡ የሚቀርበውና ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣቱም ፡ ቅጣት ፡ ከገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ጋራ ፡ በመጣመር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚሆነው ፡—

(ሀ) አድራጊው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በክፋት ፡ በጠባየ ፡ ወራዳነት ፤ ወይም ፡ በተለይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ አስቦ ፡ በመነሣት ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የተለየ ፡ ዐቅድ ፡ ባይኖረውም ፡ ተግባሩ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አድርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህም ፡ ጉዳት ፡ በዕቃዎች ፡ በሥራዎች ፤ በሕንጻዎች ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ በሆኑ ፡ ተክሎች ፡ ጉዳትን ፡ ያስከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ያፈረሰው ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ወይም ፡ እምነታዊ ፡ አምልኮ ፡ የሚደረግበትን ፡ ዕቃ ፤ ታሪካዊ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ወይም ፡ ጥበባዊ ፡ የሆነውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ መሣሪያ ፤ የሕዝብ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ተጥሎ ፡ ያለጠባቂ ፡ የሚኖረውን ፡ ሕንጻ ፡ ወይም ፡ ሐውልት ፤ ታሪካዊ ፡ የሆነውን ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ላገሩ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ የተቋቋሙትን ፡ የሞተር ፡ ዕቃዎች ፡ መኪናዎች ፡ የመኪና ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ተክሎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ በዛቻ ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡

ይልቁንም ፡ ሁከትና ፡ የአድማ ፡ ሽብር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞች ፡ ወይም ፡ በአሠሪዎቹ ፡ ፀለቤቶች ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፭ ። የተለዩ ፡ አሠራሮች ።**

አድራጊው ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ለማፍረስ ፤ ለመጉዳት ፤ ዋጋ ፡ ለማሳጣት ፡ ወይም ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በሚያደርስ ፡ እንደ ፡ ናዳ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ማዕበል ፡ ባለ ፡ ወይም ፡ በሚፈነዳ ፡ ወይም ፡ ቃጠሎ ፡ በሚያስነሣ ፡ አደገኛ ፡ መሣሪያ ፡ ተገልግሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለነዚሁ ፡ ጕዳዮች ፡ ከባድ ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰን ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፹፫ ።]

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በንብረት ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### በማታለል ፡ የተመሠረቱ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፮ ። ስለ ፡ አታላይነት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ብልጽግናን ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ ሲል ፡ አጭበርብሮ ፡ የራሱን ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ የሀብት ፡ ጥቅም ፡ በማድረግም ፡ ሆነ ፡ ፀለማድረግ ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ለማሠራት ፡ በማቀድ ፡—

(ሀ) እውነቱን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በመለወጥም ፡ ሆነ ፡ ሐሰተኛውን ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ አስመስሎ ፡ በማረጋገጥ ፡ ያልሆነውን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ በማታለል ፡ ዘዴ ፡ ተበዳዩን ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ በመምራት ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እርግጠኛው ፡ ነገር ፡ እንዳይገለጽ ፡ በተንኰል ፡ በመሸፈን ፡ ቅን ፡ ልቡናንና ፡ የልማዳዊ ፡ ደንብ ፡ ሥርዐት ፡ እንዳይደበቅ ፡ የሚከለክለውን ፡ ነገር ፡ የሰወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህ ፡ የተታለለው ፡ ሰው ፡ በደረሰበት ፡ ስሕተትና ፡ መታለል ፡ አታላዩ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የአታላይነት ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፭ ። ልዩ ፡ ሁናቴ ፤ የሚያዝበት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይኖር ፡ ቼክ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

(፩) እንዲሁም ፡ የሚያዝዝበት ፡ ገንዘብ ፡ አለመኖሩን ፡ ወይም ፡ የሚያዝዝበት ፡ ገንዘብ ፡ ማለቁን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ቼኩ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያዝዝበት ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ አለመኖሩን ፡ እያወቀ ፡ የፈረመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ አታላይነት ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ይቀጣል ።

(፪) አድራጎቱ ፡ የተፈጸመው ፤ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ቸልተኛነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊወሰን በት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፮ ። ስለ ፡ ከባድ ፡ አታላይነት ።**

ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ የሚሆነው ፡—

(ሀ) ወንጀለኛው ፡ ይህን ፡ ያታላይነት ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመው ፡ አድራጊው ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ ባገ ኘው ፡ ሥልጣን ፡ ሕዝብ ፡ የጣለበት ፡ እምነት ፡ መነሻ ፡ ሆኖት ፡ ይህ ፡ ሥል ጣኑ ፡ የማታለሉን ፡ ሥራ ፡ የሚያቃናለትና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ያታላይነት ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ የሚረዳው ፡ በመሆኑ ፡ የማታለሉ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰባቸውም ፡ በወንጀለኛው ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚገኙ ፡ ወይም ፡ የእርሱ ፡ እርዳታ ፡ የሚ ያስፈልጋቸው ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። [ቍ ፡ ፮፻፵፪ ። (ለ)]

(ሐ) አድራጊው ፡ የማኅበር ፡ የባንክ ፡ የንግድ ፡ ወይም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አክሲዮን ፤ የዕዳ ፡ ወረቀት ፤ ቦን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሰነድ ፡ በማ ውጣት ፡ ከሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ጥሪ ፡ የሚያደርግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ በመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ (አድሚኒስት ራሲዮን) ፡ ፀሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ጕዳይ ፡ ማከናወኛና ፡ ያገር ፡ ጥቅም ፡ መጠበቂያ ፡ በሆነ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ጕዳት ፡ በሚያደርስ ፡ ሁኔታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፯ ። የኢንሹራንስን ፡ ኩባንያ ፡ ስለ ፡ ማታለል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ብልጽግናን ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ በማሰብ ፡ የመንግሥት ፡ (የሕዝብ) ፡ ወይም ፡ የግል ፡ የሆነውን ፡ የኢንሹራንስን ፡ ማኅበር ፡ አታሎ ፡ ለመጠቀም ፡—

(ሀ) አደጋውን ፡ ለመከላከል ፡ በኢንሹራንስ ፡ የተረጋገጠለትን ፡ ለማግኘት ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ አደጋውን ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በውሉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ በደረሰው ፡ አደጋ ፡ ጠባይም ፡ ቢሆን ፡ ሊከፈለው ፡ በሚገባው ፡ በተወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በኩልም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ በማሳሳትም ፡ ቢሆን ፡ ኢንሹራንሱ ፡ እንዲከፈል ፡ የተወሰነበትን ፡ ጊዜ ፡ በማሳሳት ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ በመደበቅ ፡ በሐሰት ፡ በመግለጽ ፤ ይህን ፡ በመሰለው ፡ አድራጎት ፡ የኢንሹራንሱን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያታለለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፰ ። ልዩ ፡ የሆነ ፡ ማታለል ።

ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የማታለል ፡ ተግባር ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በተለወጠ ፡ ሰነድ ፡ አማካይነት ፡ የተሠራ ፡ ሲሆን ፡ ለያንዳንዱ ፡ የማታለል ፡ ሥራ ፡ ተለይተው ፡ የተቀመለከቱት ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ደንብ ፡ ተጣምሮ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፱ ። በሕዝብ ፡ እምነት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ብልጽግናን ፡ ለማግኘት ፡ ዐቅዶ ፡ መንፈስን ፡ እጠራልሃለሁ ፤ ጋኔን ፡ እስብልሃለሁ ፤ ደንቃራ ፡ እጥልልሃለሁ ፤ እጠነቍልልሃለሁ ፤ ዕድልህን ፡ እነግርሃለሁ ፤ ነገርህን ፡ እገልጽልሃለሁ ፡ ኮከብህን ፡ እቈጥርልሃለሁ ፤ ሕልም ፡ እፈታልሃለሁ ፤ የወደፊት ፡ ዕድልህን ፡ ዐውቅልሃለሁ ፤ ውስጥ ፡ እጅህን ፡ አነባለሁ ፤ ከሞተ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ አነጋግርሃለሁ ፤ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር ፡ አደርግልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በማታለልና ፡ በማሳመን ፡ ገንዘብ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፤ አሠራሩ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሚያስቀጣው ፡ ውጭ ፡ ሲሆን ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ የተደጋገመ ፡ ወንጀል ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፰፻፲፭ ።]

(፪) ይህ ፡ የማሳሳቱ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በማጭበርበር ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ የማታለል ፡ የወንጀል ፡ ሁኔታ ፡ ያስገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚህ ፡ ወንጀል ፡ የተደነገገው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። [ቍ ፡ ፮፻፶፮ ።]

ቍ ፡ ፮፻፸፪ ። አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ የማታለል ፡ ሥራዎች ።

በወስላታነት ፡ በማታለል ፡ የሌላ ፡ ሰውን ፡ አገልግሎት ፡ እንደ ፡ ማግኘት ፡ በመሰለ ፡ አሠራር ፡ ሆኖ ፡ የማይገባ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አነስተኞች ፡ የሆኑ ፡ የማታለል ፡ ሥራዎች ፡ በሠራ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ። [ቍ ፡ ፰፻፲፪ና ፡ ፰፻፲፫ ።]

ነገር ፡ ግን ፡ አድራጊው ፡ ያቀደውን ፡ ለማከናወን ፡ የማታለል ፡ ወይም ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ አቅዋም ፡ በሆኑ ፡ ዘዴዎች ፡ ተገልግሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለነዚሁ ፤ የተወሰኑት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙበታል ።

ቍ ፡ ፮፻፳፫ ። በግል ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ አመራር ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ግዴታ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲጠብቅ ፤ ወይም ፡ ሥራውን ፡ እንዲመራ ፡ አደራ ፡ ተቀብሎ ፡ የሌላውን ፡ ሀብት ፡ ጥቅም ፡ እንዲጠብቅ ፡ በእምነት ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ በተንኰል ፡ መንገድ ፡ በመለወጥ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ከመጠን ፡ አሳልፎ ፡ በመገልገል ፡ ወይም ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ተግባር ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ የደንብ ፡ መጣስ ፤ በሚጠብቀው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህን ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፤ ሰው ፤ የሀብት ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስራቱ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ ይወሰንበታል ።

ቍ ፡ ፮፻፳፬ ። ከባድ ፡ የሆነ ፡ ተንኰል ፡ ያለበት ፡ የሥራ ፡ አመራር ።

(፩) ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፤ ሐያ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መቀጮ ፡ የሚሆነው ፡—

(ሀ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፤ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ታማኝነት ፡ በተሰጠው ፡ በአንድ ፡ ሞግዚት ፡ ባንድ ፡ ጠበቃ ፤ በውል ፡ አዋዋይ ፡ ወይም ፡ በባንክ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፤ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ ወይም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ ተሰጥቶት ፡ በሹመት ፡ ያገኘውን ፡ ግልጽ ፡ ሥልጣን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍል ፡ ለሕዝብና ፡ ላገር ፡ ጥቅም ፡ በተቋቋመ ፤ የመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ ያንድ ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ በሆነው ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያደርስ ፡ ዐይነት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም፡ ሹም ፡ በመንግሥት ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚያ

ደርገውን ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፩፻፩።]

**ቍ ፡ ፮፻፶፮ ። ጥቅም ፡ ታገኛለህ ፡ በማለት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በመደለል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ የንብረትን ፡ ጥቅም ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ በማቀድ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ያለበትን ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የመንፈስ ፡ ቀላልነት ፤ የጣለበትን ፡ እምነት ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ አካሄድ ፡ ረገድ ፡ ዕውቀትና ፡ ልምድ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ትርፍ ፡ አገኛለሁ ፡ መስሎት ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ወረቀቶችን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦችን ፡ ካለው ፡ ቅርስ ፡ ጋራ ፡ የማይመዛዘን ፡ መሆኑን ፤ ይህም ፡ አሠራር ፡ ከባድ ፡ ኪሣራ ፡ እንደሚያመጣበት ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፯ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ንብረታቸውን ፡ የሚጎዳ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ በማቀድ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሕፃን ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ መንፈስ ፡ ቀላልነት ፤ በበዳዩ ፡ ላይ ፡ የጣለውን ፡ እምነት ፡ ወይም ፡ ልማድና ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡—

(ሀ) ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሰጠው ፡ እንዲያበድረው ፡ የመስጠት ፡ ቃል ፡ እንዲገባለት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲያረጋግጥለት ፡ ዕዳ ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡ እንዲያውቅለት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የንብረት ፡ ጥቅም ፡ እንዲያገኝ ፡ አንድ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሰጠው ፡ በመደለል ፡ ያነሣሣው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ እንዲተው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ ማስከፈያ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ የተቀበለና ፡ ለራሱ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፬ ።

## የሕሊናን ፡ ወይም ፡ የሰውነትን ፡ ችግር ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፯ ። አራጣ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የተበዳዩን ፡ ችግረኛነት ፤ የበታችነቱን ፤ የገንዘብ ፡ ችግሩን ፡ ወይም ፡ መንፈሰ ፡ ደካማነቱን ፤ የልማድ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ በጠባይና ፡ በመንፈስ ፡ ደካማ ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፤

(ሀ) በሕግ ፡ ከተፈቀደው ፡ ወለድ ፡ በላይ ፡ እንዲከፍለው ፡ አድርጎ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ የፈቀደለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ካበደረው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ እውነተኛ ፡ ተመዛዛኝነት ፡ የሌለውን ፡ ንብረት ፡ እንዲሰጠው ፡ ያደረገው ፡ ወይም ፡ ቃል ፡ ያስገባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ይህንኑ ፡ በማቀድ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ የአራጣ ፡ ገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነድ ፡ የገዛና ፡ በዚሁ ፡ የተገለገለ ፡ ወይም ፡ ይኸንኑ ፡ ለሌላ ፡ አስተላልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፰ ። ስለ ፡ መንጠቅ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ከወንበዴነት ፡ ሥራ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ የኀይል ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዛቻ ፡ ሥራ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በመፈጸም ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ እንዳይከላከል ፡ በማድረግ ፡ የማይገባውን ፡ የንብረት ፡ ጥቅም ፤ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስገኘት ፡ ሲል ፡ ገንዘቦችን ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸውን ፡ መብቶችን ፡ የሚሰጡ ፡ ወይም ፡ ዕዳ ፡ የሚያስቀሩትን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ጥቅም ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ እንዲሰጠው ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፴፫ ። ) እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ና፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፱ ። ስለ ፡ ማስፈራራት ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በዝምድና ፡ ወይም ፡ በፍቅር ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለመጉዳት ፡ የሚችለውን ፡ ወሬ ፡ ወይም ፡ ነገር ፡ እውነትም ፡ ቢሆን ፡ እንኳን ፡ እገልጻለሁ ፡ ወይም ፡ አስታውቃ

ለሁ ፡ በማለት ፡ አስፈራርቶ ፡ እንዳይናገርበት ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡ በንብረቱ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሰጠው ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፹ ። ከባድ ፡ ሁኔታ ።

አራጣ ፡ በመቀበል ፡ በመንጠቅ ፡ ወይም ፡ በማስፈራራት ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ የሚሆነው ፡—

(ሀ) በሕጉ ፡ መንፈስ ፡ ጥፋተኛው ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሞያ ፡ ሥራው ፡ አድርጎ ፡ ይዞአል ፡ በሚያሰኝ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ከባለሥልጣን ፡ የተሰጠውን ፡ ፈቃድ ፡ ሹመት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ይህን ፡ ወንጀል ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህንንም ፡ የወንጀል ፡ ሥራውን ፡ የሚፈጽመው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ መንፈሰ ፡ ደካማ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለመለየት ፡ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ ለመጉዳት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በአሠራሩ ፡ ወይም ፡ ደጋግሞ ፡ በመዛቱ ፡ ተበዳዩ ፡ የመከሠር ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስበት ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ እንዲደርስ ፡ ለማሰብ ፡ ሲችል ፡ ወንጀሉን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## በንግድና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ግዙፍ ፡ ባልሆኑ ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ቍ ፡ ፮፻፹፩ ። በሌላ ፡ ሰው ፡ ታማኝነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ ወይም ፡ ለመጉዳት ፡ በማቀድ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ታማኝነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ ወይም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ በሚያውቀው ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ አድርጓል ፡ በማለት ፡ በታማኝነቱ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ ደንብ ፡ በሐሰት ፡ የመወንጀልን ፡ ቅጣት ፡ ከሚወስነው ፡ ድንጋጌ ፡ ጋራ ፡ አይደራረብም ። [ቍ ፡ ፭፻፹ ፡ (፪) ።]

BACK



## ቍ ፡ ፲፻፷፪ ። ጉዳትን ፡ የሚያደርሱ ፡ ሐሰተኞች ፡ መግለጫዎች ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ያንድ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፤ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበርን ፡ ጕዳይ ፤ በመሥራችነት ፡ በማኅበረተኛነቱም ፡ በሥራ ፡ አስኪያጅነቱም ፡ በዲሬክተርነቱም ፡ ወይም ፡ በሒሳብ ፡ አጣሪነቱ ፡ በባለሥልጣንነቱ ፡ በስተዳደር ፡ (በአድሚኒስትራሲዮን) ፤ አባልነቱ ፡ ወይም ፡ በመርማሪነቱ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያውቅ ፡ ሲሆን ፡ ሁኔታውን ፡ ለሕዝብ ፡ በሚሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ላይም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለማኅበሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ በሚሰጠው ፡ የሒሳብ ፡ አቀራረብ ፡ ወይም ፡ በራፖሩ ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እውነትን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ራፖር ፡ የሰጠ ፤ ያቀረበ ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ እንዲያቀርብና ፡ እንዲገልጽ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፲፻፷፫ ። የማይገባ ፡ ውድድር ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የንግድ ፡ ተወዳዳሪው ፡ የሆነውን ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለመጉዳትና ፡ ለራሱ ፡ ለመጠቀም ፡ ሲል ፡ በንግድ ፡ ረገድ ፡ ሊጠበቅ ፡ የሚገባውን ፡ የቅን ፡ ልቡና ፡ ሥርዐት ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ በአሳሳች ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ የማይገባ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ በማድረግና ፡ ይልቁንም ፡—

(ሀ) የሌላውን ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ዕቃውን ፡ ወይም ፡ የሥራውን ፡ አያያዝና ፡ የንግዱን ፡ እርምጃ ፡ በመንቀፍ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ ላይ ፡ አሳሮ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሐሰተኛና ፡ አሳሳች ፡ የሆነ ፡ ወሬ ፡ ያወራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በሌላው ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ መሰናክል ፡ እንዲፈጠር ፡ በንግድ ፡ ዕቃው ፡ የሥራው ፡ ፍሬ ፡ በሚያስገኘው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የፋብሪካ ፡ ዕቃው ፡ ወይም ፡ በንግዱ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ዝብርቅ ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ዕቃው ፡ የሌለውን ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ብርታት ፡ ለማሳመን ፡ ሲል ፡ እውነት ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ አሳሳች ፡ የሥራ ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ መለያ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ ማርክ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መጠሪያ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) የንግድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የሌላው ፡ ባለቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ወኪሎችና ፡ ረዳቶች ፡ ተገቢ ፡ ተግባራቸውን ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ግዴታቸውን ፡ እንዳይፈጽሙ ፡ ወይም ፡ የፋብሪካውን ፡ የሥራውን ፡ አካሄድ ፡ ያሠራሩን ፡ ዘዴ ፡ ሥራው ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅምና ፡ ፍሬ ፡ ያቋቋሙንና ፡ የድርጅቱን ፡ ምስጢር ፡

በድንገት ፡ እንዲደርሱበት ፡ ወይም ፡ እንዲገልጹ ፡ የማይገባቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ በመደለል ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎቱ ፡ ያገኘውን ፡ ወይም ፡ በድንገት ፡ የደረሰበትን ፡ ምስጢር ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ለሕዝብ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ የተጠቀመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፬ ። የፋብሪካ ፡ ምልክቶችን ፡ (ማርኮችን) ፡ የመጡበትን ፡ ስፍራ ፡ ማመልከቻ ፡ ጽሑፎችን ፡ ሥዕሎችንና ፡ ዐይነቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ሕዝብን ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ ለመምራት ፡ ሲል ፡ በንግዱ ፡ ዕቃም ፡ ሆነ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የፋብሪካ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ በእንዱስትሪና ፡ በእርሻ ፡ መኪናዎችና ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የተሠሩበትን ፡ የመጡበትን ፡ አገር ፡ ዐይነታቸውንና ፡ ማርካቸውን ፡ ለመለየት ፡ በላያቸው ፡ የተለጠፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመጠቅለያቸውና ፡ በማጥናቸው ፡ ላይ ፡ የተደረጉትን ፡ ምልክቶች ፡ የለወጠ ፡ ያስመሰለ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ ለራሱ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተለወጡ ፡ በማስመሰል ፡ የተሠሩ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የተደረጉ ፡ መሆናቸውን ፡ እያወቀ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምልክት ፡ የተለጠፈባቸውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የሸጠ ፤ ለሽያጭ ፡ ያቀረበ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የላከ ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አስመጥቶ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ያስገባ ፡ ያደለ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ እጅ ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሐሰተኛ ፡ ምልክት ፡ ያለባቸው ፡ በእጁ ፡ የሚገኙት ፡ የፋብሪካ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ለመግለጽ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በእንዱስትሪ ፡ ንድፎችና ፡ ሥዕሎች ፡ ወይም ፡ በምስክር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የተጻፉ ፡ ወይም ፡ ባገር ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ በሚገባ ፡ የተጠበቁትንና ፡ የተመዘገቡትን ፡ ከዕውቀት ፡ የመነጩትን ፡ ጥበቦች ፡ ወይም ፡ የተመሰከረላቸውን ፡ የሥራ ፡ ዐቅዶች ፡ የተከለከለውን ፡ ሥራ ፡ የሠራባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፮፻፸፭ ። የድርሰት ፡ መጻሕፍትን ፡ ወይም ፡ የጥበብ ፡ ሥራዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) በማተም ፡ ወይም ፡ ቅርጽ ፡ በመሥራት ፡ የተጻፉትን ፡ ድርሰቶች ፡ በፎቶግራፍ ፡ ወይም ፡ በፎቶግራቪር ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ የማባዣ ፡ ጥበብ ፡ የተዘጋጁትን ፡ ድርሰቶች ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ የሙዚቃ ፡ የሥዕል ፡ ወይም ፡ የፕላስቲክ ፡ ድርሰቶች ፡ ወይም ፡ በደራሲው ፡ መብት ፡ የተጠበቁትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ የዕውቀት ፡ ሥራዎች ፡ በከፊልም ፡ ቢሆን ፡ በሐሰተኛ ፡ ለውጦ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ያበዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛ ፡ ቅጂ ፡ የተለወጠውን ፡ ጥበባዊ ፡ ድርሰት ፡ የሸጠ ፤ ለሽያጭ ፡ ያቀረበ ፤ ወደ ፡ አገር ፡ ያስመጣ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የላከ ፡ ያከፋፈለ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ እጅ ፡ እንዲዘዋወር ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የከስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፸፮ ። የተከለከሉትን ፡ ድርሰቶች ፡ ስለ ፡ ማሳየት ፡ ወይም ፡ ማሠራት ።**

በደራሲው ፡ መብት ፡ የተጠበቁትን ፡ የመጻሕፍት ፡ ድርሰት ፡ ጥበቦች ፡ የሙዚቃ ፡ ድርሰቶች ፡ ሲኒማዎች ፡ ዲስኮች ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሌሎች ፡ ጥበባውያን ፡ ነገሮች ፡ ያለባለቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ለሕዝብ ፡ የገለጸና ፡ በአደባባይ ፡ ያሳየ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

የከስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፸፯ ። የከስ ፡ አቤቱታ ፡ መብት ።**

እነዚህን ፡ ወንጀሎች ፡ የሠሩት ፡ እንዲከሰሱና ፡ እንዲቀጡ ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ የከስ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ በአላቸው ፡ በተበደሉት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በሞያ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፸፰ ። የተለዩ ፡ ወንጀሎች ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ አንዱን ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ ብሎ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የመለወጥ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ ልዩነት ፡ ያላቸውን ፡ አርቶች ፡ ማርኮች ፡ ወይም ፡ ምልክቶች ፡ በማበላሸት ፡ የአታላይነትን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ሲል ፡ ያደረገው ፡ ከሆነ ፡ የዚህ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ፡ በተደራራቢነት ፡ ይፈጸማል ። [ቍ ፡ ፰፭ ።]

BACK



**ቍ ፡ ፮፻፵፱ ። ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ።**

ከወንጀሉ ፡ ቅጣትና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ካለው ፡ የካሣ ፡ አከፋፈልም ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የተለወጡትን ፡ ዕቃዎች ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ድርሰቶችና ፡ እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አፈጻጸም ፡ የተገኘው ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋና ፡ ወንጀለኛው ፡ የተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ እንዲወረስ ፡ ይፈርዳል ።

ስለ ፡ ፍርዱም ፡ መግለጫ ፡ አሰጣጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ እንዲታወጅ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## በክስ ፡ አቀራረብ ፡ በፍርድ ፡ በተያዘ ፡ ነገርና ፡ በአከሣሥር ፡ ጉዳይ ፡ አሠራር ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ።

**ቍ ፡ ፮፻፶ ። በአጭበርባሪነት ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ ስላለመቻል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ደብቆ ፡ ለመፈጸም ፡ አለመቻሉን ፡ ወይም ፡ ሊፈጽም ፡ አለመፍቀዱን ፡ ሲያውቅ ፡ ግዴታ ፡ ገብቶ ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፤ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፩ ። ስለ ፡ መክሰር ።**

(፩) አንድ ፡ ባለዕዳ ፡ ጥፋተኛ ፡ በሚያሰኝ ፡ መንፈስ ፡ ቀላልነት ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነዘኅላልነትና ፡ ቸልተኛነት ፡ በማድረግ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ የማይቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በመፈለግ ፡ ከሣራ ፡ እንዲደርስበት ፡ በሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ አያያዝ ፡ ጉድለትም ፡ ሆነ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ጉዳይ ፡ ጋራ ፡ የማይመዛዘን ፡ ወጪ ፡ በማድረግና ፡ ገንዘቡን ፡ በማባከን ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ዕዳ ፡ በመግባት ፡ ድንገተኛ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ በመሞከር ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ የመክሠሩን ፡ ጉዳይ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ እንዲባባስ ፡ አድርጎ ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሀብት ፡ ማጣቱን ፡ ወይም ፡ መክሠሩን ፡ የሚገልጽ ፡ ማረጋገጫ ፡ አቅርቦ ፡ በሕግ ፡ እንዲታወቅለት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ስሙ ፡ ያልተጻፈ ፡ ባለዕዳ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ወን

BACK



ጀል ፡ ሠርቶ ፡ ሲገኝ ፡ ክሱ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ በሀብት ፡ ጠያቂው ፡ (በአሳዳሪው) ፡ አማካይነት ፡ ሆኖ ፡ ይኸውም ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርበው ፡ ባለዕዳው ፡ ሀብት ፡ ማጣቱ ፡ እንዲታወቅለት ፡ ካመለከተበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጻፉት ፡ ሥራዎች ፡ አንደኛውን ፡ እንዲፈጽም ፡ አነሣሥቶ ፡ በመንፈስ ፡ ቀላልነት ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲደርስበት ፡ ባለዕዳውን ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ወደዚህ ፡ መንገድ ፡ የመራ ፡ ወይም ፡ አላገባብ ፡ አራጣ ፡ በመቀበል ፡ ዐይነት ፡ የተጠቀመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ አይፈቀድለትም ።

ቍ ፡ ፮፻፷፪ ። በአጭበርባሪነት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) አበዳሪዎች ፡ (ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው) ፡ ሰዎች ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስባቸው ፡ በማሰብ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ገቢውን ፡ (በእጁ ፡ ያለውን) ፡ ገንዘብ ፡ ቀንሶ ፡ (አጕድሎ) ፡ ኪሣራ ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑን ፡ የገለጸ ፡ ባለዕዳ ፡—

(ሀ) የራሱ ፡ ሀብት ፡ የነበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ በመሸጥም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማጥፋት ፡ ወይም ፡ በማበላሸት ፡ ዋጋ ፡ እንዳያወጡ ፡ ወይም ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆኑ ፡ በማድረግ ፡ የሀብቱ ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ አንዳንድ ፡ ዕቃዎች ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ግዙፍ ፡ አድራጎት ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የራሱ ፡ ሀብት ፤ ከሆኑት ፡ ዕቃዎች ፡ ውስጥ ፡ በመቀነስ ፡ በመሰወር ፡ ዕዳ ፡ እንዳለበት ፡ አድርጎ ፡ የባለዕዳነትን ፡ ሰበብ ፡ በማቅረብ ፡ ወይም ፡ የሌለበትን ፡ ያለበት ፡ አስመስሎ ፡ በማመንና ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ አለብህ ፡ ብሎ ፡ እንዲጠይቀው ፡ በማነሣሣት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ የማስመሰል ፡ ዘዴ ፡ በእርግጥ ፡ ካለው ፡ ሀብቱ ፡ ላይ ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆነ ፡ ንብረት ፡ እንዳለው ፡ አስመስሎ ፡ በማሳየት ፡ ይልቁንም ፡ ትክክለኛ ፡ ባልሆነ ፡ የሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ዘዴ ፡ የተንኰል ፡ ድብዳቤ ፡ በማቅረብ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ በማሳየት ፡ እውነት ፡ አስመስሎ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ያሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስና ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ጥፋቱ ፡ ከፍተኛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ይህም ፡ ተግባሩ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ የሕዝብን ፡ ወይም ፡ ያገርን ፡ ጥቅም ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ በሆነ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተውም ፡ ጉዳት ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፡ ፍርዱ ፡ ጽኑ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ሊወሰን ፡ የሚችል ፡ ነው ፤

BACK



(፪) እንዲሁም ፡ ባለገንዘቦችን ፡ ለመጉዳት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ የፈጸመ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፫) አድራጊው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ የማታለልን ፡ በደል ፡ የሚያቋቁም ፡ አድራጎት ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ አታላይነት ፡ ወንጀል ፡ የተወሰ ነው ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌ ፡ ከዚህኛው ፡ ጥፋት ፡ ጋራ ፡ ተጣምሮ ፡ ሊፈጸምበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። በተያዘ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የአጭበርባሪነት ፡ ወንጀል ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

(፩) አንድ ፡ ባለዕዳ ፡ ተከሶ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ በዳኝነት ፡ ተወስኖበት ፡ ንብረት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በጽሑፍ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ (በአበዳሪ ዎች) ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ለማድረግ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በግዙፍ ፡ አድራጎትም ፡ ሆነ ፡ በተንኰል ፡ ዘዴ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ አንደኛውን ፡ በመፈጸም ፡ በእጁ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ እንዲቀነስ ፡ ያደ ረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ (አበዳሪዎች) ፡ እንዲጎዱ ፡ ባለዕዳውን ፡ በዚህ ፡ አድራጎት ፡ የረዳ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። በመያዣ ፡ ስም ፡ የተቀመጡትን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የተያዙ ትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፤ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) አንድ ፡ ባለዕዳ ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ ዐቅዶ ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ (በአበዳሪው) ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስበት ፡ ለማድረግ ፡ ሲል ፡ ገንዘብ ፡ አበዳሪው ፡ በይዞታ ፡ መብት ፡ በሪም ፡ በወለድ ፡ መጠቀሚያ ፡ ወይም ፡ በመያዝ ፡ መብት ፡ የወሰደውን ፡ የባለዕዳውን ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ላይ ፡ የሰረቀ ፡ የሸጠ ፤ ያጠፋ ፡ ያበላሸ ፡ ዋጋ ፡ ያሳጣ ፡ ወይም ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ (በአበዳሪው) ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ በማሰብና ፡ የዚህኑ ፡ ዐይነት ፡ ተንኰል ፡ በማቀድ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፩ ። በፍርድ ፡ የተያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ማስከፈል ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ አበዳሪዎች ፡ ለመ ጕዳት ፡ በማሰብ ፡ በፍርድ ፡ ትእዛዝ ፡ የተከበረውን ፡ ወይም ፡ የተያዘውን ፡ በከ ማራ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገበውን፡ወይም ፡ የይዞታ ፡ መብት ፡ በተሰጠበት ፡ ሊስት ፡ ውስጥ ፡ ተቈጥሮ ፡ የተጻፈውን ፡ ዕቃ ፡ ያላገባብ ፡ የወሰደ ፡ ወይም ፡ ይህ ንኑ ፡ ዕቃ ፡ ያጠፋ ፡ ያበላሸ ፡ ዋጋ ፡ ያሳጣ ፡ ወይም ፡ ካገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሀብት ፡ ጠያቂዎቹ ፡ (አበዳሪዎቹ) ፡ እንዲጎዱ ፡ በማቀድ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በእስራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፫) ወንጀሉ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ጕዳትን ፡ የሚያስከትል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ጕዳትን ፡ ስለ ፡ ማድረስ ፡ ከተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ጋር ፡ በተደራቢነት ፡ ተፈ ጻሚ ፡ አይሆንም ። [ቍ ፡ ፬፻፴፪ ። (ለ) ።]

ቍ ፡ ፮፻፷፪ ። የማይገባ ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ ማስገኘት ።

መክሠሩ ፡ በፍርድ ፡ የታወቀ ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ ስለ ፡ ማጣቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ማረጋገጫ ፡ ያቀረበ ፡ ባለዕዳ ፡ ሊከፍል ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ሆኑ ፡ ብሎ ፡ አንዳንዶ ቹን ፡ አበዳሪዎች ፡ ለመጥቀምና ፡ አንዳንዶቹን ፡ ለመጕዳት ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይልቁንም ፦

(ሀ) የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሰውን ፡ ዕዳ ፡ በመክፍል ፡ ወይም ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ የደረሰውን ፡ ዕዳ ፡ በዝርዝር ፡ ወይም ፡ የተለመደ ፡ የዕዳ ፡ መክፈያ ፡ የሆ ነውን ፡ በመክፈል ፡ ፋንታ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አንድ ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፍል ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ እንዲ ሰጥ ፤ ሳይገደድ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ይህን ፡ ማረጋገጫ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ ሊከ ፍል ፡ የማይገባውን ፡ ዕዳ ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፫ ። የድምፅ ፡ ብልጫን ፡ ለማግኘት ፡ መደለያ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ከሚጠይቁት ፡ ባለገንዘቦች ፡ አንደኛው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ እንዲሰጥለት ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ስምምነትን ፡ እንዲያስገኝ ለት ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብማለት ፦

(ሀ) በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ እንዲደግፈው ፡ ለዚህ ፡ ለተባለው ፡ ገንዘብ ጠያቂ ፡ ወይም ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ወኪል ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ በመስጠት ፡ እንዲደግፈው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የኪሣራ ፡ ማረጋገጫ ፡ መሥሪያ፡ ቤት ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ (የአድሚኒስትራሲዮን) ፡ አካል ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሚደግፍ ፡ ድምፅ ፡ እንዲሰጥለት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባለውን ፡ በማቀድ ፡—

(ሀ) ለዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተግባር ፡ እንዲከናወን ፡ የረዳ ፤

(ለ) እንደነዚህ፡ ያሉትን ፡ ጥቅሞች ፡ ወይም ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ የሚሰጥ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፹፰ ። የስምምነት ፡ ድምፅ ፡ አጭበርብሮ ፡ ስለ ፡ ማግኘት ።</u>

(፩) የስምምነት ፡ ጊዜ ፡ ማራዘሚያ ፡ ቀጠሮ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ስምምነት ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ አበዳሪዎች ፡ የሒሳብ ፡ መርማሪውን ፡ ወይም ፡ የክፍሉን ፡ ባለሥልጣን ፡ በሀብትና ፡ በመደለያ ፡ ወደ ፡ ተሳሳተ ፡ መንገድ ፡ በመምራት ፡ ያታለለ ፡ ባለዕዳ ፡ በተለይም ፡ በሒሳብ ፡ ማሳሳት ፡ ዘዴ ፡ አስመስሎ ፡ በሐሰት ፡ በተጻፈ ፡ የመልክት ፡ ደብዳቤ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በተለወጠ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ አማካይነት ፡ ያሳሳተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ለባለዕዳው ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፡ እንዲከናወን ፡ ለማቃናት ፡ የረዳው ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፹፱ ። በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።</u>

(፩) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ወንጀሎች ፡ አንደኛው ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ባንድ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚወሰነው ፡ ይህን ፡ ወንጀል ፡ በሠራው ፡ በማኅበሩ ፡ ዲሬክተር ፤ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ ለማካሄድ ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ በማኅበረተኛው ፡ የአስተዳደር ፡ አባል ፡ በሆነው ፡ ወይም ፡ የመቈጣጠርና ፡ የሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ አባል ፡ በሆነው ፡ በማኅበሩ ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) አስፈላጊ ፡ ሆኖም ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩን ፡ ስለ ፡ ማገድና ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፬፻፵፯ ።]

## ፲፫ኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።

## የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ኮንትራቫንሲዮን) ።

## ፭ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ጠቅላላ ፡ ክፍል ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### ተቀጭነትንና ፡ ደንብ ፡ መተላለፍን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚደርስበት ፡ ወሰን ።

**ቍ ፡ ፳፻፳፯ ። ጠቅላላዎቹን ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦች ፡ ስለ ፡ መመልከት ።**

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በማይናገሩበት ፡ ወይም ፡ ተቃራኒ ፡ ጽሑፎች ፡ በማይገኙባቸው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ተለዩ ፡ ባልተገለጹበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ ተላላፊነት ፡ ሥራ ፡ (በኮንትራቫንሲዮን) ፡ የነገሩን ፡ ዐይነት ፡ የሕጉን ፡ አሳብና ፡ ግብ ፡ በመመልከት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍል ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦችና ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፲ ፡ (፱) ።]

**ቍ ፡ ፳፻፳፰ ። ስለ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የታወጀው ፡ ደንብ ፡ ትእዛዝና ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያዝዘውን ፡ ወይም ፡ የሚከለክለውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመተላለፍ ፡ ወይም ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ተግባር ፡ ሳይፈጽም ፡ በመቅረት ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ዐዋጅ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደንብ ፡ ተላላፊ ፡ ሆኖ ፡ ከዚህ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በተመለከተው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ። [ቍ ፡ ፳፻፴፱ ፡ እስከ ፡ ፳፻፹፫ ።]

**ቍ ፡ ፳፻፳፱ ። በጕዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡ የሕጉ ፡ ተፈጻሚነት ።**

(፩) ስለ ፡ ሕግ ፡ መሠረትነት ፡ እንደተባለው ፡ በዚህ ፡ የሕግ ፡ ተላላፊነት ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ በግልጽ ፡ የተነገሩት ፡ የደንብ ፡ ተላላፊነት ፡ ሥራዎች ፡ ብቻ ፡ ሊያስቀጡ ፡ ይችላሉ ።

ሊያስቀጡ ፡ የሚችሉትም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፪ ። ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ና ፡ ፪ ።]

እነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ለተደረገው ፡ ሥራ ፡ በግልጽ ፡ በሚበልጥ ፡ የሚያስቀጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ባልኖሩ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። አንድ ፡ በሆነ ፡ ሥራም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ በደንብ ፡ ተላላፊነት ፡ ሕግ ፡ (ኮንትራቫንሲዮን) ፡ በ፩ኛው ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በ፪ቱ ፡ አይቀጣም ። [ቍ ፡ ፪ ፡ (፩) (፪) ።]

(፪) የደንብ ፡ ተላላፊነት ፡ ሥራዎች ፡ (ኮንትራቫንሲዮን) ፡ የሚያስቀጡት ፡ ስላለፈው ፡ ቅጣት ፡ የቅጣት ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሳይኖር ፡ ሁልጊዜም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ በተፈጸሙበት ፡ ጊዜ ፡ ጸንተው ፡ ያሉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመከተል ፡ ነው [ቍ ፡ ፭ ።]

እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከጸኑበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በተመለከቱት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፮፻፺፫ ። በሰው ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡ የሕጉ ፡ ተፈጻሚነት ።

የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ሥራዎች ፡ (ኮንትራቫንሲዮን) ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖር ፡ በአጥፊዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እኩልነት ፡ ባለው ፡ አደራረግ ፡ ይፈጸማሉ ። [ቍ ፡ ፬ ።]

ቍ ፡ ፮፻፺፬ ። በቦታ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ የሕጉ ፡ ተፈጻሚነት ።

(፩) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ አድራጊው ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ በፈጸመበት ፡ ወይም ፡ ሊፈጽማቸው ፡ ግዴታ ፡ በነበረበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተሠሩ ፡ ይቈጠራሉ ።

የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ነገር ፡ የሚወሰነው ፡ በጠቅላላው ፡ በአገሩ ፡ ሕግ ፡ የመዳኘት ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፲፩ ።]

(፪) በኢትዮጵያ ፡ የተሠሩት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ አጥፊው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁልጊዜም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጥባቸዋል ። ለነዚሁ ፡ ሥራዎች ፡ ፍርዱ ፡ በወኪል ፡ እንዲፈረድ ፡ የማድረግ ፡ ወይም ፡ እጅን ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠት ፡ ሥራዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ። [ቍ ፡ ፲፪ና ፡ ፳፩ ።]

(፫) በውጭ ፡ አገር ፡ የሚደረጉት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋም ፡ የሠራቸው ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ላይ ፡ የተሠሩ ፡ እንኳን ፡ ቢሆኑ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ አያስቀጡም ። [ቍ ፡ ፲፫ ።]

በውጭ ፡ አገር ፡ ሳለ ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ እነዚህን ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የፈጸማቸው ፡ ሲሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ አይከሰስባቸውም ። [ቍ ፡ ፲፬ ።]

(፬) በኢትዮጵያ ፡ የወታደር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የወታደራዊን ፡ ደንብ ፡ ብቻ ፡ መተላለፍ፡የተባሉት፡ነገሮች ፡ የተደረጉት፡በኢትዮጵያ፡ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቢሆኑም ፡ የኢትዮጵያ፡ሕግ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ በመከተል ፡ ፍርዱ ንና ፡ ቅጣቱን ፡ የሚወስኑት ፡ የጦር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፯፻፴፯ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ አድራጊው ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተቀጥቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ ቅጣት ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፮፻፺፭ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሰጠው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ።

ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ወንጀሎች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜ ፡ ያድራጊውን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ በመመርመር ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፡ አስተያየት ፡ ሲደረግ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠባቸው ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ቅጣቶች ፡ በዚህ ፡ አስ ተያየት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ። [ቍ ፡ ፳፪ ። ]

በደንብ ፡ ተላላፊነት ፡ የሚፈርደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጣቶችን ፡ ለመወሰን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉትን ፡ የአድራጊውን ፡ የቀድሞ ፡ ሥራዎችና ፡ የሚያስከትሉትን ፡ የሕግ ፡ ውጤቶች ፡ መመርመር ፡ የለበትም ።

# ምዕራፍ ፡ ፪ ።

# ስለ ፡ ተቀጪነት ።

## ቍ ፡ ፮፻፺፮ ። የሚያስቀጡ ፡ ተግባሮችና ፡ የሚቀጡ ፡ ሰዎች ።

(፩) በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ ደንብን ፡ ለመተላለፍ ፡ የሚደረጉ ፡ የመዘጋጀትና ፡ የሙከራ ፡ ሥራዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ደረጃዎች ፡ አያስቀጡም ፤ የሚያስቀጣው ፡ የተፈጸመው ፡ የደንብ ፡ የመተላለፍ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ለደንብ ፡ መተላለፍ ፡ የሚደረገው ፡ ማነሣሣት ፡ አባሪነትና ፡ ረዳ ትነት ፡ አያስቀጣም ። የሚቀጡት ፡ ደንብ ፡ ተላላፊው ፡ ወይም ፡ ተላላፊዎች ፡ ብቻ፡ናቸው ፤ እያንዳንዱ ፡ የሚቀጣው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በመተባበሩ ፡ ሳይ ሆን ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፴፪ ። ]

(፫) ስለ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ የተሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መንፈስ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱት ፡ ላይም ፡ ይፈጸማሉ ። [ቍ ፡ ፶፪ ። ]

(፬) በጋዜጣ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በጽሑፍ ፡ በሚደረግ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ረገድ ፡ ስለሚሆን ፡ የጥፋት ፡ ተካፋይነት ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተደነገገው ፡ መሠ ረት ፡ ይፈጸማል ። [ቍ ፡ ፵፩ ፡ እስከ ፡ ፵፯ ። ]

ቊ ፡ ፩፻፺፯ ። የሚያስቀጡ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) በጭራሽ ፡ አላፊነት ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚቀጡ ፡ አይደሉም ። [ቊ ፡ ፵፰ ። ]

(፪) ማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ደንብን ፡ ተላልፎ ፡ ከተገኘ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ የተጸፉት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ። ሕጉ ፡ በቸልተኝነት ፡ ነገር ፡ ቅጣት ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ ካልተናገረ ፡ በቀር ፡ አስቦ ፡ ወይም ፡ ካለመጠንቀቁ ፡ የተነሣ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ ደንብን ፡ ተላልፎ ፡ ከተገኘ ፡ ይቀጣል ። [ቊ ፡ ፶፯ ፡ እስከ ፡ ፶፱ ። ]

(፫) በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ረገድ ፡ አላፊነትና ፡ ተቀጭነት ፡ የግል ፡ ናቸው ። በኅብረት ፡ ለመክሰስና ፡ ለማስቀጣት ፡ አይቻልም ።

ቊ ፡ ፩፻፺፰ ። ነገርን ፡ ስለ ፡ ማጣራት ፡ የሚሰጡ ፡ ሁኔታዎች ።

የጕዳዩ ፡ መሠረታውያን ፡ ነገሮች ፡ ይህን ፡ የሠራ ፡ እገሌ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ የጥፋቱን ፡ ባለቤት ፡ ከአላፊነት ፡ በጭራሽ ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነው ፡ ካልተገኙ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሊጣራ ፡ የማይችል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥራዎች ፡ የተደነገጉት ፡ ልዩ ፡ ምርመራና ፡ ደንበኛ ፡ ምርመራዎች ፡ አይታዘዙም ። [ቊ ፡ ፵፩ና ፡ ፶፭ ። ]

ቊ ፡ ፩፻፺፱ ። ይቅርታዎችና| ፡ ቅጣትን ፡ ማቃለል ።

(፩) በሕግ ፡ ስለ ፡ ተፈቀዱ ፡ ተግባሮችና ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ የሹመት ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ተገቢ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መፈጸም ፡ እንደዚሁም ፡ ስለ ፡ ፍጹም ፡ አስገዳጅነት ፡ ስለ ፡ ግዴታና ፡ ስለ ፡ ተገቢ ፡ መከላከል ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ይሆናሉ ። [ቊ ፡ ፷፬ ፡ ፷፭ ፡ ፷፯ ፡ ፸፩ ፡ ፸፫ ፡ ፸፬ ። ]

ነገሩ ፡ እንዲያው ፡ በመጠኑና ፡ በግዴታው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ከተገቢው ፡ መከላከል ፡ አልፎ ፡ የተገኘ ፡ አስገዳችነት ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በመደቡ ፡ አጥፊው ፡ የሚቀጣ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ መጠን ፡ ቅጣቱን ፡ ይቀንስለታል ። [ቊ ፡ ፩፻፹፫ ። ]

(፪) ከሥልጣኑ ፡ ወሰን ፡ ሳያልፍ ፡ ለሚሠራ ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ በመታዘዝ ፡ ብቻ ፡ የደንብን ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ከተቀበለው ፡ ትእዛዝ ፡ አልፎ ፡ ያልሠራ ፡ ከሆነ ፡ የአዛዥና ፡ የታዛዥ ፡ ሥርዐት ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ አይቀጣም ።

ትእዛዝ ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዙ ፡ ከአሳቡ ፡ በላይ ፡ ባልሆነበት ፡ መጠን ፡ ሙሉ ፡ አላፊው ፡ እርሱ ፡ ነው ። [ቊ ፡ ፷፱ ።]

ነገር ፡ ግን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ ከተቀበለው ፡ ትእዛዝ ፡ አልፎ ፡ ዐውቆና ፡ ፈቅዶ ፡ ለሠራው ፡ ሥራ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፫) ደንብን ፡ መተላለፍ ፡ ያስቀጣል ፡ ብሎ ፡ ገልጾ ፡ ሕግ ፡ በወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተጎጂው ፡ መፍቀድ ፡ ቅጣቱን ፡ አያስቀርም ። [ቍ ፡ ፳፮ ።]

**ቍ ፡ ፯፻ ። ስሕተት ።**

የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሕግ ፡ መኖሩን ፡ አላወቅሁም ፡ ወይም ፡ ሕጉን ፡ በማሳሳት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከቅጣት ፡ ለመዳን ፡ መከላከያ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ። [ቍ ፡ ፹፩ ።] አድራጊው ፡ በጭራሽ ፡ ሳያውቅና ፡ ሳይፈቅድ ፡ የተሠራ ፡ የገቢር ፡ ስሕተት ፡ ለመሆኑ ፡ ለማስረዳት ፡ የቻለ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይቀጣም ። [ቍ ፡ ፹ ።]

**ቍ ፡ ፯፻፩ ። የሚያቀሉና ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ጥፋተኛ ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ በሚያቀሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሠርቶት ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አግባብ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱን ፡ በማቅለልም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የቅጣቱን ፡ ዐይነት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጻፈው ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ የማቃለሉን ፡ ሁኔታ ፡ ያስብለታል ። [ቍ ፡ ፹፱ ፡ ፺ ፡ ፯፻፳፫ ።]

(፪) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሕጉ ፡ ቢተቀበላቸው ፡ በሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሠርቶት ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ መጠን ፡ ቅጣቱን ፡ ያከብዳል ። ]ቍ ፡ ፺፩ና ፡ ፺፪ ፡ ፯፻፳፬ ።]

(፫) ቅጣትን ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ ቅጣትን ፡ ለማክበድ ፡ ወይም ፡ ለማቅለል ፡ ከነገሩ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ለመገኘት ፡ የሚችሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በሚገባ ፡ ያመዛዝናል ። [ቍ ፡ ፺፬ ።]

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ቅጣቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## የሚፈጸሙ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ዋና ፡ ቅጣቶች ።

**ቍ ፡ ፯፻፪ ። ደንበኛ ፡ በሆኑት ፡ በወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡ ስላለመሥራት ።**

(፩) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ መደበኛ ፡ ወንጀሎች ፡ ሥራ ፡ በተመለከቱት ፡ ሰውነትን ፡ በሚጎዳ ፡ ቅጣት ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡

በእስራት ፡ ወይም ፡ ነጻነትን ፡ ለማሳጣት ፡ በሚደረጉ ፡ ለጸጥታ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆኑ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ በግዞት ፡ አያስቀጡም ። የሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ በሚያስከትሉት ፡ የቅጣት ፡ ዐይነት ፡ ምክንያት ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ቅጣቶች ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ።

(፪) ደንብ ፡ የተላለፉት ፤ ወታደሮች፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ሲሆኑ ፡ የቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ቅጣቶች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፫) ለጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ምክንያት ፡ ለጥበቃ ፡ ወይም ፡ በሽተኛን ፡ ለማስታመም፡ በተለይም፡ ልማደኞች፡ የሆኑትን፡ ጥፋተኞች፡ ወይም ፡ ኀላፊነት ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ስለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ በሚደረጉበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአስተዳደር ፡ ችሎታ ፡ ላላቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ያስታውቃል ። [ቊ ፡ ፩፻፷፫ ፡ ፩፻፷፩ና ፡ ፩፻፷፮ ፡ ፩፻፶፫ ። ]

### ቊ ፡ ፯፻፫ ። የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ።

(፩) ደንብን ፡ የመተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ የሚፈረደው ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ በሚደጋገምበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖና ፡ ሕጉም ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ካልወሰነ ፡ በቀር ፡ የመታሰሩ፡ ጊዜ ፡ የሚቈይበት ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቢበዛ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነው ። [ቊ ፡ ፯፻፳፯ ። ]

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የደንብ ፡ ተላላፊውን ፡ ጥፋተኛነት ፡ በመገመት ፡ የቅጣቱን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ፤ ሕጉም ፡ በወሰነው ፡ በአነስተኛዎቹና ፡ በከፍተኛዎቹ ፡ የቅጣት ፡ ጊዜ ፡ ይገደዳል ። [ቊ ፡ ፹፯ ፡ (፩) ። ]

(፪) አስቀድሞ ፡ ለአመክሮ ፡ መፈታት ፡ ለማረፊያ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ። [ቊ ፡ ፩፻፯ ፡ እስከ ፡ ፩፻፲፪ ። ]

### ቊ ፡ ፯፻፬ ። መደበኛ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የፖሊስ ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ።

(፩) መደበኛ ፡ የሆነ ፡ እስራት ፡ የሚፈጸመው ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች፡ ወይም ፡ ከፖሊስ ፡ ጣቢያዎች ፡ ጋራ ፡ በተያያዙ ፡ የመቈያ ፡ መታሰሪያ ፡ ቦታዎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የተፈረደባቸው ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የሚታሰሩት ፡ ለየብቻ ፡ ነው ።

በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ እንዲታሰሩ ፡ የተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ዐመል ፡ ማረሚያ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ይላኩ ፡ ዘንድና ፡ በከባድ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ነጻነትን ፡ ከሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ፡ ወይም ፡ በግዞት ፡ እንዲቀመጡ ፡

ከሚሰጡ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ አንዱ ፡ ከተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ይቀላቀሉ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ። [ቍ ፡ ፯፻፪ ።]

(፪) የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ እንዲሠራ ፡ አይገደድም ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘትም ፡ መብት ፡ የለውም ። [ቍ ፡ ፪፲ ።]

የተቀመጠበት ፡ የእስራት ፡ ቦታ ፡ ጸጥታና ፡ የጠቅላላው ፡ ሰላም ፡ እንደማይነካ ፡ ሆኖ ፡ ከውጭ ፡ የሚመጣለትን ፡ ምግቡን ፤ ደብዳቤዎችንና ፡ ጠያቂዎቹንም ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፯፻፫ ። በቤቱ ፡ የሚደረግ ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ።

(፩) የተያዘው ፡ ሰው ፡ ከቤቱ ፡ እንዳይወጣ ፡ ወይም ፡ በታማኝ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በተጠቀሰው ፡ ዓለማዊ ፡ ወይም ፡ መንፈሳዊ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀመጥ ፡ የሰውዬው ፡ ወይም ፡ የቦታው ፡ ሁኔታ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ የሚገባ ፡ ዋስ ፡ አስጠርቶ ፡ በነዚህ ፡ ቦታዎች ፡ በአንደኛው ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ካላጋጠመ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ልዩነት ፡ አድርጎ ፡ የታገደው ፡ ሰው ፡ እንዲወጣ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችለው ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ በሐኪም ፡ ለመመርመር ፡ ወይም ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የመታከም ፡ ተግባሮችን ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብና ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆነው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ከቤት ፡ እንዳይወጣ ፡ የተደረገ ፡ ሰው ፡ በምግብ ፡ በኩል ፡ ራሱን ፡ የሚችለው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፯፻፬ ። የቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፤ ስለ ፡ ወታደሮችና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ።

(፩) የሥራቸውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ፡ በወታደሮች ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ በወታደራዊ ፡ ዲስፕሊንና ፡ በመቈጣጠር ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ በተሰጡት ፡ ተገቢ ፡ ቦታዎች ፡ ይፈጸማሉ ። [ቍ ፡ ፯፻፵፬ ።]

(፪) የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ የተፈረደባቸው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ቅጣቱን ፡ የሚፈጽሙት ፡ ስለነርሱ ፡ በተጻፉት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቤት ፡ በሚደረገው ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ለማድረግ ፡ ባልተቻለ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመረጠው ፡ አንድ ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ባልደረባ ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ በሚጣልበት ፡ ሰው ፡ ጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፪፳፭ ።]

ከቤት ፡ አትውጡ ፡ ተብሎ ፡ የሚሰጠው ፡ የመታገድ ፡ ውሳኔ ፡ በተለያዩ ፡ በብዙ ፡ ጊዜያቶች ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ፤ ስለሆነም ፡ እያንዳንዱ ፡ የመታገድ ፡ ጊዜ ፡ ከሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሊያንስ ፡ በጠቅላላውም ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፺፻፯ ። በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ፈንታ ፡ የሚደረግ ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ።

(፩) የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰን ፡ በሚቻልበት ፡ ጊዜ ፡ የነገሩ ፡ አኳኋንና ፡ ሁኔታዎቹ ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ ነጻነቱን ፡ በመቀነስ ፡ ወይም ፡ ባለ መቀነስ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ የሚያገኘውን ፡ ገቢ ፡ ለመንግሥት ፡ እንዲ ሆን ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማገዱን ፡ ቅጣት ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ለመለ ወጥ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፱ና ፡ ፻፫ ። [

የጊዜውንም ፡ ልክ ፡ በፍርዱ ፡ ውስጥ ፡ በትክክል ፡ ይወስናል ።

(፪) ስለሆነም ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ወታደሮች ፡ ላይ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱም ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ አይፈጸምም ።

ቍ ፡ ፺፻፰ ። መቀጫ ፤ መደበኛ ፡ ሁኔታ ።

(፩) ደጋጋሚ ፡ ጥፋተኞች ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ሕጉም ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ ካልወሰነ ፡ በቀር ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጮ ፡ ካንድ ፡ ብር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺፻፳፯ ። ]

በተደጋገመ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ የቅጣት ፡ ማክበድ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ አድራጊው ፡ ጥቅም ፡ በመፈለግ ፡ ወይም ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቀጮው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

የተፈረደበትን ፡ ሰው ፡ ጥቅሞችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲሁም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ትልቅነትና ፡ የተደረገውን ፡ ጥፋት ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መገመት ፡ አለበት ። [ቍ ፡ ፹፰ ።]

(፪) አድራጊው ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥቅምን ፡ በመፈለግ ፡ ወይም ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ያደረ ገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሕጉ ፡ በማፈራረቅ ፡ እንዲወሰን ፡ አስቀድሞ ፡ ያመ ለከተ ፡ ሲሆን ፡ ሁኔታዎቹም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያስገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገንዘቡ ፡ መቀጫ ፡ ከማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ጋራ ፡ ሊደረብ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፹፱ና ፡ ፺ ።]

(፫) ለተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ቢያስፈልግም ፡ በየጊዜው ፡ ዕዳውን ፡ እንዲከፍል ፡ በማ ድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ሊወስንለት ፡ ይች ላል ። ሁኔታዎቹም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያስገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ የቀጠሮ ፡ ጊዜ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለማድረስ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺፩ ።]

BACK



ቅጣቱን ፡ በሞላው ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በመፈጸም ፡ ፈንታ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፺፪ ።]

ቍ ፡ ፺፻፱ ። መቀጮን ፡ ስላለመከፈል ፡ በመታገድ ፡ ወይም ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ መቀጮን ፡ መለወጥ ።

(፩) ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተደርጎለት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቀጮው ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሳይከፈል ፡ ቀሪ ፡ ለሆነው ፡ መቀጮ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በነጻ ፡ ወይም ፡ ነጻ ፡ ባልሆነ ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ አኳኋን ፡ የሚያገኘውን ፡ ገቢ ፡ ለመንግሥት ፡ እያስቀረ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቀጮው ፡ እንዲለወጥ ፡ ያዛል ።

(፪) የጠቅላላ ፡ ውሳኔዎችን ፡ አሳብ ፡ በመከተል ፡ በያንዳንዱ ፡ አኳኋን ፡ ውስጥ ፡ የማቻቻሉ ፡ ነገር ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ። [ቍ ፡ ፺፩ና ፡ ፺፪ ።]

ቍ ፡ ፺፻፲ ። መቀጮን ፡ ስለ ፡ ማስገባት ፡ ስለ ፡ ወታደሮችና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሰ ፡ ሕፃን ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ።

(፩) አድራጊው ፡ ወታደር ፡ ሆኖ ፡ የተላለፈው ፡ የወል ፡ ሕግ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሲሆን ፡ በሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በመቀጮው ፡ ገንዘብ ፡ ፈንታ ፡ ደመወዙ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲያዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ተቀጪው ፡ ካልተስማማ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ የደመወዙ ፡ መያዝ ፡ ነገር ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

ቅጣቱም ፡ የሚወሰነው ፡ ለወታደሩ ፡ አዛዥ ፡ ከሆነው ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋራ ፡ ከተስማማ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) ደንቡን ፡ የተላለፈው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሕፃን ፡ ሲሆን ፡ የጥፋቱን ፡ ከባድነት ፡ በመገመት ፡ የኑሮውን ፡ ሁኔታ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆንም ፡ ለቅጣት ፡ የሚሰጠው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከባድና ፡ ቀላል ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ በሚገባው ፡ ወሰን ፡ ውስጥ ፡ የገንዘቡን ፡ መቀጫ ፡ ይወስናል ።

መቀጮውን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ራሱ ፡ መክፈል ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በመደበኛው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ለልጁ ፡ አላፊ ፡ የሆኑት ፡ ዘመዶቹ ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ሰቡ ፡ ይከፍላሉ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ዘመዶች ፡ ወይም ፡ ለርሱ ፡ አላፊ ፡ የሚሆን ፡ ዋስ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚገባው ፡ አኳኋን ፡ አፈጻጸሙንና ፡ መጠኑን ፡ ወስኖ ፡ የገንዘቡን ፡ ቅጣት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ ልጆች ፡ በተመደበው ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይለውጠዋል ።

BACK



## ቍ ፡ ፯፻፲፩ ። የጉዳት ፡ ካሣ ።

በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በሰውነት ፡ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ የጉዳት ፡ ካሣና ፤ ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ የተቈረጠው ፡ የገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ ሁኔታዎች ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲያስገኙ ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ይቈያሉ ። [ቍ ፡ ፺ ፡ ፺፩ ።]

### ክፍል ፡ ፪ ።

### ተጨማሪና ፡ ተደራቢ ፡ የሆኑ ፡ ቅጣቶች ።

## ቍ ፡ ፯፻፲፪ ። ማስጠንቀቂያና ፡ ወቀሳ ።

(፩) በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ቅጣት ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ በማስጠንቀቅ ፡ በመውቀስ ፡ በመገሠጽና ፡ ይቅርታ ፡ እንዲለምን ፡ በማድረግ ፡ ዘወትር ፡ እኒህን ፡ ቅጣቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በደንብ ፡ ተላላፊው ፡ ላይ ፡ ሊፈጽምበት ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፺፳፩ ።]

(፪) የተፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ቅጣቱን ፡ የሚያቃልል ፡ ሆኖ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ዋነኛ ፡ አድርጎ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፯፻፲፫ ። ከመብት ፡ የመሻር ፡ ቅጣት ፡ ተፈጻሚ ፡ ስላለመሆኑ ።

(፩) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝባዊ ፡ መብት ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ ከሥራ ፡ ወይም ፡ ከሞያ ፡ እንዲሁም ፡ ከማዕርግ ፡ ክብርና ፡ ከልዩ ፡ አስ ተያየት ፡ መብት ፡ የመታገድ ፡ ቅጣት ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ። [ቍ ፡ ፺፳፪ ።]

(፪) እንዲሁም ፡ ከወታደራዊ ፡ ማዕርግ ፡ የመሻርና ፡ ከጠሩም ፡ ሠራዊት ፡ የመወ ገድ ፡ ቅጣት ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ፡ [ቍ ፡ ፺፳፫ ።]

### ክፍል ፡ ፫ ።

### የጸጥታ ፡ ውሳኔ ።

## ቍ ፡ ፯፻፲፬ ። ዋስትና ።

(፩) የደንብ ፡ መተላለፉ ፡ ሥራ ፡ በሕዝብ ፡ ሰላም ፡ ወይም ፡ በሰውነት ፡ በንብረት ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ የተደጋገመና ፡ ይደጋገማል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ማስገደድ ፡ አይቻልም። [ቍ ፡ ፺፴፫።]

ካንድ ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥም ፡ ጊዜ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ማስገደድ ፡ አይ ቻልም ።

(፪) ዋስትና ፡ ለመስጠት ፡ እንቢ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጥ ፡ ለማስገደድ ፡ የሚቻለው ፡ በፖሊስ ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ወታደር ፡ ሲሆን ፡ በወታደር ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ደንብ ፡ ዐይነት ፡ ብቻና ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ለማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፯፻፬ና ፡ ፯፻፯ ።]

ይህንም ፡ ለማራዘም ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፯፻፲፭ ። ስለ ፡ መውረስ ።

(፩) ለእምነት ፡ ለጸጥታ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ የሚረዱ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚሆኑት ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የተገኙት ፡ አደገኛ ፡ ዕቃዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ እንዲወረሱ ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፡ እንዲወረሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፻፵፬ ።]

የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ተግባር ፡ የሚያስገድድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ምክንያት ፡ እነዚህን ፡ አደገኛ ፡ ዕቃዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ አስቀድሞ ፡ መውረስ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፻፵፭ ።]

(፪) አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ የነዚሁ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ መሣሪያዎች ፡ ባለቤትነት ፡ መብት ፡ ለመንግሥት ፡ እንዲተላለፍ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፺፱ ።]

ቍ ፡ ፯፻፲፮ ። የሥራ ፡ ፈቃዶችን ፡ ስለ ፡ መከልከልና ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ ማገድ ።

ከሚያስቀጣው ፡ ተግባር ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ ተደጋግሞ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ ወረቀትን ፡ መልሶ ፡ መውሰድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ መዝጋትና ፡ ያንድ ፡ የሕዝብ ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የማኅበር ፡ ተግባርን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በተወሰነ ፡ አኳኋን ፡ ማገድን ፡ ለመወሰን ፡ የሚቻለው ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [ቍ ፡ ፻፵፯ ፡ ፻፵፯ ።]

የእነዚህ ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ፡ ጊዜ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ከ፯ ፡ ወር ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሁኔታ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜና ፡ የነገሩን ፡ ከባድነት ፡ በትክክል ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፯፻፲፯ ። ዐይነተኞቹ ፡ የአፈጻጸም ፡ ሁኔታዎች ።

በሕግ ፡ የተከለከሉትን ፡ ወይም ፡ አደገኞች ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ የመውረስ ፤ የተሰጠውን ፡ ፈቃድ ፡ መልሶ ፡ የመውሰድ ፤ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ የመዝጋት ፤ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ ሥራውን ፡ የማቆም ፡ (የማገድ) ፡ አደራረግ ፡ በተለይ ፡ የሚወሰነው ፡—

(ሀ) የገንዘብ ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ አጠባበቅ ፡ ጉዳይን ፡ የሚመለከተው ፡ ደንብ ። [ቍ ፡ ፯፻፵ ፡ እስከ ፡ ፯፻፵፯ ። ]

(ለ) የጋዜጣና ፡ የማስታወቂያ ፡ ጉዳይን ፡ የሚመለከተው ፡ ደንብ ። ]ቍ ፡ ፯፻፵፰ ፡ ፯፻፷፯ ። ]

(ሐ) የጦር ፡ መሣሪያንና ፡ ጥይትን ፡ እሳትንና ፡ የሚፈነዱትን ፡ ወይም ፡ አደገኞች ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ የመጠባበቅ ፡ ጉዳይን ፡ የሚመለከተው ፡ ደንብ ። [ቍ ፡ ፯፻፷፫ና ፡ ፯፻፹፩ ። ]

(መ) የቲያትሮችን ፡ (የትርእይቶችና) ፡ የጨዋታዎችን ፡ ሆቴሎች ፡ የመጠባበቅ ፡ ጉዳይን ፡ የሚመለከተው ፡ ደንብ ። [ቍ ፡ ፯፻፸፭ ፡ ፯፻፸፮ ። ]

(ሠ) የሕዝብን ፡ ጤናና ፡ ንጽሕና ፡ የመጠበቅ ፡ ጉዳይን ፡ በተለይም ፡ መርዛሞችን ፡ አፍዛገሮች ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ የመሥራትና ፡ መድኀኒቶችንና ፡ ፈውሶችን ፡ አልኮልን ፤ መጠጦችን ፤ በጠቅላላውም ፡ ምግቦችንም ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ ወይም ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የመሸጥ ፡ ጉዳይን ፡ የሚመለከተው ፡ ደንብ ፡ [ቍ ፡ ፯፻፸፫ ፡ ፯፻፹፯ ፡ እስከ ፡ ፯፻፹፱ ። ] በተጣሰ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፲፰ ። የግል ፡ ነጻነትን ፡ ስለ ፡ መከልከልና ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።

(፩) በተለይ ፡ የወንጀል ፡ መደጋገም ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ መደጋገም ፡ ተግባር ፡ የሚደረግ ፡ መሆኑ ፡ የሚያሠጋ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ለመደጋገም ፡ በሚረዱት ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ እንዳይደርስ ፡ መከልከል ፡ እንዲደረግ ፡ ተገቢና ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። [ቍ ፡ ፩፻፵፱ ። ]

የመከልከሉም ፡ ጊዜ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ክልከላው ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ።

(፪) በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፤ ባንድ ፡ ቦታ ፡ የመሰንበትን ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ክልከላ ፡ ባንድ ፡ ጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ ማኖርን ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ የተሰጡ ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀቶችን ፡ መውሰድን ፡ በመንግሥቱ ፡ ግዛት ፡ አገሮች ፡ እንዳይኖር ፡ ወይም ፡ ከነገር ፡ እንዲወጣ ፡ ማድረግን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጡት ፡ ሌሎች ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባሮች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ። [ቍ ፡ ፩፻ ፡ እስከ ፡ ፩፻፲፬ ። ]

## ክፍል ፡ ፬ ።

## የማስታወቂያ ፡ ውሳኔዎች ።

ቍ ፡ ፯፻፲፱ ። ለባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅና ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

(፩) ለጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡

አግባብ ፡ ላለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጕዳዩን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።
[ቍ ፡ ፯፻፰ ። ]

(፪) እንዲሁም ፡ የሕዝብ ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ በሚያስገድድበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርዱ ፡ በግልጽ ፡ እንዲወጣ ፡ ይደረጋል ። [ቍ ፡ ፯፻፱ ።]

**ቍ ፡ ፯፻፳ ። በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።**

(፩) አስፈላጊ ፡ ሆኖም ፡ ሲገኝ ፡ ደንበኞቹ ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ አባሎች ፡ የተከሳሹን ፡ ያለፉት ፡ ሥራዎቹን ፡ እንዲያውቁለት ፡ ለማድረግ ፡ እንዲቻል ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ረገድ ፡ የሚሰጡት ፡ የመጨረሻ ፡ ቅጣቶች ፡ በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ እንዲጻፉ ፡ ይደረጋል ። [ቍ ፡ ፯፳ ።]

(፪) በፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የተጻፉትን ፡ ወንጀሎች ፡ ለመግለጽ ፡ የተሰጡት ፡ ደንቦችና ፡ ውሳኔዎች ፡ ለነዚህም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፩ ። ስለ ፡ ክስ ።**

(፩) ይህን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሕጎችንና ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በሚከተለው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(ሀ) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ሙሉነት ፡ በነጻነት ፡ ክብርና ፡ በግል ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ተበዳዩ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መደበኛ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የተፈቀደለትና ፡ ችሎታ ፡ የተሰጠው ፡ እንደራሴው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(ለ) በአስተዳደር ፡ ወይም ፡ በአስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ በተወሰኑት ፡ ደንቦች ፡ ትእዛዞችና ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበውና ፡ የሚያስቀጣው ፤ ለክፍሉ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ባለጕዳይ ፡ ለሆነው ፡ ድርጅት ፡ በመንግሥት ፡ ሕግና ፡ በውስጥ ፡ ደንባቸው ፡ መሠረት ፡ ወኪሎቻቸው ፡ በሆኑት ፡ አማካይነት ፡ ነው ።

(ሐ) በሌሎች ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ክሱን ፡ የሚያቀርበው ፡

BACK



የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ እንደራሴ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ወታደራዊ ፡ ብቻ ፡ ለሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የዲሲፕሊን ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። ጊዜ ፡ መስጠት ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ጥፋተኛውን ፡ የሚያስቀጡ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተፈጽመው ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ሥሩ ፡ ይህን ፡ አትሥሩ ፡ የሚሉትን ፡ የሚያዝ ፡ ወይም ፡ የሚከለክልና ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ የሚጥስ ፡ የተወሰነው ፡ የሕግ ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ። [ቍ ፡ ፯፻፺፫ና ፡ ፯፻፺፬ ።]

የሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ ከጠባያቸው ፡ ልዩነት ፡ የተነሣ ፡ ላሠራሩ ፡ ቀናነት ፡ ቅጣቱ ፡ አንድ ፡ ዐይነትና ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፍርድን ፡ ከመፍረድ ፡ ወይም ፡ ከማስፈጸም ፡ ታግዶ ፡ እንዲቈይ ፡ ለማድረግ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ ለዚህ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ። [ቍ ፡ ፻፺፬ ፡ እስከ ፡ ፪፻፭ ።]

## ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማቅለል ።

(፩) ቅጣቱን ፡ የሚያቀሉ ፡ ተገቢዎች ፡ ምክንያቶች ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት፡እስራት ፡ ፋንታ ፡ ጥፋተኛውን ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፤ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ ከአነስተኛው ፡ መደበኛ ፡ ቅጣት ፡ ሳይወርድ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

ቅጣቱን ፡ የሚወስነው፡በአድራጊው፡ጥፋት ፡ መጠን ፡ ነው ። ]ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። (፩) ]

(፪) ጥፋቱ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ በደል ፡ አነስተኛ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይና ፡ በተለይም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባር ፡ መጀመሪያ ፡ ወይም ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወቀሳን ፡ ወይም ፡ ተግሣጽንና ፡ ለወደፊት ፡ የሚሆነውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በመናገር ፡ ብቻ ፡ ለማለፍ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። መደበኛ ፡ የሆነ ፡ የቅጣት ፡ ማክበጃ ።

በጠቅላላ ፡ ማክበድ ፡ ምክንያቶች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሕግ ፡ ወሰን ፡ ሳይወጣ ፡ ቅጣቱ ፡ በበረታ ፡ አኳኋን ፡ ይወሰናል ። [ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። (፪) ]

የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ ሕጉ ፡ በሚያመለክትበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራትንና ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮን ፡ ይፈርዳል ።

BACK



## ቍ ፣ ፯፻፹፭ ። ጥፋት ፣ ሲደራረብ ፣ ስለሚከብድ ፣ ቅጣት ።

(፩) ከባድ ፣ የሆኑ ፣ ወንጀሎች ፣ ተደራርበው ፣ በተሠሩ ፣ ጊዜ ፣ ተፈጻሚ ፣ ይሆናሉ ፣ የተባሉት ፣ ልዩ ፣ ድንጋጌዎች ፣ ለዚህ ፣ ሳይሆኑ ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ሥራ ፣ ተደራርቦ ፣ በተሠራ ፣ ጊዜ ፣ ለያንዳንዳቸው ፣ የተወሰነው ፣ ቅጣት ፣ ተደምሮ ፣ ይፈረዳል ። [ቍ ፣ ፻፹፱ ፣ እስከ ፣ ፻፺፪ ።]

የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ሥራ ፣ መደራረብ ፣ በሚኖርበት ፣ ጊዜ ፣ እየተለየ ፣ የሚሰጠው ፣ እያንዳንዱ ፣ ቅጣት ፣ ሲወሰን ፣ ይኸው ፣ መደበኛ ፣ የሕግ ፣ ከፍተኛ ፣ ቅጣት ፣ እንደ ፣ ተጠበቀ ፣ ሆኖ ፣ የቅጣቶቹ ፣ ድምር ፣ ከተባለው ፣ መደበኛ ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ከፍተኛ ፣ ቅጣት ፣ በላይ ፣ ለማለፍ ፣ ይችላል ።

(፪) ከአድራጎቱ ፣ የተነሣ ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ተግባር ፣ ተደራርቦ ፣ በተሠራ ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የጠቅላላ ፣ ውሳኔዎችን ፣ አሳብ ፣ በመከተል ፣ ቅጣቱን ፣ ለማከበድ ፣ ይችላል ። [ቍ ፣ ፻፺፪ ።]

## ቍ ፣ ፯፻፹፮ ። ጥፋትን ፣ በመደጋገም ፣ ስለሚከብድ ፣ ቅጣት ።

(፩) የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ፍርድ ፣ በሚሰጥበት ፣ ጊዜ ፣ ስላለፈው ፣ ስለ ፣ ማናቸውም ፣ ዐይነት ፣ ወንጀል ፣ የተፈረደው ፣ ቅጣት ፣ በሙሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ ከተፈጸመበት ፣ ወይም ፣ ከተሠረዘበት ፣ አንሥቶ ፣ አንድ ፣ ዓመት ፣ ካለፈ ፣ ጥፋትን ፣ ደጋጋሚነቱ ፣ አይቈጠርበትም ።

በውጭ ፣ አገር ፣ የተሰጡት ፣ ፍርዶች ፣ አይቈጠሩም ። [ቍ ፣ ፻፺፭ ።]

(፪) ከዚህ ፣ በላይ ፣ በተነገረው ፣ አሳብ ፣ የጥፋት ፣ መደጋገም ፣ ተደርጓል ፣ በሚባልበት ፣ ጊዜ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ስለ ፣ አዲሱ ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ሥራ ፣ በተጻፈው ፣ በመደበኛው ፣ ከፍተኛ ፣ ቅጣት ፣ አይታገድም ፣ (አይወሰንም) ፣ የነገሩ ፣ ሁኔታዎችና ፣ ጥፋተኛነቱ ፣ በቂ ፣ ምክንያት ፣ ባስገኘ ፣ ጊዜ ፣ በተለይም ፣ አንዱን ፣ ነገር ፣ በመደጋገም ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ሥራን ፣ የማይተው ፣ ሆኖ ፣ በሚገኝበት ፣ ጊዜ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ስለ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ቅጣቶች ፣ የተጻፈውን ፣ መደበኛውን ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ፣ ከፍተኛ ፣ ቅጣት ፣ እስከ ፣ አጠፌታ ፣ ለማድረስ ፣ ይችላል ። [ቍ ፣ ፯፻፫ና ፣ ፯፻፰ ።]

## ቍ ፣ ፯፻፹፯ ። ስለ ፣ መደጋገምና ፣ ስለ ፣ መደራረብ ።

ወንጀሉ ፣ ተደጋግሞና ፣ ተደራርቦ ፣ በተሠራ ፣ ጊዜ ፣ የገንዘቡ ፣ መቀጮ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በተጻፉት ፣ ሁለት ፣ ቍጥሮች ፣ መሠረት ፣ ይወሰናል ። እስራቱም ፣ ቢበዛ ፣ በድምሩ ፣ ከሁለት ፣ ዓመት ፣ ሊያልፍ ፣ አይችልም ።

BACK

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።
## ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማገድና ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።

### ቍ ፡ ፯፻፹፰ ። የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የሚቀርብባቸው ፡ ሁኔታዎች ።

የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መከታተል ፤ የሕግ ፡ ውሳኔ ፡ አቤቱታን ፡ ለማቅረብ ፡ ሲያስገድድ ፡ አቤቱታ ፡ ስለሚቀርብባቸው ፡ ምክንያቶች ፤ ስለሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ስለ ፡ አቤቱታው ፡ ተገቢነት ፡ የተሰጡት ፡ ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። [ቍ ፡ ፯፻፹፩ ፡ ፪፻፲፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፳፪ ።]

### ቍ ፡ ፯፻፹፱ ። የተከሳሹ ፡ መሞት ።

(፩) ሞት ፤ በደንብ ፡ ተላላፊ ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብንና ፡ መከታተልን ፡ ፍርድ ፡ መስጠትን ፡ ያግዳል ።

(፪) የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሞቱ ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ያስቀረዋል ።

### ቍ ፡ ፯፻፺ ። የይርጋ ፡ ዘመን ።

ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ ቢሆን ፡ ክስ ፡ ሳይቀርብበት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፤ የተፈረደውም ፡ ቅጣት ፡ ሳይፈጸም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል ።

መነሻ ፡ ስለሚደረገው ፡ ጊዜ ፤ የተወሰኑትን ፡ ጊዜዎች ፡ ስለ ፡ ማገድና ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ፡ የተሰጡት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፪፻፳፮ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፪ ። ፪፻፴፫ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፰ ።]

### ቍ ፡ ፯፻፺፩ ። ምሕረትና ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት ።

የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራዎች ፡ በሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በምሕረት ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ ቀሪ ፡ እንዲሆኑ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ። [ቍ ፡ ፪፻፴፱ ፡ እስከ ፡ ፪፻፵ ።]

### ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። ስለ ፡ መሰየም ።

ቅጣት ፡ ለተፈረደበት ፡ ሰው ፤ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ፈተና ፡ በኋላ ፡ የሚደረገው ፡ የመሰየም ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ የተነገሩትን ፡ ምክንያቶች ፡ በመከተል ፡ ቅጣቱ ፡ ከፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ እንዲፋቅና ፡ የታገደው ፡ መብቱ ፡ በሙሉ ፡ እንዲመለስለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመጠየቅና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ሊያዝለት ፡ ይችላል ። ]ቍ ፡ ፪፻፵፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፵፯ ። ]

ይህ ፡ የመሰየም ፡ ጉዳይ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪሉ ፡ ጥያቄ ፡ ካላቀረበ ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

## ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ልዩ ፡ ክፍል ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## በሕዝባዊና ፡ በማኅበራዊ ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

### ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። መሠረቱ ፤ ጠቅላላ ፡ ሥርዐት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ከተመለከ ተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ።

(ሀ) የመንግሥቱን ፡ ክብር ፡ የገንዘብን ፡ የሕዝባዊን ፡ ብልጽግናና ፡ እምነት ፤

(ለ) የሕዝባዊን ፡ አኗኗር ፡ ሥርዐት ፤ ሰላምን ፤ ዕርጋታን ፤ ጸጥታን ፤ ጤንነትንና ፡ መልካም ፡ ኑሮን ፡—

(ሐ) የየብስን ፤ የአየርን ፤ የጅረትንና ፡ የባሕርን ፡ መገናኛ ፤ እንዲሁም ፡ የፖስታ ፡ የቴሌፎንና ፡ የቴሌግራፍን ፡ መላላኪያና ፡ የሩቅ ፡ ግንኙነት ፡ ደንበኛ ፡ ሥርዐ ትንና ፡ የጸጥታን ፡ ነጻነት ፡—

ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ጠቅላላ ፡ አድራጎት ፡ የመንግሥትን ፡ የቀረጥና ፡ የግ ብር ፡ ገቢ ፡ የጉምሩክ ፡ የኤኮኖሚክን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከትና ፡ የጤናን ፡ ወይም ፡ የምግብን ፡ ወይም ፡ የፖሊስን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ ለመጠበቅ ፡ በመ ልካም ፡ ሁኔታ ፡ ለመያዝ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማቋቋም ፡ ሲሉ ፡ የክፍሉ ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ ያወጡትን ፡ ሕጋዊ ፡ ደንብ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ወይም ፡ የአጠባበቅ ፡ ሥርዐትን ፡ የሚቃወም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ተግ ባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ሥራው ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ድን ጋጌዎች ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ ያልተመለከተ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## በመንግሥትና ፡ በሕዝብ ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## በሕዝባዊ ፡ ክብርና ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

### ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። ሕጋዊ ፡ ገንዘብን ፡ ስላለመቀበል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ በማዕድንና ፡ በወረቀት ፡ የተ

BACK



ሠሩትን ፡ ያገር ፡ ገንዘቦች ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፴፭ ። ወደ ፡ ሐሰት ፡ የተለወጠ ፡ ገንዘብ ፡ በእጁ ፡ መኖሩን ፡ ሳያስታውቅ ፡ ስለ ፡ መቅረት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የተለወጠ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በማዕድን ፡ ወይም ፡ በወረቀት ፡ የተሠራውን ፡ ገንዘብ ፡ እውነተኛ ፡ መስሎት ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ የሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ የተበላሸ ፡ መሆኑን ፡ እንዳወቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ አጋጣሚው ፡ የጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠን ፡ የሚያውቅ ፡ ቢሆን ፡ የመ ጣበትን ፡ ስፍራ ፡ አለዚያም ፡ ይህ ፡ ሐሰተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በእጁ ፡ መኖሩን ፡ ለክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሳያስታውቅ ፡ ወይም ፡ ገንዘቡን ፡ ሳያስረክብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፴፮ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆኑ ፡ መስፈሪያዎችና ፡ ሚዛኖች ፡ (ክብደቶች) ፡ መሥራት ።

ማንም ፡ ሰው ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ [ቍ ፡ ፫፻፸፭።]

(ሀ) ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ በሚያደርገው ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፤ በሕግ ፡ ተመ ርምረው ፡ ያልተፈቀዱትን ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ከተሰጠው ፡ ደንብና ፡ ሥርዐት ፡ ጋራ ፡ ተስማሚ ፡ ያልሆኑትን ፡ የመስፈሪያና ፡ የሚዛን ፡ መሣሪያ ዎች ፡ ሲሠራባቸው ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ በጠቅላላ ፡ አድራጎት ፡ ስለ ፡ ሕጋዊ ፡ መስፈሪያዎችና ፡ ሚዛኖች ፡ ትክክለኛነት ፡ ማረጋገጫ ፡ መውጊያ ፡ ስለ ፡ ሚዛኖችና ፡ መስፈሪያዎች ፡ መመ ርመርና ፡ መገልገል ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝና ፡ የታወጀውን ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የመወረሱ ፡ ቅጣት ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ በመታሰርና ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፴፯ ። ውድቅ ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በተለወጡ ፡ የመመላለሻ ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በተለወጠው ፡ ወይም ፡ ውድቅ ፡ በሆነው ፡ ወይም ፡ በተሠራበት ፡ በሕዝብ ፡ መመ ላለሻ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ቲኬት ፡ የተገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቁ ፡ ፯፻፴፰ ። የማዕርግ ፡ ስምና ፡ የምስክር ፡ ወረቀትን ፡ በማጭበርበር ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ ደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የማይገባውን ፡ የገንዘብ ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ [ቁ ፡ ፫፻፺፫ ።]

(ሀ) የችሎታ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ዲፕሎም ፡ (ብረቬ) ፡ ወይም ፡ የትምህርት ፡ ማዕርግ ፡ ወረቀት ፤ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ በሚደረገው ፡ ፈተና ፡ ውድድር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ አሠራር ፡ ላይ ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ የሌለውን ፡ ወይም ፡ መብቱ ፡ የማይፈቅድለትን ፡ ዲፕሎም ፡ (ብረቬ) ፡ የትምህርት ፡ ምስክር ፡ ወረቀትና ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ያለው ፡ አስመስሎ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቁ ፡ ፯፻፴፱ ። ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሲቪል ፡ ኒሻኖችንና ፡ የማዕርግ ፡ ምልክቶችን ፡ መሥራት ፤ በነዚሁ ፡ መነገድና ፡ እነዚሁን ፡ ነገሮች ፡ ማድረግ ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የሲቪል ፡ ኒሻኖችን ፡ ሚዳዮችን ፡ ወይም ፡ የማዕርግ ፡ ምልክቶችን ፡ የሠራ ፤ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ ያስቀመጠ ፡ ወይም ፡ ያስተላለፈ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በእንደዚሁ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በተለወጡ ፡ ኒሻኖች ፡ ወይም ፡ ሚዳዮች ፡ ወይም ፡ ሊገለገልባቸው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ በኒሻኖች ፡ ወይም ፡ በመለያ ፡ ምልክቶች ፡ የተገለገለ ፡ ወይም ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

የመወረሱ ፡ ቅጣት ፡ ሳይቀር ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።

ክፍል ፡ ፱ ።

## በቀረጥ ፡ በግብር ፡ ገቢ ፡ በአስተዳደርና ፡ በገንዘብ ፡ (በፊናንስ) ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

ቁ ፡ ፯፻፵ ። የቀረጥና ፡ የግብር ፡ መብቶችን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ [ቁ ፡ ፫፻፺፬ ፡ እስከ ፡ ፫፻፺፮ ።]

(ሀ) በመንግሥቱ ፡ ገቢ ፡ ምንጭ ፡ ላይ ፡ ይልቁንም ፡ በቀረጥና ፡ በግብር ፡ በጉምሩኮች ፡ በፖስታና ፡ በቴሌግራፍ ፡ በአደን ፤ በዓሣ ፡ ማጥመድ ፡ ወይም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ አሠራር ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ መሳሰለው ፡ የገቢና ፡ የግብር ፡ አከፋፈል ፡ መብት ፡ ጉዳይ ፡—

(ለ) በቴምብርና ፡ በአደባባይ ፡ በሚለጠፉ ፡ የሕዝብ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የቴምብር ፡ ቀረጥ ፡ ደንብ ፤ የመዝገብ ፡ ማስገቢያ ፡ የስም ፡ ማዛወሪያና ፡ ሌላም ፡ የዚሁኑ ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ የያዘውን ፡ በክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ለነዚሁ ፡ ጉዳዮች ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፵፭ ። ስለ ፡ ከበሩ ፡ ማዕድኖች ፡ አጠባበቅ ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

እንዲሁም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ስለ ፡ ተከበሩ ፡ ማዕድኖችና ፡ ድንጋዮች ፡ (ሚኔራሎች) ፡ አጠባበቅ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፤ ስለ ፡ ማከናወን ፤ ስለ ፡ መግዛትና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈረሰ ፡ ሰው ። [ቍ ፡ ፫፻፶፰ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፵፮ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ወረቀቶች ፤ ስለባለዋጋ ፡ ወረቀቶች ፤ ስለ ፡ አክሲዮኖችና ፡ ስለ ፡ ግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ቍ ፡ ፭፻፶፯) ፡ ከተከለከለው ፡ ውጪ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ወረቀቶች ፤ ስለ ፡ ቼኮች ፤ ስለ ፡ ሐዋላ ፡ ወረቀቶችና ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፡ ወረቀቶች ፤ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ እንዱስትሪ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ ማስገኘት ፡ የተቋቋመውን ፤ የማኅበር ፡ አክሲዮኖችን ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ የሚወጡትን ፡ ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፡ ወይም ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፵፯ ። ስለ ፡ ባንኮችና ፡ የአደራ ፡ ገንዘብ ፡ ማስቀመጫ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

ማንም ፡ ሰው ፤ ስለ ፡ ባንክ ፡ ማኅበሮች ፡ አቋቋም ፤ የአበዳሪ ፡ ወይም ፡ የተበዳሪ ፡ ማኅበሮችና ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ከሕዝብ ፡ የአደራ ፡ ወይም ፡ የቁጠባ ፡ ገንዘብ ፡

BACK



ለመቀበል ፡ ሲሉ ፡ ጥሪ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ ለሚነካ ፡ አሠራር ፡ የተቋቋሙትን ፤ የሕዝብ ፡ ወይም ፡ የግል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የሚነኩትን ፡ የአቋቋም ፡ የአከፋፈት ፡ ያመራርና ፡ የመቈጣጠር ፡ ደንቦችንና ፡ ትእዛዞችን ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። ስለ ፡ ዕጣዎች ፤ ስለ ፡ ሎተሪዎች ፤ ስለ ፡ ጨዋታዎችና ፡ ውርርዶች ፡ ጕዳይ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የከፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሳይፈቅድለት ፡ የዕጣ ፡ (የሎተሪ) ፡ የውርርድ ፡ ወይም ፡ የቁማር ፡ ጨዋታ ፡ ሥራ ፡ በአደባባይ ፡ አቋቁሞ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በአደባባይ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ በተከፈተ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በግል ፡ ሆኖ ፡ ለመሰብሰቢያ ፡ በተዘጋጀ ፡ ስፍራ ፡ የቁማር ፡ ጨዋታ ፡ ወይም ፡ የውርርድና ፡ የቁማርን ፡ ጠባይ ፡ የያዘ ፡ መወዳደሪያ ፡ አቋቁሞ ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ የትርፍ ፡ ማግኛ ፡ ዘዴ ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ በተከለከለ ፡ በማናቸውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ጨዋታ ፡ ሲነግድ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ ስለነዚሁ ፡ ጕዳዮች ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ለሕዝብ ፡ ጥቅምና ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ የተቋቋሙ ፡ የዕጣ ፡ (የሎተሪና) ፡ የቁማር ፡ ጨዋታ ፡ ተግባሮች ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የተቋቋሙ ፡ ከሆኑ ፡ አያስቀጡም ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፭ ። ስለ ፡ ዋጋ ፡ መቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ዕቃ ፡ ብረታ ፡ ብርት ፡ የንግድ ፡ ዕቃና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሸቀጥ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ ያለውን ፡ በሞኖፖል ፡ የተሰጠ ፡ ወይም ፡ ያልተሰጠ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ተወስኖለት ፡ በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ እንዳይሸጥ ፡ በደንብ ፡ የተከለከለውንና ፡ ወይም ፡ በታሪፍ ፡ በተወሰነው ፡ ልክ ፡ እንዲሸጥ ፡ ግዴታ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ከዋጋው ፡ በላይ ፡ የሸጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተወስኖ ፡ በተደነገገው ፡ ወይም ፡ ከተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ይልቁንም ፡ ለርስት ፡ ለቤት ፡ ለእርሻ ፡ ኪራይ ፡ ከተወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ እንዲከፈለው ፡ የጠየቀ ፡ ወይም ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ለመጠበቅና ፡ ለመቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፯ ። የሞያ ፡ ሥራዎችን ፡ አካሄድ ፡ ስለ ፡ ማቋቋምና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተከለከለው ፡ ውጪ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ በነጻ ፡ ለሚሠራው ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ለሆነው ፡ ለጊዜው ፡ የሚሠራም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ እያቋረጠ ፡ የሚቀጥልም ፡ ቢሆን ፤ ወይም ፡ በተዘዋዋሪነት ፡ የሚፈጸም ፡ ቢሆን ፡ እንዲሁም ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ለሆነው ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ የወጣውን ፡ የንግድ ፡ ወይም ፡ የእንዱስትሪ ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጥበትን ፡ ሥራውን ፡ ለማካሄድ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ምርመራ ፡ የሚደረግበትን ፤ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ የሆነበትን ፡ ወይም ፡ በመዝገብ ፡ የሚጻፍበትን ፡ ሁኔታ ፤ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ ስለማስሄድ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አመራር ፡ ጉዳይ ፡ የወጡትን ፡ ደንቦች ፡ ትእዛዞች ፡ ድንጋጌዎችና ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በመጣስ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ተግባር ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንደ ፡ ባንክ ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ መብቶች ፡ ያሉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሞያ ፡ ሥራዎች ፡ ስለሚመለከቱትና ፡ እንዲሁም ፡ የሕክምናን ፡ የጤና ፡ አጠባበቅን ፡ የጸጥታን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተበጠቁ ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፤ ፪ ።

## በወታደራዊ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፤ በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

ቍ ፡ ፯፻፹፰ ። የወታደራዊ ፡ ደንብን ፡ መተላለፍ ፡ የሚለይበት ፡ ሁኔታ ።

ስለ ፡ ወታደራዊ ፡ ወንጀል ፡ ብቻ ፡ ተብለው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሙሊያ ፡ የሆኑት ፤ የወታደርን ፡ ሥራና ፡ ተግባር ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ የሚለዩት ፡ ነገሮች ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ትእዛዞችና ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናሉ ። [ቍ ፡ ፪፻፺፮ ፡ እስከ ፡ ፫፻፴፩ ።]

**ቍ ፡ ፪፻፺፰ ። የወታደራዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቅጣቶች ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ማዕርግ ፡ ያለውና ፡ የማናቸውም ፡ ጦር ፡ ክፍል ፡ የሆነ ፡ ወታደር ፡ ወይም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ የሚያገለግል ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ምርኮኛ ፡ ወይም ፡ ግዞተኛ ፡ የወታደር ፡ ደንብ ፡ ብቻ ፡ የተባለውን ፡ በመተላለፍ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ ወታደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መተላለፍ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሕግ ፤ በተወሰኑት ፡ ቅጣቶች ፡ መሠረት ፡ በክፍሉ ፡ የወታደር ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ይቀጣል ።

(፪) ማናቸውም ፡ የወል ፡ ሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተነገሩት ፡ ሰዎች ፡ የተደነገጉት ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ መደበኛ ፡ የሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ። [ቍ ፡ ፫፻፳፰ ።]

**ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍና ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ።**

በአንድ ፡ ወታደር ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወይም ፡ በረዳት ፡ አገልግሎቶች ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ለመሥራት ፡ የሚሰነዘረው ፡ የአጥፊነት ፡ ሥራ ፤ እንዲሁም ፡ ስለነዚሁ ፡ ጥቅም ፡ ተብሎ ፡ በባለችሎታ ፡ ወታደራዊ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ በመከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ የታወጁትን ፡ (የተነገሩትን) ፡ ደንቦች ፡ ትእዛዞች ፡ የትእዛዝ ፡ ቃሎች ፡ ወይም ፡ ጥንቃቄዎች ፡ በመጣስ ፡ የሚሠራው ፡ ማናቸውም ፡ በደል ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ቍ ፡ ፫፻፵፩ ፡ እስከ ፡ ፫፻፵፯) ፡ ድንጋጌ ፡ የሚያስከትል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እነዚህ ፡ ጥፋቶች ፡ በወታደሮችና ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ በሚሠራ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ ተገምተው ፡ በጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ (መጽሐፍ ፡ ፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፪) ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮን ፡ ወይም ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራትን ፡ ቅጣት ፡ ያስከትላሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻ ። ደንቡ ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የፖሊስን ፡ ሠራዊት ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲሁም ፡ ፖሊሶች ፡ በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ ሲገኙ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚገባቸውን ፡ ጥበቃ ፡ የሚወስኑትን ፡ ደንቦች ፡ የትእዛዝ ፡ ሕጎችንና ፡ ትእዛዞችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ፡ የተመደበውን ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወይም ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (የዲሲፕሊን) ፡ ጠባይ ፡ ያለውን ፡ ቅጣት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩት ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦች ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ።

(፪) የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባሎች ፡ የአስተዳደር ፡ የማስፈጸም ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞች ፡ ሆነው ፡ (ቍ ፡ ፫፻፵፪ና ፡ ተከታዩ) ፡ የሚያከናውኑትን ፡ ሥራ ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣንና ፡ በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የሥራ ፡ አፈጻጸምን ፡ ተግባር ፡ የሚመለከት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።**

ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ አሳልፎ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ አላገባብ ፡ የተገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፩፻፲፩ ።]

በገንዘብ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። የማስገደድን ፡ መብት ፡ ከመጠኑ ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ።**

ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ ያንዱን ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ በምርመራ ፡ ስም ፡ ለመጐብኘት ፡ ለመበርበር ፡ ዕቃውን ፡ ለመያዝ ፡ ወይም ፡ ለመውረስ ፤ ቤቱን ፡ ለማሸግ ፡ ወይም ፡ የታሸገውን ፡ ለመክፈት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ያንዱን ፡ ሰው ፡ ሰውነት ፡ ለመበርበር ፡ ወይም ፡ ለመፈተሽ ፡ ለማሰር ፤ በማረፊያ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ለማቈየት ፡ ወይም ፡ በዐይነ ፡ ቍራኛ ፡ ለመጠበቅ ፤ የምርመራ ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ አድራጎት ፡ እንዲፈጽም ፡ በሚገባ ፡ ታዞ ፡ ይህንኑ ፡ ተግባር ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ከተሰጠው ፡ መብት ፡ በላይ ፡ አሳልፎ ፡ በመሥራት ፡ ይልቁንም ፡ በሚያበሳጭ ፡ አኳኋን ፡ በብልግና ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ አሠራር ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ የፈጸመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፩፻፲፭ ፡ እስከ ፡ ፩፻፲፯ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፫ ። ሐቀኛነትን ፡ ስለማጓደል ።**

ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፤ የውስልትና ፡ ወይም ፡ የሐቀኛነት ፡ ማጉደልን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ሲል ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ የተገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በላ

ይኛው ፡ ቊጥር ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ። [ቊ ፡ ፬፻፳ ፡ እስከ ፡ ፬፻፳፱ ፡ ፬፻፳፮ ።]

ቊ ፡ ፫፻፶፩ ። የአድልዎ ፡ እርዳታ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ሲል ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ጒዳይ ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ ውስጥ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ወይም ፡ የሚጠባበቀውን ፡ ሰው ፡ በአድልዎ ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቊ ፡ ፬፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፬፻፳፭ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቊ ፡ ፫፻፶፪ ። ከባለሥልጣን ፡ የሚሰጡትን ፡ ወረቀቶች ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፤

(ሀ) በተለመደው ፡ የምርመራ ፡ ዘዴ ፡ ለዚሁ ፡ ጒዳይ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ሳያረጋግጥና ፡ በዚህም ፡ ወረቀት ፡ ሊጠቀም ፡ የሚገባው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ መሆኑን ፡ አጣርቶ ፡ ሳያውቅ ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ የተባለውን ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ጽሑፍ ፡ ለመቀበል ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ሳያጣራ ፡ ላልታወቀና ፡ የመታወቂያ ፡ ሰነዱ ፡ ላልተመረመረ ፡ ሰው ፡ ፓስፖርት ፡ የመለያ ፡ ወረቀት ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ የፍርድ ፡ ሰሌዳ ፡ ቅጅ ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ የችግረኛነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ የግል ፡ ጠባይን ፡ የያዘ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ፡ ራሱ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ እንዲሰጥ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ማስረጃ ፡ የሚወስደው ፡ ሰው ፡ የዚሁ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤት ፡ አለመሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ማስረጃ ፡ ሊያገኝ ፡ የማይገባው ፡ መሆኑን ፡ እያረጋገጠ ፡ የማይገባው ፡ ሰው ፡ እንዲሠራበት ፡ የተወው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቊ ፡ ፫፻፶፫ ። አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ ጒዳዮች ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (የዲስፕሊን) ፡ ቅጣቶች ።

የደንብ ፡ መተላለፉን ፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የኦፊሲየል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡

BACK



ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ጠባቂ ፡ የሆነ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትለው ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አፈጻጸም ፡ ጕድለት ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በወንጀል ፡ በኩል ፡ የሚወሰንበትን ፡ ቅጣት ፡ ከመፈጸም ፡ ይልቅ ፡ ያስተያየቱን ፡ ሐሳብ ፡ ደግፎ ፡ በመግለጽ ፡ አጥፊው ፡ በባልደረባው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ በሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ ጕድለት ፡ ብቻ ፡ ተገቢ ፡ ቅጣቱን ፡ እንዲቀበል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ አለቃው ፡ ሊያስተላልፈው ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## <u>በባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።</u>

### <u>ቍ ፡ ፯፻፶፯ ። ግልጾች ፡ የሆኑ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ግልጾች ፡ የሆኑትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ወይም ፡ በአደባባይ ፡ የተለጠፉትን ፡ የማስታወቂያና ፡ የዐዋጅ ፡ ሰሌዳዎች ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ከስፍራቸው ፡ ያነሣ ፡ የቀደደ ፡ የለዋወጠ ፡ የሰረዘ ፡ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ ያቈሸሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፬፻፹፯ ።[

እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### <u>ቍ ፡ ፯፻፶፰ ። ግዴታ ፡ የሆነውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ስላለመስጠትና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ መዝገብ ፡ ስላለማጻፍ ።</u>

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ከተደነገገው ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ልዩ ፡ ውሳኔ ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ መዝገብ ፡ የማጻፍ ፡ ጕዳይ ፡ መፈጸም ፡ ይገባል ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ደንቦች ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ በሕግ ፡ የታዘዘውን ፡ ያልፈጸመ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ ያላደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጕዳዩ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ካለበት ፤ [ቍ ፡ ፬፻፹፰ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ስለ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ በሞያ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ሊሰጡ ፡ ይገባል ፡ የተባሉትን ፡ መግለጫዎች ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፯፻፯ ።] (21

**ቊ ፡ ፬፻፺፱ ። ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ማስታወቂያ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ያንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የፈጸመው ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፤ በምክር ፡ የተወሰነ ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ውሳኔ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዳይገለጽ ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡ የወጣውን ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ድንጋጌና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቊ ፡ ፬፻፹፱ና ፡ ፬፻፺፫ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቊ ፡ ፭፻ ። በመብት ፡ አለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ያጣውን ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ ለሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተላለፈውን ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ለጊዜው ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ጭራሹ ፡ የተሻረውን ፡ ወይም ፡ የተወሰደበትን ፡ ሥልጣኑን ፡ ( ሹመቱን ፡ ) እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሲጠቀምበትና ፡ ሲገለገልበት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቊ ፡ ፬፻፵ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቊ ፡ ፭፻፩ ። ባለሥልጣንን ፡ የመርዳት ፡ እንቢታ ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የባለሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ በተለይም ፡ የሕዝብ ፡ ሰላም ፡ እንዳይናወጽ ፡ ለማገድ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛው ፡ ሸሽቶ ፡ እንዳያመልጥ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስ ፡ የእርዳታ ፡ ድጋፍ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሲጠራው ፡ ወይም ፡ ሲጠይቀው ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የተጠየቀውን ፡ እርዳታ ፡ ቢሰጥ ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስበት ፡ ሳይሆን ፡ ይህን ፡ እርዳታ ፡ ለማድረግ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቊ ፡ ፬፻፴፫ ።]

እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቊ ፡ ፭፻፪ ። ትእዛዝ ፡ እንዲፈጽም ፡ ሲጠየቅ ፡ እንቢተኛ ፡ ስለ ፡ መሆን ።**

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ አንድ ፡ የባለሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ [ቊ ፡ ፬፻፴፫ ።]

(ሀ) ስሙን ፡ እንዲነግር ፡ ወይም ፡ የማስታወቂያ ፡ ወረቀቱን ፡ እንዲያሳይ ፡ ጥያ

ውን ፡ (ሥራውን) ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራውን ፡ አድራሻውን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሌላ ፡ የግል ፡ መታወቂያ ፡ ምልክቱን ፡ እንዲገልጽለት ፡ ሲያገዘው ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ፡ የሰጠ ።

(ለ) እንዲቆም ፡ ወይም ፡ እንዲዘዋወር ፡ የሕዝቡን ፡ የመተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ እንዲለቅ ፡ የያዛቸውን ፡ ወረቀቶች ፡ የመንገድ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ አጠራጣሪ ፡ የሆኑትን ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ እንዲፈተሽ ፡ ሲጠየቅ ፡ አላስፈትሽም ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ የመሳሰለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲፈጽም ፡ ሲጠየቅ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በላይኛው ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ በሰላምና ፡ ያለ ፡ ሥጋት ፡ በሚኖርበት ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

### ቍ ፡ ፬፻፸፫ ። ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያዎችና ፡ ጥይቶች ፡ ጥበቃ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችንና ፡ ጥይቶችን ፡ ስለ ፡ ማዘዋወር ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ [ቍ ፡ ፬፻፸፩ ።]

(ሀ) ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያዎችና ፡ ስለ ፡ ሌሎችም ፡ ተተኳሽ ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ ጥይቶችም ፡ በፋብሪካ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፤ መኖራቸውን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፤ በነዚህ ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መነገድ ፡ በይዞታ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥና ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ እነዚሁኑ ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ በነዚሁ ፡ ስለ ፡ መገልገል ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) መግዛት ፡ ላልተፈቀደላቸው ፡ በተለይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ ለታናናሾች ፡ ልጆች ፡ የሸጠ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊውን ፡ መቈጣጠር ፡ ሳያደርግ ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ መሣሪያዎችን ፡ እንዲይዙ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፬፻፸፬ ። የተከለከለ ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስፍራ ፤ እንዲገዛ ፤ ወይም ፡ እንዲይዝ ፡ ያልተፈቀደለትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንዲይዝ ፡

የተፈቀደለትም ፣ ቢሆን ፤ ባልተፈቀደለት ፣ ስፍራና ፣ በተከለከለ ፣ ጊዜ ፣ በዚሁ ፣ መሣሪያ ፣ የተገለገለ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤

እስከ ፣ አንድ ፣ መቶ ፣ ብር ፣ በሚደርስ ፣ መቀጮ ፣ ወይም ፣ እስከ ፣ ስምንት ፣ ቀን ፣ በሚደርስ ፣ በማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ፣ ይቀጣል ።

ቍ ፣ ፯፻፹፭ ። ስለ ፣ ውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ ጥበቃ ።

ማንኛውም ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ ወደ ፣ አገር ፣ ውስጥ ፣ መግባቱን ፣ ስለ ፣ ማስታወቅ ፤ ባገር ፣ ውስጥ ፣ ስለ ፣ መተላለፍ ፣ ሁኔታ ፣ ባገር ፣ ውስጥ ፣ ነዋሪ ፣ ስለ ፣ መሆኑ ፣ ስለ ፣ አጠባበቁ ፣ የወጣውን ፣ ትእዛዝና ፣ ደንብ ፣ የተላለፈ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤

በገንዘብ ፣ መቀጮ ፣ ወይም ፣ በማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ፣ ይቀጣል ።

ቍ ፣ ፯፻፹፮ ። ስምን ፣ ያላገባብ ፣ ስለ ፣ መለወጥና ፣ በሌላ ፣ ስም ፣ ስለ ፣ መጠራት ።

(፩) ማንም ፣ ሰው ፣ የሕዝብ ፣ አገልግሎት ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ባለሥልጣን ፣ ከሚያደርገው ፣ መቈጣጠር ፣ ለማምለጥ ፣ ወይም ፣ ማን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ የታወቀበትን ፣ ለመደበቅ ፣ በማሰብ ፣ የዘር ፣ መጠሪያ ፣ ስሙን ፣ የለወጠ ፤ እውነተኛ ፣ ስሙን ፣ በሌላ ፣ የተካ ፤ ወይም ፣ በስሙ ፣ ላይ ፣ ሌላ ፣ ቅጽል ፣ ስም ፣ የጨመረ ፤ ወይም ፣ የሌላ ፣ ሰው ፣ መጠሪያ ፣ በሆነ ፣ ስም ፣ ያለአገባብ ፣ የተጠራ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤ በላይኛው ፣ ቍጥር ፣ የተመለከተው ፣ ቅጣት ፣ ይፈጸምበታል ።

(፪) በሞያ ፣ ሥራ ፣ ለደራሲነት ፣ ወይም ፣ ለሌላ ፣ ይህን ፣ ለመሰለ ፣ ጕዳይ ፣ ለመሰየም ፤ ሕገ ፣ ወጥ ፣ ሳይሆን ፣ እውነተኛ ፣ ባልሆነ ፣ ስም ፣ መገልገል ፤ ወይም ፣ ልማድ ፣ በሚፈቅደው ፣ ተጨማሪ ፣ ስም ፣ መጠራት ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በተመለከተው ፣ ድንጋጌ ፣ አያስቀጣም ።

## ክፍል ፣ ፪ ።

### በሕዝብ ፣ ሰላም ፣ ጸጥታና ፣ እርጋታ ፣ ላይ ፣ ስለሚሠራ ፣ የደንብ ፣ መተላለፍ ።

ቍ ፣ ፯፻፹፯ ። የጋዜጣንና ፣ የማስታወቂያን ፣ መታተም ፣ ጕዳይ ፣ ስለ ፣ መጠበቅ ።

ታትመው ፣ የወጡትን ፣ ጋዜጦችንና ፣ ማስታወቂያዎችን ፣ መጻሕፍቶችን ፣ መግለጫዎችንና ፣ በአደባባይ ፣ የሚለጠፉትን ፣ ማስታወቂያዎችን ፣ እንዲሁም ፣ ማናቸውም ፣ ጠባይ ፣ ያላቸውን ፣ የታተሙ ፣ ጽሑፎችን ፣ ወይም ፣ በአደባባይ ፣ የሚለጠፉ ፣ ማስታወቂያዎችን ፣ ስለ ፣ መግለጥ ፣ ስለ ፣ ማከማቸት ፣ ስለ ፣ መሸጥ ፣ ለሕዝብ ፣ ስለ ፣ ማደልና ፣ ስለ ፣ መቈጣጠር ፣ የወጣውን ፣ ደንብና ፣ ትእዛዝ ፣ የተላለፈ ፣ ማንኛውም ፣ ሰው ፦

በገንዘብ ፣ መቀጮ ፣ ወይም ፣ በማረፊያ ፣ ቤት ፣ እስራት ፣ ይቀጣል ።

BACK



## ቍ ፡ ፯፻፷፫ ። የሚያስደነግጡ ፡ መግለጫዎች ፡ ወሬዎች ፡ ወይም ፡ ጽሑፎች ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆኑ ፡ ወሬዎችን ፡ የነዛ ፡ የበተነ ፡ ያስታወቀ ፡ ወይም ፡ ለባለሥልጣኖች ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ የሕዝቡን ፡ ጸጥታና ፡ የመልካም ፡ አኗኗር ፡ ሥርዐት ፡ ሊያበላሹ ፡ የሚችሉ ፡ የተንኰል ፡ ወሬዎችን ፡ እንዲባባስ ፡ አድርጎ ፡ በማጋነን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፬፻፹፬ና ፡ ፬፻፹ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፷፬ ። ሐሰተኛ ፡ የአደጋ ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ለአደጋ ፡ መጠባበቂያ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፡ የተቋቋሙትን ፡ የመመላለሻ ፡ (የትራንስፖርት) ፡ ወይም ፡ የእርዳታ ፡ ወይም ፡ የሕክምና ፡ ወይም ፡ የአደጋ ፡ ታዳጊ ፡ የፖሊሶች ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ የእሳት ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ መቅሠፍት ፡ መከላከያ ፡ ክፍሎችን ።

(ለ) የሕክምና ፡ ተግባርን ፡ የሚያከናውኑ ፡ ሰዎችን ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የማያስፈልግ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ ምልክት ፡ በመንገር ፡ ወይም ፡ ለማይጠቅም ፡ ጕዳይ ፡ ያደጋ ፡ መከላከያ ፡ ጥሪ ፡ በማስተላለፍ ፡ በማይረባ ፡ ጕዳይ ፡ የጠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፷፭ ። በሌላ ፡ ሰው ፡ ሥራና ፡ ዕረፍት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሥራና ፡ ሰላማዊ ፡ ዕረፍቱን ፡ ያወከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይልቁንም ፡ አምባጓሮ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ጸብ ፡ በማንሣት ፤ የጩኸት ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፡ በመዝፈን ፡ ግርግርታና ፡ ጫጫታ ፡ በማድረግ ፡ የጩኸት ፡ ድምፅ ፡ በሚሰጡ ፡ ምልክቶች ፡ በመጥሪያዎች ፡ ወይም ፡ በደወሎች ፡ ወይም ፡ በሚጮሁ ፡ መኪናዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ያለመጠን ፡ በመገልገል ፤ በሥራው ፡ ወይም ፡ በሰላማዊ ፡ ዕረፍቱ ፡ ወይም ፡ በእርጋታው ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ በማድረግ ፡ ጤና ፡ የነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይህ ፡ የማወክ ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመው ፡ በፖሊስ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ ደንብ ፡ ከተወሰነው ፡ ሰዓት ፡ ባለፈ ፡ በሌሊት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በማድረግ ፡ በሆስፒታሎች ፤ በትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ቤቶች ፡ አቅራቢያ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በክፋት ፡ ወይም ፡ በጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ በመነሣሣት ፡ የተደረገ ፤ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡

የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቁ ፡ ፯፻፹፮ ። ሃይማኖትን ፡ የመስደብና ፡ የማዋረድ ፡ ንግግር ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ በሆነ ፡ አደባበይ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ በተከፈተ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ ሊመለከትና ፡ ሊሰማ ፡ በሚችልበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በንግግር ፡ ወይም ፡ በምልክት ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያስነውር ፡ ወይም ፡ የሚያስንቅ ፡ ሁኔታ ፡ ያሳየ ፤ ወይም ፡ በመስደብና ፡ በማዋረድ ፡ ዐይነት ፡ የተናገረ ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ስሜትና ፡ እምነት ፡ በሚያዋርድ ፡ ሁኔታ ፡ በአምልኮት ፡ ወይም ፡ በማምለኪያ ፡ ምልክቶች ፡ በሃይማኖት ፡ ሥርዐቶችና ፡ በሃይማኖት ፡ አገልጋዮች ፡ ላይ ፡ የተናገረና ፡ በምልክትም ፡ ሆነ ፡ በቃል ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ የመናቅና ፡ የማዋረድ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፤ ወይም ፡ እጅግ ፡ በቢዛ ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። [ቁ ፡ ፬፻፹፮ና ፡ ፬፻፹፯ ።]

ቁ ፡ ፯፻፹፯ ። የበዓል ፡ ቀኖችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የግዴታ ፡ እንዲከበሩ ፡ በሕግ ፡ የተወሰኑትን ፡ የበዓላት ፡ አከባበር ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ዐዋጅና ፡ ደንብ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፹፮ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

ቁ ፡ ፯፻፹፰ ። አልኮል ፡ የሚያደርሰውን ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ።

(ሀ) አልኮልና ፡ እስፒርቶ ፡ ያሉባቸውን ፡ መጠጦች ፡ በፋብሪካ ፡ ስለ ፡ መሥራትና ፡ በነዚሁ ፡ ስለ ፡ መነገድ ፡ የወጣውን ፡ የመቈጣጠር ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በሕግ ፡ ከተፈቀደው ፡ ጊዜ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሰዓት ፡ ለሕዝብ ፡ ከተከፈቱ ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የአልኮል ፡ መጠጦችን ፡ የሸጠ ፤ የገዛ ፤ የጠጣ ፤ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) እነዚሁኑ ፡ አልኮል ፡ ያለባቸውን ፡ መጠጦች ፤ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ አእምሮዋቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ባለመሆኑ ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ ለማይጠየቁ ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ መስከራቸውና ፡ አደገኛ ፡ መሆናቸው ፡ በግልጽ ፡ ለሚታይ ፡ ሰዎች ፡ ከመጠን ፡ ባለፈ ፡ ብዛት ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ በሆኑ ፡ ቦታዎች ፡ የሸጠ ፤ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ያቀረበ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ወይም ፡ እንዲሸጥላቸው ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) በሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ አደባባይ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ በተከፈተና ፡ ሕዝብ ፤

በሚያየው ፡ ስፍራ ፤ ሌላው ፡ ሰው ፡ እንዲሰክር ፡ ያግባባ ፤ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ያሰከረ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ የሰከረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። ሰክሮ ፡ ወይም ፡ አእምሮ ፡ የሚያናውጽ ፡ ነገር ፡ ቀምሶ ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማወክ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ጠጥቶ ፡ ሰክሮ ፡ አእምሮ ፡ የሚያናውጽ ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ቀምሶ ፡ በሕዝብ ፡ አደባባይ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ በሆነ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የሚያስነቅፍና ፡ የሚያስነውር ፡ ሥራ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ (በአድሚኒስትራሲዮን) ፡ በኩል ፡ ሊፈጸሙበት ፡ የሚገባቸው ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ የጥንቃቄ ፡ ቅጣቶች ፡ የሚፈጸሙበት ፡ መሆናቸው ፡ ሳይቀር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፭ ። የምግብና ፡ የመጠጥ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ።

የምግብና ፡ የመጠጥ ፡ ቤቶችን ፡ የምግብ ፡ ቤቶችንና ፡ ሆቴሎችን ፡ ወይም ፡ የመጠጥ ፡ መሸጫ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ ይልቁንም ፤

(ሀ) ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ንግዶች ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ መብት ፡ የንግዱን ፡ አካሄድ ፡ ሥርዐትና ፡ ስለ ፡ አጠባበቁ ፡ ማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፤

(ለ) የንግድ ፡ ቤቶቹ ፡ ስለሚዘጉበትና ፡ ስለሚከፈቱበት ፡ ሰዓትና ፡ ሌላውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የጣሰ ፡ ማንኛውም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ንግድ ፡ ባለሀብት ፡ ዲሬክተር ፡ ባለይዞታ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፮ ። የቲያትር ፡ ቤቶችንና ፡ የሕዝብ ፡ መደሰቻ ፡ ስፍራዎችን ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ።

ማንኛውም ፡ ባለሀብት ፡ አደራጅ ፡ ዲሬክተር ፡ ባለይዞታ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የቲያትር ፡ ቤቶችን ፤ የሕዝብ ፡ መደሰቻና ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ የጨዋታ ፡ ስፍራዎችን ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትንም ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውን ፡ ስፍራዎች ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተለይም ፡—

(ሀ) ሥራውን ፡ አቋቁሞ ፡ ለሕዝብ ፡ ስለማሳየት ፡ ጕዳይ ፡ ፈቃድ ፡ የመቀበልን ፡

BACK



ደንብ ፡ ባለመፈጸምና ፡ እንዲሁም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ በሚሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ የሚፈጸመውን ፡ ግዴታና ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ጕዳይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፹፭ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጪ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለአፈጻጸሙ ፡ ሥርዐት ፡ ለሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ሕግናትን ፡ ለመጠበቅ ፡ የተደረገው ፡ ድርጅት ፡ አስቀድሞ ፡ በምርመራ ፡ እንዲመረመር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ደንብ ፡ ሳይፈጽምና ፡ ሳይፈቅድ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ለሕዝብ ፡ ወይም ፡ ለግል ፡ ሰው ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያና ፡ ለሕዝብ ፡ ማስደሰቻ ፡ የሚቋቋሙት ፡ የቲያትርና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታ ፡ ቤቶች ፡ የሚከፈቱበትንና ፡ የሚዘጉበትን ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ መወሰንና ፡ ሥራውንም ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። እንስሳትን ፡ በሚያሰቅቅ ፡ ሁኔታ ፡ ስለ ፡ ማንገላታት ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ በሆነ ፡ አደባባይ ፡ ለሕዝብ ፡ በተከፈተ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ በሚታይ ፡ ስፍራ ፡ በእንስሳት ፡ ላይ ፡ ማንኛውም ፡ ተገቢና ፡ መብታዊ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ የጨካኝነትን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፤ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ያጉላላ ፡ ወይም ፡ ያሠቃየ ፡ ወይም ፡ አሰቃቂ ፡ የሆነ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እንስሳዎች ፡ በጭካኔ ፡ የሚሠቃዩበት ፡ አካላቸው ፡ በመቈረጥ ፡ የሚጐድልበት ፡ ወይም ፡ በጭካኔ ፡ የሚገደሉበት ፡ ሁኔታ ፡ የሚታይበትን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለሕዝብ ፡ ለማሳየት ፡ እንስሳት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲዋጉ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ከተያዙ ፡ እንስሳት ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ ውጊያ ፡ ያዘጋጀ ፡ ወይም ፡ በተያዙ ፡ በእንስሳት ፡ ላይ ፡ ዓላማ ፡ የመተኰስ ፡ ድርጅትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የዚሁኑ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ የሚቈይበትን ፡ ያደራጀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፤ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

### ክፍል ፡ ፫ ።

### በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የሕግ ፡ መተላለፍ ።

## ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። የሰዎችን ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ስለ ፡ መንካት ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ከፉዎች ፡ ወይም ፡ አደገኞች ፡ የሆኑ ፡ ውሾችን ፤ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አው

BACK



ሬዎችን ፡ በማነሣሣት ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ድንጋይ ፡ በመወርወር ፡ ወይም ፡ ጠንካራና ፡ ስለታም ፡ የሆኑ ፡ ዕቃዎችን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ በመጣል ፡ ወይም ፡ ለማቍሰል ፡ ለመጉዳት ፡ አደጋ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ የጣለበት ፡ ወይም ፡ የወረወረ በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ለፖሊስ ፡ ሳያስታውቅና ፡ ሳያስፈቅድ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የሚሆን ፡ ተገቢ ፡ ምልክት ፡ ሳያደርግ ፡ ወጥመድ ፡ ዘርግቶ ፡ የማስደንገጫ ፡ መኪና ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ የሆኑ ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ዐይነት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በማናቸውም ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፸፱ ። አደገኞች ፡ የሆኑ ፡ የሰዎችን ፡ ወይም ፡ የእንስሶችን ፡ ጥበቃ ፡ ስለ ፡ ማጒደል ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) በእብድነት ፡ የታሰሩትን ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ ሊጠየቁ ፡ የማይችሉትን ፡ በአልኮል ፡ መጠጥ ፡ ወይም ፡ በሚያፈዙ ፡ ነገሮች ፡ የተመረዙትን ፡ በሽተኞች ፡ ወይም ፡ በአደገኛነታቸው ፡ ምክንያት ፡ ለነዚሁ ፡ በተዘጋጀው ፡ የጥበቃ ፡ ቤት ፡ የታሰሩትን ፡ እንዲሁም ፡ ክፉት ፡ አደገኛነት ፡ ተናካሽነት ፡ ወይም ፡ ተዋጊነት ፡ ያላቸውን ፡ እንስሳዎችን ፡ ወይም ፡ አውሬዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ የአኗኗራቸውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ እንስሶች ፡ ከሚጠበቁበት ፡ ቦታ ፡ የጠፉ ፡ ወይም ፡ ያመለጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ለባለሥልጣኖች ፡ ሳያስታውቅ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ተገቢ ፡ ተግባሩን ፡ የዘነጋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፸፭ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

ቍ ፡ ፯፻፹ ። ስለ ፡ ሌሊት ፡ ደንብ ፡ ጥበቃ ።

እንዲሁም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በየክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ ሌሊት ፡ ሰዓት ፡ እላፊ ፤ በሌሊት ፡ መዘዋወርን ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ የወጡ ትን ፡ ደንቦች ፡ ያላከበረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፯፻፸፭ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

BACK



ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። የሕንጻ ፡ ሥራዎችን ፡ አፈጻጸም ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፤ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፤ [ቍ ፡ ፬፻፶፰ ።]

(ሀ) የሕዝብ ፡ ወይም ፡ የግል ፡ የሆኑትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ቤቶችና ፡ ሕንጻዎች ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ ማደስ ፤ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ የሆኑትን ፡ ስፍራዎች ፡ አዳራሾች ፤ ሱቆች ፡ ወይም ፡ የሲኒማና ፡ የቲያትር ፡ ቤቶች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስፍራዎችንና ፡ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ ለመኖሪያ ፡ ለንግድ ፡ ለእንዱስትሪ ፡ የተመደቡትን ፡ ስፍራዎች ፡ ጸጥታ ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። መንገዶችንና ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስፍራዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) መሰናክል ፡ ሊሆኑ ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ዕቃዎች ፡ ለሥራ ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ጉድፎች ፡ ጥራጊዎችና ፡ ቆሻሻዎች ፡ በሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ አደባባይ ፡ በሕዝብ ፡ መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መግቢያና ፡ መውጫ ፡ በሆኑ ፡ ስፍራዎች ፡ ላይ ፡ በማስቀመጥ ፡ በማንጠልጠል ፡ በማራገፍ ፡ ወይም ፡ በመጣል ፡ ትእዛዞችንና ፡ ደንቦችን ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ሳያከብር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ደንብ ፡ ሆነው ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚገባቸውን ፡ መጠነኛ ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባሮችን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እንደዚሁ ፡ ካሉት ፡ ስፍራዎች ፡ ላይ ፡ ያስቀመጣቸው ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የሠራቸው ፡ ቍፋሮዎች ፡ ጉድጓዶች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ሕዝብን ፡ እንዳያደናቅፉና ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲታዩ ፡ አስፈላጊውን ፡ መጠነኛ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ወይም ፡ የብርሃን ፡ ምልክት ፡ ሳያደርግ ፡ በቸልታ ፡ የተወና ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ በመተላለፊያና ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የተደረጉትን ፡ የብርሃን ፡ መስጫ ፡ መብራቶች ፡ እንዳችም ፡ ተገቢ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ በማጥፋት ፡ ወይም ፡ በማበላሸት ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ መሳሰለው ፡ ነገር ፡ ጥበቃ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ ባለመፈጸም ፡ በሕዝብ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ መሰናክል ፡ የሚያደርስ ፡ ጉዳይ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፹፩ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

BACK



## ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። የመገናኛ ፡ ጸጥታን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ እግረኞች ፤ ስለ ፡ ከብቶች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ የተሽከርካሪ ፡ መኪናዎች ፡ መዘዋወር ፡ ጉዳይ ፡ የነዚህንም ፡ ነገሮች ፡ የማመላለሻ ፡ አገልግሎት ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ መመርመርና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ እንዲሁም ፡ ለነዚሁ ፡ ተሽከርካሪ ዎች ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ አያያዛቸው ፡ ስለ ፡ መታደሳቸውና ፡ ስለ ፡ አገልግሎታቸው ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ መቀበል ፡ ጉዳይ ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝና ፡ ሕጋዊ ፡ ደንብ ፡ ባለ ማክበር ፡ ደንብ ፡ ተላላፊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፬፻፺፱ ፡ እስከ ፡ ፭፻፪ ።]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፹፩ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። የእሳት ፡ አደጋ ፡ የሚፈነዱ ፡ መሣሪያዎችንና ፡ አደገኞች ፡ ነገሮችን ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጪ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ [ቍ ፡ ፬፻፹፰ ፡ እስከ ፡ ፬፻፺፬ ።]

(ሀ) የቃጠሎን ፡ ወይም ፡ የእሳትን ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፤ ይልቁንም ፡ የኤሌ ክትሪክ ፡ መሥመር ፡ ሽቦ ፡ አዘረጋግንና ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ አደገኛ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ የጭስ ፡ መውጫዎችን ፡ ምድጃዎችን ፤ የውሃ ፡ ማፍሊያዎ ችን ፡ ወይም ፡ በእሳት ፡ አገልግሎት ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ነገሮችና ፡ ስፍራዎች ፡ አደጋ ፡ እንዳያደርሱ ፡ ስለ ፡ ማለያየትና ፡ ተገቢውን ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ የወጡትን ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ደንቦች ፡ ትእዛዞችና ፡ ማስታ ወቂያዎች ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ዲናሚቶች ፡ ቦምቦች ፡ አዳፍኔዎች ፡ ለበዓል ፡ ቀን ፡ የሚተኰሱ ፡ የፈንጠ ዝያ ፡ እሳቶች ፡ ወይም ፡ ፒታር ፡ የሚፈነዱ ፡ መጫወቻዎች ፡ እተከለከለ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይተኰሱ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ተኵሶች ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊውን ፡ ተገቢውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ስለማድረግ ፡ የወጣውን ፡ የማስ ጠንቀቂያ ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ ወይም ፡ በእሳት ፡ የተያያዙ ፡ የነበ ልባል ፡ አኤሮስታቶችን ፡ ትንታጎችን ፡ የወረወረ ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ የመሳ ሰሉትን ፡ የእሳትና ፡ የቃጠሎ ፡ አደጋ ፡ ሊያደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ ነበልባሎች ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ ስፍራ ፡ የጣለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የሚቀጣጠሉና ፡ የሚያቃጥሉ ፡ የሚመርዙ ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ የሆኑና ፡ በጠቅላላውም ፡ የቃጠሎ ፡ አደጋ ፡ ሊያደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ ባሩዶች ፡ ዘይ ቶች ፡ ጋዞችና ፡ ከነዚህም ፡ ጋራ ፡ ተዳራቢ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ እንዲሁም ፡

ማንኛዎቹንም ፡ የሚፈነዱና ፡ የሚቃጠሉ ፡ ቅመማ ፡ ቅመሞችን ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ፡ (ስለ ፡ መቀመም) ፡ በይዞታ ፡ ስለ ፡ ማኖር ፡ በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ በጭነት ፡ ስለ ፡ ማዘዋወር ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ስለሚደረገው ፡ የአያያዝ ፡ ጥንቃቄና ፡ አጠባበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃና ፡ ስለ ፡ ጽዳት ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

### ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጽዳትና ፡ ንጽሕና ፡ መቈጣጠር ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ [ቍ ፡ ፭፻፫ ፡ እስከ ፡ ፭፻፭ ።]

(ሀ) ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ጒዳይ ፡ ስለ ፡ ውሃዎችና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቦታና ፡ ቤቶች ፡ ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ቤቶችና ፡ ስለ ፡ ሕንጻዎች ፡ ስለ ፡ ማደሪያ ፡ ቤቶች ፡ ስለ ፡ መኖሪያዎች ፡ ስለ ፡ ፋብሪካዎች ፤ ስለ ፡ እንዱስትሪና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ቤቶች ፡ ጽዳት ፡ ስለ ፡ ጤናማነትና ፡ ስለ ፡ ንጽሕና ፡ አጠባበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ስለ ፡ በሽታዎች ፡ ይልቁንም ፡ የአእምሮና ፡ የተላላፊ ፡ በሽታዎችን ፡ የወረርሺኝ ፡ በሽታዎችንና ፡ የከብት ፡ ተላላፊ ፡ በሽታዎችን ፡ በጥንቃቄ ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ በሽታዎች ፡ መምጣታቸውን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፤ በክትባትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስለ ፡ መከላከል ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። መርዛማና ፡ አፍዛዥ ፡ የሆኑ ፡ መድኀኒቶችን ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ [ቍ ፡ ፭፻፲ ።]

(ሀ) መርዛማ ፡ አፍዛዥ ፡ ጎጂ ፡ የሆኑትንና ፡ በመርዝነታቸውም ፡ በሰው ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርሱትን ፡ መድኀኒቶች ፡ ወይም ፡ ቅመሞች ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ለጤና ፡ ማግኛ ፡ መድኀኒትነት ፡ የሚያገ

ለግሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ሐኪም ፡ ገልጾ ፡ በሚገባ ፡ ትእዛዝ ፡ ሳያስተላልፍለት ፡ የሠራ ፤ ቀምሞ ፡ ያዘጋጀ ፤ የሸጠ ፤ የሰጠ ፡ ለስጦታ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የሞያ ፡ ሥራው ፡ የሚያስገድደውን ፡ ወይም ፡ መጠነኛው ፡ የልማዱ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ የሚያዘውን ፡ ደንብ ፡ ባለመፈጸም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ አደገኛ ፡ ቅመሞችና ፡ መድኀኒቶች ፡ ያለፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ መሸጥ ፡ በግልጽ ፡ ያልተከለከለም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፤ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ ለማይጠየቁ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ ወይም ፡ ለበሽተኞች ፡ ወይም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ መድኀኒት ፡ ወይም ፡ ቅመም ፡ ለማይገባቸውና ፡ ለጤንነታቸውም ፡ አደገኛ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ለሚታወቅ ፡ ሰዎች ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እንዲወስዱ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ቅመማት ፡ ወይም ፡ መድኀኒቶች ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ፡ ወይም ፡ በነዚሁ ፡ ስለ ፡ መገልገል ፡ ጉዳይ ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥርዐት ፡ ወይም ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ ሊያደርግ ፡ የሚገባውን ፡ ተገቢ ፡ የአጠባበቅ ፡ ደንብ ፡ ባለመጠበቅ ፡ በተለይም ፡ ተዘባርቀው ፡ በመቀመጣቸው ፡ በስሕተት ፡ አደጋ ፡ የሚያደርሱ ፡ መሆናቸው ፡ የሚያሠጋ ፡ ሲሆን ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያስቀመጠ ፡ ወይም ፡ የተገለገለባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የግል ፡ ተግባሩ ፡ ወይም ፡ በችሎታው ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ሌሎችን ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ ሲችል ፡ እነዚህ ፡ ቅመማ ፡ ቅመሞች ፡ ወይም ፡ መድኀኒቶች ፡ የመርዝ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሳያስታውቅ ፡ ወይም ፡ ሳያስጠነቅቅ ፡ በመቅረት ፡ ተግባሩን ፡ በዝንጋታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፤ ፭፻፳፯ ። ሕሊና ፡ እንዲያጣ ፡ ወይም ፡ እንዲፈዝ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተማለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ በግልጽ ፡ በታወቀለት ፡ ሞያው ፡ በሕክምና ፡ ወይም ፡ በመድኀኒት ፡ ቀማሚነት ፡ ጥበቡና ፡ ሞያው ፡ የተፈቀደለት ፡ ሳይሆን ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ የተፈቀደ ፡ ነገር ፡ ሳይኖር ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሕሊና ፡ በሚነሳ ፡ ወይም ፡ ለማሰብ ፡ የሚችልበትን ፡ አእምሮውን ፡ በሚያፈዝና ፡ ክፉና ፡ በጎውን ፡ ለመለየት ፡ በማያስችለው ፡ ሁኔታ ፡ የሕክምና ፡ ጥበብ ፡ መማሪያ ፡ ወይም ፡ መለማመጃ ፡ ለማድረግ ፡ ሲል ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ሁኔታ ፡ አእምሮ ፡ እንዲያጣ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ። [ቍ ፡ ፭፻፲፭ና ፡ ፭፻፲፯ ።]

(፪) ለሕክምና ፡ ጥበብ ፡ መመርመሪያና ፡ መለማመጃ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ማስደ

ስቻ ፡ በተፈቀደ ፡ አኳኋን ፡ የሚደረጉ ፡ ተግባሮች ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ የተፈቀዱ ፡ የአሳብ ፡ መገናኛ ፡ ወይም ፡ በሩቅ ፡ የሚደረግ ፡ የ፡ጠባይ ፡ መለዋወጫ ፡ (የሂፕኖቲዝም) ፡ ሥራዎች ፡ አያስቀጡም ።

ቍ ፡ ፯፻፹፰ ። የምግብ ፡ የመጠጥና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የንግድ ፡ ሸቀጦችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ [ቍ ፡ ፯፻፲፩ና ፡ ፯፻፲፪ ።]

(ሀ) የምግብ ፡ ሸቀጦችን ፤ የሥጋን ፤ የወተትን ፤ አልኮል ፡ ያለባቸውን ፡ ወይም ፡ የሌለባቸውን ፡ መጠጦች ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችንና ፡ ድርቆሾችን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፤ ስለ ፡ መያዝ ፤ ስለ ፡ ማመላለስ ፤ አስቀምጦ ፡ ስለ ፡ ማኖር ፡ ስለ ፡ መነገድ ፡ ስለ ፡ አያያዛቸው ፡ ሥርዐትና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የገበያ ፡ ሱቆችን ፡ የመዝጊያና ፡ የመክፈቻ ፡ ሰዓት ፤ ስለ ፡ ቤቶችም ፡ ጽዳትና ፡ አጠባበቅ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለ ፡ አድራጎት ፡ ሲፈጽም ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፱ ። የሕክምና ፤ የበሽተኞች ፡ ማስታመም ፡ ዘዴ ፡ ጥበብና ፡ የሆስፒታሎች ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ አስተዳደር ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ [ቍ ፡ ፯፻፲፰ና ፡ ፯፻፲፱ ።]

(ሀ) የሕክምናን ፤ የመድኃኒት ፡ መቀመምን ፡ የከብት ፡ ሕክምናንና ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ተደራቢ ፡ የሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ የግል ፡ ሞያ ፡ ሥራ ፡ የሆነውን ፡ ጥበብ ፡ ለመሥራት ፤ የሜካኖቴራፒያንና ፡ የተፈጥሮ ፡ መድኃኒቶችን ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ ግል ፡ ሞያ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡ የወጣውን ፡ የፈቃድ ፡ መቀበል ፡ ደንብ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ጥበባውያን ፡ ሥራዎችንና ፡ ሞያዎችን ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የመድኃኒት ፡ ቅመሞችንና ፡ መድኃኒቶችን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የማከሚያ ፤ የተመላላሽ ፡ በሽተኞች ፡ ማከሚያ ፤ ወይም ፡ በሆስፒታል ፡ የሚተኙትን ፡ በሽተኞች ፡ በሕክምና ፡ ስለ ፡ ማስታመምና ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ የሕክምና ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መፈጸም ፤ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ጥበብና ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ በሆስፒታልና ፡ በተመላላሽ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡

BACK



የንግድ ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ ሆስፒታሎችን ፡ ወይም ፡ የማከሚያ ፡ ቤቶ ችን ፡ ለመክፈትና ፡ ለማቋቋም ፡ ስለ ፡ ማስፈቀድ ፡ መቋቋማቸውን ፡ ለባለሥ ልጣን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፺ ። የማስታወቅን ፡ የግዴታ ፡ ተግባር ፡ ስላለመፈጸም ።**

የሐኪምነት ፤ የጥርስ ፡ ሐኪምነት ፤ ያዋላጅነት ፡ የከብት ፡ ሕክምና ፡ ሥራ ፡ እንዲ ያከናውኑ ፡ በክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በግልጽ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ማንኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡ በሕጉ ፡ ወይም ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ጉዳዩን ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ባለሥ ልጣኖች ፡ እንዲያስታውቁ ፡ የሚገደዱበትን ፡ በተለይም ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ መዛመቱን ፤ የማያፈገዝ ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ማዘውተር ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ የተራባ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ የከብት ፡ በሽታ ፡ ባገር ፡ መግባቱን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ለማኅበራዊው ፡ ጠቅላላ ፡ ኑሮ ፡ የሚያሠጋ ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ መሠራቱን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፤

እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ አድራጎት ፡ የተደጋገመ ፡ ሲሆን ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፩ ። የማከምን ፡ ተግባር ፡ ስላለመፈጸም ።**

ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ የሕክምና ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የአስታማሚነት ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሐኪሞች ፡ አስታማሚዎች ፡ መድኀኒት ፡ ቀማሚ ዎች ፤ የከብት ፡ ሐኪሞች ፡ አዋላጅ ፡ ሴቶች ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመ ሳሰለ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ መሰናከል ፡ ሳያጋጥማቸው ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖራቸው ፡ እርዳታቸውን ፡ በሚጠይቀው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ የሚደርስበት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ለማከም ፡ ወይም ፡ የሚያ ስፈልገውን ፡ መድኀኒትና ፡ የማስታመም ፡ ተግባራቸውን ፡ ሳይፈጽሙ ፡ የቀሩ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚሁ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምባቸዋል ። [ቍ ፡ ፭፻፳፯ ፡ ፭፻፴፯ ።]

**ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። ስለ ፡ አቀባበር ፡ ሥርዓት ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሙታኖችን ፡ ስለ ፡ ማሳየት ፤ ተገቢ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ፤ ስለ ፡ መቅበርና ፡ ስለ ፡ ማቃጠል ፡ የወጣውን ፡ ያጠባበቅ ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተ ላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

### በሰዎችና ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፫ ። መሠረቱ ፤ ጠቅላላ ፡ ደንብ ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ሰዎችንና ፡ ንብረታቸውን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ሥራው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስወስን በት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ተገልጸው ፡ በተወሰኑት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### በሰዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

### ለሰውነት ፡ ጥበቃ ፡ የተወሰኑትን ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፬ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የእጅ ፡ እልፊትና ፡ ቀላል ፡ የኀይል ፡ ሥራ ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፤ [ቍ ፡ ፭፻፵፬ ።]

(ሀ) ሌላውን ፡ ሰው ፡ ሳይመታ ፡ ወይም ፡ ሳያቈስል ፡ የገፋው ፡ ወይም ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ የግጭት ፡ ሥራ ፡ የፈጸመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሆነ ፡ ብሎም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ቈሻሻ ፡ የጣለበት ፤ እጣቢ ፡ ያፈሰሰበት ፡ ወይም ፡ የሚያቈሽሽና ፡ የሚቀነቅን ፡ ነገር ፡ የጣለበት ፡ ወይም ፡ ያፈሰሰበት ፡ የወረወረበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፭ ። ሬሳ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ሞቶ ፡ የተወለደውን ፤ ሞቶ ፡ ተወለደ ፡ የሚባለውን ፡ የሕፃን ፡ ወይም ፡ የሰው ፡

ሬሳ ፡ ለክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሳያስታውቅ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሬሳ ፡ በድንገት ፡ ማግኘቱን ፡ ለባለሥልጣኖች ፡ ሳያመለክት ፡ የደበቀ ፤ የቀበረ ፤ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ የጣለ ፤ ያቃጠለ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ በአልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ወይም ፡መብታዊ ፡ በሆነ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ አቍስሎ ፡ ወይም ፡ ገድሎ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለባለሥልጣኖች ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፺፮ ። የሰውን ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ ስለ ፡ መንካት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ የሰውን ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ለዚሁም ፡ ማረጋገጫ ፡ የወጣውን ፡ በመተላለፍ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፤ በአእምሮው ፡ ጐደሎነት ፡ ምክንያት ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ የማይጠየቀውን ፡ ወይም ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለመለየት ፡ የማይችለውን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ በራሱ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በግላዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያላገባብ ፡ የያዘ ፡ ያስያዘ ፤ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። [ቍ ፡ ፭፻፶፯ ። ]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፺፯ ። የግል ፡ ምስጢርን ፡ የመጠበቅ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ቀላል ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከተውን ፡ ቅጣት ፡ የማያስወስንበት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝና ፡ በጥላቻም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ስሜት ፡ የግል ፡ ምስጢርን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ሕጋዊ ፡ ደንብ ፡ ጥሶ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ሕይወትና ፡ የኑሮውን ፡ ወይም ፡ በደብዳቤ ፡ የሚላላከውን ፡ የግል ፡ ምስጢሩን ፡ የገለጸበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፭፻፹፫ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፺፰ ። በክብር ፡ ላይ ፡ ቀላል ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ ያደረሰው ፡ የስድብ ፡ ወይም ፡ የማዋረድ ፡ ተግባር ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ በመሆኑ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ቅጣት ፡ የማያስወስንበት ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ይልቁንም ፡ ስድቡ ፡ ወይም ፡ የማዋረዱ ፡ ጉዳይ ፡ በግልጽ ፡ ስላልተደረገ ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ተበዳዩ ፡ የስድቡ ፡ ፍቺ ፡ አልገባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮና ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ።

ተሰዳቢው ፡ መልሶ ፡ በመሳደቡ ፡ ወይም ፡ ሰዳቢው ፡ ይቅርታ ፡ በመጠየቁ ፡ ከቅጣት ፡ ለመዳን ፡ ስለ ፡ መቻል ፡ የተወሰኑት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ። [ቍ ፡ ፭፻፲፫ ፡ ፭፻፲፬ ፡ ፭፻፲፭ ።]

## ክፍል ፡ ፪ ።

## መልካም ፡ ባህልን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ ጉዳይ ፡ የተመለከተውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

### ቍ ፡ ፰፻፶፱ ። ሥርዐትንና ፡ መልካም ፡ ባህልን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ በአደባባይ ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ በሚያየውና ፡ በሚሰማበት ፡ ስፍራ ፡ ሕጋዊውን ፡ ሥርዐትና ፡ መልካም ፡ ባህልን ፡ ያልጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፯፻፺፰ ፡ እስከ ፡ ፰፻፲ ።] በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፰፻፷ ፡ ስለ ፡ አስነዋሪ ፡ ልመናና ፡ በብልግና ፡ አድራጎት ፡ ሁከት ፡ ስለ ፡ ማንሣት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ ጐዳና ፡ ወይም ፡ በአደባባይና ፡ ለሕዝብ ፡ በተከፈተ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡—

(ሀ) በራሱ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃደኛ ፡ መስሎ ፡ የማይታየውን ፡ ሰው ፡ ለማስቸገር ፤ ኀፍረተ ፡ ቢስ ፡ በመሆንና ፡ መልካም ፡ ባህልን ፡ ተቃዋሚ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ያወከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለግብረ ፡ ሥጋ ፡ ተግባር ፡ እንዲነሣሣ ፡ ያደፋፈረ ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕናና ፡ ለመልካም ፡ ባህል ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ አድራጎት ፡ እንዲፈጽም ፡ በልመና ፡ ወይም ፡ አስነዋሪ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ያነሣሣውና ፡ ያደፋፈረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ወይም ፡ ለአመንዝራነትና ፡ ለብልግና ፡ ሥራ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ የጎረቤቱን ፡ ወይም ፡ በአካባቢው ፡ የሚገኙትን ፡ ነዋሪዎች ፡ ያወከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፰፻፷፩ ። ለብልግና ፡ ተግባር ፡ የሚያነሣሣ ፡ ማስታወቂያና ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በብልግና ፡ ከመጠን ፡ ባለፈ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ስሜት ፡ እንዲነሣሣ ፡ ለማድረግና ፡ ለማግባባት ፡ በማቀድ ፡ በማናቸውም ፡ ጥበብና ፡

BACK



ዘዴ ፡ በአደባባይ ፡ ማስታወቂያ ፡ የለጠፈ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መግለጫና ፡ ማስታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ አሳቡ ፡ እንደዚህ ፡ ወዳለው ፡ ሥራ ፡ እንዲያዘነብልና ፡ እንዲሳብ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፰፻፱ ። ፅንስን ፡ ለመከልከል ፡ ስለሚችል ፡ መግለጫ ።

ማንም ፡ ሰው ፡—

(ሀ) ሰው ፡ እንዳይራባ ፡ ፅንስን ፡ ለመከልከል ፡ የሚሆን ፡ ጥበብ ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ በአደባባይ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ማስታወቂያ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ላልጠየቁትና ፡ የሞያ ፡ ሥራቸው ፡ ላልሆነ ፡ ሰዎች ፡ ለፅንስ ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆን ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ወይም ፡ መድኀኒት ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ለመከልከል ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ በሚገልጽ ፡ ዐይነት ፡ የዚሁኑ ፡ ዘዴ ፡ መግለጫ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ መድኀኒት ፡ የላከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ፅንስን ፡ የሚያስወርዱ ፡ ዘዴዎችን ፡ ወይም፡ ቅመማ ፡ ቅመሞች ፡ ( መድኀኒቶችን ) ፡ ለሕዝብ ፡ ያስታወቀ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ሲል ፡ አገልግሎቱን ፡ ለሕዝብ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፤ ፪ ።

## በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፤ መተላለፍ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## የሀገርን ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ቍ ፡ ፰፻፲ ። ታሪካዊ ፡ ጥበባዊና ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፤

(ሀ) ታሪካዊ ፡ የሆኑትን፡ (አርኬዎሎጂክ) ፡ ጥንታዊ ፡ ሐውልት ፡ ጥበባዊ ፡ የሆኑትን ፡ ያገሩን ፡ ንብረቶችና ፡ የተፈጥሮ ፡ አቀማመጥ ፡ ያላቸውን ፡ስፍራዎች ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ተፈጥሮና ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውን ፡ ምንጮች ፡ ያገሩን ፡ ሀብቶች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፤

(ለ) ታሪካዊ ፡ የሆኑትን ፡ የጥንት ፡ ሀብቶችና ፡ ዕቃዎች ፡ የአርኬዎሎጂክ ፡ የጂዎ

ግራፊ ፡ ወይም ፡ ያገሩ ፡ ጥቅም ፡ የሆኑትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባለዋጋ ፡ ነገሮች ፡ ማግኘትን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅና ፡ ለክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ መግለጽ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ባለመፈጸም ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ በሀገሩ ፡ ጥንታዊና ፡ ታሪካዊ ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ተፈጥሮና ፡ ጠባይ ፡ ባለው ፡ ጥንታዊ ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መነገድ ፤ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚላከውን ፡ ስለ ፡ መቈጣጠርና ፡ ይህንንም ፡ የመሳሰለው ፡ ነገር ፡ እንዳይደረግ ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ የወጣውን ፤

(ሐ) ወይም ፡ ደግሞ ፡ ታሪካዊና ፡ (የአርኬዎሎጂክ) ፡ የሆነውን ፡ ሐውልት ፡ ያፈረሰ ፤ ያጠፋ ፤ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ አቀማመጥ ፡ የያዘውን ፡ ታሪካዊ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ የሚጠበቀውን ፡ ቦታ ፡ ያበላሸ ፤ ያፈረሰ ፡ እንዲሁም ፡ እነዚህን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፰፻፩ ። ያገር ፡ ተክልንና ፡ እንስሳትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ያገር ፡ ተክልንና ፡ ቅጠልን ፤ ዛፍንና ፡ አትክልትን ፤ የዱር ፡ አውሬንና ፡ እንስሳትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፫ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

## በሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

ቍ ፡ ፰፻፪ ። የሕዝብንና ፡ የግል ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ የሕዝብንና ፡ የግል ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብና ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፍ ፤ [ቍ ፡ ፮፻፴፱ ፡ እስከ ፡ ፮፻፶፭ ።] ይልቁንም ፤

(ሀ) በሚገባ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ከሕዝብ ፡ ወይም ፡ ከግል ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ አፈር ፡ ድንጋይ ፤ ዕንጨት ፤ አሸዋ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ነገሮች ፡ ለምለም ፡ ሣር ፤ የአጥር ፡ ዕንጨት ፡ ወይም ፡ አትክልት ፡ ወይም ፡ ፍራፍሬ ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በማናቸውም ፡ ወራት ፡ ቢሆን ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ በአጥር ፡ በተዘጋ ፡ በተዘራ ፡ ሰብል ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ባለበት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለፈ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ መሬት ፡ መካከል ፡ የገባ ፡ ወይም ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የቀንድ ፡ ከብቶችንና ፡ የጋማ ፡ ከብቶችን ፡ ይህንኑ ፡ ያስጋጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) መብት ፡ ወይም፡ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ በተከለከለ ፡ የማደኛ ፡ ወይም ፡ በዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

## ቍ ፡ ፯፻፷ ። ቀላል ፡ ስርቆት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በችግር ፡ ወይም ፡ በፍላጎት ፡ ወይም ፡ በቀላልነት ፡ ተነሣሥቶ ፡ ግምቱ ፡ አነስተኛ ፡ የሆነውን ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊበላው ፡ ወይም ፡ ሊገለገልበት ፡ አስቦ ፡ የሰረቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እስከ ፡ ኀምሳ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በሚደርስ ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

አድራጊው ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በችግረኛነቱ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለሕይወቱ ፡ በፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖበት ፡ ማድረጉን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቅጣቱ ፡ ነጻ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

(፪) ወደ ፡ ላይ ፡ በሚቈጠር ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ በሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ባልተለያዩ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ ቀላል ፡ ስርቆሽ ፡ ቅጣትን ፡ አያስከትልም ።

(፫) እንደ ፡ ነገሩም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታና ፡ የተሰረቀውም ፡ ዕቃ ፡ ለምን ፡ ዐይነት ፡ አገልግሎት ፡ እንደሚጠቅም ፤ ባለዋጋነቱም ፡ እጅግ ፡ አነስተኛ ፡ መሆኑንና ፡ ይህ ፡ የስርቆሽ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ ያላገባብ ፡ ብልጽግናን ፡ ለማግኘት ፡ በማሰብ ፡ አለመሆኑ ፡ በግልጽ ፡ የሚገመት ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መገንዘብ ፡ አለበት ። [ቍ ፡ ፮፻፴ ።]

## ቍ ፡ ፯፻፸ ። የእህልና ፡ የተክል ፡ እሸት ፡ ስለ ፡ መልቀም ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ወራት ፡ ቢሆን ፤

(ሀ) የሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ከሆነው ፡ እርሻ ፡ ወይም ፡ ከአትክልት ፡ ውስጥ ፤ የእህል ፡ እሸቶችን ፤ የአትክልትና ፡ የዛፍ ፡ ፍሬዎችን ፡ እስፍራው ፡ ላይ ፡ ለመብላት ፡ ያለፈቃድ ፡ የሰረቀ ፡ የቀጠፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ከእርሻዎች ፡ ከአትክልቶች ፡ ወይም ፡ ሰብላቸው ፡ በሙሉ ፡ ካልተነሣባቸው ፡ ማሳዎችና ፡ በጀንበር ፡ መጥለቂያና ፡ መውጫ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ሰዓት ፡ በሰው ፡ አትክልት ፡ ስፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ እህሎችን ፡ ፍሬዎችንና ፡ ሌሎችንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ የለቀመ ፡ የቃረመ ፤ የሰበሰበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፷ ፡ የተጻፈው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

**ቍ ፡ ፰፻፰ ። አጠራጣሪ ፡ የሆኑትን ፡ አንዳንድ ፡ ዕቃዎች ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መያዝ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ከየት ፡ እንዳመጣቸውና ፡ ከምን ፡ እንዳገኛቸው ፡ ለምን ፡ ዐይነት ፡ አገልግሎት ፡ እንደሚጠቅሙት ፡ በቂ ፡ በሚመስል ፡ ምክንያት ፡ ለማስረዳት ፡ የማይችለውን ፡ ቍልፎችን ፡ መክፈቻዎችን ፡ የቍልፍ ፡ ማንጠልጠያ ፡ ዘለበቶችን ፡ ጉጠቶችን ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምሳሮችንና ፡ መሣሪያዎችን ፡ እንዲሁም ፡ ሰነዶችንና ፡ ባለ ዋጋ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የሚያጠራጥሩ ፡ ዕቃዎችን ፡ ይዞ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፰፻፱ ። በሀብት ፡ ረገድ ፡ ስለሚፈጸም ፡ መግለጫ ፡ ያለ ፡ መስጠትና ፡ የመሰወር ፡ ጉዳይ ።**

እንዲሁም ፡—

(ሀ) ወድቆ ፡ የተገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ውስጥ ፡ የጠፋውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ተሸሽጎ ፡ የተገኘውን ፡ ሀብት ፡ [ ቍ ፡ ፯፻፵፰ ። ]

(ለ) በስርቆት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ወንጀል ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ሳያውቅ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ያገኘ ፡ የገዛ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደ ፡ ጠረጠረና ፡ እንዳወቀ ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፡ ሁኔታና ፡ ሌሎችም ፡ አካባቢ ፡ ምክንያቶች ፡ እንደ ፡ ፈቀዱለት ፡ በእጁ ፡ መኖሩን ፡ ለክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፰ ፡ በተጻፉት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፰፻፲ ። የሰውን ፡ ሀብት ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ፡ ስለ ፡ ማራከስ ።**

እንዲሁም ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ በአደራ ፡ የተቀበለውን ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ በመያዝና ፡ በአጠባበቅ ፡ ጕድለት ፡ ቤቱን ፡ ሕንጻውን ፡ ወይም ፡ የቤቱን ፡ ግንብ ፡ ያበላሸና ፡ ዋጋ ፡ እንዲያጣ ፡ ያደረገ ፤ ወይም ፡ በራሱ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ በሚያከናውነው ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ የሌላው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስበት ፡ ያደረገ ፡ የመውጫ ፡ የመግቢያ ፡ መንገዱን ፡ የዕቃ ፡ ማጠቢያ ፡ በማድረግ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ዕቃውን ፡ በመቆለል ፤ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡ ቦዮችን ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ በመያዝ ፤ ወይም ፡ የቦዮችን ፡ ትልም ፡ ወደሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ በመምራትና ፡

ውሃው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ እንዲፈስ ፡ በማድረግ ፤ የተሽከርካሪ ፡ መኪ፣ ዎችን ፡ ወይም ፡ በእንስሳ ፡ የሚሳቡ ፡ ጋሪዎችን ፤ ጭነት ፡ በማብዛትና ፡ ጭነቱን በሚያራግፍበት ፡ ጊዜ ፡ ከመጠን ፡ ባለፈ ፡ ፍጥነት ፡ በመንዳት ፡ ወይም ፡ በመሣሪያ ዎችና ፡ በጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ በመገልገል ፡ ይህን በመሳሰለ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ [ቍ ፡ ፮፻፵፫ና ፡ ፮፻፵፬ ።]

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፲፭ ። የሕዝብ ፡ የሆኑትን ፡ ቤቶችና ፡ ሐውልቶች ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፤ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ለሕዝባዊ ፡ መደሰቻ ፡ የተመደቡትን ፡ ሐውልቶችና ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ ያቈሸሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ [ቍ ፡ ፮፻፵፬ ።]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፲ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸምበታል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በጠቅላላው ።

ቍ ፡ ፯፻፲፮ ። በተንኰል ፡ መንገድ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መጉዳት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ብልጽግናን ፡ ለማግኘት ፡ በማቀድ ፡ ሳይሆን ፡ በማታለልና ፡ በማጭበርበር ፡ ዘዴ ፡ በክፋትም ፡ ሆነ ፡ በመጉዳት ፡ ምኞት ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያደርስ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ያግባባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፯፻፲፯ ። ስለ ፡ ወስላታነት ።

እንዲሁም ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ሲያውቅ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ተቋቁመው ፡ አገልግሎታቸውን ፡ በዋጋ ፡ በሚያበረክቱ ፡ እንደ ፡ ሆቴል ፡ እንደ ፡ መጠጥ ፡ ቤትና ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ማደሪያ ፡ ቤት ፡ ባሉት ፡ የንግድ ፡ ሱቆች ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የተመገበ ፡ ወይም ፡ የጠጣ ፡ ወይም ፡ የማደሪያ ፡ ስፍራ ፤ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደረገ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፲፮ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፲፬ ። ሌሎችን ፡ አገልግሎቶች ፡ በአጭበርባሪነት ፡ ስለ ፡ ማግኘት ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ዋጋ ፡ ሳይከፍልበት ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ አገልግሎት ፡ ለማግኘት ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ በተለይም ፡—

(ሀ) የሕዝብ ፡ ወይም ፡ የግል ፡ በሆነ ፡ በየብስ ፡ በባሕር ፡ ወይም ፡ በአየር ፡ መመላለሻ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የተገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ዋጋ ፡ በሚከፈልባቸው ፡ በቲያትር ፤ በሲኒማ ፤ በጨዋታ ፡ ቤቶች ፤ በኤክስፖዚሲዮኖችና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ዋጋ ፡ በሚከፈልባቸው ፡ ስፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ዝርዝር ፡ ገንዘብ ፡ ተጨምሮበት ፡ በአቶማቲክ ፡ ሞተር ፡ በሚሠራ ፡ የአገልግሎት ፡ መኪና ፡ ተጠቅሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፲፪ ፡ በተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፭ ። ዐውቃለሁ ፡ ባይ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ [ቍ ፡ ፯፻፰፭ ። ]

(ሀ) የወደፊቱን ፡ እተነባለሁ ፡ ብሎ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ በሌላ ፤ ሰው ፡ እምነት ፡ ለመጠቀም ፡ በማቀድ ፡ ጋኔን ፡ በመጐተት ፡ መንፈስ ፡ ርኩስን ፡ በመለመን ፡ የተሸሸገ ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኝበትን ፡ ዘዴ ፡ በማመልከት ፡ ከሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ የጥንቈላ ፡ ዘዴ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ በእምነቱ ፡ የተጠቀመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ዐውቃለሁ ፡ ብሎ ፡ በአደባባይ ፡ የተናገረና ፡ በማስታወቂያ ፡ መግለጫ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፲፪ ፡ በተጻፉት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፮ ። ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መሰብሰብ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ወይም ፡ የክፍሉን ፡ ባለሥልጣን ፡ ሳያስፈቅድ ፡ በአደባባይ ፡ እየዞረ ፡ ገንዘብ ፡ የሰበሰበ ፡ ወይም ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ይህ ፡ የገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ ጕዳይ ፡ የተፈጸመው ፤ ሃይማኖታዊ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምባቸው ፡ ሕንጻዎች ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ስብሰባ ፡ ስፍራ ፡ ባንድ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የግል ፡ በሆኑ ፡ የማኅበር ፡ ክፍሎች ፤ ይህንኑ ፡ ሞያ ፡ አድርገው ፡ በያዙ ፡ ክፍሎች ፤ በስፖርትና ፡ በሌላውም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ክፍል ፡

BACK



ሆኖ፡የገንዘቡም ፡ ስብሰባ ፡ በተለይ ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ የዚህኑ ፡ ሥራ ፡ ለማካ ሄጃ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የተባለው ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌ ፡ አይፈጸምባቸውም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በኤኮኖሚክና ፡ በንግድ ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ አስተዳደር ፡ ረገድ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

### ቍ ፡ ፰፻፲፯ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገቦችና ፡ ስለ ፡ ሒሳቦች ፡ አያያዝ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ በደንብ ፡ ወይም ፡ በውስጠ ፡ ደንብ ፡ የተወሰነውን ፡ በመተላለፍ ፡ የንግድ ፡ መዝገቦችን ፡ ወይም ፡ ሒሳቦቹን ፡ በሚገባ ፡ ያልያዘ ፡ ወይም ፡ ችላ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያንዱን ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከቱትን ፡ የመላላኪያ ፡ ሰነዶችን ፤ ፋክቱሮችንና ፡ ሌሎችንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የንግድ ፡ ሰነዶች ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያላቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የማረፊያ ቤት ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

### ቍ ፡ ፰፻፲፰ ። በግዴታ ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ የእንቢተኛነትን ፡ መልክ ፡ ስለ ፡ ማሳየት ።

ማንኛውም ፡ ባለዕዳ ፡ ወይም ፡ ፫ኛ ፡ ወገን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ የመክሰስ ፤ ወይም ፡ ዕዳ ፡ የማስከፈል ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ሹማምቶች ፡ ማንኛውንም ፡ በሥልጣናቸውና ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ሊያዙት ፡ በሚችሉት ፡ ረገድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሲጠይቁት ፡ እንቢተኛ ፡ በመሆን ። [ ቍ ፡ ፯፻፹፫ና ፡ ፯፻፹፭ ። ] በተለይም ፡

(ሀ) በራሱ ፡ ይዞታ ፡ የማይገኙም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ጠቅላላ ፡ ንብረት ፡ ከሆኑት ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ወይም ፡ የሚፈለጉትን ፡ ዕቃዎች ፡ መያዣዎች ፡ ዕዳዎች ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ግዴታዎች ፡ ወይም ፡ እንዲያቀርብ ፤ እንዲያረጋግጥ ፡ ወይም ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ወይም ፡ እንዲያመጣ ፡ ሲጠየቅ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ቃሉ ፡ እንዲሰማ ፡ ወይም ፡ እንዲገጣጠም ፡ ደንበኛ ፡ ጥሪ ፡ ሲደረግለት ፡ ባንድ ፡ ስብሰባ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገኝ ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ ሊፈጸም ፡ በሚገባው ፤ የክስ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ በሚደረገው ፡ አሠራር ፡ ላይ ፡ ስለሚ

BACK



ሰጠው ፡ ድምፅ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ሲጠራ ፡ እንቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የማረ ፊያ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፰፻፲፱ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ መርከቦች ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ ።

ስለ ፡ ባሕር ፡ ንግድና ፡ ስለ ፡ ባሕር ፡ መርከቦች ፡ የወጡ ፡ ድንጋጌዎችን ፤ ትእዛዞ ችንና ፡ ደንቦችን ፡ በመጣስ ፡ በተለይም ፡—

(ሀ) የመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ መኰንኖች ፡ (ኦፊሰሮች) ፡ የመርከብ ፡ ሠራተኞች ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ መስጠት ፡ መርከቦችን ፡ እንደ ፡ መጉብኘት ፡ እንደ ፡ መመ ርመር ፡ እንደ ፡ መቈጣጠር ፡ የመሳሰሉትን ፡ ተግባሮች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ ያለ ባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ መጣስ ፤

(ለ) ስለ ፡ መርከቡ ፡ መዝገቦች ፡ ስለ ፡ ደብተሮችና ፡ ስለ ፡ ሰነዶች ፡ አያያዝ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ መጣስ ፤

(ሐ) የመርከቡን ፡ ጭነት ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ የሚሄዱትን ፡ መንገደኞች ፡ ወይም ፡ ፖስታ ፡ በመርከብ ፡ የማሳፈርንና ፡ ከመርከብ ፡ የማውረድን ፡ መር ከቡ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ ወይም ፡ በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ የሚደረ ገውን ፡ አካሄድ ፡ ስለ ፡ መምራት ፡ ሥራ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ መጣስ ፤

(መ) ስለ ፡ ጽዳትና ፡ ስለ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ የታዘዙትን ፡ ግዴታዎች ፡ መጣስ ፡ በጠቅላላው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፤ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚያስቀጣ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ያስቀጣል ።

ቍ ፡ ፰፻፳ ። በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠውን ፡ የማኅበር ፡ ሥራ ፡ በማካሄድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ።

በሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የወንጀል ፡ ቅጣትና ፡ ግዙፎች ፡ የሆኑትን ፡ የጥን ቃቂ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ቅጣቶች ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ ደንብ ፡ ተላላፊዎች ፡ መቅጫ ፡ ለወጣውም ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ። [ ቍ ፡ ፯፻፹፱ ። ]